# የቡርቃ ዝምታ

ተስፋዬ ገብረአብ



# የቡርቃ ዝምታ

(ታሪካዊ ልብ-ወለድ ድርሰት)

ተስፋዬ ገብረአብ

አዲስ አበባ
1992

© ተስፋዬ ገብረአብ , 1992

## ምስጋና

«የቡርቃ ዝምታ» በተሳካ ሁኔታ ይጠናቀቅ ዘንድ የሀሳብና የሞራል ድጋፍ ላደረጉልኝ ወዳጆቼ፣

. ለኃይለመለኮት መዋዕል

. ለመኩሪያ መካሻ

. ለመኮንን ሙሉጌታ

የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

መታሰቢያነቱ
ለእናቴ ለመብራት ወልደማርያም

# ቅድመ - ታሪክ

ጨርሶ ማመን አቃተኝ:: ግን ጆሮዬ ይሰማል! አይኔ ያያል! የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን ያበደ መሰለኝ:: ሀየሎም መገደሉን መስማቴ ግን ህልም ወይም ቅዠት አልነበረም::

ከአንድ ወዳጄ ጋር እዚሁ አዲስ አበባ ዮርዳኖስ ሆቴል ተቀምጠን ቢራ ይዘን ነበር:: የሆቴሉ ባር በሰዎች ተሞልቶአል:: የኮማንደር ሀየሎም አርአያ የእረፍት ዜና ሲነገር ተቡዋድኖ ሲጠጣ የነበረው ሰው ሁሉ በድንገተኛ ፀጥታ ተመታ:: ከሶስት ሀበሾች ጋር ተቀምጦ የነበረ ራሰ በራ ነጭ በድንገተኛው ፀጥታ ክፉኛ በመደንገጡ! ስለዜናው ይነግሩት ዘንድ አጠገቡ የነበሩትን ሀበሾች ወተወታቸው! የሚያስረዳው ግን አላገኘም:: የሆቴሉ ተስተናጋጅ ሁሉ በድንጋጤ ደንዝዞ በቴሌቭዥኑን መስኮት ከነግርማ ሞገሱ ብቅ ብሎ የሚታየው ሰው ላይ እንዳፈጠጠ ቀረ::

ያን ቀን ከዜናው በሁዋላ ያለውትሮዬ በጊዜ ቤቴ ገብቼ ተኛሁ:: የሰማሁት ዜና ኩርምትምት አደረገኝ:: ጋዜጠኛ እንደመሆኔ ሀየሎምን በቅርብ የማወቅ እድል ገጥሞኛል:: ለረጅም ሰአት ስለ ሀየሎም እያሰብኩ ቆየሁ:: የሀየሎም የእረፍት ዜና የሚያስለቅስ ሳይሆን የሚያሽማቅቅና የሚያናድድ ነበር የሆነብኝ::

ቀፋፊ ሌሊት አሳለፍኩ ...

በነጋታው ለስራ ጉዳይ አስመራ መሄድ ነበረብኝ:: ለሶስት ቀናት እንዲራዘምልኝ አደረግሁ:: የሀየሎም እረፍት ህልምም ቅዥትም አልነበረምና በሌ አይሮፕላን ማረፊያ ተገኝተን የሀየሎምን አስከሬን በእንባ ሸኘነው -ወደ አዲነብርኢድ:: ሀየሎም ወደ ተወለደባት ፀጥተኛ መንደር ሄዶ አረፈ::

እነሆ ኢትዮጵያዊው - ጀግና ሀየሎም አርአያ - በተራ ግጭት - በተራ ግለሰብ ድንገት ወደቀ::

አሳዛኝ ፍፃሜ!

በሶስተኛው ቀን ወደ አስመራ አቀናሁ:: ከኤርትራ መንግስት አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን ጋር ከጋዜጣ ስራ ጋር የተያያዘ ቀጠሮ ነበረኝ:: አስመራ ደርሼ ስራዬን በተፈለገው መንገድ ካበቃሁ በሁዋላ ባለስልጣኑ በወኪሉ አማካይነት ራት ሊጋብዘኝ እንደሚፈልግ ገለፀልኝ:: ተስማማሁ:: ወኪሉ በባለስልጣኑ ፀሀፊ በኩል ተጠርቶ መጣ:: ተዋወቅን:: ስሜን ነገርኩት:: እሱም «አብርሃ ፀሎት» ሲል ተዋወቀኝ:: እኔና አብርሃ ፀሎት ተያይዘን ከመውጣታችን በፊት ግን ባለስልጣኑ አንድ ጉዳይ አንስቶ ከአብርሀ ጋር ተነጋገረ:: ጉዳዩ በተዘዋዋሪ ሀየሎምን የተመለከተ ስለነበር ትኩረቴን ሳበው!

«ልጅትዋ ተሻላት?» ሲል ነበር ባለስልጣኑ አብርሃን የጠየቀው::

«ደህና ነች:: ምግብ መውሰድ ጀምራለች:: ሌሊት ግን ትቃዥ ነበር:: የሀየሎምን ስም ደጋግማ ታነሳ ነበር:: ዜናውን ድንገት ከሬድዮ በመስማትዋ መሰለኝ ራስዋን የሳተችው ...»

«ምፅዋ ለምን አትወስዱዋትም? አሁን አየሩ ቀዝቃዛ ስለሆነ እዚያ ይሻላት ይሆናል ...»

አብርሃ ፀሎት ራሱን በመነቅነቅ ተስማማ:: ከዚያም ተያይዘን ወጣን:: ስንወጣ እጅግ ጉዋጉቼ በሀየሎም ምክንያት ራስዋን ስለሳተችው ሴት ማንነት ጠየቅሁት:: ግራ ተጋባሁ:: የሀየሎም ባለቤትና ልጆች አዲሳባ ናቸው:: ቤተሰቡ ትግራይ መሆናቸውን አውቃለሁ:: በሀየሎም የእረፍት ዜና ራስዋን እስከመሳት የምትደርሰው ሴት ማን ልትሆን ትችላለች?





«ታጋይ ናት» አለኝ አብርሃ::

«የሻእቢያ?»

«የለም:: የኢህአዴግ::»

«ታዲያ እዚህ ምን ታደርጋለች? በኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ ነው የምትሰራው?»

«የለም:: ቻይና ቆይታ መመለስዋ ነው:: አሁን እዚህ እረፍት ላይ ናት ...»

«ኤርትራዊት ናት?» ስል ጠየቅሁ::

ምላሽ ግን ሳይሰጠኝ ዘገየ::

መኪና ውስጥ እንደገባን!

«ራት ሪዋ ሬስቶራንት መጋበዝ ሳይሻልህ አይቀርም» አለኝ፣ ሞተር እየቀሰቀሰ::

«ይሁን» ካልኩ በሁዋላ! ርእሰ ወሬውን ወደ ልጅቱ አዞርኩ «... ኤርትራዊት ናት?» ስል መልሼ ጠየቅሁት::

«አይደለችም! ኢትዮጵያዊት ናት» ካለ በሁዋላ «... ይቅርታ ስለ ልጅቱ ከዚህ በላይ ባትጠይቀኝ ደስ ይለኛል» አለኝ::

ይህን ሲለኝ ይበልጥ ሆዴን ቆረጠኝ:: የማወቅ ጉጉቴ አየለ:: ልጅቱ ታጋይ ናት:: ኢትዮጵያዊት ናት:: ቻይና ነበረች:: አሁን ኤርትራ እረፍት ላይ ናት:: ለሀየሎም ያላት ፍቅር ገደብ የለውም:: ግን ግትየ ከኤርትራውያን ጋር ያላት ግንኙነት ምንድነው? ባለስልጣኑ ወደ ምፅዋ እንድትወሰድ ሀሳብ አቅርበዋል:: በዚያ ደረጃ እንዴት ሊታሰብላት ቻለ?

ባህርዬ ሆኖ ያጉዋጉዋኝን ነገር ካላወቅሁ ውጋት ነው የምሆነው:: አብርሃ ፀሎትን አልለቀቅሁትም!

«ዝርዝር ነገሮችን የማወቅ ፍላጉት የለኝም» ስል ጀመርኩ «... አንድ የከነከነኝን ጥያቄ ብቻ ላቅርብልህ! ልጅቱ ኤርትራ ምን ትሰራለች? ቅድም ካደረጋችሁት ጥቂት የቃላት ልውውጥ እንደተረዳሁት ደግሞ የኤርትራ መንግስት እየተንከባከባት ይመስላል:: ለምን? የሀየሎም ዘመድ ናት? የትግራይ ሰው ናት? እዚህ ዘመድ

አላት? ሌላ ልዩ ምስጢርስ አለ? ምንድነው?» ብዬ እየቀላለድሁ ላግባባው ሞከርኩ።

አብርሃ ፀሎት ከልቡ ሳቀ። ስቆ ሲያበቃ፣

«ነገሮችን በጣም አታወሳስባቸው። የኤርትራ መንግስት ልጅቱን አልተንከባከባትም። በመንግስት ደረጃም አትታወቅም። በግል የሚያውቋዋት ባለስልጣናት ግን አሉ። በአንዳንድ ልዩአጋጣሚዎች የተግባቡዋትና የሚያቀርቡዋት ባለስልጣናት ይኖራሉ። ይኸው ነው። በተረፈ እንደገመትከው የትግራይ ሰው አይደለችም። ኦሮሞ ናት። አሁንስ በቅቶሃል?» ሲል አፈዘዘኝ።

'የባሰው መጣ' አልኩ ለራሴ።

«አላምንህም!» አልኩት።

«ለምንድነው የማታምነኝ?»

«የኢህአዴግ ታጋይ - ኦሮሞ፤ ራስዋን እስክትስት ድረስ በሀየሎም ሞት የምትደነግጥ ሴት፤ ኤርትራ ምን ልትሆን ትመጣለች? ነገሩ ጨርሶ የሚገጣጠም ...»

ተናግሬ ሳልጨርስ አንድ የቆየ ነገር ወደ አእምሮዬ መጥቶ ብልጭ አለ። ማመን አልቻልኩም። አይኖቼን አብርሃ ፀሎት ላይ አፍጥጬ ቀረሁ፣

«ምን ሆንክ?» አለኝ።

«ልክ ነህ!» አልኩት ፈገግ ብዬ።

«እንዴት?» አለኝ።

«ልጅቱን አወቅሁዋት። አስታወስኩዋት።»

«አይመስለኝም» አለ በጥርጣሬ እያየኝ።

«አሳምሬ አውቃታለሁ! እስዋም በሚገባ ታውቀኛለች» አልኩት በሙሉ ልብ።

«ማነው ስምዋ?» ሲል ጠየቀኝ።

ስምዋ ኩኑ ሊረሳኝ አልቻለም። ቁመትዋ፣ መልክዋ፣ ሳቅዋ ሳይቀር ፊቴ መጥቶ ድቅን አለ። ገረመኝ። በጣም ተገረምሁ።





'በየት ዞራ መጣች?' ብዬ ተደነቅሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅሁዋት ደርግ ከመውደቁ በፊት፤ በትግሉ ጊዜ ትግራይ በሚገኘው የኢህአዴግ ሬድዮ ጣቢያ በጋዜጠኝነት ስራ ላይ ሳለሁ ነበር። «ታሪክ ፀሐፊ ነኝ» ብላ ነበር የተዋወቀቺኝ። በተለይ የሀየሎምን ታሪክ ለይታ ለመፃፍ እንደምትፈልግ ጭምር አጫውታኝ እንደነበር አስታውሳለሁ። በአስር ቀናት የሬድዮ ጣቢያ ቆይታዋ ብዙ አውግተናል። የህወሀት መሪዎች በሚገኙበት አካባቢ ማረፍዋን ጭምር እንደነገረችኝ ትዝ ይለኛል። በርግጥ ከዚያ ወዲያ ስለ ልጅቱ የተለየ ነገር የሰማሁት ደርግ ከወደቀ በሁዋላ ነበር። በደህንነት መስሪያ ቤት ውስጥ የሚሰራ አንድ ታጋይ ስምዋን አንስቶ፣ «ከለየላቸው ማጅራት መቺዎች ጋር ተመሳጥራ ከፍተኛ ዝርፊያ ስታካሂድ ተይዛ ታሰረች» ሲል አጫውቶኝ ነበር። በወቅቱ ስለልጅቱ በሰማሁት ወሬ ግራ በመጋባቴ «የስም ሞክሼ እንዳይሆን» አልኩት። የሀጥታው መስሪያ ቤት ሰራተኛ የሆነው ታጋይ ግፁም ትክክለኛ የሆነ መረጃ እንዳለው ገለፀልኝ። ቢሆንም ግን ለማመን ተቸገርኩ።

ልጅቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ምሩቅ መሆንዋን አውቃለሁ። በዚህ ላይ ከህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳላት ከማወቅ ባሻገር ሁለት ሶስት ጊዜ ያህል የደህንነት ሚኒስትር ከሆነው ክንፈ ገብረመድህንና ከሌሎች ባለስልጣናት ጋር በመዝናኛ ቦታዎችና በመኪና ውስጥ አይቻያታለሁ። ስለዚህ ልጅቱ ከማጅራት መቺዎች ጋር ለመተባበር የሚያስችል የጀርባ ታሪክም ሆነ ባህርይ ሊኖራት እንደማይችል እርግጠኛ ነበርኩ። ከዚያ ወዲያ ግን ለሁለት አመታት ያህል ስለልጅቱ አልሰማሁም። ወደ ውጭ ሀገር ተሰዳለች ወይም እዚያው እስር ቤት ተከርችማ ሲሆን እንደሚችል ግን ግምት ነበረኝ።

የአሁኑ ግን የተምታታ ሆነብኝ። ባልተጠበቀ አጋጣሚና ሁኔታ ኤርትራ መኖርዋን በመስማቴ ግራ ተጋባሁ። ጆሮዎቼ ነቁ። ልቤ ተነሳሳ። የተደበቀ ታላቅ ምስጢር ድንገት መዳፌ ላይ የወደቀ ያህል ተሰማኝ።

አብርሃ ፀሎት፣

«ካወቅሀት በል ንገረኝ፤ ስምዋ ማነው?» ሲል አፋጠጠኝ። አላመነታሁም። ስምዋን ከነአባትዋ ጠራሁለት።

ፈገግ አለ ...

«ተሳሳትኩ?» ስል ጠየቅሁት::

«ልክ ነህ!»

«ላገኛት እፈልጋለሁ» አልኩት::

«መልካም እነግራታለሁ» አለ::

ራት በልተን ተለያየን::

በነጋታው ማለዳ ላይ አብርሃ ፀሎት ወዳረፍኩበት ሆቴል ደውሎ፣ «ልታገኝህ ፈቃደኛ ሆናለች» አለኝ::

በጣም ተደሰትኩ::

አብርሃ አያይዞ «ዛሬ እኩለ ቀን ላይ ግን ወደ ምፅዋ ትሄዳለች:: አብረሃት ብትሄድ ምን ይመስልሀል? እንዲያውም ልታይህ በጣም ነው የጓጓችው?» አለ::

«ሙሉ ፈቃደኛ ነኝ» የሚል ነበር የኔ ምላሽ::

ካረፍኩበት ካርቱም ሆቴል ድረስ መጥታ እንደምትወስደኝ ገለፀልኝ:: ተስማማሁ:: እኩለ ቀን እስኪደርስ ቡናውንም ሻዩንም እያጋባሁ በየሩብ ሰአቱ ደቂቃ መቁጠር ሆነ:: መልክዋ ትዝ ይለኛል:: ጠይም፣ ረጅም፣ ውብ::

በተለይ ቀልድና ሳቅዋ አይረሳኝም:: በራስዋ ላይ መቀለድና መሳቅ ታዘወትራለች:: እንደ ርችት የሚፈነዳ፣ ጨርሶ ከጆሮ የማይጠፋ ውብ ጣእመ ዜማ ያለው ሳቅና ቀልድ:: በሳል እንደነበረችም አስታውሳለሁ:: ያላነበበችው የመፅሀፍት ዘር የለም:: ላያት ቸኩልኩ:: ሰአቱ ግን ተገትሮአል:: ገና አምስት ላይ ነው:: ድፍን አንድ ሰአት ይቀራል:: ናፈቅሁዋት:: የምስጢር ጉተራ ሳትሆን እንደማትቀር ልቤ ሹክ አለኝ ...

ራሴው ለራሴው የጥያቄ ዶፍ እያዘነምሁ ካርቱም ሆቴል ደጃፍ ላይ ከወዲያ ወዲህ መንጎራደዴን ቀጠልሁ::

ለምን ታሰረች? ከህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር የነበራት ግንኙነት ምንድነው? የሀየሎም ድንገተኛ እረፍት ሀሊናዋን እስክትስት





ያስደነገጣት ለምን ይሆን? ቻይና ለምንና እንዴት ሄደች? አሁንስ ኤርትራ ምን ትሰራለች? ለምን በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ አልተመለሰችም? የደህንነት ሰዎች 'ከማጅራት መቺዎች ጋር ተመሳጥራ ታስራለች' የሚል ወሬ ለምን ነዙ? የሀየሎምን ታሪክ መፃፍዋን ለምን አቋረጠች? ወይስ አሁንም በመፃፍ ላይ ናት?

ጥያቄዎቹ ቀጥለዋል:: ምላሽ ግን የለኝም:: ምክንያቱም ሰአቱ ተገትሮአል:: ሃያ ደቂቃ ይቀራል ...

* * *

... እነሆ ታይቶ በማይጠገበው የቀይ ባህር ዳርቻ ለረጅም ሰአት ተቀምጬያለሁ:: አይኖቹ ሄዶ ሄዶ ከአድማስ ጋር ከሚዋሃደው ዝምተኛ ባህር ላይ አተኩረዋል::

አጠገቤ አንዲት ሴት አለች:: የኦሮሞ ምድር ሴት:: ከንፈሮችዋ ይንቀሳቀሳሉ:: የኔ ጆሮዎች ያዳምጣሉ:: ረጅም ታሪክ ... እንደ ቀይ የምሽት ማራኪ ንቅናቄ ... ለስስ ያለ ድምፅ:: የሚመስጥ ወግ ... በውብ ጣፋጭ ዜማ የታጀበ ትረካ ... ተዝቆ የማያልቅ ታሪክ:: ተደብቆ የኖረ ታሪክ:: ከዝምተኛ እንደበት የሚመነጭ:: ያለማቋረጥ - እንደቡርቃ ወንዝ የሚፈስ ... የዝምታ ጥላ ያጠላበት ታሪክ ...

# ክፍል - አንድ

# ነፍጠኞች ወዮላችሁ!

# የቡርቃ ዝምታ አብቅቶአል!

## ምእራፍ አንድ

### - 1 -

የደህንነት ሚኒስትሩ ቀልቡን የሳተ ነዉ የሚመስለው:: እንዳበደ ሰው እየተጣደፈ ወደ ፕሬዚዳንቱ ቢሮ ገሰገሰ:: ዛሬ በርግጥም ወፈፍ ያደረገው ይመስላል:: ክራቫቱ ተወላግዶአል:: ሲጋራ አያያዙ ልክ አይደለም:: ከመኪናው እንደወረደ የሩጫ ያህል ነበር ወደ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ቢሮ የበረረው:: አተነፋፈሱ ሳይቀር የጤና አይመስልም:: ምናልባትም ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት ውስጥ የዛሬውን ያህል ከባድ ጉዳይ ገጥሞት አያውቅም::

ሆኖም በጥድፊያ ይምጣ እንጂ ወደ ፕሬዚዳንቱ ቢሮ በቀላሉ ዘው የማለት እድል አልገጠመውም:: ፕሬዚዳንቱ ቀጠሮውን ቢያውቁም እንኳ ጥቂት መጠበቅ አለበት:: ይህ ህግ ነው:: የፕሬዚዳንቱ ፅህፈት ቤት ብቻ ሳይሆን የቢሮክራሲው ህግ!

«አስቸኳዩ ነው! እሳቸውም ያውቁታል!» ሲል ፕሮቶኮል ሹሙ ላይ አፈጠጠበት::

«ይገባኛል ክቡር ሚኒስትር ... መምጣትዎን ማወቅ ስላለባቸው ብቻ ነው!»

ይህን ብሎ የፕሬዚዳንቱን ቢሮ በዝግታ ከፍቶ ገባ::

ሚኒስትሩ ይንጉራደድ ጀመር:: ጢም የሚባል ፊቱ ላይ የለም:: እርጅናና መታከት ቆዳው ላይ ይነበባል:: ስራው እንደከበደው ያስታውቅበታል:: ጉብጦአል:: በርግጥ ሁኔታዎች ያጉብጣሉ::

ፋታ የለም! ጦርነት ... ጦርነት ... ፖለቲካ ... አመፅ ... ስሞታ ... ብሶት ... ምሬት ... ሽንፈት ... ጦርነተ ... ፖለቲካ ... የህዝብ ቁጣ ... የአለቃ ቁጣ ... ቁጣ ...

«ይግቡ ክቡር ሚኒስትር! ይግቡ ...»

ፕሮቶኮል ሹሙ ተጣደፈ::

እያይዘም «ደንብ ሆኖ ነው ያጉላላሁዎ:: ምን ይደረግ? በርግጥ የሚገቡኝ ነገሮች አሉ:: የማይገባኝ ደደብ ቢጤ አይደለሁም:: ሆኖም ምን መሰሎት? ... ደንብና ህግን በተመለከተ...»

ሚኒስትሩ አንዱዋንም ቃል ሳይሰማ ነበር ጥሎት ወደ ፕሬዚዳንቱ ምቹ ቢሮ የዘለቀው::

* * *

«ምንድነው የተፈጠረው ችግር?» በሚል ጉርናና ድምፅ ነበር የተቀበሉት::

እሳቸውም የታከቱ ይመስላሉ:: ላለፉት አስራ አምስት ዓመታት አንዳችም መልካም ወሬ የሰሙ አይመስሉም:: መፍትሄ የሚፈልጉ የችግር ቋዋጥኖች እየመጡ ቢሮአቸው ይጉለታሉ::

ዛሬስ ምን ይሆን?

የደህንነት ሚኒስትሩ 'እጅግ ላንገብጋቢ ጉዳይ' ብሎ ከደወለላቸው ገና ሩብ ሰዓት እንኳ አልሞላም:: የሚኒስትሩ ሁኔታ ከወትሮው





ሰየት ስላሰባቸው አይኖቻቸውን እንደመቁናጥ እያናወጡ ነበር የጠበቁት::

«ሶስት አስደናቂ ጉዳዮች በአንድ ጊዜ ተፈፅመዋል!» ሲል ጀመረ ሚኒስትሩ፣

«ምንድናቸው!?»

ትእግስት ባጣ ድምፅ ጠየቁ::

«የመጀመሪያው...» አለ የደህንነት ሚኒስትሩ «የወያኔ ቀንደኛ መሪዎች በእጃችን መዳፍ ውስጥ እንደገቡ የሚያስቆጥር ሙሉ እድል ተገኝቶአል::»

በፕሬዚዳንት መንግስቱ አይኖች ላይ የብርሃን ጮራ ታየ:: 'እኮ እንዴት?' በሚል ስሜትም በደህንነት ሚኒስትሩ ላይ አፈጠጡ::

«አዎን ... ቀዩ ጆፌ ተሳክቶለታል» ሲል ቀጠለ ሚኒስትሩ «... ታስታውሰዋለህ ቀዩን ጆፌ? ከስድስት ወራት በፊት ሰራዊታችንን ከድቶ ወደ ወያኔ እንዲቀላቀል ያደረግነው መስመራዊ መኮንን ...»

«ነግረኸኛል!» አሉ ፕሬዚዳንቱ ለማስታወስ እየጣሩ::

«መልእክት ሰመላክ ችሎአል:: እጅግ አንገብጋቢ መልእክት:: ከሁለት ቀናት በሁዋላ የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ገበሬው 'ክሳድ ግመል' ወንበዴዎቹ ደግሞ 'አውሮራ' ብለው በሚጠሩት ስፍራ ለዘጠኝ ቀናት የሚቆይ አመታዊ ስብሰባ ያደርጋሉ:: ጆፌው የስብሰበውን ቦታና ቀን፣ ስእት ጭምር የሚገልፅ መረጃና ጨርሶ የማያምታታ ካርታ ልኮልናል:: የሚያስደንቀው ጉዳይ ቀዩ ጆፌ የአየር ሃይላችንን ሚስጢሮች እንደሚያውቅ ሆኖ በመቅረቡ መረጃዎችን በፅሁፍ እንዲያቀርብ ወደ ዋሻቸው አስጠግተውታል:: እጅግ ወሳኝ ወታደራዊ መረጃ ነው ያገኘነው::»

ፕሬዚዳንቱ ፊት ላይ ፈገግታ ታየ:: የተስፋና የእርካታ ስሜትም ይንቦገቦግ ጀመር:: በዚህ አመት ይህን መሰል አስደሳችና ተስፋ የሚያሳድር ሪፖርት ሲሰሙ ይህ የመጀመሪያው ሳይሆን አልቀረም::

«ለመሆኑ በስብሰባው የሚካፈሉት እነማን ናቸው?»

ሚኒስትሩ የማስታወሻ ደብተሩን ገላልጦ ማንበብ ጀመረ::

«... መለስ ዜናዊ - ዋና ፀሀፊው ማለት ነው፣ ስዩ አብርሃ፣ ፃድቃን ገብረትንሳኤ፣ አባይ ፀሀዬ፣ ስብሀት ነጋ፣ አለምሰገድ ገብረአምላክ፣ ክንፈ ገብረመድህን - ይኸ የህወሀት የስለላ ጉዳይ ሀላፊ ነው:: ተወልደ ወልደማርያም - ስዩም መስፍን - ይኸ የውጭ

ጉዳዮቻቸውን የሚከታተል ነው፤ እና ... እና ለዘመናት እንደ እሳ እየተሙለጨለጨ ሲያመልጠን የኖረው የወያኔ ቁልፍ ሰው ... ሆሎም አርአያ! ... እነዚህ ናቸው ፊትአውራሪዎቹ፡፡ እነዚህ ተወገዱ ማለት ወያኔ አከተመለት ማለት ነው፡፡ በጣም ቁልፍ ሰዎች ናቸው፡፡ በጣም ... በጣም ... ባለን አቅም ሁሉ መስዋእትነት ከፍለን እነዚህን መርዘኞች ካጠፋን ሁሉም ነገር ይዘጋል ... ሁሉም ነገር ይዳፈናል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብም የእፎይታ ባለቤት ይሆናል፡፡ ይኸው ነው!»

«ይሄ ሆሎም የሚባለው የፖሊት ቢሮ አባል ነው እንዴ?»

«የፖሊት ቢሮ አባል አይደለም፡፡ ስብሰባው ላይ ግን ተገኝቶአል፡፡ ምናልባት በልዩ ሁኔታ እንዲሳተፍ አድርገውት ሊሆን ይችላል፡፡»

ፕሬዚዳንት መንግስቱ ሲጋራቸውን አቀጣጠሉ፡፡

«የቀዩ ጂፌ መረጃ ምን ያህል ይታመናል!?»

«ይታመናል! መቶ በመቶ! ልጁ ጭራቅ ነው! አውሬ! በዚያ ብልህነቱና ጥበቡ ይህን ሊፈፅም እንደሚችል እምነት ነበረኝ፡፡ በስድስት ወራት ጊዜ ውጤት አሳየ፡፡ እድለኛም መሆን አለበት፡፡ ዞሮ ዞሮ ዛሬውኑ የህዝብ ልጅ የሆኑ ታማኝ ፓይለቶች እንዲመደቡልኝ እፈልጋለሁ፡፡ ስልጠናው ላይ ራሴ መገኘት እሻለሁ፡፡ የስብሰባውን ዋሻ ለይተው ዶግ አመድ የሚያደርጉ ቀራጥ አብራሪዎች ያስፈልጉናል!»

«መልካም ቀጥልበት!»

ፕሬዚዳንቱ ሌላ ሲጋራ ለኰሱ፡፡

በደህንነት ሚኒስትሩ ሙሉ እምነት አላቸው፡፡ የተግባር ሰው በመሆኑ ይንከባከቡታል፡፡ የቅርብ ወዳጅ ናቸው፡፡ የስልጣናቸውና የህይወታቸው ደጀን እንደሆነም ይገባቸዋል፡፡ ምስጢረኛቸው ነው፡፡ የልብ ፍላጐታቸውን ሁሉ ያውቃል፡፡ ለስጋና ለነፍስ የሚያስፈልግ ማንኛውንም ነገር ያቀርብላቸዋል፡፡ ማንኛውንም!

ያዘዙትን አይኑን ሳያሽ ነው የሚፈፅመው፡፡ በርግጥ የዚያኑ ያህል ደግሞ እንደውሻ ያንቀዋሽሹታል፡፡ ደግነቱ የደህንነት ሚኒስትሩ የውሻንም ሆነ የአንበሳን ባህርያት የመላበስን ልዩ ችሎታ በተፈጥሮው የታደለ ነው፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ ምን ይሆን?

«ሁለተኛው ጉዳይ...» አለ የደህንነት ሚኒስትሩ፡፡

«... ዛሬ ማለዳ የሻእቢያ ቁልፍ ሰው እጃችን ላይ ገብቶአል፡፡





በማይታመን ትንሽ ፍንጭ፤ ጨርሶ ተስፋ በሌለው ግምታዊ ሁኔታ፤ አብርሃ ፀሎት የተባለ የአስመራ ከተማ የሻእቢያ የስለላ ሃላፊ በቁጥጥራችን ስር ውሎአል፡፡ እስካሁን አንድም መረጃ አልሰጠም፡፡ ቢሆንም የተለያዩ ሙከራዎችን በማድረግ ልናናዝዘው እንችላለን፡፡ በተለይም በቅርቡ ለምናደርገው የሳይኮሎጂካል ዎር ፌር ጥናት ሊጠቅመን ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡»

ፕሬዚዳንት መንግስቱ ራሳቸውን ላይ ታች ሲወዘውዙ ቆይተው፤

«ወደ ሶስተኛው ጉዳይ ዝለቅ!» ሲሉ አዘዙት፡፡

«ሶስተኛው መጥፎ ወሬ ነው፡፡ አንድ ሺህ ኦሮሞ ገበሬዎች ቡርቃ በተባለች መንደር ላይ አምፀዋል፡፡ አስቸኳይ መፍትሄ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው፡፡»

«የት ነው ቡርቃ ደግሞ?» ሲሉ ጠየቁ ፕሬዚዳንቱ፡፡

«አርሲ፡፡ ካካ ተራራ ስር ኰረብታ ላይ የተመሰረተች፤ በደን የተከበበች የገበሬዎች መንደር ናት፡፡»

«ካካ ተራራ ደግሞ ወዴት ነው? ጭላሎን ነው የማውቀው?»

«ካካ ተራራ በጭላሎ አውራጃ ውስጥ የሚገኝ ትልቅ ተራራ ነው፡፡ ቁመቱ ከጭላሎ ይበልጣል፡፡ አፄ ምንሊክ ያኔ አገር ሲያቀኑ ከኦሮሞዎች ጋር ከፍተኛ ውጊያ ያካሄዱት በዚህ አካባቢ መሆኑ ይነገራል፡፡ አሁን ድረስ የቡርቃዎች ልብ አልረገበም፡፡ መሳሪያም አላወረዱም፡፡ የቀበሌ አስተዳደር ለማዋቀር ተሞክሮ አሻፈረኝ ብለው በራሳቸው ባህላዊ ስርአት በመተዳደር ላይ ያሉ አረመኔዎች ናቸው፡፡ ዘንግተኸው እንደሁ እንጂ 'ወርቅ ሲነጠፍላቸው ፋንዲያ ይሸለናል ካሉ ተውአቸው' ብለኸን ነበር፡፡»

«ታዲያ እነርሱ የጭላሎ ገበሬዎች አይደሉ እንዴ?»

«ለከነህ! በወቅቱ 'የጭላሎ አውራጃ የአንድ መንደር ገበሬዎች' በሚል ነበር ሪፖርት የቀረበው፡፡ የመንደሪትዋ ስም 'ቡርቃ' ነው የሚባለው፡፡ በጦረኛነታቸው የታወቁ ናቸው፡፡ እንደሚነገረው ቡርቃ ከምንሊክ ጦር ጋር ሲዋጉ በነበሩ አመፀኞች የተመሰረተች መንደር ናት፡፡»

«አሁን ታዲያ ምን ይፈጠር ነው የሚሉት?» አሉ ፕሬዚዳንቱ በቁጣ፤ አይኖቻቸው እንደመቂናጥ ከወዲያ ወዲህ ይካለቡ ያዙ፡፡ ትንፋሻቸው ከመቅፅበት መቆራረጥ ጀመረ፡፡

«በውል የታወቀ ነገር የለም፡፡ ከመፈክሮቻቸው ለመረዳት እንደሞከርነው ግን በአካባቢው ካሉ አማራ ገበሬዎች ጋር ካላቸው

መጥፎ ግንኙነት ጋር ይያያዛል:: ግንኙነት ማለቴ ኦሮሞዎቹ በንጉሳውያን ገገሮች አስተዳዳር የተፈፀመባቸውን አንዳንድ በደል በቀጥታ ከአካባቢው አማሮች ጋር ያያያዙት ይመስለኛል:: ለአመፅ የገፋፋቸው ዋናው ምክንያት ግን ከሰባ አመት በፊት የተነገረ አንድ ትንቢት መሆኑ ይወሳል:: ትንቢቱ ፍሬከርስኪ የጠንቋዮች ተረት ነው:: ዋቆ ተብሎ ከሚጠራ አንድ ሽማግሌ ጋር የተያያዘ ነው:: የመነሻ ታሪኩን ዝርዝር በሪፖርት ላቀርብ እችላለሁ:: አሁን ግን አስቸኳዋይ ውሳኔ ያስፈልገናል::»

«አመፁን ለመግታት ምንድነው ያሰባችሁት?»

«አመፁን በቅስቀሳና በተለያየ መንገድ ለማቆም እንሞክራለን:: ገበሬዎቹ አሻፈረን ብለው የሰፈሩበትን ተራራ ለቀው ወደ አማሮቹ መንደር መጉዋዝ ከጀመሩ ግን የግዴታ እርምጃ መውሰድ ይኖርብናል::»

«ገበሬዎቹ ታጥቀዋል?»

«ጠመንጃዎች አሉዋቸው:: ጦርና ቸቦዎችንም ይዘዋል::»

«ችቦው ደሞ ምን የሚሆን ነው?»

«የአማሮቹ ጎጆ ላይ እሳት መለኮስ ያሰቡ ይመስለኛል::»

«አማሮቹስ?»

«ተመሳሳይ ትጥቅ ነው ያላቸው::»

«አንድ ላይ ነው የሚኖሩት?»

«አይደለም:: አማሮቹ ከቡርቃ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ 'ቅዱስ ሚካኤል' ከምትባል ኮረብታ ጀርባ ነው የሚኖሩት:: እነዚህም አማሮች የምኒሊክ ወታደሮች የልጅ ልጆች መሆናቸው ነው የሚነገረው:: የቡርቃ ገበሬዎችን አመፅ እንዲከላከሉ ሰፍረው በዚያው ራሳቸውን ወደ ገበሬነት የለወጡ ናቸው»

«እንግዲያው በእቅዳችሁ መሰረት ቀጥሉ!»

ሚኒስትሩ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ቴሌፎኑ አመራ:: አንስቶም ይደውል ጀመር::

የሚፈልገው ድምፅ መጣለት::

«ስራው በታቀደው መሰረት ይከናወን!» ሲል አዘዘ::

ከዚያም በተረጋጋ መንፈስ ወደ ፕሬዚዳንቱ ተመለሰ::

ፕሬዚዳንቱ ሲጋራቸውን በዝግታ እየማጉ በአሳብ ጭልጥ ብለው ጥቂት ቆዩ:: ንደታቸው ከሲጋራው ጢስ ጋር እየበነነ መጥፋት





ጀመረ:: ደንታ ማጣት በሚታይበት ድምፅም፣

«ከጀርባ የፖለቲካ ግፊት ያለ ይመስልሃል?» ሲሉ ጠየቁት::

«ጨርሶ አይታሰብም:: ቡርቃ ላይ አንድም የተማረ ሰው የለም:: ገበሬዎቹም ሬድዮ የላቸውም:: የጠንቋዮች ቅዠት ነው ለዚህ ያበቃቸው::»

ፕሬዚዳንቱ ጥቂት ሲያውጠነጥኑ ቆይተው፣

«በዚህ ወቅት ከኦሮሞዎች ጋር መጋጨት አያስፈልግም:: ያለነሱ ሙሉ ድጋፍ የትም መድረስ አንችልም:: በአሁኑ ወቅት የኤርትራና የትግራይ ወንበዴዎችን ገጥግጦ የያዘልን የኦሮሞ ወጣት ነው:: ይህንን ህዝብና ሃይል ጨርሶ ማጣት የለብንም::»

እንደገና በዝምታ ለደቂቃዎች ያህል ቆዩ::

«ጥናቱስ ምን ላይ ደረሰ?» አሉ ፕሬዚዳንቱ፤ ድንገት ርእሰ ወሬ ለውጠው::

«የትኛው ጥናት?»

«በወንበዴዎች ላይ የሳይኮሎጂካል ዎር ፌር ...» ብለው አቋዋረጡ::

«ቅድመ ሁኔታዎችን አጠናቀን ጨርሰናል:: ሰው ምልመላ ላይ ነን:: በርግጥ ሰው ምልመላ ላይ አንዳንድ አከራካሪ ሁኔታዎች ገጥመውናል: በተለይ የኤርትራ ጉዳይ ከበድ ያለ ነው:: ካሉን ኤክስፐርቶች ጠንካራውን መመደብ እንዳለብን ደግሞ ግልፅ ነው:: በአጋጣሚ የሙያ ብቃቱን በተሻለ ሁኔታ በማስመስከር ላይ ያለ አንድ ባለሙያ ነበረን:: ችግሩ ግን ይህ ሰው የፓርቲያችን አባል አይደለም:: ስራው ደግሞ በፓርቲ አባሎች መሰራት እንዳለበት ተወስኖአል::»

«አባል ለምን አላደረጋችሁትም?»

«በቅርቡ ነው ከምእራብ ጀርመን የተመለሰው:: በዚህ ምክንያት ስጋት ነበረኝ:: ልጁ ደሞ መገናኘት ያዘወትራል፤ እንጂ ቢጠየቅ እንኩዋ የሚደሰት አይነት ሰው ነው::»

«ከተማመናችሁበት አባል አድርጉት! ወደ አስመራ ከመሄዱ በፊት ግን እኔም ላነጋግረው እችላለሁ:: ማነው ስሙ?»

«እኖሌ ዋቆ!»

ፕሬዚዳንቱ አይናቸውን ጠበብ ፊት አደረጉ::

«ኦሮሞ ነዋ! በዚህ ላይ ምእራብ ጀርመን?»

የደህንነት ሚኒስትሩ ፈገግ አለ።

«እኔም በመጀመሪያ የዚያ አይነት ስሜት ነበር ያደረብኝ። ልጁን ሳየው ግን ሀሳቤን ለወጥኩ። በጣም ብርቱ ነው። ፈጣን ነው። የልቡን ይናገራል። ሶስት ባለሙያዎች የሚሰሩትን ብቻውን ማከናወን የሚችል ንቁ ልጅ ነው። ለፖለቲካ ጉዳዮች ደንታ ያለው ባይመስልም፤ ከሙያው ጋር በተያያዘ የሚያቀርባቸው ሀሳቦች ግን መሬት ጠብ አይሉም። በርግጥ በዚሁ ልጅ ላይ ዛሬ ጠዋት አንድ አስደንጋጭ ነገር ሰምቼ ነበር። ልጁ ዛሬ አመፅ በተቀሰቀሰበት ቡርቃ ነው የተወለደው። ለአመፁ መቀስቀስ በሰበብነት የሚጠራው ዋቆ የተባለው ሽማግሌ በማደጎ ልጅነት ያሳደገው ነው።»

የፕሬዚዳንቱ አይኖች ወዲያ ወዲህ ይካለቡ ጀመር። ማመን እያቃታቸውም «... አብዳችሁዋል!?» ሲሉ ጮሁ።

የደህንነት ሚኒስትሩ ግን የመበገር ስሜት አላሳየም።

«አኖሌን ከአመፁ ጋር የሚያገናኘው ምንም ጉዳይ የለም። ይሄን አጣርተናል። ሌላው ቀርቶ ከጀርመን መልስ ቡርቃ ሄዶ አባቱን የጠየቀው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ጨርሶ ጠባብ የሆነ የጎሰኝነትን ስሜት አያንፀባርቅም። በዚህ ላይ ወደሀገር ቤት እንዲመለስ ያደረገው ጓዋድ ጂብሪል ነው። ከጂብሪል ጋር ጓዋደኛሞች ናቸው። ጀርመን ሀገር ነው የተዋወቁትና የተወዳጁት። ይልቁን አኖሌ ራሱ ዛሬ ወደ ቡርቃ ሄዶ አመፁን ለማቆም ጥረት እንዲያደርግ ልንልከው ነው ያሰብነው። ይህም መፈተኛው ይሆናል።»

ፕሬዚዳንቱ ረገብ አሉ፤ ባህርያቸው ነው። ጠንከር ሲሉባቸው ላላ ይላሉ።

«ቢሆንም ክትትል ይደረግበት። በድምፅ መቅጃ መሳሪያዎች ሳይቀር ተከታተሉት። ሙሉ በሙሉ አትመኑት። የጠላቶቻችን ቃፊሮች ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ ሰርገው ገብተዋል! ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል! የስሜን ወንበዴዎች በአማራና በኦሮሞች ነው የሚጠቀሙብን። ጥንቃቄ ያሻል።»

ቡና ቀረበላቸው። እያጣጣሙም ወጋቸውን ቀጠሉ፤

«ውጤቱን ከስር ከስር ማወቅ እፈልጋለሁ!»

«የትኛውን?»

«የሶስቱንም።»

«ማለት?»





«የቡርቃውን፣ የወያኔ መሪዎቹንና የጥናቱን ...»

«መልካም!»

ለጥቂት ሰከንዶች በዝምታ ተዋጡ። ሚኒስትሩ ልክ በዚህ ጊዜ ፕሬዚዳንቱን መሰናበት እንዳለበት ያውቃል። አሳምሮ ያውቃል።

- 2 -

የቢሮው በር በችኮላ ተበረገደ ...

አኖሌ ዋቆ ደንግጦ ቀና ሲል ከቅርብ አለቃው ጨፍጋጋ ፊት ጋር ተጋጨ - ጂብሪል አሊ። አኖሌና ጂብሪል እንደ ጓዋደኛ ተግባብተውና ተነጋግረው መስራትን ያዘወትራሉ። ጂብሪል በህዝብ ደህንነት ውስጥ የሚኒስትሩ ልዩ አማካሪ ሲሆን፤ በጀርመን ሀገር ከታወቀ ዩኒቨርስቲ በስነ ልቦና ትምህርት የማስትሬት ዲግሪ ያለው አኖሌ ዋቆ ግን በከፍተኛ ኤክስፐርት ደረጃ የሚያገለግል የበታች ሰራተኛ ነው።

«እንደምነህ አኖሌ!»

«ምን ሆነሃል? የተቻኮልክ ትመስላለህ» አለው።

በርግጥም ጂብሪል መቻኮል ብቻ ሳይሆን ፊቱም ልክ አልነበረም። መረበሹ ይታወቅበታል። እንደነገሩ ከሚያበጣጥረው ጠጉሩና፤ ከተመሰቃቀለው ጢሙ ጋር ፈገግታው ሲጠፋ አውሬ ነው የሚመስለው። የያዘውን ፋይል አኖሌ ጠረጴዛ ላይ ወርውሮ ወንበር ስቦ ተቀመጠ።

«ችግር አለ እንዴ ጂብሪል?»

«ያውም በኩንታል!» ብሎ የወትሮው ባልሆነ ድምፅ አምባረቀበት።

አኖሌ ግራ ተጋባ።

ባልተለመደ ሁኔታ ያፈጠጠበትን አለቃውን በጭንቀት ከማስተዋል አልፎ የሚለው ጠፋው። ጂብሪል ሊናገር ቢፈልግም ከምን እንደሚጀምር የተቸገረ መሰለ። ባህርይው እንኳዋ እንዲያ አልነበረም። ጉዳዮችን አቅልሎ ማየትና መፍትሄ ማቅረብ እንደ ልዩ ችሎታው የታመኑለት ናቸው። ጂብሪል ምንም እንኳዋ የሰራተኛው ፓርቲ አባል ቢሆንም ብዙውን ጊዜ የታዘዘውን ሁሉ እንደ ጡሩምባ ከማስተጋባት የተቆጠበ የስራ ሰው ነው። የደህንነት ሚኒስትሩን ግማሽ ስራ ያከናውናል ይባላል። ከፍጥነቱ የተነሳ ስራዎችን በየክፍል ኃላፊዎች ቢሮ እየተዘዋወረ ማከፋፈል ይቀናዋል።

የዛሬው የጂብሪል ባህርይ ግን እደናጋሪ ሆነበት - ለአኖሌ።

እንደወትሮው በቀጥታ ወደስራ ከመግባት ይልቅ ቁጣ አስቀደመ።

«ምን ሆነሃል ጂብሪል!?» አለው ደግሞ።

«እውነቱን እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ!» የሚል ምላሽ ሰጠው ከረር ባለ ድምፅ።

አኖሌ ትንፋሹ እጥር አለበት። የገዛ ጆሮውን ተጠራጠረ። ከአንድ ቀን በፊት አብረው ነው ያመሹት። ምን ተገኘ ባንድ ሌሊት?

«የተፈጠረ ችግር አለ?» አለው አኖሌ።

«ምንም እንደማትዋሽ ቃል ግባልኝ!?»

አኖሌ ከተቀመጠበት በርግጐ ተነሳ። በእሳት ጨዋታ የተጀመረ ያህል ተሰማው። ከልብ ጉዋደኛው እንዲህ ያለ ቁጣ ሲወርድበት ስሜቱን ሊቆዋቆዋመው አልቻለም። ሆኖም ጂብሪልም ተፈናጥሮ ብድግ አለና ሽጉጡን ከሽንጡ ላይ መዘዘ፣

«ተቀመጥ!»

አኖሌ እንደደነዘዘ ተቀመጠ። አይኑን ከሽጉጡ አፈሙዝ አልነቀለም። ተፋጠጡ። አኖሌ በደከመ ድምፅ፣

«ጉዳዩ ምንድነው?» ሲል ጠየቀው።

«ቃፊር ነህ!»

«ማን!? እኮ እኔ!?» እንደ ብራቅ እየጮኸ፣ ጣቱን የገዛ ልቡ ላይ ጠንቆለ። በግልባጩ ቁጣው ነደደ።

«አዎን አንተ! አኖሌ ዋቆ! ለኦሮሞ ወንበዴዎች ወይም ለሻእቢያ አሊያም ለሲአይኤ ... ለሰይጣንም ሊሆን ይችላል፤ እየሰለልክ ነው ... በደንብ አዳምጠኝ ... ሀቁን ካልነገርከኝ ጭንቅላትህን እዚሁ ነው የማፈነዳት። ባንተ ጦስ እግሬ ላይ ሰንሰለት እንዲቆለፍ አልፈልግም። ገባህ!?»

ከዚያም ድምፁን ረገብ ለማድረግ እየሞከረ፣

«... ሰላማዊ ኑሮዬ እንዲናጋ አልሻም። ሀቁን ንገረኝ። ህይወትህን ለማዳን ያለሁህ ብቸኛ ረዳት እኔ ብቻ መሆኔን እስተውል። እኔን ለማታለል በቃጣህበት ደቂቃ ያለምህረት አሳልፌ እሰጥሃለሁ። ከዚያም በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ለዘልአለም ታሽልባለሁ። ምናልባትም ከመገደልህ በፊት በጆሮ ለመስማት እንኳዋ የሚከብዱ ስቃዮችን በቁምህ ትቀበላለህ።»





አኖሌ ዋቆ ተስፋ በመቁረጥ የልብ ጉዋደኛዬ ብሎ የሚያምነው ሰው የሚያወርድበትን ሀጢያት በዝምታ አዳመጠ። አዳምጦ ሲያበቃ አዘነ። ከልቡ አዘነ። ያዘነው ከአስራ ስምንት ወራት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት በመወሰኑ ነበር።

አኖሌ የሃያ ዘጠኝ ዓመት ወጣት ነው። መልከ መልካም፤ መለሎ። ትምህርቱን የጨረሰባትን የሀምቡርግ ከተማ ለቆ በጦርነት ወደምትታመሰው ሀገሩ የተመለሰው ይህንኑ አሁን ሽጉጥ ይዞ የሚዝትበትን ሰው አምኖ ነበር። ምእራብ ጀርመን ያሉ ወዳጆቹ መክረውት ነበር - እንዳይመለስ። አስጠንቅቀውት ነበር - ሊደርስበት የሚችለውን ችግር እያስረዱ። ማስጠንቀቂያቸውን ግን ችላ አለው። ስራና የመኖሪያ ቤት ካገኘ፤ መኪና ማስገባት ከቻለ፤ የልጅነት ፍቅረኛውን አግብቶ ከኖረበት ማህበረሰብ ጋር መቀላቀልን እንደ ትልቅ ፀጋ ነበር የቆጠረው። በእድሜ የገፉ አሳዳጊ አባቱን በህይወት ለማግኘትም ጉዋጉቶ ነበር። በተስፋም ነበር የተመለሰው። አባቱን በህይወት ማግኘት ችሎአል። ጂብሪልም ቃል የገባለትን የመኖሪያ ቤትና የስራ ጉዳይ ጨረሰለት። ያጣው ቢኖር የልጅነት ፍቅረኛውን ብቻ ነበር።

ሀወኒ ትባላለች። እገር ምድሩን አስሶ የገባችበትን ማወቅ አልቻለም። ቢሆንም ኑሮው መልካም መሆን ጀምሮ ነበር። የዛሬው ዱብእዳ ግን እንግዳ ሆነበት። በጀርመን ሀገር ቆይታው ትምህርቱን ቶግቶ ከመከታተል አልፎ የጐሳ የፖለቲካ ተሳትፎ አልነበረውም። በርግጥ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ ይከታተላል። በአውሮፓ ደማቅ ከተሞች ተቀምጠው ስለ ኢትዮጵያ ገበሬዎች የሚሰብኩትን ፖለቲከኞች ግን ከልቡ ነበር የሚንቃቸው። አሁን ግን ጂብሪል «የየትኛው ድርጅት ቃፊር ነህ?» ሲል አፋጦ ይዞታል።

በእጅጉ አዘነ። ለመፀፀት ግን ጊዜው እንዳለፈበት ተረዳ። ተስፋ ባጣ ድምፅ፣

«የማንም ሰላይ አይደለሁም!» የሚል ምላሽ ሰጠው።

«እርግጠኛ ነህ?»

«አትጠራጠር!

ጂብሪል በረጅሙ ተነፈሰና ሽጉጡን ሽንጡ ላይ ሽጦ እነበረበት ወንበር ላይ ተቀመጠ።

ለደቂቃዎች በዝምታ ሲተያዩ ቆዩ።

«አኖሌ ... እርግጠኛ ነህ?»

ጂብሪል በሚማፀን ድምፅ ነበር ደግሞ የጠየቀው::

አኖሌ ግራ ተጋባ:: የጂብሪል የሚለዋወጥ ስሜት አደናገረው:: ቴአትር የሚሰራ መሰለው::

«እመነኝ!» አለ በተስፋ::

«እኔ አልጎዳህም:: እውነቱን ብቻ ንገረኝ:: ከዋሸህ እብረን ነው ሲኦል የምንወርደው:: እባክህ!?»

አኖሌ ጠረጴዛውን በቡጢ ደለቀና ጮኸ::

«አይደለሁም! አይደለሁም! እኔ አኖሌ ዋቆ የምፈፅመውን የማውቅ ሰው ነኝ! ለስለላ ስራ የሚያበቃ ዝንባሌም ባህርይውም የለኝም! አማሮች በኦሮሞ ላይ ያላቸው አጉል ንቀት ያናድደኛል:: ይህን ስሜቱን ደግሞ ከተዋወቅንባት እለት ጀምሮ አሳምረህ ታውቀዋለህ:: ይህም ሆኖ ጉዋደኞቹ ሁሉ አማሮች እና ትግሬዎች ናቸው:: ተራ ጠባብ ዜጋ አለመሆኔን ከዚህ መገንዘብ ትችላለህ:: በተቀረ ያንተ መንግስታዊ ምስጢሮች መቼ ነው ያጉዋጉኝ? አንድ አመት ሙሉ ስታውቀኝ ምን ነበር ፍላጐቴ? ከመፅሀፍ ብብት ወጥቼ አውቃለሁ? ላንተ የፖለቲካ ዝባዝንኬዎች ጆሮዬን ሰጥቼ አውቃለሁ? ስለህይወት ያለኝን ፍልስፍና አታውቅም? እንዴት እንግዳ ሆነህ ትመረምረኛለህ? ወይም በኔ ላይ የታሰበ ልዩ ጥቃት ካለ ብናየው በተሻለ»

አኖሌ ጥቂት ጋብ ካለ በሁዋላም፣

«... ኸረ ለመሆኑ ምን አይነት አስተማማኝ መረጃ ቢደርሳችሁ ነው እኔን ቃፊር ለማለት የበቃችሁት?» ሲል በመደነቅና ለመስማት በመጉዋጉዋት ጠየቀው::

«መረጃ ከተገኘብህስ?» ሲል ጂብሪል ድንገት አፈጠጠበት::

«ስቀለኝ!»

«አኖሌ ...»

«ግደለህም ... መቼም እብድ አይደለሁም::»

«አንድ ጉዳይ ልንገርህ!»

«ምን?»

«በዚህች ደቂቃ የደህንነት ሰዎች የመኖሪያ ቤትህን አገላብጠው እየበረበሩ ነው» ብሎ የአኖሌን ስሜት ለማጤን ተዘጋጀ::





አኖሌ ግድ አልሰጠውም:: ይልቁን ፈገግ አለ፣

«ሻንጣዎቼን ገነጣጥለዋቸው ይሆናላ! ቁልፍ ብትጠይቀኝ ግን የፍተሻ ስራችሁን ያቀልላችሁ ነበር:: እነዚያ ውድ ሻንጣዎች በግዴለሽነት ከተገነጠሉ መቼም ሊፈፀማችሁት የዱርዬነት ተግባር ከሳራውን መጠየቁ አይቀርም::»

«ቤትህ የሚያጠራጥር ሰነድ አለህ?»

«በጀርመንኛ የተፃፈ ዲግሪዬ አለ:: ፖሊሶችህ የአነግን የመታወቂያ ካርድ ያገኙ ይመስላቸው ይሆናል::»

«የተፃፈልህ ፖለቲካ ነክ ደብዳቤ ይኖራል?»

«ደብዳቤ የማጠራቀም ባህል የለኝም::»

«የጦር መሳሪያ ይኖርሃል?»

«የሁለተኛውን የአለም ጦርነት የሚያሳይ ፊልም አለኝ::»

«ፀረ ኢትዮጵያ መንግስት የሆኑ መፃህፍት መፅሄትና ጋዜጦችስ?»

«እነሱ ይኖሩኛል!» አለው እያፌዘ::

የጂብሪል አይኖች ፈጠጡ::

«እንድተረጉመው ያዘዝከኝ አንድ የጀርመን ጋዜጣ አለኝ:: የመንግስቱ ሃይለማርያም አስተዳደር ስለሚፈፅማቸው ዝርዝር የግድያ ታሪኮች ይተነትናል» ብሎ ሲጋራ አቀጣጠለ::

ጂብሪል አቀርቅሮ ሲያሰብ ቆየ::

ሰአቱን አየ:: ስምንት ሰአት ከቀኑ:: አሁኑኑ ወደ ዋናው ጉዳይ መግባት እንደሚኖርበት ነበር የሚያስበው:: ቢያንስ አኖሌ ሰላይ ሊሆን እንደማይችል ያለው እምነት ትክክል እንደሆነ መገንዘብ ችሎአል:: ስለዚህ እለቱ ከመጠናቀቁ በፊት ጉዳዩን ቶሎ መፈፀም ይጠበቅበታል:: የደህንነት ሚኒስትሩም ውጤቱን በጉጉት እንደሚጠብቁ ያውቃል::

«ልጅ አኖሌ ...» ብሎ በእርጋታ ጀመረ «ቃፊር ስለመሆንህ የደረሰን መረጃ የለም:: የእስካሁኑ መጨዋጨዋህ አጭር ፍተሻ ብቻ ነው:: ይኸውልህ የስለላ ስራ ተዋናይም ያደርጋል:: ይህን ሁሉ የማስመሰል ንዴት ቢሮዬ ተለማምደ መምጣቴን ብታውቅ ትደነቅ ወይም ትስቅ ይሆናል ...»

አኖሌ በመገረም ጂብሪል ላይ አፈጠጠ::

ጂብሪል እያይዞም «... በዚህ መልኩ ልቀርብህ የወሰንኩት ጥርጣሬና ስጋት ውስጤን ስለበጠበጠው ነው፡፡ በርግጥ አሁንም ቢሆን ቃፊር ላለመሆንህ በቂ ማረጋገጫ የለኝም፡፡ የደህንነት ሚኒስትሩ ግን ክፉኛ ጠርጥረውሀል፡፡»

«እኮ በምን ምክንያት!?» ሲል አምባረቀ፡፡

«መነሻ አላቸው፡፡ ያውም በቂ መነሻ፡፡ የኢሰፓ አባል አለመሆንህ፤ ከጀርመን ሀገር በፈቃድህ መመለስህ፤ የተማርክ ኦሮሞ መሆንህ - ሁሉ ለጥርጣሬ ሊያበቃ ይችላል፡፡ ሚኒስትሩ ግን ሌሎች ለጥርጣሬ የሚያበቁ ፍንጮችንም አግኝተዋል፡፡ ዛሬ ያንተን ንፁህነት ለማሳመን ባለኝ ሃይል ሁሉ ተሙዋገትኩልህ፡፡ ቤትህ እንዲፈተሽና እንድትታሰርም ታዞ ነበር፡፡ ያ ሁሉ በኔ ሃይል ተሸሯል፡፡ አንተ ላይ ጥቂት የክህደት ፍንጭ ቢገኝ ባለን ቅርርብ ምክንያት ብቻ የኔም ነገር ያከትማል፡፡ ስለዚህ ያን ማድረጌ ለራሴም ስል ነበር፡፡ ስለዚህ በዚህ የጋራ ጉዳይ ላይ መነጋገር አለብን፡፡ ይህን ጥርጣሬ ለማጥፋት የምትችልበት እድል ተፈጥሯል፡፡»

«በምንድነው የተጠረጠርኩት? ግልፅ ሆነህ ንገረኝ»

አኖሌ ፋታ አጣ፡፡

ጂብሪል ለጥቂት ደቂቃዎች አቀርቅሮ ከቆየ በሁዋላ፣

«ከትናንት ማምሺያ ጀምሮ ቡርቃ በምትባለው የትውልድ መንደርህ የሚኖሩ አንድ ሺ የኦሮሞ ገበሬዎች አምፀዋል» ሲል ተነፈሰ፡፡

አኖሌ ዋቆ እንደ እንጨት የደረቀ መሰለ፡፡ ጀርባው ላይ ቀዝቃዛ ላብ ኩለል ብሎ ሲወርድ ታወቀው፡፡ ከመቅፅበት በርካታ ጉዳዮች፣ ታሪኮች በአእምሮው ብልጭ ድርግም ይሉ ጀመር፡፡ ቀስ ብሎ ከመቀመጫው ብድግ አለ፡፡

«አባቴ ሞተ ማለት ነዋ!?»

በደከመ ድምፅ ለራሱ ነበር የተናገረው፡፡

«አባትህ አልሞቱም፡፡ ሆኖም በሞት አፋፍ ላይ መሆናቸውን የሚገልፅ መረጃ ደርሶናል» አለው ጂብሪል፡፡ አኖሌ ለምን ይህን ሊል እንደቻለ እያውጠነጠነ፡፡

«አደገኛ ሁኔታ ነው ጂብሪል!» አለ በፍርሃት እየራደ፡፡

«እንዴት?»

አኖሌ መልስ ለመስጠት ዘገየ ...





የአዲስ አበባ ሰዎች የማያውቁት ታሪክ፤ ሊገባቸው ስለማይችለውም ስሜት፤ ለሰባ አመታት በቡርቃ ብቻ ሳይሆን በአር ተራራዎችና ሸለቆዎች ስለተነገረው ትንቢት እያሰላሰለ ነበር፡፡

የቡርቃ ዝምታ!

ምናልባትም በቃፊርነት ከመጠርጠር የከፋ አደጋ ፊቱ ተደቅ ታየው፡፡ ሲጋራውን ምጥጥ አድርጎ መተርኮሻው ላይ ደፈጠጣት፡ አይኖቹ ... ልቡ ... አእምሮው ... ይበልጥ ነቁ፡፡

ጂብሪል ከአኖሌ መልስ ሲያጣ ስለጉዳዩ ማብራራቱን ቀጠለ፣

«... ያመፁት ገበሬዎች የአባትህን፣ የአንተንና እጮኛ የምትሳትን የሀወኒን ስሞች እያነሳሱ በማሞገስና በማቅራራት ላይ መሆናቸውን ከሁለት ሰአት በፊት መረጃ ደርሶኛል፡፡ 'የአማሮችን ጉጀ እናጋያለን' እያሉም ይዝታሉ!»

አኖሌ አይኖቹን ጨፍኖ በውስጡ ይሰቃይ ጀመር፡፡ ይህ እንደሚመጣ የቡርቃ ገበሬዎች ሲያወጉ ደጋግሞ ሰምቶ ነበር፡፡ ሆኖም የቡርቃ ዝምታ ትንቢት ለሱ ተረት እንጂ ወደ ተግባር የሚለወጥ ህያው ህልም አልመሰለውም ነበር፡፡ የቡርቃ እረኞች ጣፋጭ ለዛ እንጂ ... መች የገበሬዎቹ የልብ ምኞት ይሆናል ብሎ ገመተና?

ጂብሪል ቀጠለ፣

«በገበሬዎቹ ቀረርቶ ውስጥ ያንተ ስም መነሳቱ ሚኒስትሩ እንዲጠረጥሩህ አደረጋቸው፡፡ 'አኖሌ ገበሬዎቹን ለአመፅ ቀስቅሶአል' ለማለት ጭምር ከጀሉ፡፡ በዚህ ስሜት ላይ ሳለን ደግሞ ከቡርቃ ወደ አንተ የተላኩ ሶስት ገበሬዎች ሰጋሀር ላይ ተያዙ፡፡ ሲመረመሩ 'አባቱ ከመሞታቸው በፊት ሊያዩት ይፈልጋሉ?' የሚል ምክንያት ሰጡ፡፡ ከቡርቃ አካባቢ የደረሰን መረጃ እንደሚያስረዳው ግን ገበሬዎቹ የአመፁ መሪ እንድትሆን አንተን መርጠውሃል፡፡»

እንደ እንቁራሪት የፈጠጡ አይኖቹን ጂብሪል ላይ ተክሎ ቀረ፡፡ በተሙዋመዋተ ድምፅም፣

«ይህን ሁሉ ሚኒስትሩ ሰምተዋል?» ሲል ጠየቀው፡፡

«ሰምተውታል!»

«ምን አሉ ሲሰሙ?»

ጂብሪል ሪዙን በጣቱ እያፍተለተለ፤

«ትዝ ይልህ እንደሆን ስለቡርቃና ስለራስህ የነገርከኝ ጥቂት ታሪክ ነበረ፡፡ እነዚያን ተረቶች ተጠቀምኩባቸው፡፡ ገበሬዎቹ ከእንስሳ

ባልተሻለ ሁኔታ የሚኖሩ መሆናቸውን፣ ከዚያ ቀበሉ አንተና ሀወኒ ብቻ ፊደል እንደቆጠራችሁ፣ ገበሬዎቹ በራሳቸው የሀልም አለም ተውጠው፣ ተንሳፈው እንደሚንቀዥ፣ ዘላበድኩ:: ከዚያም አንድ ሀሳብ ለሚኒስትሩ አቀረብኩ:: ያ ሀሳብ ሚኒስትሩን ጥቂት አረጋጋቸው:: ባንተ ላይ ታስቦ የነበረው እርምጃ እንዲዘገይ ፈቀዱ:: አሁንም በጉዳዩ ላይ በግልፅ ተወያይተን አስቸኳዩ መፍትሄ ካልፈለግን አንተም እኔም አደጋ ውስጥ ነን::»

«ምንድነው ነገሩ! እንነጋገር!» አለ በጭንቀት እንደተወጠረ::

«የገበሬዎቹ ጥያቄ ፖለቲካዊ ስሜት አለው:: የሚያነሱት ጥያቄ የብሄር ጭቆናን ነው:: አማሮች ከአካባቢው እንዲወጡላቸው ይፈልጋሉ፣ የበቀል ስሜት አርግዘዋል:: ይህን መሰል መርዝ የቋጠረ ሁኔታ እንዴ ከተለኮሰ እንደ ሰደድ እሳት ነው የሚያያዘው:: መንግስት በሰሜን ያለው የፀጥታ ሁኔታ በተመሰቃቀለበት በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ሌላ ትኩሳት እንዲጨመርበት አይሻም:: ስለዚህ ቢቻል አመፁ በሰላማዊ መንገድ እንዲረግብ ይፈለጋል:: ካልሆነ መንግስት ሃይል ከመጠቀም ሌላ አማራጭ የለውም:: የሃይል እርምጃ ከተወሰደ ደግሞ የቡርቃ ገበሬዎች በጅምላ ሊያልቁ ይችላሉ:: ይህን አንተም እኔም መንግስትም የምንፈልገው አይመስለኝም:: ሚኒስትሩን የሳመንኩዋቸው ገበሬዎቹ አንተን እንደመሪ ስለመረጡህ፣ የአካባቢው ተወላጅም ስለሆንክ በመንግስትና በገበሬዎቹ መካከል እንደ ድልድይ ታገለግላለህ በሚል ነው:: ይህ ላንተ ጥቅም አለው:: ወገኖችህን ከእልቂት ታድናለህ፣ የራስህም ህይወት ከአደጋ ይተርፋል::»

አኖሌ አላመነታም::

«ጥያቄ የለውም ጂብሪል ... አሁኑኑ እነሳለሁ!» ሲል አረጋገጠለት::

«ደግ አስበሃል!» አለ ጂብሪል በመርካት «... ሆኖም ገበሬዎቹ ለአመፁ መሪ ትሆን ዘንድ አንተን የመረጡበት ምክንያት አልገባኝም:: ሌላም ግር ያለኝ ነገር አለ:: ቅድም ስለ አመፁ ሳነሳብህ በቀጥታ አባትህ እንደሞቱ አመንክ:: አመፁንና የአባትህን ሞት ምን ያገናኘዋል? ገበሬዎቹ የሀወኒን ስም የሚያነሱትስ ለምንድነው? ለመሆኑ ሀወኒ ማናት? የት ናት?» ሲል የጥያቄ ዶፍ አወረደበት::

አኖሌ ትክዝ ብሎ፣

«ታሪኩ ረጅም ነው:: ሌላ ቀን ላውጋህ:: እንድታውቀው ያህል ግን አመፁ የተቀሰቀሰው 'የቡርቃ ዝምታ' ተብሎ በሚታወቅ ትንቢት ምክንያት ነው:: አባቱ የሞቱ ለት አመፅ እንደሚነሳ የቡርቃ ዝምታም እንደሚያበቃ ይነገር ነበር አለው::»





«ምንድነው የቡርቃ ዝምታ?» ጂብሪል ግራ ተጋባ::

«ቡርቃ ወንዝ ነው:: በመሬት ውስጥ ለውስጥ የሚጉዋዝ ወንዝ:: በመሬት ውስጥ የመሄዱን ጉዳይ ገበሬዎቹ ከማኩረፍ ጋር ነው ያያዙት::»

«ማነው የሚያኩርፈው?»

«ወንዙ! የቡርቃ ወንዝ!»

«የወንዝ ማኩረፍ ምን ማለት ነው አኖሌ?»

«ታሪኩ ረጅም ነው ያልኩህ ለዚህ ነው:: ገበሬዎቹ 'ቡርቃ ከመሬት በታች ውስጥ ውስጡን የሚሄደው ኦሮሞዎች በአማራ ወራሪዎች በመገዛታቸው እፍረት ተሰምቶት ነው! ብለው ያምናሉ:: እንደ ገበሬዎቹ እምነት የቡርቃ ወንዝ ጥንት እንደ ዋቢሸበሌ ደረቱን ገልብጦ የኦሮሞን ምድር ሁሉ ይዞር ነበር:: ምንሊክ አርሲን ሲወርና የገዳውን ስርአት ሲያጠፋው ግን የቡርቃ ወንዝ በኦሮሞዎች ተንበርካኪነት አዝኖና አፍሮ 'መሬታችሁን በጃችሁ ካላገባችሁ እኔን አታዩኝም' ብሎ አካላቱን ሁሉ እንደ ዘንዶ ሰብስቦ ከመሬት በታች እንደቀበረ ከጥንት ጀምሮ እንደ ተረት ይነገር ነበር::»

ጂብሪል በመገረም ራሱን ግራ ቀኝ ሲነቀንቅ ቆይቶ፣

«የሀወኒ ጉዳይስ?» አለው::

«እኔም ግራ ገብቶኛል ጂብሪል» ብሎ ሊያሳምነው ይጥር ጀመር::

«... እኔና ሀወኒ አባትና እናት የለንም:: በማደጉ ያሳደገን አሁን በሞት አፋፍ ላይ የሚገኘው ዋቆ አባዱላ ነው:: እኔና ሀወኒ እንድንማር የተደረገው በቡርቃ ገበሬዎች ፍላጎትና ትብብር መሆኑን አውቃለሁ:: ከፍ ስንል እንድንተጫጭ አደረጉን:: እስከዚያን ቀን ድረስ እህቴ ነበር የምትመስለኝ:: በተቀረ ሀወኒ እሁን ያለችበትን ጨርሶ አላውቅም:: የማውቀው ነገር ቢኖር እንደማፈቅራትና እንዳንት ግጥም የምትወድ ውብ ልጅ መሆንዋን ብቻ ነው::»

«ወላጆቻችሁ እንዴት ሞቱ?»

«ምክንያቱን አላውቅም:: ለአባቴ አንስቼለት ነበር:: 'ሌላ ጊዜ አወጋሃለሁ' ነበር የሚለኝ:: ከዚያ ወዲያ ስለተራራቅን እኔም ስለ ወላጆቼ የማውቅ ልዩ ጉጉት አልነበረኝም:: አባቴ ስለሙዋቾች ወላጆቼ ሳነሳ ይከፋ ይሆናል ብዬም አስብ ነበር:: ግን በአንድ አጋጣሚ ሞተው ሊሆን ይችላል:: ምን ልዩነት ያመጣል?»

«መልካም! አሁን ጊዜ የለንም! ወደ ቡርቃ መሄድ አለብህ:: ሚኒስትሩ ዘንድ ደርሼ እስክመለስ ከቡርቃ የመጡትን ገበሬዎች

አነጋግር። በር ላይ እሉልህ» ብሎት ፈትለክ አለ።

እኖሌ ጃኬቱን አንጠልጥሎ ደረጃዎቹን በፍጥነት ወርዶ ወደግቢው በር ገሰገሰ።

* * *

... የቡርቃ ገበሬዎች 'የቡርቃ ዝምታ!' የተሰኘውን ትንቢት ለሰባ አመታት አዚመውታል። ትንቢቱ የሚፈፀምበትን እለትም በናፍቆት ሲጠብቁ ነበር። ቡርቃ ከካካ ተራራ ስር ተነስቶ ከመሬት ባታች ውስጥ ለውስጥ የሚጉዋዝ ትልቅ ወንዝ ነው። አልፎ አልፎ በተደረመሰ ጉሬ በኩል የቡርቃ ወንዝ ልክ እንደ ዋቢሸበሌና እንደ አዋሽ በከፍተኛ ፍጥነት ሲጉዋዝ ይታያል።

ከሰባ አመት በፊት የአካባቢው ገበሬዎች 'ብሻን ሴጣን - የሰይጣን ውሃ' እያሉ ይጠሩት ነበር። በጦር አዛዥ ማእረግ 'አባዱላ' ተብለው የሚታወቁት ዋቆ ግን 'ቡርቃ' ሲሉ ሰየሙት። ቡርቃ ማለት በኦሮሚኛ 'ምንጭ' ማለት ነው። ከዚህ ስያሜ ጋርም ዋቆ አንድ ትንቢትና አፈታሪክ ለተከታዮቻቸው እንደዋዛ ይተርኩላቸው ነበር፤ እንዲህ እያሉ፣

«ይህ ወንዝ ጥንት በአያቶቻችን ዘመን ስሙ 'ቡርቃ' ተብሎ ይታወቅ ነበር። መነሻውም ከዚህችው በልምላሜዋ ከታወቀችው ከቡርቃ መንደር ሲሆን፤ የኦሮሞዎችን መሬት ሁሉ ውሃ እያጠገበ፣ እያካለለ ይጉዋዝ ነበር። የቡርቃ ወንዝ በኦሮሞ ምድር ዳርቻዎች ሁሉ ይዞር ነበር። ቡርቃ ፈጣን፣ ውሃው እንደ ኩል የጠራ ወንዝ ነበር። ጥንት ኦሮሞዎች ውሃ የሚጠጡት ከቡርቃ ጨልፈው ነበር። ምግባቸውን የሚያበስሉት፤ ልብሳቸውን የሚያጥቡት በቡርቃ ውሃ ነበር። ኦሮሞዎች ህመም ሲሰማቸው ከቡርቃ መጉንጨት ብቻ ይበቃቸው ነበር - ይፈወሳሉ።

መቼ ያ ብቻ ሆኖ?

«ቡርቃ የኦሮሞን ምድር እያካለለ ሲጉዋዝ፤ ከአለት ሲጋጭ፣ ድምፁ ሙዚቃ ሆኖ ልብ ያማልላል። ከገደል ሲዘል ድፍረቱ ለኦሮሞዎች ጀግንነትን ሲያስተምር፤ ለጠላቶቻችን ደግሞ ፍርሃትና ሽብርን ይለቅ ነበር። የቡርቃ ወንዝ ለጥ ባለው መስክ ዝግ ብሎ ሲጉዋዝ ደግሞ ህፃናት ይንቦጫረቁበታል። 'ቡርቃ ተረት አውራልን?' ይሉታል። ስለዘለለው ገደል፣ ስላጥለቀለቀው ሜዳ፣ ስላቋዋረጠው ሸለቆ፣ በሩቅ መንደሮች ስለሚኖሩት ኦሮሞዎች ይተርክላቸዋል።

ታዲያ ምን ያደርጋል?

«የኦሮሞዎችን ግዛት ነፍጠኛ በጉልበቱ ወሰደው። በዚህ





እጅግ የተናደደው የቡርቃ ወንዝ እንደ ዘንዶ ተምዘግዝጐ፤ አካላቱ
ሁሉ ሰብስቦ ከመሬት ስር ተደበቀ። 'ኦሮሞዎች ለነፃነታቸ
ተጋድለው ክብራቸውን ሳያስጠብቁ ከተደበቅሁበት ጉሬ አልወጣ
ብሎ ከመሬት ማህፀን ገብቶ ተከተተ። ሰዎች ከምንጩ ሲጠጡ
ወዲያው ውሃው መርዝ ሆኖ አንጀታቸውን በጣጥሶ ይገድላቸዋል
በዚህ ምክንያት 'የሰይጣን ውሃ' ተባለ። ቡርቃ ግን በኦሮሞዎ
ሽንፈት አፍሮና አዝኖ ነው የተደበቀው» እያሉ ነበር ዋቆ አባዱ
ለወጣቶቹ ገበሬዎች የሚያወጉት።

በወቅቱም በዚህ ታሪክ የተቆጡ ኦሮሞዎች በዋቆ መሪነ
በነፍጠኞች ላይ ዘምተው እጅግ አሰቃቂ ጦርነቶች ተካሄዱ። ከሃያ
በላይ ወጣቶች ዋቆ አባዱላን ተከትለው በፈረሳቸው የአርሲን ተራሮ
አጥለቀለቁ። በየሸለቆው ሲወድቁም 'ቡርቃ በቃህ! ዝምታህ እስከመቼ
እያሉ ይጮሁ ነበር። 'ማረን ቡርቃ!' እያሉም በጦር ተሸቃሸቁ።

የወጣቶቹን ጀግንነትና እልቂት ያስተዋለው የቡርቃ ወንዝ ታዲ
ለዋቆ አባዱላ በህልም ተገልጦ

«ዋቆ! ዋቆ! የዚህ ዘመን ወጣቶች ክብራችሁን ማስመለ
አቅቶአችሁዋል። የኔም ዝምታ ይቀጥላል። አንተ እድሜህን ጨርሰ
የሞትክ እለት ግን፤ የኦሮሞዎች ቁጣ እንደገና ተቀስቅሶ ምድ
ትናወጣለች። ወጣቶች በወጣቶች እየተመሩ ጀግንነታቸው
ያስመሰክራሉ። ያን ጊዜ እኔም አንገቴን ብቅ አደርጋለሁ። ኦሮሞዎ
በሙዚቃዬ ይመሰጣሉ። ጀግንነቴን ይማሩታል፤ ይወርሱታል
ተረቴንም ያዳምጣሉ!» አለው እየተባለ ይነገራል።

ከዚያ ወዲያ የቡርቃ ሰዎች የዋቆ አባዱላን እለተ ሞት በተስ
ይጠብቁ ጀመር። ያን ጊዜ የቡርቃ ዝምታ ያበቃና ጀግናው ቡር
እንደጥንቱ በኦሮሞ ምድር ደረት ላይ እያፏዋጨ ሲጉዋዝ ይታያል
**የቡርቃ ዜማ፣ የቡርቃ ጀግንነት፣ የቡርቃ ተረት ህልም ሆ**
**አይቀርም...**

* * *

... ጂብሪል ከሚኒስትሩ ቢሮ እንደወጣ የሩጫ ያህል ነበር ወ
አኖሌ የገሰገሰው። አኖሌ ከገበሬዎቹ ጋር ወግ ይዞ ነበር።

«አንድ ጊዜ ላናግርህ...» አለው በችኮላ ድምፅ።

አኖሌ ፊጥኖ ወደ ጂብሪል ተራመደ።

«እንግዲህ ሚኒስትሩ በጣም ተስፋ አሳድረውብሃል። አሁን
ሾፌርና መኪና ስለሚዘጋጅልህ ወደ ቡርቃ ገስግስ። ምናልባት ዛ
ማምሻውን ወይም ነገ ማለዳ የሁለቱ ወገኖች ግጭት ሊከሰት ይችላል

ገበሬዎቹ የአባትህን መሞት ብቻ ነው እየጠበቁ ያሉት። አባትህ ከሞቱ ገበሬዎቹ እንደ ጉርፍ ሊተሙ ይችላሉ። ገበሬዎቹ ወደ ሰፈሩበት ኮረብታ ዙሪያ አንድ ሻምበል የስፓርታኪያድ ጦር ተልኮዋል። አዛዡ ሻለቃ ጉተማ ይባላል። እሱም የአርሲ ልጅ ነው። ችግሩን በቅንጅት እንድትፈቱ አሁኑኑ በሬድዮ ይነገረዋል። የኮድ ስምህ 'አልፋ ዋይት!' ነው -እንዳትረሳው። በተረፈ አደራ አኖሌ! ከባድ ሃላፊነት ነው የተጣለብህ ...»

«እነዚህ ገበሬዎች አብረውኝ ቢሄዱ ይጠቅሙኛል» አለ አኖሌ።

«ይዘሃቸው ሂድ!»

«ሌላ ደግሞ ...» አለና እንደ ማሰብ አለ «አንድ ነገር ቃል ግባልኝ!»

«ምን?»

«የገበሬዎችን ቁጣ ለማብረድ የምናገራቸው አንዳንድ ቃላት ካሉ እንደኔ የፖለቲካ አቋዋም ተደርገው መወሰድ አይኖርባቸውም። በተጨማሪ ቀንቶን ባሰብነው መንገድ አመፁን ካቆምነው 'አናርኪስቶችን ምንጠራ' በሚል ሰበብ የቡርቃ ገበሬዎች ላይ አደጋ እንዳይደርስ ቃል ግባልኝ?»

«ለመጀመሪያው ጥያቄህ ... ያሻህን ተናገር። አመፁ ብቻ ይቁም! የሁለተኛውን ጥያቄህን ግን እርሳው። ምንጠራው ከጅምላ የጥይት ውርጅብኝ በላይ አይጉዳቸውም! አይቀርላቸውምም። ይህ የሚሆነው እኮ ሁሉም ከሞት ከተረፉ ነው።»

አኖሌ ጥርጣሬና ፍርሀት ውስጡን አመሱት። በሌላ ወገን ደግሞ መጠቃት ተሰማው። ለቡርቃ መንደር ወገኖቹ የሚያስብላቸው! ምናልባትም ስሜታቸውን የሚረዳላቸው ከቶ እንደሌለ ሲረዳ እንባ ... እንባ .... አለው። ከፊቱ ያለውን ተስፋ መፈለግ ጀመረ። ምንም የለም። ምንም!

ምንም እንደሌለ ሲያምን ብቸኝነት ተሰማው። ሀወኒን አሰባት። በአለም ላይ ፍቅረኛውም እህቱም እስዋ ናት። አሁን ግን የት እንዳለች አያውቅም። ሆድ ባሰው። እንዲህ ሆኖ እንኩዋ አያውቅም ነበር። እንባው ቅርብ ሆነበት። መጮህ አማረው!

«የት ነሽ ሀወኒ!?»





# ወ ን በ ዴ ዎ ቹ !

# ኤርትራና ትግራይ

## ምእራፍ ሁለት

### - 1 -

በተራራማዋ የትግራይ ምድር ውስጥ ክሳድ ግመል የምትባል አነዲት መንደር አለች። በርግጥም በዚህ ስፍራ የህወሀት መሪዎች መሽገዋል። ራሳቸውን ከኢትዮጵያ መንግስት የአየር ድብደባ ለመጠበቅ የመሬት ውስጥ ዋሻዎችን በመስራት ላይ ናቸው። በድማሚትና በመሰርሰሪያ ማሽን እየተቦረቦሩ የሚሰሩት ዋሻዎች እስኪጠናቀቁ ድረስም በጊዜያዊ መጠለያቸው ስራቸውን በማከናወን ላይ ነበሩ።

ዛሬ ከማለዳው አንድ ተኩል ጀምሮ የህወሀት ፖሊት ቢሮ አባላት ስብሰባ ሲያካሂዱ ውለው ተበትነዋል። ወደ ተሲያቱ ቀጣይ ስብሰባ የተመለሱት በጥድፊያ ነበር። ወደ ስብሰባው ዘግይተው

የገቡት ሀየሎም አርአያና አቦይ ስብሀት ነበሩ:: ከመሰብሰቢያው አዳራሽ አድሞ ደጃፍ ላይ ሲጋሮቻቸውን እየማጉ ሲያወጉ ቆዩ::

ሀየሎም በቅርቡ ስለተካሄደበት የግድያ ሙከራ እያወጋቸው ነበር፣

... በአጋጣሚ ነበር ከመስዋእትነት ያመለጠው:: ከወልዲያ በሞተር ብስክሌት ተነስቶ ወደ ጉብዬ ከተማ ይጉዋዝ ነበር - ብቻውን:: አስር ደቂቃ እንደተጉዋዘ ሻንጣ የያዘ አንድ ጐልማሳ ሰው የአስፋልቱን ዳርቻ ይዞ ሲጉዋዝ ተመለከተ:: ሀየሎም ጠረጠረ:: ሻንጣዋ ላይ አይኑን ጣለ:: 'ሰውየው በእግሩ መጉዋዝ ለምን መረጠ?' የሚል ጥያቄም ለራሱ ያነሳል:: 'እኔን ለመግደል ከደርግ የተላከ ሰላይ ይሆናል' ብሎ ግን አልገመተም:: አለፈውና ከመቅፅበት ዘወር አለ:: ሰውየው ሻንጣውን መሬት አኑሮ ዚፑን አይን ለአይን ተገጣጠሙ:: ሰውየው ሻንጣውን መሬት አኑሮ ዚፑን ሲፈታና ሀየሎም ዞሮ ሲመለከት - እኩል:: ሀየሎም ሽጉጡን መሻርጠ ከሞተሩ ዘሎ ወረደ፣ 'እጅ ወደላይ!' ሲል ጮኸ:: ሁለት እጁን ሰቀለ - ባለሻንጣው:: ተጠጋው ሀየሎም:: ሻንጣዋን ጐተታት:: ከፈታት:: እስከ አፍጢሙ ጥይት የጐረሰ ኡዚ::

ይህንኑ ለአቦይ ስብሀት እያጫወታቸው ሳለ የሀየሎም ስም ከጀርባቸው ተጠራ:: የሴት ድምፅ ነበር:: ሁለቱም ዘወር አሉ:: ሀወኒ ዋቆ ነበረች:: ዳገቱን በችኰላ ስትወጣ ተመለከቱዋት::

«ማነች ይህቺ ሴት?» አቦይ ስብሃት ጠየቁ «... ደጋግሜ አያታለሁ:: ተጋዳሊት አልመሰለችኝም::»

«የትግሉን ታሪክ ለመፃፍ ነው የመጣችው» ሲል ምላሽ ሰጠ ሀየሎም::

«ከየት?»

«ጐንደር መምህር ነበረች:: ጠፍታ ወደ ነፃ መሬት እንደገባች እኔ ዘንድ ጥቂት ቆይታ ነበር:: ሁዋላ ወደ ሱዳን ወጣች:: ጀርመን ወደሚገኝ እጮኛዋ የመሄድ ፍላጐት ነበራት:: እንዳሰበችው በቀላሉ የማይሳካ መሆኑን ስታውቅ ግን ተመለሰች:: እንድትታገል ጠይቀናት ነበር:: አልተስማማችም:: ሆኖም የትግሉን ታሪክ ለመፃፍ እንደምትፈልግ አስታወቀች:: ወደዚህ የመጣችውም በተለይ ከህወሀት አመራር የትግሉን አጀማመር ለማግኘት ነበር:: አላነጋገረችህም?»

«የለም! ከአባይና ከመለስ ጋር ግን አይቼያታለሁ»

ሀወኒ አጠገባቸው ደርሳ ነበር:: ዳገቱ ስላደከማት ደጋግማ ትስልና ታለከልክ ጀመር::

«ይቅርታ! አቆምኩዋችሁ!»





«ደህና» ብለው ሁ ለቱም ጨበጡዋት::

«ለጥብቅ ጉዳይ እፈልግሀለሁ!»

«ዘወትር ለጥብቅ ጉዳይ ትፈልጊኝ የለ?» ሲል ቀለደባት::

«የምሬን ነው::»

«ዛሬ አልችልም ሀወኒ:: እናመሻለን:: ነገ ምሳ ሰአት ላገኝሽ?»

«ጥሩ! እሳቸውንም ሳነጋግር እፈልጋለሁ» አለች ወደ አቦይ ስብሀት ዞራ::

ሁለቱም በመስማማት ራሳቸውን ወዘወዙ::

«ይቅርታ አዘገየሁዋችሁ! ወደስብሰባ እየገባችሁ መሰለኝ» ብላ ተሰናበተቻቸው::

እንደገና ቁልቁለቱን ትወርድ ጀመር:: ሀየሎምና ስብሀት ወደስብሰባው ሣሽ ሲያመሩ ጥቂት ቃላትን ተለዋወጡ፣

«እላማዋ በርግጥ ታሪክ መፃፍ ይመስልሃል?» አሉ አቦይ ስብሀት::

«አትጠራጠር! እጅግ ቅን ልጅ ናት!»

«ያልተለመደ ይመስላል::»

«እዎን! አንድ ቀን ብታዋራት ግን ልብዋ ይገባሃል::»

አቦይ ስብሀት ፈገግ አሉ:: ጥቂት ቃላቶችንም እንደዋዛ ጣል አደረጉ::

«በርግጥ አንተ ልቦችን በማወቅ ከኔ እንደምትሻል ግልፅ ነው ...»

አቦይ ስብሃት የጀመሩትን አቁዋርጠው ሲጋራቸውን ለመጨረሻ ጊዜ ማጉት::

ሀየሎም ከልቡ እየሳቀ አቦይ ስብሃትም አጅበውት ወደ ዋሻው ገቡ::

... ሀወኒ ዋቆ ቁልቁለቱን በችኮላ ተንደረደረች:: ሁሌ እንደቸኰለች ነው:: ጠይም መልከ መልካም ናት:: ቁመት አድሎአታል:: ቀጭን ናት ሀወኒ:: ስትስቅ የጥቅምትን አደይ አበባ ታስንቃለች - ይሉዋታል:: ጥርሶችዋ ስለሚያምሩ ብቻ መቼ ሆኖ? አይኖችዋ ይደምቃሉ:: የሀወኒ ውበት ብስለትዋ ነው ብለው የሚሙዋገቱም አሉ:: ውበትማ ብርጭቆም ውብ ሊሆን ይችላል::

ሀወኒ እኮ ከሴትነትዋ በፊት ሰው መሆንዋን የምታውቅ ናት። ሴቶች ብልህ ስለሆኑ መላ ያውቃሉ የሚል ወግዋ አይጠገብም። ይህ ለሀወኒ ሙሉ በሙሉ ይሰራል። ሀወኒ ዘማሪ አባባል አለ። ወፍ ነው የምትመስለው። አካባቢዋን ለመወዳጀት ጊዜ አይፈጅባትም። ለዚህም ነው መሰል ሀየሎም በጣም ይወዳታል። ወደ ተራሮች ጫፍ ይዞአት ይወጣና ለረጅም ሰአት ያወጋሉ። ስለቡርቃ ታወራዋለች። ስለ ኦሮሞ ገበሬዎች፣ ስለ አሳዳጊ አባትዋ! ታጫውተዋለች። ቅንነትዋ ያስገርመዋል። ሰዎች ሁሉ ምነው እንደ ሀወኒ በሆኑ? ብሎ ይመኛል። አንዳንድ ጊዜ እንባው በአይኑ ግጥም እስኪል ድረስ ምኞትዋን ስትከምር አዳምጦአታል። በመካከሉም ስለራሱ እንዲነግራት ትወተውተዋለች። ይቆራርጥባታል። ከዚያም እስዋ ታወጋዋለች።

- ጐንደር እያለሁ በተደጋጋሚ ስለ ጀግንነትህ እሰማ ነበር። በተዋወቅሁት ብዬ እሰብክ። ታውቃለህ ግን ሁኔታህ ሁሉ ፑካቼቭን እንደሚመስል:-

- ማነው ፑካቼቭ? -

- የሩሲያ ድሆች አመፅ መሪ የነበረው ነዋ -

ሀየሎም ብዙ የትግል ታሪኮችን አንብቦአል። የነቼ ጉቬራን ታሪክ እንደ ውሃ ነው የጠጣው። የካስትሮን አጣጥሞታል። የጋሪባልዲን ... የማኦን ... ታሪኮች ያውቃል። በርግጥ እንደ ቬትናሞች የትግል ታሪክ የመሰጠው የለም። የቬትናም ታጋዮች ለሱ ቅርብ ናቸው። የፑካቼቭን ስም ግን ሰምቶ አያውቅም!

- አ! ፑካቼቭንማ ቆይ አመጣልሀለሁ! ግን ከየት? መቀሌ ይኖር ይሆን? በጦርነቱ ቤተመፃህፍቱ ነዶአል እንጂ?

- እንዴት ስሙን እንኳ ሳልሰማ ቀረሁ? -

- ፑካቼቭም ያንተን ስም አልሰማም:- ብላ ሳቀች።

የሀወኒ ሳቅ ረጅምና ውብ ነው። ሀየሎም የሀወኒን ሳቅ ይወደዋል። በትግራይ ዱራዱር ውስጥ ዘወትር ከሚያዳምጣት ሶረኔ ከምትባለው ወፍ ድምፅ ጋር ያመሳስለዋል።

- ፑካቼቭ በርግጥ እኔን ይመስላል? -

- ባየኸው ሀየሎም! በርግጥ የምትለያዩበት አንድ ነገር አለ። እሱ የሚማርካቸውን መኳንንቶች ያለርህራሄ ይገድል ነበር። የፑካቼቭ መልክም ጐኑ ደግሞ ድሆች ሁሉ ወገኖቹ ነበሩ:-

ሀየሎም በተመስጦ እያዳመጣት ሳለ ድንገት ፀጥ አለች።





ችኩልዋ ሀወኒ ምን ፋታ አላት? ደሞ ቀጠለች፣

- አንተ ግን የትግራይን ሰዎች ታስቀድማለህ አይደለም?:-

- በጭራሽ ሀወኒ -

- የእውነት ንገረኝ ሀየሎም! አንተም እንደ ፑካቼቭ ለተበደሉ ህዝቦች ነው የምትታገለው? ግን አንድ ኦሮሞና ሌላ የትግራይ ሰዎች ወድቀው ብታይ ቀድመህ የቱን ታነሳለህ?!

- ኦሮሞውን:-

- አላምንህም ሀየሎም:-

- እመኚኝ! እየፈፀምነው የመጣነው ነው። የገደሉንን ወታደሮች መስዋእትነት እየከፈልን ነው የምንማርካቸው። ከማረክናቸው በሁዋላ የሚተኩሱብን አሉ። ለምን አናጠፋቸውም ታዲያ? ይህን ስልሽ ለትግራይ ታጋይ ህይወት አልሳሳም ማለቴ አይደለም። አላማችንን እንዲያውቁልን እንፈልጋለን። እንኳዋን ስለ ኢትዮጵያ ስለ ሱዳን ወንድሞቻች እሰባለሁ። ስለ አፍሪቃም እቆረቆራለሁ:-

- ይህ የምትለኝ ፕሮግራማችሁ ብቻ ነው። በውስጣዊ ስሜት ደረጃስ?-

- የትግራይን ህዝብ ከህይወቴ በላይ እወደዋለሁ። ይሄ ግን ሌላውን በመጥላት አይመነዘርም:-

- አዲስ አበባ የመግባት እቅድ አላችሁ?:-

- አይቀርም!:-

- ይሳካላችሁ ይሆን?:-

- ሁላችንም በህይወት ላንገባ እንችላለን። ትግሉ ግን በድል እንደሚጠናቀቅ እርግጠኛ ነኝ:-

- ፑካቼቭ ፒተርስበርግን ከብቦአት ነበርኮ። ሁዋላ የሩሲያ ንጉሳዊ መንግስት ጦር ጠንክረና የድሆችን ሰራዊት ሁሉ ጠራረገው። በመጨረሻ ያ ብርቱ ሰው ተያዘ፣ በአንድ ሩብል ገመድም ተሰቀለ። ነፋስም ያን በድን አካል ሲያወዛውዘው ዋለ። ሲዘምሩለት የነበሩትም በሚወዛወዘው በድን አካል አላገጡ። ማምሻውን ታዲያ የዛሩ ንጉስ ታላቅ የራት ግብዣ አዘጋጀ። ምግቡም ጠረጴዛውን ሞላው። ቮድካ ቀረበ። እስኪነጋም ሀሴት ሆነ:-

- አለምን ያንቀጠቀጡትን እስር ቀናት አስታውሺያቸዋ! - አለ ሃየሎም። እና ቀጠለ፣

- ምናልባትም ከስሜታዊ ጉርፍነት ወደ ተደራጀ አመፅ ያደጉት የፑካቼቭ የልጅ ልጆች ሩሲያን አጥለቀለቁዋት:: የዛሩን መንግስት እንደ መኸገር አፈረጡት:: የክሬምሊንን የብረት በር በክንዳቸው ቀራረጡት:: በአለም ላይ ያሉ ስግብግቦች፣ ግፈኞችና ሆዳሞች ተንቀጠቀጡ ... የውልሽ ሀወኒ ... ከብዙ አመት በፊትም ከዚህ ከትግራይ ምድር መጥረቢያ ይዘው የአፄ ሀይለስላሴን ጦር ያፍረከረኩ ገበሬዎች ነበሩ:: ቀዳማይ ወያኔ እንላቸዋለን:: ግን ስላልቻሉ ተደመሰሱ:: ከብዙ አመታት በሁዋላ ደግሞ የዚህ ዘመን ወጣቶች ተነስተናል:: እኛ ግን ድል እናደርጋለን:: ምክንያቱም ስሜት የሚነዳን የቁጣ ጉርፍ አይደለንም:: አላማ አለን:-

ሀወኒ በተመስጦ ስታሰላስል ቆይታ፣

- ያልከው ሁሉ ገብቶኛል:: እኔም ቢሆን የፑካቼቭን ታሪክ በድጋሚ መፃፍ አልፈልግም:: ግን ለምንድነው ታሪክ በግለሰብ በኩል እንዲፃፍ የማትፈቅዱት?:-

- ትግሉ የህዝብ ስለሆነ ነዋ!:-

- ቢሆንም አንተ ለትግሉ መሳካት ወሳኝ ሰው ነህ!:-

- ወሳኝ አይደለሁም ሀወኒ:: ጠቃሚ የሚባለው ቅፅል ስም ይበቃኛል:: እኔና ጉዋደኞቼን ትግሉና ህዝቡ ነው የፈጠረን:: እኔን ብቻም ደሞ አይደለም:: ሌሎች ጀግኖችንም ፈጥሮአል:: ወደፊትም ይፈጥራል:: ስለዚህ ግለሰቦችን ማእከል ማድረግ ብዙውን ጊዜ የህዝቡን ተሳትፎ ያኮስሰዋል:: 'ምንሊክ ጣሊያኖችን ድባቅ መታ' እንደሚባለው ማለት ነው:-

- ባንተ በኩል የህዝቡን ትግል መግለፅ አይቻልም?-

- ይቻል ይሆናል:: ጥንቃቄ ግን ይጠይቃል:-

- ጓደኞችህ ግን አልተባበሩኝም:-

ሀየሎም ሳቀ::

- እውነታቸውን ነውኮ ሀወኒ:: የኔን ስም ሰማይ ጥግ የሰቀለው ደርግ ነው:: አንቺም ደሞ ይህንኑ ተከትለሽ ነው ለመሄድ የሞከርሽው:-

ሀወኒ ለጥቂት ደቂቃዎች ዝም አለች:: የሀየሎምን ታሪክ የመፃፍ ምኞትዋ፣ አየለ::

ይህ የሆነው ትናንት ማምሻውን ነበር::

ነገ ተሲያትም ቀጠሮ አላቸው ...





እንደገና ተራሮቹ አናት ላይ ተቀምጠው ያወጋሉ::

ሀወኒ ... ከሀየሎም ጋር ቀጠሮ ከያዘች በሁዋላ ቁልቁለቱን እየተንደረደረች በግል ከተሰጣት ዋሻ ደረሰች::

ጣራዋ ላይ አፈር የተደመደመባት ከትላልቅ ግንዲላዎች የተገነባች ዋሻ ናት:: የመደብ አልጋና ጠረጴዛ እንዲሁም አንድ ሬዲዮ ቴፕ አላት:: ጠረጴዛዋ ላይ ወረቀቶች ተበታትነዋል:: ወረቀቶቹ ብቻ ሳይሆኑ ሀሳብዋም ተበታትኖባታል:: ሀየሎምን ማእከል ያደረገ የጦርነት ታሪክ ለመፃፍ የምታደርገው ሙከራ ቅጥ እያጣ ሄዶአል:: ቅጥ ያጡትን ቡጭቅጭቂ ወረቀቶች ማንበብ ጀመረች...

*ሀየሎም አርአያ በ1949 ትግራይ ውስጥ አዲነብርኢድ በምትባል ለንዲት ትንሽ መንደር ተወለደ:: በልጅነቱ የእግርኩዋስ ጨዋታ አጥብቆ ይወድ ነበር:: የአካባቢውን ልጆች እያሰባሰበም እሱ የቡድኑ መሪ እየሆነ፣ ጠመንጃዎችን ከእንጨት እየሰራ፣ ወደ ተራራዎች እየወጡ ይጫወቱ ነበር::*

*ሀየሎም በጉርምስና ዘመኑ ወደ ትግል ወጣ::*

*እለቱም ሰኔ 18፣1968 ነበር::*

*ከእህቱ ልጅ ጋር ተያይዘው ወደበረሀ ወጡ:: በልጅነቱ ብርቱ መንፈስ የነበረው ሀየሎም፣ አዲነብርኢድ ትጠበው የነበረው ሀየሎም፣ ከፖሊሶች እየተጣላ ሽጉጥ እየነጠቀ፣ ቤተሰቦቹን ማስጨነቅ የጀመረው ሀየሎም፣ ልቡ ወደበረሃ ሸፈተ:: በጆሮው ሽው ያሉ ወሬዎች ነበሩና እኒያ ጭምጭምታዎች ቀልቡን ሳቡት:: በስሜት ጠሩት - ወደ በረሃ::*

*ከእህቱ ልጅ ጋር ዱር እየቆራረጠ መገስገስ የጀመረው ጠብመንጃውን እንዳነገተ ነበር:: ለእደን የዞረባቸውን ገደሎች ያውቃቸዋልና አልተቸገረም::*

*ጊዜው ክረምት ነበር:: ይዘንባል:: ከትግራይ ተራራዎች ተጠረቃቅሞ እየተጠማዘዘ የሚጉዋዘው ጉርፍ ታላላቅ ተራራዎችን ነምሶ የመደርመስ ችሎታ ነበረው:: ከድንጋይ ድንጋይ እየተላተመ የሚንፏዋለለው ጉርፍ ለሀየሎም እንደ ትንቢት ነጋሪ ነበር:: ዊዳህ ከተባለ ቦታ ደርሶ በዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠው ቂጣና ገንፎ ከሚበሉ ጥቂት ታጋዮች ጋር ሲቀላቀልም ሀየሎም የተራራው ሰው መሆኑን አረጋገጠ:: ዳዊትን ሆኖ ከጐልያድ ሊፋለም ተዘጋጀ:: ድል አድራጊ ተብሎ ተተነበየለት:: ሀዲሽ የሚለው የቤተሰብ ስሙ 'ሀየሎም' በሚለው ተተካ:: በርግጥም ተራሮችን መሸገባቸው:: ሜዳና ሸለቆዎችን አሰሳቸው:: ጥይቶች በሳሉት:: ሰንቶቹ አጠገቡ ወደቁ?*

የወደቁት ለቀሩት አይራቸውን እየሰጡ በረሃ ቀሩ:: አብሮት የመጣው የእህቱ ልጅ ሳይቀር ሀክፊን በተባለ ቦታ ተሰዋ:: ሀየሉምም አንድ ቀን እንደ ጉዋደኞቹ አንድ ተራራ ላይ እንደሚወድቅ እርግጠኛ ነበር ...

ሀበኒ የማስታወሻ ደብተርዋን እየገለባበጠች ማንበብ ቀጠለች::

... የሰሜን ኢትዮጵያ ሰዎች ጦርነቱን ገፉበት:: እነሱ እንደሚሉት ጦርነቱ የተቀሰቀሰው ፍትህን በመነፈጋቸው ነው:: የልማት፣ የቀዋንቁዋ፣ የመሬት፣ የስልጣን ጥያቄዎችን ደግመው ደጋግመው አነሱ:: ስልቻ ለሚሞሉት ጥያቄዎቻቸው ጆሮ የሰጣቸው ግን አልነበረም:: ይህ እናደዳቸው፤ ንዴታቸው ወደ ቀጣ - ቀጣቸው ወደ አመፅ - አመፁ ወደ ጦርነት አደገ:: ጦርነቱም በየማእዘኑ ይቀጣጠል ያዘ:: ሰሜነኞች ሞትን ናቁ:: ከሞት ያልተሻለውን ኑሮ ጠሉ:: ጀግንነታቸው መጣባቸው:: ጠመንጃና እምቢልታቸውን የሽረሪት ድር ካደራበት የድንጋይ ግድግዳ ላይ አወረዱ:: እንደጥንቱ፣ እንደጠዋቱ፣ እንደአባቶቻቸው እየዘፈኑ፣ ከበሮውን እየደለቁ፣ ሲዋጉ የሰሜን ተራሮች ላይ ወጡ:: ከስመጥር መሪዎቻቸው አንዱም ሀየሉም ሆነ:: ይህ ታጋይ ተከታዮቹን ይዞ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ወታደሮች ላይ የሰነዘረው የዱላ ነበልባል ከጊዜ ጊዜ እየበረታና እየሰፋ ሄደ:: ጥይቶች ቢበሳሱትም ሀየሉም ሊቆም አልቻለም:: የሰራዊቱ ጥንካሬ ተስፋ ሆነው:: ሞትን ያሸንፍ ጀመር::

አንድ ጊዜ ህዋነ የሚባል ቦታ ወታደሮች አድፍጠው ይጠብቁት ነበር:: ሀየሉም አንዲት እና ቤት ውስጥ ሆኖ ያዋጋና ይዋጋ ነበር:: ወታደሮች ያቺን እና ቤት ጠረጠሩዋት:: ይከቡዋትም ጀመር:: ውጊያው ተጋጋለ:: የመንግስት ወታደሮች ሀየሉም እዚያች ጉጆ ውስጥ መሆኑን አረጋገጡ::

ጨኸቱና ግርግሩ በረታ::

«ሀየሉም እዚህ ነው!» የሚሉ ድምፆች ተራራዎች ላይ አስተጋቡ::

የወታደሮች ጆሮ ቆመ! ያ ብርቱ ጭራቅ ከተያዘ የጦርነቱ ሁሉ ማብቂያ ይሆናል ሲሉ ተነጋገሩ:: ያልተጠበቀ መተራመስ ተፈጠረ ...

አዛገሮች ይጮሁ ጀመር!

«እንዳትገድሉት ከነህይወቱ ያዙት!»

«እንዳያመልጣችሁ!»

«ጉጆዋን ኢጋዩዋት!»





ሀየሉም ይህን ሁሉ እናዋ ቤት ውስጥ ሆኖ ያደምጣል:: ብቻውን በመሆኑ ይህቺ የመጨረሻዋ ደቂቃ መሆንዋን አመነ:: ቢሆንም ሀየሉም ተስፋ ይቆርጣል ብሎ ማን ያስባል? ቀለበታቸውን ወደ እናዋ ቤት እያጠበቡ፣ እየተኮሱ ከሚመጡት ወታደሮች ጋር ይታኮስ ጀመር:: ጥይቶች ግርግዳውን እየበሱ አጠገቡ ያርፋሉ:: በጆሮው ስር ያፋዋጫሉ:: ድንገት ጉኑን ቀዘቀዘው:: ተመትቶአል:: የካኪ ሸሚዙ በደም ታጥቦአል:: ይህም የሁሉም ነገር ማክተም ምልክት መስሎት ነበር:: ግን ስህተት ነበር:: እኒያ ከጥይት የፈጠኑት ጀግኖች ጉዋደኞቹ እንደ በረሃ ዘንዶ መሬት ለመሬት እየተሳቡ ደርሰውለታል:: ጉጆዋንም ከበበው እየተስገበገቡ ሀየሉምን ለመማረክ የሚመጡትን ወታደሮች እንደ ዝምብ አረገፍዋቸው:: መሪያቸውንም በታላቅ ጀግንነት አዳኑት:: ሀየሉም ምን ያልተዋጋበት ስፍራ አለ?

ፀለምት፣ ወልቃይት፣ ደደቢት፣ እዳጋሀብረት፣ አዲዳእሮ፣ ሽራሮ፣ እልገዳ፣ ማይቀነጣል፣ አቢይአዲ፣ ገርአልታ፣ ነበለት፣ አህፈሮም፣ አክሱም፣ አድዋ፣ ሀውዜን፣ አፅቢ፣ አበርገሌ፣ ሳምሬ፣ ግጀት፣ ለቆጣ፣ ቦርቻሌ፣ ደላ፣ ዳንዴ፣ መቻሬ፣ ጨርጨር፣ ጉጉበዱ ...

ግን የቱ ተጠርቶ የቱ ይተዋል?

ሀየሉም እንደሆነ ተራሮቹን፣ ሸለቆዎቹን ተሽሎክሉኩባቸዋል:: መድፍ፣ ሞርታር፣ ታንክ፣ ብረት ለበሶቻቸውን አጋይቶባቸዋል:: የወታደሮችን የማዘዣ ጣቢያዎች ወደ አመድ ክምርትነት ለውጦባቸዋል:: በቆረጣ አስቃይቶአቸዋል:: ምራኮቻቸውን ሰባብሮታል:: ታዲያ ስሙን ማን የማያነሳሳው አለ? የራያ ሰዎች ወንድ ልጃቸውን ሀየሉም ሲሉ ሰይመዋል:: በከባድ ውጊያ መሀል መደንገጥን ጨርሶ የማያውቀው ሀየሉም የካቲት ሲመጣ ለድልና ለመስዋእትነት ይዘጋጃል:: የውስጥ እግሩ ሲገማመስ በማዳበሪያ ክር በወስፌ ይሰፋው ነበር:: ምን ያ ብቻ፣ የገዛ እግሩን በስብ እየተኮሰ ልክ እንደ ወንበር እግር ይጠግነዋል:: ታዲያ ሀየሉም ሩሁሩሀ ነበር::

ስለሙሴ ሲናገር እንባውን ማቆም አይችልም:: የመጀመሪያው የህወሀት መሪ የነበረው ሙሴ፣ መዳን እየቻለ ደሙ ፈሶ አልቆ ህይወቱ በማለፍዋ ዘወትር ይብከነከናል:: ታዲያ የሙሴን ጥበብና ትእግስት እንዳለች ነበር የወረሳት:: ሩሁሩሁ ሀየሉም ኩህለን የተሰዋ እለትም እንባውን ማቆም አቅቶት ነበር:: በተሙዋሙዋቂ ተኩስ መሀል ... መደማመጥ በማይቻልበት ... የቦምብ ድምፅ በሚሰማበት ... ሀየሉም ሳንቃው እስኪሰነጠቅ ይጮሃል፣ ሬድዮው ላይ ያምባርቃል፣

- ኩህለን! ኩህለን! ኩህለን!:-

ድንገት የኩሀሉን ድምፅ መጣለት!

- ምን ሁኔታ ላይ ናችሁ? - ሲል ሀየሎም ይጠይቀዋል::

- የተሙዋሙዋቀ ውጊያ ነው:: እንደ ቀድሞው እየፈፀምኩ ነው:- ይለዋል::

እንዲሀ ማለቱ ለሀየሎም ግልፅ ነበር::

ኩሀለን ምንም እንኩዋን መሪ ቢሆንም የሚመራቸው ታጋዮች ተሰውተውበት ራሱ መስመር ይዞ ውጊያው ላይ ገብቶ ኖሮአል::

- ሰበቸኩዋይ ውጣ!-

ሀየሎም በሀይለቃል አዘዘው:: ኩሀለንን ማጣት ምን ማለት እንደሆነ ያውቀዋል - ሀየሎም::

- ተቀብያለሁ! - ይላል ኩሀለን:: አያይዞም

- ግን ይህን ቦታ ብተወው ለጠላት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል:: ይህን ቦታ የደርግ ወታደሮች ከያዙት ግራና ቀኝ የገቡት ታጋዮች ይመታሉ! -

- ምን ያህል ሰው አለህ? -

- ደሀና ነው -

ሀየሎም ቁና ሙሉ አየር ተነፈሰ:: ረጋ አለ:: ገባው:: ኩሀለን ብዙ ተሰውተውበታል:: አለበና እንደገና ይጮሀ ጀመር!

- የያዝከውን ቦታ ለቀህ ውጣ -

ሳቀ ኩሀለን:: ረጋ ብሎም!

- እሺ ሀየሎም! - አለው::

ከዚያም ግንኙነቱን አቋዋረጠ:: ሀየሎም ግን እንደገና በሬድዮ ይፈልገው ጀመረ:: ከጥቂት ፍለጋ በሁዋላ አገኘው:: አሁን ግን የኩሀለን ድምፅ ለወጥ ብሎአል::

- ብዙ ገድለናል ሀየሎም! ማርከናል:: መሸሽም ጀምረዋል! በዚሀ ላይ እኔ ...

የኩሀለን ድምፅ ድንገት ሰረገ::

ሀየሎም 'ኩሀለን' እያለ ይጮሀ ጀመር:: መልስ የለም:: ኩሀለን ለዘልአለሙ ዝም ብሎ ኖሮአል:: ሀየሎም አለቀሰ:: አልቻለም:: በተሙዋሙዋቀ ውጊያ መሃል አነባ:: ጦርነትን ረገመ:: ስንቶች ወደቁ? ስንቶች? ስንቶች? ስንቶች?





ኩሀለን ቅን ነበር:: ብርቱና ግልፅ:: በከባድ ጦርነቶች መሀል የሚቀልድና የማይደነግጥ ነበር::

የሀየሎም ገጠመኞችና ያለፈባቸው አስቸጋሪ ውጊያዎች ቁጥር ስፍር አልነበራቸውም:: የአግአዚ ኦፕሬሽን ብቻውን ታላቅ ገድል ነው:: እስራኤላውያን በኡጋንዳ - ኢንቴቤ የፈፀሙትን ገድል ያስታውሳል ...

ሀወኒ የፃፈችውን መቦጫጨቅ አሰኛት:: በዚህ አያያዝ የትም እንደማትደርስ ተረዳች:: ታሪክ እንዲህ እንደማይፃፍ ታውቀዋለች:: የሰበሰበችው መረጃ በቂ አለመሆኑ ግልፅ ነበር:: 'ታዲያ ምን ማድረግ አለብኝ?' ብላ ራስዋን ጠየቀች::

መተው?

ታሪክ ፀሐፊ የመሆን ምኞትዋ የተዳከመ መሰላት:: አድካሚ ሆነባት:: የሰበሰበችውን መረጃ ብታገላብጥም ባዶ ሆነባት:: ስሜት የለውም:: ለጋዜጣ የሚላክ ዝባዝንኬ! ትርጉም የሌላቸው የተበጣጠሱ ብዥ ያሉ ገጠመኞች ሆኑባት:: ታጋይ ባለስልጣኖቹ ደግሞ ለመናገር ፈቃደኛ አይደሉም:: ፖለቲካ እንጂ ታሪክ መናገር አይወዱም::

የሰበሰበቻቸውን ፎቶግራፎች ስታገላብጥ የሙሴ ፎቶ እጅዋ ላይ ገባ:: የደስደስ ያለው ወጣት ነው:: ፎቶውን ሲያዩት በህይወት ያለ ይመስላል:: ትክ ብላ ታስተውለው ጀመር:: ስለሱ ብዙዎች ነግረዋታል:: ስሙን ሲያነሱ ደግሞ እንባ እንደሚቀድማቸው አስተውላለች:: 'ሙሴ ጀግና ነበር ወይስ ነቢይ?' አለች ለራስዋ:: ሙሴ ከኤርትራ ሻዕቢያን ተሰናብቶ ነበር ወደ ትግራይ ሰዎች የመጣው:: አመጣጡ የትግራይ ወገኖቹን መርቶ ወደ ነፃነት ሊወስድ ነበር:: አልሆነም:: ባጭሩ ቀረ:: ቢሆንስ ኖሮ ግን? እስራኤላውያንን ከግብፆች ባርነት ያወጣቸው ሙሴ ነበር:: ሆኖም የተስፋይቱን መሬት ተራራ ላይ ሆኖ ነበር በርቀት የተመለከታት:: እግዚአብሄር ወደ እስራኤል ምድር አይገባ ዘንድ አገደው::

... ከግማሽ ሰአት ቆይታ በሁዋላ ሀወኒ ከተቀመጠችበት ተነስታ ትንጎራደድ ጀመር:: ልብዋ ፍርሃት ፍርሃት አለው እንጂ የተሙዋላ ታሪክ ለመፃፍ መፍትሄው ምን እንደሆነ አልጠፋትም:: ግን ፈራች! ሞትን ፈራች! ሀየሎም ወዳለበት ግንባር መሄድ ብቻ ነው መፍትሄው:: ጥይት ግን ሰው ከሰው አይመርጥም:: ጥይቶች ታሪክ ፀሐፊዎችን ለይተው ሲስቱ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም::

ለአይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር ሀወኒ ከምሽግዋ ወጥታ በተራሮቹ ጥግ ላይ ወደተሰሩት የመፀዳጃ ቤቶች አዘገመች:: ከሳድ ግመል የከረመች ቢሆንም እንደገመተችው በቂ ታሪክ ማግኘት አልቻለችም::

የሰበሰበቻቸው ታሪኮች ግልፅ አይደሉም። ቦንብ ከጀቶች ተጣለብን ይሉዋታል - ታጋዮቹ። ቦንብ ከሰማይ ሲወርድ ምን እንደሚመስል ግን አታውቅም። ድምፁን ጭምር አታውቀውም። ስለዚህ ብዥ ይልባታል። ለነገሩ የሀየሉምን ታሪክ ለመፃፍ ትምጣ እንጂ ከዚያ በላይ የሚመስጡ ገድሎችንም መስማት ጀምራለች። አንዱ የሙሴ ታሪክ ነው። የሙሴ ሁኔታ ውስጥዋ መቀጣጠል ጀምሮአል። ግን ሁሉም ታጋዮች ብዙ አይናገሩም። ሙሴ ማን እንደሆነ፣ እንዴት ሊሰዋ እንደቻለ መናገርም እምብዛም አልቻሉም። ወይም አልፈለጉም። አሊያም ሲያስታውሱት ይረበሻሉ።

- ከብዙ አመት በፊት ነበር - አላት አንድ ቀን አንዱ ታጋይ። - - *አራት ወጣቶች ያሮና አካባቢ እገላ የሚባል ቦታ ለስብሰባ ተቀምጠው የሙሴን መምጣት ይጠባበቃሉ። በተስፋ ይጠብቁታል። ሙሴ ማለት የተዋጣለት መሪ ነው። ሁሉም ታጋዮች ይወዱታል። ይመኩበታል። ሙሴ ካለ ድል አለ። ወጣትና ጠንካራ ነው - ሙሴ። አይደክመውም። ይዋጋል፤ ያዋጋል፣ ከዚያም ደከመኝ ብሎ አያርፍም። ደሞ መፃህፍት ያነባል። ታጋዮችን ያስተምራል። ድል የሚመጣበትን መንገድ ጠንቅቆ የሚያውቅ ብሩህ አእምሮ የነበረው ወጣት ነበር። እናም አራቱ ወጣቶች እገላ እሚባል ቦታ ሆነው ይጠብቁታል። እነዚህ ታጋዮች የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ጥለው የወጡ የትግራይ ልጆች ናቸው። ወይም የመንግስት ስራቸውን ለቀው ወደ በረሃ የገቡ ናቸው። ታዲያ የሚመኩበት ሰው ቢኖር በርግጥም ሙሴ ነበር። ታዲያ እገላ በተባለ ስፍራ ተሰብስበው እየጠበቁት ነበር። አዲስ የአመራር አቅጣጫ ለመንደፍ የሚያስችል ስብሰባ ለማካሄድ ፈጥኖ ይመጣ ዘንድ ልከውበታል። ሆኖም በሙሴ ምትክ ረጅም አፍንጫ ያለው፤ ጠጉሩ ተገማምዶ ትከሻው ላይ የወረደ ሰው ወደ አራቱ ወጣቶች ሲገሰግስ በሩቅ ታየ። አራቱ ወጣቶች ማንነቱን በጠጉሩና በአፍንጫው ለዩት። ፀሀዬ ነው። እሱም ታጋይ ነው። ከብርቱዎቹ አንዱ። አጠገባቸው እንደደረሰ ደብዳቤ አቀበላቸው። ከመካከላቸው አንዱ ወረቀትዋን በችኮላ ከፈታት። ብጣቂዋ ወረቀት የሙሴን እንደወጣ መቅረት የምትገልፅ ነበረች። ወረቀትዋን የከፈታት ሰው ስዩም መስፍን ይባላል። እንባበ ሲያበቃ ብድግ ብሎ ለብቻው ሄደ። ከአንድ ቋጥኝ ላይም ተቀመጠ። እንባው ይወርድ ጀመር። ካንጀት በሚፈነቅል ስሜት እየተንሰቀሰቀ አነባ።*

*ግን ለምን?*

*መለየት? ተስፋ ማጣት? ባዶነት? ምን ነበር?*

*ሶስቱም ወጣቶች ወደ ስዩም መጡ። አባይ ፀሀዬ፣ መለስ ዜናዊ፣ ስብሀት ነጋ ይባላሉ።*





*- ስዩም ምን ሆነሃል? - ሲሉ ጠየቁት።*

*- ሙሴ ተሰዋ! -*

*ቃል የተነፈሰ አልነበረም። ሶስቱም ፈንጠር ፈንጠር እያሉ ለየብቻ ተቀመጡ። ይህ የትግሉ ማብቂያ የሽንፈት ምልክት ይሆን? በትግል ለሚሰዋ ታጋይ ማንባት የተለመደ አይደለም። ይህ ግን የተለየ ሁኔታ ነው። ሙሴ ከምንም ነገር በላይ ነበር። የሙሴን አቅም ማጣት ታላቅ አደጋ መሆኑን ሁሉም ያውቁታል።*

... ሀመኒ ባሀሳብ ትባዝናለች። የሰበሰበቻቸውን የታሪክ ብጥስጣሾች ልትቀጣጥል ትጥራለች። ግን ከቶ የሚሞከርና የሚገፋ አልሆነም። ቃላት መደርደር ብቻ ሆነባት። ህይወት ልትሰጠው ከበዳት። መፍትሄው አንድ ብቻ ነው።

*መዝመት! ሀየሉም ወዳለበት ግንባር!*

ያንጊዜ እውነተኛውን ታሪክ እንደምትፅፍ አልተጠራጠረችም። ሀመኒ አዲስ ድፍረትና ወኔ ለማግኘት ራስዋን እያበረታታች ነበር፤ ከመፅዳጃ ቤት ወደ ዋሻዋ የተመለሰችው። ልብዋ ግን አልቆረጠም። ግማሽ የመሞት እድል እንደሚገጥማት ስታስብ ፍርሃት ውስጥዋን ያርበደብደዋል። ሞትን መጋፈጥ ፈራች። ብርሃንን ማየት ትሻለች። ህይወት ጣፋጭ መሆንዋ ይሰማታል። 'ሞትን ለምን እጋፈጠዋለሁ?' ብላ ራስዋን ትጠይቃለች። ልብዋ ተከፋፈለ። ጊዜው ግን አሁን ነው። የህወሀት ፖሊት ቢሮ አባላት በሙሉ እዚህ አሉ። ስብሰባቸውን ጨርሰው ከመበተናቸው በፊት አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ አለባት። ከቆረጠች ሀየሉምን ተከትላ ወደ ውጊያው ሜዳ መጉዋዝ አለባት፤ ካልሆነም ስራዋን እርግፍ አድርጋ ትታ ወደ ውጭ ሀገር መኰብለል። ከሁለት አንዱን የግድ መወሰን አለባት። ውሳኔዋንም ለሀየሉም ትነግረዋለች።

**ልብዋ ግን ዋለለ። መወሰን አቃታት። በተከፋፈለ ልብ አልጋ ውስጥ ገብታ ጋደም አለች። ከሳድ ግመል ይበርዳል። ሲበርዳት ሰውነትዋን ማሻሸት ትወዳለች። ያኔ ይሞቃታል። ሙቀቱ ደግሞ እንዳች ስሜት ይጭርባታል። ያሰቃያታል። ጀርመን ያለው የልጅነት ፍቅረኛዋ ከልብዋ አልጠፋም። አብሮ አደግዋ ነው። ዋቆ አባዱላ የሚባል የእድሜ ባለፀጋ ነው ያሳደጋቸው። ወንድምዋም እጮኛዋም ነው። ሩቅ አገር አለ። ታዲያ አልጋዋ ውስጥ ገብታ ሲሞቃት እየተወራጨች የሩቁን አገር ሰው ስም በፍቅር ታነሳለች ...**

«እኖሌ የኔፍቅር ... የት ነህ!?»

## - 2 -

ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ ሀምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ደብረዘይት ወይም ቢሾፍቱ ተብላ የምትጠራ አንዲት ከተማ አለች። ወታደራዊ ጄቶች በየእለቱ ሲረግጡዋት ስለሚውሉ የፍርሀት አገር ሆናለች። ቀፈጥሮ ያለውን ሳይቆጥብ በሰጣት ሀብት ላይ ተኝታበታለች።

ከቢሾፍቱ ከተማ እምብርት ወደ ሆራ ሀይቅ በሚያመራው ውብ ጐዳና ዳርቻ ላይ በከተማዋ ታዋቂ የሆኑ አንድ ሬድዮ ጠጋኝ አሉ። እኚህ ሰው አርጅተዋል። ቢሆንም ብርቱ ናቸው። ግንባራቸው በላቦት እያብረቀረቀ የተበላሹ ኤሌክትሪክ ነክ እቃዎችን ይጠግናሉ። ለነገሩ ምን የማይጠግኑት አለ? ሰአት፣ የእጅ ባትሪ፣ ቡታጋዝ፣ ማቀዝቀዣ... ዝናቸው በሴተኛ አዳሪዎቹ ዘንድ እጅግ ተጋንኖ በመስፋፋቱ የተሰበረ የቢራ ጠርሙስም ይጠግኑ ይሆናል በሚል እምነት ስባሪውን እንጠልጥለው የሚሄዱ አሉ።

የመጠገኛ ሱቃቸው ለዘመናት በተከማቹ የተበላሹ ቁሳቁሶች ከመጠቅጠቅዋ የተነሳ መተላለፊያ የለም። ኤርትራውያን «አቦይ ግርማ ፅዮን» ሲሉዋቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ «የዳዊት አባት» ሲሉ ይጠሩዋቸዋል።

እነሆ አቦይ ግርማ ፅዮን ዛሬ ያልታሰበ እንግዳ ከተፍ አለባቸው። አያውቁትም። የቢሾፍቱ ሰው አይደለም። የሚጠገን ሬድዮም አልያዘ። ገፅታውን በፍጥነት ያጠኑት ጀመር። በልባቸው «እሱ ይሆን?» አሉ።

«ጤና ይስጥልኝ!» አለ ወጣቱ ጥርት ባለ አማርኛ።

«እግዚአብሄር ይመስገን!»

«የተበላሸ ሰአት ነበረኝ»

«ምን አይነት ሰአት ... ልጄ?» አሉ የልባቸው ምት እየፈጠነ።

«ሮመር 33» አላቸው።

«እነዚ ሰአት ወር አይሰሩ። አምጣ ... በል። ዛሬ ስራ የለ ... ቀዘቀዘ ... ሰው የተባለ ሳይመጣ ... ዋለ» ካሉ በሁዋላ «እንደምን ሰንበተሃል... የአገሬ ልጅ» አሉት በትግርኛ።

ከበርጩማቸው በመከራ ተነስተው አገላብጠው ሳሙት። ወጣቱ ከቀረበለት የወላለቀ ባለ አራት እግር ወንበር ላይ በጥንቃቄ ተቀምጦ ያወያቸው ጀመር።

እነሆ አቦይ ግርማ ፅዮን ዛሬ ታላቅ እንግዳ መጥቶባቸዋል። «ተበለፅ! ተበለፅ!» እያሉም ስለዚህ አይናቸውን ወደጉዋዳ ወረወሩ። ... ይጣሩ ያዙ። ወጣት ቆንጆዬ ልጅ እንገትዋን ብቅ አደረገች።





ይጣሩ ያዙ። ወጣት ቆንጆዬ ልጅ አንገትዋን ብቅ አደረገች።

«ጋሻ መጥዩአል... ሻሂ በሊያ ነጹኺ...»

በተወለጋገደው አማርኛ ሳቀባቸው።

«ሸዋ ምን ያህል አመት ቆዩ አቦይ?»

«ሰላሳ አመት» አሉ በፈገግታ።

«አማርኛ ሳይችሉ ቀሩ ታዲያ?»

«እምቢ አለኝ» አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ «ልጆቹን ደሞ ትግርኛ አቃታቸው። ወደፊት ሀገራቸው ሲገቡ ምን እንደሚሆኑ ቅዱስ ሩፋኤል ይወቅ።»

«የአካባቢው ፀጥታ እንዴት ነው ታዲያ?» አለወሬ ለውጦ።

«የፍረወይኒን መቼም ሰምተሀል።»

«አላውቃትም» አለ።

«አንድ እህታችን ናት። ፍረወይኒ ወልደማርም ትባላለች። አንድ አመት ሞላ ከተገደለች። ከልቤ ግን ልትወጣ አልቻለችም። ሁመራ ሳለን ጀምሮ ነው የማውቃት። ልጅዋን ወደ በረሀ የላከች ጀግና ናት። ታዲያ ኤርትራዊ ለሆነው ሁሉ 'ድምፂ ሀፋሽ ሰሚእካ?' ነው የመጀመሪያ ጥያቄዋ። ብዙ ጊዜ መከርናት። ተቆጣናት። አልሰማ አለችን። እንደፈራነው ሆነ። ለቅሶ ቤት ተቀምጣ 'ወዲ አፍወርቂ ሎሚ ጉዳም ተዛረቡ። እዚ ጅግና ወዲ ኤረ' እያለች ስታንሾካሹክ አስመራ የኖረ አንድ ወታደር ሰምቶ ጠቆመባት። ተያዘች። ተገደለች።»

ለጥቂት ደቂቃዎች ሁለቱም በትካዜ ቆዩ፣

«የፍረወይኒን ታሪክ እስኪ ሌላ ቀን ያወጉኛል። የዛሬ ስራችንን ቶሎ እንጨርስ። መልእክት ይኖረኝ ይሆን?»

«እውን አለህ» ካሉ በሁዋላ ድምፃቸውን ዝቅ አድርገው ይናገሩ ጀመር፣

«... ቦሎኛ 99 ተፈፅሞአል፤ ለጊዜው ስራህን ልትቀጥል ስለማትችል በአስር ቀን ጊዜ ውስጥ ወደነበርክበት ተመለስ። ወጪህ በተለመደው ስፍራ ተዘጋጅቶልሀል - ነቢያት በቼፊሊያ»

እንግዳው ሰው መልእክቱን እንደሰማ ባለበት ደንዝዞ ቀረ። አቦይ ግርማ ፅዮን በእንግዳቸው ድንገተኛ ድንጋጤ ክፉኛ ተረበሹ፣

«ከባድ ችግር አለ?» ሲሉ ጠየቁት።

«አዎን»

«ምንድነው የኔ ልጅ?»

ምላሽ ሳይሰጣቸው ቀረ።

«ንገረኝ ልጄ? ምስጢር መሆኑን መቼም አውቃለሁ። ስጨነቅ ውዬ ከማድር ግን ጥቂትም ቢሆን ንገረኝ።»

«እኔ ወዲህ የመጣሁት ለአንድ ድርጅታዊ ተግባር ነበር። ያንን ተግባር ማከናወን የምችለው ግን ቦሎኛ 99 ከተባለው ሰው ጋር ብቻ ነበር። ቦሎኛ 99 በደርግ እጅ ወድቀአል። ስለዚህ እኔ ስራዬን ለጊዜው መስራት አልችልም።» ብሎ በንዴት ይብከነከን ጀመር።

«ቦሎኛ 99 ትልቅ ሰው ነው?»

«በጣም! አስመራ ላይ ወሳኝ ስራዎችን ሲያከናውን የቆየ ነባር ታጋይ ነበር። ማንነቱን ከደረሱበት ምስጢር እንዲያወጣ ያሰቃዩታል። ምስጢር ደግሞ ሊያወጣ አይችልም። ስለዚህ ራሱን መግደሉ አይቀርም። አሊያ እነሱ ይገድሉታል።»

ለደቂቃዎች ያህል በየራሳቸው ሀሳብ ተመስጠው ሲተክዙ ቆዩ።

ከዚያም ሽማግሌው! «ትብለፅ» ሲሉ ይጣሩ ጀመር «ሻሂውን ዘገያችሁ»

«ሻዩ ይቅርብኝ አቦይ!» አለ ወጣቱ።

«ይደርሳል እኮ»

«እቸኩላለሁ። ምናልባት የሚያስተላልፉልኝ መልእክት ካለ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ተመልሼ እመጣለሁ። ካልሆነ ሄጃለሁ ማለት ነው። ደህና ይሁኑ አቦይ።»

«ደህና ሁን ልጄ! » አሉ ከተቀመጡበት እየተነሱ።





# ጣይቱ ምናለች!?

## ምእራፍ ሶስት

### - 1 -

የግል ታርጋ የለጠፈች አንዲት ቶዮታ - ላንድ ክሩዘር ናዝሬት ላይ ስትደርስ የመተሃራን መንገድ ትታ ወደ አርሲ በሚያደርሰው ጎዳና ተገነጠለች። ሾፌሩ የተመሰገነ ነው። በርግጥ ኖሮበታል! መንገዱም የሰጠ ነው። ላንድ ክሩዘርዋ አምስት ሰዎችን ብትጭንም ቅምም አላላት። በምቹው ጎዳና ትጋልባለች።

መኪናዋ ውስጥ ከሁዋላ የተጫኑትን ሶስት ገበሬዎች ለሚያያቸው ሞኞች ይመስላሉ። ገፅታቸው የድል ነው። ግን በአዳፋ ኩታዎቻቸው ስር ያለውን ያርሲ ልብ ማን ያውቀዋል? በተጨማተረው ባርኔጣቸው ስር ያለውን ያርሲን ሰዎች ጭንቅላትስ ከቶ ማን ይስተካከለዋል? በርግጥ የአርሲዎችን ሩህሩህነት ... የአርሲዎችን ጀግንነት ... የአርሲዎችን ምኞትና ህልም ... አዲስ

ባ ጨርሶ አላወቀችውም፣

«አባቦሩ!»

አኖሌ ነበር በኦሮሚኛ።

«ወዬ ልጂ?»

«እስር ቤት ውስጥ ደበደቡዋችሁ እንዴ?»

«ሰደቡን እንጂ አልነኩንም ... ልጂ!»

«ማነው ተሳዳቢው!»

«ቆየ እኮ ልጂ?»

«ምኑ አባቦሩ?»

«ስድቡ ከተጀመረ ነዋ?»

«አባቦሩ!»

«የኔ ልጅ!»

«ምን ብለው ሰደቡዋችሁ!?»

«እኔን ... 'ጅል ጋላ!' አሉኝ።»

አቃሰተ። በጦር ጉኑን የተወጋ ያህል አመመው።

በአፍንጫው ትኩስ ትንፋሽ ሰንጥቆ ሲወጣ ተሰማው።

«ይህን ያለውን ደንቆሮ ያስታውሱታል?»

«ከምትነዱዋቸው አህዮች አትሻሉም! ሲሉም አላገጡብን።»

«ያው ውሻ ነው እንዲህ የሚግማማው?»

«መቼ ይሆን የምትሰለጥኑት? ሲሉም ጠየቁን።»

«እርሶ ታዲያ ምን መለሱለት አባቦሩ!?»

«ማን እየገዛን እንሰልጥን? አልኩት።»

«ምን መለሰ ይህን ሲሉት?»

«ሲሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች አሉና ተረቱብን።»

«ለተረትማ ማን ብሎአቸው? ኑሮአቸው ተረት ነው። አስተሳሰባቸውም ተረት ነው። እንደ ባልቴት ተረት ከማውራት የተሻለ ምን ያውቃሉ? ደደቦች! እነሱን ብሎ ደሞ ስልጡን? ለዚህች ሀገር ምን ቁምነገር የፈየዱ መሰላቸው? ሶስት ሺህ አያሉ





የሚመኩበትን ዘመን ሙሉ ጠጅ በመጣልና በመጠጣት ነው ጊዜያቸውን የፈጁት!»

«አኖሌ ልጂ!?»

«አባቴ!?»

«ያንን ሰማይ ታየዋለህ!?»

«የቱ!?» ብሎ በመስኮት አማተረ።

«እስከ አድማስ የተዘረጋውን!»

«አዎን አባቴ!»

«እንኩዋን መሬቱ ሰማዩም የኦሮሞዎች ነው። ጊዜ ነው ያዋረደን። ጊዜ ደግሞ ሁሉንም እንደነበረ ያደርገዋል።»

የሳንድ ክፉዘርዋ ሾፌር ኦሮሚኛ ባይችልም የአኖሌንና የገበሬውዩን ንግግር በምስጢር ቴፕሪከርደሩ እየቀረፀ ነበር።

በአኖሌ ገፅታ ላይ የሚነበበው ቁጣ ፖለቲካዊ ይዘት እንዳለው አልተጠራጠረም። በሙያው ተክኖበታል። የስለላ ስራውንም ይወደዋል - የገንዘብ ምንጭ ሆኖለታልና።

«ጋሼ ነመራ!» አለ አኖሌ ወደ ሁለተኛው ገበሬ ዞሮ።

«ልጂ?»

«ልጆች ደህና ናቸው?»

«ደግ ናቸው ... ደግ ናቸው ...»

ወደ ሶስተኛው ገበሬም መለስ አለ።

«ጋሼ ዋቅማ ...»

«ወዬ የኔ ልጅ ...»

«ሁሉም ቤተሰብ ደህና ነው?»

«ደግ ናቸው ... የኔ ልጅ»

«መሀቡባ አገባች?»

«ገናነች ልጂ! አንተን ሁሌ እንዳነሳች ነው። ከአፍዋ ጠፍተህ አታውቅም። ሲነጋም ሲመሽም 'አኖሌ ...' እንዳለች ነው።»

ደሞ ወደሌላ ርእስ ዘለለ፣

«እመፁ ሲቀሰቀስ ምን ይመስል ነበር ... አባቦሩ?»

አባቦሩ ግን መልስ ለመስጠት ዘገዩ:: ይልቁን የደማ የእግራቸው አውራ ጣት ላይ ቁራጭ ጨርቅ ቢጤ ይደመድሙበት ጀመር:: ሽበት ጨርሶአቸዋል:: ብስል ቀይ ናቸው - ረጅም::

«አባቦሩ!»

ቁና ሙሉ አየር ተነፈሱና እንዲህ አሉት ...

«... ያደግህበት ደጃፍ ዛሬ የጦር ሰፈር መስሎአል:: የቡርቃ ገበሬዎች 'ሀወኒ ... አኖሌ ...' እያሉ ነው:: ገበሬው በናንተ ተስፋ አድርጎ ነበር:: ያኔ ወደ ትምህርት ስትላክ ሱሪ አለባበስ እንድታውቁና የፀዳ ጨርቅ እንድትለብሱ አልነበረም:: አማርኛችሁ እንዲጣፍጥም አልነበረም:: ጉዳዩ ሌላ ነበር:: ታሪካችሁም ብዙ ነው ... እናንተ የማታውቁት::»

አኖሌ አንድ ነገር ጭንቅላቱን ጠቅ አደረገውና ከመቅፅበት ለአባቦሩ ጥያቄ ሰነዘረ::

«ለመሆኑ የኔና የሀወኒ ወላጆች እንዴት ነው የሞቱት?»

ሶስቱ ገበሬዎች ርስበራስ ተያዩና በዝምታ አቀረቀሩ::

«ለአባቴ ጉዳዩን ሳነሳበት ይከፋው ነበር::»

«ዛሬ ያወጉሃል» አሉ አባቦሩ በደከመ ድምፅ::

«ልዩ ነገር አለው እንዴ አባቦሩ?»

«የለውም ልጄ:: እንደሰው ልጅ ነው የሞቱት::»

«በህመም ነው?»

«የለም!»

«በጉርፍ አደጋ ይሆናላ?»

«ቡርቃ ምን ወንዝ አለና ልጄ? ወንዙማ ውስጥ ለውስጥ መሄድ ከጀመረ መቶ አመቱ ነውኮ? ምን ጉርፍ አለ ቡርቃ?»

«በምን ሞቱ ታዲያ? በቃጠሎ?»

«የለም!»

«በሰው እጅ ነው የተገደሉት?»

«የለም!»

«ታዲያ በምን ሞቱ?»

«ያደርስሃል!»





ሳንድ ክሩዘርዋ እጅጉን ቸኩላለች::

አዎን ... መኪና ውስጥ ያሉት የአርሲ ገበሬዎች የመኪናዋን መቸኮል የወደዱት ይመስላሉ:: በርግጥ አርሲዎች ችኩል አይደሉም:: ሰባ አመት ሙሉም ታግሰዋል:: ዛሬ ግን ትእግስታቸው ያለቀ ይመስላል ...

## - 2 -

የአመፀኞቹ ገበሬዎች ቁጣ እንደ ሰደድ እሳት ተቀጣጥሎአል:: የገበሬዎቹ እግሮች ለእሾህና ለጠጠር አይበገሩም:: እንደ ወይራ በጠነከሩ ተረከዞቻቸው ያን የጥጥ ፍራሽ የመሰለ ምድር እየሰረጎዱ ጃሎታውን ያስነኩታል:: በጦሮቻቸው በውሃና በልምላሜ የሞከሞከውን መሬት ይቦጭቁታል:: እየቦጨቁ ይፎክራሉ:: ጉልማሶቹና ወጣቶች!

«ቡርቃ ሲ..ጋአ!»

«የሮን ጌሲ ጂራ - ቡርቃ!» ይላሉ::

ሽማግሌዎችም በማንቀጠቀጥ ድምፃቸው ይቀሰቅሳሉ::

*«አሰላማሌኩም ...*

*ዋቀዮ መራንፍራ*

*ዱኒ ኬኛ ... አርባጉጉ ጂራ*

*አማሬ ... ቡርቃ ጂራ*

*ቀንጨራ ሃሰኔ ጭራ!»*

*ሌሆቹስ መቼ ዝም አሉ?*

*«ሌሊመሶ አኖሌ ... ሌሳጅርታ!?»*

*«ሊጎተለሆ ሀወኒ ... ሌሳጅርታ!?»*

በረጅም ቀጭን ድምፅ ይጣራሉ:: ጥሪያቸው የካካን፣ የባቱንና የጭላሎን ተራራዎች ይገጨዋል:: የአርባጉጉን ሸለቆ ያሸብረዋል:: የገደል ማሚቶም ያን ጥሪ ... ያን ቀረርቶ ... ያን ጃሎታ ... እያቀባበለ እስከ አካ ... እስከ ደምቢዶሎ ... እስከ ጅማ ... መቱ ... እስከ የረርና ዝቁዋላ ... ያስተጋባዋል::

በርግጥ የቡርቃ ዝምታ ሊያበቃ ይሆን?

አልተጠራጠሩም። ኦሮሞዎቹ ገበሬዎች ቅንጣት ታህል ታውቀኣቸዋል። ጊዜው መቅረቡ ተሰምቶአቸዋል። ዳሩ ጠንቋዋዮችና አረኞች ወሬውን በመሰላቸው መንገድ ሲያዳርሱት ነው የሰነበቱት።

ገበሬዎች በጅንበር ግባት ላይ በየሀማጋው አፍ ለአፍ ገጥመው ይህንኑ ሲንሾካሾኩና ጃሎታውንም ሲያደሩት አመሹ። የሰማው ላልማሰው "ጊዜው ደረሰ! የቡርቃ ዝምታም ሊያከትም ነው!" እያሰ ያዳርሳል። ወሬው ከቡርቃ መንደር ተነስቶ ወደ ጉሮ - ወደ ጃራ - ወደ ጉና - ወደ በቆጂ በረረ። ማቲው ፋርሽካ ፋርሽካ የሚለውን የበቆሎ ቂጣ እርቦው ላይ ወረወረ። በወጨት የሞላ ገንፎውን የሚያርስ ሞፈሩን ጣለ። የሚቅም ጫቱን የገል ገለበጠው። ማንደጃው ላይ ባፍጢሙ ደፋው! ምንጣፉን እንጥፎ ፊቱን ወደ መካ መዲና አዙሮ ቁራኑን የሚቀራ - ሀሙማን ላይ ጫት ሲተፋ ያደረ አዋቂ - መቁጠሪያውን ይዞ የሚቆጥር ሁሉ ወደ ቡርቃ መንደር ኮረብታ አንጋጠጠ።

አቡቢንቲ መላው ሰውነታቸው ላይ ያርከፈከፉ - ለጋ ቅቤ ራሳቸው ላይ የጨፈጨፉ - በሞጆው ባለአበባ ሻማ ያሸበረቁ - የቤት ፈትል የለበሱ - ረጃጅም ጠጉራቸውን እንደነገሩ ያዝረከረኩ ሴቶች! ቁንዲፍቱ ጨርቃቸውን ነፋስ ቢል እያረገበቻው ወደ ቡርቃ አቀኑ። ቁንዲፍቱ በትል ያንጠለጠሉ - ቀሪቦ በአንኮላ ሲመዘምዙ የዋሉ - ያተጨማደደና የጠቆረ ተነፋነፍ ያጠለቁ - የተቡተረፈ ቡት ጫማ የተጫሙ - መስቀለኛ በረባሶአቸው የተነቀሰ - ገፅታቸው ላይ እልህና ቁጭት የተቸከቸከባቸው - ሲያቅራሩ እንደ ነጐድጓድ ድምፅ - ምሬትና ቁጣ የገነፈለባቸው - ወንዶች! የኦሮሞዎች አምላክ ዋቀዮ ስለ ቡርቃ የሚያስደነግጡ - ወንዶች! የኦሮሞዎች አምላክ ዋቀዮ ስለ ቡርቃ ዝምታ ማብቃት! ስለቡርቃ ወንዝ ኩርፊያ ማክተም! በቅዱስ መንፈሱ ሽክ ያላቸው ያህል ቁና ቁና እየተነፈሱ የቡርቃን አቀበት ተያያዙት።

ኦሮሞዎቹ ያልያዙት ሁዋላቀር የጦር መሳሪያ አይነት የለም። ውጅግራ - አልቤን - ፋስ- ቢላዋ - ድንጋይ - የወይራ ዱላ - ከአህያ ጆሮ ጭራሮ የተሰራ ችቦ - ክብሪት - መጥረቢያ - በረጃጅም በጠያይምና በወፋፍራም እጆቻቸው ጨብጠዋል። አይኖቻቸው እሳት እየተፉ ሰብአዊ ፍጡርን ያስበረግጋሉ። መንታ ምላስ ያለው ስለታሙ ጦራቸው ደረት ላይ ቢሰነዘር ልብን ከነግሳንግሱ በጭቆ ይመለሳል።

... ወሬው ወደ አገልጆ ሳጉሬና አርቦዬ ተዛምቶአል። የአገልጆ ኦሮሞዎች ወሬውን ሲሰሙ የቁጣ ሳቅ ገነፈለባቸው። ያለው በፈረስና በበቅሎ - አቅሙ የፈቀደ በእግሩ - ሁለቱም ያልሆነለት አረንጉዋዴ የስጋጃ ምንጣፍ ከመሰለው መስክ ላይ ጠይም ግምባሩን እሳስሞ ለዋቀዮ ምስጋናውን ያደርስ ጀመር።

ወሬውን ከመንደር መንደር የሚያደርሱት እነ ሆርዶፋ ናቸው።





ሽምጥ ጋላቢዎቹ ወጣቶች ትላልቅ ገደሎችን በፈረሶቻቸው የሚዘሉት እንደዋዛ ነው። የፈረሶቹ ኮቴ ምድር ውስጥ እየተተከለ ሲነቀል ዱባ የሚውጥ ጉድጉዋድ እየተወ ያልፋል። ሆርዶፋ እንደዛሬዋ እለት ደስታ አሳብዶት አያውቅም። ከቡርቃ ተነስቶ እንደ አበሽማኔ እየተወነጨፈ ጉምጉማ ለመድረስ ጊዜ አልፈጀበትም። ሌሎች ወጣት ኦሮሞዎችም ወሬውን ይዘው ወደ አሰሳ - ወደ ቦሮ - ወደ ኮፈሌ - ወደ ቆሬ - ወደ ጢሮአፈታ ሽመጠጡ። ወሬውን የዚያኑ እለት ጉቢሳ ሳይቀር አደረሱት።

ቡርቃ በጭንቅ ተይዛለች።

«የሮን ጌሴ ጂራ!» ሽማግሌዎቹ።

*«ቡርቃ ሲጋእ!» ጉልማሶቹ።*

*«ዲኒ ኬኛ - ቆንጨራ ካሰኔጭራ!» ወጣቶቹ።*

*«ሌልመኮ አኖሌ - ሌሳጅርታ!?» ልጃገረዶቹ።*

*«ሊንተሰቶ ሀወኒ - ሌሳጅርታ!?» አሮጊቶቹ።*

በአርሲ ያሉ ኦሮሞ ገበሬዎች ሁሉ ከቡርቃ ትንቢት ጋር ተያይዞ ሊፈጠር ስለሚችለው ልዩ ተአምር ሲያወጉ አመሹ። በርግጥ ቡርቃ አንገቱን እንደ ዘንዶ መዞ የኦሮሞን ምድር ለማጥለቅለቅ መቶ አመት ከተደበቀበት ዋሻ ይወጣ ይሆን?

ጉዳዩን ስሜታዊ ሳይሆኑ በርጋታ ያጤኑ በእድሜ የገፉ አዛውንቶች ደግሞ ትንቢቱ ስለሚፈጥረው እልቂት ሳያስቡ አልቀሩም። መላ ሊፈይዱ ወደ ቡርቃ አቀበት መገስገስ የጀመሩም አሉ። ዳሩ ግን ለሰባ አመታት ሲጠበቅ የኖረውን ያን አመፅ ከቶ ማን ያቆመዋል?

***«ጊዜው ደርሶአል - ቡርቃ በቃህ!»***

***«ጠላቶቻችንን በቆንጨራ እንጨፈጭፋቸዋለን!»***

***«ልጃችን አኖሌ ... የት ነህ?»***

***«ልጃችን ሀወኒ ... የትነሽ?»***

ኦሮሞዎቹ ገበሬዎች በከፍተኛ አስፈሪ ድምፅ የሚያስተጋቡት ይህን ነበር ...

- 3 -

ከለምለሚቱ ቡርቃ ብዙም ሳይርቅ አንዲት በርካታ አማሮች የሰፈሩባት መንደር አለች። የሰፈሩበት ሜዳ እጅግ ውብና ለእርሻ ተስማሚ ነው። መሬቱ ለእህል የሰጠ ነው። የሰርዶው ልምላሜ

ዚያች ታይቶ አይጠገብም። አካባቢው ቅዱስ ስፍራ ይመስላል። ... ሲሆኑ መንደር ላይ የሰፈሩት አማሮች አብዛኞቹ የምንጃር ሰዎ ... ወደ አካባቢው የመጡት ከአያሌ አመታት በፊት ደጃዝማች ሃይለራጉኤልን ተከትለው ነበር። ..ግጥ የአብዛኞቹ አባቶች ራሳቸውን እንደ አገር አቅኚ የሚቆጥሩ ወታደሮች ናቸው። በወቅቱ በመላዋ አርሲ ኦሮሞች ይከበሩ ከነበሩት ዋቆ አባዱላ ጋርም እልህ የሚያስጨርስ ፍልሚያ አድርገዋል። ሆኖም ኦሮሞዎቹ ሀይል ሲበረታባቸው ወደ ቡርቃ ኮረብታ፣ ወደ ካካ ተራራ ግርጌ ተሰባሰቡ። ደጃዝማች ሃይለራጉኤል የተቀዳጁትን እንጂ አልተንበረከኩም ነበር። የዋቆ አባዱላን ተከታዮች አላሳደዱዋቸውም። ድል ተጠቅመው ኦሮሞዎች ብዛት ስላላቸው ቂሙ በርትቶ አንድ ቀን ይነሱብናል በሚል ስጋት ከዋቆ አባዱላ ጋር እርቅ መሰረቱ። ዋቆ አባዱላ በወቅቱ ሀይላቸው ስለተዳከመ እርቁን ይፈፅሙ እንጂ ነፍጠኞች የፈፀሙባቸውን ግፍ ለወገኖቻቸው ከማስተማር አላረፉም ነበረ። ይህን የተረዱት አማሮች ከእለታት አንድ ቀን የቡርቃ ሰዎች ይነሱብናል የሚል ስጋት ነበራቸው። እነሆ አልቀረም። ከብዙ አመታት በሁዋላ የቡርቃ ገበሬዎች እንደጉንዳን ሰራዊት እየተመሙ ከቡርቃ ኮረብታ፣ ከዋቆ አባዱላ ደጃፍ ላይ ተሰባስበው ያቅራራሉ። ይዝታሉ ...

... አማሮቹ ገበሬዎች የእመፁን ወሬ እንደሰሙ ድንጋጤ ትንፋሻቸውን ቆረጠው። ሴቶች እንባቸውን ያዘሩ ጀመር። ወንዶች ማድረግ ስላለባቸው ነገር በቅጡ ማሰብ እንኳዋ አልቻሉም። ቀስ በቀስ ግን አንድ ሁለት እያሉ የቅዱስ ሚካኤል ደብር ወዳለበት ኮረብታ ያቀኑ ጀመር። አማሮቹና ኦሮሞዎቹን የሚለየው ኮረብታ ኮረብታ ያቀኑ ጀመር። አማሮቹና ኦሮሞዎቹን የሚለየው ኮረብታ በታቦቱ ስም ቅዱስ ሚካኤል ኮረብታ ተብሎ ይጠራል። ከኮረብታው እናት ደጃዝማች ኃይለራጉኤል ያሳነፁት ይኸው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በመልካም አቀማመጥ ጉብ ብሏል።

... እኩለ ቀን ሲሆን የጡሩምባ ድመፅ በአማሮቹ መንደር ያስተጋባ ጀመር። አያይዞም የቅዱስ ሚካኤል ደብር ደወል ግርማ ሞገስ ባለው ድምፅ በርጋታ ጥሪውን አሰማ። ጥሪው ግን ከወትሮው ለየት ይላል። የአሁኑ የደወል ድምፅ ከኮረብታ ኮረብታ እስኪያስተጋባ ድረስ ሃይልና ቁጣ ነበረበት።

ከዘጠና ደቂቃዎች በሁዋላ ወደ ቅዱስ ሚካኤል ኮረብታ ሽምጥ የሚጋልቡ ፈረሰኞች ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር። ጦርና ጉራዴ፣ መውዜርና ጉዋንዴ የያዙ ጠያይም አማራ ገበሬዎች ያን ለምለም ናቸው። አማሮቹ ለፈረስ ግልቢያ የሚሰንፉ አልነበሩም። ፈረሶቹም መስክ እንደዋዛ ያቁዋርጡት ያዙ። ፈረሶቹ የተቀለቡና የሰለጠኑ ጥሪውን የተገነዘቡ ይመስል ጆሮአቸውን ገትረው ወደ ተራራው





ይሽመጥጡ ገቡ። ተሲያት ላይ ከአምስት መቶ ያላነሱ አማራ ገበሬዎች ጦራቸውን እየሰበቁ ጃሎታውን ያስነኩት ያዙ ...

«ፍፃሜ ቀርቦአል!» የሚሉ ድምፆች።

«ስምንተኛው ሺ!»

«እነዚህን ቆራጣ ጋሎች! እናቅምሳቸውና ደሞ ሃምሳ አመት ይተኙ!»

«የአማራውን ክንድ ረሱት ደሞ!?»

«መንግስት አቀበጣቸው! የጋላ ወዳጅ የማጭድ ቀዳጅ የለም። መፍጀት ያስፈልጋል!»

«ቁዋንቁዋቸው በሬዲዮ መነገር ከጀመረ ወዲህ ቀበጡ!»

«መሪ እንምረጥ!»

የደብሩ አለቃ ከአንድ ቁዋጥኝ ላይ በዲያቆናት ድጋፍ ወጡ! ከዝግባ እንጨት የተሰራች መስቀል ይዘዋል። ማደፍ የጀመረ ጥምጣማቸውን በጥንቃቄ ጠምጥመዋል። ቁዋጥኙ ላይ ከወጡ በሁዋላ ህዝቡ ዝም እንዲል ምልክት ሰጡ። ቀረርቶው ቀስ በቀስ ጋብ እያለ፣ እየበረደ ... በመጨረሻም ረጭ አለ። የደብሩ አለቃ ከነትጥቁ የተሰባሰበውን ገበሬ ላንዳፍታ በአይናቸው ገረፍ ካደረጉት በሁዋላ ደከም ባለ ድምፅ ንግግር ጀመሩ፣

«... ወንድሞቼ! ወሬውን መቸም ሁላችሁም ሰምታችሁዋል። አርሲዎች ሊያጠፉን ይሻሉ! ለምን ይህን እንዳሰቡ እናውቃለን! ግጭቱ የሚያስከትለውንም እንረዳለን! መፍትሄው ምን መሆን እንደሚገባውም አናጣውም» ብለው ለአፍታ ዝም አሉ።

ገበሬውም በፀጥታ ያዳምጣሉ!

«... ቅዱስ ሚካኤል ከጐናችን ነው ወንድሞቼ። በልባችሁ ቅንጣት ታህል ሽብር አይግባ። ኦርቶዶክሶች በየትም አለም ለማንም ሲንበረከኩ ታይተውም ተሰምተውም ተፅፎም አያውቅም። ኦርቶዶክሶች ባሉበት ስፍራ ሁሉ አንገታቸው ላይ ላሰሩዋት ክር ሲሉ ጀግንነት ፈፅመው ነው ያለፉት። አርሲዎች ሊጨፈጭፉን ተነስተዋል። እኛም ቅዱስ ሚካኤልን ደጀን አድርገን እንከላከላቸዋለን። የለኮሱት እሳት ራሳቸውን ይበላቸዋል። በዚህ ጥርጣሬ አይግባችሁ። ክብራችሁን አታስነኩ ልጆቼ! እግዚአብሄር አምላክ ከጐናችን ነው። ከመካከላችሁ ጉበዝ ፊታውራሪ ምረጡና መክቱዋቸው። እኛም ባህታውያን ወደ እግዚአብሄር እንፀልያለን!»

ቀረርቶና ጫጫታ ተከተለ። የደብሩ አለቃ እንደገና

መስቀላቸውን ብድግ አደረጉ:: መልሶ ረገብ አለ:: ረጭ!

«ጉበዝ አለቃ ምረጡ!» አሉ::

ሆኖም ገበሬዎቹ ይተያዩ ጀመር:: የመፈታተሽ ያህል ይገለማመጡ ያዙ:: ማን አለ? ማን የለም? የሚሉ ይመስል አንገቶች ሰገጉ:: አንዱ ሌላውን እያየ ይመዝናል:: ሹክሹክታ ተጀመረ:: አፍላፍ ገጥመውም ሲማከሩ ሲጠቁዋቆሙ ደቂቃዎችን ካሳለፉ በሁዋላ፣

«አስናቀ!» የሚሉ ድምፆች አየሩን ሞሉት::

«አስናቀ!»

«ብቻውን አሩሲን ይገጥማል!» የሚሉ ሙገሳዎችም ተከተሉ::

አስናቀ በወፍራም ክንዱ ጠመንጃውን እንደያዘ፣ ሸሚዙን እስከ ክሳዱ እንደጠቀለለ ወደፊት ወጣ:: ቁመቱ የትየለሌ ነው:: ፊገግታው ደማቅ፤ ትክሻውና ፊቱ ጋሻ መሬት የሚያህል፤ በራስ መተማመን ያለው፤ ግርማ ሞገሱ፣ ክብርና ኩራቱ አይኖቹና በለበጣ ፈገግታው ላይ የሚታይ፤ መካከለኛ እድሜ ላይ ያለ ሰው ነበር አስናቀ:: የደብር አለቃው በለቀቁለት ቁዋጥኝ ላይ እንደ ገመሬ ዝንጀሮ ነበር እመር ብሎ የወጣው:: ገበሬዎቹ በኩራት ያጤኑት ጀመር:: አስናቀ እፊቱ የሰፈሩትን ገበሬዎች በአይኑ ሙሉ እያፈሰ፣

«እምናችሁብኝ ስለመረጣችሁኝ አመሰግናለሁ:: ደግሞም አላሳፍራችሁም!» ሲል ገበሬዎቹን በልበ ሙሉነት አጤናቸው:: አስናቀ መምህር ነበር:: ከቡርቃ አካባቢ ብዙም በማትርቅ አንዲት የገጠር ቀበሌ ውስጥ ነበር የሚያስተምረው:: ሆኖም ከእጅ ወደ አፍ የሆነውን የመምህርነት ስራ ትቶ ንግድና እርሻ ከጀመረ አስራ አምስት አመት ሞልቶታል:: የአርሲ ገጠሮች ተስማምተውታል:: በአካባቢው የተከበረና በተለያዩ ማህበራዊ ግልጋሎቶች ላይ ቀድሞ በመድረስ የታወቀ ነው:: በተናጋሪነቱም በአካባቢው ገበሬዎች ይመሰገናል::

«... ወገኖቼ! የአሩሲ ጋሎች ሊጨፈጭፉን ማሰባቸውን ስሰማ ከልብ አዘንኩ:: ብዛታቸው ድል የሚያስገኝላቸው መስሎአቸው ከሆነ ተሳስተዋል:: ጥራት እንጂ ብዛት ድል እንደማያስገኝማ በአረቦችና በእስራኤላውያን ጦርነት አየነው! ስለዚህ ስጋት አይግባችሁ! ልክ እናገባቸዋለን!»

ጭብጨባው ነጕድጕዋድ መሰለ::

«በሶ አልጨበጥንም!» የሚሉ ድምፆች ይወረወሩ ጀመር::

አስናቀ ንግግሩን አራዘመ፤





«... ለመሆኑ እኛ ላይ ማመፅ ለምን አስፈለገ? ምን አጠፋን? መንገድ በሰራን ... ትምህርት ቤት በተከልን ... ወፍጮ ቤት ባቁዋቁዋምን ... መጨፍጨፍ አለብን? ሌላው ቀርቶ እነዚህ አሩሲዎች ዶሮ እንኳ መች ይመገቡ ነበር? እንደውሻ አርጅታ እስክትሞት ድረስ እንቁላልዋን ብቻ ነበር የሚለቅሙት:: አይደለም እንዴ? እኛ ነን ዶሮ መብላት እንኩዋን ያሳየናቸው»

ሳቁ ከጫፍ እጫፍ ተተረተረ::

አስናቀ ቀጠለ፣

«ራሳቸው ሲተርቱ 'አውራ ዶሮ ጭንቅላቱ ላይ ስጋ ተሸክሞ ይዞራል፤ አይበላው ወይ አያስበላው!' ይላሉ:: ታዲያ ተረታቸው ነውኮ የተፈፀመው:: በየደረሱበት ሁሉ ራስ ብሩን ይኰንናሉ:: ራስ ብሩ የፈፀሙትን በጉ ተግባር ረስተው ይሆን? የራስ ብሩ ጥፋት በኛ ላይ መላከክ አለበት ያለውስ ማነው? የተወለድንበትን መሬት ለቀን የትነው የምንሄደው? ንገሩኝ ወገኖቼ? አማራው ደግሞ ጥቃትን አይሸከምም:: የሚሸከምበት ትከሻም የለው:: አይደለም እንዴ ጀግኖች? ተሳስቼ ይሆን?»

ሻሎታውና ጭብጨባው ተደበላለቀ:: አስናቀ ደማቅ ፈገግታውን ለገበሬዎቹ እየመገበ በኩራት ያስተውላቸው ጀመር:: ልቡ ሞላ ...

## - 4 -

በአራት የአሜሪካ ሪዮ ጀምስ መኪኖች የተጠቀጠቀ ሁለት መቶ የስፓርታኪያድ ጦር አባላት ወደ ቡርቃ እየገሰገሱ ነው:: ከነጉባ የተነሱት ወታደሮች፣ ሮቤንና ዲንሾን አልፈው፤ አዳባና ዶዶላን አቁዋርጠው አሰሳ የጋቡት በከፍተኛ ፍጥነት እየገሰገሱ ነበር:: አሰሳ ላይ ለአፍታም ሳይቆሙ ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: መራሮ ከመድረሳቸው በፊትም ወደ ቡርቃ በሚያደርሰው የገጠር መንገድ ተገነጠሉ:: የካካ ቀፉፉ በርቀት ታያቸው:: የመንገዱ ዳር ልምላሜ ታይቶ አይጠገብም:: ሰማዩ ብሩህ ነው:: አየሩ ለስስ ያለ ሲሆን ንፁህና መንፈስን የሚያድስ ነው:: ሪዮ ጀምሶቹ በጕርናፍ የተቦረቦረው የገጠር መንገድ አላስቸገራቸውም:: ጡሩምባቸውን በፀጥተኛው ገጠር ላይ እያምባረቁ ነጕዱ:: የዚህ ዘመቻ መሪ በክፍት ዋዝ ጂፕ ላይ ተቀምጦ ፊትፊት ይመራል::

ሻለቃ ጉተማ መልካም ባህርይ የለውም:: እብሪተኛ ነው:: እብሪተኛ ብቻ ሳይሆን ቁጣ፣ የበላይነት መንፈስና ንጭንጭ የተጠናወተው ጭምር ነው:: ለበላዮቹ የሚሽቆጠቆጠውን ያህል የበታቾቹን ማራወጥ ይወዳል:: ፊቱ ስለታምና አይኖቹ ውስጥ ነገር የሚነበብበት፣ መሰሪነት አብሮት የተፈጠረ ርህራሄ የማያውቅ

እርጉም ሰው ነው። ከስሩ ያለውን ማንኛውንም ሰው ይንቃል። ከተዳፈሩት ሴራ ይጎነጉናል። የጠላውን ጠልፎ ካልጣለ እንቅልፍ የለውም። ሌሊትና ቀን የተንኮል መረቡን ሲገምድ የሚውል የጦር መኰንን ነው።

ወታደሮቹ ሳንጃቸውን ጠመንጃቸው ላይ ሰክተዋል። ለውጊያ ቸኩለዋል። ፍርሃት አይታይባቸውም። ካልታጠቁ ገበሬዎች ጋር እንደሚዋጉ ስለተነገራቸው በግልባጩ ለውጊያው ነው የቸኮሉት። በአስር ሜትር ርቀት በርግጥ የሰው ልብ ላይ ጩቤ መትከል መቻላቸውን ማረጋገጥ ይሻሉ። ተቅበጥብጠዋል። ከአራት ያላነሰ የእጅ ቦምብ ታጥቀዋል። በራስ የመተማመን ወኔያቸው ከፍ ብሎአል። ስለዚህም በሆታ ያዜማሉ፣

መች ተዋጋና - ውጋ!

መች ተዋጋና - ንቀል!

ያስባል ገና!

ይበላሃል ጅቡ!

ይበላሃል ጅቡ!

ሃይ ሃይ ሃይ - ጀግናው ቶሎና!

ይዘነጥልሃል!

ይዘለዝልሃል!

ጅቡ ተቆጥቶአል!»

ሻለቃ ጉተማ መኪኖቹን በቀጣ አስቆመና ያምባርቅ ጀመር።

«ጅብ የህፃን ልጅ ማስፈራሪያ ነው። አንበሳው በሉ!»

ሆኖም ወታደሮቹ 'አንበሳው! እያሉ አላዜሙም። ሌላ ግጥም ለወጡ ...

ያሆ!

ያሆ!

ዲያም ... የለመዲየው!

ወርዲየህ ... አንክተው!

ግፋ!

ወርዲየህ ... ክተፈው!





ቁጡውና ነጭናጫው ሻለቃ መለዮውን አወለቀ። ሲጋሩን አቦነነ። ጉልበቱ ላይ ካለው ኪሱ ሽጉጡን ስቦ ሽንጡ ላይ ሰካው። ቁመናው መቼም ለመኰንንነት የሰጠ ነው።

ምናለ መንጌ ምናለ?

ኤርትራን ለአረብ ...

ውጋ!

ዳህላክን ለአረብ

ንቀል!

ምፅዋን ለአረብ!

ውጋ!

አልሰጥም አለ»

ሻለቃ ጉተማ ወደ መገናኛ ሰራተኛው ዞሮ አለ።

«ቡርቃ ቀርበናል! መከላከያ ሚኒስትሩን አገናኘኝ!»

የመገናኛ ሰራተኛው የቡልጋሪያ ስሪት የሆነውን ሬድዮ RU20 ይጠቀጥቀው ጀመር።

«አልፋ ብራቮ!

አልፋ ብራቮ!

ድድድ ... ድዳ! ...»

**ሆኖም መልስ ስላልመጣለት ያንኑ የኮድ ቃል መልሶ ያሰማ ጀመር። ይሁን እንጂ ሊሳካለት አልቻለም።**

***ሆታው ቀጥሎአል ...***

***«ምናለች ጣይቱ ምናለች?***

***ምናምንቴውን ...***

***ውጋ!***

***እንቶፈንቶውን ..***

***ንቀል!***

***አራሙቻውን ...***

***ውጋ!***

***መንጥሩት አለች!»***

* * *

ከግማሽ ቀን በሁዋላ ... የረጅም ርቀት ሬድዮው በተደጋጋሚ ጢጢጢ እያለ ይጠራ ጀመር:: ሻለቃ ጉተማና ሌሎቹ መስመራዊ መኰንኖች የመገናኛ ሰራተኛውን ከበቡት፣

«... ዴልታ አስካር!

ዴልታ አስካር!'

ድድድ ... ድዳ ..!» የሚል ድምፅ አስተጋባ::

የመገናኛ ሰራተኛው በተቻኮለ ድምፅ፣

«ከመከላከያ ሚኒስቴር ነው!» ካለ በሁዋላ ምላሽ ይሰጥ ጀመር::

«አልፋ ብራቮ!

አልፋ ብራቮ!

ዳድዳ ...!'»

ከዚያም መልእክቱ ይጐርፍ ጀመር:: የሚደረደሩትንም ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቁጥሮች የመገናኛ ሰራተኛው በችኰላ እየተረጐመ ለመኰንኖቹ ይገልፅ ጀመር::

«አልፋ ዋይት የሚባል ሰው ልከናል:: ... ተባብራችሁ ችግሩን ፍቱት:: ... አመፁ መቆም ካልቻለ ... ርምጃ ይወሰድ:: ... ቅስቀሳም ይካሄድ:: ... ሆቴል ... ሆቴል ... ማይክ::»

ሻለቃ ጉተማ እንደማፋዋጨት አለ:: ሆቴል ሆቴል ማይክ ... 'ሀይለጊዮርጊስ ሀብተማርያም - ሚኒስትር' ማለት መሆኑን አሳምሮ ያውቃል::

የመገናኛ ሰራተኞቹ የመዝጊያ ኮዳቸውን ይለዋወጡ ጀመር:: ከሶስቱ መኰንኖች መካከል ትንፍሽ ያለ አልነበረም:: ይተያዩ ጀመር:: ፀጥታውን የሰበረው ምክትል አዛዡ የመቶ አለቃ ነበር፣

«ማነው አልፋ ዋይት?»

«አኖሌ ዋቆ መሆን አለበት» አለ ሻለቃው::

«ምንድነው'ሱ?»

«የዋቆ የማደጐ ልጅ!» አለ በግማሽ ቀን ጊዜ ውስጥ ከሰበሰበው መረጃ በመነሳት::





«ዋቆ ጠንቋዋይ ይሆን?»

ሻለቃ ጉተማ በጥያቄው የፌዝ ፈገግታ አሳየ:: ይልቁን የአርሲ ልጅነቱንና የኦሮሚኛ ቋዋንቋዋ ችሎታውን ተጠቅሞ ስለ ዋቆ የሰበሰበውን መረጃ ይዘረግፍላቸው ጀመር::

«... ዋቆ ማለት የመቶ ሰባት አመት ሽማግሌ ነው:: በአካባቢው የሚታወቅበት ብዙ የመጠሪያ ስም አለው:: አባዱላ ይሉታል:: 'የጦር መሪ' ማለት ነው:: የቡርቃ አድባርም ይሉታል:: 'ቡርቃ ኦሮሞ' ሲሉም ያሞግሱታል:: 'የኦሮሞ አያት' ማለት ነው:: እንደሚባለው ይህ ሰው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ክንዱ ገና አልዛለም ነበር:: በዚያ እድሜው ጦር ይሰብቃል:: በትክሻው ጠመንጃ ያነግታል:: ድምፁ ጠንካራ ነው:: አረማመዱና አረጋገጡ የአፍላ ጐረምሳ ነው:: አይኖቹ የነብር ይመስላሉ:: ታዲያ ቅቤ ነበር አሉ ምግቡ:: የቡርቃ ገበሬዎች ናቸው የሚቀልቡት:: ወተት ነው የሚጠጣው:: ማር ነበር የሚልሰው:: ጥሬ ስጋም ይወዳል:: የሚቀርብለት ቡና ላይ ቅቤ ጠብ ካልደተደረገበት ንክች አያደርጋትም:: ጠዋት ገንፎ በወጪት ይቀርብለታል:: እሱን ካጋባ በሁዋላ የበሬ ደም ይቀርብለታል:: ደሙን ከታረደ በሬ ሳይሆን በሬውን በቁም እየበጡ ቀድተው ነው የሚያቀርቡለት:: ብርዝ አልፎ አልፎ ይቀምሳል:: አረቂ አጠገቡም አይደርስ:: ሃይለኛ ተናጋሪ ነው:: ሰንበት ዞሮ ሲመጣ ገበሬዎችን ሀማጋው ላይ እየሰበሰበ አማራን ያጥላላል:: 'አረቂን ያመጣው አማራ ነው' እያለ ይቀሰቅሳል:: 'ውሰዱ ልጆቼ! ታዲያ ልጆቻችሁን ወተት ብቻ አጠጡዋቸው:: እኛ ኦሮሞዎች ስምንት ሺህ አመት ሙሉ ወተት ነው የጠጣነው:: እነርሱ ደግሞ ሶስት ሺህ አመት ሙሉ ጠጅና ልብ የሚያቆሽሽ አረቂ ነው የጠጡት:: ሙቶ ውሰዱ ልጆቼ:: የኦሮሞ ምድር ገና አልሞላም:: ውሰዱና ሙሉት:: መሬታችን እንደሁ እንኳዋን ለኛ ለአማራውም ተትረፍርፎለታል:: ልጆቼ! ልጆቼ! አደራችሁን ለአማራ ሦሰስኛ ላቹ በገንቦና በማሰሮ ቅቤ እየሞላችሁ ፍትህን አትሰምኑ!' እያለ ይቀሰቅሳል ነው የሚባለው» ካለ በሁዋላ ወረቀቶቹን እያገላበጠ ያነብላቸው ጀመር:: «... 'ፍትህን በምልጃ ከምታገኙ የበደልን ቁዋጥኝ እንደተሸከማችሁ ቆዩ:: ፍትህ ዋቀዮ የሚሰጣችሁ በረከት እንጂ በገንቦ ማር የሚለወጥ የሰሜን አሞሌ ጨው አይደለም:: ልጆቼ ... ልብ በሉ ... አሽሙር ኦሮሞ አደግ አይደለም:: ውሽማ ማስቀመጥ የኛ ባህል አይደለም:: እንጀራ መሸጥ የኦሮሞ ልማድ አይደለም:: ከዚህ በሽታ ተጠንቀቁ:: ተንኮል የኦሮሞ አይደለም:: መንገብገብ የኦሮሞ አይደለም:: ፍርሃት የኦሮሞ አይደለም:: የኦሮሞ ልብ ንፁህ ነው:: ኦሮሞ ሰው አይንቅም:: ቅን ነው:: ሁሉም የአምላክ ፍጡር ነው::' እያለ ነበር ዘወትር የሚደሰኩረው:: የዛሬውን አመፅ

የቀሰቀሰውም ይህ የጃጀ ጆንያ ለዘመናት የረጨው መርዝ ነው::»

ሻለቃ ጉተማ ሲጋራውን ለኮሰ:: ከዚያም ተቀምጦበት የነበረው ቁዋጥኝ ላይ ወጥቶ ወደ ቡርቃ ተራራዎች በጦር ሜዳ መነፅሩ አሻግሮ ይመለከት ጀመር::

«አኖሌ የዋቆ የማደጉ ልጅ ከሆነ እንዴት ነው ከኛ ጋር እንዲሰራ ሊላክ የቻለው?» ሲል ሙቶ አለቃው ጠየቀ::

«እኔም አልገባኝም!» አለ ጉተማ ተንኮል እያሸተተ:: «ግን እስኪ እዚህ ይድረስና እንየዋ! ካባቱ ያልተሻለ ደነዝ መሆን አለበት:: ምክንያቱም ...»

መኰንኑ ሊናገር የፈለገውን ስላላወቀ ንግግሩን ገታና ከንፈሩን በጥርሱ ይነክስ ጀመር:: ይህን አመፅ በማቆም ታላቅ ጀብዱ ቢፈፅም አንድ ወደላይ የማእረግ እድገት እንደሚያገኝ አልተጠራጠረም:: አኖሌ የተባለ ደንቃራ ሰው ግን መሃል ላይ እየገባበት ነው:: ይህም ለብቻው የሚቀዳጀውን ዝና ይሻማዋል::

«... ለማንኛውም ይምጣና እንየዋ!»

በጦር ሜዳ መነፅሩ ቡርቃ ከረብታ ላይ እንደ ጨፌቃ የተጠቀጠቁት ገበሬዎች ጉንዳን መስለው ይታዩታል:: ሰአቱን አየ:: አስር ተኩል:: ዘወር ሲል ከሩቅ አቡዋራው እየተኸመለመለ ሲመጣ ተመለከተ:: መነፅሩን በችኮላ አይኑ ላይ ተከለ:: በአቡዋራው ውስጥ ስቴሽን ዋገን ታየችው:: 'አልፋ ዋይት መሆን አለበት' አለ ለራሱ ...

* * *

«አኖሌ ዋቆ እባላለሁ - ከአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው የመጣሁት» አለው በኦሮሚኛ::

«ሻለቃ ጉተማ» ካለ በሁዋላ «... ኦሮሚኛውን ለጊዜው እናቆየውና በመንግስት የስራ ቋንቋዋ እንነጋገር::»

ሆነ ብሎ ነበር በነገር የተቀበለው:: አኖሌ ሽምቅቅ አለና የሻለቃውን ገፅታ ማጤን ጀመረ:: ቀፈፈው::

«መልካም! ለማንኛውም መረጃዎች እንለዋወጥና መደረግ ስላለበት ጉዳይ እንመካከር» ብሎ ሲጋራ አቀጣጠለ::

ሻለቃው ከንፈሩን በልጠጥ አድርጐ በሁለት እጆቹ ወገቡን ይዞ





እየተንጐራደደ፣

«አባትህ አገር እያመሰ ነው:: ከዚህ የተለየ ምን አይነት መረጃ ትፈልጋለህ?» ብሎ በንቀት አስተያየት ከላይ እስከታች ይገሸልጠው ጀመር::

አኖሌ ሊታገስ ሞከረ፤ ወገኖቹንም አሰበ::

«እኔም በመንግስት ተወክዬ ነው የመጣሁት:: ምናልባት ያልተነገረህ ከሆነ ደብዳቤ...» ብሎ ከደረት ኪሱ ወረቀት ሲያወጣ፣

«እሱ ተነግሮኛል:: የጨነቀኝ ግን ያንተ ውክልና አይደለም:: እኛ ከአመፀኞቹ ጋር ልንፋለም ተዘጋጅተናል:: አንተ ምን መፍትሄ ይዘህ እንደመጣህ ንገረኝና ልስማ:: እኔ በዚህ ፈታኝ ደቂቃ ላይ ተጨባጭ እርዳታ እንጂ አማካሪ አልሻም:: ገባህ?»

«ይገባኛል:: እመጣጤም ላግዝህ ነው» ብሎ ሊያረጋጋው ሞከረ::

«ምንድነው የምታግዘኝ?»

«ረጋ ብለህ ብንመካከር አይበጅም? የቁጣህ ምክንያት አልገባኝም::»

«ርጋታን ልታስተምረኝ አትሞክር የኔ ወንድም:: ጦርነት ላይ ነን:: ጥይት እየተኰሰክና እየተተኰሰብህ ምን ርጋታ አለ? እናንተ ሲቪሎች ጦርነትን ስለማታውቁት ውጊያ የቼዝ ጨዋታ ይመስላችሁዋል:: ይሄ ቅብጠት ነው!»

አኖሌ አቀርቅሮ ሲያስብ ቆየ::

ከመታገስ ሌላ አማራጭ እንደሌለው አምኖ የሻለቃውን ቁጣ በትእግስት ያባብል ጀመር:: እቅዱ እንዲበላሽበት አልፈለገም:: በትህትናና በዝምታ ያደምጠው ጀመር:: ሻለቃው ስለ መስዋእትነትና ስለ ጦርነት አስከፊነት ደንፍቶ ሲያበቃ መልሶ የራሱ ድምፅ ሙኸበት:: አኖሌ ተደምሞአል::

«ለመሆኑ እነዚህ ገበሬዎች ለአመፁ መሪ አንተን እንደመረጡ አውቀሃል?» ሲል ሻለቃው አይኖቹን እያጉረጠረጠ ጠየቀው::

«አውቃለሁ:: የመንግስት ባለስልጣናትም ይህን ያውቃሉ::»

«ይህን እያወቁ አንተን ወዲህ ላኩህ?»

በእምንታ ራሱን ላይ ታች ነቀነቀለት::

«አመፁን ምራ ብለው ነው የላኩህ?» ሲል አላገጠበት::

«አይደለም። አመፁን ለመግታት ነው የተላክሁት?»

«ጥሩ ነዋ! ... ጠመንጃ እንሰጥህና እንደ ወታደሮቼ ፊት ገብተህ ትዋጋለህ። ጀግንነት ያ ነው። ከጉኔ ሆነህ ምንድነው የምታማክረኝ? የጦር ሜዳን የውጊያ ጥበብ ታውቃለህ ወይስ በአቁዋራጭ ለመሾምና ለመሸለም ...»

«ሻለቃ ጉተማ ... እኔ መፍትሄ የምለው የመከላከሉን ውጊያ አይደለም። የተላክሁበት ሌላ ተግባር አለ።»

ሻለቃው ትክ ብሎ አኖሌን ያጤን ጀመር።

«ምን ልትፈፅም ነው ያሰብከው?»

«ውስጣቸው ገብቼ አመፁን እንዲያቆሙ እነግራቸዋለሁ!»

ሻለቃው በድንገተኛ የፌዝ ሳቅ ተጥለቀለቀ። በአኖሌ ሞኝነት ተገረመ። በሰባ አመት ትንቢት ተገፍተው ያመፁት ገበሬዎች ስለ አመፀ መቆም የሚያነሳባቸውን ሰው ወዲያው ጨፍጭፈው እንደሚገድሉት አልተጠራጠረም። ይህን አስቦ ሻለቃው በአኖሌ እቅድ ተደሰተ። ሄዶ አመፁን እንዲያቆሙ ሲማፀናቸው ኩሩዎቹ አርሲዎች ምራቃቸውን ነው የሚተፉበት። ባይገድሉት እንኩዋ አሽቀንጥረው ይወረውሩታል። ወይም አዋርደው ይመልሱታል ሲል አሰበ።

«መልካም ነዋ! እንዲያ ከሆነ ሞክር ...» ብሎ ረገብ አለ።

መስመራዊ መኮንኖቹ በአኖሌና በሻለቃው መካከል የተፈጠረው ውጥረት ረገብ በማለቱ ተንፈስ አሉ። አኖሌም ውስጣዊ ደስታ ተሰማው። ሆኖም ሻለቃው ከቁጣው የረገበበት ድንገተኛ ምክንያት አልተገለጠለትም።

«ወታደሮቹ ግን ቀድመው መተኮስ እንዳይጀምሩ በጥብቅ ልታስገነዝባቸው ይገባል» አለ አኖሌ።

«እሱን ለኔ ተወው። በየሙያችን ብንራመድ የተሻለ ይመስለኛል። የሻለቅነቱን ማእረግ ያገኘሁት በጉቦ እንዳይመስልህ። ጥይት በጆሮዬ አፍዋጭቶ ስጋዬ ተነዳድሎ ነው። በየሙያችን! አይመስልህም ወንድሜ!?»

«መልካም!» አለ በጣቱ ጢሙን እያፍተለተለ።

«ገበሬዎቹ ከነጦራቸው ከኮረብታው መውረድ ከጀመሩ ግን የጥይት ውርጅብኝ እንደሚዘንብባቸው ንገራቸው።»

አኖሌ ትእግስቱ ቢሙዋጠጥም እንደምንም ራሱን ሲቆጣጠር ጥረት አደረገ።





«ሻለቃ ጉተማ እነዚህ ሰዎች ወገኖችህ መሆናቸውን አትዘንጋ!» አለው ድምፁን ለማለዘብ እየታገለ።

«የእኔ ወገን የኢትዮጵያ ህዝብ ነው!» ብሎ ወደ መስመራዊ መኮንኖቹ ገልመጥ አለ። «የኢትዮጵያን ህዝብና መንግስት የሚነካውን ሃይል ሁሉ እፋለማለሁ። ይህ ደግሞ አላማዬ ነው። በዚህም ስለሚመኩ ይመስለኛል የመከላከያ ሚኒስትሩ ከብዙ ሺህ መኮንኖች መሃል እኔን የመረጡት። ካላወቅህ እንድታውቀው ነው። ለህዝብና ለመንግስቱ ባለኝ ወገናዊነት ስለሚያምኑ ነው የሀገር መከላከያ ሚኒስትሩ በስም ጠርተው ይህን ስራ ያዘዙኝ። ሜጀር ጄኔራሉ ህዝባዊነቴን ...»

«እኔ ስለጄኔራሉ ምርጫም ሆነ ስላንተ ህዝባዊ እምነት ...»

አኖሌ ተናግሮ ሳይጨርስ ሻለቃው በጩኸት አቁዋረጠው ...

«... መከላከያ ሚኒስትሩን እያንጉዋጠጥህ እንደሆነ ይገባሃል?»

«እኔ አላንጉዋጠጥኩም!» አለ አኖሌ።

ሻለቃ ጉተማ ወደ መስመራዊ መኮንኖቹ ዞሮ አፈጠጠባቸው።

«ይህን ሁኔታ እንደዋዛ አላልፈውም። በሰማችሁዋት ቃል ላይ ሁሉ ትፈርማላችሁ። ይሄ የሀገር ጉዳይ ነው!»

«ሻለቃ ... ምናልባት...»

አኖሌ በመታከት ሊናገር ጀመረ። ሆኖም እጁን ብድግ አድርጐ አቁዋረጠው።

«ከዚህ ወዲያ በቃን! ወደ ተግባርህ መሄድ ትችላለህ»

አኖሌ ከተቀመጠበት ሲነሳ ሹፌሩም አብሮ ብድግ አለ።

«በል ደህና ቆየን» አለው ተስፋ ባጣ ድምፅ።

ሻለቃው ምላሽ አልሰጠውም። መቶ አለቃው ግን፣

«ይቅናህ ጉዋድ አኖሌ!» ሲል ተነፈሰ።

ኮረብታውን ቁልቁል መውረድ ጀመሩ።

«አኖሌ ...» አለው ሾፌሩ።

«እህ!» በታከተ ድምፅ።

«የመከላከያ ሰዎች እንዲሁ ናቸው። ብዙ አትዘን። ርስበራስ

እንደተጠላለፉ እንደተገዳደሉ ናቸው:: ይህ ሻለቃም ባንተ ላይ ሪፖርት መፃፉ አይቀርም:: ጄኔራሉን መዝለፍህን ከገለፀ ደግሞ ጥርስ ውስጥ ልትገባ ትችላለህ»

«የምን ጥርስ?»

«የመከላከያ ሚኒስትሩን መዝለፍህ ከታመነበት በጣም መጥፎ ነው:: እኔ አሰራሩን ስለማውቅ ነው:: በመከላከያ ሚኒስቴር አስራ ሶስት አመት ሰርቼያለሁ:: በህዝብ ደህንነት ደግሞ አምስት አመት አገልግያለሁ:: አሰራርዋን ልቅም አድርጌ ነው የማውቃት::»

«እና ምን ላድርግ? ሰምተኸዋል ሲናፈጥብኝ:: ሰውዬው እበት ቢጤ ነው:: ለማውራት እንኳዋ እድል መች ሰጠኝ?»

«ቢሆንም ከፍተኛ መኮንን ነው:: ያምኑታል:: ካንተ ይልቅ እሱ ይታመናል»

«ሰው ያለምክንያት ይገደል ከሆነ ያሻቸውን ያድርጉኝ!»

«ስሜታዊ አትሁን እኖሌ»

መልስ አልሰጠውም:: ሲጋራውን እያቦነነ መኪናዋ ወደቆመችበት አቅጣጫ ተጣደፈ::

«እኖሌ ...» አለው ሾፌሩ የሩጫ ያህል እየተከተለው::

«እህ!»

«በተፈጠረው ሁኔታ ከልብ ነው ያዘንኩት:: እንዳንተ አንጀቴን የበላው ሰው የለም:: ምስጢር ለመጠበቅ ከማልክልኝ ልረዳህ ዝግጁ ነኝ::»

እኖሌ በመገረም ቆም አለ:: ሾፌሩን ትክ ብሎ አስተዋለው:: በርግጥም ገፅታው ላይ በራስ የመተማመን ስሜት ያነበበ መሰለው:: ግን እንዴት?

«አንተ ሾፌር ነህ:: ምንድነው የምትረዳኝ? ምን የተፈጠረ ልዩ ነገርስ አለ?»

«መጀመሪያ ከባድ አደጋ ውስጥ መሆንህን እመን እኖሌ! የሻለቃውን ዛቻ እንደዋዛ አትናቀው:: መኮንኖች በአብዛኛው መሰሪዎች ናቸው:: ስራ አይወዱም:: ተንኮል ሲጎነጉኑ ነው የሚውሉት:: እኔ ስለማውቃቸው ነው:: ደፋር ለመምሰል የሚጥሩ ፈሪዎች፣ አቃጣሪዎች፣ የገዛ ወዳጃቸውን አርደው የሚበሉ ጨካኞችና ስግብግቦች ናቸው - ባብዛኛው:: ይህ ሻለቃም አንተን ካላጠፋ አይለቅህም:: ይህንን መጀመሪያ ማመን አለብህ::»





እኖሌ ሰአቱን አየ:: ከዚያም ወደ ቡርቃ ከረብታ እንጋጠጠ:: ሳይመሽ እዚያ መድረስ አለበት:: አለበለዚያ ለአይን ያዝ ሲያደርግ አማፅያኑ እንደ ጉንዳን ሰራዊት እየተግተለተሉ ሊወርዱ ይችላሉ::

ግን አመፁን ማቆም ይችል ይሆን?

እኖሌ እርግጠኛ አይደለም:: ሆኖም የወታደሮቹን ሁኔታ ገልፆ አባቱን ሊማፀናቸው ይችላል:: አባቱ አንድ ቃል ከተነፈሱ ደግሞ ሁሉም ይታዘዙ ይሆናል? እና በመታከት ወደ ሾፌሩ መለስ አለ:: መኪናቸው አጠገብ ቢደርሱም ከፍተው አልገቡም:: ይተያዩ ጀመር::

«አደጋ ውስጥ ነኝ ይገባኛል» አለ እኖሌ ሾፌሩን በመገረም እያስተዋለው «... ግን ምን ማድረግ ይቻላል? እኔ የፈጠርኩት አይደለም» ብሎ ጂብሪልን አስታወሰ:: የሚመጣውን ችግር ሁሉ ጂብሪል ይቋቋምልኛል የሚል ስሜት አደረበት:: ከዚህ ብልጣ ብልጥ ሾፌር ጋር የሚያደርገው ውይይት አልጥምህ አለው::

«ከልቤ ነው የማግዝህ እኖሌ!» አለ ሾፌሩ::

«ምን አቅም አለህና? የሻለቃውን ክስ ለማስተባበል ልትመሰክርልኝ ነው?»

«አምን:: የሁለታችሁን ንግግር ሙሉ በሙሉ ቀድቼዋለሁ»

«ምን!?»

እኖሌ ቆሌው ተገፈፈ:: ሾፌሩ ባዶ እጁን እንደነበር አይቶታል::

«በሙሉ በምስጢራዊ መቅረጫዬ አስቀርቼዋለሁ!» ብሎ ከጃኬቱ የውስጥ ኪስ አንዲት የእጅ መዳፍ የምታክል ጠፍጣፋ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ አውጥቶ አሳየው::

እኖሌ በመደነቅ ረቂቅ መሳሪያዋንና ሾፌሩን አስተዋለ::

«ከየት አመጣህ?»

«ቃንዛዬ ነው:: ሾፌር አይደለሁም::»

«አላምንም!» አለ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ::

ፈገግ አለ ሾፌሩ::

«ጂብሪል ነው የመደበህ?»

«አይደለም:: ጂብሪል የኔን ስራ አያውቅም:: ሚኒስትሩ ራሳቸው ናቸው የመደቡኝ:: ጂብሪል ሾፌር ነው የምመስለው:: በህዝብ ደህንነት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ይሰለላል:: የኔን የመረጃ ሰራተኛነትም ሶስት ሰዎች ብቻ ናቸው የሚያውቁት:: ሚኒስትሩ፣

እኔ አሁን ደሞ አንተ።»

ምድሩ ዞረበት። ፍርሀት አንዘፈዘፈው።

«ሌላው ቀርቶ መኪና ውስጥ በኦሮሚኛ ያደረጋችሁትን ንግግር በሙሉ ቀድቸዋለሁ። በርግጥ ኦሮሚኛ አላውቅም።»

አኖሌ ብርክ ያዘው። በመኪና ውስጥ ከአባቦሩ ጋር ያወጉትን ሁሉ መለስ ብሎ አስታወሰና ስሜቱ ቀዘቀዘበት።

ሾፌሩንም የመማፀን ያህል ያስተውለው ጀመር።

«ለምንድነው ይሄን ሁሉ የምትነግረኝ?»

«ስላዘንኩልህ ላድንህ ብዬ ነው።»

«ከምርህ ነው?»

ራሱን በአዎንታ ላይ ታች ወዘወዘ።

«አመሰግንሃለሁ። ለምስጋናዬም ቃላት የለኝም። ውለታህን እመልሳለሁ።»

«ግን አንድ ችግር ደግሞ አለ»

«ምን?»

«ይህቺ መሳሪያ መቅዳት እንጂ አትደመስስም።»

«ቀዳህ ማለትክ ደመሰስክ ማለት ነው። አይነጣጠሉም።»

«አይደለም። በዚህች ቴፕ እንደ ከሞላህ ልትደመስሰው አትችልም። ያለው እድል ካሴቱን መጣል ብቻ ነው። ካሴቶቹ ደግሞ በቁጥር ነው የሚሰጡኝ። መኪና ውስጥ የተደረጉ ውይይቶችንም የግድ ማስረከብ አለብኝ።»

«ታዲያ ምን ይሻላል?» አለ እንደገና ግራ ተጋብቶ።

«ያለው እድል አንድ ብቻ ነው» አለ ሰላዩ ሾፌር «... በአዲስ ካሴት ሌላ የውሸት ንግግር መቅዳት አለብን። ያንን አስረክባለሁ። የበለጠ እንድትታመን የሚያደርጉ ጨዋታዎችን እንቀዳለን። ከዚያ መንገድ ላይ የቀዳነውን እናስወግደዋለን። ግን ካሴት እንዳይጉድልብኝ ገንዘተን መተካት ይኖርብናል።»

«ይህማ ቀላል ዘዴ ነው። ምን ችግር አለው?» ብሎ ፈገግ አለ።

«ካሴቶቹ ግን እዚህ ሀገር አይገቡም። ፓይለቶች ብቻ ናቸው ሊያስገቡዋቸው የሚችሉት። እነሱ ደሞ ብዙ ይጠይቃሉ»





«ምን ያህል?»

«የአውሮፕላን ፍተሻውን ታውቀዋለህ መቼም። እነዚያን ካሴቶች ይዞ የተገኘ ሰው ያለጥያቄ ይረሸናል። ስለዚህ ፓይለቶቹ ነፍሳቸውን ሸጠው ነው የሚያመጡልኝ። እየህ ብዙ ሰዎች በዚህ መንገድ ተሹመዋል። መቀዳታቸውን ሳያውቁ እንደዋዛ በተናገሩት ብቻ የተገደሉም ጥቂት አይደሉም»

«ምን ያህል ነው ገንዘቡ?»

«አስር ሺህ ብር።»

አኖሌ ለጥቂት ሰከንዶች ሲያስብ ቆየ። የካሴቶቹን ዋጋ ያውቀዋል። ጀርመን ላይ አንድዋ ካሴት አራት የጀርመን ማርክ ነው የምትሸጠው። ይህ ጊንጥ ሰላይ ሊጠቀምበት እንደሚፈልግ ተረዳ። ግን ጉዳዩ የካሴት ዋጋ አይደለም። ንግግራቸው በህይወትና በሞት ዙሪያ ነው። ሾፌሩ በፀጥታ ይጠብቀዋል።

«መልካም ነዋ!» ሲል ተነፈሰ። «... አሁን ወደ ቡርቃ ኮረብታ እንሂድ። ምናልባትም የህይወቴ ፍፃሜ እዚሁ ይሆንና ሁሉም ነገር ያበቃል። አይመስልህም?»

ሾፌሩ ግን ምላሽ አልሰጠውም። በዚያችው ሰከንድ ፀፀት ልቡን ይጭረው ጀምሮአል። ሃያ ሺህ ብር የሚያወጣውን ጉዳይ በአስር ሺህ ብር እንደዋዛ መጣሉ ተሰማው። ራሱን ይረግም ጀመር።

ገበሬዎቹ ወደ ተሰባሰቡባት ኮረብታ አቀኑ ...

አኖሌ መጠቃትና ብቸኝነት ተሰማው። በተለይ ብቸኝነት።

«ሀወኒ! የትነሽ!?» እያለ ውስጡ ይጮሀል። እሪ ይላል። ወደ ከረብታዋ በቀረቡ ቀጥርም መረበሹ ይብስበት ጀመር ... ውስጡም [illegible]ቶውን ቀጠለ ...

«የት ነሽ ... ሀወኒ!'?»

- 5 -

አኖሌ በገበሬዎቹ እንደታጀበ ወደ ቡርቃ ኮረብታ አቀና። አሁን ጥቂት ነፃነት ተሰምቶታል። ምክንያቱም የስለላ መቅረፀ ድምፅ ይዞ የሚከተለው ሾፌር አጠገቡ የለም። ወደ ቡርቃ ኮረብታ የሚያወጣ ጥርጊያ ባለመኖሩ ሾፌሩ ሊቀር ግድ ሆነ። ለነገሩ ሾፌሩ ወደ ኮረብታው ባለመውጣቱ የተከፋ አይመስልም። ሁኔታው ወዳልታወቀ ተራራ መጉዋዝ አስግቶት ነበር። የመንገድ አለመኖር ሰበብ እጅግ ስለተስማማው ገበሬዎቹንና አኖሌን ከመኪናው አውርዶ ወደሁዋላው

ለመፈርጠጥ ጊዜ አልወሰደበትም። አኖሌም ጥቂት እፎይታ ተሰምቶታል። ከገበሬዎቹ ጋር እንደልቡ እያወጋ አቀበቱን ተያያዘው ...

«አባቦሩ ...»

«ወዬ ልጄ ...»

«ከዚህ ቀደም ይህን የመሰለ አመፅ ተደርጐ ያውቃል?»

«አንድ ጊዜ አገልጋዮች አምፀው ነበር።»

«መቼ!?»

«ሰላሳ አመት ሆነው መሰለኝ ...»

«ውጤቱ ምን ሆነ ታዲያ?»

«አለቁ! በሙሉ አለቁ ልጄ ...»

«በሙሉ!» አለ ሰቅጥጦት «አንድም ሳይቀር?»

አባቦሩ መልስ ሳይሰጡት ቀሩ። አኖሌ ቆፈን የወረደበት ያህል እጁ እግሩ ይንቀጠቀጥ ጀመር።

«አገልጋዮች መሳሪያ አልያዙም ነበር?»

«ጦር ነዋ! ...»

«እልቂቱ መጥፎ ነበር ታዲያ?»

«የእልቂት ጥሩ አለው እንዴ ልጄ? ...»

«ለምን ነበር አገልጋዮች ያመፁት?»

«በደል በዛ። ሲበዛ መሸከም አቃታቸው ...»

ሌላው ገበሬም በአባቦሩ ንግግር ላይ ጨመሩበት።

«... አገልጋዮች ተቆጡና አመፁ። በዚያም ሰበብ በመንግስት ወታደሮች ተጨፈጨፉ። ታዲያ ሬሳው በየጢሻው ወድቆ ለዋቀዮ በግልፅ ይታየው ነበር። ዋቀዮ በሰዎች ጭካኔ ክልብ በማዘኑም አለቀሰ። ከአይኖቹ ሁለት የእንባ ዘለላዎች ወደ ምድር ወረዱ። እኒያ ሁለቱ የእንባ ዘለላዎች ...»

አባቦሩ ድንገት መሃል ላይ ገብተው አቋረጡ።

«ነመራ አሁን በቃህ!»

የአባቦሩ ንግግር የተግሳፅ ያህል ስለነበር ሽማግሌው ገበሬ





ወጋቸውን ገታ አደረጉ። አኖሌ ግራ ገባው። የአባቦሩ የተግሳፅ ምክንያት አልገባውም።

ወደ ዋቆ አባዱላ ጐጆ ሲቃረቡ በቡርቃ አድባር ጐጆ ዙሪያ ለአመፅ የተሰበሰበው የገበሬዎች ሰራዊት በግልፅ ይታይ ጀመር። አኖሌ ባልተረዳው ስሜት ተሰቃይቶ አቃሰተ። ጊዜው ለአይን ያዝ ሊያደርግ ምንም አልቀረውም። መልእክ ሞት ካንዣበበባቸው የቡርቃ አድባር ጐጆ ዙሪያ፤ በኮረብታውና በሀማጋው ላይ ጦራቸውን - ጠመንጃዎቻቸውንና ችቦአቸውን ይዘው የሚያቅራሩት ገበሬዎች ድምፅ ከአኖሌ ጆሮ ደረሰ። ልቡ ቀዘቀዘበት።

«አባቦሩ?» ሲል በሞተ ድምፅ ተጣራ።

«የቡርቃ ሰዎችን ቁጣ ታየዋለህ?»

«ምንድነው መፍትሄው?»

«እንድረስና እናየዋለና!»

«ወታደሮቹ ለመተኮስ አያመነቱም አባቦሩ። በዚህ ሁኔታ መፋለም የእሳት ራት መሆን ነው»

«እንመክራለና ልጄ!»

«የቡርቃ ሰዎች ለምንድነው የኤንና የሀወኢን ስም የሚጠሩት? አባቦሩ!»

«ስለሚወዱዋቸሁ ነው ልጄ!»

ሶስተኛው ገበሬ ተጨማሪ ሰጠ።

«ሀገዘቡ ገር ነው። መቆጣቱን ብቻ ነው ያየው። በርግጥ የሰው ጅቦችን ለአይኑም ጠልቶአቸዋል። ስለዚህ ጅቦቹን ሊወጋ ጦር ይዞ መጣ። ታዲያ የቡርቃ ሰው ጦሩን ጋሻውንና ወኔውን እንደያዘ ይውጣ እንጂ ሌሎች ምን እንዳሰቡና ምን እንደያዙ አያውቅም ...»

ወጣቶች የፈረስ ጉግስ ትርኢት ሲያሳዩ ለአኖሌ ወሰል ብሎ ይታየው ጀመር። ገበሬዎቹ አኖሌ ከሶስቱ ሽማግሌዎች መሃል ሆኖ አቀበቱን ሲወጣ ሲያዩ እልልታና ተኩሱን ያንደቀድቁት ጀመር። «ወጣቶች በወጣቶች እየተመሩ» የሚለው ትንቢት ታወሳቸው። አንዳንዶቹ ችቦ ለኮሱ። የፈረሶች ጆሮ ቆመ። ጭድ የተጠቀጠቀው የችቦው ጫፍ ፍዋህ - ፍዋህ እየለ ብርሃን ይሰጥ ጀመር። ከችቦው ብርሃን ጉልቶ ደግሞ የሚያስገመግም ፉከራ ይሰማል።

*«እሰሳማሌይኩም!*

*ዋቆዮ መራንፍራ!*

*ዳ.ኒ ኬኛ ጭላሎ ጅራ!*

*ቀንጨራ ካሰኔ ጭራ!»*

ጦራቸውን መሬቱ ላይ ይሰቀስቃሉ:: የዋቆ፣ የአኖሌንና የሀመኒን ስም ያነሳሳሉ::

*«ሌልመከ አኖሌ!*

*ሌሳ ጅርታ!?*

*ኢንተለዮ ሀመኒ!*

*ሌሳ ጅርታ!?*

*ዋቆ! ዋቆ!*

*አሰላማሌይኩም!*

*አባዱላ መራንፍራ!*

*ዳ.ኒ ኬኛ ከፋሌ አሰላ ጂራ!*

*ቀንጨራ ካሰኔ ጭራ ...»*

አባበሩን ተከትሎ እንደ እሸን በፈሉት ገበሬዎች መካከል ሰንጥቆ ሲያልፍ ሴቶች እርጥብ ሳር እየነሰነሱ እልልታቸውን አቀለጡ:: ወንዶቹ በቡርቃ አድባር ትንቢት የተነገረለትን መሪያቸውን ለማየት ተጋፉ:: እንባቸው በጉንጫቸው ወረደ:: በእልህ እየተንቀጠቀጡ የሚያለቅሱም ነበሩ:: ሽማግሌዎቹ ጉልበት ቢከዳቸውም ከንፈራቸውን በቁጭት እየነከሱ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይቀሰቅሳሉ::

«እዩት ቁመቱን! እዩት ግርማ ሞገሱን! የቡርቃ አባት ያሉት ሀቅ ሆነ:: ዋቀዮ ነው ለዚህ ታላቅ ተግባር ያጨው! ከሚነበለበል እሳት መሀል ያዳነው ለዚህ ቀን እስቦት ኖሮዋላ! የቡርቃ አድባር ብለዋል! ቡርቃ ሆይ በቃህ!»

አንዳንድ ወጣቶች የአኖሌን ታሪክ ለማወቅ ሽማግሌዎቹን ይጠይቁ ጀመር:: ታሪኩን እናውቃለን የሚሉም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይደስኩሩ ጀመር::

«መልአክ ነው የሚመስለው:: ኩራቱስ? ቁመቱስ? የዋቆ አባዱላ መንፈስ ነግሮት ከተፍ ማለቱስ!?» እያሉ ያዳንቃሉ:: እልልታው አስገመገመ:: እርጥብ ሳር እዚህም እዚያም ይነሰነሳል:: በርግጥ ቡርቃ የእርጥብ ሳር እጥረት የለባትም::





ፈረሰኞች ሽምጥ ይጋልባሉ:: ጦሩ ወደ መሬት ይሰቀሰቃል:: ሲነቀል ያን ሀብታም ምድር ይቦተርፈዋል:: ገበሬዎቹ በአፍሪቃ ምድር በልምላሜው የማይስተካከለው በሌለው የጠገበ መሬት ላይ ሆታቸውን አቀለጡት:: ሽማግሌዎቹ ያለማቋረጥ ይደስኩራሉ ...

«... ወጣቶች አዳምጡኝ!» የሰማንያ ሶስት አመት ባለ እድሜ ነበሩ እንዲህ የሚሉት «... እንደ ቅቤ ከለሰለሰው የአርሲ ምድር ላይ ከበቀለው ሰርዶ ከብቶች አንድ እፍኝ ቢነጩ ጠግበው ይውላሉ:: የካካ ተራራ ኩራት ያስመሰግናል:: የኦሮሞን ምድር ሜዳ ሄዶ ሄዶ ማን ያዳርሰዋል:: የኦሮሚያ ሰማይ ከዘመን ዘመን፤ ከእለት እለት ውሃ ይታለባል:: ከኦሮሞች ከርሰምድር ያለው ውሃ ለሚሊዮን ዘመናት ቢመጠጥም አይደርቅም:: ሀብታም ነን:: ግን ይህ ሁሉ ሀብት ያለነፃነት ሰማይ ላይ እንደተንጠለጠለት ከዋክብት ነው:: **ጭላሎ ይታዘበናል፤ ካካ ይታዘበናል፤ ባቱ ይስቅብናል፤ መስካችን ፊሳ ነው።። በሉ እንማማል:: ውርደታችንን በቡርቃ ወንዝ ተለቃልቀን ሳናፀዳ ... ማር ሳንልስ፤ ገንፎ ሳንመገብ - ቅቤ ሳንቀምስ - ከበሬ አንገት በቀሙ በሰንጢ ተበጥቶ የተቀዳ ደም ወደ ጉሮሮአችን ሳይንቆረቆር እንማል። ይህን ብናደርግ የሞት ወንዝ ወደ ምድራችን ይንቆርቆር!»**

**በየቦታው በሚንቀጠቀጥ ድምፅ የሚደስኩሩ ሽማግሌዎች ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር፤**

**«... ይህ ሁሉ የምድራችን ጥጋብና ሀብት ከየት የመጣ መሰላችሁ? የኦሮሞ ምድር ራስዋ ለልጆችዋ የቸረችን እንጂ ከማንም ያልለመንነው - ከማንም ያልተበረከተልን ገፀ በረከት መሆኑን ኦሮሞዎች ተገንዘቡ...»**

**«...እናንተ ጉረምሶች አይበገሬነታችሁን አሳዩን!»**

**«...እንደ ዋቆ አባዱላ የጀግና ሰው ታሪክ ስሩ!»**

**«...አኖሌን ተከተሉት!»**

**«...ነፍጠኞችን አትራሩላቸው!»**

**ሶስቱን ገበሬዎች ተከትሎ የአመፀኛውን ሰራዊት ሰንጥቆ ወደ አባቱ ጉጆ ተጣደፈ:: ልቡ በፍጥነት እየመታ፤ ይህ የገነፈለ ስሜት ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን እንደሚችል እየገመተ፣ ነበር በሞት አፋፍ ላይ ወደሚገኙት አባቱ ጉጆ የደረሰው ...**

**ጉዋዳው ጨልሞአል::**

**አምስት ሽማግሌ ገበሬዎች በዋቆ አባዱላ የመኝታ መደብ ዙሪያ ከበዋል:: አኖሌ ምንም አልታየውም::**

«በሩን ዝጉት!» የሚል የሽማግሌ ድምፅ በድንግዝግዙ ውስጥ ተሰማ። አባቦሩ በሩን ዘጉት።

«ኩራዝ አብሩ!»

ኩራዝ በራ።

አኖሌ ዙሪያ ገባውን ተመለከተ። ስምንት ሽማግሌዎችና - አባቱ። አባቱ በአደፈ ነጠላ ከእግር እስከ ራሳቸው ተሸፍነዋል።

መሞታቸውን አወቀ። ሁሉንም አንድ ባንድ ያስተዋለው ፊቱ በድንጋጤ አመድ የተረጨበት መስሎ ነበር።

«አባቴ መቼ ሞተ!?» ሲል ጠየቀ።

«ዛሬ ጠዋት» አሉ አባቦሩ።

በዝግታ ተራምዶ አባቱ ራስጌ ላይ ተደፍቶ ተንሰቅስቆ ያለቅስ ጀመር። ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ከአባቱ አስከሬን ዳርቻ የቆሙት ሽማግሌ፣

«አኖሌ ጊዜ የለንምና ይብቃህ!» አሉት።

ቀና ብሎ ፊቱን በመሃረም አበሰ። አባቱ አስከሬን አጠገብ የቆሙትን ሽማግሌ ትክ ብሎ ተመለከታቸውና አስታወሳቸው። አባቦኩ በሚለው የክብር ማእረግ የሚጠሩ የተከበሩ ሰው ናቸው። አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያያቸው። በመላው አርሲ መልካም ስም እንዳላቸው ያውቃል። እዚህ ለምን እንደመጡ ግን አልገባውም። ሆኖም ይህን ሁሉ ለማሰብ ጊዜ የለም። ከባድ ሃላፊነት ተጥሎበታል። ምን ማድረግ እንዳለበት ማውጠንጠን ሲጀምር አባቦኩ ንግግር ጀመሩ።

«አኖሌ ልጃችን! እንኩዋን በደህና መጣህልን። የቡርቃ ሰዎች በዚች ደቂቃ ትልቅ የሞት አፋፍ ላይ ናቸው። ስለዚህ ወገኖቻችን ከከንቱ እልቂት ለማዳን እኛ የምንልህን ብቻ ትፈፅማለህ። ዋቆ አባዱላ እስካሁን አለመሞታቸውን ዋሽተን የተናገርነው አመፁ እንዳይነሳ ግጭት እንዳይጀመር ሰግተን ነው። ለሰባ አመታት እንደዋዛ ሲነገር የኖረው ትንቢት ወይም የቡርቃ ዝምታ ተረት ያልታሰበ መዘዝ እምጥቶአል። አደጋው እንዳይከፋ ብለን ነው ወደዚህ እንዲሰበሰቡ የለቀቅናቸው። አሁን ግን አንድ መላ እናበጅለታለን። በቅድሚያ አባቦሩ የሚገልፁልህ አቢይ ጉዳይ ይኖራል።»

አባባሩ ከተቀመጡበት ተነስተው መናገር ጀመሩ።

«... ከብዙ አመታት በፊት አገልጆ በምትባለው መንደር አመፅ ተቀስቅሶ ነበር። አገልጆዎች በደል ሲበዛባቸው ተቆጡና አመፁ። የንጉሱ ወታደሮችም የመንደሪትዋን ህዝብ በጥይት ጨፈጨፏቸው።





ጐጆዎችን በእሳት አጋዩ። የመንደሪትዋ ነዋሪ ሁሉ አለቀ። ለወሬ ነጋሪ እንኳዋ በመንደሪትዋ የቀረ አልነበረም። በርግጥ ማምለጥ የቻሉ በፈረስ ግልቢያ ብቻ አርሲን ጥለው ሸሽተዋል። ይህ እልቂት ሰማይ ላይ በተከበረ ዙፋኑ ለነበረው ፈጣሪያችን በግልፅ ይታየው ነበር። ፈጣሪያችን በአማርኛ ጭካኔ ከልብ በማዘኑም አለቀሰ። ከአይኖቹ ሁለት የእንባ ዘለላዎች ወደ ምድር ወረዱ። እኒያ ሁለት የእንባ ዘለላዎች ሁለት ነፍስ አዳኑ። ልጆቻቸውን ታቅፈው ሲሸሹ በጥይት ከጀርባቸው የተደበደቡ ሁለት የአገልጆ እናቶች ብብት ውስጥ እጅግ አምርረው የሚያለቅሱ ሁለት ህፃናትን አገኘን።»

አኖሌ ትንፋሹ ቁርጥ አለበት። ጐጆዋ በፀጥታ ተዋጠች።

«... እነዚያን ሁለት ህፃናት ያገኘናቸው ማምሻውን ለቀብር ወደ አገልጆ ሄደን ነው። የቡርቃ ሰው እነዚያን ህፃናት ይዞ በእልልታና በደስታ ይጨፍር ጀመር። የፈጣሪ ተአምር መሆኑን አወቅን። እነዚያ ህፃናት የዚያ ሁሉ በደል ማስታወሻ ይሆኑ ዘንድም የቡርቃ ሰው ሁሉ ተንከባክቦ አስተምሮ አሳድጐ ሰው ለማእረግ ሊያበቃቸው ወሰነ። ልጃችን አኖሌ ... ያንተና የልጅነት እጮኛህ የህወኒ ታሪክ ይኸ ነው።»

አኖሌ እንደምንም ስሜቱን አምቆ ይሰማ ጀመር።

«አባታችን ዋቆ ስምህን አኖሌ ያሉህም አኖሌ በተባለ ቦታ የተጨፈጨፉትን ወገኖቻችንን ለማስታወስ ነበር። ግን ሁሉም እንደ ቡርቃ ዝምታ ተረት ብቻ ሆነ ...

«ዋቆ አባዱላ ህልም ነበራቸው - ምናልባትም ከንቱ ህልም። ጤዛ ሆኖ የቀረ ምኞት። ዋቆ አባዱላ ይኸን ታሪክ ከፍ ስትሉ ሊያወጉዋችሁ ነበር አሳባቸው። እናንተ ግን ፊደል ከቆጠራችሁ በሁዋላ ... ዋቆንም ... እኛንም ... ቡርቃንም ረሳችሁ ... ናቃችሁን ... የቡርቃ አድባር በዚህ ሁኔታ ክፉኛ አዘኑ። ልባቸው ቆሰለ። ተስፋ አጥተውም ለሞት በቁ። የቡርቃ ህዝብ ግን ትንቢቱን ሳይዘነጋ ቆየ። ከዋቆ ጋር እያይዞ አምላክ የሚፈጥረውን ተአምር በጉጉት ሲጠባበቅ ዘመናት አለፉ። ዛሬ ታዲያ የቡርቃ ገበሬዎች የህልማቸውና የትንቢቱ ዳር የደረሰ አድርገው ቆጠሩት። አዎን የቡርቃ ዝምታ ህልም ነው ... ተረት ነው ... የሚጣፍጥ የማታ ወግ ነው ... ይኸን ለቡርቃ ገበሬዎች ማስረዳት ያስፈልጋል። እኛ ብንነግራቸው ግን አይቀበሉንም። አንተን ግን ያውቁሃል። ታሪክህን ሰምተዋል። ዋቆ ለመሪነት እንዳጨህም አስነግረናል። አንተና ህወኒ በአምላክ ተአምር ለመሪነት መመረጣችሁን ገበሬዎች ሁሉ አምነዋል። ስለዚህ አንተ ካልመራሃቸው ኰረብታውን አይወርዱምና የዋቆን አደራ መቀበልህን ሆኖም ጊዜው ገና መሆኑን ለህዝቡ ንገር።

አሮሞዎች ሙታንን ሳይቀብሩ ጦር አይሰብቁም በላቸው። በመጨረሻ የምገልፅልህ የአባትህን ኑዛዜ ነው። ዋቆ አባዱላ አንድ ቃል ብቻ ነው ለአንተና ለሀወኒ የተውት። 'የቡርቃን ህዝብ እንዳትረሱት፤ አደራ!' ብለዋል።»

ከዚያም ጉጆዋ በፀጥታ ተዋጠች። ከደጅ ግን ቀረርቶውና ሆታው ይሰማል። የፈረሶች ማስካካት ... የሚቀጣጠል ጭድ ድምፅ ... የፈረሶች ግልቢያ ...

አኖሌ በሀፍረት ተሸማቀቀ። እንባው ጉንጩን ያለብሰው ጀመር። ማንነቱን ያጣ ሆኖ ተሰማው። የክህደት ስሜት አቃጠለው። ግምባሩን ጉልበቶቹ መሀል ወሽቆም ይንሰቀሰቅ ጀመር ... የሰማው ታሪክ ... የቡርቃ ዝምታ ... ጣፋጭ ተረትና ትንቢት ... የአባቱ ታላቅ ምኞትና ተስፋ ማጣት ... የቡርቃ ገበሬዎች ቁጣ ... ጥሪ ... ረጅም ጥሪ ...

«ኤልመኮ አኖሌ ... ኤሳ ጅርታ!?»

- 6 -

አማሮቹ ገበሬዎች ቅዱስ ሚካኤል ተራራ ላይ ለፍልሚያው ተዘጋጅተው ይጠብቃሉ። መሪያቸው መምህር አስናቀ ከዳር እዳር እንደ አንበሳ እየተንጎማለለ ወገኖቹን ያበረታታል። በርግጥም አማሮቹ ጠመንጃቸውን ወልውለው አብቅተዋል። ጦራቸው ተሞርዶአል። የአይበገሬነት ወኔያቸው ተቀጣጥሎአል።

ለአይን ያዝ ማድረግ ሲጀምር መምህር አስናቀ ጡሩምባውን በረጅሙ ነፋ። ይህን ጊዜ ተዋጊዎቹ ገበሬዎች ከያደፈጡበት ብቅ ብቅ ይሉ ጀመር። ጆሮአቸውንም አንቅተው ከመሪያቸው የሚነገረውን ለማዳመጥ ተጠባበቁ፣

«ጭኮአችሁን! ሰነፍ ቀሎአችሁን! አነባበሮአችሁን ይዛችሁ ተሰብሰቡ!» የሚል ድምፅ ከእያንዳንዱ ገበሬ ጆሮ ደረሰ።

አፍታም ሳይቆይ በደብሩ ገላጣ ሜዳ ላይ ጦረኞቹ ጨፈቃ መስለው ተኮለኮሉ። መምህር አስናቀ መናገሪያው ቁዋጥኝ ላይ እመር ብሎ ከወጣ በሁዋላ፣

«በሉ ከስንቃችሁ ቆንጥራችሁ ተመገቡ!» ሲል አዘዘ።

ገበሬዎቹ የታዘዙትን በመፈፀም ላይ ሳሉ መምህር አስናቀም ከጥቁር ጤፍ የተጋገረ ስስ ቂጣውን አጨድ እያደረገ ይደበኩር ጀመር...

«አልገባቸውም እንጂ እኛ ሀዋርያቸው ነበርን። መንገድ መስራት የት ያውቁ ነበር? እንጀራ መመገብ አስለመድናቸው። ጨው አያውቁም ነበር። ገንፎውን እንደተፈጠረ አማስለው ነበር የሚበሉት። ዘይት የት ያውቁ ነበር? ሽቶ ባይናቸውም አይተው አያውቁም ነበር። ወገኖቼ አድምጡኝ ... የኢትዮጵያን ታሪክ መለስ ብለን ብናይ መልካም ነገሮች በሙሉ የተሰሩት በአማራው ነው። ሶስት ሺህ ዘመን ሙሉ አማራና ትግሬ እየተፈራረቀ ነግሶአል።

ትግሬው ምን ገነባ? ምንም!

መነጋገር ካለብን ለሀገርና ለህዝብ ጠቃሚ ተግባር ሰርተው ባለፉ ነገስታት ገድል ላይ ነው። አፄ ምንሊክና አፄ ኃይለስላሴ የሰሩትን ብቻ እንኳዋ ብናይ የኢትዮጵያ ስልጣኔ የአማራው ብቸኛ ድካም መሆኑን እንገነዘባለን። አማራው አዋቂ ነው። ሃያል ነው። በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ ህዝብ ነው። አማራነት ውበት ስለሆነ ልንመካበት ይገባል። በየትም አለም የሚያስመካ ብሄር ነው - አማራ። አማራ ማለት ጀግና ማለት ነው። በአሜሪካ በአውሮፓ በችሎታቸው ነጮችን ዘቅዝቀው የሚያዩ አማራዎች አሉ። እዚሁ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ሂዱ ... የዩኒቨርስቲው ሞተሮች አማሮች ናቸው። ታዲያ ይሄን ብሄር ማንም እየተነሳ ሊዘልፈው ይገባል? እኛስ የዚህ ብሄር አባላት አይደለንም? ማንም ተነስቶ እንጨፍጭፋችሁ ሲለን አንገታችንን ለካራ የምናቀርብ የስለት በጎች ነን? አናደርገውም! ማንነታችንን እናሳያቸዋለን! ሁለት መቶ አመት ዝም የሚያሰኝ በትር እናቀምሳቸዋለን! ወገኖቼ ፀያፍ ተናግሬ ከሆነ አርሙኝ!»

ገበሬዎቹ በርጋታና በዝምታ ይተያዩ ጀመር። ሰነፍ ቆሎአቸውን በጥንቃቄ ይቆረጣጥሙ ገቡ። አነባበሮአቸውን በዝግታ እየገመጡ ያላምጣሉ። እያላመጡ ይተያያሉ። መሪያቸውን ያስተውላሉ። አስናቀ ንግግሩን አራዘመ ...

«... ወገኖቼ ዛሬ እንዳባቶቻችን መፋለም አለብን። እንደነ በላይ ዘለቀ ... አዎን ... በላይን ታውቁት የለም? አማራ ነው። የምድረ ጎጃም አማራ። ጎጃሜ! የጎጃም ጀግና አርሶ አደሮችን አስከትሎ ፋሺስት ጣሊያንን ባማርኛ 'ውሃ! ውሃ' ያሰኘ ጀግና ነው። እንደ በላይ ነው ዛሬም መፋለም ያለብን! ...»

ድንገት ወደ ኮረብታዋ ሁለት ሰዎች ሲመጡ በሩቅ ታዩ። አስናቀ እንደ ንስር የማያተኩሩ አይኖቹን አሻግሮ ወረወረ። ሁለቱም የመንግስትን ወታደራዊ የደንብ ልብስ የታጠቁ ናቸው። ገበሬዎቹ ከተቀመጡበት መነሳት ሲጀምሩ፣

«ቆዩ ባላችሁበት!» ሲል አስናቀ በጩኸት አዘዘ «እነዚህ ወታደሮች ናቸው! እኛን ሲያድኑ እንጂ ሊተናኮሉን አይመጡም!»

ሻለቃ ጉተማ ነበር የመጣው። ሸጉጡን ጎኑ ላይ ሽጦአል።

አስናቀ አጠገብ እንደደረሰ፣

«እንደምን አመሻችሁ?» አለ በተረጋጋ ድምፅ::

«እግዚአብሄር ይመስገን!» የሚል የህብረድምፅ ምላሽ መጣለት::

«እዚህ የተሰበሰባችሁት ራሳችሁን ለመከላከል መሆኑን ሰምቻለሁ:: ህብረታችሁ መልካም ነው:: ሆኖም የመንግስት ወታደሮች አካባቢውን በሙሉ ስለተቆጣጠሩት ወደየጉጆቻችሁ ተመለሱ:: ምንም የሚያሰጋ ችግር የለም! አመፁ ቢቀጣጠል እንኳዋ ከወታደሮቹ የሚያልፍ አይሆንም!»

ሻለቃ ጉተማ ንግግሩን ሲያበቃ የሞቀና የደመቀ ጭብጨባ ነበር የጠበቀው:: ሆኖም ገበሬዎቹ ገፅታ ላይ የእፎይታ ስሜትና የታመቀ ጭንቅ አየር ሲወጣ አስተዋለ እንጂ የጠበቀውን አላዳመጠም::

ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላም አማሮቹ ገበሬዎች የቅዱስ ሚካኤልን ደብር መሳለም ጀመሩ:: አንድ አዛውንትም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፣ «ቅዱስ ሚካኤል ሆይ! ... እኛ የማንም የበላይ ... የማንም የበታች አይደለንም ... አማራ ገበሬዎች ነን:: አንተ ደግሞ የኦሮሞችም የኛም አምላክ ነህ» ሲሉ ተሰሙ::

* * *

መምህር አስናቀ ሻለቃ ጉተማን ተከትሎ ወደ ወታደሮቹ ጣቢያ አቀና:: ያለማቋዋረጥም አማሮቹ ገበሬዎች ስለደረሰባቸው የመንፈስ ጭንቀት ተናገረ:: ሻለቃው ግን የመምህሩን ዲስኩር ከቁብም አልቆጠረው::

ወደ ቡርቃ ኮረብታ ስለላከው ሰላይ እያሰበ ነበር ::

ከአርባ አምስት ደቂቃ ጉዞ በሁዋላ ከጊዜያዊው ማዘዣ ጣቢያው ደረሱ:: ጨልሞ ነበር:: ጨረቃዋ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ደምቃ ወጥታለች:: በማዘዣ ጣቢያው ሀያ ደቂቃ ያህል እንደቆዩ ሻለቃ ጉተማ በጨረቃዋ ብርሃን ከቡርቃ ኮረብታ አቅጣጫ የታረሰውን ማሳ አቋዋርጦ በግልቢያ የሚመጣ ፈረሰኛ ተመለከተ:: የላከው ሰላይ ለመሆኑ አልተጠራጠረም:: አጠገቡ እስኪደርስ ለመጠበቅ እንኳዋ ፋታ አጥቶ ይቁነጠነጥ ጀመር:: እኖሌ ዋቆ በዚህች ቀውጢ ደቂቃ ምን በመፈፀም ላይ እንዳለ ለማወቅ እጅግ ጉዋጉዋ::

«እንኩዋን ደህና መጣህ' ምን ወሬ አለ!?» ሲል የጠየቀው ገና ከፈረሱም ሳይወርድ ነበር::

ሰላዩ ወጣት የቡርቃ መንደር ገበሬ ነው:: ሻለቃው ቡርቃ ወጣቱ ከደረሰ ጀምሮ በትንሽ ክፍያ የስለላ ስራ እያሰራው ነበር:: ወጣቱ





ከፈረሱ ዱብ ብሎ፣

«አመፁ ቆሞአል!» ሲል በደስታ ስሜት ጮኸ::

ሻለቃው ግን በድንጋጤ ባለበት ቀዝቅዞ ነበር የቀረው:: ጨርሶ ያልጠበቀው ዜና ነበር:: ያልፈለገው ወሬ:: አይኖቹን ወጣቱ ገበሬ ላይ እንደተከለ ፈዘዘ:: ያየውንና የሰማውን በኦሮሚኛ የሚተርክለትን ገበሬም ከልብ አልነበረም የሚያዳምጠው::

«... የሚደንቅ ሁኔታ ነው የተፈጠረው» አለ ሰላዩ «የቡርቃ ሰዎች ሊዋጉ ተዘጋጅተው ነበር:: የዋቆን የእረፍት ዜናና የእኖሌ ዋቆን መምጣት ለመስማት እንዳቆበቆቡ ነበር:: የሚደንቀው ተአምር እኖሌ ደርሶ ኑዛዜውን ከቡርቃ አድባር እንደተቀበለ ወዲያው የዋቆ ህይወት አለፈች:: እኖሌ 'አዳምጡኝ!' እያለ ቢጮህ ማን ይስማው:: ታዲያ የአርሲ አድባር አባቦኩ የስልጣን መከሰቻቸውን ከፍ ሲያደርጉ **እንደ ንብ ያምም የነበረው ሁሉ ድንገት ፀጥ ይል ጀመር::**

**ያን ጊዜ እኖሌ ተናገረ።**

**ሲናገር ሲጀምር** እንባው በአይኑ ሞላ:: እኔ ራሴ እንኩዋ **አልቻልኩም::** ከሶገልጆ **ጭፍጨፋ ተርፎ!** የቡርቃ ህዝብ አሳድጎት አስተምሮት፣ ማለፊያ ሆኖ ድምፁ እየተንቀጠቀጠ ሲናገር ቡርቃዎች ስለ ፈጣሪ ተአምራዊ ስራ ያወጉ ጀመር ...»

ሻለቃው ግን ሊያስቀጥለው አልቻለም::

«ምን ምን እንደተናገረ ብቻ ንገረኝ!» ሲል አምባረቀበት::

«ምን ያልተናገረው አለ? 'የታገሰ ነው የጊደርዋን ወተት የሚጠጣው' ይል ነበር ደጋግሞ:: አብሳቱ እናን ጉረምሳ ዱጋ! **እያለ ይህንኑ ይደጋግም** ነበር:: ከዚያም ቀጠለና ደሞ 'ግን ለእያሌ **አመታት አይደለም!** ለሚልዮን ስአታትም አይደለም! ጦራችሁን **እንዲያዛችሁ ቆዩ ወገኖቼ!** ቀጣችሁን እንደተቀጣችሁ ቆዩ! ብሶታችሁን **እንዳመቃችሁ ቆዩ!** ከንዳችሁን እንዳፈረጠማችሁ ቆዩ! ቡርቃ ማለት **እናንተ ናችሁ!** ዝም ያላችሁትም ወንዙ ሳይሆን እናንተ ናችሁ! **የኦሮሞን ምድር** የሚያጥለቀልቀው የቡርቃ ወንዝ ትንቢት ለእናንተ **የተነገረ ምሳሌ** ነው! በቡርቃ ወንዝ ተመስለው ይዘምሩ የነበሩት አባቶቻችን ናቸው! ከገደል የዘለሉት እባቶቻችን ናቸው - ቡርቃ **ወንዝ** አይደለም:: ቡርቃ እኛ ነን:: ወገኖቼ ለጊዜው ዝም እንዳልን **እንቆይ!** ልብ በሉና አድምጡኝ! እንደገና ሌሎች ሁለት ህፃናቶች **ብቻ** ቀርተው ሌላው ሁሉ የሬሳ ክምር እንዲሆን እድል አንስጣቸው! **ጠላቶቻችን** የሚፈልጉት ሞኝ በሬ እንድንሆንላቸው! አሻፈረኝ ካልን **ደሞ** እንድንጠፋ ነው:: ይህ ይፈፀም ዘንድ አንፍቀድላቸው! ዛሬ **ግን** ለአባታችን ለዋቆ አባዱላ ሙሾዋችንን እናውርድ! ቡርቃን ከብበው

ያደፈጡት ወታደሮች በኛ መቃብር ላይ የበሬዎቻችንን ሻኛ ቆርጠው ለሆዳሞች በበርባሬ እያጠቀሱ ጥሬውን ሲበሉ ጉምዥተዋል፡፡ እንመቻቸው፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ አንፍቀድ! አብሳቱ አናን ጉረምሳ ዱጋ! አብሳቱ አናን ጉረምሳ ዱጋ! በሉ ሙሾዎችንን እንደ አሮሞ ባህል እናውርድ! አባታችንን ... አድባራችንን! የታሪክ አያታችንን እንሸኝ! ወገኖቼ እንገታችሁን ቀና አድርጋችሁ አንቡ! ቃል እገባላችሁዋለሁ፡፡ እኔም አለሁ! የአያታችንን ኑዛዜ እፈፅማለሁ ...»

ሻለቃው በቁጣ አቋዋረጠው ...

«ገበሬዎቹ ዲስኩሩን አምነው ጦራቸውን አወረዱ!?»

«እንዴታ! እያንዳንዱ ገበሬ ቀስ በቀስ ጦሩን መሬቱ ላይ እየተከለ በርከክ ማለት ጀመረ፡፡ እኔምኮ ተንበርክኬ አልቅሼ የደንቡን አድርሼ ነው የመጣሁት፡፡ የዘገየሁትም ለዚህ ነው፡፡ ገበሬዎች እንባቸውን በፀጥታ አፈሰሱ፡፡ ሴቶች ባደፈ ነጠላቸው ፊታቸውን ሸፈኑ፡፡ ወንዶች በእንባ የተሞላ አይኖቻቸውን ወደ ሰማይ ሰቀሉ ...»

ሻለቃ ጉተማ፣ «ይህ ወጠጤ ፍየል» ሲል አጉተመተመ፡፡

መበለጡ አናደደው፡፡





# አዲነብርኢድ ሆይ!

# ካንቺ ርቄ ወዴት?

## ምእራፍ አራት

### - 1 -

አራት ሚግ ሀያሰስት በምብ ጣይ የጦር አይሮፕላኖች ከአስመራ የተነሱት ማለዳ ላይ ነበር፡፡ አይሮፕላኖቹ አየሩን በጩኸታቸው እተረማምሰው ወደ ትግራይ አቀኑ፡፡ የህወሀት ፖሊት ቢሮ አባላት ከጠዋቱ አንድ ሰአት ተኩል ጀምሮ ስብሰባ እንደሚያካሂዱ የተገኘውን መረጃ የተጠራጠረው አልነበረም፡፡ ከኮሎኔል መንግስቱ ሀይለማርያም ጀምሮ ውጤቱን የሚጠባበቁት ትንፋሻቸውን ውጠው ነበር ...

ሚጐቹ ኢላማቸውን ለማስተካከል ክሳድግመልን ጆሮ በሚበጠርቅ ድምፃቸው አናግተው አንድ ጊዜ ዞሩዋት፡፡ የተሰጣቸው

ምልክትና ካርታው አንዳችም ስህተት አልነበረበትም።

የመጀመሪያዋን በምብ ጣይ አይሮፕላን የያዘው አብሪራ አፅቀ ስላሴ ይባላል። ወጣት ነው። በበርካታ ውጊያዎች ተሳትፎአል። ሁለት ጊዜ አይሮፕላኖቹ ተመትተውበት በጃንጥላ ወርዶ አምልጦአል። በዛሬው ተግባሩ ግን አይሮፕላኑ ቢመታበት በጃንጥላ ወርዶ ማምለጥ እንደማይችል ማሰብ ጀመረ። ቢወርድ በህወሀት ነፃ መሬት ላይ እንደሚያርፍ ያውቃል። ይህ ከሆነ ይያዛል። ከተያዘ እንደሚገድሉት ያምናል። ቢሆንም ተግባሩን ከመፈፀም ወደሁዋላ አላለም። ሙያውን ይወደዋል - ባለአላማም ነው።

ሰአቱ ሞልቶአል ...

አብራሪዎቹ አካባቢውን ከተሰጣቸው ካርታ ጋር የሚያገናዝቡባት ደቂቃ። አንዳችም ስህተት እንደሌለበት እርግጠኛ የሆኑባት ሰከንድ።

ሰአቱ ሞልቶአል ...

... ሶስት ሰአት ከማለዳው።

በዚህ ሰአት የ «ወንበዴዎቹ» መሪ መለስ ዜናዊ የእለቱን የመወያያ አጀንዳ አሳውቆና አጠናቆ እንደሚሆን የአዲሳባ መንግስት እርግጠኛ ሆኖአል።

ሰአቱ ሞልቶአል...

የመጀመሪያው ሚግ አፍንጫውን ወደ ክሳድግመል ተከለ። «አምላኬ ሆይ! እርዳኝ!» ዝቅ ሲል ምልክቶቹ ቁልጭ ብለው ታዩት። «አምላኬ ሆይ! እርዳኝ!» ብሎ ሲለምን የሚደውልበት አለ በልቡ። ይህን ፀሎት ባሰማ ቁጥር ዘወትር በህሊናው የሚደውልበት ሌላ ፀሎት አለ - ተገላቢጦሽ፣ «አዎን አምላኬ ሆይ ሌሎች ይሞቱ ዘንድ እኔ እተርፍ ዘንድ እርዳኝ!»

የህወሀት መሪዎች ወደሚገኙበት የበረሀ የመሰብሰቢያ ዋሻ ቀልቀል ተወረወረ። ወረደ ቁልቁለቱን! አፍንጫውን እንደጦር ቀስር አሽቆለቆለ። ከዚያም በአይን ሊታይ በማይችል ፍጥነት የሚጉ አፍንጫ ተቀልብሶ ወደ ሰማይ ዞረ ...

ወደ ደመናው ክርስ ተፈተለከ። የሰማይ ሆድ የተተረተረ የሚያስመስለውን ድምፅና የቦምብ ውርጅብኝ አራግፎ ተፈተለከ። ድብልቅልቁ የወጣ ፍንዳታ! ክሳድ ግመል ተንቀጠቀጠ።

ሻምበል አፅቀ ስላሴ በደስታ ቡዋረቀ። የታለመለትን ግብ አግኝቶታል። ከህወሀት የፀረ - አይሮፕላን ጥይትም አምልጦአል። እየሩ ላይ ጥቂት ዋኘ። በትግራይ ሰማይ ላይ አክሮባት እየሰራ የአስመራን አቅጣጫ በያዘባት ደቂቃ ክሳድ ግመል እየተናወጠች





ነበር። የአቡዋራው አውሎ ነፋስ እሳተ ጐመራ መስሎ ይታየው ነበር-በድል አድራጊነት ለሰከረው አብራሪ።

ሁለተኛው የጦር አይሮፕላን ቀጠለ ... ሶስተኛው... አራተኛው... ሁሉም ኢላማቸውን አግኝተዋል። አንዳቸውም አደጋ አልደረሰባቸውም። ክሳድ ግመል እንደሰዶም እንደ ጐመራ ስትጋይ እንደዋዛ ገልመጥ አድርገው እያዩዋት ተፈተለኩ። በርግጥም የህወሀት መሪዎች የመሰብሰቢያ ዋሻ የቆሻሻ ማቃጠያ ጉድጉዋድ መምሰሉ ሀቅ ነበር።

*   *   *

ሀወኒ እንደወትሮው በማለዳ ነበር ከእንቅልፍዋ የነቃችው። እንደሰረኔ እያንጐራጐረች ወደ ኮረብታዎቹ ወጣች። የክሳድ ግመል የማለዳ ፀሀይ ቀድማ የምትወጣው ኮረብታዎቹ ላይ ነው። እዚያ ነጫጭ ደንጊያዎች አሉ። ፈጥነው ስለማይሞቁ ይቀዘቅዛሉ። ሀወኒ ሥዲያ ይሄ ነው የሚያስደስታት። ከደንጊያዎቹ ጋር አብራ መሞቅ ትጀምራለች። ከኮረብታዋ ግራ በቅርብ ርቀት ላይ ህፃናት የሚማሩበት ትምህርት ቤት አለ። እነርሱ ወደ ክፍል እየተንጫጩ መግባት እስኪጀምሩም ፀሀይ መሞቅ ትወዳለች። ከዚያ ግን ህፃናቱን ለማዋራት ከኮረብታዎቹ ላይ ተንደርድራ ትወርዳለች።

ህፃናቶቹ ይወዱዋታል - በተለይ ሽዊት። ከበው በትግርኛዋ ይስቁባታል። የያዘቻቸውን ጥቂት ቃላት ለቃቅማ ትንተባተባለች። ለህፃናቱ ጨዋታ - ለሀወኒ የቋንቋ ትምህርት። ትልቅ ሆና ትግርኛ ባለመቻልዋ ህፃናቱ በጣም ይገረማሉ። ምናልባትም ያልተፈታላቸው እንቆቅልሽ ሳይሆን አይቀርም።

ነጫጮቹ ድንጋዮች ላይ ተቀምጣ ፀሀይ መሞቅ ጀመረች። ዛሬ ግን እንደወትሮው አላንጐራጐረችም። ሀሳብ ገብቶአታል። ከራስዋ ጋር ሙግት ላይ ሰንብታለች። ክሳድ ግመል ዋሻ ውስጥ ተቀምጣ ሀየሎምን ማእከል ያደረገ የጦርነት ታሪክ መፃፍ እንደማትችል ተረድታዋለች። ሀየሎምን ተከትሎ ወደ ጦር አውድማ መጉዋዝ ደግሞ አስፈርቶአታል። ስጋትዋ ግልፅ ነበር። መሳ ት አትፈልግም። መሞት ማን ይፈልጋል? በርግጥ ታጋዮቹ ይሰዋሉ! «እነርሱ ግን አላማ አላቸው» ብላ አሰበች። «እኔ አላማ የለኝም?» ብላ ራስዋን ጠየቀች። አላማዋን አሰበች። «የሀየሎምን ታሪክ መፃፍ! እና ይህን ለማድረግ ህይወቴን አሳልፌ መስጠት አለብኝን? ከሞተኩስ?» ብላ አሰበች። ሳታስበው ሰውነትዋ ብርድ እንደያዘው ሰው ተንቀጠቀጠ።

ስለህይወት ያላትን አመለካከት ፈተሸችው። ተሟገተች። «ማንም ሰው ከሞት አይቀርም። ቢሆንም መኖር ደስ ይላል።

መሞትም ከሆነ እድሜ ሲያልቅ ቢሆን ይመረጣል» ስትል አሰበች። ሀወኒ አሁንም ሀሳብዋን መቁረጥ አልቻለችም። ሀየሉምን ተከትሎ መሄድ አደጋ እንደሚኖረው አጢናለች። የሀየሉምን ታሪክ ለመፃፍ ያላት ጉጉት ደግሞ ሰማይ ጥግ ነክቶአል።

ልብዋ ዋለለ። ስለዚህ ለጊዜው ይህን አሳብ ተወችውና ማንጐራጐር ጀመረች። ነጫጮቹ ድንጋዮች ሞቀዋል፣ እስዋም ግላለች። ህፃናቶቹ ተማሪዎችም እየተንጫጩ መምጣት ጀመረዋል። ሀወኒን በአይናቸው መፈለግ የጀመሩም አሉ። ሊስቁባት ፈልገዋል - ትግርኛ ባለመቻልዋ!

ሀወኒ ጣፋጮቹን ልጆች ስታይ ፈገግ አለች። የመኖር ጉጉትዋ ይበልጥ ጨመረ። አዎን ልጅ ትወዳለች። ልጅ መውለድ ትፈልጋለች። የራስዋን ልጅ የምታሳድግበትን ጊዜ ማየት ትፈለጋለች። ስለዚህ መሞት የለባትም። ብድግ ብላ ወደህፃናቱ አዘገመች። ሸዊትን በሩቅ አየቻት። ሞጥማጣዋ ሸዊት! የሀወኒ ትግርኛ አለመቻል ከልብ የሚያስቃት ሸዊት። ሚጢጢ ፍጥረት! ውብ፤ ጣፋጭ ሸዊት።

ወደ ህፃናቱ አዘገመች ...

ግን አጠገባቸው ከመድረስዋ በፊት ከባድ የጦር አይሮፕላን ጩኸት ክሳድ ግመልን አርገበገባት። ትርምስና ጩኸት ተከተለ።

ሀወኒ በሁለት እጆችዋ ጆሮዎችዋን ጥርቅም አድርጋ ይዛ ጩኸትዋን አቀለጠችው...

*   *   *

የአይሮፕላን ድብደባው በህወሀት አመራር አባላት፣ በተራ ታጋዮችና በህፃናት ላይ የሞትና የመቁሰል አደጋ አድርሶ አለፈ። ከቆሰሉት መካከል ሀወኒ አንዱዋ ነበረች። በቦምብ ፍንጣሪ ትከሻዋ ላይ ተመታች። ከዚያ በላይ የጐዳት ግን አወዳደቁዋ ነበር። ከድንጋይ በመጋጨትዋ ግንባርዋ ላይ ከፉኛ ቆስላ ሩህዋን ስታ ህክምና ሲደረግላት ቆየች።

በሶስተኛው ቀን ማምሻውን ግን እየተሻላት መጣ። መቃዠትዋን ቀነሰች። እተነፋፈስዋ ጭምር ተሻለ። ተሲያቱን ሰላማዊ እንቅልፍ ወሰዳት። እስከምሽት ድረስም ያለቅዠት ተኛች።

ራስዋን ስታውቅ ሀየሉምና ክንፈ ገብረመድህን ሊጠይቁዋት መጥተው ከመደብ አልጋዋ ግርጌ ተቀምጠው ነበር። አንዲት ታጋይ ነርስ በቀዝቃዛ ፎጣ ግንባርዋን ታረጥብላታለች።





«ሀወኒ!» አለ ሀየሉም።

«ሀየሉም» ስትል በደከመ ድምፅ ተነፈሰች።

«አይዞሽ ተርፈሻል» አላት ክንፈ።

ለማስታወስ እየሞከረች፣

«የአይሮፕላን ድብደባ ነበር?» ስትል ጠየቀች።

«ብዙ አትናገሪ። አረፍ በይ» አላት ሀየሉም።

ይህን ብሎ ግንባርዋን በእጁ ነካ።

ሀወኒ አይኖችዋን በርጋታ ከደነቻቸው። ግን አልተኛችም ለማስታወስ ጥረት ማድረግ ጀመረች። ቀኑ ተምታታባት።

ለምን ያህል ጊዜ በዚህ መልኩ እንደቆየች አታውቅም።

... ለማስታወስ ጣረች። ማለዳ ተነስታ ወደኩረብታ መውጣትዋ ታወሳት። ከዚያ ምን ሆነ? የአይሮፕላንኖች ጩኸት ፍንዳታዎች ይታወሳታል። ግን እንዴት ነበር ሁኔታው የተከሰተ መጀመሪያ አስደንጋጭ ጩኸት! እስዋም አብራ መጮሀ አልተዘነጋትም። አይንዋንም ጨፈነች። ጮሀ... ጮሀ... ስትገል የህወሀት አመራር የስብሰባ አድሞ በቦምብ ጢስ ታፍኖ ተመስክተ እንደገና ሌላ የጦር አይሮፕላን ድምፅ ...

የት ነበርኩ ያን ጊዜ? ብላ ማሰብ ጀመረች። ሙሉ በመ በቅደም ተከተል ማስታወስ ተሳናት። ከኮረብታው ወርዳ የታጋ ልጆች ወደሚማሩበት አድሞ መሄድዋን አስታወሰች። ህፃ በአይሮፕላኑ ጩኸት ሲንጫጩና ሲላቀሱ... ሸዊት የምትባለዋ ህ ወደእስዋ እየሮጠች ስትመጣ እንደነበር ትዝ አላት። ከዚያስ?

«ሸዊት ንእ... አጆዪ» እንዳለቻት ማስታወስ ቻለች። ከዚያ ከዚያስ? ማስታወስ አቃታት። ጫጫታዎች! ፍንዳታዎች! የሚሰነጥቁ የአይሮፕላን ድምፆች ...

በጆሮዋና በአእምሮዋ የቀረው ይኸው ነበር።

ሀወኒ አይኖችዋን ገለጠች። ክንፈና ሀየሉም አሁንም አሉ

«ክንፈ» አለች።

«አይዞሽ ሀወኒ»

«ሀሳብ ገብቶን ነበር። ግን ተርፈሻል» ሲል ተነፈሰ - ሀየሉ

«ሰዎች ተጐዱ?» ስትል ጠየቀች።

«ደህና ነው» የሚል መልስ ሰጠ ክንፈ።

የሁለቱም ገፅታ ላይ ደህና ስሜት እንደማይነበብ ግን በግልፅ ይታይ ነበር።

«ስብሰባ ላይ ነበራችሁ?»

«አልነበርንም። ማታ ስላመሸን አጋጣሚ አርፍደን ነበር። ሆኖም ወደ ስብሰባው ቦታ እያመራን ነበር» አላት ክንፈ።

«የተጐዳ ሰው አለ?»

«ደህና ነው»

«ማን ተጐዳ?»

«ሰዬና አባይ ቆስለዋል። ግን ለክፉ አይሰጣቸውም» ሲል መለሰ ሀየሎም።

ሀወኒ ለማስታወስ ጥረት አደረገች። እስዋ ህፃናቶቹ አካባቢ ነበረች።

በቁጣንጣሪው ተመትታለች። ህፃናቶቹ ዘንድ ጉዳት ደርሶ ይሆን? ይህንኑ ጠየቀቻቸው። ሀየሎምና ክንፈ እየተያዩ ዝም አሉ።

«ህፃናቶቹ ተጐዱ እንዴ?» ብላ ጮኸች።

ሀየሎም ሲጋራ ለኩሶ ሲያበቃ፣

«አምን ተጐድተዋል» አላት «... በጣም የምትወጃቸውን ሸዊትን ጨምሮ አምስት ተሰውተዋል። አስር ደግሞ ቆስለዋል።»

ሀወኒ በጉንዋ ድፍት ብላ ትንሰቀሰቅ ጀመር። ሀኪምዋ ብትገስፃትም ከአንጀትዋ የሚፈነቅላትን የስቃይ ስሜት መገደብ አልቻለችም።

«ስመሆኑ እዚህ መሆናችን እንዴት ታወቀ?» ስትል ጠየቀች።

«ስላይ አስርገውብን ነበር። አሁን እንኳዋ ይዘነዋል» አላት ክንፈ።

«ጦርነት መጥፎ ነው!» ብላ ራስዋን ግራና ቀኝ እየወዘወዘች ተወራጨች።

«የጦርነት ጥሩ የለውም - ሀወኒ» አላት ሀየሎም።

«ለምን አታቆሙትም ታዲያ! ተውትና ጥፉ ሀየሎም። ይህን ጨካኝና ግዙፍ ሀይል ልትቋቋሙት አይቻላችሁም። ትርፉ ህዝቡን





ማስጨረስ ነው የሚሆነው። አትችሉትም ሀየሎም! እብደት ነው ... መራራ ነገር ነው። ለምን አገር ለቃችሁ አትጠፉም?»

ሀወኒ ጨርሶ ራስዋን የሳተች ያህል እየተንገፈገፈች ስትናገር ሀየሎምና ክንፈ ተያዩ።

«ወዴት እንሰደድ ሀወኒ?» ሲል ጠየቀ ሀየሎም።

«ህዝብ ከሚያልቅ ወደሚመቻችሁ ሀገር ጥፉ!»

«እኔማ ከአዲነብርኢድ ወዴት እጠፋለሁ? የአዲነብርኢድን መሬት ከቶ ማነው የሚከለከለኝ?»

ይህን ሲል የተበታተነ ጠጉርዋን እያስተካከለላት ነበር። ልብ የሚነካ ፈገግታ እየመገባትም ያወጋት ቀጠለ...

«... የት እንሂድ ሀወኒ? በገዛ ምድራችን በምብ ያወርዱብናል። ስንፈጠር ጀምሮ ሊኖረን የሚገባውን መብት ነፈጉን። ስለዚህ ትግል ጀመርን። ሸዊትን የመሰሉ አበቦችን እየከፈልን ነው ያለነው። እያንዳንዱዋ ህይወት ታቀስለናለች። ምርጫ ግን የለንም። ሁላችንም ራሳችንን ለመስዋእትነት አዘጋጅተናል። ሞት አይቀርም። ህዝባችንን ከውርደትና ከድህነት ለማውጣት ሲባል የሚከፈል መስዋእትነት ደግሞ ተራ ሞት አይደለም። በተስፋ ህይወትን መስጠት የመሰለ አስደሳች ነገር የለም ሀወኒ።»

ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ክንፈና ሀየሎም ተሰናብተዋት ሄዱ። ሁለቱ የህወሀት መሪዎች ተሰናብተዋት እንደወጡ ብርድ ልብስዋን ጎትታ ፊትዋ ላይ ሸፈነችው። ሰውነትዋ ወባ እንደያዘው ሰው ተንቀጠቀጠ። ለመጀመሪያ ጊዜም ከተራ ፖለቲካዊ ልዩነት ባሻገር መራራ ... እጅግ መራራ ጥላቻ አሳደረች - በደርግ ስርአት ላይ። የቀጣ ስሜት በደምዋ ተሰራጨ። እንባ አልወጣትም። ሳታውቀው የብርታት ስሜት በልብዋ አደረ። ሀወኒ በዚያች ደቂቃ በደርግ ላይ ያሳደረችው ጥላቻ፣ ለትግል እንድትወስን አደረጋት። በዚያች ደቂቃ ውሳኔዋን ለሁለተኛ ሰው የገለፀች ባይሆንም በሙሉ እምነት ከተራ ታሪክ ፀሀፊነት ባሻገር ጠመንጃ አንስቶ ደርግን ለመፋለም የሚያበቃ ወኔና ቀጣ መሰነቅ ቻለች...

## - 2 -

አኖሌ በሶስተኛው ቀን ቡርቃን ለቀቀ ...

ዛፎቹ ...

ፈፋው ...

የቡርቃ ወንዝ የዝምታ ተረት ...

ሀማጋው ...

እንደ ሎጥ ዘወር ሳይል መጉዋዝ ፈልጐ ነበር:: አቃተው ... እንደ ሎጥ ዘወር ሳይል ከሩዘርዋ ከመግባቱ በፊት ዘወር አለ:: አልቻለም:: ወደ ቶዮታ ላንድ ክሩዘርዋ ከመግባቱ በፊት ዘወር አለ:: የሚሸኙት ገበሬዎች በዝምታ ቆመው አይን አይኑን ያዩታል ...

አባቦሩ ...

ፈረሰኛው ሆርዶፋ ...

መህቡባ ... ሀዋ ...

ብዙ ደጋግ ገበሬዎች ...

ብዙ አይበገሬዎች ...

መኪናዋ ጉዞ ጀመረች:: ከቡርቃ መራቅ ጀመረች::

በርግጥ ከቡርቃ ትራቅ እንጂ ከኦሮሞች ምድር ግን ገና አልወጣችም:: መቼምም አትወጣም:: ያሻትን ያህል ብትጋለብ ያው ምድሩ እንደሆነ የኦሮሞዎች ነው::

ሾፌሩ እያፏዋጨ ... እያንጐራጐረ ረገጣት:: አኖሌ ሾፌሩን የማዋራት ፍላጐት ስላልነበረው በራሱ አሳብ ዙሪያ ይዋኝ ጀመር:: ለመጀመሪያ ጊዜም ከወትሮው በተለየ በሚነድ ስሜት ስለ ኦሮሞዎች አጥብቆ ማሰብ ጀመረ:: ከተራ ቲዮሪ በላይ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ መላ አካሉን ናጠው:: በመኪናዋ መስኮት አይኖቹን አሻግሮ ሀብታሙን መሬትና ዛፎቹን ያስተውል ጀመር:: እረኞችን በተለየ መንገድ ማየት ጀመረ:: 'ኦሮሞዎች' የሚል ስሜት ውስጡን ያምሰው ጀመር:: የኦሮሞች ለም መሬት:: ለዚያ መሬት ሲባል የደረሰባቸውን በደል 'የኦሮሞዎች ነው' ያሉትን ማሰብ ጀመረ:: አባቦሩ 'ሰማዩም ቢሆን የኦሮሞዎች ነው' ያሉትን አስታውሶ ፈገግ አለ:: የኦሮሞን ሰማይ ልብ ብሎ ሊያስተውልና ሊያደንቅ አንገቱን በመስኮት ብቅ አድርጐ አንጋጠጠ:: ከማንም አገር ሰማይ በላይ ተውቦ ታየው:: ከጫፍ እጫፍ ሰማዩ ጥቁር ደመና አርግዞአል:: ቅዝቃዜንም ይተነፍሳል:: ሰርዶው የኤሌክትሪክ ምስሶዎችን እስከ ወገባቸው ውጦአቸዋል::

የቡርቃ ዝምታ ... የጥንት ተረት ... መራራ ተረት ... ህልም ያረገዘ ... ትንቢት ያዘለ ... በምኞት የታመቀ ተረት ...

በፈጣን መኪና ላይ ብዙ ሺህ ዛፎችን አለፉ:: 'ከማንም አገር የተሻሉ ዛፎች' ሲል አሰበ:: ውፍረታቸውስ? ደሞ አንዳንዶቹ ከርሳቸው ውስጥ ማር ሸሽገዋል:: ማር የሚያንጠባጥብ ዛፍ በየትም አለም ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅ - ሲል ለራሱ አንሾካሾከ:: ኦሮሞዎች ታዲያ ማር ከመጥገባቸው የተነሳ የሚንጠባጠበውን ቀይ ማር ዘወር





ብለው እንኳዋ አያዩትም::

«ዝምታ ዋጠህሳ?» አለው ሾፌሩ::

«ይቅርታ ...» ብሎ ረጅም አየር አስወጣ::

ነጐደ ደሞ ወደ ግል አሳቡ::

የዋቆ አባዱላ ዲስኩሮች ይታወሱት ጀመር:: በወቅቱ ችላ ያላቸው:: አባቱ ሀማጋው ላይ ለገበሬዎች የሚተርኩት:: የአሳዳጊ አባቱ ንግግሮች! ወደ ጆሮው ይንቆረቆሩ ጀመር::

- ምንሊክ የገዳውን ስርአት አጠፋው:: የኦሮሞ ሹማምንትንና ኦሮሞዎችን ጨፈጨፈ:: የኦሮሞ ያልሆነና ለእድገት የማይበጅ ባህላችንን የሚያጠፋ ስርአት ጫነብን:: ሰብእናችን ላይ ዘመተብን:: ወታደሮቻቸው እንደ በቅሎ ተፈናጠጡን - መሬታችንን ወሰዱ - **የኦሮሞ ህዝብ የነፍጠኞች አሽከር ሆነ - ለአንድ የነፍጠኛ የጦር መሪ ሁለት መቶ ኦሮሞ በሽልማት ተሰጠ** - ከነመሬታቸው:: የኦሮሞ **ቋንቋዋና ባህል እንዲጠፋ ተረባረቡ** - ይህን የተቃወመ ሁሉ እንደ **ዝንብ ረገፈ - ጥፍር እየነቀሉ! ብልት እየቆረጡ** አዋረዱን - ያን **ጀግና ህዝብ አንገቱን አስደፉት - ያን ቅን ህዝብ ተጠራጣሪ አደረጉት - ያን ሀብታም ምድር** በዘበዙት:: ወገኖቼ! ታዲያ ምንሊክ ማነው? **ወንጀለኛ ወይስ አርበኛ?**

«ሀዘን አታብዛ አኖሌ!» አለው ሾፌሩ:: እያይዞም «አባትህ እድለኛ ናቸው:: መቶ ሰባት አመት መኖር ታላቅ እድል ነው» አለው:: አኖሌ መልስ አልሰጠውም::

**የዋቆ አባዱላ ቁጣ ያዘለ ድምፅ በጆሮው ተመላለሰበት:: ሀማጋው ላይ ገበሬዎችን እየሰበሰቡ የተናገሩዋቸው መራራ ቃላት ቃል በቃል ወደ ጆሮው ተንቆረቆሩ ...**

**- ነፍጠኞች አቡቢንቲ የተባለ ሽቶ አንድ ብር ይሸጡልናል:: ሶስት እንቁላል ግን ከኛ በአምስት ሳንቲም ይገዛሉ:: ወተትና እንጀራ መሸጥ በኦሮሞ ነውር ነው:: እነሱ ግን አንድ እንጀራ መሸጥ ጀምረዋል:: ይኸ ነው ስልጣኔ? ቁንዲፍቱ መጥመቅ የኦሮሞ አይደለም:: የሰው ሚስት መወሽም የኦሮሞ አይደለም:: ነፍጠኞች ባህላችንን አቆሸሹት:: መሬታችንን ነጠቁን:: መሬታችን ቅቤ ነው:: ጥቁር ቅቤ ነው መሬታችን! ያስጐመጃል! ምንሊክ የሚባለው ስግብግብ ይህን ሀብታም መሬት ሲያይ ጐመዠ:: እኛን ማክበር አቃተው:: እንደፈረስ ልጋልባችሁ አለን:: አሻፈረን አልነው:: በመሳሪያ ብዛት ተማምኖ ጨፈጨፈን:: የሴቶቻችንን ጡት ጥሬ ስጋ እንደሚበላ ሆዳም ሰው እየተስገበገቡ ቆረጡት:: የሴቶቻችንን ጡት እኛ ከበግ ላይ ፀጉር እንደምንሸልተው እንዲያ ነበር**

'በስመ - አብ' ብለው የሚቆርጡት፡፡ እነዚህ ሰዎች በግ ሲያርዱ 'በስመ - አብ' አይሉም፡፡ ይጀምራሉ፡፡ የሴቶቻችንን ጡት ሲቆርጡ ግን 'በስመ - አብ' አይሉም፡፡ ግን ሀይማኖት አለን ይሉናል፡፡ ታዲያ ፈጣሪ የሚያየው የትኛውን ደም ነው? የበጉን ወይስ ከሴቶቻችን ጡት የሚፈሰውን? ወገኖቼ ውሻ ለምን እንደተዋረደ ታውቃላችሁ? ሲረግጡት እየተረገጠ፣ ሲያዋርዱት እየተዋረደ፣ ሲገዙት እየተገዛ፣ ሲጨቁኑት እየተጨቆነ፣ ሲበድሉት ተቆጥቶ አልገዛም ብሎ ጭራውን ስለቆላ ነው፡፡ ውሻ ሲበድሉት ተቆጥቶ አልገዛም ብሎ ቢሆን ኖሮ የልጆቻችን ስም ይህን ጊዜ «ውሾ» በሆነ ነበር - እና የውሻን መሰደቢያነት በህግ ብቻ መለወጥ ይቻላል!? ንገሩኝ ወገኖቼ ይቻላል!?-

ወደ ናዝሬት ሲቃረቡ አኖሌ ሰአቱን አየ፡፡ እኩለ ቀን ሲሆን ምንም አልቀረው፡፡ እለቱ ቅዳሜ ነው፡፡ አኖሌ አንድ ሀሳብ መጣለት - ናዝሬት መቆየት፡፡ በዚህ ጩፍጋጋ ስሜቱ አዲሳባ መግባት አልፈለገም፡፡ ናዝሬትን በአግባቡ ያውቃታል፡፡ በተማሪነት ዘመኑ የሚያውቃቸው አንድ ሁለት ወዳጆቹም አሉ፡፡

ወደ ሾፌሩ ዘወር ብሎ፣

«እኔ ናዝሬት ለመቅረት አስቤያለሁ» ካለ በሁዋላ «... ባለፈው ስለተነጋገርነው ጉዳይ ምን' አሰብሃል?» ሲል ጠየቀው - አሁንም ድምፁን እየቀረፀው እንዳይሆን እየሰጋ፡፡

«አዲስ አበባ እንደተመለስክ እንነጋገራለን!» አለው፡፡

«አዲስ አበባ እንደተመለስክ እንነጋገራለን!» አለው፡፡

«ገንዘቡን በአንድ ጊዜም ባይሆን ቀስ በቀስ እከፍልሃለሁ፡፡ ይኸ

ቃሌ ነው፡፡ አንተም ካሴቱን አሳልፈህ እንደማትሰጥ ቃል ግባልኝ፡፡»

«እመነኝ! እንድትጎዳ አልፈልግም፡፡ ታዲያ ምስጢር ጠብቅ፡፡ ካንተ በቀር ማንም ማወቅ የለበትም፡፡ አለያ ሁለታችንም በቀላሉ እንጠፋለን፡፡»

«ደህና!» ካለ በሁዋላ፣ «... መቼም ሪፖርት ማቅረብ ይኖርብሃል፡፡ ምንድነው ያሰብከው?»

«አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ካሴቱን አልጠየቅም፡፡ ገልብጬ በፅሁፍ ነው የማቀርበው፡፡ በርግጥ ጉዳዩ ከባድ ሲሆን ወዲያው ካሴቱን እንዳቀርብ እጠየቃለሁ፡፡ እኔ ግን ሶስት አስተማማኝ ነገሮች ይኖሩኛል፡፡ የመጀመሪያው ከፊታችን ያሉት ቀናት እሁድና ሰኞ ናቸው፡፡ ሰኞ ሚኒስትሩ ቢሮ አይገቡም፡፡ ሌላው በኦሮሚኛ መናገርህን ስለምገልፅ ካሴቱን ላይጠይቁ ይችላሉ፡፡ ሶስተኛው ወዲያው በወረቀት የሚቀርብላቸው ትርጉም ተራ ነገር ስለሚሆን ወዲያው አይተው ነው የሚወረውሩት፡፡ ቢሆንም ግን ዝግጁ ሆኖ መጠበቅ ስለሚያስፈልግ ሰኞ የማስመሰያ ድራማውን እናዘጋጃለን፡፡»





አኖሌ በመስማማት ራሱን ላይ ታች ወዘወዘ፡፡

«እንግዲህ እኔን አዳማ ራስ ተወኝ!»

«ደግ!»

«ደብረዘይት ላይ ቢራ መጠጫ ልስጥሃ!» አለ እጁን ወደ ኪሱ እየሰደደ፡፡

«ምንም አልፈልግም! በቂ ገንዘብ ይገርለሁ!» አለ በመጀነን፡፡

አኖሌ አዳማ ራስ ወረደ፡፡ ሰላዩ ሾፌርም ወደ ደብረዘይት አቅጣጫ ሸመጠጠ፡፡ ወይም ወደ ቢሾፍቱ ...

* * *

የቀረበለትን ቢራ ባንድ ትንፋሽ ጨልጦ ሌላ አዘዘ ...

ብቸኝነቱን በቢራ ማባረር እንደማይችል ግን ተሰምቶታል፡፡ ስለ ኦሮሞዎችም ሆነ ስለዋቆ አባዱላ ዲስኩር ማሰብ አልፈለገም፡፡ ራሱን ማዝናናትና የሰሞኑን ውጥረት ማቃለል ፈልጎአል፡፡

ሳሙኤል ትዝ አለው፡፡ ሳሙኤል የአስመራ ልጅ ነው፡፡ ጀርመን ነበር የሚተዋወቁት፡፡ ሳሙኤል አዲስ አበባ የመጣው በቅርቡ ቢሆንም አዘውትረው ይገናኛሉ፡፡ በቤተሰብ ንግድ ውስጥ እንደሚሰራ የነገረው ሲሆን በርግጥም የመዝናኛ ወጪያቸው ዘወትር በሳሙኤል ነው የሚሸፈነው፡፡ ይግባባሉ - በማንኛውም ነገር፡፡ አውርተው አይጣገቡም፡፡ ሳሙኤል ቁምነገሩንም መቀበጡንም ይችልበታል፡፡

አኖሌ ወደ ሳሙኤል መደወል ፈለገ፡፡ ቢያንስ ብቸኝነቱን ይገፍለታል፡፡ ከሆቴሉ ማስተናገጃ ወደ አዲሳባ ደወለ፡፡

«የለም!» አለችው ስልኩን የተቀበለችው ሴት፡፡

«የት ሄደ?»

«አላወቅሁም፡፡»

«በቅርብ ይመለስ ይመስልሻል?»

«አልነገረኝም፡፡»

«አኖሌ ደውሎ ነበር በይልኝ፡፡ ከናዝሬት ነው የደወልኩት»

«እሺ ... እነግራለሁ፡፡»

አኖሌ የስልኩን እጀታ እንደያዘ ማሰብ ጀመረ፡፡ ሌላው ወዳጁ ያው ጂብሪል ነው፡፡ ቢሮ ደወለ፡፡ የሚያነሳ የለም፡፡ ወደ መኖሪያ

ቤቱ ሞከረ:: ታናሽ እህቱ አንስታ አለመኖሩን ነገረችው::

«የት ሄደ?»

«አሁን ነው ወጣ ያለው:: ይመለሳል::»

«እንግዲያው ናዝሬት አዳማ ራስ መሆኔን ንገሪውና ከቻለ ይምጣ:: እዚያው እንደማመሽ ንገሪው::»

ስልኩን ዘጋና ወደመቀመጫው ተመለሰ:: ቢራውን ጨልጦ ሶስተኛ አዘዘ:: በአዳማ ራስ መዋኛ ዙሪያ በርካታ ወጣት ሴቶች ተኮልኩለዋል:: ይስቃሉ:: ይጮሀሉ:: አኖሌ ቀልቡ ተሳበ:: አይኖቻቸው አንድ ቦታ የማያርፈው የናዝሬት ቆነጃጅት የወሲብ ስሜቱን ቀሰቀሱበት:: ውበታቸው ታይቶ አይጠገብም:: አኖሌ አይኖቹን ካንድዋ ወደሌላዋ ያንከራትት ጀመር:: እነርሱም መች አረፋና:: ወግ ጀመሩት - የአይን ወግ::

ድንገት ዜኒት ትዝ አለችው:: የሀወኒ የልብ ጉዋደኛ የነበረችው ዜኒት:: ናዝሬት እንደምትኖር ያውቃል:: የቴሌፎን ቁጥርዋም ከጀርመን እንደተመለሰ ሀወኒን ሲያፈላልግ ዜኒትን አለው:: ሁለት ጊዜ ደውላ አግኝቶአት ነበር:: ጥቂትም አውግተዋል:: እምብዛም አላቀረባትም:: ልታገኘው ጭምር ፈልጋ ነበር:: አሁን ግን ድንገት ፈለጋት:: መንጠራራትዋና ጉራዋ ያናድደዋል:: ቁጥርዋን ከማስታወሻ ደብተሩ ላይ ይፈልግ ጀመር:: አገኘው:: ጊዜ ሳያጠፋ ደወለላት - ራስዋ ነበር ያነሳችው፣

«አኖሌ! ... ጨርሶ አላምንም ... በጣም አስቀያሚ ነህ! እሺ?»

«ይልቁን አሁኑኑ ነይ፤ በጣም እፈልግሻለሁ!»

«ጉረኛ ነህ!»

«ስድቡ ይቆይልሽ ... ዜኒ!»

«የት ነህ?»

«አዳማ ራስ»

በግማሽ ሰአት ውስጥ ጥቁር ሰማያዊና ነጭ ቀለም ያለው ውብ ቁታ ለብሳ ከተፍ አለች:: እጅግ አምሮባታል:: ዳሩ ሁሌ ውብ እንዳማረባት ናት:: አሁንም ከነጉራዋ ናት:: በመዋኛው ዙሪያ ያሉት ሁሉ ቅርፅዋንና ውበትዋን ያደንቁላት ዘንድ ገንዳውን ሽር እያለች ዞረችው - እንደ ሴቴ ሽረሪት::

«ይህ ጉራሽ መቼ ይሆን የሚለቅሽ?» አላት አጠገቡ እንደደረሰች::





«አስቀያሚ ነህ አኖሌ ሙት!» አለችና ሳመችው::

በናፍቆት ደህንነታቸውን ሲጠያየቁ ጥቂት ቆዩ:: ስለሀወኒ አለመገኘት አነሳሱ:: ዜኒት ስታወራ አይንዋን ግራና ቀ ታተረማምሰዋለች:: 'ልክፍት ነው!' አለ አኖሌ በልቡ:: በርግጥ ዜኒት ውብ ናት:: ዳሌዋ አካባቢ ሰፋ ሲል ይምክር እንጂ ከሳ እስከታች ቀጭን ናት:: አይኖችዋን ስትገልጥ ማንኛውም ሰው ላ ሽብር ትለቃለች:: የከንፈሮችዋ ማማር ለብቻው ነው:: ሁልጊ መሳሳምን ያውጃል:: እንደቀላ ነው:: እንደሞቀ ያስታውቃል ለነገሩ ቃጠሎ ናት:: ስትጨብጥ እንኩዋ መዳፍዋ ይፋጃል:: በክንደ በኩል ተሳልፎ ልብ ላይ ይነዝራል:: ጡትዋና የወገብዋ ቅጥነት ፊገጊታዋ ወሲባዊ መልእክት አለው:: የትምህርት ቤት ስምዋ ስኩዋር ነው::

«አሁንም ሀወኒን እየጠበቅህ ነው?» አለችው::

ትከሻውን በግዴለሽነት ሰበቀ::

«የት ያለች ይመስልሃል?»

«ማን ያውቃል?»

«ሱዳን ስደተኛ ጣቢያ የማሽላ ቂጣ ትጠፈጥፍ ይሆናላ!»

«ንግድ እንዴት ነው» ሲል ወሬ ለወጠ::

«ናዝሬት ተመችቶኛል!» ብላ ሳቀች::

ዜኒት ናዝሬት ላይ የልብስ መሸጫ ሱቅ አላት:: ታውቅበታለች:: ሱቅ የከፈተችው ከቤተሰብዋ ሰባሪ ሳንቲም ሳትደጎም ነው:: ጥቅም የሚያስገኙ ሹሞችን አሳዳ ማጥመድን ተክናዋለች:: የሚደንቀው ግን አስፈላጊ ካልሆነ ከሁሉም ጋር አትማግጥም:: ምርጫ ከወሩ ግን ታደርገዋለች:: አራት ምላስ አላት ይሉዋታል - የሚቀኑባት ጉረቤቶችዋ:: የመጀመሪያውን ከምትወዳቸው ወላጆችዋ ጋር ትነጋገርበታለች፤ ሁለተኛውን ከሹማምንት ጋር፤ ሶስተኛውን ከምትወዳቸው ወንድና ሴት ወዳጆችዋ ጋር ስትጠቀምበት፤ አራተኛውን ምላስ ሱቅ ውስጥ ልብስ ትሸጥበታለች እያሉ ያሙዋታል::

አኖሌን በጣም የሚገርመው ነገር የሀወኒና የዜኒት ጉዋደኝነት ነው:: ሀወኒ ሩህሩህ ናት:: ሀቅን ተከትላ ነው የምትሄደው:: ብትጎዳም ትሸከመዋለች:: ዜኒት ደግሞ የተገላቢጦሽ - ለጥቅም ስትል የምትሞት:: ሆኖም ይዋደዱ ነበር::

«ለመሆኑ ናዝሬት ለምን መጣህ?» አለችው::

«ቢራ ያገርና ላጫውትሽ»

«ግዴለህም ማርቲኒ ልውሰድ ... ዛሬ መቸም አብረን ነን» ብላ ፊገግታዋን አጠጣችው።

አኖሌ በቅርቡ የገጠሙትን ሁኔታዎች አጠር አድርጐ አጫወታት።

ወሬው አልጣማትም። እንዲህ ያለ ወሬ ጥሞአትም አያውቅም። አንድም ጥያቄ ሳታነሳለት ወደ ሌላ ርእስ ዘለለች።

«አዲሳባ ሱቅ መክፈት እፈልጋለሁ። አታግዘኝም?»

«ሹሞችን ታውቂ የለም እንዴ?» አላት እየቀለደ።

«አዲሳባ ላይ ማንንም አላውቅ» ብላ ትክዝ አለች።

ለአኖሌ ደግሞ ይህ እጅግ አሰልቺ ወሬ ሆነበት። እሱም ወደ ሌላ ርእስ ዘለለ።

«ልሳምሽ?»

እንደ እንቁራሪት ፈጠጡ አይኖችዋ። ልትናገር ያሰበችውን እንኩዋ ትታ አፏዋን ከፍታ ቀረች። ጉንጮችዋ ቀሉ። አይኖችዋ ውስጥ ሴሰኝነት ተምበለበለ።

«ሲገርም ...» አለች።

«ምን?»

«እንዲህ ትለኛለህ ብዬ አልጠበቅሁም።»

«እንዴት?»

ሳቀች። በጣም ሳቀች። ቀስት የመሰሉ ጨረሮች ከአይኖችዋ ውስጥ ሲተኰሱ ያየ መሰለው።

«ምን አሳቀሽ?»

«የምትገርም ሰው ነህ።»

«እንዴት?»

«አንድ ነገር ልጠይቅህ አኖሌ ..»

«ምን?»

«በጣም እፈልግሻለሁ ያልከኝ ለዚህ ነው?»

«አዎን» አለ ፍርጥም ብሎ።





«ልትስመኝ?»

ራሱን በእምንታ ነቀነቀ።

«ገምቼ ነበር። በጣም ልክ ነኝ።»

በተራው እሱ ሳቀ። ከልቡ እየሳቀ ጣቶቹን በጣቶችዋ አቆላልፎ ሳባት። እስዋ ቀድማ ሳመችው። መላው ሰውነቱን ነዘረው። ማመን አቅቶት ትክ ብሎ እያት። እውነትም ስኩዋር ናት። ስኩዋር ብቻ አይደለችም። በአይን የማይታዩ ጥቃቅን የኤሌክትሪክ ሃይል ሰጪ ማግኔቶች ከንፈሮችዋ ውስጥ ሳይቀበሩ አይቀርም። ከንፈርዋ ይነዝራል .. ማቃጠሉስ!

«ስኩዋር ነሽ ዘኒ ...»

«አስቀያሚ!» አለችው።

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ እጁን ይዛው ተነሳች። ስሜትዋን መቆጣጠር እንዳቃታት ይታወቅባታል። አይኖችዋ ውስጥ የወሲብ ጥማት ይምበለበላል።

«እንሂድ ...»

«የት?»

«አሳይሃለሁ ...»

እውነትም አሳየችው። መኝታ ክፍልዋን አየ። በርግጥ ማየት ብቻ አይደለም። ንፁህና በጥሩ እቃዎች የተሞላ ቤት አላት። ምሽቱ ቀንደ ሆነላቸው። ምናልባትም አኖሌ ከጠበቀው በላይ። ደስታው ውስጥ ግን የዋቆ አባዱላ ማብቂያ ቢስ ዲስኩር ይረብሸዋል!

ሀማጋው ላይ ...

አልህ የሚያንቀጠቅጠው ድምፅ ...

እርጅና ያልበገረው ...

- የካፋ ህዝብ ለምኒልክ አልገብርም ብሎ ሲፋለም እኛ ለማገዝ ቀርቶ አይዞህ ለማለት አቅም አልነበረንም። ህዝቡ አለቀ - በየተራራው። ግን ሰው ሞቶ አያልቅም። አገሩ ወደመ። ጐጆ ጋየ። የካፋው ጋኪ ሻረቾ አንድ አመት ሙሉ ሳይንበረከክ ተፋለመ። ከዚያ አልቻለም። እንደ ወንጀለኛ ተዋረደ። ዛሬ የጋኪ ስም ተረስቶአል። ጋኪ ሽፍታ ነው? ራስ ብሩስ? ራስ ብሩ አርሲ ላይ ከአስራ አምስት ሺህ ጋሻ በላይ መሬት ነበረው። ዛሬ ግን ራስ ብሩ አርበኛ ... ጋኪ ሽፍታ ... እኛ ደሞ አሽከሮች ...

«ምን ሆንክ አንተ!?» ብላ አምባረቀችበት።

ከእንቅልፉ እንደነቃ ሰው ባነነ። አቅፎ ይስማት ጀመር።

«ምን ነበር የምታስበው?» አለች በመከፋት።

«ይቅርታ ዘኒ የኔ ቆንጆ ...»

«አትመችም እኮ አኖሌ» አለችው።

«እንደ አቃቂ ፍራሽ» ብሎ ቀለደ።

«እንዙር እንውጣ» ብላ ተስፈንጥራ ተነሳች።

በዚህ ፍጥነትዋ ዳግም የዋቆ አባዱላን ዲስኩር እንደማያጠነጥን አመነ። ተመቸችው። በተለይ ቅብጠትዋ። በጣም ትቀብጣለች። ጊዜ አትሰጥም። ፈጣን ናት - ሁሉም ያለማቋረጥ ታወራለች። በዚች ነገር ላይ። ይዛ የምትለቀው ርእስ ማለቂያ የለውም። አጭር ጊዜ ውስጥ ሶስት ጊዜ ትመቻለህ፤ አራት ጊዜ ደግሞ አትመችም ብላዋለች። ስሙን እንዲለውጥ ደግሞ ከአምስት ጊዜ በላይ ያሳሰበችው ሲሆን፤ ኦሮሞ እንደማይመስልም ነግራዋለች። ያንጊዜ ግን በጣም ስለገረመው አጥብቆ ጠየቃት፤

'ኦሮሞ ምናይነት ነው ዘኒ?' አላት።

'ስልህ እንጃ - ታምራለህ ለማለት ነው'

'ኦሮሞ አያምርም እንዴ?'

'እንደሱ ማለቴ ሳይሆን ...' ብላ ማብራራት ስላቃታት ድንገት ግልፍ አለች '... ለምን ትነተርከኛለህ? አፌን በፕላስተር ለጥፈዋ! ነዝናዛ ነህ እንዴ አኖሌ?'

ስቆ ተዋት። ዜኒት እንዲያ ናት።

«ወዴት ነን ታዲያ?» አላት መኪና ስታስነሳ።

«ልጋብዝህ! የናዝሬትን ብብቶች አሳይሃለሁ!»

«ጃኬት ልልበሳ» አለ።

ተያይዘው አዳማ ራስ ሲደርሱ እንግዳ ተቀባይዋ ሁለት ማስታወሻዎችን ሰጠችው። የመጀመሪያውን ገለጠው። ጂብሪል ነበር የተወለት። ከአንድ ሰአት በሁዋላ እንደሚመለስ መልእክት ትቶአል። ሁለተኛውን በችኮላ ገለጠው። ሳያነብ አይኑን ወደታች ወረወረ። ሳሙኤል ወልደአብ ይላል። ሁለቱም በመምጣታቸው በጣም ተገረመ።





«ማናቸው?» አለች ዜኒት በጉጉት።

«ይሄኛው የደህንነት ሹም ነው። አለቃዬ ነው። ይሄ ደግሞ ሳሙኤል ይባላል፤ ነጋዴ ጉዋኛዬ ነው» ካለ በሁዋላ «... ሳሙኤል እዚህ መሆኔን በምን አወቀ?» ሲል ራሱን ጠየቀ።

«ትዳር አለው?» ስትል ጠየቀችው።

«ማንኛው?»

«የደህንነቱ ሹም።»

አይኖችዋ ላይ የብልጠት ጨረሮች ሲፈነጣጠቁ አየ።

«የለውም፤ ምነው?»

«ምንም።»

ሳቀ። ሲስቅባት አፈረች።

«ቁርጬ ድመት መሰልኩህ እንዴ አሌክስ? ...»

«ጣፋጭ ነሽ» አላትና «በፈጠረሽ አሌክስ አትበይኝ» ሲል ተማፀናት።

«ለምን?»

«ይኰስኩሰኛል።»

«ሲቆላመጥ ነው እኮ»

«አኖሌና አሌክስን ምን አገናኘው?»

«ወይም ስምህን ለውጠዋ! ሀረግዬ ትሙት ... ካንተ በፊት ስምህን አውቄ ቢሆን ኖሮ አጠገብህም አልደርስ ነበር። ቀፋፊ!»

ጂብሪልንና ሳሙኤልን ለመጠበቅ ከመዋኛው ዳር ተቀምጠው መጠጥ አዘዙ። ሁለቱም ደስተኛ ሆነዋል። ግንኙነታቸው ጊዜያዊ ስሜትን ከማርካት እንደማያልፍ ግን አሳምረው ያውቁታል።

*   *   *

የአልማዝ ቤት እንደወትሮው ሞቅአል ...

አንዲት ሴት ያደቡ ሶስት ጐረምሶች ሲገቡ ዳንስ መድረኩ ላይ የሚወዛወዙትን ኮረዶች ጠጪው በመስገብገብ እያያቸው ነበር። የኮረዶቹ እድሜ ከሃያ አይበልጥም። አጐጠጐጤ ጡቶቻቸው፤ ከንፈሮቻቸው፤ በጫት የፈጠጡ አይኖቻቸው፤ ውዝዋዜያቸው ትንንገርታዊ ነው። አኖሌ ለአፍታ ገረመማቸው። እንደወትሮው

አልቁዋመጠም:: በመሰላቸት ፊቱን መለስ አድርጐ አለፈ::

ጥግ ላይ ቦታ ያዙ:: የሬጌ ሙዚቃ ጠባብዋ ጭፈራ ቤት ውስጥ ይጐርፋል:: አራቱም መጠጥ አዘው የባጥ የቆጡን ሲቀባጥሩ! አኖሌም ስለከረመበት ለጂብሪል ሲያወራ እንደቆዩ ዜኒት ሳሙኤልን ገንጠል አደረገችው::

ጂብሪል የአኖሌን ትከሻ ቸብ አደረገውና፣

«ለማንኛውም አመፁ መቆሙ ትልቅ ድል ነው:: እዚያ አደረግሁ ስላልከው ዲስኩር ብዙ አትስጋ:: በስላ ሙያ ውስጥ አሁን አንተ የተጠቀምክበት ዘዴ እንደ አማራጭ ተቀምጦአል:: በርግጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅና በርእሰ ብሄር ውሳኔ የሚፈፀም ስልት ነው:: ሆኖም የሰሜን ውጥረት አስጨንቆ በያዘን በዚህ ወቅት ስለቡርቃ ገበሬዎች እምብዛም አያሳስበንም» ብሎ ዊስኪውን ተጐነጨ::

አያያዘናም ቀጠለ፣

«በነገራችን ላይ ለአስቸኩዋይ የስራ ጉዳይ ወደ አስመራ እንድትጉዋዝ ተወስኖአል:: በጣም ይገርማል አኖሌ፤ ሚኒስትሩ ባንተ ላይ ያላቸው እምነት እያደገ መጥቶአል:: ይህ ላንተ ክብር ነው:: የሚደንቀው ደግሞ ወደ አስመራ ከመሄድህ በፊት ጉዋድ ፕሬዚዳንት ራሳቸው ሊያነጋግሩህና መመሪያ ሊሰጡህ ይፈልጋሉ::»

አኖሌ በመገረም ነበር የሚያደምጠው:: በቅርቡ በተቃዋሚ ሀይሎች ላይ የስነልቦና ጦርነት ለማካሄድ ሰፊ ዘመቻ እንደሚጀመር ጭምጭምታውን ሰምቶአል:: ከሙያው አንፃር በጥናቱ ላይ ተካፋይ እንደሚሆንም ገምቶአል:: በፕሬዚዳንቱ ደረጃ በጥብቅ የሚታይ ስራ ነው ብሎ ግን አልገመተም ነበር:: ጂብሪል ቀጠለ፣

«ታላቅ እድል ነው የገጠመህ:: እኔ እንኩዋ ፕሬዚዳንቱን አነጋግሬያቸው አላውቅም:: ሚኒስትሩ ያስጠነቀቁኝ ነገር ግን አለ:: ምናልባት 'የፓርቲ አባል ለምን አልሆንክም?! የሚል ጥያቄ ሊያነሱልህ ይችላሉ:: ማመልከትህንና እስካሁን ግን ምላሽ እንዳልተሰጠህ ነው መናገር ያለብህ:: ሌላው 'ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያስወሰነህ ዋናው ምክንያት ምንድነው' ይሉህም ይሆናል:: ሀገርህን ለማገልገል በነበረህ ከፍተኛ ስሜት ምክንያት መመለስህን መናገር አለብህ:: እንዳትዘላብድ አደራ! ሰውየው ከተቆጡብህ አንድ ሌሊት አያሳድሩህም:: ገባህ?»

አኖሌ በተከፋፈለ ልብ እያዳመጠ ራሱን ላይ ታች ወዘወዘ:: ደቂቃዎች አለፉ:: ጭፈራው ደርቶአል:: ዜኒትና ሳሙኤል ወጋቸውን ይጠርቁ እንጂ ልባቸውና ጆሮአቸው እነጂብሪል ወሬ ላይ ነበር:: ሁለቱም በጥንቃቄ አዳምጠዋቸዋል:: ሁለቱም የየራሳቸው ፍላጐት አላቸው::





«ይልቁን አንድ ወሬ ልንገርህ» አለ ጂብሪል ድንገት ትዝ ብሎት::

«ምን?»

«ስለ ሀወኒ ...»

ድንግጥ አለ:: ጆሮዎቹ ቆሙ:: ፈራ:: እያመነታም፣

«በህይወት አለች?» ሲል ተነፈሰ::

«አይታወቅም! ሆኖም ጐንደር ለአንድ አመት ታስራ ነበር::»

«ምን አጥፍታ?»

«በጣም አሳፋሪ ምክንያት ነው» ብሎ ጢሙን ያሻሸ ጀመር::

«ፖለቲካ መሆን አለበት::» አለ የቀድሞ ስሜትዋን እያስታወሰ::

«መሆኑ ነው:: ግን በቂ ምክንያት አልነበረም:: የምታስተምርበት ትምህርት ቤት ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን አሰርቶ ሲያስመርቅ የከተማውን ከንቲባ መርቆ እንዲከፍት በእንግድነት ይጠራዋል:: ሀወኒ አበባ የምታበረክት ህፃን ልጅ እንድታዘጋጅ ይነገራታል:: መርጣ ታቀርባለች:: የአቀረበቻት ልጅ የአንድ የወላይታ ብሄረሰብ አባል የሆነ መምህር ልጅ ነበረች:: የልጅቱ የቆዳ ቀለም ከኛ ከሰሜነኞች ጠቆር ሲል እንደሚችል መቸም ትገምታለህ:: ይሄ በሲቀመንበሩ እንደመቀለድ ተቆጠረባት::»

«በዚህ ምክንያት አንድ አመት እስር?»

«ስህተት ነው» አለ ጂብሪል:: «ግን መገደልም ሊኖር ይችል እንደነበር ማሰብ ይገባል::»

ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ቆዩ::

«ከዚያስ የት ደረሰች?»

«አልታወቀም:: ከተፈታች ከሃያ ቀን በሁዋላ ከአካባቢው ተሰወረች:: ወደ ሱዳን ወጥታለች የሚል ጭምጭምታ አለ::»

አኖሌ አስተያየት ከመስጠት ተቆጠበ:: በዝምታም ቢራውን ይገለብጥ ጀመር:: ጂብሪል በአኖሌ ሁኔታ አልተደሰተም፣

«ምን ተሰማህ?» ሲል ጠየቀው::

«ምንም!» ብሎ ትከሻውን በግዴለሽነት ሰበቀ::

ሲያብል ነበር:: አጥንቱ ድረስ የዘለቀ የመሰቃየት ስሜት መዝምዞታል:: ልቡ እሪታውን እያቀለጠው ነው:: ግን የልቡን

እሪታ ማንም ሊያዳምጥ አይቻለውም።

አኖሌ ሲጋራውን በዝግታ እየሳበ 'ያውም ያርሲን ልብ?' ይል ነበር - ለራሱ። የትኛው ሳይካትሪስት ነው የአርሲን ልብ ማወቅ የሚችል? መልሰም ለራሱ ይህን አከለበት '... ግን ስማኝ አንተ ሰላይ ድመት! እኛ አሮሞዎች ልቦቻችንን የዘጋነው ሸርና ተንኮላችሁ ድመት! እኛ ታክቶን ነው። ታሪካችንን መለስ ብለህ ማየትም ትችላለህ። አብሮ መኖር ባህላችን ነው፣ ተካፍሎ መብላት ልማዳችን ነው። ይህ ባህላችን ግን እንደ ቂላቂልነት ተቆጠረብን።'

«ይቺ ልጅ እንዴት ናት?» አለው ጂብሪል ዘወር እያለች በማያባብል አይንዋ ወደ ምትማትረው ዜኒት እያስተዋለ።

«ጥሩ ናት» ብሎ ፈገግ አለ።

«አነበብካት እንዴ?»

«በጣም!»

«ታሪክዋ ጥሩ ነው?»

«እንደ ኦ ሄንሪ ስራዎች!»

«ያንተ ያለህ!» አለ በቅናት።

«ለምን አታስደንሳትም። በአይንዋ ገሽልጣ ልትገድልህ ነውኮ»

ጂብሪል ሳያመነታ ብድግ ብሎ እጁን ወደ ዜኒት ዘረጋ። ፊትዋ በፈገግታ እንደተዋጠ ተስፈንጥራ ተነሳች። ወደ ዳንሱ ባህር ዘለቁ። ሳሙኤል ወደ አኖሌ መለስ አለና፣

«እሺ ወዳጄ ... ወደ አስመራ ልትጉዋዝ ነዋ!» አለው እንደዋዛ።

«ማን ነገረህ?» አለው እጅግ ደንግጦ።

«የሌሊት ወፍ!» ብሎ ሳቀበት።

አኖሌ በቡርቃ የገጠሙትን ሁኔታዎች ይተርክለት ጀመር። ስለ አባቱ አሙዋሙዋት፣ ስለቡርቃ ዝምታ ትንቢት፣ ስላይ ሾፌር እንደመተደበበት፣ ድምፁን ቀድቶ አስር ሺህ ብር እንደጠየቀው፣ 'መከላከያ ሚኒስትሩን ሰድበሀል' ብሎ ስለሻለቃ ጉተማ ድንፋታ፣ ቡራ ከረዩ እንዳለ፣ ከጀርመን መመለሱ እንደቆጨው አጠር አጠር አድርጎ አጫወተው። የአስመራ ጉዞውን አስመልክቶም ደስተኛ አለመሆኑን፣ ለሙያው እያሉ የማይፈልጋቸውን ስራዎች እየጫኑበት እንደሆነ አወጋው። ሳሙኤል ራሱን ላይ ታች እየወዘወዘ በጥንቃቄ አዳመጠው...





- 3 -

ሀወኒ በጉዞ ላይ ናት...

አሁን ታጋይ ሆናለች - የኢህአዴግ ተጋዳሊት። ባለአላማ ሆናለች። ህዝባዊው አላማ ሞቆአታል። የደስታ እንባና ሳቅ ይፈራረቅባታል። እያንጎራጎረች ትጉዋዛለች። ጉዞው ተስማምቶአታል። ቸኩላለች - ሀየሎም ዘንድ ለመድረስ። በምትፈልገው ሙያ መመደብዋ አስደስቶአታል። የታሪክ ቀረፃና የዜና ወኪል ሆና ነበር ሀየሎም ወደሚመራው ክፍለ ሰራዊት የተላከችው። የተሳፈረችበት ስቴሽን ዋገን የአላማጣን ተራራ ሽቅብ መቡዋጠጥ ሲጀምር ሀወኒ የካርል ማርክስን አንድ ግጥም ለማስታወስ እየጣረች ነበር። የአራተኛ አመት የዩንቨርስቲ ተማሪ ሳለች ነበር አንድ ያበደ ማርክሲስት በቃሉ ሲዘምረው ያዳመጠችው። ነገረኝ ብላው ቃል በቃል በወረቀት ገልብጣ አጥንታው ነበር - በወቅቱ።

ጥቂት ስንኞች ታወሱዋት፣ ካርል ማርክስ፣

*... ከባድና ረጅም በሆነው ጉዳና*

*እንጉዋዝ በርቀት አብረን እንሁንና*

*ያለመሪ ኩከብ ያለ ጥልቅ አላማ*

*በደስታ መኖር መች ይጠቅመንና ...*

ወደ አውደ - ውጊያ መጉዋዝዋ ፍርሀት አላሳደረባትም። ከአይሮፕላን ድብደባው ወዲህ ሞትን የመድፈር ወኔ ሰንቃለች። ያለአላማ መኖርን ደግሞ ንቃዋለች። በደርግ ላይ ያሳደረችው የጥላቻ ስሜት እንደብረት አጠነከራት። ሽዊትና እንያን እንቦቃቅላ ህፃናት ኩቶ ልትረሳቸው አቃታት። ባሰበቻቸው ቁጥር የሰራ አካላትዋ ይንቀጠቀጣል።

ሌሎች ስንኞችን አስታወሰች - ካርል ማርክስ፣

*... ለትልቁ አላማ ለሰው መልካም እድል*

*ሀይወቱ ትምላ ትሁን የትግል ድል*

*ሰው ያደነቀውን መልካም ነገር ሁሉ*

*አትደብቂኝ ጥበብ ንገሪኝ በሙሉ ...*

ታሪክ ፀሀፊነትዋ ነፍስ ሊዘራ የሚችለው አላማ ካላት ብቻ መሆኑም እየተሰማት መጥቶአል። ግብ የሌለው ፀሀፊ መቅዘፊያ ከሌላት ጀልባ ተለይቶ ሊታይ እንደማይችል መረዳት ጀምራለች። ለመፃፍ ስሜት ያስፈልጋል። ስሜት የሌለው ፀሀፊ ምን ሊተርክ

ይችላል? ራሱን ከአንድ አላማ ጋር ሳያዋህድ ብእሩን ከወረቀት የሚያገናኝ ፀሀፊ ቃለንባኤ ያኘና እንጂ ከቶ እንዴት ታሪክ ፀሀፊ ለመሆን ይቻለዋል?

*የመጨረሻ ስንኞች - ካርል ማርክስ፣*

*...የተሞነጨረች በአሳረኛ ብእር*

*ቀለስተኛ ሀይወት አንፈልግም እኛ*

*ስቃይ የወረራት!*

*እንደ ሰዎች ሁሉ ፍላጐት ይሰማን*

*ንዴትና ቁጣ - ስሜትና ኩራት ...*

ለትግል እንደወሰነች ለሀየሎም ነበር የነገረችው::

በመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ አመራሩ ስብሰባውን አጠናቆ ወደየምድብ ስፍራው መበተን በጀመረባት ደቂቃ ላይ ነበር ለሀየሎም ያሳወቀችው:: ስሜቱን መቆጣጠር ሲያቅተው ተመለከተች:: በደስታ ጮሆ አቀፋት:: ስሜቱን መቆጣጠር ሲያቅተው ተመለከተች:: በደስታ ጮሆ አቀፋት:: እንዲህ አላት ከጠበቀችው በላይ ሆነባት - የሀየሎም የደስታ ስሜት:: እንዲህ አላት ታዲያ ሀየሎም፣

«... ሀወኒ ደስተኛ እንደምትሆኚ እርግጠኛ ነኝ:: ለእርሞ ወገኖችሽ በእጅጉ አስፈላጊያቸው ነሽ:: ስልጠናና ምደባሽን በተመለከተ ከክንፈ ጋር ጨርሱ:: እኔ አሁን መሄድ አለብኝ::»

«አንተ ዘንድ መመደብ ነውየምፈልገው?»

«ለክንፈ ንገሪው::»

«መልካም እንግዲህ ደህና ያገናኘን» ካለች በሁዋላ «አንድ ግጥም ልንገርህ? የሆ ግጥም! ... አንተ የምትወደው የሆቺሚን የራሱ::»

«እሺ»

*የዘመናችን ግጥም፣*

*ገጣሚዎችም ሁሉ፣*

*ተዋጊዎችም ይሁኑ፦*

በዚሁ ነበር የተለያዩት...

በርግጥም ሀየሎም ለቬትናም ታጋዮች ልዩ አክብሮትና ፍቅር ነበረው:: ብዙ ጊዜ አውግቶአታል:: በተለይ ንጌአን በተባለች መንደር ለተወለደው ሆቺሚን ልዩ ስሜት አለው:: የንጌአን ሰዎች አንንበረከክም





በማለታቸው «ንጌአን የተወለደ ማንኛውንም ነገር ይቃወማል» እየተባለ እንደሚቀልድ ያወጋት በስሜት ተውጦ ነበር:: ሆቺሚንና ጉዋዶቹ ፈረንሳዮችንና አሜሪካኖችን እንዴት ማንበርከክ እንደቻሉ ጭምር በሰፊው ተረከላት:: አግረመንገዱን ታን ስለተባለችው የሆቺሚን ታላቅ እህት ጭምር አነሳ:: ታን ለነፃነት አርበኞች ጠመንጃ በማቀበል ወንጀል ተከሳ ረጅም ጊዜ በከርቸሌ የቆየች ብርቱ ሴት ናት:: ፖሊሶቹ እንደውዳቂ እቃ እየገፈታተሩ ወደ ጉሮኖዋቸው ሲያስገቡዋት ታዲያ «ሌሎች ሴቶች ህፃናትን ይወልዳሉ:: አንቺ ግን ጠመንጃ ትወልጂያልሽ» ሲሉ ነበር ምሬታቸውን ያሰሙዋት:: ታን ከርቸሌ ውስጥ በስብሳ አልቀረችም:: በታናሽ ወንድምዋ የሚመሩት የቬትናም ታጋዮች ነፃ አጠጡዋት:: የሚደንቀው ግን የነፃ አውጪዎቹ መሪ ታናሽ ወንድምዋ መሆኑን አታውቅም ነበር:: ምክንያቱም ሆቺሚን ከዘጠኝ በላይ ስሞች ነበሩት:: መሞቱ ጭምር እያሌ ጊዜ ተነገሮ ነበር፤ እያለ ነበር ሀየሎም የሚያወጋት:: መች በዚያ አብቅቶ:: ሆቺሚን ሀምሳ ስምንት አመት የታገለ፤ ቤት ንብረት ያላፈራ፣ የመላው አለም ጭቁኖች የትግል መምህር መሆኑን አውግቶአታል:: ቃሀዉ የተባለ አንድ ገጣሚ «አጐት ሆ» በሚል መጠሪያ ለሚታወቅ መሪያቸው ድንቅ ግጥም እበርክቶለታል፤ «የቬትናም ህዝብ ለሆቺሚንና ለታጋዮቹ ልዩ ክብርና ፍቅር ነበረው:: በአረመኔዎቹ አሜሪካኖች የቦንብ በረዶ ቢወርድባቸውም አልተበገሩም:: በተለይ ደቡብ ቬትናሞች በአለም ላይ በአስከፊነቱ ወደር የሌለውን የቦምብ ድብደባ ተቋቁመውታል:: ከዚያም አሜሪካና ፈረንሳዮች ተዋርደው ከቬትናም ተባረሩ:: እኛ ይህን መሰል የአለም ጭቁን ህዝቦችን የትግል ታሪክ መሰረት አድርገን ነው የምንታገለው:: ደሞ እናሸንፋለን::»

*የመንገድ ጉዋዶችዋ ከተዋጠችበት ግለ - ሀሳብ ነቀነቁዋት፤*

«ሀወኒ ዝምታ ዋጠሽሳ!»

«አለሁ ኧረ... እናንተም እኮ ወሬ ይዛችሁ ረሳችሁኝ::»

አብረዋት የሚጉዋዙት ሶስቱም መንገደኞች የህወሀት ታጋዮች ነበሩ:: አንድዋ ሴት ታጋይ ናት:: አክሱማይት ትባላለች:: ፎቶግራፍ አንሺ ናት:: ሁለቱ ወንዶች ፍቅረ እና ሀይሌ ይባላሉ:: ሀይሌ ፊልም ቀራጭ ሲሆን ፍቅረ ደግሞ ጊታሪስት ነበር:: ወደ ፍልሚያው ጉራ እያመሩ ነበር:: ወሬ አለ - ውስጥ ውስጡን:: ታላቅ የዘመቻ ወሬ:: ዘመቻ ካለ ደግሞ ታሪክ መዝጋቢዎችም ሆኑ የሙዚቃ ሰዎች ሁሉ ወደፍልሚያው መስከ ያቀናሉ:: ሀወኒ ባጋጣሚ የቪዲዮ ካሜራ ቀራጭነት ችሎታ ስለነበራት ከእነርሱ አንድዋ መሆን ችላለች:: ያደረባትን የደስታ ስሜት ከቶ መቆዋቆዋም አልቻለችም::

መኪናቸው የአላማጣን አቀበት ወጥታ ስታበቃ፣ እንደዋዛ አንድ

ጥያቄ ጣል አደረገች፡፡

«ከመካከላችሁ ሀየሎምን ማነው በደንብ የሚያውቀው? እስኪ ከሀየሎም ጋር የተያያዘ ገጠመኞቻችሁን አውጉኝ?»

ታጋዮቹ ምላሽ ለመስጠት አልተቻኮሉም፡፡ አክሱማይት ፈገግ ብላ፣

«ሁላችንም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከሀየሎም ጋር ሰርተናል» ካለች በሁዋላ «... እኔ ወደ ባህል ክፍል ከመዘዋወሬ በፊት በጨርጨር ውጊያ አብሬው ነበርኩ፡፡» ብላ ትረካዋን ጀመረች፡፡

«... ሲቀይሩኝ ታዲያ እሪ አልኩ፡፡ ከሀየሎምጋር መስራት እጅግ ያስደስታል፡፡ በተለይ ቀልዱ...» ብላ በሞቀ ስሜት በፈገግታ ተጥለቀለቀች፡፡

ሀወኒ «ምን እያለ ይቀልዳል?» ስትል ገፋፋቻት፡፡

«መች ጥርስ ያስከድንና» ብላ ብቻዋን መሳቅ ጀመረች፡፡ «... አንድ ጊዜ ምን አደረገን መሰላችሁ፡፡ እንደምታውቁት እኔ ትዳር መፈቀዱን ከተቃወሙት ሴት ታጋዳዮች ቀንደኛዋ ነበርኩ፡፡ ጋብቻ ሲፈቀድ በትግሉ ያፈራሁዋቸው ጥንካሬዎች ቀጣይነት አይኖራቸውም፤ ወንዶች የበላይነታቸውን ሲያሳዩን ይችላሉ፤ ማርገዝና መውለድ ከመጣ ከወንዶች እኩል ዳገት መውጣትና መውረድ ሊቀር ነው፤ የሚል ስጋት ነበረኝ፡፡ ሆኖም እንደምታውቁት ትዳር አማራጭ የሌለው የማይቀር ተፈጥሮአዊ እውነት መሆኑ ሲነገር ተቀበልኩት፡፡ ቢሆንም ግን በሀሳብ ደረጃ ተቀበልኩት እንጂ እኔ ላለማግባት ወስኜ ነበር፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው» አለች አክሱማይት በፈገግታ ተውጣ «... መጋሎ አርተቦ በተባለ ቦታ ላይ ፍቅር ውስጥ ገባሁ፡፡ በወቅቱ ህዝብ የማደራጀት ስራ ላይ ተመድቦ ይሰራ የነበረ ሰው አፈቀርኩ፡፡ ማህፈረ የእብዮ ይባላል፡፡ ከሀወኒ በቀር ያው ሌሎቻችሁ ታውቁታላችሁ፡፡ ፍቅር እንዲያ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ያን ሁሉ ክርክር ባላደረግሁ ነበር» ስትል ተጉዋገሮቹ በሳቅ አውካኩ፡፡

አክሱማይት ቀጠለች፣

«... ጊዜው ደሞ ጦርነቱ በተከታታይ የሚካሄድበት ነበር፡፡

ለሀየሎም ፍቅር ውስጥ መግባቴን ቀስ ብዬ አማከርኩት፡፡ ያኔ ሀየሎም እንደሚቀልድ አላውቅም ነበር፡፡ ጀግና መሆኑን አሳምሬ አውቃለሁ፡፡ ለህዝቡ ፍቅር እንዳለው፤ ጉዋዶቹን፣ ከራሱ በላይ እንደሚወድ ሲነገር እሰማ ነበር፡፡ በርግጥም ፍቅር ውስጥ እንደገባሁ ስነግረው በቁምነገር ነበር ያናገረኝ፡፡ አበረታታኝ፡፡ 'ማህፈረም ቢሆን አንዳንድ ችግሮች አሉበት እንጂ በአላማው ፅኑ ነው፡፡ ከተጋባችሁ





ግን እንቺም ታግኚዋለሽ፡፡ ምርጫሽ መልካም ይመስለኛል' እያለ መከረኝ፡፡ እኔም በጣም ተደስቼ ተለያየን፡፡

«ከአራት ቀናት በሁዋላ መጋባታችንን አሳውቀን አንድ ቤት ማደር ጀመርን፡፡ በነጋታው ውጊያ ተጀመረ፡፡ አጋጣሚ ሆነና ደሞ ማህፈረ በውጊያ ላይ ቆሰለ፡፡ ይህ ሲሆን በጣም ደነገጥሁ፡፡ ልንሰዋ መውጣታችንን አውቃለሁ፡፡ ግን እንጃ! በጣም... በጣም አፈቅረው ስለነበር ቀድሞኝ እንዳይሰዋ ምኞት ነበረኝ፡፡»

አክሱማይት ሁለት እጆችዋን ልብዋ ላይ አሳርፋ፣

«አሁንም ቢሆን እንደዚያ ነው የማስበው፡፡ እንዋደዳለን፡፡ ቀድሞኝ እንዲሰዋ አልሻም፡፡ በጭራሽ! ልጅም ወልደናል፡፡ ፀሀዬ ብለነዋል ስሙን» ካለች በሁዋላ ወደ ትረካዋ ዘለቀች፡፡

«... ማህፈረ መቁሰሉን ሳውቅ ራሴን ልስት ምንም አልቀረኝም፡፡ ከተኛበት የህክምና ጣቢያ ራስጌው ላይ ሆኜ እንባዬን አንቀዋቀዋቅሁት፡፡ እያለቀስኩ ጠጉሩን ሳሻሽው ሀየሎም ድንገት መጣ፡፡ እንባዬን ቶሎ ጠራረግሁ፡፡ ማልቀሴ ፅናት የሌለኝ ያስመሰልብኛል ብዬ ፈራሁ፡፡ ሀየሎም ትክ ብሎ ሲያየኝ ቆየና፣

'ማህፈረ ጥይት የሚመታው ታጋይ አልነበረም፡፡ ከተጋባችሁ ሀያ አራት ሰአት እንኩዋ ሳይሞላ እንዴት ሊቆስል ቻለ?' አለና ከረር መረር አድርጎ ጠየቀኝ፡፡

ደነገጥሁ፡፡ ምን እንደምለው እንኩዋ ግራ ገብቶኝ ድንኩዋኑ ውስጥ ተኝተው ወደነበሩት ቁስለኞች ዘወር ስል ሁሉም ፊታቸውን እያዞሩ በብርድ ልብሳቸው ሲሸፋፈኑ ተምታታብኝ፡፡ ትልቅ ጥፋት ፈፅሜ ይሆን? ብዬ መልሼ ደግሞ ወደማህፈረ ስዞር እሱም በክሹፋ ፊቱን ሸፈነ፡፡ ሁሉም በኔ ላይ መጥፎ አመለካከት ያሳደሩ መስሎ ተሰማኝና ዝም ብዬ ብቻ ሀየሎም ላይ አፈጠጥኩ፤ ሀየሎም ከኔ መልስ ሲያጣ፣

'ማታ ምን አድርገሽው ነበር?' ብሎ መልሶ ጠየቀኝ፡፡

እንዲህ ሲለኝ ሰውነቴ የተተረተረ ያህል ተሰማኝ፡፡

'ኧረ ምንም አላደረግሁት!' ብዬ ጮህኩ፡፡

በውስጤ ግን ስንቱን እያሰብኩ ነበር መሰላችሁ፡፡

'ተሳስማችሁ ነበር?' ሲል መልሶ ጠየቀኝ፡፡

ትንፋሼ ቁርጥ አለ፡፡

'አዎ' እንዳልል አፈርኩ፡፡ 'አይ' እንዳልል ፈፅመነዋል፡፡ ደሞ

መሳሳም ምን ነውር አለው?

'አንተ ሀየሎም ለምን እንደሱ ትለኛለህ?' ብዬ አይኔን የማሳርፍበት ሳጣ፣

'ነገ በዚሁ ጉዳይ ላይ ውይይት እናደርጋለን' ብሎኝ ወጣ።

እኔ ግራ ተጋብቼ፤ አይኔ ፈጦ ወደማህፈሬ ጠጋ ስል ቁስለኞቹ ታጋዮች በሙሉ የተሸፈኑበትን ብርድ ልብስ እየገለጡ በሳቅ ይጮሁ ጀመር። አይናቸው እንባ ሞልቶ ሳቃቸውን እንኳዋ ማቆም አልቻሉም።

እኔ ግን እውነት ስለመሰለኝ፣

'ከተጋባን ወዲያ 'ስመሽዋል ወይ? ብሎ እንዴት ይጠይቀኛል?' ብዬ አንጀ ማህፈሬን መልሼ ደሞ ታጋዮችን እያየሁ ብጠይቅ፤ እነሱ ተጨማሪ ቀልድ አገኙና በኔ ላይ አመሹብኝ። መቀለጃ አገኙ። ሀየሎም ሲቀልድ መሆኑን ያመንኩት ግን በነጋታው ነበር። ቁርስ ስንመገብ ጮክ ብሎ ለታጋዮቹ ሁሉ ስለኔ እየተናገረ ቁርስ ሰአት በሙሉ በኔ ጉዳይ እየተሳቀ አለፈ። ርጉም ነውኮ!»

ጊታሪስቱ ፍቅረ ደግሞ ትዝታውን እንዲህ ሲል ያወጋ ጀመር፣

«...ሁላችሁም እንደምታውቁት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በድርጅታችን ውስጥ ሲጋራ ማጨስ የተከለከለ ነበር። ታዲያ ደርግ በቀይ ኮከብ ዘመቻ ሻእቢያን ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ቆርጦ የተነሳ ጊዜ ሻእቢያን ለማገዝ ከተጉዋዘው የህወሀት የታጋዮች ሀይል ጋር እኔም አብሬ ተጉዤ ነበር። ኤርትራ ከሻእቢያ ታጋዮች ጋር ሳለን ታዲያ እዚያ ሲጋራ ማጨስ ክልክል ስላልነበር እኔም ብርዱን ለመከላከል ለመድኩትና ከኤርትራ ታጋዮች ጋር ተቀላቅዬ ሳቦነው ከረምኩ። ያው ሁላችሁም እንደምታውቁት ደርግ ናቅፋን መቆጣጠር አቅቶት በክልሾ ተጠልዛ፤ አናትዋን ተኮርኩማ ወደ 'መጣችበት ከተመለሰች በሁዋላ እኛም ግዳጃችንን በተገቢው መንገድ ፈፅመን መልስ ወደ ትግራይ ሆነ። እኔ ታዲያ ከነሲጋራ ልምዴ ነበር የተመለስኩት። እየተደበቅሁ ማጨስ ጀመርኩ። መሳቀቁ ግን ገደለኝ። ማጨስ አይበለው መቼም። እንዲሁ ስነባብቼ ከእለታት አንድ ቀን ተሀድሶ አልቀረልኝም ተያዝኩ። ምእራብ ትግራይ ሳለን ይመስለኛል። እኔ በአካባቢው ነበር። ታጋዩ ሁሉ ይጨፍራል። ጉዋይላው ቀልጦአል። እኔ በአካባቢው አልነበርኩም። በመካከሉ ላይ ነበር የመጣሁት። ገና ብቅ ስል ሀየሎም ጠራኝና 'ክራር ተጫወት' ይለኛል። 'እሺ' ብዬ የክራር መምቻ ለማውጣት እጄን ወደ ኪሴ ሰደድኩ። ምን ዋጋ አለው! ጣቶቼ ክራር መምቺያውን ያገኙ መስሎአቸው ሲጋራ አንጠልጥለው ወጡ። አልደብቀው ነገር ፊት ለፊት ሆነብኝ። ሲጋራዋ ጣቴ ላይ እንዳለች የማደርገው ጠፋኝ። ታጋዮቹ ሁሉ ደንግጠው ርስበርስ ይተያዩ ያዙ።





ይህን ጊዜ ሀየሎም ፈገግ አለና፣ በተሰባበረ አማርኛ «ጉርጉዋሪ አሳ ... ያወጣል ዘንዶ!» ሲል ተረተ።

ታጋዮች በሙሉ በሳቅ ጮሁ። ውጥረቱ ቀለለ። ጉዳዩ ቀልድ ሆኖ በቀልድ ታለፈ»

ፍቅረ ይህን ብሎ ወደኪሱ ጣቱን ሰዶ ሲጋር አውጥቶ ከለኮሰ በሁዋላ «እኔ ሀየሎም ታላቅ ወንድሜ ነው የሚመስለኝ» ሲል አከለ። ድምፁ በኩራት የተሞላ ነበር።

ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ እንደተጉዋዙ፣ አክሱማይት፣

«ሀይሌ መቼም ከሀየሎም ጋር የተያያዘ ብዙ ገጠመኞች ይኖሩሀል።» አለች።

ሀይሌ ፈገግ አለ።

«የሀየሎምማ የቱ ተነስቶ የቱ ይተዋል?» ብሎ በሀሳብ ጭልጥ አለ። እያየዘም እንዲህ አለ፣

«እኔ ከሀየሎም ባህርያት ከቀልዶቹም፣ ከጀግንነቱም በላይ ሩህሩህነቱ ነው ቀድሞ የሚታሰበኝ» ሲል ጀመረ። ከአያሌ ገጠመኙ አንዱንም እንዲህ እያለ ያወጋ ጀመር፣

«...ጊዜው 1971 ይመስለኛል። የየካቲት አስራ አንድ ዋዜማ። ህወሀት የተመሰረተበትን እለት ድብድቦ ከተማ ላይ ለማክበር የድርጅቱ አመራር ይወስናል።»

ይህን ብሎ ወደ ሀወኒ ዞሮ እየተመለከተ «... ድብድቦ በአድዋና በእንትጮ መካከል የምትገኝ ትንሽ መንደር ናት።»ካላት በሁዋላ ትረካውን ቀጠለ «... ይህቺን ከተማ ለመቆጣጠር በሀየሎም የሚመሩ ሶስት ሀይሎች በተለያየ አቅጣጫ ማጥቃት በእንዲፈፅሙ ተወሰነ። ጥናቱም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ።

እኔ የነበርኩባትን ሀይል የሚመራው ነጋሽ ሽሪፎ ነበር። በነጋሽ መሪነት የኛ ሀይል ከአዲአርባእተ ተነስታ ወደ ድብድቦ ድንበር ጉዞ ጀመረች። ተሲያት አካባቢ ነበር ጊዜው። ጉዞአችን በወኔ የተሞላ ነበር። መሪያችን ነጋሽም ቢሆን በጣም የሚወደድና ሁላችንም የምናከብረው ታጋይ ነበር። አስታውሳለሁ፤ እየዘፈንን ነበር የምንጉዋዘው፤ ከነጋሽ ጋር መሆን መቼም ልዩ ብርታት ይሰጣል። 'ትግራይ አደይ! እለንልሽ እኛ ልጆችሽ!' እያልን ስናዜም ጥንካሬ ይሰማን ነበር። በዚህ መልኩ ማጥቃት ከምንፈፅምበት ቦታ ደረስን።

ድብድቦን ለመቆጣጠር ከመንደሪትዋ ግርጌ ከፍተኛ ኮረብታ ይዞ የተቀመጠውን የደርግ ጦር መደምሰስ ነበረብን። እየተጉዋዝን

ሳለ ግን ሸጥ አጋጠመን:: የውጊያ እቅዱ ሲነደፍ ስለዚያ ሸጥ የተነሳ ነገር ስላልነበር ነጋሽ ግራ ተጋባ:: ሸጡ ኩረብታ ላይ ላለው የደርግ ጦር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር፤ እኛን ደግሞ አጋልጦ የሚሰጥ ሆኖ ተገኘ:: ያንን ሸጥ ተሻግሮ የደርግ ሀይል ላይ ጥቃት መክፈት ጨርሶ የሚሞከር አልነበረም:: ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ግን ነጋሽ ሸሪፎ 'ሸጡን ተሻግረን ግዳጃችንን መፈፀም አለብን' ሲል አሳወቀን:: ነጋሽ ይህን ካለ በሁዋላ የውጊያ አሰላለፋችን አሳውቆን ማጥቃቱን እንድንከፍት አዘዘ፤ ራሱ ነጋሽም ግንባር ቀደም ነበር::

'ህጁም! ህጁም!' ብሎ ፊት ለፊት እየመራ ተኩስ ከፈተ:: ምሽግ ተከተልነው:: ነጋሽ እየመራን ገባ:: ኩረብታው እናት ላይ ምሽግ የያዙት የደርግ ወታደሮች ግን ከኛ ጋር መፋለም አልከበዳቸውም:: ጭርሱኑ ይቀልዱብን ጀመር:: ከላይ እኛን ቁልቁል እያዩ እያውካኩ ይሳደቡና ያላግጡብን ያዙ:: ተኩስ አዘነሙብን:: ቦንቦቻቸውን እየነቀሉ ወረወሩብን:: እኛ አፀፋውን መመለስ ቀርቶ ራሳችንን መከላከል እንኳዋ አልቻልንም:: ውጊያው በተጀመረ በአስር ደቂቃ ውስጥ ነጋሽ ሸሪፎ ግንባሩ ላይ ተመቶ ተሰዋ:: መች ነጋሽ ብቻ ሆኖ:: አስቴር ፀሀዬም ተሰዋች:: አስቴር ፀሀዬ ጨርሳ አትረሳኝም:: ቀይ ቆንጆ ነበረች:: የተማረች ወጣት ሴት ናት:: ወደ ትግል ሜዳ ከመውጣትዋ በፊት መምህር ነበረች:: ምንም እንኳዋን ከጥሩ ኑሮ ላይ ወደ ትግል የመጣች ብትሆንም ጀግናና ጠንካራ ታጋይ ነበረች:: ሌላው ቀርቶ እንደሌሎች የህወሀት ሴት ታጋዮች፤ ሞዴስ የመሳሰሉ ነገሮችን የምትይዝበት ሻንጣ እንኳዋ አልነበራትም:: አስቴር ልዩ ፍጡር ነበረች:: ታዲያ በዚያ ውጊያ እንደነጋሽ በግንባር ቀደምትነት ስትፋለም በቦምብ ደረትዋ ላይ ተመትታ ተሰዋች:: አባቡ የሚባል ታጋይም ነበር:: ከአድዋ ወጣ ብላ በምትገኝ አዲ አቡን በምትባል ቦታ የተወለደ ወጣት ጀግና ነው:: በቦምብ ሲመታ ሁለት እግሩ ተገነጣጥሎ ተለያይቶ ተሰዋ:: ወዲ ማዘር የምንለው ጠንካራ ታጋይም ነበር:: እሱም ተሰዋ::

ግማሽ ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለትግሉ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ጀግኖችን አጣን:: የደርግ ወታደሮች ይህን ሁሉ የሚፈፅሙት ያለ ችግር ነበር:: ከዚያ አፈገፈግን:: አልቻልንም::

የነጋሽ ሬድዮ ወድቃ ትጮሀለች:: የነጋሽን የአመራር ቦታ አብርሀ መጅሙእ የተባለ ጋንታ መሪ ተካው:: ሬድዮንዋን አንስቶ ከሀየሎም ጋር ግንኙነት ፈጠረ:: አብርሀ የነጋሽን መሰዋት ለሀየሎም ገለፀለት:: የአስቴርን ጭምር የነገረው ይመስለኛል::

'ለምን አልፈፀማችሁትም' እያለ ከወዲያ በኩል ሀየሎም ይናገራል:: የመሬት አቀማመጡ መጥፎ መሆኑንና ማጥቃት መፈፀም ጨርሶ እንደማይቻል አብርሀ መጅሙእ ለሀየሎም በሬድዮ





ገለፀለት:: ይህን ጊዜ ሀየሎም 'እሁኑኑ ራሴ እመጣለሁ' ብሎ የሬድ
ግንኙነቱን አቋረጠ::

እኛም እዚያው ሸጥ ውስጥ አስቴር ፀሀዬን ቀበርናት:: ከተሰው
ላይ መሳሪያ መሰብሰብም ጀመርን:: የነጋሽን አስከሬን ማምጣት ግ
የማይቻል ሆነ:: ከየተደበቅንበት ብቅ ስንል ኩረብታው ላይ በም
ሁኔታ ላይ የሚገኙት የደርግ ወታደሮች እያውካኩና አፀያፊ የብልግ
ስድብ እየተሳደቡ የጥይት በረዶ ያዘንሙብናል::

«ሁኔታው ሁሉ ወለል ብሎ ይታየኛል... የተሰው ታጋዮቻችን
ጠመንጃዎች ሁሉ ሰበሰብን:: በቦምብ ሰውነቱ የተበጣጠሰውን የአባቡ
ጠመንጃ ለማምጣት ግን ጨርሶ ሳንችል ቀረን:: የነጋሽን አስከሬ
ማግኘትና የአባቡን ጠመንጃ ማንሳት የማይሞከር ሆነ:: ወታደሮ
ጠመንጃዋን እንዳናነሳ ነቅተው ይከታተሉን ነበር:: ደፍሮ ማ
ያንሳት - ጠመንጃዋን:: በመካከላችን ገብረሚካኤል የሚባል እንደ
ታጋይ ነበር:: ሳናስበው ድንገት ብድግ ብሎ ወደ ጠመንጃዋ ተፈተለከ
ትንፋሻችንን ውጠን እንመለከተው ጀመር:: የደርግ ወታደሮች የጥይ
እሩምታ ያዘንሙበት ጀመር:: ገሬ አጉንበሶ በረረ:: ጠመንጃዋ አጠገ
እንደደረሰ ከመቅፅበት አንስቶአት ዚግዛግ እየሰራ ይበር ጀመር
ከአሁን አሁን ተመትቶ ወደቀ ብለን አይናችን ፈጦ፤ ትንፋሻች
ቆሞ ነበር:: ሳይመታ አመለጠ:: ከፍተኛ ደስታና መጨዋጨዋ
ተፈጠረ:: ገሬ ይህን የጀግንነት ተግባር ለምን እንደፈፀመ ግን ግል
ነበር::

ከዚህ ውጊያ ቀደም ሲል በፈሪነት ተገምግሞ ነበር:: ገ
በግምገማው የተነሳውን ነጥብ 'አልቀበልም' ብሎ ተሙዋገተ:: የጋንታ
ታጋዮች ግን 'ገብረሚካኤል ፍርሃት አለበት' ብለው በአንድ ድም
በማፅደቅ ወደ ባዶ ስድስት (ማረሚያ ቤት) እንዲላክ ወሰኑ:: ይህ
ውሳኔ ታዲያ ሀየሎም ሻረው:: 'ገብረሚካኤል በርግጥ ፈሪ ከሆ
በሚቀጥሉት ውጊያዎች እናየዋለን' ብሎ ነበር የጋንታዋን ውሳ
የሻረው:: ከዚያ ወዲያ ታዲያ ገሬ በተለያዩ ውጊያዎች ጀግንነ
በግልፅ ይታይ ጀመር:: በዚህ ቀንም ሁላችንም ለመፈፀም
ያልደፈርነውን ተግባራዊ በማድረግ ግምገማው ስህተት እንደነበ
አረጋገጠልን::

«በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን ሀየሎም ሸጉጥ ብቻ ታጥቆ ካለንበ
ደረሰ:: መሽቶ ነበር:: ብቻውን ነበር የመጣው:: እንደደረሰ ወዲ
ምእራፍ ከሚባል ማንጁስ ላይ ሲሞኖቭ ጠመንጃ ተቀብሎ እኛ
ከሰበሰበ በሁዋላ እየመራን ነጋሽ ማጥቃት በሞከረበት መንገድ ተኩ
ከፈተ::

ኩረብታው ላይ ያሉት ወታደሮች እንደገና ጥይት ማዝነብና

ላለ ግን ሽጥ አጋጠመን:: የውጊያ እቅዱ ሲነደፍ ስለዚያ ሽጥ የተነሳ ነገር ስላልነበር ነጋሽ ግራ ተጋባ:: ሽጡ ኮረብታ ላይ ላለው የደርግ ጦር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር፤ እኛን ደግሞ አጋልጦ የሚሰጥ ሆኖ ተገኘ:: ያንን ሽጥ ተሻግሮ የደርግ ሀይል ላይ ጥቃት መክፈት ጨርሶ የሚሞከር አልነበረም:: ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ግን ነጋሽ ሽሬፎ 'ሽጡን ተሻግረን ግዳጃችንን መፈፀም አለብን' ሲል አሳወቀን:: ነጋሽ ይህን ካለ በሁዋላ የውጊያ አሰላለፉን አሳውቆን ማጥቃቱን እንድንከፍት አዘዘ፤ ራሱ ነጋሽም ግንባር ቀደም ነበር::

'ህጁም! ህጁም!' ብሎ ፊት ለፊት እየመራ ተኩስ ከፈተ:: ተከተልነው:: ነጋሽ እየመራን ገባ:: ኮረብታው እናት ላይ ምሽግ የያዙት የደርግ ወታደሮች ግን ከኛ ጋር መፋለም አልከበዳቸውም:: ከላይ እኛን ቁልቁል እያዩ እያውካኩ ጭርሱኑ ይቀልዱብን ጀመር:: ቦንቦቻቸውን እየነቀሉ ይሰደቡና ያላግጡብን ያዙ:: ተኩስ አዘነሙብን:: ራሳችንን መከላከል ቀርቶ እኛ አፀፋውን መመለስ ወረወሩብን:: ውጊያው በተጀመረ በአስር ደቂቃ ውስጥ እንኳ አልቻልነም:: መች ነጋሽ ብቻ ሆኖ:: ነጋሽ ሽሬፎ ግንባሩ ላይ ተመቶ ተሰዋ:: ቀይ አስቴር ፀሀዬም ተሰዋች:: አስቴር ፀሀዬ ጨርሳ አትረሳኝም:: ወደ ትግል ሜዳ ቆንጆ ነበረች:: የተማረች ወጣት ሴት ናት:: ከጥሩ ኑሮ ከመውጣትዋ በፊት መምህር ነበረች:: ምንም እንኳዋን ላይ ወደ ትግል የመጣች ብትሆንም ጀግናና ጠንካራ ታጋይ ነበረች:: ሌላው ቀርቶ እንደሌሎች የህወሀት ሴት ታጋዮች፤ ሞደስ የመሳሰሉ ነገሮችን የምትይዝበት ሻንጣ እንኳዋ አልነበራትም:: አስቴር ልዩ ፍጡር ነበረች:: ታዲያ በዚያ ውጊያ እንደነጋሽ በግንባር ቀደምትነት ስትፋለም በቦምብ ደረትዋ ላይ ተመትታ ተሰዋች:: አባቡ የሚባል ታጋይም ነበር:: ከአድዋ ወጣ ብላ በምትገኝ እዲ አቡን በምትባል ቦታ የተወለደ ወጣት ጀግና ነው:: በቦምብ ሲመታ ሁለት እግሩ ተገነጣጥሎ ተለያይቶ ተሰዋ:: ወዲ ማዘር የምንለው ጠንካራ ታጋይም ነበር:: እሱም ተሰዋ::

ግማሽ ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለትግሉ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ጀግኖችን አጣን:: የደርግ ወታደሮች ይህን ሁሉ የሚፈፅሙት ያለ ችግር ነበር:: ከዚያ አፈገፈግን:: አልቻልነም::

የነጋሽ ሬድዮ ወድቃ ትጮህለች:: የነጋሽን የአመራር ቦታ አብርሀ መጅሙእ የተባለ ጋንታ መሪ ተካው:: ሬድዮንዋን አንስቶ ከሀየሎም ጋር ግንኙነት ፈጠረ:: አብርሀ የነጋሽን መሰዋት ለሀየሎም ገለፀለት:: የአስቴርን ጭምር የነገረው ይመስለኛል::

'ለምን አልፈፀማችሁትም' እያለ ከወዲያ በኩል ሀየሎም ይናገራል:: የመሬት አቀማመጡ መጥፎ መሆኑንና ማጥቃት መፈፀም ጨርሶ እንደማይቻል አብርሀ መጅሙእ ለሀየሎም በሬድዮ





ገለፀለት:: ይህን ጊዜ ሀየሎም 'አሁኑኑ ራሴ እመጣለሁ' ብሎ የሬድዮ ግንኙነቱን አቋረጠ::

እኛም እዚያው ሽጥ ውስጥ አስቴር ፀሀዬን ቀበርናት:: ከተሰውት ላይ መሳሪያ መሰብሰብም ጀመርን:: የነጋሽን አስከሬን ማምጣት ግን የማይቻል ሆነ:: ከየተደበቅንበት ብቅ ስንል ኮረብታው ላይ በምቹ ሁኔታ ላይ የሚገኙት የደርግ ወታደሮች እያውካኩና አፀያፊ የብልግና ስድብ እየተሳደቡ የጥይት በረዶ ያዘንሙብናል::

«ሁኔታው ሁሉ ወለል ብሎ ይታየኛል... የተሰው ታጋዮቻችንን ጠመንጃዎች ሁሉ ሰበሰብን:: በቦምብ ሰውነቱ የተበጣጠሰውን የአባቡን ጠመንጃ ለማምጣት ግን ጨርሶ ሳንችል ቀረን:: የነጋሽን አስከሬን ማግኘትና የአባቡን ጠመንጃ ማንሳት የማይሞከር ሆነ:: ወታደሮቹ ጠመንጃዋን እንዳናነሳ ነቅተው ይከታተሉን ነበር:: ደፍሮ ማን ያንሳት - ጠመንጃዋን:: በመካከላችን ገብረሚካኤል የሚባል አንድ ታጋይ ነበር:: ሳናስበው ድንገት ብድግ ብሎ ወደ ጠመንጃዋ ተፈተለከ:: ትንፋሻችንን ውጠን እንመለከተው ጀመር:: የደርግ ወታደሮች የጥይት እሩምታ ያዘንሙበት ጀመር:: ገሬ አጉንብሶ በረረ:: ጠመንጃዋ አጠገብ እንደደረሰ ከመቅፅበት አንስቶአት ዚግዛግ እየሰራ ይበር ጀመር:: ከአሁን አሁን ተመትቶ ወደቀ ብለን አይናችን ፈጦ፤ ትንፋሻችን ቆሞ ነበር:: ሳይመታ አመለጠ:: ከፍተኛ ደስታና መጨዋጨዋህ ተፈጠረ:: ገሬ ይህን የጀግንነት ተግባር ለምን እንደፈፀመ ግን ግልፅ ነበር::

ከዚህ ውጊያ ቀደም ሲል በፈሪነት ተገምግሞ ነበር:: ገሬ በግምገማው የተነሳውን ነጥብ 'አልቀበልም' ብሎ ተሙዋገተ:: የጋንታዋ ታጋዮች ግን 'ገብረሚካኤል ፍርሃት አለበት' ብለው በአንድ ድምፅ በማፅደቅ ወደ ባዶ ስድስት (ማረሚያ ቤት) እንዲላክ ወሰኑ:: ይህን ውሳኔ ታዲያ ሀየሎም ሻረው:: 'ገብረሚካኤል በርግጥ ፈሪ ከሆነ በሚቀጥሉት ውጊያዎች እናየዋለን' ብሎ ነበር የጋንታዋን ውሳኔ የሻረው:: ከዚያ ወዲያ ታዲያ ገሬ በተለያዩ ውጊያዎች ጀግንነቱ በግልፅ ይታይ ጀመር:: በዚህ ቀንም ሁላችንም ለመፈፀም ያልደፈርነውን ተግባራዊ በማድረግ ግምገማው ስህተት እንደነበር አረጋገጠልን::

«በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን ሀየሎም ሽጉጥ ብቻ ታጥቆ ካለንበት ደረሰ:: መሽቶ ነበር:: ብቻውን ነበር የመጣው:: እንደደረሰ ወዲ ምእራፍ ከሚባል ማንጁስ ላይ ሲሞኖቭ ጠመንጃ ተቀብሎ እኛን ከሰበሰበ በሁዋላ እየመራን ነጋሽ ማጥቃት በሞከረበት መንገድ ተኩስ ከፈተ::

ኮረብታው ላይ ያሉት ወታደሮች እንደገና ጥይት ማዝነብና

ሳለ ግን ሽጥ አጋጠመን:: የውጊያ እቅዱ ሲነደፍ ስለዚያ ሽጥ የተነሳ ነገር ስላልነበር ነጋሽ ግራ ተጋባ:: ሽጡ ኮረብታ ላይ ላለው የደርግ ጦር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር! እኛን ደግሞ አጋልጦ የሚሰጥ ሆኖ ተገኘ:: ያንን ሽጥ ተሻግሮ የደርግ ሀይል ላይ ጥቃት መክፈት ጨርሶ የሚሞከር አልነበረም:: ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ግን ነጋሽ ሽረፎ 'ሽጡን ተሻግረን ግዳጃችንን መፈፀም አለብን' ሲል አሳወቀን:: ነጋሽ ይህን ካለ በሁዋላ የውጊያ አሰላለፉን አሳውቆን ማጥቃቱን እንድንከፍት አዘዘ! ራሱ ነጋሽም ግንባር ቀደም ነበር::

'ህጁም! ህጁም!' ብሎ ፊት ለፊት እየመራ ተኩስ ከፈተ:: ተከተልነው:: ነጋሽ እየመራን ገባ:: ኮረብታው እናት ላይ ምሽግ የያዙት የደርግ ወታደሮች ግን ከኛ ጋር መፋለም አልከበዳቸውም:: ከላይ እኛን ቁልቁል እያዩ እያውነኩ ጭርሱን ይቀልዱብን ጀመር:: ቦንቦቻቸውን እየነቀሉ ይሳደቡና ያላግጡብን ያዙ:: ተኩስ አዘነሙብን:: እኛ አፀፋውን መመለስ ቀርቶ ራሳችንን መከላከል ወረወሩብን:: ውጊያው በተጀመረ በአስር ደቂቃ ውስጥ እንኳዋ አልቻልንም:: መች ነጋሽ ብቻ ሆኖ:: ነጋሽ ሽረፎ ግንባሩ ላይ ተመቶ ተሰዋ:: ቀይ አስቴር ፀሀዬም ተሰዋች:: አስቴር ፀሀዬ ጨርሳ አትረሳኝም:: ወደ ትግል ሜዳ ቆንጆ ነበረች:: የተማረች ወጣት ሴት ናት:: ምንም እንኳዋን ከጥሩ ኑሮ ከመውጣትዋ በፊት መምህር ነበረች:: ጀግናና ጠንካራ ታጋይ ነበረች:: ላይ ወደ ትግል የመጣች ብትሆንም ሌላው ቀርቶ እንደሌሎች የህወሀት ሴት ታጋዮች! ሞያ'ስ የመሳሰሉ ነገሮችን የምትይዝበት ሻንጣ እንኳዋ አልነበራትም:: አስቴር ልዩ ፍጡር ነበረች:: ታዲያ በዚያ ውጊያ እንደነጋሽ በግንባር ቀደምትነት ስትፋለም በቦምብ ደረትዋ ላይ ተመትታ ተሰዋች:: አባቡ የሚባል ታጋይም ነበር:: ከአድዋ መጣ ብላ በምትገኝ አዲ አቡን በምትባል ቦታ የተወለደ ወጣት ጀግና ነው:: በቦምብ ሲመታ ሁለት እግሩ ተገነጣጥሎ ተለያይቶ ተሰዋ:: ወዲ ማዘር የምንለው ጠንካራ ታጋይም ነበር:: እሱም ተሰዋ::

ግማሽ ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለትግሉ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ጀግኖችን አጣን:: የደርግ ወታደሮች ይህን ሁሉ የሚፈፅሙት ያለ ችግር ነበር:: ከዚያ አፈገፈግን:: አልቻልንም::

የነጋሽ ሬድዮ ወድቃ ትጮሀለች:: የነጋሽን የአመራር ቦታ አብርሀ መጅሙእ የተባለ ጋንታ መሪ ተካው:: ሬድዮንዋን አንስቶ ከሀየሎም ጋር ግንኙነት ፈጠረ:: አብርሀ የነጋሽን መሰዋት ለሀየሎም ገለፀለት:: የአስቴርን ጭምር የነገረው ይመስለኛል::

'ለምን አልፈፀማችሁትም' እያለ ከወዲያ በኩል ሀየሎም ይናገራል:: የመሬት አቀማመጡ መጥፎ መሆኑንና ማጥቃት መፈፀም ጨርሶ እንደማይቻል አብርሀ መጅሙእ ለሀየሎም በሬድዮ





ገለፀለት:: ይህን ጊዜ ሀየሎም 'አሁኑኑ ራሴ እመጣለሁ' ብሎ የሬድዮ ግንኙነቱን አቋረጠ::

እኛም እዚያው ሽጥ ውስጥ አስቴር ፀሀዬን ቀበርናት:: ከተሰውት ላይ መሳሪያ መሰብሰብም ጀመርን:: የነጋሽን አስከሬን ማምጣት ግን የማይቻል ሆነ:: ከየተደበቅንበት ብቅ ስንል ኮረብታው ላይ በምቹ ሁኔታ ላይ የሚገኙት የደርግ ወታደሮች እያውካኩና አፀያፊ የብልግና ስድብ እየተሳደቡ የጥይት በረዶ ያዘንሙብናል::

«ሁኔታው ሁሉ ወለል ብሎ ይታየኛል... የተሰው ታጋዮቻችንን ጠመንጃዎች ሁሉ ሰበሰብን:: በቦምብ ሰውነቱ የተበጣጠሰውን የአባቡን ጠመንጃ ለማምጣት ግን ጨርሶ ሳንችል ቀረን:: የነጋሽን አስከሬን ማግኘትና የአባቡን ጠመንጃ ማንሳት የማይሞከር ሆነ:: ወታደሮቹ ጠመንጃዋን እንዳናነሳ ነቅተው ይከታተሉን ነበር:: ደፍሮ ማን ያንሳት - ጠመንጃዋን:: በመካከላችን ገብረሚካኤል የሚባል አንድ ታጋይ ነበር:: ሳናስበው ድንገት ብድግ ብሎ ወደ ጠመንጃዋ ተፈተለከ:: ትንፋሻችንን ውጠን እንመለከተው ጀመር:: የደርግ ወታደሮች የጥይት እሩምታ ያዘንሙበት ጀመር:: ገሬ እጐንብሶ በረረ:: ጠመንጃዋ አጠገብ እንደደረሰ ከመቅፅበት አንስቶአት ዚግዛግ እየሰራ ይበር ጀመር:: ከአሁን አሁን ተመትቶ ወደቀ ብለን አይናችን ፈጠ! ትንፋሻችን ቆሞ ነበር:: ሳይመታ አመለጠ:: ከፍተኛ ደስታና መጨዋጨዋህ ተፈጠረ:: ገሬ ይህን የጀግንነት ተግባር ለምን እንደፈፀመ ግን ግልፅ ነበር::

ከዚህ ውጊያ ቀደም ሲል በፈሪነት ተገምግሞ ነበር:: ገሬ በግምገማው የተነሳውን ነጥብ 'አልቀበልም' ብሎ ተሙዋገተ:: የጋንታዋ ተጋዮች ግን 'ገብረሚካኤል ፍርሃት አለበት' ብለው በአንድ ድምፅ በማፅደቅ ወደ ባዶ ስድስት (ማረሚያ ቤት) እንዲላክ ወሰኑ:: ይህን ውሳኔ ታዲያ ሀየሎም ሻረው:: 'ገብረሚካኤል በርግጥ ፈሪ ከሆነ በሚቀጥሉት ውጊያዎች እናየዋለን' ብሎ ነበር የጋንታዋን ውሳኔ የሻረው:: ከዚያ ወዲያ ታዲያ ገሬ በተለያዩ ውጊያዎች ጀግንነቱ በግልፅ ይታይ ጀመር:: በዚህ ቀንም ሁላችንም ለመፈፀም ያልደፈርነውን ተግባራዊ በማድረግ ግምገማው ስህተት እንደነበር አረጋገጠልን::

«በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለን ሀየሎም ሽጉጥ ብቻ ታጥቆ ካለንበት ደረሰ:: መሽቶ ነበር:: ብቻውን ነበር የመጣው:: እንደደረሰ ወዲ ምእራፍ ከሚባል ማንጁስ ላይ ሲሞኖቭ ጠመንጃ ተቀብሎ እኛን ከሰበሰበ በሁዋላ እየመራን ነጋሽ ማጥቃት በሞከረበት መንገድ ተኩስ ከፈተ::

ኮረብታው ላይ ያሉት ወታደሮች እንደገና ጥይት ማዝነብና

በምብ መወርወር ጀመሩ:: ሀየሎም ሁኔታውን በጥንቃቄ ካየ በሁዋላ እቅዱ ስህተት እንደነበር ተገነዘበ:: በርግጥም ጥናቱ የተካሄደው በጦር ሜዳ መነፅር በርቀት በመመልከት ብቻ በመሆኑ የዚያ ሽጥ መኖር አልታወቀም ነበር:: ሀየሎም እንድናፈገፍግ ካደረገ በሁዋላ፣

'የነጋሽ ሽሪፎ አስከሬን የት ነው?' ሲል ጠየቀን:: ያለበትን ነገርነው:: ሊላማ ውስጥ ነበር:: ይህን ጊዜ ሀየሎም አምስት ጠንካራ ተኩዋሾችን መረጠና ወደ ኮረብታው የሽፋን ተኩስ እንዲያዘንቡ አዘዘ:: አምስቱ ታጋዮች የተኩስ እሩምታ ወደ ኮረብታዋ ሲያዘንሙ ሁለት ታጋዮች መሬት ለመሬት እየተሳቡ የነጋሽን አስከሬን እንዲያመጡ ላካቸው:: በዚህ ሁኔታ የነጋሽን አስከሬን ካገኘን በሁዋላ ሀየሎምን አጅበን የመልስ ጉዞ ጀመርን::

ጉዞው በዝምታ የተሞላ ነበር:: ሀየሎም አንዳችም ቃል አይተነፍስም ነበር:: ጨርሶ ጨልሞ ነበር:: እንዲያውም እኩለሌሊት ያለፈ ይመስለኛል:: ከድብድቦ ወጣ እንዳልን ሰጥ ያለ የገጠር ሜዳ ላይ ደረስን:: ሀየሎም ነጋሽ ሽሪፎን እንድንቀብር አዘዘን:: ቀበርነው:: ከቀብር በሁዋላ እንድንተኛ ነገረን:: በደንቡ መሰረትም ዘብ ተመደበ:: አጋጣሚ እኔ ነበርኩ ለሌሊቱ ጥበቃ በቅድሚያ የተመደብኩት::

እኩለ ሌሊት አልፎአል...

የጨረቃ ብርሀን አልነበረም:: ሌሊቱ ፀጥተኛ ነበር:: ፍፁም ፀጥተኛ:: ታጋዮች አርፈዋል:: ድካም ስላደቀቃቸው ሁሉም በያገኙበት አሸልበአል:: እኔም ነቅቼ የጥበቃ ስራዬን እያከናወንኩ ነበር:: በፀጥተኛው ሌሊት ድቅድቅ ጨለማው ላይ አፍጥጬ የጥበቃ ተግባሬን በንቃት ማካሄዴን ቀጠልኩ፣

አካባቢያችን በድንገተኛ ጩኸት ተናጋ!

ሰውነቱ ሰሁለት የተተረተረ ያህል ተሰማኝ:: የቀለጠ የእሪታ ድምፅ ነበር የተሰማው:: እያንዳንዱ ታጋይ ከየተጋደመበት እየተወረወረ ተነሳ:: እኔም እንደደነዘዝኩ ባለሁበት አለሁ::

ሀየሎም ኖሮአል እሪታውን የሚያቀልጠው!

የሀየሎም ድምፅ መሆኑን ስናውቅ በያለንበት ጥርኝ አክለን በፀጥታ ተዋጥን:: የትግራይ ህዝብ የቅርብ ዘመዱ ሲሞትበት በሚያሰማው የልቅሶ ዘይቤ ነበር ሀየሎም እየተንሰቀሰቀ የሚያለቅሰው::

'ነጋሽ ዓርከይ! ነጋሽ ሐወይ! ነጋሽ ጅግና! ነጋሽ ዓርከይ! ዋይ! ዋይ! ነጋሽ ሐወይ!' እያለ ነበር በምሬት እየተንሰቀሰቀ የሚያነባው::

ታጋዩ ሁሉ በያለበት ኩርምት ብሎ የሀየሎምን እሪታ ያዳምጥ





ጀመር:: በትግሉ ማልቀስ እጅግ የተከለከለ ነበር:: ሀየሎም ግን ሌሊቱን ሙሉ እንድችው ሲያለቅስ አነጋ:: አስታውሳለሁ:: ለሶስት ወይም ለአራት ሰአታት ያህል እየተንሰቀሰቀ አለቀሰ:: አንድም ታጋይ ሊያፅናናው አልሞከረም:: ግን በሀየሎም መንሰቅሰቅ ውስጥ፤ በሀየሎም እሪታ ውስጥ እልህና ቁጣ በግልፅ ይሰማ ነበር:: እኔ በግሌ እንዲያ ተሰማኝ::

የዚያን ቀኑ የሀየሎም ሁኔታ ሰዘልአለሙ በአእምሮዬ ተቀርፆ ቀርቶአል:: ስለሀየሎም ወሬ ሲነሳ ጉልቶ የምትታየኝ ያቺ ሌሊት ናት:: አንዳንድ ጊዜ ታዲያ ሀየሎም ያን ሁሉ እንባ ያፈሰሰው፤ ለረጅም ሰአት ጉልበቱ ላይ ተደፍቶ እንዲያ የተንሰቀሰቀው በርግጥ ለነጋሽ ብቻ ነውን?' ብዬ አስባለሁ:: በግሌ አይመስለኝም:: ያለፈውን... የሌሎቹንም ሁሉ ጨማምሮ ሀዘኑን የተወጣ ይመስለኛል::»

ወልዲያ ላይ እረፍት ተደረገ ...

ሀወኒ ከሀየሎም ጋር የተያያዙ ታሪኮችን ከማጠያየቅ አልቦዘነችም:: የወልዲያ ህዝብ ሀየሎምን አሳምሮ ያውቀዋል::

ብዙዎች ከሀየሎም ጋር የተያያዘ አያሌ ገጠመኞቻቸውን አጫወቱዋት:: ካነጋገረቻቸው መካከል ለየት ያለ መረጃ የሰጣት ግን አንድ መልከ ቀና ጉረምሳ ነበር::

«ሀየሎም ወልዲያ ሲገባ መኪናውን በድንጋይ አመድ ካደረጉት ወጣቶች አንዱ እኔ ነኝ» አላት::

በመደነቅ አይንዋ ፈጠጠ፣

«ለምን?» አለችው::

«ወያኔዎች ሲዘርፉ ነው የሚመጡት ተብሎ ስለተነገረን የቢራ ጠርሙስ የሚያካክል የባልጩት ድንጋይ ይዘን ጠበቅናቸው:: ያን ሁሉ ድንጋይ ስናወርድባቸው ግን ወደሰማይ ነበር የሚተኩሱት:: ሀየሎምም ታዲያ ከጠበሉ ቀመሰ» ብሎ ፈገግ አለ::

ሀወኒ ጉዋጉታ «በድንጋይ መታችሁት?» ስትል ጠየቀችው::

«ራሱ ነበር ኡዋዝ ጂፕዋን የሚነዳት:: በድንጋይ እየበረቃቀስናት አንገቱን ቀብሮ መኪናዋን አስፈተለካት:: እየተከተልን አወረድንበት:: ሸሸና አመለጠ:: ሁዋላ በአንድ የህዝብ ስብሰባ ላይ ንግግር አደረገ:: ያንን ቀን ጨርሶ አልረሳውም:: 'ሀየሎም ይናገራል' ስለተባለ ሰው ሁሉ ሊያየው ግልብጥ ብሎ ወጣ:: እኔም በኡዋዝ ጂፕ ላይ በድንጋይ

ድባት የመታነው ታጋይ ይሆናል ብዬ ስላልገመትኩ በዝና ስሙ የሚነገረውን ሰው ለማየት ጉዋጉቼ ሄድኩ:: አታምኚኝም ብት ብሎ ሳየው አፈሁን በሁለት እጄ ይገፍ እይኑን አፍጥጬ ቀረሁ::

ሀየሎም «እኛ ህወሀት ነን! እኛ የትግራይ ምድር ሰዎች ነን:: እናንተ ደግሞ አማሮች ናችሁ:: እዚህ መድረክ ላይ እኛና እናንተ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ሀሳባችንን ብንገልፅ ግን በፍላጐታችን መካከል ቅንጣት ልዩነት እንኳ አይገኝም» በሚል መንደርደሪያ ግማሽ ሰአት ተናገረ::

በዚያኑ እለት እኔና ሀያ ወጣት ጉዋደኞቼ ለትግል ወሰንን:: ተሰባሰብን ከተነጋገርን በሁዋላ በቀጥታ ሀየሎምን ማነጋገር እንደምንፈልግ ገለፅን:: ወዲያው አገናኙን:: ሁላችንንም ጨበጠን:: መታገል እንደምንፈልግ ነገርነው:: በጣም ተደስቶ በቡጢ ደረታችንን እየመታ 'ወደ ደብረታቦር ከናንተ ጋር ነው የምገባው' አለን:: ይሄን ሲለን ሁላችንም እንባችን መጣ:: በደስታ አበድን:: ሙሁን! በዚያኑ ደቂቃ ወደደብረታቦር ለመገስገስ ተመኘን:: ደስታ አሰከረን:: ከዚያም እኔ አንድ ጥያቄ ጠየቅሁት፣

'ያኔ ድንጋይ ሲወርድብህ ያልተኰስከው ለምንድነው?' አልኩት::

ሀየሎም ሳቀና፣

'ህዝብ ላይ የሚተኩስ፣ ከህዝብ ጋር የሚጣላ፣ ህዝብ ላይ በደል የሚፈፅም መጨረሻው አሳፋሪ ውድቀት ነው' አለን::

ከዚያ ከኢህዴን ጉዋዶች ጋር አገናኘን:: አሁን ፖለቲካዊና ወታደራዊ ስልጠናውን ጨርሰናል:: እኔ ከባድ መሳሪያ ላይ ስለተደለደልኩ ወደ ማሰልጠኛ ጣቢያ እያመራሁ ነው» ሲል አጫወታት::

ሀወኒ ተመሰጠች፣

«ለመሆኑ» አለችው «ከዚያ ወዲህ ሀየሎምን አጊኝተኸው ታውቃለህ?»

«አላውቅም» ሲል መለሰላት:: አያይዞም «... ግን ምን ያደርግልኛል:: እኔ ራሴ ትንሹ ሀየሎም ሆኛለሁ:: በነገራችን ላይ ማን ነበር ስምሽ ... አትሳሳቺ:: ኢህአዴግ ማለት ሀየሎም ብቻ ማለት አይደለም:: ይህን ስልሽ ግን በግል ሀየሎምን የማፍቀር መብታችን እንደተጠበቀ ሆኖ ነው»

በደመቀ ሳቅ ተሰናበታት::

ከወጣቱ ታጋይ ከተለየች በሁዋላ በአንድ ሻይ ቤት በረንዳ ላይ





ተቀምጣ የጉዞው ሰአት እስኪደረስ ድረስ በራስዋ አሳብ ተመሰጠች::

'ኢህአዴግና ሀየሎም አንድ ናቸው ወይስ ሁለት?' ስትል ለራስዋ ጥያቄ አቀረበች? ምላሽ ግን አልነበራትም:: ይልቁን ጥያቄዎችዋ ቀጥለዋል - ለራስዋ:: ሀየሎምን ነው የወደድኩት ወይስ ኢህአዴግን? ሀየሎም እንደ ሰው ሩህሩህና ጀግና ስለሆነ ይሆን የወደድኩት? በርግጥ የድርጅቱ ሰዎች ሁሉ እንደ ሀየሎም ተወዳጅ ናቸው? 'ኢህአዴግና ሀየሎም ሁለት አይደሉም' ለማለት አልቻለችም:: ለዚህ ምላሽ ለማግኘት ጊዜ እንደሚያስፈልጋት አመነች::

አያይዛ ግን በአለም ላይ ስመጥር ጀግና ስለሆኑ ግለሰቦች እያሰላሰለች ነበር:: በአንድ በኩል ሽፍታ ወይም ሩዋ የሚል ቅፅል ስም ተሰጥቶአቸው ትግላቸውን በህዝባዊ አላማና ግብ ባለማስደገፋቸው ባጭሩ የተቀጩ አሉ:: ይህን መሰል ጀግኖች ቁጥር ስፍር የላቸውም::

በድል አድራጊነት አገራቸውን ነፃ ያወጡም አያሌ ናቸው:: ድሉን ለማየት ባይበቁም በአላማቸውና በተከታዮቻቸው በኩል ድልን የሚቀዳጁ አሉ:: ታሪካቸው የተሻፈላቸው ዛሬ በድፍን አለም ጀግንነታቸው፣ ፅናታቸውና የትግል አርአያነታቸው ደምቆ ይነበባል:: ካልተፃፈ ግን አፈታሪክ ሆኖ ይቀራል:: በሌሎች አገሮች በተካሄዱ የህዝብ ትግሎችም ሆነ የአገሮች ጦርነቶች አያሌ ጋዜጠኞችና ደራስያን ከተዋጊዎች ጋር አብረው ይዘምታሉ:: ከፍፃሜ በሁዋላ ታዲያ ተነበው የማያልቁና የማይጠገቡ መፅሀፍት አገር ምድሩን ያለብሱታል:: እኒያ መፅሀፍትም አዲሱን ትውልድ ያንፃሉ::

የኢህአዴግ ትግል በዚህ ጐኑ ደካማ መሆኑን አሰበች:: የጦርነቱን እንቅስቃሴ በቪዲዮ ፊልም ብቻ በመቅረፅ ታሪክን ማስቀረት እንደማይቻል ታምናለች:: ታሪክን በማቆየቱ ረገድ ታላቅ አቅም ያለውና ሊተካ የማይችለው መፅሀፍ ብቻ ነው:: መፅሀፍ ካለ ሌላው ሁሉም ነገር ይኖራል:: መፅሀፍ ከሌለ ግን ምንም ነገር አይኖርም::

በህዝብ ውስጥ እንደዋዛ የተበተኑ የትግሉ ታሪክ ቁርጥራጭ አካላት በሙሉ ያለመታከት ከነለዛቸው ሊሰበሰቡ እንደሚገባቸው አሰበች:: ይህ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ለአመራር አካሉ ሀሳብ ማቅረብ እንዳለባት ጭምር አመነች:: ምናልባትም ሀየሎምን ማእከል ያደረገ አንድ መፅሀፍ ማዘጋጀት ከቻለች ድርጅቱ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚችል ገመተች:: ደረቅ አሳብ ከማቅረብ ይልቅም ሰርቶ ማሳየት የተሻለ ሀይል እንደሚኖረው አሰበች:: ከሃሳብዋ የባነነችው ስምዋ ሲጠራ ነበር:: አክሱማይት ነበረች:: ወደስዋ ስትመጣ አየቻት:: ስትራመድ ግራ እግ... ገመተች ይላል::

ጉንጭዋ ላይም እንደጉራጌ የተጋደመ ጠባሳ ይታያል። ጥይት መሆኑ ሀወኒን አላጠራጠራትም። አጠገብዋ እንደደረሰች ፈገግ ብላ ጨበጠቻት፤

«እድለኛ ነሽ ሀወኒ… ሀየሉምን ከልጅነቱ ጀምሮ የሚያውቀው አንድ ታጋይ አግኝቼልሻለሁ። እስከ ደብረታቦር ከኛ ጋር ነው የሚሄደው» አለቻት።

«እውነት?»

«ነግሬዋለሁ። ተስማምቶአል። በርግጥ ነጭናጫ ነው። ማንኛውም ነገር ያነጫንጨዋል። በዚህ ጉዳይ ያልተገመገመበት አንድም መድረክ የለም። ካልተነጫነጨ የታገለ አይመስለውም» እያለች አሳቀቻት።

ተያይዘው መኪናቸው ወደምትገኝበት አካባቢ ሲያመሩ፣ ሀወኒ እንደዋዛ አንድ ጥያቄ ጣል አደረገችላት፤

«ለመሆኑ ከማህፈረ ጋር ስለፍቅራችሁ ታወራላችሁ?»

ይህን ጥያቄ ያነሳችው ታጋይ ፍቅረኛሞች ከሲቪሉ የሚለዩበት ባህርይ ካላቸው ለማወቅ ፈልጋ ነበር፤

«እናወራለን። ለምን አናወራም?»

«ምን ትባባላላችሁ? እሱ ምን ይልሻል?»

«ጀግና ስለሆንሽ ነው ያፈቀርኩሽ። በአላማሽ ፅኑ በመሆንሽም ነው አንቺን ለጋብቻ የመረጥኩሽ። 'በመሬት ጥያቄም ሆነ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል በሚለው ፅንሰ ሀሳብ ላይ ፅኑ እምነት ስላለሽ እወድሻለሁ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለቅንነትሽ ልዩ ግምት እሰጠዋለሁ' ይለኛል»

ሀወኒ ፈገግ አለች።

«አንቺስ ምን ትይዋለሽ?»

«እሱ ከሚለኝ ብዙ የማይለዩ ነገሮችን ነው የምነግረው።»

«ሌላስ ምን ታወራላችሁ?»

«በብዛት ስለትግሉ ነው የምንነጋገረው»

«እኔና አንቺ እንደምናወራው?»

«አዎን።»

«ቆንጆ እንድትሆኚለት ይፈልጋል? ለምሳሌ በአለባበስ…»





አክሱማይት በጣም ሳቀች። ከመሳቅ በላይ ደሞ መገረም ጭምር ገፅታዋ ላይ ተነበበ።

«ምን አሳቀሽ?»

«አሁን ስላልሻቸው ነገሮች አንድ ታጋይ ከቶ እንዴት ሊያስብ ይችላል? የሚገርም ጥያቄ ነው። በጣም የሚገርም። ማህፈረ በጣምነው የሚወደኝ። ልጃችንን ደግሞ ከራሳችን በላይ እንወደዋለን። እኛ ብንሰዋ ፀሀዬ ያድጋል። ይሄ በጣም አስደሳች ነገር ነው። በአባትና በእናቱ አላማና ታሪክ የሚያምን ልጅ ወልደናል። ደስ አይልም ሀወኒ?»

«በጣም ደስ ይላል - አክሱም። በጣም!» አለቻት።

ይህን ያለቻት ግን ከልብዋ አልነበረም። ይልቁን ሀዘን ነበር የተሰማት። አክሱማይት ከሰብአዊ ባህርያት ማፈንገጥዋ እየታሰባት ነበር።

ማምሻውን ወደደብረታቦር የሚያደርጉትን ጉዞ ጀመሩ። የጨረቃዋ ዙሪያ ደም ለብሶአል። የጥይት ድምፅ ግን አይሰማም። ሌሊቱ ፍፁም የተረጋጋ ነበር። ሀወኒ ጆሮዎችዋን ከፈተች። ልብዋ… ቀልብዋ… ሁሉ የሀየሉምን የልጅነት ታሪክ ሊያዳምጥ አሰፈሰፈ። ካልተነጫነጨ የታገለ የማይመስለው የህወሀት ነባር አባል እንዲህ ሲል ነበር ንግግር የጀመረው፤

«… ስለሀየሉም ልጅነት ምን የሚወራ ይኖራል? … በመሰረቱ አንቺም ቢሆን በዚህ ወቅት የሀየሉምን የልጅነት ታሪክ ማወቅ መፈለግሽ ግራ ያጋባል። በርግጥ አክሱማይት ምክንያትሽን ነግራኛለች። ጉዳዩን ባላምንበትም የተወሰኑ ነገሮች እነግርሻለሁ…»

ሀወኒ እንደ ርችት የሚፈነዳ ሳቅዋን ለቀቀችው… አክሱማይትም በሳቅ አጀበቻት። ነጭናጫው ታጋይ ግራ ከመጋባቱና ከመደንገጡ የተነሳ መሀል አስቀምጠው የሚስቁበትን ሴቶች በየተራ ገረመማቸው።

«ምን ነካችሁ?» አለ።

«ይቅርታ» አለች አክሱማይት «… ነጭናጫ መሆንህን ነግሬያት ስለነበር ነው ሀወኒ የሳቀችው»

ታጋዩ በንዴት ጦፈ፤

«እኔ በጣም የሚገርመኝ ነገር ቢኖር፣ እኔ ሳላምንበት - በመርፌ ግጥም አድርጋችሁ ስለሰፋችሁልኝ ነጭናጫ ስለሚባለው ጭራ ነው። እኔ ነጭናጫ አይደለሁም። ነጭናጮች እናንተው ናችሁ። ያልመሰለኝን መናገር መነጫነጭ ነው?»

ከአክሱማይት ጋር በትግርኛ አንድ ሁለት መባባል ሲጀመሩ ሀወኒ እየሳቀች ታያቸው ጀመር። ለአምስት ደቂቃ ያህል

ተጨዋጨኸው ተስማሙ::

«ይቀጥልልሻል ሀወኒ» አለች አክሱማይት «ሳትሳቀቂ ያሻሽን ጠይቂው:: የሀየሎምን የልጅነት ታሪክ ላንቺ መንገር እንዳለበት አምኖአል:: እየተነጫነጨም ቢሆን አምኖአል::»

አክሱማይትን ከገላመጣት በሁዋላ ጆርባውን ሰጥቶአት ፊቱን ወደሀወኒ አዞረ::

«... ሀየሎም በልጅነቱ እግር ኳዋስ ጨዋታ ይወድ ነበር:: ይኸው ነው የልጅነቱ ታሪክ:: በርግጥ የአዲነብርኢድን ወጣቶች እያሰባሰበ ለጠብም ለፍቅርም፣ ለአደንም የማስተባበር ባህርይ ነበረው:: ከዚህ በላይ ምን ሊባል ይችላል? በርግጥ አድማ የማድረግ ዝንባሌዎቹን መጥቀስ ይገባል:: አመፅ ነገሮች ላይ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነበር:: እምቢተኛ ነበር - ሀየሎም:: በዚህ ጠባዩ አንድ ጊዜ ከትምህርት ቤት ተባሮ እንደነበር አስታውሳለሁ::

«በአፄ ሀይለስላሴ ስርአት ላይ ይካሄዱ በነበሩ የተማሪዎች የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ላይም ተካፍሎአል:: ይሄ አይበቃሽም?» ብሎ ወደ አክሱማይት ተገላመጠ:: ሁለቱም ከመናገራቸው በፊት ደግሞ ራሱ ቀጠለ «... በርግጥ በወቅቱ የተሙዋላ ፖለቲካዊ ብስለት ነበረው ለማለት አይቻልም:: ሁላችንም እንዲያ ነበርን:: መቼም ሀየሎምን በሚገባ አውቀዋለሁ:: ከትግል በፊትም ሆነ ከትግል በሁዋላ አሳምሬ አውቀዋለሁ:: ሳያስበው ነው ወደ ትግል የገባው:: ሁላችንም ደሞ እንዲያ ነበርን:: ለአብነት ለሩሲያ አብዮትና ለሌኒን ታላቅ ክብር ነበረው:: የአብዛኞቻችንም ሁኔታ ይህን ይመስል ነበር ማለት ይቻላል:: ይህም ሆኖ ግን ሀየሎም አዲነብርአድ ላይ ፍትህ በመንፈግና ጉቦ በመብላት ለታወቁት ፖሊሶች ጥሩ መድሀኒታቸው እንደነበር የታወቀ ነው:: ሽጉጣቸውን፣ ኰፍያቸውን እየነጠቀ ደም እምባ ነበር የሚያስለቅሳቸው:: ዘወትር ወደቤቱ እማላጅ እንደጐረፈ ነበር:: አብሪተኞችን ከልጅነቱ ጀምሮ አጥብቆ የሚጠላ፤ ደካሞችን የሚደግፍ፤ በጉዋደኞቹ ሁሉ የተወደደ፤ ግሩም ሰው ሆኖ ነው ያደገው:: ይህ ሁሉ ህዝባዊ ባህርይ እንዳለው ቢጠቁምም በዚያን ወቅት ግን ድንገት ነበር ትግሉን የተቀላቀለው:: ጠመንጃ ይዞ ወጥቶ ረጅም አመት በረሀ ቆይቶ፣ ታግሎ ፣ አታግሎ፣ ወደዚህ ደረጃ መድረስን የመሳሰለ ነገር በአእምሮው ያልነበረ ሊሆን እንደሚችል ግልፅ ነው:: ይኸ በአብዛኞቻችን የነበረ ነው:: በርግጥ እነወዲ ዜናዊ እንዲያ ላያስቡ ይችላሉ:: ከጠየቅሽኝ ርእሰ ጉዳይ ወጥቼ ይሆን?»

«ልክ ነህ:: ቀጥል ተስማምቶኛል» አለች ሀወኒ::

«... መልካም:: ጥያቄሽ ራሱ ችግር ስላለበት ነው ይህን ያልኩሽ:: እንዳልኩሽ የሚሰማኝን መናገር አለብኝ:: አንድ ቃል በተነፈስኩ





ቁጥር 'ነጭናጫ' የሚል ቀንድ ግንባሬ ላይ መትከል ተገቢ አይደለም:: ካቆምኩበት ለመቀጠል ያህል... በ1967 ከሀየሎም ጋር ወደአዲስ አበባ ሄደን እንደነበር ባነሳልሽ ይጠቅምሽ ይሆናል:: ወሩ ጥቅምት ይመስለኛል:: ልክ ነኝ፤ ጥቅምት መግቢያው ላይ ነበር:: የየካቲቱ ህዝባዊ አብዮት ተቀጣጥሎ ግርግር የጦፈበት ጊዜ ነበር:: ሀየሎም ደጋግሞ 'እነዚህ ወታደሮች አላማሩኝም' ይል ነበር:: ሁለት ወራት ያህል አብረን አዲሳባ እንደቆየን፣ 'እኔ ወደአዲነብርኢድ መመለሴ ነው' አለኝ:: 'ትንሽ እንቆይ?' አልኩት::

'ለምን?' አለኝ::

ምላሽ አልነበረኝም:: አያይዞ፣ 'ለመማር፣ ስራ ለመያዝ፣ የአዲሳባ ሰው ለመሆን?' የሚል ጥያቄ አቀረበልኝ::

'መልካም እንግዲህ አንተ ተመለስ:: እኔ ዘግይቼ እከተልሀለሁ' አልኩትና ተሰነባበትን::

እኔ አዲስ አበባ ቆየሁ:: ሁዋላ እንደሰማሁት ከአዲስ አበባ እንደተመለሰ ወደ አባቱ እርሻ ነበር የሄደው:: ሽራሮ፣ ገምሀሎ እሚባል ቦታ ከእህቱ ልጅ ጋር ጥቂት ጊዜያት የቆየ ይመስለኛል:: እንግዲህ ይህ ጊዜ የህወሀት መስራች የሆኑት ወዲ ዜናዊም ሆነ እነ ስዬ፣ እነ አባይ እነ ስብሀት እነ ስዩም በአካባቢው ይንቀሳቀሱ የነበረበት ጊዜ ነው:: ሀየሎም በወቅቱ ስለእንቅስቃሴው ብዙ እውቀት የነበረው አይመስለኝም:: ይልቁን ይኸ ያልኩሽ ወንድሙ ከነ ስዬ ጋር ግንኙነት መስርቶ ነበር:: ውሎውን ግን ለሀየሎም አይነግረውም:: ሁዋላ ሀየሎምንም ይዞት መሄድ ጀመረ:: በዚህ ጊዜ ነው እኔ ከአዲሳባ በቀጥታ ወደበረሀ የሄድኩት:: እዚያ በደረስኩ ሰሞን ሀየሎምም መጣ:: በመጀመሪያዎቹ የትግሉ ጊዜያት ለትግል ከወጡት መካከል ወደ ከተማ እየተመለሱ ለደርግ መረጃ የሚያቀብሉ ስለነበሩ እነርሱን እንድንጠብቅ እኔና ሀየሎም ተመድበን እንደነበር ትዝ ይለኛል:: ይኸ ግን የትግሉ የአጀማመር ታሪክ እንጂ የሀየሎም የልጅነት ጊዜ ስላልሆነ ከርእሴ የወጣሁ ይመስለኛል» ብሎ ድንገት አቋረጠ::

«የለም! የለም! » ብላ ተቃወመች ሀወኒ «... እንዲያውም እጅግ ጠቃሚው ምእራፍ ይኸ ይመስለኛልና ቀጥልበት» ስትል አደፋፈረችው::

ትንሽ አቅማምቶ ቀጠለ፣

«... ስለሀየሎም የትግል አጀማመር ሲጠቀስ የሚገባው ምንም የውትድርና ስልጠና ሳይሰጠው ራሱን ብቁ አድርጐ የመገኘቱ ጉዳይ ነው:: ወደ በረሀ ሲወጣ ጭምር እንደታጋይ ታጥቆና የአባቱን ጠመንጃ ይዞ ነበር:: ይህ ሁኔታ ሀየሎምን ልዩ ያደርገዋል:: ከማንኛችንም

ታጋዮች ቀድሞ ችሎታውን ማስመስከር የጀመረ፤ ተወዳጅነትና አመኔታን ያተረፈ ታጋይ ነበር። በርግጥ ሁዋሳ ታሳላቅ ውጊያዎች መካሄድ ሲጀምሩ የተለያዩ የውትድርና ጥበቦችን አጥንቶአል። በማንበብ ልምዱን አዳብሮአል። በተግባር ያገኘውን ልምድ ካነበበው ጋር እያዛመደ በአሳማ ፅናት እያረቀ የድልና የጀግንነት ምሳሌ ለመሆን የበቃ ወንድማችን ነው። ሀየሎም ያልተሳተፈበት ውጊያ ተደርጐአል ማለትም ከቶ አይቻልም። በውጊያዎች ሁሉ ሀየሎም የብርታት ብርሀን ሆኖ ያገለግላል። ስለሀየሎም ተነግሮ ያልቃል ብሎ የሚያስብ ካለ መቼም የዋህ ነው። እኔንም ከዚህ በላይ ባትነዘንዙኝ ለፅድቅ ይሆናችሁዋል ...»

ሳቁበት።

ከዚያ በላይ አንዲትም ቃል ለመተንፈስ እንደማይፈልግ ጭምር ተገነዘቡለት። ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ እንደቆዩ፤

«ታሪክ ፀሀፊ ከሆንሽ በአጠቃላይ በኢህአዴግ ወይም በህወሀት ደረጃ ያለውን የትግል ታሪክ ብትቃኚው አይሻልም?» ሲል ጠየቃት «...የሀየሎምን ብቻ ነጥለሽ የምታዪው ከሆነ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ነው የምትጉዋዢው።»

ሀወኒ በረጅሙ ተነፈሰች። ይህን ለመሰሉ ጥያቄዎች ማብራሪያ መስጠት ታክቶአታል።

* * *

በቤጌምድር ግዛት ውስጥ ወርቃ የምትባል አንዲት ትንሽ መንደር አለች። ወርቃ በታላላቅ ኮረብታዎች ተከባለች። የከፍተኛ ኮረብታዎቹ ጫፍ ጣናንና ባህርዳርን አሻግሮ ያማትራል። በእነዚህ ከፍተኛ ኮረብታዎች አናት ላይ ብዙ ሺህ ጠመንጃዎች አሉ። የጠመንጃዎቹ አፈሙዝ ወደባህርዳር ያመለክታል። አሁን ጠመንጃዎቹ ዝምታ ላይ ናቸው። ትእዛዝ ይጠብቃሉ። በሚታዘዙባት ደቂቃ ግን በደርግ ግዙፍ ሀይል ላይ ይዘፍኑበታል። ካልታዘዙ ምንጊዜም ፀጥተኞች ናቸው።

የተዋጊዎቹ አዛዥ ከኮረብታዎቹ እምብዛም ባልራቀ የአንድ ገበሬ ጎጆ ውስጥ ይገኛል። የጎጆዋ አካባቢ ሌሊትና ቀን በታጋዮች ይጠበቃል። በኮረብቶቹ ላይ የመሸጉት ንቁ ታጋዮች መሪያቸው አጠገባቸው መኖሩን ያውቃሉ። በአካባቢያቸው መገኘቱ የሚያሳድርባቸው ልዩ ስሜት ጭምር አለ። በራስ የመተማመን ወኔያቸውን ይጨምረዋል። ልበ ሙሉነት ይሰማቸዋል። ስለዚህ ዘወትር ስሙ ከአንደበታቸው አይጠፋም - ሀየሎም!፤ ወዲ አርአያ!

ሊመሽ ምንም አልቀረው ...





አንዲት ረጅም ቀጭን ሴት ሀየሎም ወደሚገኝበት ጎጆ ስታመራ ታየች። የያዘችው ሻንጣ እንደ አሸዋ ቢከብድም የመበገር ሁኔታ አልታየባትም።

ታጋይ መች ይደክመውና!? ምን ሲደረግ!?

«ወዴት ነው?» የሚል ድምፅ ሰማችና ቆመች። በመፅሀፍ የተሞላ ሻንጣዋንም ጣል አደረገችው። በድንግዝግዝ ውስጥ ድምፅ ወደሰማችበት ጢሻ አተኮረች። ራሱ ላይ የጠመጠመው ክሹፍ የደብር አለቃ ያስመሰለው ጠመንጃ ያነገተ ተዋጊ ከሰንሰል ቅጠሎች ውስጥ ተመዞ ወጣ።

«ሀየሎምን ማነጋገር እፈልጋለሁ» አለችው።

ታጋዩ ግን መልስ ሳይሰጣት በርቀት ያስተውላት ጀመር።

«ሀወኒ ማለት አንቺ ነሽ?»

«ነኝ አዎ»

በፈገግታ ተጠጋት።

እንደበረሀው ልማድ ጭንቅላት ለጭንቅላት እየተገጫጩ ተሳሳሙ።

«ሀየሎም እንደምትመጪ ከነገረን ቆየ። ምነው ዘገየሽ?»

«መኪና በጣም ችግር ነበር።»

ታጋዩ ሻንጣዋን አፈፍ አድርጐ ወደ ጎጆዎቹ እየመራ ወሰዳት።

«እንተዋወቃለን። ረሳሺኝ ልበል?»

«ረሳሁህ። የት ነበር የተገናኘነው?»

«ከጐንደር እንደመጣሽ» ብሎ ፈገግ አለ። አያይዞ «ለመሆኑ ትግርኛ ለመድሽ?»

«ቁሩብ ... ቁሩብ»

ሁለቱም ሳቁ። 'ትንሽ - ትንሽ' ማለትዋ ነበር።

ከጐጆዎቹ ጉዋሮ ከአስር የማይበልጡ የትግራይ ታጋዮች ራት እየተመገቡ ነበር። በትሪ ላይ የተዘረጋውን እንጀራ ከበው እጆቻቸውን አንዴ ሲሰነዝሩ ትሪው ባንድ አፍታ ባዶውን ይቀራል። ዳሩ ትሪ አይደለም። ለሁለት የተሰነጠቀ ጀሪካን ነው። አንድ ጀሪካን በቁመቱ ለሁለት ሲሰነጠቅ ምን የመሰለ ሁለት ትሪ ይወጣዋል።

ታጋዮቹ በባህላቸው መሰረት እንግዳዋን ወደ ገበታው

ጋበዙዋት። ተጠግታ መሻማት ጀመረች። ገና ከእሳት የወረደው የአደስ ወጥ እንጀራው ላይ ሲገለበጥ የዘንጋዳው እንጀራ እየራሰ ስለሚቆራረስ ጠቅልሎ ለመጉረስ አይመችም። ዳሩ ለአመጋገብ ምን ህግ ያሻዋል? እንጀራና ወጡን እንደ ንፍሮ እየዘገኑ ለመጉረስ መሞከር የተለመደ ነው።

«ማን ልበል ስምሽን?»

ለእንግዳዋ ጥያቄ ያቀረበላት የግንባሩ የመረጃ ሀላፊ ነበር። ራት ላይ ባጋጣሚ አጠገብዋ ነበር የተቀመጠው።

«ሀወኒ። ያንተስ?»

«ወዲ አስመራ ይሉኛል።»

«ኤርትራዊ ነህ?»

«አይደለሁም። የትግራይ ልጅ ነኝ - ግጀት የምትባል መንደር ነው የተወለድኩት። እድገቴ ግን አስመራ ስለሆነ ታጋዮቹ ወዲ አስመራ ይሉኛል። እዚህ ተመድበሽ መምጣትሽ ነው?»

«እንዴታ!»

ደስታ ፊትዋ ላይ ተንቦገቦገ።

«ምን ክፍል ተመደብሽ?»

«ታሪክ ቀረፃና የዜና ወኪል።»

«አማራ ነሽ?»

«የለም። ኦሮሞ ነኝ።»

«ሀወኒ የሚለው ስም ግን የአማርኛ መስሎኝ ነበር።»

«በርካታ አማሮች ደግሞ የትግሬ ስም ይመስላቸዋል። ቃሉ የኦሮሚኛ ነው። 'ምኞቴ' ማለት ነው» አለችው።

እንጀራው ስላለቀ አስተናጋጆቹ ትሪውን ይዘው ሄዱ። አፍታም ሳይቆዩ በእንጀራና ወጥ ሞልተውት ተመለሱ።

«መቼ ነው ወደ ትግል የገባሽው?» ሲል ጠየቃት።

«ቆየሁ»

«ከውጪ ነው የመጣሽው?»

«የለም። ጎንደር መምህር ነበርኩ። በቀላል ነገር አመት ሲያስሩኝ አኩርፌ ኰበለልኩ። ሀሳቤ እንኳዋ ወደ ሱዳን ማለፍ ነበር። በአጋጣሚ





የህወሀት ሰራዊት ያዘኝ። የመጀመሪያ ቀን ማን እንዳናገረኝ ታውቃለህ? - ሀየሎም ነበር።»

«አሃ» አለ ወዲ አስመራ «... ሰሞኑን ሲያወራልን የነበረው ለላንቺ ኖሮዋላ! በጣም ያደንቅሻል። ቅን ናት ሲል ነበር።»

«እውነት?»

ፊትዋ ባንዴ ቀላ። በሀሴት ሞቀች። እስዋ በሌለችበት ሀየሎም ስለርስዋ ያወራውን መስማትዋ ልዩ ደስታ ፈጠረላት። በዚያ ስሜት ታወጋው ጀመር፣

«ይገርምሀል... ወደ በረሀ ከመውጣቴ በፊት የሀየሎም ስም ለኔ አዲስ አልነበረም። ጎንደር ሆኜ ስለርሱ ሲነገር እሰማ ነበር። ወደ ኢህአዴግ ነፃ መሬት እንደገባሁ መጀመሪያ ያገኘኝ ታጋይ ወደ ሀየሎም ሲያቀርበኝ ያ ስመ - ገናና ሰው የዚህ አይነት ቅርፅና መልክ ይኖረዋል ብዬ ጨርሶ አላሰብኩም ነበር። እኔ ስደርስ አንዲት ጎጆ ውስጥ ጋቢ ለብሶ ፊልም እያየ ነበር። ጅንን ሰው ነበር የጠበቅሁት። ሀየሎም ለሰላምታ እጁን ሲዘረጋልኝ እሱ ይሆናል የሚል አሳብ ውስጤ አልነበረም። ጨበጥኩት። ቁጭ በይ አለኝ። ቁጭ አልኩ።

'ስምሽ ማነው?'

'ሀወኒ?'

'የኔ ደግሞ ሀየሎም'

ሰውነቴ ውስጥ የኤሌክትሪክ ሞገድ የተለቀቀ ያህል ነዘረኝ።

'አንተ ነህ ሀየሎም?' ብዬ ጮህኩ።

እሱም በሁኔታዬ ደንገጥ አለ።

'ምነው?' አለኝ።

'ስምህ በጣም ገናና ነው። ብዙ ሰዎች ያደንቁሀል። ወታደሮች ደግሞ ይፈሩሀል' አልኩት።

ሀየሎም ብዙ ስሜት አልሰጠውም። በግራ እጁ ጢሙን እያፍተለተለ ቆየና፣ 'በድንበር አካባቢዎች በብዛት ስለተንቀሳቀስኩ ይሆናል ያን የመሰለ ታሪክ የሰማሽው። በተረፈ የኔ አስተዋፅኦ ከሌላው ተጋዳይ የተለየ አይደለም' አለኝ። ከዚያም ታሪኬን እንደዋዛ ጠየቀኝ። የትምህርት ደረጃዬን፣ ስለቤተሰቦቼ፣ ስለፖለቲካ ዝንባሌዬ አስረዳሁት። በመጨረሻ ፍላጎቴ ምን እንደሆነ ማወቅ ፈለገ። ቢቻል ወደ ጀርመን ለመሻገር እንደምፈልግ ስገልፅለት፣

'ጀርመን ምን ተደርጊያለሽ?' ሲል ጠየቀኝ::

የልጅነት ፍቅረኛዬ እዚያ መኖሩን ስነግረው ራሱን ላይ ታች ነቀነቀና 'አይዞሽ በሰላም ያሰብሽው ቦታ ትደርሻለሽ' ብሎ አፅናናኝ:: በነጋታው ቁርስ ላይ ጠራኝና አብረን በላን:: ረጅም ሰአት የፈጀ ቁርስ ነበር:: ሀየሎም ስለትግሉ ያብራራልኝ ጀመር:: ታሪክ ፀሐፊ የመሆን ፍላጎቴ ከፍተኛ ስለነበር ጥያቄ አበዛሁበት:: ያለመታከት አብራራልኝ:: የግል ታሪኩን በተለይ ደጋግሜ ጠይቄው ነበር:: የዚያን አይነት ጥቂዎችን ይዘላቸዋል:: እኔ ደግሞ የግል ታሪኩን ነበር የበለጠ ለመስማት የጉዋጉዋሁት... በእምነት ደረጃም ታሪክ በግለሰቦች በኩል ቢፃፍ የበለጠ የተዋጣ ይሆናል ብዬ ነው የማምነው:: ሀየሎም በአብዛኛው ስለኢትዮጵያ ህዝብ ነበር የሚያወራልኝ:: ተዋረድን፣ ደኸየን፣ የሚሉ ቃላት ነበሩት:: ሲናገር የፖለቲካ ሰው አይመስልም:: ድህነት መጥፋት አለበት፣ መዋረድ የለብንም፣ መሰደብ፣ መገደል፣ አይገባንም የሚል ነገር ደጋግሞ ይናገር ነበር:: ወደድኩት:: በጣም ወደድኩት:: ምሳ ሰአት እንደምንገናኝ ነግሮኝ ይሄዳል:: የሀየሎምን ወሬ ለመስማት በጉጉት ነበር ምሳ ሰአትን የምጠብቀው:: የዋለበት ውሎ ሲመለስ 'ሀወኒ' ብሎ ሲጣራ የማነበውን ወርውሬ በርሬ ነበር የምወጣው:: በአስራምስተኛው ቀን ነው መሰለኝ 'ወደ ሱዳን የሚሄድ መኪና ተገኝቶአልና ነገ ማታ ስለምትጉዋገር ተሰናጂ' አለኝ:: ልቤ ለሁለት ተከፈለ:: ጥቂት ቀናት መቆየት ፈለግሁ:: በርግጥ ፈርቼ ነበር:: ጦርነት ቢነሳ እሞታለሁ የሚል ስጋት ነበረኝ:: በሌላ በኩል ደግሞ ሱዳን ጨለማ ሆኖ ታየኝ:: ሱዳን ምን እንደሚገጥመኝ ጨርሶ አላውቅም ነበር:: ሆኖም ለመሄድ ወሰንኩ:: በነጋታው እቃዎቼን በትንሽ ሻንጣ አሰናድቼ ለጉዞ ተነሳሁ:: መኪናው ይመጣል ከተባለበት ሰአት ቀደም ብሎ ሀየሎም አስጠራኝ:: ያቺን ደቂቃ በህይወቴ ሙሉ አልረሳትም:: 'መሄድሽ ነው?' ሲል ጠየቀኝ::

'አዎን'

ትክ ብሎ ሲያየኝ ቆየና፣

'መልካም ጉዞ እመኝልሻለሁ:: ካርቱም እንደደረስሽ መሐመድ ኡስማን የሚባል ሰው ይቀበልሻል:: ያሰብሽው ሁሉ እስኪሞላልሽ ድረስ ይንከባከብሻል' አለኝና ለስንብት እጁን ዘረጋልኝ::

እንባዬ ሳላውቀው በአይኔ ግጥም ብሎ ሞላ:: ሀየሎምን መለየት ከባድ ነበር:: ሩህሩህ ሆኖ ነበር ያገኘሁት:: የዘረጋልኝን እጁን ስጨብጠው 'ሀሳብሽን ከለወጥሽና ለመታገል ልብሽ ከፈቀደ በእልልታ እንቀበልሻለንና ሳታመነቺ ተመለሺ' አለኝ:: ስሜቴን ፈራሁት:: 'ቅሪ' ቢለኝ እቀር ነበር:: ግን ሳይለኝ ቀረ:: እድሉን ሙሉ በሙሉ ለኔ ተወልኝ:: የዘረጋልኝን እጁን እንደጨበጥሁ ቆየሁ::: 'ቻው ሀወኒ -





አልረሳሽም' አለኝ::

እንባዬን እየጨማመቅሁ ሀየሎምን ትቼ ቆሞ ወደሚጠብቀኝ ማርቸዲስ የጭነት መኪና በረርኩ:: በመንገድ ላይ ታጋዮቹ በጣም ተንከባከቡኝ:: ሱዳን ወይም አውሮፖ ከመኖር መታገል የበለጠ እንደሚያስደስት እየነገሩኝ ካርቱም ገባን::

'ሀየሎም ለምንድነው እንድታገል አጥብቆ ያልጠየቀኝ?' በሚል ጥያቄ ራሴን ማሳበድ የጀመርኩት ወዲያው ነበር:: ምናልባት በስነልቦና ደረጃ ለትግል እንዳልተዘጋጀሁ ተረድቶ ይሆን? ከራሴ ከውስጥ በመነጨ ፍላጎት ለትግል ካልወሰንኩ ውጤትማ ልሆን እንደማልችል አምኖ ይሆን? ብዬ ደግሞ አሰባለሁ:: በተከፋፈለ ልብ ነበር ካርቱም ኢህአዴግ ጽህፈት ቤት የሰነበትኩት:: በሁለተኛው ሳምንት ግን ሀሳቤን ለወጥኩና ወደ ትግራይ ተመለስኩ:: አመጣጤ ለመታገል አልነበረም:: ድርጅቱ የሚፈቅድልኝ ከሆነ የጦርነቱን ታሪክ ለመጻፍ ብቻ ለመጠየቅ ነበር:: መጣሁ:: ጠየቅሁ:: ተፈቀደልኝ:: ደስታዬ ወሰን አጣ:: ምናልባትም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተወደደም ተጠላም ግዙፍ ስፍራ የሚይዘውን ይህን የጦርነት ታሪክ ለመፃፍ እድል ማግኘት አስደሳች ይመስለኛል:: ድርጅቱ በጀት መደበልኝ:: ታጋዮች ከሚመገቡት የተሻለ ምግብ ጭምር ለኔ ተፈቅዶ ነበር:: ከወታደራዊ ምስጢሮች በቀር ማንኛውንም ዶክመንት እንድመለከት ታዘዘ:: ብዙ ታጋዮችን አነጋገርኩ:: የህወሀትና የኢህዴንን ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ ወታደራዊ መሪዎች፣ እውቅ ተዋጊዎችን ሁሉ አገኘሁዋቸው:: ከአንዳንድ የሻዕቢያ ሰዎች ጋር ጭምር ተዋወቅሁ::

ከአራት ወራት በፊት ጀምሮ ግን በከባድ ችግር ውስጥ በጀግንነት በሚያልፉ ታጋዮች ፅናት መቅናት ጀመርኩ:: ራሴን መናቅና መታዘብ አመጣሁ:: ግን እዋልል ነበር:: በዚህ መካከል ክሳድ ግመል ላይ በአይሮፕላን ድብደባ ቆሰልኩ:: እድሜ ለደርግ በአይሮፕላኑ ድብደባ ጠንካራ ታጋይ ሆኜ ወጣሁ:: እያንዳንድዋ ደርግ የሚፈፅማት ግፍ ታጋዮችን እንደምትወልድ! አመፀኛ ልቦችን እንደምታፈራ ጭምር ተገነዘብኩ:: ይህ ትልቅ ትምህርት ነበር - ለኔ» ብላ በረጅሙ ተነፈሰች::

ከራት በሁዋላ ሻይ በኩባያ መጣላቸው:: የኩባያው ክፈፍ ከንፈርዋን ስለለበለባት እንዲቀዘቅዝላት አስቀመጠችው::

«እዚህ ምን ስራ ላይ ነው ምድብህ?» ስትልም ወዲ አስመራን ጠየቀችው::

«የመረጃ ስራ ነው የምሰራው» ካለ በሁዋላ «... በነገራችን ላይ እኔ በአግአዚ ኦፕሬሽን ከመቀሌ እስር ቤት ካመለጡት መካከል ነኝ:: ስለኦፕሬሽኑ ሰምተሻል?» ሲል ጠየቃት::

«ጫፍ ጫፉን» አለች፡፡

«የማይታመን የጀግንነት ተግባር ነው የተፈፀመው፡፡ ከፃፍሽ ከሱ ብትጀምሪ ይሻልሻል፡፡»

«በሀየሉም በኩል የትግሉን ታሪክ መዳሰስ ነው ፍላጐቴ» አለችው፡፡

ወዲ አስመራ በመቃወም ራሱን ግራቀኝ ናጠ፡፡

«ትግሉ የህዝብ ታሪክ ነው፡፡ የህዝብ ቁጣ ነው፡፡ ሀየሉምን ህዝቡ ነው የወለደው፡፡ ስለዚህ ትግሉን በግለሰብ በኩል መግለፅ ህዝባዊነቱን ያኰስሰዋል» ሲል አስተያየት ሰጠ፡፡

«ሀየሉምን ህዝቡ ነው የወለደው? ምን ማለት ነው ይኸ? ህዝቡ ሀየሉምን ጀግና ሁን ብሎ መረጠው? ወይስ ሀየሉም በተፈጥሮው ሩህሩህና ጀግና ነበር? ብቻ ይህ ርዕስ ጉዳይ አከራካሪ ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን ታሪክ የግድ በአንድ መንገድ ብቻ መገለፅ ያለበት አይመስለኝም» አለች፡፡

«ሀየሉምን ማእከል ካደረግሽ ስለትግሉ የተዛባ ግንዛቤ ነው የምታስተላልፊው፡፡ ሀየሉም የህዝብ ሀብት ነው፡፡ ለዘልአለም በልባችን፤ በወደፊቱ ትውልድ አእምሮም የሚኖር ቅርስ ነው፡፡ ቢሆንም...» ከማለቱ

«ሀወኒ!» የሚል የጥሪ ድምፅ በጨለማ ውስጥ ተሰማ፡፡ በድምፁ አወቀችውና ከተቀመጠችበት ብድግ አለች፡፡

«እዚህ ነኝ ሀየሉም» ማለት ፈልጋ ነበር፡፡

አቃታት ...





# ደንስ ጀግና!

# ክራቫትክን አውልቅና!

## ምእራፍ አምስት

### - 1 -

«እንደምን ከረምክ ልጄ?»

«ጤና ይስጥልኝ አባቴ ...»

«ተመልሰህ መጣህ ማለት ነው? ችግር ገጠመህ?»

«ችግር አልገጠመኝም አቦይ» አለ ወጣቱ ሰው፡፡ «አንድ የሚያስተላልፉልኝ አስቸኳዋይ መልእክት አለ፡፡ የታሰረው ወዳጃችን ከእስር ቤት ያመልጥ ዘንድ መሞከር ያለብን ይመስለኛል፡፡ ምናልባት ለዚያ የምታገለግል አንዲት እጅግ ጠባብ ቀዳዳ ታይታኛለች፡፡ ይህን

«ጫፍ ጫፋን» አለች።

«የማይታመን የጀግንነት ተግባር ነው የተፈፀመው። ከፃፍሽ ከሱ ብትጀምሪ ይሻልሻል።»

«በሀየሉም በኩል የትግሉን ታሪክ መዳሰስ ነው ፍላጐቴ» አለችው።

ወዲ አስመራ በመቃወም ራሱን ግራቀኝ ናጠ።

«ትግሉ የህዝብ ታሪክ ነው። የህዝብ ቁጣ ነው። ሀየሉምን ህዝቡ ነው የወለደው። ስለዚህ ትግሉን በግለሰብ በኩል መግለፅ ህዝባዊነቱን ያኮስሰዋል» ሲል አስተያየት ሰጠ።

«ሀየሉምን ህዝቡ ነው የወለደው? ምን ማለት ነው ይኸ? ህዝቡ ሀየሉምን ጀግና ሁን ብሎ መረጠው? ወይስ ሀየሉም በተፈጥሮው ሩህሩህና ጀግና ነበር? ብቻ ይህ ርዕሰ ጉዳይ አከራካሪ ነው። ዞሮ ዞሮ ግን ታሪክ የግድ በአንድ መንገድ ብቻ መገለፅ ያለበት አይመስለኝም» አለች።

«ሀየሉምን ማእከል ካደረግሽ ስለትግሉ የተዛባ ግንዛቤ ነው የምታስተላልፊው። ሀየሉም የህዝብ ሀብት ነው። ለዘልአለም በልባችን፤ በወደፊቱ ትውልድ አእምሮም የሚኖር ቅርስ ነው። ቢሆንም...» ከማለቱ

«ሀወኒ!» የሚል የጥሪ ድምፅ በጨለማ ውስጥ ተሰማ። በድምፁ አወቀችውና ከተቀመጠችበት ብድግ አለች።

«እዚህ ነኝ ሀየሉም» ማለት ፈልጋ ነበር።

አቃታት ...





# ደንስ ጀግና!

# ከራቫትከን አውልቅና!

## ምእራፍ አምስት

### - 1 -

«እንደምን ከረምክ ልጄ?»

«ጤና ይስጥልኝ አባቴ ...»

«ተመልሰህ መጣህ ማለት ነው? ችግር ገጠመህ?»

«ችግር አልገጠመኝም አቦይ» አለ ወጣቱ ሰው። «አንድ የሚያስተላልፋልኝ አስቸኳይ መልእክት አለ። የታሰረው ወዳጃችን ከእስር ቤት ያመልጥ ዘንድ መሞከር ያለብን ይመስለኛል። ምናልባት ለዚያ የምታገለግል አንዲት እጅግ ጠባብ ቀዳዳ ታይታኛለች። ይህን

ልጠቁማቸው ፈልጌ ነው።»

«መልካም። በል መልእክቱን ግለዕልኝ።»

ለግማሽ ሰአት ያህል ረጋ ብሎ ተናገረ።

«አቦይ!! ይዘውታል የተናገርኩትን?»

«አንዲት ቃል አትጉድልም ልጄ! እንዳለች ነገ ተሰያት አስመራ ትደርሳለች።»

«አመሰግናታለሁ።»

«ለሀገራችን ነው ልጄ ...»

«ሌላም አጭር መልእክት ልጨምርልዎ»

«ትችላለህ ቀጥል»

«ያቀረብኩት አሳብ ተቀባይነት የሚያገኝ ከሆነ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንዳንድ መረጃዎችን እንዳስተላልፍ አዲስ አበባ የመቆያ ጊዜዬ ሊራዘምልኝ ይገባልና ይህንኑ ጨምረው ያስተላልፉ።»

«ሻይ ይፈላልህ ታዲያ? የአገራችን ቂጣም አለ።»

«መልካም!» ብሎ ተደላደለ።

ሻይ እየጠጡ በበርካታ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ። ስለሸዋ ሰዎችና ሹማምንት ሲያወጉም በአገሪቱ ላይ የስንፍና ባህል እጅግ መንሰራፋፋቱን አንስተው ተነጋገሩ።

- ህዝቡ ተስፋ በማጣቱ መጠጥ ለምዶአል። ከእኩለ ቀን በሁዋላ ወደ አረቄና ጠላ ቤት የሚጉርፈው ወጣት ቁጥር ጥቂት አይደለም። ሰዎቹ ሙያ አይማሩም። ጥረው ተጣጥረው ኑሮአቸውን አያሸንፉም። ባለስልጣኖቹ ሀገራቸውን አይወዱዋትም። እነርሱ ራሳቸው የማያፈቅሩዋትን ሀገር ሌላው ይወድላቸው ዘንድ ግን በራዲዮ ይናገራሉ። ሌላው ሁሉ ቀርቶ ለባንዲራቸው ፍቅር የላቸውም። ባንዲራ ያለበት ጥበብ ልብስ ቢሞቱ አይለብሱም። የአሜሪካ ባንዲራ ያለበትን ከናቴራ ግን ይለብሳሉ። በዚህ ላይ የምቀኝነት ባህል ስር ሰዶአል። ጎረቤቶች ርስበራስ ይሰዳደባሉ። ልብስ ማጠብ አይወዱም። ሹማምንቱ ዘመዶቻቸውን ብቻ ስራ ያስገባሉ። ያስፈራራሉ፤ ይዋሻሉ፤ አይማሩም፤ ሰው ይንቃሉ፤ ቤተክርስቲያን አይሄዱም፤ ሹማምንቶች እግዚአብሄርን ስለማይፈሩ ሰውን ከፍየል ለይተው አያዩትም - ያርዱታል። መንገዶቹ ሰገራ ብቻ ናቸው። ዛሬ ቢጠረግ ነገ ያው ነው። ወጣቶቹና ጎልማሶቹ ጫት ያኝካሉ። የውሃ እጥረት የለም። ልምላሜ ግን አይታይም። ሌላው ቀርቶ ዛፎችን ይቆርጣሉ እንጂ





መልሰው መትከል የሚባል ነገር አያውቁም። አቡዋራው እየተነሳ ሰውን ያለብሰዋል። ዛፍ ተክለው ቢሆን ኖሮ ግን ከአቡዋራው በዳኑ ነበር። ሀይቆቹ ውስጥ አሳ ሞልቶአል። የሚያጠምዳቸው ግን የለም። ይልቁን ህዝቡ አቡዋራ አቡዋራ የሚል ሽሮ ሲያንተከትክ ይውላል። ድህነቱ ልክ የለውም። እርሳስ እየሰበሩ ተካፍለው የሚማሩ ወንድማማቾች ይበረክታሉ። ማቲዎች ምሳቸውን ባቁላ ይቆረጥማሉ። ሀብታሞች ደግሞ እብሪተኞች ናቸው። ሰራተኞቻቸውን ይደበድቡዋቸዋል። ስለራሳቸው ረጅም ሰአት በመለፍለፍ ጊዜያቸውን ያሳልፋሉ። በዚህ ላይ ቦርጫም ናቸው። ጥሬ ስጋ ይወዳሉ። ሆዳቸው የእርጉዝ በግን ይመስላል - ይህን አስከፊ ሁኔታ የፈጠረውም የፊውዳሎቹና አምባገነኑ ስርአቶች ናቸው- ተባባሉ።

ከዚያም የሻእቢያ እንቅስቃሴ ተነሳ።

- ዲፕሎማሲያዊ ስራው ተጠናክሮአል። የኤርትራ ወጣቶች መስዋእትነት በአለም ላይ ወደር የማይገኝለት ነው። የኤርትራ ነፃነትም የማይቀር መሆኑን ማንም ተገንዝቦታል -

እቦይ ግርማፅዮን በመጨረሻ ስለ ፍረወይኒ ሳያነሱ አላለፉም ...

«ፍረወይኒ ባልዋ በመንግስት ወታደሮች ከተገደለ ወዲህ በህይወትዋ ደስተኛ አልነበረችም። አንድ ቀን ልጅዋን ወደ በረሃ ለመላክ ወስና አማከረቺኝ። 'ወደ እንጦጦ ይሂድ! እዚህ ምን ይሰራል? ሁላችንም ከተሰደድንማ ለወራሪዎቹ ሰርግ ነው። ኤርትራ ባዶዋን ቀረች። ወዲ አፍወርቂ ... እዚ,ወደይ ... ከመይ ጌሩ ይእዘበና ... ንህና ሀማቃት ... ክብድና ፈተና ... ነግራማት ... ንህናዶ ኤርትራውያን ኢና? ምሽክናይ እዚ,ወደይ ... እዚ ጅግና ወዲ ኤረ ... ጥራይ ኢዱ ፈቀዶ በረኻ ክርተት ይብል?' እያለች ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች። አስናናታለሁ! አቆጣታለሁ! ወይፍንከች!

«አንድ ቀን ደግሞ ከምሽቱ አራት ሰአት መጣች። ብቅስል ጋቢ ለብሳ በር ላይ ቁማ ስማዩን ታያለች። 'ፍረወይኒ ምንሆንሽ?' አልኩዋት 'ና ተመልከት' አለችኝ ወደ ጨረቃዋ እያመለከተችኝ። የጨረቃዋ ዙሪያ ደም ለብሶ ነበር። 'እዛምጀጋኑ!' ብላ እንባዋ እየወረደ 'ተመልከት ወንድሞቻችን እየተዋጉ ነው። ጨረቃዋ የምትደማው ጀግኖቹ የማይታመን ጀብድ ሲፈፅሙ ነው። ተመልከት የሚረጨውን ደም!' ብላ ጦርነቱ በቀጥታ የሚታያት ያህል የፍልሚያውን ሁኔታ ትነግረኛለች።

«ስለ ወገኖቻችን ወሬ የምትሰማበት ምንም መንገድ ስላልነበረ

የጨረቃን፤ የጉጉትን እንቅስቃሴ፤ የከዋክብትን ሁኔታ እያየች ትግሉ የደረሰበትን ሁኔታ ትተነብያለች። በወቅቱ ሬዲዮ አልነበራትም። እንዳልኩህ ይህ በሆነ በሶስተኛው ቀን በተመሳሳይ ሰአት መጣችና ልጅዋን በረሃ ለመላክ መወሰንዋን ነገረችኝ። ብቸኛ ስለሆነች ረዳት ደጋፊ ያስፈልጋታል። ልጅዋ ጉንዋ ቢሆን ይሻል ነበር። ግን ይህን አልነገርኩዋትም። ስሜትዋን ሳበላሸው አልፈለግሁም። ከማበረታታትም ተቆጠብኩ። ከጡት መያገርዋ ስር የተጣጠፈ ወረቀት አውጥታ 'ይህ ደግሞ ለኢሳይያስ የፃፍኩት ደብዳቤ ነው' አለችና ታነብልኝ ጀመር። ደብዳቤው እኔንም አስለቀሰኝ። የዋህዋ ፍረወይኒ ለወዲ አፍወርቂ በፃፈችው ደብዳቤ እስዋ ያልመጣችው በጨጉዋራ በሽታ ስለምትሰቃይ መሆኑንና በዚህ ሁኔታ ላይ ሆና ብትመጣ ሸክም እንደምትሆን ተንትናለች። አያይዛም ልጅዋን መላክዋን በወኔ ገልፃለች። በመጨረሻም 'ማርያም አስመረይቲ ትከተልኩም!' ብላ ደምድማለች። 'ጥሩ ነው' አልኩዋት። ተደሰተች። መልእክት ካለኝ ከስሩ ቦታ ስላለው እንድጨምርበት ነገረችኝ። ራስሽ ጨምሪበት አልኩዋትና 'ኤርትራውያን ሁሉ ሰላምታቸውን ያቀርቡልሃል' የሚል ቃል አከለችበት። ከዚያ አመስግናኝ ሄደች።

«እንደምኞትዋ ልጅዋን ወደ በረሃ ላከችው።

«ይህም ሁኔታ በአካባቢው መወራት ሲጀምር በአጋጣሚ እኔም ወዲህ ወደ ደብረዘይት ለመምጣት ዝግጅት ላይ ስለነበርኩ ብቻዋን ከምትሆን ብዬ ይዤያት ወደዚህ መጣሁ። እዚህም አልቀረላት። በየለቅሶው፤ በየሰርጉ ስለኤርትራ ጀግኖች እያነሳች ስትንሾካሾክ አንድ ወታደር ጠቁሞባት ተያዘች። ብትክድ ምናለበት 'ወንዶች ከሆናችሁ ጀግኖቹ ወንድሞቼ ወዳሉበት ሳህል ሂዱ። እኔማ በጨጉዋራ በሽታ የምሰቃይ ደካማና ብቸኛ ሴት ነኝ። ባሌንም ገደላችሁት። እኔንም ግደሉኝ። ልጄን ግን አታገኙትም። ከጀግኖቹ ጋር በረሃ ነው' እያለች ስትጮህ፤ ገደሉዋት።

«አሙዋሙዋቱዋ እንኩዋ የጀግና ነበር። ራስዋን እንደመሳትም አድርጉአት ነበር? ፖሊሶች ግራና ቀኝ ክንድዋን ጨምድደው ይዘዋት ሲሄዱ የመንደሩ ነዋሪ ሁሉ ግልብጥ ብሎ ወጣ። የማይወዳት አልነበረም። ሁሉም 'ፍረወይኒ ወልደማርያም' እያለ በሙሉ ስምዋ ነበር የሚጠራት። በፖሊሶች ተይዛ ስትወሰድ በጩኸት ትናገር ስለነበር አንዱ ፖሊስ 'አፍሽን ዝጊ! አንቺ ሰደተኛ ትግሬ!' ብሎ ጮኸባት። ሽጉጥ መዞ ሊያስፈራራት ሞከረ። ፍረወይኒ መች ተበገረች ታዲያ። በአማርኛ 'ስሙኝ ወገኖቼ! አዎን ስደተኛ ነኝ!' እያለች ትጮህ ጀመር 'ግን ለምን መሰላችሁ የተሰደድኩት? ወታደሮች አገራችንን ወረሩት። ግን መስሉአቸው እንጂ ኤርትራን እንደሁ አያገኙዋትም! ወዲ አፈወርቂ ጆሮአቸውን ጨምድዶ እየረገጠ





ያስወጣቸዋል። ይህን ደሞ ባይናችሁ ታያላችሁ! ወታደሮች ከአገራችን ከወጡ ክበሮዬን እየመታሁ ወደ ሀገሬ እገባለሁ። አለምን ሁሉ የምታንቀጥቀጥ ሀገር አለችኝ። ደሞ ለእናንተስ ይህን መሬት ማን ሰጣችሁ? ይህ ምድር የኦሮሞዎች አይደለምን? እናንተ ግን ፈሪዎችና ሆዳሞች ናችሁ። ሙት ናችሁ። ልባችሁ እናትን ለመደብደብ ይጨክናል። እኔን ለመግደል ቸኮላችሁ! ጀግኖቹ ግን ሳህል ናቸው' ካለች በሁዋላ በትግርኛ ደሞ ቀጠለች '... አዘም ጀጋኑ አይሳዓሩን! አጆኻ ዝወደይ! ከምታ ዝበልኩኻ ጌርካያ!? ሕራይ ድኣ ገበርኻ! ፀባ አስቲኻኒ ሞት ከም አዳም፤ ወላኒ ኢሬትሪያ አደይ ናፃ ወፂያ እንተዘይርዓኹ ወዲ አፍወርቂ ከምዝዕወት ይፈልጥ እዩ ... አቡኡ ኻእ ፈልጦም እንድዩ ... ገዝኦም እኮ ጥቃ እንዳያ ገርንኪኤል እዩ ... ደቂ ፀሎት ኢዮም ... እዚ አንበሳ ውድና ነዞም በላእቲ! ሀመድ ጌርዎም ኢዩ። ሀመድ ትኹን አዲእዎም። ርጉማት! እወ እዚ ወደይ **... አደ ወሲዳ ትምከን ... ዓሻታት! ንአይ ቀቲልኩምሞ እንታይ ክይትረኽቡ' ስትል ሰማናት። ኤርትራውያን ተአኪብና በኺና! እንቃዪጦ ክግበር ኢልካዮ ... ፍረወይኒ ሐፍትና ሕጂ የላን ... ምኽክነይቲ ፍረወይኒ ናፅነት ኤሬትሪያ ከይራእየት ከይዳ ... ናብ ዝፈትዋ ፈጣሪ ... ፍረወይኒ ፅብቅቲ ... ፍረወይኒ ጉዋል ኤረ ...»**

አቦይ ግርማፅዮን ግምባራቸውን ጉልበታቸው ላይ ደፍተው ተንሰቅስቀው እነቡ። እንግዳውም መሀረም አውጥቶ አይኖቹን አባበሰ። ከዚያም ለደቂቃዎች በዝምታ ቆዩ። እንግዳው ሰአቱን አየ። ሊሄድ ማሰቡ ኖሮአል። ብድግ ብለው ተሰናበቱት።

«በእድሜያችን እናየው ይሆን?» ሲሉ ጠየቁት።

**«ምኑን አቦይ»**

**«ናፅነት ኤሬትሪያ?»**

**«አይቀርም አቦይ» አለ ወጣቱ ሰው አይኖቹን በመስኮት ወደ ደጅ አሻግሮ እየወረወረ «... ግን መቼ እንደሆን ከኤርትራውያን እምላክ በቀር ማን ያውቃል?»**

* * *

ቢሸፍቱ መሸች ...

ከበልበላ ወንዝ አድካሚ የመስኖ እርሻ የእለት ስራ የተለቀቁ ላባደሮች ጉዳናውን ሞልተው ወደ ጉጆአቸው ሲቸኩሉ ታዩ። ቁራዎች ወደማደሪያቸው፤ አየርወለዶች ደግሞ ወደ መጠጥ ቤቶች ተጣደፉ። ሴትኛ አዳሪዎች በበኩላቸው ሙዚቃውን በረጅሙ ለቀው የእለተ - ቅዳሜ እንግዶቻቸውን ለማስተናገድ ሽር-ጉድ የሚሉባት

ደቂቃ ደረሰች።

የአቦይ ግርማፅዮን የቀጠሮ ሰአት ጭምር ተቃረበ ...

አረንጉዋዴ ባርኔጣቸውን እናታቸው ላይ ጣል አድርገው ወደ ጉዳናው ወጡ። ልብሳቸው ንፁህ ናት። ቱር ብላ የተተኮሰች! አሮጌ ልብስ - ግን ፅዱ። ረጅም ጃንጥላቸውን እንደ ከዘራም ይጠቀሙባታል።

ወደ ቀጠሮው ስፍራ በርጋታ እዘገሙ ...

አየር ሃይል ሆቴል።

ሆቴሉ ዘወትር እንደሞቀ ነው። የአየር ሃይል አባላት በብዛት ይስተናገዱበታል። አብዛኞቹ እነርሱው ናቸው። ሲቪል ቢለብሱም የከተማው ህዝብ የአየርሃይል አባላትን በቀላሉ ያውቁዋቸዋል። ሲጀነኑ! አሊያም ከነፍሳቸው በላይ በሚያፈቅሩዋት መነፅራቸው ይለዩዋቸዋል። ለነገሩ ጢም አለሚጨታቸው - አረማመዳቸው - ህክምና ወዛቸው ሁሉ ከሌላው የቢሾፍቱ ነዋሪ የተለየ ነው። ጣቢያቸውና ገበያቸውም ልዩ ነው - መቀበሪያቸው ጭምር።

ሽማግሌው ወደ ቀጠሮው ስፍራ ተቃረቡ ...

አቦይ ግርማፅዮን ዘወትር ቅዳሜ ለአይን ያዝ ሲያደርግ አየርሃይል ሆቴል ብቅ እንደሚሉ የሆቴሉ ሰዎች ሁሉ ያውቃሉ። በረንዳዋ ላይ ተቀምጠው የሚጠጡዋትም አትለወጥም - ቀጭን ሻይ። በረንዳዋ ላይ ተቀምጠው የሚጠጡዋትም አትለወጥም - ቀጭን ሻይ። ሻያቸውን እጣጥመው እንዳመጣጣቸው ለዘጠና ደቂቃ ያህል ቀጭን ሻያቸውን እጣጥመው እንዳመጣጣቸው የመልስ ጉዞ ይጀምራሉ። ታዲያ እዚያ ከሚያዘወትሩት የአየርሃይል አባላት ጋር ሁሉ መልካም ወዳጅነትን መስርተዋል። በጀ አይሉም እንጂ 'እንጋብዝዎ' የሚላቸውም አይጠፋም። ከዚህም ከዚያም መጨዋወቱን ግን ስራዬ ብለው ይዘውታል።

ከሆቴሉ ደርሰው በተለመደው ስፍራ አረፍ አሉ ...

ሆቴሉ እንደወትሮው በተስተናጋጅ አልተጨናነቀም። አሊያም የደሞዝ ጠጪው ገና መግባት አልጀመረም! ቀዝቀዝ ብሎአል። የደሞዝ ጊዜ በማለፉም ሊሆን ይችላል።

ሽማግሌው ሻያቸውን አዘዙ - ቀጭን ሻይ። ሰአታቸውን አዩ። የቀጠሮው ሰአት ሞልቶአል። እናቱ ላይ ነው። በዚህች ደቂቃ አንድ ሰው ሰላምታ ሊያቀርብላቸው ይገባል። አንድ ሰው። አንድ የሻእቢያ ሰው። አንድ የኤርትራ ምድር ሰው።

«ጤና ይስጥልኝ አቦይ ግርማፅዮን»

በትግርኛ ነበር ሰላምታ ያቀረበላቸው - ቢኒያም ኖሮአል።





መምህር ቢኒያም። የሞቀ ሰላምታ ተለዋወጡ። ቀይ ቀጭን! ፊቱ ምጥጥ ያለ! ጉልማሳ ሰው ነበር ቢኒያም። ሙሉ ጂንስ ለብሶ ነበር ...

«መልእክት አለኝ?» ሲል ጠየቃቸው።

«አዎን አለህ።»

«ደግ ነዋ! ይንገሩኝ። ዛሬ ብዙ ሰው የለም! ጥሩ ነው ...»

«አዎን። ግን ይህን ቦታ መምረጥህ መቼም እንደከነከነኝ ነው።»

ቢኒያም ፈገግ ብሎ!

«መካከላቸው ስለገባን መቼም ቢሆን አይጠረጥሩንም» አላቸው።

ከዚያም አቦይ ግርማፅዮን ግዳጃቸውን ይወጡ ጀመር ...

• ለሻእቢያ እጅግ ቀልባ፡ የሆነ አንድ ሰው አስመራ ላይ በደህንነቶች እጅ ወድቆአል። «ቦሎኛ 99» ይባላል። እሱን ለማስፈታት ይጠቅም ይሆናል በሚል የአዲስ አበባው «መረብ 72» መልእክት ማስተላለፍ፡ ፈልጉአል። ጉዳዩ እንዲህ ነው።

«ፊንፊኔ» የሚባል አንድ ሰው በቅርቡ ወደ አስመራ ይጉዋዛል። ይህ ሰው በአስመራ ቆይታው ከከፍተኛ ባለስልጣኖችና የሻእቢያ አባላት ከሆኑ እስረኞች ጋር መገናኘቱ ከቶ የማይቀር ነው። ስለዚህ «ቦሎኛ 99» ከእስር እንዲያመልጥ ይህን ሰው መጠቀም ይቻላል ብሎ ያምናል የአዲስ አበባው «መረብ 72»። ለዚህም በቂ መነሻ አለው። «ፊንፊኔ» ታማኝ የመንግስት ሰው አይደለም። ከጥቂት ቀናት ወዲህ ደግሞ ከመንግስት ጋር ወደሚያጋጨው ያልታሰበ ችግር ውስጥ በመግባት ላይ ይገኛል። ይህ ሰው ውጭ የነበረና በራሱ ፍላጎት ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰ ቢሆንም አሁን በፀፀት ላይ ይገኛል። «መረብ 72» «ፊንፊኔ»ን ለማጥመድ የሚያስችሉ አንዳንድ አሳቦች አሉኝ ይላል። ስለዚህ ከሻእቢያ ጋር በቅርቡና በአስቸኩዋይ መገናኘትና ሀሳቡን ማቅረብ ይሻል። የአዲስ አበባ ቆይታው ይራዘምለት ዘንድም ጠይቆአል።

ቢሾፍቱ ጨለመች ...

ሽማግሌው አቦይ ግርማፅዮን የሻይ ሂሳባቸውን ከፍለው አየርሃይል ሆቴልን ለቀቁ። የእለት ስራቸውን አብቅተዋል። ከዚህ ወዲያ ያለው የመምህር ቢኒያም ተግባር ነው። ቢኒያም መልእክቱን እንዴት አስመራ እንደሚያደርሰው አያውቁም። ለማወቅም

አይፈልጉም። በኤርትራውያን አይፕሮፕላን አብራሪዎች በኩል ሊሰደው እንደሚችል ግን ይጠረጥራሉ። ቢኒያምና የአዲሳባውን የሸአቢያ ድር በድልድይነት የሚያገናኙት አቦይ ግርማፅዮን ናቸው። በዚህ ታዲያ ይኩራሉ። ለሀገራቸው ይህን ያህል አስተዋፅኦ ማድረግ በመቻላቸው ደስታቸው ወሰን የለውም።

ተግባራቸውን በተገቢው መንገድ አከናውነው የሆቴሉን ግቢ በለቀቁባት ደቂቃ አምስት ያህል የአየር ወለድ መኮንኖች በአውቶ ጂፕ ታጭቀው ወደ ሆቴሉ ግቢ ዘለቁ።

ዛሬ ቅዳሜ ነው ...

መኮንኖቹ ቅዳሜን እንደዋዛ አሳልፈዋት አያውቁም። ምርጥ ልብሶቻቸውን የሚጠቀሙት ዛሬ ነው። ከዚያም በሰበብ አስባቡ በሚጭቀው ያገኙትን ገንዘብ እየመነዘሩ ዊስኪ ጠርሙስ ውስጥ ይዋኛሉ። የሴትኛ አዳሪዎች ጭን ውስጥ ይዋኛሉ። የቢሾፍቱ ጨለማ ውስጥ ይዋኛሉ።

ቅዳሜ የዋና ሌሊት ናት ...

## - 2 -

ከውጫሌ ወደ መርሳ በሚያመራው ጉዳና ላይ አንድ የሙስሊም ቆብ የደፋ ነጋዴ ግራ ጉንጩን በጫት እንደወጠረ ስምንት እህዮች እየነዳ ይገሰግሳል። ውርጌሳ አካባቢ ያሉ ኩረብቶች የኢትዮጵያ መንግስትና አማፅያኑ የማይቆጣጠሩዋቸው ፈሪ መሬቶች ናቸው። ከውጫሌ ወደ መርሳ ነጋዴዎች እቃ ጭነው እንዲያልፉ ባይፈቀድላቸውም ጉቦ እየሰጡ ማለፋቸው አልቀረም። ቢሆንም ይኸ እጅግ አልፎ አልፎ የሚፈፀም ነው። ያውም በእኩለ ሌሊት ...

ይህ ሙስሊም ነጋዴ ግን እጅግ ተዳፍሮአል። ስኩዋርና ኒያላ ሲጋራ ይዞ ተስያቱን ሙሉ በጉዳናው ላይ ገስግሶ ኬላ ላይ ደረሰ። ኬላ ጠባቂ ወታደሮች የገዛ አይናቸውን ማመን አቃታቸው። እንዲህ ያለ ቀበጥ ነጋዴ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅ።

ስምንት እህያ!?

የኬላው አዛዥ 'ራሱ ነጋዴው ዘጠነኛ ወደል እህያ መሆን አለበት' እያለ ነበር ወደነጋዴው የተጠጋው።

«ቁም!» ሲል አምባረቀበት።

ነጋዴው እህዮቹን ማቆም አልቻለበትም። ተክለፈለፉበት። ከፊታቸው ሄዶ ሊያቆማቸው ሲቃጣ ወደ ግራና ቀኝ እየተበታተኑ አስቸገሩት።





«ጤና የለህም ... አንተ ኩስ!»

ነጋዴው እህዮቹን ትቶ ባለበት ቆመ። የጉማ አለንጋውን እየወዘወዘ ወታደሩ እስኪጠጋው ጠበቀ።

«ወዴት ነው የምትሄደው!?» ሲል በቁጣ ጮኸበት።

የኬላው አዛዥ የአስር አለቅነት ማእረግ ከንዱ ላይ የሰፈረ ወጣት የበታች ሹም ነበር።

ነጋዴው ግን ጨርሶ ስጋት አልታየበትም፣

«አስር አለቃ ጫካ ማለት አንተ ነህ?»

«ነኝ! ምንድነው የፈለግከው?»

ስሙ በመጠራቱ መደንገጥ ብቻ ሳይሆን በዚያች ቅፅበት ብዙ ነገሮችን ገመተ። አዎን ይኸ ነጋዴ የአንዱ ሹም ቅጥረኛ ሊሆን ይችላል! ከሆነ ደሞ ሊያሳዝዘው ይችላል። ምናልባትም 'ኩስ!' ብሎ መሳደቡ ያስቀጣው ይሆናል?

«መልካም! ብቻህን ላነጋግርህ እችላለሁ?»

«ደህና!» አለና ገንጠል አለ ከነጋዴው ጋር።

ነጋዴው ከደረት ኪሱ የተጣጠፈች ወረቀት አውጥቶ አሳየው። ወጣቱ የበታች ሹም ከቀዳሚ መምሪያው በቀጥታ በስሙ የተፃፈለትን ደብዳቤ በአንድ ትንፋሽ ከጠጣው በሁዋላ፣

«ይቅርታ ጌታዬ ... በመሳደብ ክብርዎን ዘለፍኩ! አሁን የፈለጉትን ሊያዙኝ ይችላሉ» ብሎ እጅ እንደመንሳት አለ።

ነጋዴው ጫቱን እያላመጠ ያንሾካሹክለት ጀመር፣

«ወታደሮችህ ማወቅ የለባቸውም። የንግድ ፈቃድ ያለኝ ነጋዴ መሆኔን ብቻ ነው የምትነግራቸው፤ ገባህ?»

«ገባኝ ... ተረድቼያለሁ ጉዋድ!»

«ጉዋድ የሚለውንም ተወው ...»

«እሺ ጌታዬ ...»

«ጌታዬም አያስፈልግም።»

«ተቀብያለሁ!» ብሎ በተጠንቀቅ ቆመ።

«መጠንቀቅም አያሻህም ... ዘና በል።»

«አይሆንልኝም ...» ብሎ እጆቹን የሚያሳርፍበት ጠፋው።

ነጋዴው ሳቀ:: አህዮቹን እየነዱም ኬላው ላይ ወዳሉት ወታደሮች አመሩ:: ለጠባቂዎቹ ወታደሮች ሰላምታ ካቀረበላቸው በሁዋላ፤

«ነጋዴዎች የሚንቀሳቀሱበት ሰአት ይታወቃል?» ሲል ጠየቃቸው::

«ሲመሽ ነው!» አለ ወጣቱ የበታች ሹም «... በዚህ መንገድ መቼም አይሞክሩዋትም:: በረሃ በረሃውን ነው እያሳበሩ የሚሄዱት::»

«በጉዳናው አያልፉማ!?»

«ጨርሶ!»

ነጋዴው በሀሳብ ተዋጠ:: እሱ ጉዳናውን ይዞ የሚሄድ ከሆነ በቀላሉ ጥርጣሬ ውስጥ ይወድቃል:: ይህም አደገኛ ሙከራ ነው::

«ወያኔዎች ከዚህ ምን ያህል ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ናቸው?»

«ሶስት ቢሆን ነው:: ከዚያ አይበልጥም::»

«ይተናኮላሉ?»

«እንዲያውም! ለነሱማ ሲሳይ ነው:: ነጋዴዎች እንዲመላለሱላቸው ይፈልጋሉ:: ቢሆንም ግን ይፈትሻሉ:: ፍተሻቸው ጥብቅ ነው ይባላል::»

«ነጋዴዎች የሚመላለሱባቸው መስመሮች በየት በኩል ናቸው?»

«በጡሃ መውረጃው ነው:: ጨረቃ ሳትወጣ አድብተው ነው የሚያልፉት:: እንደዛቸዋለን እኮ! መንገድ ስተው እርሻው ላይ ብቅ ሲሉ ከእጃችን ይገባሉ:: የወያኔ ነጋዴዎች ከሆኑ ታዲያ ይታኮሳሉ:: እጃቸውን አይሰጡም:: ከቻሉ ይዘው ሊሸሹ ይሞክራሉ:: ካልሆነላቸው ጥለው ያመልጣሉ::»

«ሀየሎም የሚባለውን የወያኔዎች መሪ ታውቁታላችሁ?» ሲል እንደዋዛ ጠየቃቸው::

«በወሬ እንሰማለን!» አሉ ወታደሮቹ በጋራ::

«በአይን ያየውም አለ» አንዱ ወታደር ጣልቃ ገባ::

«ማነው ያየው?»

«እኔ ነኝ!» አለ አንድ ልጅ እግር ወታደር::

«የት ነው ያየኸው?»





«ቆቦ ሲደመሰስ እኔ ከተማው ውስጥ ቀርቼ ነበር::»

«ተማርከህ?»

«የለም! ተመሳስዬ ነው:: ዘመዶች ስለነበሩኝ እነሱ ሸሸጉኝ:: ሁዋላ ከህዝቡ ጋር ወጥቼ አየሁት:: ስለሱ ሲወራም ብዙ ሰምቻለሁ::»

በዚህ ጊዜ ሌላ ወታደር ጣልቃ ገባ::

«ሀየሎም በአይን ይታያል የሚባለውን እንኳዋ አላምንም! የሀሰት ይሆናል ሀየሎም ብለው ያሳዩት:: እንደሚነገረው ሀየሎም ማለት የዲያቢሎስ አጉት ነው:: እስከዛሬ ጥላውን እንጂ ስጋውን ያየ የለም:: ከማይዋሽ ሰው ነው የሰማሁት:: ሲሄድ አይታይም:: ከነ አካሉ የሚታየው ለጥቂት ሰዎች ብቻ ነው:: በተቀረ እንደ አውሎ ነፋስ እየተሽከረከረ ነው የሚዋጋው:: እንዲያውም እየተሽከረከረ ሲመጣ ወታደሮች ተኩሰው አቁስለውታል:: ከአውሎ ነፋሱ ላይም ደም ሲንጠባጠብ የማይዋሽ ሰው ባይኑ አይቶ ነግሮኛል::»

ወታደሮቹ ሳቁበት:: ነጋዴውም ፈገግ አለ:: ሌላው ወታደር ደግሞ ቀጠለ፤

«... አውሎ ነፋስ የሚባለው እንኳዋ ተራ ወሬ ነው:: ከተማ ገብቶ ከጄኔራሎች ጋር ዊስኪ መጠጣቱንና ሲወጣም ሂሳቡን ከፍሎላቸው 'ሀየሎም ነኝ!' ብሎ ወረቀት ፅፎ መሄዱ ግን ሀቅ ነው::»

«መልኩ ምን ይመስላል?» ሲል ነጋዴው አይቼዋለሁ ወዳለው ወታደር ዞሮ ጠየቀ::

«አፍንጫው የገደል ንስርን መንቆር ይመስላል:: አለባበሱ እንደ ሁሉም ወያኔዎች ነው:: አይኖቹ የደከሙ ነው የሚመስሉት:: እንደሚወራው ግን አርባ ኪሎ ሜትር ማየት ይችላል::»

ነጋዴው ፈገግ አለ፤

«አርባ ኪሎ ሜትር የት እንደሚደርስ ታውቃለህ?»

«እሱማ ሩቅ ነው:: የሚባለውን ነውኮ::»

«ታጅቦ ነው የሚሄደው?»

«እኔ ሳየው ብቻውን ነበር:: መኪና ራሱ እየነዳ ሲያልፍ ወያኔዎች 'ሀየሎም፤ ወዲ አርአያ!' እያሉ ይጠሩት ነበር:: ጠጉሩን አያበጥረውም:: የስፖርታኪያድ መለዮ ደፍቶ ነበር:: በሸራብ ላይ ሬንጀር ጃኬት ለብሶ ነው ያየሁት:: የላይ ከንፈር ጢሙ እድግ አድጎ በማጭድ ቅርፅ ተቀልምሞአል:: ሲያዩት እዚህ ግባ የማይሉት

ሰው ነው። ይሁን እንጂ ሽጉጥ አውጥቶ የሚተኩስበትን ፍጥነት በአይን ማየት አይቻልም እየተባለ ሲወራ ነበር። ሀየሎምና ኢሳያስ አፍወርቂ ቻይና ሄደው ካራቴ መማራቸውንም ህዝቡ ሲያወራ ነበር። የተማሩበትን ሂሳብ የከፈለላቸው ደሞ የሊቢያው መሪ መሀመድ ጋዳፊ ነው ተብሎ ሲወራ በጆሮዬ ነው የሰማሁት።»

«ሀየሎም ካራቴ ተምሮ ከሆነ ከመሬት ዘልሎ ዛፍ ላይ መውጣት ይችላል ማለት ነዋ?» ሲል ነጋዴው በፌዝ ጠየቀው።

ወታደሩ ግን ፌዙ ስላልገባው በቅንነት ምላሽ ሰጠ።

«እንዲያ ሲያደርግ እንኳዋ አላየሁም። ጩቤ ከአስራ አምስት ሜትር ርቀት ወርውሮ ይሰካል ሲሉ ግን ሰምቻለሁ። በሁለት እጆቹ ክንዶቹ ላይም ጥይት የሚያከሽፍ እፅ ራያዎች ቀብረውለታል። ጠዋት ጠዋት አንድ ሊትር ያልፈላ ወተት ብቻ ነው የሚጠጣው። ሌላ እህል ባፉ ንክች አያደርግም። እህል ከቀመሰ መድሀኒቱ ይረክሳል ነው የሚባለው።»

ሲመሽ ነጋዴው ጉዞውን ቀጠለ።

አካባቢው አስፈሪ ነው። የጅብ ጩኸት ይሰማል። አልፎ አልፎ የጥይት ድምፅ አለ። አንድ ሰአት ተኩል ያህል እንደተጓዘ ከሁዋላው ጥላ ነገር ከብዶት ዘወር ቢል ጠመንጃ ተደግኖበታል። እየተርበተበተ ሁለት እጆቹን ወደላይ ሰቀለ፣

«ምንድነህ!?»

«ነጋዴ ነኝ!»

ሁለት ታጋዮች ተጠግተው ፈተሹት።

«በዚህ ሰአት እንዴት በፍጥነት መድረስ ቻልክ?» አለው ታጋዩ እየፈተሸው።

«ጉቦ ሰጥቼ ማለፍ ቻልኩኝ። ዛሬ አላህ ረድቶኛል።»

«ጥሩ ነዋ! ምንድነው የያዝከው?»

«ስኳርና ኒያላሲጋራ ነው።»

«ጥሩ ነዋ! መሳሪያ አልያዝክም?»

«አልያዝኩም።»

«ጥሩ ነዋ! የደርግ ወታደሮች አልተተናኮሉህም?»

«ትንሽ አስቸግረውኝ ነበር። ሁለት ጊዜ ጉኔ ላይ በሰደፍ





ደቆሱኝ። ከዚያም ለእያንዳንዳቸው ሁለት መቶ ብር ሰጠሁ።»

«ጥሩ ነዋ! ከደርግ መቼም ጥሩ ነገር አይጠበቅም። ስምህን ልትነግረኝ ትችላለህ?»

«ኑር ሰይድ።»

«ጥሩ ነዋ! እንግዲህ ብዙ አላጉላላህም። አንድ ጠርናፊዬ ያነጋግርህና ከዚያ ሸቀጥህን ባሻህ ከተማ ትሸጣለህ። ህዝቡ ስኳር በጣም ተቸግሮአል። ብዙ ዋጋ እየጫናችሁ ባትበዘብዙት ጥሩ ነው።»

ከዚያም ጉዞ ጀመሩ።

ሁለት ታጋዮች ከፊትና ከሁዋላ አጅበው ይዘውት ሄዱ። ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ጥቂት ታጋዮች ካሉበት ጎጆ ውስጥ ደረሱ። እየመራ የመጣው ሰው፣

«አህዮችህ እዚህ ይቆዩ። ምንም አትስጋ» አለው።

«ወዴት ልትወስደኝ ነው?» አለ ነጋዴው ፈራ ተባ እያለ፤

«ተከተለኝ።»

ተከትሎ ጉዞ ጀመረ። ጫቱን እያላመጠ፣ ሀሳቡን ካራምባም፣ ከቶቦም እያነሳ እየጣለ፣ ከአንድ ጎጆ በር ላይ ሲደርሱ ታጋዩ ቆም አለና በድጋሚ ፈተሸው።

«ወዴት ነው የምንሄደው?»

«ጠርናፊያችን ያነጋግርሃል።»

«ምንድነው ጠርናፊ?»

«የመጀመሪያህ ነው ወደ ነፃ መሬት ስትመጣ?»

«ሶስተኛዬ ነው» ብሎ ዋሸ።

ጠርናፊ የሚለውን ቃል አለማወቁ አናደደው። መጠየቁ ደሞ የበለጠ አበገነው። ፊቱም ገረጣ።

ታጋዩ ወደ ጎጆው ይዞት ገባ።

ሶስት ታጋዮች ሻይ እየጠጡ የሞቀ ወሬ ላይ ነበሩ። 'ኖር ኖር' ብለው እንግዳውን ነጋዴ ጨበጡት። መቀመጫም አቀረቡለት። ነጋዴው ለመረጋጋት እየሞከረ ተቀመጠ።

«ሻይ ይቀዳልህ?» አለው ልጅ እግሩ ቀጭን ታጋይ።

«እሺ ይሁን:: አላህ ያክብርልኝ::»

«መንገድ ላይ ችግር ነበር?»

«ምንም አይል» አለ - እንዳይቀባጥር እየተጠነቀቀ::

ጉጀው ውስጥ ከነበሩት ሶስት ታጋዮች አንደኛው፣

«ለመሆኑ ስለ ኢ.ህአዴግ ትግል ህዝቡ ምን አስተያየት አለው?» ሲል ጠየቀው::

«ኦ ... ህዝቡ ናፍቆአችሁዋል:: 'ኢትዮጵያ ሀየሎምን የመሰለ ጀግና የምታፈራው በምእተ አመት አንድ ጊዜ ነው' እያለ ህዝቡ ይነጋገራል:: ሀየሎምን ለማየት የማይጉዋጉዋ የለም:: ከነ ዘርአይ ደረስ፣ ከነ ሞገስ አስገዶም፣ ከነ አሉላ አባነጋ፣ ከነ አብርሃ ደቦጭ፣ በሁዋላ ሀየሎም ተወለደ እያለ ያወጋል - ህዝቡ»

«አዎን ...» አለ ታጋዩ «... እነዋለልኝ መኮንን፣ እነ አብዲሳ አጋ እነ አፄ ቴዎድሮስ፣ እነ ሀይለማርያም ማሞ፣ እነ በላይ ዘለቀ፣ እነ መለስ ተክሉ እነ ማርታ መብራሁቱ፣ እነ ጥላሁን ግዛው ... እነዚህንስ አታውቃቸውም?»

ኑር ሰይድ በጥያቄው ግር ተሰኘ:: መደናገሩ እንዳይታወቅበት ግን ፈገግ ሲል ሞከረ:: ታጋዩን ለማስደሰት ብሎ ነበር የሰሜን ስመጥር ሰዎችን ማነሳሳቱ፣

«ከትግራይ ማለቱ እንጂ ከመሳው ኢትዮጵያማ በርካታ ጀግኖች ተፈጥረዋል» ሲል ጉዳዩን ቀለል ሊያደርገው ሞከረ::

«እነ ዘርአይ የትግራይ ሰዎች ናቸው እንዴ?»

እሁንም ያልጠበቀው ጥያቄ ገጠመው::

«ማለቴ ... ትግራይና ኤርትራን ምን ለያቸው? አንድ ናቸው ብዬ ነው:: ቋንቋዋ ... ባህል ...» አለና ያሰበውን ሳያጠቃልል አቆመ::

«ፖለቲከኛ ነው የምትመስለው::»

ኑር ሰይድ አልተርበተበተም::

«ህዝቡ ሁሉ ሳይወድ ፖለቲከኛ ሆኗል» አለ ፈገግ ብሎ::

«ብዙ ሰላር ነጋዴዎች ግን ይህን ስለመሰሉ ጉዳዮች ደንታ የላቸውም::»

ኑር ዝምታን መረጠ:: ይህ ታጋይ ሆን ብሎ እየተነኩዋከሰው





መሆኑን ተረዳና ሲጋ:: ታጋዩ ቀጠለ፣

«ስለቶችህ እጅግ ራስ ወዳዶች ናቸው!»

በዚህ ድንገተኛ ንግግር አመዱ ቡን አለ:: ታጋዩ ላይ አፈጠጠ::

«እኔ ነጋዴ ነኝ:: አለቃ የለኝም::»

«ትናንት ማምሻውን ግን ስላንተ ሲያወጉ ነው ያመሹት::»

«እነማን?»

«አለቆችህ ...»

«እንዴት ... ስለኔ ... ምን ... እኔ ምንም አለቃ አላውቅም ... ምናልባት የስም መመሳሰል እንዳይሆን ...»

«አይመስለኝም:: ስላንተው ነው ይነጋገሩ የነበረው:: በርግጥ ምስጢር መጠበቅ ነበረባቸው:: አንተን ወደ እሳት ከላኩህ በሁዋላ እነሱ ዊስኪ እየገለበጡ ምስጢራቸውን ያራግፋሉ:: በጣም ቂላቂሎች ናቸው:: ግን ሀየሎም ቢገደል ትግሉ የሚቆም ይመስላቸዋል? አንተም ከንግዲህ ሌላ ድራማ ባትሰራ ይመረጣል:: ሁሉንም ያወቅነው ትናንት ማምሻውን ነው::»

መልስ አልሰጠውም:: ታጋዩ ቀጠለ ...

«... ብዙ የሚያሰጋህ ነገር የለም:: እኛ ካንተ ጋር ፀብ የለንም:: ስርአቱን ነው የምንታገለው:: አጋልጣቸውና ይህን አስቀያሚ ስራ እርግፍ አድርገህ ተወው:: እጁ በደም ለታጠበ ስርአት ለምን ታገለግላለህ?»

ለደቂቃዎች ሲተያዩ ቆዩ::

«እንግዲህ የምታደርጉኝን አድርጉ» አለ ተስፋ በቆረጠ ድምፅ::

«ምን እንድትፈፅም ነው የታዘዝከው?»

«ሀየሎምን እንድገድል::»

«ብቻህን?»

«የለም! ተባባሪዎች አሉ ...»

«ከተባባሪዎችህ ጋር የት ነበር ቀጠሮአችሁ?»

«ባንክ ቤቱ ደጃፍ ላይ እንድቆም ነው የተነገረኝ::»

«ከዚያስ?»

«ተባባሪዎች ራሳቸው መጥተው የምልክቱን ኮድ እንደሚነግሩኝ

ነው ያሳወቁኝ፡፡»

«ምንድነው የኮድ ቃሉ?»

«አውሎ ነፋስ፡፡»

«ምን ማለት ነው፤ አውሎ ነፋስ?»

«የሆየሎም የኮድ ስም ነው ...»

«ለምን ትዋሻለህ!?» ብሎ ታጋዩ በቁጣ አፈጠጠበት፡፡

ኑር ሰይድ ቅጭም ብሎ ከታጋዩ ጋር ተፋጠጠ፡፡

«ትሰማኛለህ!? እንደ ደርግ ገራፊዎች ገልብጠን ስጋህን አንተለትለውም፡፡ በእሳት አንጠብስህም፡፡ ውሃ የሞላ ጠርሙስ በሲባጐ አስረን ብልትህ ላይም አናንጠለጥልም፡፡ የገማ ውሃ ውስጥ ጭንቅላትህን ነክረን አሳርህን አናበላህም፡፡ ኢህአዴግ ይህን መሰል ድርጊት የመፈፀም ባህልና ልማድ የለውም፡፡ በቅንነት ከተባበርከን አንተም ትጠቀማለህ፡፡ በተዘዋዋሪ ህዝቡን አገለገልክ ማለት ነው፡፡ መናገር የማትፈቅድ ከሆነ ግን በግልፅ ንገረኝ፡፡ እናስገድድህም፡፡ ሆኖም ለሆዳቸው ሳደሩ አረመኔዎች ጥብቅና መቆም የሚያረካህ አይመስለኝም፡፡ ላስፈራራህ አልፈልግም፡፡ መዋሸትህን ግን አረጋግጥልሀለሁ፡፡»

ኑር ሰይድ እያመነታ ቆየ፡፡

ታጋዩ ቀጠለ ...

«የኮድ ቃላችሁን ልንገርህ?»

ኑር ሰይድ የፌዝ ፈገግታ አሳየው፡፡

«እንድነግርህ ትፈልጋለህ?»

የታጋዩ እርግጠኛነት ድንገተኛ መገረምን ጫረበት፡፡

«የኮድ ቃላችሁ 'ጥቁር ቀበሮ' አይደለም?»

የገዛ ጆሮውን ማመን አቃተው፡፡ሙሉ በሙሉ ተስፋ ቆረጠ፡፡

«ልክ ነው!» ሲል ተነፈሰ፡፡

«በል ቀጥል ... አንዲትም የተሳሳተ መረጃ አልሻም፡፡»

ኑር ሰይድ ይናዘዝ ጀመር፡፡

በመጨረሻም ታጋዩ በመርካት ፈገግ አለና፣

«አሁን በቅጡ እንተዋወቅ፣ እውነተኛ ስምህን ንገረኝ» አለው፡፡





«ሳህሉ ባንትይርጉ» አለ፡፡

«ሀየሎም እባላለሁ፡፡»

- 3 -

አኖሌ ጉዞውን ወደማያውቃት አስመራ ተያይዞታል - በአይሮፕላን፡፡ 'አስመራ - ትንሽዋ ሮማ' ሲባል ሰምቶአል፡፡ ጥቂትም አንብቦአል - ስለውበትዋ፡፡ ጂብሪልም አዳንቆ አውግቶታል፡፡ ከፀጋዬ ገብረመድህን ቅኔዎች ቀንጭቦ ጭምር በቃሉ አነብንቦለታል፡፡

«ምነው ሁሉ እንዳንቺ አስመራ ... እንደ ከተሞች መዲና ... አቀያየሱ ቢጠራ .. በየክፍሉ - በየበሩ - በየመልኩ - በየተራ ... ፋኖሱን እንደ ደመራ ... ቡናቤቱን እንደሰራ ... እያለ፡፡

ሲያያት ቸከለ፡፡

ስለ አስመራ ቆንጃጅትም የሚበቃውን ያህል ሰምቶአል፡፡ ከወደዱ ይሉኝታ እንደማያውቁ ... ከጠሉ ደሞ ግልፅ እንደሆኑ ... ለጥቅም ሲሉ ራሳቸውን እንደማያዋርዱ ... ብርቱዎች መሆናቸውን ሰምቶአል፡፡ ሮዛም ትጠብቀዋለች፡፡ ሲያያት ቸከለ፡፡ የሳሙኤል የአክስት ልጅ፡፡ እንደ ሳሙኤል ገለፃ የሮዛ አፍንጫና ከንፈር ፈዝዘው የሚያዩት አይነት ውብ አይደለም፡፡ ጨዋታዋ ግን አይጠገብም፡፡

የሚጉዋዝበትን ተልእኮ ደሞ አሰበ፡፡ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ራሳቸው በቢሮአቸው አነጋግረውት ነበር፡፡ ትሁት ሆነው ነው ያገኛቸው፡፡ ይቀልዳሉ፤ ይጫወታሉ፡፡ ፈገግታቸው ቅቤ ነበር፡፡ ጥናቱ ባስቸኳዋይና በጥራት እንዲከናወን መመሪያ ሰጥተውታል፡፡ አስመራ ላይ ቢሮክራሲያዊ መጠላለፍ እንዳይገጥመው መመሪያ እንደሚሰጥ ነግረው አበረታተውታል፡፡ የቡርቃን አመፅ ለማቆም ያደረገውን ጥረት አድንቀው 'ኢትዮጵያዊ ስሜት!' ያለው ብርቱ ወጣት መሆኑን ጠቁመውታል፡፡

አኖሌ በተምታታ ስሜት ነበር ከፕሬዚዳንቱ ቢሮ የወጣው፡፡ ድንፋታና ጉራ ነበር ከኰሎኔሉ የጠበቀው፡፡ በግልባጩ ድመት ሆነው አገኛቸው፡፡ ስለ አዶልፍ ሂትለር ያነበበውን አስታወሰ፡፡ ብዙ አምባገነኖችና ጨካኝ ሰዎች ትሁት መሆናቸውን አንብቦአል፡፡ ይህም ፍርሃት ለቀቀበት፡፡ ወደ ታላላቅ ባለስልጣናት ደጅ መጠጋጋቱን አልወደደውም፡፡ ቡርቃ ላይ የተፈጠረበት አዲስ ስሜትም ቢሆን ምቾት አልሰጠውም፡፡ የጂብሪልን ብስጭት የተላበሰ ሮሮ አስታወሰ፡፡ 'እነዚህ ቀፋዎች ጦርነቱ በበረታና ባባነናቸው ቁጥር ማንኛውም ነገር እንዲጠና ይፈልጋሉ፡፡ በቅርቡ የእቁባቶቻቸውን ውሎ ጭምር ሳያስጠኑን አይቀርም' ብሎት ነበር - ከአንድ ቀን በፊት፤ መጠጥ ላይ፡፡፡

አኖሌ ፈገግ አለ። 'ቶሎ ምን ማለት ይሆን?' ሲል ራሱን ጠየቀ። 'ምናልባት 'ደንቆሮ' ማለት ሊሆን ይችላል ሲል ገመተ።

የዋቆ አባዱላ ዲስኩር በበኩሉ ጆሮው ውስጥ ያለማቋረጥ ይሰማዋል። ከብዙ አመታት በፊት ሀማጋው ላይ ለተሰበሰቡ ገበሬዎች ያስተማሩት፤ አለያም ለኦሮሞ ህዝብ ያስተላለፉት መልእክት ...

- ራስ ብሩን እድሜ አይምሰላችሁ የገደላቸው። አለመጠን ያግበሰበሱትን ጮማ መሸከም አቅቶአቸው ነው የወደቁት። ወገኖቼ የኛ የኛ ክንድ መቼ ዛለ? ግን በጉልበታችን መብታችንን ካላስከበርን የኛ ቅልጥም ከወይራ ዛፍ አይሻልም። ማንም እየቆረጠ እሳት ውስጥ ይማግደዋል! -

አኖሌ ምን እንደሚፈልግ ማሰብ ጀመረ። አልገባውም። 'ኦሮሞዎች መብታቸውን ተነጥቀዋል። እና ምን ይደረግ? እነግ ያልቻለውን እኔ እወጣለሁ?' ሲል ራሱን ጠየቀ። ለራሱም ራሱ መልስ ይሰጥ ጀመር። 'እኮ ምን ተአምር ለመፍጠር? የሽፈተ ሁሉ ያሸንፋል? የአመፅ መሪ ለመሆን ብቃት ይኖረኝ ይሆን? ትግል ለመጀመር ምን አይነት ባህርይ ያስፈልጋል? ትግል ምንድነው? ጥይት? የቆቅ ኑሮ? ቆነጃጅት የሌሉበት? ውጣ ውረድ የበዛበት? ሞት? እና እኔ ታጋይ መሆን እችላለሁ? የኦሮሞን ህዝብ መብት ለማስከበር እመጥናለሁ? -

አኖሌ እንደገና ይህንንም አሳብ ተወው። ይሀን አሳብ ትቶ ወደ ተጨባጭ ተልእኮው ተመለሰ። ጂብሪል ከኢሳይያስ አፍወርቂ ጀምሮ ያሉትን የሻእቢያ መሪዎች ስም፤ ስልጣን፤ የግል ባህርይና የትምህርት ደረጃ የያዘ ሰነድ አስታቅፎታል። ስለኤርትራ አማፅያን የሚያስረዱ በርካታ ጥናቶችንም ሰጥቶታል። ከተቀመጠበት ተነስቶ ከአይሮፕላኑ የሻንጣ ማስቀመጫ ኪስ የእጅ ቦርሳውን አወረደ። በጥንቃቄ ከተቀመጡት ዶኪመንቶችም አንዱን መዞ አወጣ። ትላንት ማምሻውን አንድ ርእስ ማየቱ ትዝ ብሎታል። «የኤርትራ ወንበዴዎች የትግል አጀማመር» የሚል።

ዶክመንቱን አውጥቶ ያገላብጠው ጀመር። ጥናቱ የሻለቃ ማእረግ ባለው አንድ የአየር ሃይል መኮንን የተዘጋጀ ሲሆን፤ ጥናቱ የተካሄደበት ጊዜ ደርግ ስልጣን በያዘባቸው አመታት ውስጥ ይመስላል።

አኖሌ ማንበብ ጀመረ ...

ጥቂት ገፆችን እንዳለፈ የጥናቱ ግልፅነት ይመስጠው ጀመር።

«... ሳህል ውስጥ አንዲት አሮጊት ከመንግስት ጦር ጋር ተጠግተው የምግብ እርዳታ እንዲያገኙ ተደርጎ ነበር ...» ሲል





የሚጀምረው አንቀፅ በስሜት ይዞት ነጎደ።

«... ባልቴትዋ ግን የሚተርፍ ምግብ እያጠራቀሙ ወደ በረሃ እንደሚልኩ ስለተረጋገጠ ለጥያቄ ቀርበው፤ ስለጉዳዩ ያብራሩ ዘንድ ሲጠየቁ፤

'አዎን እልካለሁ፤ ምክንያቱም ልጄ በረሃ ውስጥ ነው ያለው' ሲሉ ይመልሳሉ።

'ልጅዎ ሽፍቶአል፤ እንዴት ለሽፍታ ምግብ ይልካሉ?' ሲባሉ፤

'ይርበዋል፤ ይደክመዋል፤ ወገኖቹ ሁሉ ደሞ ይወዱታል።' ሲሉ መለሰዋል።

ሻእቢያ ህዝቡን ያስተምረዋል። ከውጭ የሚመጣለትን ምግብ ለራሱ ሳይበቃው ለህዝቡ ያድላል። ከህዝቡ ለወሰደው ለማናቸውም ነገር በመጠኑም ቢሆን ይከፍላል። ለዚህም መሆን አለበት የህዝብ ድጋፍ ያለው።

«... ኢትዮጵያና ኤርትራ በፌዴሬሽን እንዲወሃዱ የተባበሩት መንግስታት በ1950 ዓ.ም ወሰነ። ያኔ ነው እንግዲህ ኤርትራውያን ወደ ካይሮ መሰደድ የጀመሩት። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ ኢብራሂም ሱልጣን - እንድሪስ አደም - ኡስማን ሳለህ ሳቤ - ወልደአብ ወልደማርያምና ፋሽስት ኢጣሊያን ሲያግዙ የነበሩ ባንዳዎችም የስደት ጉዋድ ነበሩ።»

አኖሌ ግማሹን ታሪካዊ ትንተና ዘለለውና ማንበቡን ቀጠለ። ሻእቢያ እንዴት ጠንካራ ድርጅት ሊሆን ቻለ? ለሚለው ጥያቄ በቂ መልስ እንደሚያገኝ እየተሰማው በችኮላ ሰመጠበት።

«... ጀብሃ ገና ከጅምሩ በአድሃሪዎች መሪነት የተመሰረተ ነው» ይላል ጥናቱ ማብራሪያውን ሲቀጥል «... አይዲያሊዝምን ከማቴሪያሊዝም ለማገናዘብ ከሚሞክረው 'የኢዝላሚክ ሶሻሊዝም' የቅኝት ፍልስፍናም በመጠኑ ተርከፍክፎበታል። የክርስቲያኑ ታጋይ መሪዎች እነ እድሪስ መሐመድ አደምና ወልደአብ ወልደማርያም ናቸው። እድሪስ መሐመድ አደም የቤኒአሚር ተወላጅ ሲሆን ከመነሻውም ኤርትራ ከሱዳን ትደባለቅ እያለ ሲለፍፍ የነበረ ነው። ከህዝቡ በልቶ ህዝቡን ከመጨረስና ከማስጨረስ በስተቀር እጅግም የሰራው ቁምነገር አልነበረም። ህዝቡን እሱ የሚበዘብዘው አንሶት እራሱ ባመጣው ጣጣ በመንግስት ወታደር ሲደበደብ ጥሎት ይሸሻል እንጂ ሊከላከልለት አይችልም ነበር። ይህ የሚያሳየው ለህዝቡ አለመቆሙንና ህዝቡንም ማደራጀት አለመቻሉን ሲሆን የህዝቡም ድጋፍ አልነበረውም።

«... እነ ኡስማን ሳለህ ሳቤ 1960ዎቹ አጋማሽ ገደማ ከጀብሀ ሲገነጠሉ ህዝቡ ላይ የደረሰውን ጭቆና ምክንያት በማድረግ ነበር። 'በህዝብ ላይ ሻእቢያ ተብሎ የሚታወቀውን ቡድንም አቋቋቁዋሙ። 'በህዝብ ላይ የሚሰራ ግፍ መቆም አለበት! የፖለቲካ ህሊና መፈጠር አለበት' በማለት የተገነጠለው ሀይልም የራሱን ግንባር ማጠናከር ጀመረ። የዚህ ሀይል የተዋጊው አዛዥ ኢሳይያስ አፍወርቂ ይባላል። ኢሳያስ ወታደራዊውን ክንፍ በሚመራበት ወቅት ጀብሀ ሻእቢያን እንደለመደው ለማጥቃት ሞክሮ ሻእቢያ በኢሳይያስ መሪነት ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ እንዲሸሸ አድርጐታል። የሻእቢያን የፖለቲካ ፕሮግራም በግልፅ ማወቅ ቢያስቸግርም በይፋ የሚያራምደው የኤርትራን ነፃነት ለማረጋገጥ እንደሆነ ይነገራል። ሆኖም በመሳሪያ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም ረገድ የበሰለ መሆኑን መገመት ይቻላል። ከህዝቡ ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ የውጊያ አሰላለፋቸውን ስናይ ሻእቢያ ከጀብሀ የተሻለ መሆኑን እንገነዘባለን። ሻእቢያን አጠንክሮ የያዘው የአንድ ሰው የአመራር ችሎታ እንደሆነ ብዙ ተመልካቾች ይጠቁማሉ። በምርኮኝነትም ሆነ በወዶ ገብነት የገቡ የሻእቢያ ወታደሮችም ይህን አይደብቁም። ሰውየው ይኸው ኢሳይያስ አፍወርቂ የሚባለው ነው።

«... በሻእቢያ አስተዳደር ውስጥ ገንዘብ ለወታደሩ በደመወዝ መልክም ሆነ በሌላ ሁኔታ አይከፈልም። በእያንዳንዱ ወታደር ላይ የሚገኝ ልዩ ሀብት ወይም የእርዳታ እቃ በቀጥታ የሰራዊቱ ይሆናል። ገንዘብ የሚጠቀሙት ከህዝቡ ጋር ለሚደረገው የንግድ ልውውጥ ነው። ከህዝብ ምግብ ሲወስዱም ገንዘብ ይከፍላሉ። ከወታደራዊ ልምምድ ሌላም የፖለቲካና የርእዮተ አለም ትምህርት አላቸው።

«... ስለ ሻእቢያ በግልፅ የሚታይ አንድ ነገር አለ። ኢሳይያስ አፍወርቂ የሚባል ሰው ይኑርም አይኑር ለሻእቢያ እጅግ አስፈላጊ የሆነ አንድ ሰው ግን አለ። የሜዳው ተዋጊዎች ክብራቸውን ስነስርአታቸውን ያገኙት በዚህ ሰው የአመራር ችሎታ ስለሆነ ኢሳይያስ እንዲሁ «ዞርበል!» ተብሎ የሚገፈተር ሰው አይደለም። የኡስማን ሳላህ ሳቤ ችግርም ይኸው ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል። የኢሳይያስን አካሄድ ላይወደው ይችላል የሚል ጥርጣሬ አለ። ግን ምን ያድርገው?

«ጊዜያዊ ወታደራዊ የደርግ መንግስትም እዚህ ሰውዬ ላይ ማተኮር አለበት። ኢሳይያስ ማነው? ምን ይፈልጋል? ያለምንም ዋስትና ባዶ እጁን ዝም ብሎ እንዴት በረሃ ሊኖር ይወስናል? ወይስ ኢሳይያስ ራሱ አጉል ጀብደኛ ወይም አድሃሪ ይሆን? ኢሳይያስ የህዝቡን ጥያቄ በትክክል ያውቃል ማለትስ ይቻላል? ደጋግመን ልናነሳው የሚገባን ጥያቄ ነው»

አኖሌ በረጅሙ ተነፈሰ ... ጥናቱ የቆየ ቢሆንም አላረጀም።





በእድ ብዙት አልተሻሸም። አቡዋራም ጠግቦአል። አለቆች ያዩት አይመስልም። አኖሌ የጂብሪልን ንግግር አስታወሰ። 'ማስጠናት ይወዳሉ - ግን አያነቡትም - ቢያነቡትም አይገባቸውም - ቢገባቸውም ትክክለኛ ውሳኔ አይወስኑም - ፈሪዎች ናቸው' ያለው ትዝ ብሎት ፈገግ አለ። 'የኔ ጥናትም የመደርደሪያ ራት ከመሆን አያመልጥም' ሲል አሰበ።

በጥናቱ ላይ ተረማምዶ በአሳብ ወደ ቡርቃ ነጐደ።

የቡርቃ ሰዎች ከጠር የተሻለ የውጊያ መሳሪያ የላቸውም። ምናልባት ጠንካራ ክንዶችና - አይበገሬ ልብ ሊኖራቸው ይችላል። አዎን ብሩህ አእምሮም አላቸው። ያመፁ ጊዜ ባዶ እጃቸውን ለጦርነት ተዘጋጅተው ነበር። ሆኖም ጦሮቻቸውን ለጊዜው እንዲያስቀምጡ ተማፅኖአቸዋል። በርግጥ በወቅቱ ከዚያ ሌላ አማራጭ አልነበረም። በስሜት ብቻ ተገፍቶ ከታጠቁና ከሰለጠኑ ወታደሮች ጋር መፋለም ወጤቱን ከንቱ እልቂት ብቻ ነው የሚያደርገው - እያለ ቢያሰላስልም አኖሌ ይህን እምነቱን ሊገፋበት አልቻለም። 'ኢሳይያስ ያለምንም ዋስትና ባዶ እጁን ዝም ብሎ እንዴት በረሃ ሊቆይ ወሰነ?' የሚለው ጥያቄ ጭንቅላቱ ውስጥ ቀርቶአል። ኢሳይያስ ምን አይነት ሰው ነው? ጀብደኛ ወይስ እውነተኛ ለህዝብ የሚታገል ጀግና? አድሀሪ ወይስ ሩቅ ተመልካች - ሩቅ አዳሪ?

ዋቆ አባዱላ ሆማጋው ላይ ለተሰበሰቡት የቡርቃ ገበሬዎች ንግግር ሲያሰሙ ፊቱ ድቅን አለ ...

- ክንዳችን ከወይራ እንጨት ይጠነክራል! መሬታችን ግን ለስላሳ ነው። ሀብታሙን መሬታችንን ለማረስ ያን ያህል ጠንካራ ክንድ አያሻም። ጨቅላዎች በቀላሉ ያርሱታል። ይህ ከሆነ ዘንዳ እኛ ጐልማሶች ይህን ክንዳችንን በሚንቁን ነፍጠኞች ትከሻ ላይ ለምን አክርረን እንሰነዝረውም? ነፍጠኞች አማርኛ ተማሩ እያሉ ቁም ስቅል ያሳዩናል። አማርኛ ምን ጠቀመን ወገኖቼ? በርግጥ የነፍጠኛ ሎሌዎች ግብር ሊሰበስቡ ሲመጡ እንዳይቸገሩ ረድቶአቸው ይሆናል። ጦር ሜዳ ላይ እኛን ወደ እሳቱ ለመግፋት ቋንቋዋውን ይጠቀሙበት ይሆናል። በራዲዮናቸው ንጉሳቸውን ሲያሞግሱ እንድንሰማቸውም ይፈልጉ ይሆናል። ሌላማ ምን ሲፈይድልን? አይደለም እንዴ ወገኖቼ?

አኖሌ እልም አለ ወደ ቡርቃ ...

የተጨቆኑ ህዝቦች ሁልጊዜ መብታቸውን ለማስከበር ሲሉ ለመታገል ዝግጁ ናቸው። መሪ ግን ይፈልጋሉ። ከመካከላቸው ጠንካራ መሪዎች እስኪያገኙ ድረስ ግን ያልተደራጀ ከንቱ መስዋእትነትን እየከፈሉ፣ እየተጨቆኑ ይቆያሉ። የኤርትራ ህዝብ

ይህን ከባድ ፈተና እየተቋዋቋዋመው ነው። ኦሮሞዎችም እንደ መሀመድ እድሪስ ጥሎአቸው የሚሸሽ ሳይሆን ክብራቸውን የሚያስጠብቅላቸው መሪ ይፈልጋሉ።

የታመቀ አየር ተንፍሶ ሲያበቃ፣

«ወኔ ቢስ ነኝን?» ሲል ራሱን ጠየቀ። መልስ ለመስጠት ፈራ። የቡርቃ ሰዎች ከአመፅ መሀል አውጥተው አሳድገው፣ አስተምረው እንዲመሩቸው ጠየቁት። እሱ ግን 'ቆዩ!' አላቸው። እስከመቼ?

ሀወኒን ድንገት አሰባት ...

ቢያማክራት ጭንቀቱ ይቀለው ነበር። ወይም ይዞአት ከአፍሪቃ እጅግ ወደራቁ አገሮች በተሰደደ። ስለ ኦሮሞም ለዘልአለሙ ማሰብ ባቆመ። አዎን ... በአንድ የሩቅ አገር ሰዎች መሀል ጥሮ ግሮ መኖርን ተመኘ። በርግጥ ትክክለኛው ፍላጐቱ በስደት መኖር ስለመሆኑ ራሱም በቅጡ አያውቀውም።

ስለ አዲሳባ ኑሮ ደሞ አሰላሰለ። ትዳር መስርቶ መኖር። ፖለቲካ ውስጥ ሳይገባ። በሙያው እየሰራ እድሜውን መግፋት። ትዳር ስለመመስረት ሲያስብ የሚያውቃቸውን ሴቶች በአሳቡ ያስስ ጀመር።

ሀወኒ የለችም። ሌላ ማን? 'ሜሮን ... ዝጋታም ናት። ሳምራዊት መልክ ብቻ፤ እንደሳሎን እቃ። ሊዲያ ... ለወሲብ ብቻ የተፈጠረች ጉድ፤ የጉድ ጉድ። ፌሩዝ ... ጥሩ ብትሆንም ካልሰለምክ እያለች የምትረብሽ። አበባ - ዘረኛ። ሰላማዊት - ትምክህተኛ' እያለ ሲያጣጥላቸው ከቆየ በሁዋላ ዮዲት ላይ ሲደርስ ቀጥ አለ። ይወዳታል። ጥሩ ናት። በሁሉም ነገር ተስማምተው ነበር። አማራ ናት። ቤትዋ ወስዳ ከአባትዋ አስተዋውቃው ነበር። ጥቂት አውርተው ተጋጩ። አልተግባቡም። ስለ ኦሮሞ ያላቸው አመለካከት ጨፈገገው። ገና ስሙን ሲሰሙ ግንባራቸው ሲቋዋጠር አስተውሎአል። አዘነባቸው። 'ወደል ነፍጠኛ' አላቸው በልቡ። ከመጀመሪያው ቀን በሁዋላ ደጃቸው ሳይደርስ ቀረ። ዮዲትን ማግኘቱን ግን ቀጠለ። ዮዲት የዩንቨርስቲ ተማሪ ናት - የሶስተኛ አመት፣ የህግ። ቆንጆዬና ብስል ናት። እናሌ እያፈቀራት መሆኑን ቢረዳም አብሮአት ሊቀጥል አልፈቀደም። አባትዋን አጥብቆ ጠላ። ለጉዞ ከመነሳቱ በፊት አግኝቶአት ነበር። እንደምታፈቅረው ስትወተውተው የልቡን በግልፅ ነግሮ ሊለያት ወሰነ፤ የወጪ እየጠጡ ነበር - ጐርደን ጂን፣

- ልጐዳሽ አልፈልግም - አላት - እንደምወድሽ ግን እመኚ -





- ከወደድሽኝ ለምን ትሸሸኛለህ?

- አባትሽን አጥብቄ እጠላቸዋለሁ -

- በአባቴ ምክንያት እኔን መራቅ ይገባሀል?

- አንቺ ለአባትሽ ደንታ የሌለሽ ብትሆኚ ደግ ነበር። ለአባትሽ ያለሽ ፍቅር መለኪያ የለውም። ሁለቱ ስሜቶችሽ ወደፊት ይጋጩብሻል። ስለ አባትሽ መልካምነት ስታነሺ ክፉ መናገሬ አይቀርም። ቤተሰቦችሽ ዘንድ እንድሄድ ስትጠይቂኝ ስለማልስማማ እንጋጫለን። ይቅርታ የኔ ፍቅር -

- አባቴን አምርረህ የምትጠላበት ምክንያት በቂ አይደለም እናሌ?

- ይገርምሻል ዮዲት። ከባህሬይ የተሻለ ማሰብ አይችሉም፡-

- ማነው ባህሬይ?

- ባህሬይን አታውቂውም? ለነገሩ ባታውቂው ይሻልሻል። አንድ ደብተራ ነው። ስለ ኦሮሞ በግእዝ ያሰፈረው ፅሁፍ 'የጋላ ታሪክ፣ የነገዳቸው ቁጥር፣ ነፍሳትን ለመግደል ያላቸውን አራባጅነትና የጭካኔ መጥፎ ልማዳቸውን ለማሳወቅ የጋላን ታሪክ ለመፃፍ ጀምሬያለሁ' በሚል የጥላቻ አረፍተነገር ነው የሚጀምረው። ከዚያ ወዲያ ያለውን ተይው። ምንም አያደርግልሽ። አባትሽ ከዚያ ባህር የተቀዱ ሰው ናቸው። በድጋሚ ይቅርታ - ይህን የምለው ላሳዝንሽ ብዬ አይደለም፡-

- ይህ ለኔና ላንተ መለያየት ምክንያት ሊሆን አይችልም እናሌ። ለምን በግልፅ ጠላሁሽ አትለኝም?

- አልጠላሁሽም ዮዲት -

- ባትጠላኝም ሌላ አፍቅረህ ይሆናል -

- በጭራሽ! -

- ወንዶችን ማመን ላይቻል ነው፤ እናሌ -

- ጥሩ ልጅ ነሽ ዮዲት፤ ከኔ የተሻለ ሰው ማፍቀር ትችያለሽ። እኔ እንዳልጠላሁሽ ግን እመኚ። በህይወቴ ሁለት ጊዜ ብቻ ነው ያፈቀርኩት። አንደኛዋ ደግሞ አንቺ ነሽ -

- ሌላዋስ? -

- አሁን የለችም። የቆየ ታሪክ ነው፡-

- ማን ትባላለች?

- ሀወኒ፡ -

- የትናት አሁን?

- አላውቅም፡፡ ሰደት ላይ ልትሆን ትችላለች፡፡ ሞታም ሊሆን ይችላል-

- ላባቴ ምርጫዬ አንተ መሆንህን ነግሬዋለሁኮ አኖሌ፡-

- አዘነብሽ?-

- ደስ አላለውም፡፡ እኔ ግን ፍርጥ፣ ቁርጥ አድርጌ ነው የነገርኩት፡-

- 'አረመኔ እንዴት ታገቢያለሽ' ብለው አገር ይያዝልኝ አላሉም?፡-

- አኖሌ እባክህ እንዲያ አትበል፡-

- አንቺ ያላስተዋልሻቸው አያሌ ነገሮች አሉ ዮዲት፡፡ እነዚያ ያላስተዋልሻቸው እውነታዎች ግን ባጭር ጊዜ ውስጥ ገሀድ የሚሆኑ ይመስለኛል፡-

- ምንድነው ገሀድ የሚሆነው አኖሌ?

- የሮባ ዳዲ ትንቢት መፈፀሙ የማቀር አይመስለኝም -

- ማነው ሮባ?

- የባህሬይ ባላጋራ - ብሎ ፈገግ አለ፡፡ አያይዞ እንዲህ አላት፣ «Harold G.Marcus የተባለ ታሪክ ፀሀፊ Imperialism & Expansionism in Ethiopia በተባለ መፅሀፉ ሮባ የተባሉትን የአርሲ ኦሮሞ ጠቅሶ ፅፎአል፡፡

'The hour has not come, but it will come; perhaps our children will see the departure of the oppressor' ነበር ያሉት ሮባ ዳዲ፡፡ በርግጥም ልጆቻቸው እኛ መሆናችን ነው፡፡ ያንን ቀን መናፈቅ ጀምሬያለሁ ዮዲት፡፡ የሚንቁን ሁሉ ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ የደረሰ ያህል የሚርዱበት ተናፋቂ እለት -

- አኖሌ ዛሬ ብዙ ጠጥተሀል፡፡ ስሜታዊ ሆነሃል፡-

- በጭራቁ ምኒልክ ዙሪያ ስናወራ አባትሽ ምን አሉኝ መሰለሽ፡፡ 'እግዚአብሄር ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ምኒልክን ላከ!' የብሂላቸው ትርጉዋሜ ስውር አይደለም፤ ዮዲት፡፡ የሰው ልጅ ሁሉ ጌታ የሆነው እግዚአብሄር የላከው ነገር ፍፁማዊ ነውና አሜን ብላችሁ ተቀበሉ ማለታቸው ነው፡፡ በዚህ እምነታቸው አባትሽ ከባህሬይ በምን ይለያሉ? ለመሆኑ እስኪ አንድ ጥያቄ ላቅርብልሽ ዮዲት፤ እግዚአብሄር ላንቺ





የዶሮ ፍትፍት ሲያጎርስ በክርኑ የኔን ጥርስ የሚያራግፍ ይመስልሻል፡-

መልስ አልሰጠችውም፡፡ - ከአስመራ እንደተመለስክ በዚህ ርእስ ላይ በጥብቅ እነጋግርሀለሁ - አለችው፡፡

ተሳስመው ተለያዩ፡፡

... አይሮፕላንዋ ፍጥነትዋን ቀነሰች፡፡ አስመራ ቀርበው ኖሮአል፡፡ አኖሌ ስለ ዮዲት ማሰቡን ትቶ ወደ ሮዛ ተሻገረ፡፡ የሳሙኤል የእክስት ልጅ፡፡ የማይጠገብ ጨዋታ ያላት የአስመራ ልጅ ... ሊያገኛት ቸኮለ፡፡

- 4 -

የደህንነት ሚኒስትሩ ጂብሪልን በአስቸኩዋይ ወደ ቢሮአቸው ካስጠሩት በሁዋላ ቀጣቸው ገፅታቸው ላይ እየተንበገበገ፣ ከሰላምታ በፊት እንዲህ ነበር ያሉት፣

«የጠራሁህ እጅግ አደገኛ ስለሆኑ ሁለት ጉዳዮች ላዋይህ ነው፡፡ ማታ በወንበዴዎች ሬድዮ የተነገረውን አዳምጠሃል?»

«ስብሰባ ስላመሸሁ አላዳመጥሁም ... ክቡር ሚኒስትር፡፡»

«ደህና እኔው እነግርሃለሁ» አሉ ጠረጴዛቸው ላይ የተበታተነውን ወረቀት እያተረማመሱ «... ሀየሎም አርአያ በተባለው ወንበዴ ላይ ጥቃት እንዲፈፅም ታማኝ ብለህ የላክኸው ሰው እቅድህን ሁሉ ሲዘከዝክ አምሽቶአል፡፡»

በጥፊ የተመታ ያህል ደርቆ ቀረ፡፡

«ውርደት ነው! ቅሌት ነው! ይህ የአመላመል ስህተት እንዴት ተፈጠረ? ለዚህ ጥያቄ በቂ መልስ ማቅረብ ሊኖርብህ ነው፡፡ በርግጥ ስህተት ከሆነ ማለት ነው» ብለው በንዴት በሚነድ አይናቸው ገረፉት፡፡

«ምን ለማለት እችላለሁ ክቡር ሚኒስትር!» ብሎ በመረበሽ አይናቸውን ይሸሽ ጀመር፡፡ «... ይህን የመሰለ ሁኔታ በመላው አለም ሲያጋጥም የነበረና ወደፊትም ሊያጋጥም የሚችል ነው፡፡ ሰላዮች አስቸጋሪ ፍጡራን ናቸው፡፡ ይከዳሉ፤ ለሁለት ተቃራኒ ሀይሎች ይሰልላሉ፤ በጀግንነት መስዋእት የሚሆኑም አሉ፡፡ ይሄ የላክነው ልጅ ደህና ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ ከባድ ሀላፊነቶችን በብቃት የፈፀመ ሰው ነው፡፡ የፓርቲ አባልም ነው፤ ጉዋድ ሚኒስትር ...»

«ደህና! ትምህርታዊ ማብራሪያውን ለሌሎች ሰጥየው:: ፕሬዚዳንቱ ዘንድ እስኪቀርብ ሁለተኛው የአኖሌ ዋቆ ጉዳይ ነው:: በርግጥ በዚህ ድረስ ሙገሳ ደርድረህለት ለዚህ ስራ አጭተኸዋል:: በርግጥ በዚህ ደረጃ ታማኝ ሰው ነው ማለት ይቻላል.»

«ጉዋድ ሚኒስትር ... አኖሌ አስተማማኝ ሰው ነው::»

«ምን ያህል ፐርሰንት?» አሉት::

አሰበና አመነታ::

«በፐርሰንት ለማስቀመጥ ያስቸግረኛል:: ስለሌሎች ሰዎች መናገር በጣም ይከብዳል:: በከፍተኛ ስልጣን ላይ ያሉ ቁልፍ የፓርቲው ሰዎች ጭምር ሊከዱ ይችላሉ:: የፓርቲያችን አባል ያልሆኑ ሰራተኞችም ታማኝ ሲሆኑ ብዙ ጊዜ አጋጥመውናል:: ይሄ አከራካሪ ይመስለኛል:: የኤርትራው ተግባር ባለሙያን ስለሚጠይቅ ከበድ ያለ ተግባር ነው:: አኖሌ በብቃት ሊሰራው ይችላል ብዬ አምናለሁ:: ምስጢር ይጠብቃል ብዬም አምናለሁ:: ጥንቁቅ ነው:: ይህን ያህል አውቃለሁ:: ሙቶ በሙቶ ጠጥቶ ራሱን አይስትም:: ይህን ያህል አውቃለሁ:: የሰዎችን ልብ ጠልቆ ማወቅ ግን ስለ አኖሌ መናገር ያስቸግራል:: የሰዎችን ልብ ጠልቆ ማወቅ ይከብዳል ...»

«የኦነግ አባል ሊሆን አይችልም?»

«በጭራሽ!» ሲል አረጋገጠ ጂብሪል::

«እርግጠኛ መሆን ትችላለህ?» አሉ የደህንነት ሚኒስትሩ::

«እርግጠኛ ነኝ ጉዋድ ሚኒስትር:: ከሌሎች ሀይሎች ጋር ከቶ ግንኙነት ሊኖረው አይችልም:: እኩይ ተልእኮ ይዞ የመጣ አለመሆኑን ከልብ አምናለሁ:: አኖሌ በዚህ ደረጃ ጨርሶ አይጠረጠርም::»

«እንዳልከው ልጁ ሌላ ተልእኮ ላይኖረው ይችል ይሆናል:: መጠንቀቅ ግን ያሻል:: ትላንት በወንበዴ ሬድዮ መግለጫ እንደሰጠው ቡችላ ለፍርፋሪ ሲሉ ሀገር ሊሸጡ የሚደራደሩ ደላሎችን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል:: በጣም ... በጣም መጠንቀቅ ያሻል::»

ዝም አለ ጂብሪል:: ለምላሽ እንኩዋ ፈጣን ነበር:: ዛሬ ግን አመነታ:: ሚኒስትሩ ቀጠሉ፣

«ይህን ልጅ እዚህ መስሪያ ቤት ያመጣኸው አንተ ነህ:: ተጨማሪ ሀላፊነት አለብህ::»

መልስ አልሰጣቸውም::

«ለማንኛውም:: በየእለቱ የቴሌፎን ሪፖርት ያቅርብልህ::»





ጂብሪል «መመሪያውን ተግባራዊ አደርጋለሁ» የሚል ምላሽ ከሰጠ በሁዋላ ከተቀመጠበት ተነሳ::

«ቆይ ... ቆይ አልጨረስንም» አሉት::

ተመልሶ ተቀመጠ::

«ሌላ አስቸኩዋይ ጥናት የሚያስፈልገው ጉዳይ አለ::»

ጂብሪል ማስታወሻ ደብተሩን ገለጠ::

«በወያኔና በሻእቢያ አባልነት ተጠርጥረው የታሰሩ ሰዎች ስም ዝርዝር በአስቸኩዋይ ይለይ!»

«መልካም!»

«በከፍተኛ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩና በመንግስት መዋቅሮች ውስጥ የተሰገሰጉ የኤርትራና የትግራይ ተወላጆች ስምና ሙሉ አድራሻ በአስቸኩዋይ ይቅረብልኝ::»

«በመላው ኢትዮጵያ ከተሞች ነው?»

«እ...»

«መልካም!»

«በደህንነት መዋቅሮቻችን ውስጥ የኤርትራና የትግራይ ተወላጆች መኖር አለመኖራቸው በድጋሚ ይጣራ!»

«መልካም!»

«ጨርሻለሁ!»

ጂብሪል ወደ ቢሮው ሲያመራ 'ፍፃሜ መጥቶአል!' የሚል ቃል መጣበት:: የተሰጡት ትእዛዞች ፍርሀት ለቀቁበት:: 'እነዚህ ሰዎች ተስፋ ቆርጠዋል ማለት ነው?' ሲል ራሱን ጠየቀ::

ሚኒስትሩን ዛሬ ከልክ በላይ ያነጫነጫቸው በህወሀት መሪዎች ላይ የተሰነዘረው የግድያ ሙከራ በመክሸፉ መሆኑን ጂብሪል አውቆአል:: ስለዚህ ቁጣቸውን ችላ አለው:: ይልቁን የኢትዮጵያን የወደፊት እድል ለማሰብ ሞከረና ተደበላለቀበት:: ጨለማ እንጂ ብርሃን አልታይህ አለው:: እንደልማዱ አንድ ቅኔ አስታወሰ - የአንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ ስንኞች፣

*... ደንስ ጉበዝ!*

*ደንስ ጀግና!*

*ከራሻትክን አውልቅና ...*

ስንኖ፣ ስለጠፋበት ማሰብ ጀመረ ...
ጥቂት መስመሮችን ብቻ ይዞአል ...
... ምንም - ምንም እንዳታስብ፣
ሁሉን ሁሉን እንድትረሳ!
ጭንቅላትክን ግዘፍበት!
የጃገ ፋንፋር አንኳዋኳዋበት!
አናፋበት ሸልልበት!
የሲቃ ሳቅ አስካካበት ...
ዝግ ብሎ ያሰበ እንደሁ
ይነግርሃል አንዳች እውነት!
መኪናውን አስነስቶ በረረ - አልኮል አስፈልጎታል።
ሲበሳጭ እንዲሁ ያደርገዋል ...



# ክፍል - ሁለት

# ማርያም አስመረይቲ

# በረሃ ያሉትን አደራ!

## ምእራፍ ስድስት

### - 1 -

እምባሶይራ ሆቴል ሰባተኛ ፎቅ ላይ ሆኖ አስመራን ቁልቁል እያየ ይቆዝማል፡፡ ለአይን ያዝ አድርጐአል፡፡ ሲቪል የለበሱ ወታደሮች ደረታቸውን ገልብጠው በኰምቢሽታቶ ጐዳና ላይ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ይታዩታል - አኖሌ ዋቆ፡፡

አስመራ ደርሶ ስራውን ከጀመረ አስር ቀን ቢሞላውም እንኩዋ ከተማዋን ተዘዋውሮ ለማየት እምብዛም ፍላጐት አላደረበትም፡፡ የሚሰበው ነገር አጣ፡፡ አስመራ የምታዛጋ መንደር ሆነችበት፡፡ የቀድሞ ውበትዋን እያነሳሳች የምትተክዝ ባልቴት፡፡ የወታደሮች መፈንጫ ሆነችበት - አስመራ፡፡ ያቀረቀረ ህዝብ፡፡ ቀለማቸው

የረገፈ ግድግዳዎች፡፡ ባዶ፡፡ እና፡፡ ሞት የነገሰባት፣ ፍርሀት ያየለባት፣ ተስፋ ቢስ ከተማ ሆነችበት - አስመራ፡፡

በዚህ ላይ በከተማዋ የሚያውቀው ሰው የለውም፡፡ ሮዛ የተባለችው የሳሙኤል ዘመድም አልደወለችለትም፡፡ 'የምታርፍበትን ሆቴል ስለነገርኩዎት ራስዎ ትደውልልሀለች' ነበር ያለው ሳሙኤል፡፡

በረንዳ ላይ ቆሞ ፍርሀት ያራዳትን ከተማ እያየ መቆዘሙ ሰለቸው፡፡ ይልቁን የእለት ውሎውን ሪፖርት ማዘጋጀት እንደሚገባው አሰበ፡፡ እና ከመኝታ ክፍሉ ማስታወሻ ደብተሩንና ወንበር ይዞ ወደ በረንዳው ተመለሰ፡፡

ዛሬ አብርሀ ፀሎት ከተባለ እስረኛ ጋር ነበር ውይይት ለማድረግ የሞከረው፡፡ ውይይቱ የተሳካ ነበር፡፡ እስረኛው መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ባይሆንም በአንድ ነጥብ ግን አኖሌን መሳብ ችሎ ነበር፡፡ አኖሌ በሻእቢያ ሰላይነት ተጠርጥሮ በታሰረው በዚህ ሰው ባህርይ በእጅጉ ተገርሞአል፡፡ ማርያም ግምቢ ተብሎ ከሚጠራው ልዩ እስር ቤት ሄዶ ነበር ያነጋገረው፣

- እኔ የፖሊስ መርማሪ አይደለሁምና በተለየ መንገድ እንድትቀርበኝ እፈልጋለሁ፡፡- ይለዋል እንደተገናኙ፡፡ የሚያነጋግራቸውን እስረኞች ሁሉ በዚህ መንገድ ተለሳልሶ ነበር የሚቀርባቸው፡፡

አብርሃ ፀሎት የተባለው እስረኛ ለአኖሌ የተለሳለሰ አቀራረብ ምላሽ ሳይሰጥ ስሜቱ በማይታወቅ ሁኔታ ገረመመው፣ አኖሌ ቀጠለ፣

- ብዙ ድብደባ አድርሰውብሀል? -

በፋሻ የታሸገ ግራ እጁን እያየ ነበር ይህን ጥያቄ ያቀረበለት፡፡

- ደህና ነው - ሲል ምላሽ ሰጠ አብርሀ፡፡

- ስብራት አለው እጅህ?፡-

- አይመስለኝም -

- የሻእቢያ ሰላይ መሆንህን አጫውተውኛል፡፡ እውነት ነው?-

- ልክ ነው፡-

- በቀላሉ ማመንህ ያልተለመደ ነው - አለው አኖሌ ጠሪ





ለማራዘም፡፡

- መካድ ትርጉም አልነበረውም፡፡ ፖሊሶች እጄ ላይ መረጃ አገኝተዋል፡-

- ከደህንነት ሰዎች ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ አለመሆንህን ነው ፖሊሶቹ የነገሩኝ፡፡ ሰላይነትህን ካመንክ ወዲያ አለመተባበር ስቃይህን ማብዛት አይሆንም?-

- ስቃዩን ፈርቼ የተሳሳተ መረጃ ብሰጣቸው ምን ይጠቀማሉ? የደህንነት ሰዎች የሚፈልጉት የሻእቢያን የአስመራ የስለላ መዋቅር ማግኘት ነው፡፡ ይህን ባላገኙት ቁጥር የሚያረካ የሰዎችን ስም ዝርዝር ከኔ ይፈልጋሉ፡፡ አጋጣሚ ሆኖ እኔ ከአንድ ሰው ጋር ብቻ ነው ግንኙነት የነበረኝ፡፡ የሚመስለኝም ያው ሰው ነው፡፡

- የሰውየውን ስም ሰጥተኻቸዋል?፡-

- አላምሬ ነዋ!፡-

- ማነው ሰውየው?

- ሻምበል ቃለመስከት ካሳዬ ይባላል፡

- ተያዘ ታዲያ?-

- በሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊት ውስጥ በዚህ ስም የሚጠራ መኮንን የለም ነው የሚሉኝ፡፡ መልኩን ጭምር በዝርዝር ተናገርሁ፡፡ ጠጉሩና አይኑ ጥቁር፣ ቁመቱ ሜትር ከሰባ፣ አፍንጫው ሰልካካ፣ ጠይም፣ ጥርሶቹ ችምችም ያሉ ነጫጮች፣ ጢሙን ሙልጭ አድርጎ የሚላጭ፣ ድምፁ ቀጠን ያለና ስስታም፣ እረማመዱ ፈጣን፣ መሆኑን ዘርዝሬ ነገርኳቸው፡፡ የምንገናኘው ኮምቢሽታቶ ላይ እንደነበር፣ የምንለያየውም በዚያው ጎዳና መሆኑን፣ ከመለመለኝ ሶስት ወር ብቻ እንደሆነ፣ በተያዝኩበት እለት በእጄ የተገኘውን መረጃ ለአንድ ለሌላ ሰው እንዳስተላልፍ እንደሰጠኝ፣ የተጠቀሰው ሰው በዚያው በኮምቢሽታቶ ጎዳና ላይ ራሱ መጥቶ ሲጋራ እንድለኩስለት እንደሚጠይቀኝ፣ እኔም በክብሪት ወይስ በላይተር ብዬ እንዳማርጠው፣ ምርጫው ክብሪት እንደሚሆን፣ የምሰጠው መልእክትም በክብሪቱ ውስጥ ስለሚገኝ፣ ክብሪቱን ለተጠቀሰው ሰው ከሰጠሁ በሁዋላ የእለቱ ተግባሬ እንደሚያበቃ ነበር የተነገረኝ፡፡ ይህን ከመፈፀሜ በፊት ነው የተያዝኩት፡፡ እናም ይህንኑ አብራራሁ፡፡ ፖሊሶች ግን ጨርሶ አላመኑኝም፡፡ እየቀለድሁባቸው መሆኑን ይጋግሙሁ ይነግሩኛል፡፡ እውነቱ ግን ያለው ነው፡-

አኖሌ የፈዘዘ ፈገግታ አሳየው፣

- በርግጥም ቀልድ ይመስላል - አለው፡፡ አያይዞም - ለአብነት ጠጉሩና አይኑ ጥቁር መሆኑን ገልፀሃል፡፡ ይሄ ፌዝ ነው፡፡ ምክንያቱም ያንተና የኔ ጠጉርና አይንም ጥቁር ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ከቀጠልክ ስቃዩ ሊበዛብህ ስለሚችል መረጃ መስጠት ካልቻልክ በሌሎች አንዳንድ ነገሮች ለምን ትብብር አታደርግም?፡-

- ለምሳሌ ምን? - አለ አብርሃ፡፡

- ህዝቡ ዐረ ሻእቢያ አቋዋም እንዲይዝ በመቀስቀስ፣ በመሳሰለው፡-

- እሱን አልፈልግም -

- ለምን!? - እኖሌ ተገረመ፣

- ምክንያቱም እኔ ቴሌቪዥን ላይ ቀርቤ የማደርገው ቅስቀሳ የኤርትራን ህዝብ ስሜት የኢትዮጵያ መንግስት በሚፈልገው መንገድ ሊገራው አይችልም፡፡ መፍትሄው ሌላ ነው፡-

- በሚዲያ ቀርበህብትናገር ምናልባት ነፃ ልትለቀቅ ትችላለህ፡-

- ነፃ ለመለቀቅ ነው መናገር ያለብኝ ወይስ ሻእቢያን ለመጉዳትና የኢትዮጵያ መንግስትን ለመጥቀም? - ሲል አፋጠጠው፡፡ አያያዘናም - ራሴን ነፃ ለማድረግ ስል የምናገራት አንዲት ቃል ከቶ የለችም፡፡ መንግስት ድል የሚያገኝበትን መንገድ ግን ልጠቁም እችላለሁ፡፡ በርግጥ የደህንነት ሰዎች ኤርትራ ላይ ድል ስለሚገኝበት መንገድ ሀሳብ እንድሰጥ አልጋበዙኝም፡፡ የነሱ ልዩ ችሎታ እስረኛን ማሰቀየት ብቻ ነው፡-

- ድል የሚገኝበት መንገድ ምንድነው? - ሲል ጠየቀው እኖሌ፡፡

አብርሀ በሉት ደከም ያለ ፈገግታ ካሳየው በሁዋላ፣

- ሀሳቤን አዳምጠህ ለመመርመር ነው ወይስ ሀሳቡን ከመንከቡት በርግጥም የማስፈፀም አቅም አለህ?

እኖሌ አመነታ፣

- የማስፈፀም አቅም የለኝም፡፡ ሀሳቡን ከመንከቡት ለኮሎኔል መንግስቱ የማቅረብ ችሎታ ግን አለኝ፡-

አብርሀ በሉት - ይህማ ትልቅ ስልጣን ነው - ካለ በሁዋላ እንዲህ እያለ ያወጋው ጀመር፣

- የኤርትራን ህዝብ ልብ ለማሸነፍ ዘዴው ቀላል ነው፡፡ በቅድሚያ ህዝቡ ላይ የሚደረገው የአውሮፕላን ድብደባ መቆም





አለበት፡፡ ሁለተኛ ወታደሮች ጎጆውን እንዳያቃጥሉበት፣ ከብቶቹንና ፍየሎቹን እንዳያርዱ፣ ልጃገረዶችን እንዳይደፍሩ፣ ዛፎችን እንዳይቆርጡ ማዘዝ፣ ይህ በደብዳቤ የሚፈፀም ሳይሆን በማስሚዲያ በአዋጅ ነው መነገር ያለበት፣ የገበሬውን አንድ በግ ያላግባብ ያረደ ሞት እንዲፈረድበት ማወጅ፣ በግልባጩ ደግሞ ወታደሩ ዛፍ እንዲተክል፣ በትርፍ ጊዜው ገበሬውን በእርሻ፣ በአጨዳና በአረም እንዲያግዝ ማድረግ፣ በገጠሮች ክሊኒክ፣ ትምህርት ቤትና መንገድ መገንባት፣ መቸም የገንዘብ ችግር የሚገጥም አይመስለኝም፡፡ የአንድ ቢኤም የጦር መሳሪያ ጥይት ዋጋ አንድ ክሊኒክ እንቀባሮ ይገነባል፡፡ በተጨማሪ ከኤርትራ ተነቅለው ወደ መሀል አገር የተወሰዱ የፋብሪካ ማሽነሪዎች በሙሉ እንዲመለሱ ማድረግ፣ በተለይ በተለይ ወታደሮች ልጃገረዶችን አስገድደው እንዳይደፍሩ ጥብቅ ትእዛዝ መስጠት፡፡ ይህን ድርጊት የፈፀመ ወታደር ህዝብ በተሰበሰበበት በሞት እንዲቀጣ ማድረግ፡፡ ይህን የመሳሰሉ እርምጃዎች ከተወሰዱ ቢያንስ የገበሬው ልብ መዋለል ይጀምራል፡፡ 'ይህንን ለህዝብ አሳቢ መንግስት ምን ሳጠር ነው የምንለው?' ማለት ይጀምራል፡፡ በረሃኞችንም 'ከመንግስት ጋር ታረቁ' ማለት ይጀምራል፡፡ የኤርትራን ህዝብ ልብ ማግኘት የሚቻለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ይህም ብቸኛ አማራጭ መሆኑን አረጋግጥልሀለሁ -

እኖሌ በተመስጦ ነበር ያዳመጠው፡፡ አብርሀ ንግግሩን ጋታ ሲያደርግ ግን እንደመባነን አለ፡፡ አያመነታም፣

- ሀሳብህ ያጉዋጉዋል፡፡ መንግስት ግን ይህን እንደ መፍትሄ ሀሳብ አይቀበለውም፡፡ ምክንያቱም ... አለና ሊል የፈለገውን መልሶ ዋጠው፡፡

ሻለቃ ዘውዱ አሰፋ ወሰለ፡፡ የቡርቃን ገበሬዎች ለማረድ አድርበት የነበረውን ስሜትና መስገብገብ ሲያስብ ዘገነነው፡፡ የእስረኛውን የሚያጉዋጉዋ ሀሳብ በየትም አለም ያሉ አምባገነኖች ከቶ አይቀበሉትም፡፡ አምባገነንነት ደግሞ ፖሊሲ ሳይሆን ባህርይ ነው፡፡ ባህርይን እንደ ፖሊሲ መሻር አይቻልም፡፡ ከቶ አይቻልም - እያለ ለራሱ አጉረመረመ - እኖሌ ዋቱ፡፡

በዚሁ ነበር ከአብርሀ ጋር የተለያዩት፡፡ ሲለየው ግን አደነቀው፡፡ እያደነቀው ነበር ወደ ቀጣዩ ስራው የተጉዋዘው፡፡

በመንገድ ላይ ታዲያ 'ሙማዬ' ተብሎ በቅፅል ስም ለሚጠራው ረዳቱ አንዳንድ ጥያቄዎችን አቀረበለት፡፡

- ስማ ሙማዬ፣ ወታደሮች የህዝቡን ከብት እየነጠቁ ያርዳሉ እንዴ?፡-

ሙማዩ ሳያመነታ ነበር ምላሽ የሰጠው ...

- ምናለበት? የወንበዴ ዘሮች አይደሉ እንዴ?፡-

- ልጃገረዶችንም እንትን ይላሉ የሚባለውስ?

- ሸንኩርቶቹ!? ቀምሰው አያውቁም እርሶ!? -

አኖሌ ልቡ ቀጥ ልትል ነበር፡፡ ጨቤ ልቡ ላይ የተሰካ ያህል አቃሰተ፡፡ ሙማዩ ግን እንዳሻው ማውጋቱን ቀጠለ፡፡

- ሸንኩርት ያልቀመሰ የጦር አባል በድፍን ኤርትራ ተፈልጎ አይገኝም፡፡ እኔ እንኩዋ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የገጠመኝ፡፡ ግን አቃታትና ሞተች -

አኖሌ ቆሌው ተገፈፈ፡፡ በመደነቅም ያየው ጀመር!

- አልቻለችኝም፡፡ የገዛ ነጠላዋን አልብሼያት ሄድኩ፡፡ የሰባ አመት ምህረት ታሪክ ነው የማወጋው፡፡ አሁንማ አግብቻለሁ፡፡ አስመራ ላይም ሸንኩርቶች እንደልብ አይገኙም፡፡ ገጠር ነው ምቹ፡፡ ያኔ ደሞ አዛገሮች ቀራጦች ነበሩ፡፡ በሉዋቸው ይሉናል፡፡ በዚህ ላይ ልጅነት አለ ...

አኖሌ መስማት ስለጨነቀው አቋረጠው!

- በል ፈጠን እያልክ ጎዳ፡፡ ዛሬ ስአቱም ሳይታሰብ እልም ነው ያለው፡-

... እምባሶይራ ሆቴል! በክፍሉ በረንዳ ላይ ሆኖ ውሉውን በማስታወሻ ደብተሩ እያሰፈረ ሳለ ስልክ ሙኸ፡፡ ሄዶ አነሳው፡፡ የሆቴሉ ኦፕሬተር መስመሩን ሲለቅለት! 'ሀለው!' አለ፡፡ የሴት ድምፅ ወደ ጆሮው መጣ፡፡ ውብ ድምፅ! ልስልስና ጥፍጥ ያለ፡፡ 'ሮዛ መሆን አለባት' አለ ለራሱ፡፡ አልተሳሳተም፡፡ 'ሮዛ እባላለሁ' ብላ ራስዋን አስተዋወቀችው፡፡ አማርኛዋ የትግርኛ ቃና ቢኖረውም ችግር ግን አልነበረበትም፡፡ አኖሌ የሚለው ስም አስቸግሮአት ቃል በቃል እየረገጠች ነበር የጠራችው፡፡ ስትለማመደው እንደቆየች አወቀባት፡፡ ቁጡብ መሆንዋን አኖሌ ፈጥኖ ገመተ፡፡ ጥሉበት የሰውን ባህርያት ወዲያው ወዲያው ፈርጆ ማስቀመጥ ይወዳል፡፡ ሙያው ያሳደረበት ተፅእኖ ሳይሆን አይቀርም፡፡

«ካንተ ጋር እንድንገናኝ ሳሙኤል ነገረኝ፡፡ አስመራን እንዳስጉበኝህ ጭምር፡፡ ሳልደውልልህ ዘገየሁ! ይቅርታ፡፡ ከከተማ ወጣ ብዬ ስነበትኩ፡፡ በድጋሚ ይቅርታ፡፡»





«ምንም አይደለም፡፡ የትና መቼ ነው ታዲያ የማገኝሽ?» ሲል ጠየቃት፡፡

«ነገ በስድስት ሰዓት በአስመራ አቆጣጠር፡፡ ባር ኢምፔሮ፡፡ ታውቀዋለህ ኢምፔሮን?»

«አውቀዋለሁ» ካለ በሁዋላ «... በምንድነው ታዲያ የማውቅሽ?» የሚል ጥያቄ አስከተለ!

«እኔ ስለማውቅህ ችግር የለውም» ስትለው አላመናትም፡፡

«የት ነው የምታውቂኝ?»

«ከሳሚ ጋር ጀርመን ላይ የተነሳችሁት ፎቶ አለኝ፡፡ መልክህ የሚጠፋ አይደለም፡፡ ፊትህ ላይ ደግሞ የማይረሳ ነገር አለ፡፡»

«ምን?» አለ አኖሌ፡፡

የልብ ምቱ ጨመረ፡፡ በሮዛ ግልፅነት መደሰት ጀመረ፡፡

«... ፊትህ ላይ ጥልቅ ሀዘን በሚገባ አነበብኩ፡፡ ፎቶህን ሳይ ሁልጊዜ ለነማማ ይህ ልጅ አንድ ያላገኘውና ያጣው ነገር ያለ አይመስላችሁም? እያልኩ ስወተውታቸው ፊትህን ትክ ብለው ይመለከቱና 'ለኛ ምንም አይታየንም' ይሉኛል፡፡ ታዲያ ይህንኑ አንድ ቀን ለሳሚ ስነግረው! እንባ እስኪወጣው ድረስ ስቆ ስቆ ሲያበቃ 'አኖሌ ምንም አሳዛኝ ፊት የለውም፡፡ እንደ ኦሮሞ ምድር የዱር አራዊቶች በደስታ የሚኖር ሰው ነው' አለኝ» ብላ ረጅም ሳቅ አሰማችው፡፡

አኖሌም አብሮአት እየሳቀ!

«ሳሚ ሙዞም ስለኔ ደግ ነገር ያወራል ብዬ አላስብም፡፡ ድራሹ ይጥፋ!» ካለ በሁዋላ «... አንቺ ስላደረብሽ ስሜት ግን በጣም ተገርሜያለሁ፡፡ እንዳልተሳሳትሽ ደግሞ አረጋግጥልሻለሁ፡፡ ከእርካታ ጋር የተፋፋቅሁ ሰው ነኝ፡፡ ያን ስሜት ይሆናል ያነበብሽው፡፡ ዞሮ ዞሮ ስለኔ ጥቂት በማሰብሽ አመሰግንሻለሁ፡፡ ካንቺ ጋር ማውራትና መግባባት ይቻላል የሚል ስሜት ጭምር ክልብ አሳድሬያለሁ፡፡ የነገው ቀጠሮም ፈጥኖ እንዲደርስ እመኛለሁ፡፡»

«እኔም ቸኩያለሁ» አለችው ከልብ በሆነ ድምፅ፡፡

«በይ ቻዎ ሮዚና!»

«ግራሴ ቼቬዲያሞ!»

ስልኩን ዘግቶ ወደ በረንዳው ተመልሶ የማስታወሻ ደብተሩን ማገላበጥ ቀጠለ፡፡ አኖሌ በቀን አስራ ስድስት ሰአት ነው የሚሰራው፡፡

እስረኞችን፣ ህዝቡን፣ የታሪክ ሰዎችን፣ ጄኔራል መኮንኖችን፣ ተራ ወታደሮችን፣ ከፍተኛና መስመራዊ መኮንኖችን ያነጋግራል። ውሎውን ደግሞ በየእለቱ ወደ አዲሳባ ሪፖርት ያደርጋል።

የአስመራ የህዝብ ደህንነት ሹም ኮሎኔል ዝናው ዘውትር ተሲያት ላይ እየደወለ ማምሻውን ካልጋበዝኩህ እያለ ቢያስቸግረውም ከአንድ ምሽት በላይ አልተገኘለትም። ጉረኛና ቅብጥብጥ በመሆኑ ጠልቶታል። ሆኖም ማንኛውንም መረጃ በጠየቀው መሰረት በፍጥነት ስለሚያቀርብለት ምንጊዜም የሞቀ ፈገግታውን ይቸረዋል። እንደሁኔታውም በጉራ ለተወጠረች መንፈሱ ምግብ ይሆን ዘንድ ሽርፍራፊ አድናቆቶችን ይወረውርለታል።

አኖሌ በአስር ቀን ውስጥ የሰበሰባቸውን መረጃዎች እየገለባበጠ ይፈታትሽ ጀመር። ካነጋገራቸው በርካታ እስረኞች መካከል ሶስት የኢትዮጵያ ወታደሮች የእንባ ከረጢቱን አስፈትተውታል። ስለ ህዝብና ዴሞክራሲ፣ ስለሰላምና ጦርነት አጥብቆ እንዲያስብም አድርገውታል። በነዚህ ወታደሮች ምክንያት የራሱን ፖለቲካዊ እምነት ለመፈተሽ ጭምር ተገዶአል። በተለይ ፍትህ የማግኘት ጥያቄ በህሊናው ደጋግሞ ጮኸ። ስለመንግስት ባለስልጣናት ህሊና ጭምር አሰበ። በርቀት ሲያስባቸው ፈራቸው። በእኒያ ሶስት ወታደሮች ምክንያት ስለራሱ የጉዞ አግጣጫ ደጋግሞ ለማሰላሰል ተገደደ። እራሱ ለሚያቀርበው ስፍር ቁጥር የሌለው ጥያቄ ምላሽ ግን አያገኝም። ከሶስቱ ወታደሮች ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ ቀይታ ሲያስብ ያልተለመደ የአመፅ ስሜት በመላው ሰውነቱ ተሰራጭቶ ይሞቀዋል! የእኒያ ሶስት ይነዝረዋል። ንዝረቱ ከስቃይ ጋር የተቀላቀለ ነበር። የእኒያ ሶስት ምስኪን ወታደሮች ገፅታ ፊቱ ድቅን ሲል ራሱን በነርሱ ቦታ አስቀምጦ ይሰቃያል ...

... ሞት የተፈረደባቸውን እስረኞች መዝገብ ሲያገላብጥ ነበር ስማቸውን ያገኘው። የመቶ አለቃ አክሊሉ ይባላል - መጀመሪያ ያነጋገረው ወታደር። ገና ያየው እለት በመኮንኑ ገፅታ ላይ ፍርሀት ሳይሆን ተስፋ ማጣትን ነበር አኖሌ ያነበበው!

- ምን አጥፍተህ ታሰርክ? - ይለዋል።

- አዛዤን ገድዬ፡-

- ምክንያቱን ታብብራልኛለህ?»

መኮንኑ ታሪኩን አሳጥሮ አጫወተው።

ጊዜው ከሶስት ወራት በፊት ነበር ...





ከሰራዊና ከሀማሴን አውራጃዎች የተመለመሉ የህዝባዊ ሰራዊት አባላት ጊንዳእ በሚባል ቦታ መከላከያ ይዘው እንዲቀመጡ ከተደረገ በሁዋላ ምፅዋ አካባቢ ያለች አንድ ኮረብታ ለመያዝ ውጊያ እንዲከፍቱ ታዘዙ። የዚህ ውጊያ አላማ እኒያ ሰዎች ኤርትራውያን ስለሆኑ እሾህን በሾህ እንዲሉ እርስ በርሳቸው ከተጫረሱ በሁዋላ ሻእቢያ ሲዳከም መደበኛው ጦር እንዲዋጋና የመደበኛ ሰራዊቱን መስዋእትነት ለመቀነስ ታስቦ ነበር። የህዝባዊ ሰራዊቱ አባላት ግን ይህን ስለተረዱ ውጊያ ሲጀመር ጥይቱን ወደ ሰማይ ይረጩት ጀመር። የሻእቢያ ተዋጊዎችም ሁኔታውን ስለተገነዘቡ የምላሽ ተኩሳቸውን ወደሰማይ ላኩ። አዛዡ 'ተነቃነቅ!' እያለ ቢያንባርቅም ሽማግሌዎቹ ካሉበት አልተነሱም። አባትና ልጆች በደመነፍስ ተግባቡ። ሊጎዳዱ አልቻሉም።

አስመራ ያለው የሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊት አዛዥ ይህ «የአባትና ልጆች ቀልድ» ሪፖርት ሲደረግለት ለመቀጣጫ ሃያ ወታደሮች እንዲረሸኑ ያዛል። ተረሸኑ። ይህ እርምጃ ሁለት ሺህ የሚሆኑትን ኤርትራውያን ሽማግሌዎች ክፉኛ አስቆጣ። ቁጣው እያደገ ሄደናም የሰራዩና የሀማሴን አውራጃዎች የህዝባዊ ሰራዊት አባላት የነበሩበትን ተራራ ለቀው መውረድ ጀመሩ።

ጉዞ ወደ አስመራ ሆነ።

ፖለቲካ ሀላፊዎች በዚህ ድንገተኛ አመፅ ይደናገጣሉ። በመንገድ ላይ ቀድመው ይለምኑዋቸዋል። ወይ ፍንክች! ያስፈራሩዋቸዋል። ወይ ንቅንቅ! ጉዳዩ ጄኔራል ሁሴን ዘንድ አስመራ ደረሰ። ጄኔራሉ ብዙ አላሳሰባቸውም። 'ረሽኑዋቸው' ሲሉ አዘዙ። አመፅን በማፈን የሰለጠነ አንድ የኮማንዶ ሀይል ወደ አስመራ የሚጉርፈውን የሽማግሌዎች ሰራዊት እምባደርሆ ከተባለች መንደር አካባቢ በአንድ ኮረብታ ስር አውቶማቲክ መትረየሶችን ጠምዶ አድፍጦ ጠበቀው። ሽማግሌዎቹ ኤርትራውያን እየተግተለተሉ የሞት ቀለበት ውስጥ እንደገቡ የእሩምታ ተኩስ ዘነበባቸው። አብዛኛው ሞተ። ከፊሉ ቆሰለ። የሞቱት በደም የተቦካ ጭቃ መሰሉ። በዚህ ዘመቻ የመገናኛ መኮንን የነበረው መቶ አለቃ አክሊሉ ህዝባዊ ሰራዊቱ ላይ የጥይት ዶፍ ሲዘንም እሱ ወባ እንደያዘው ሰው ይንቀጠቀጥ ነበር። አዎን ትዝ አለው - የሚስቱ አባት ከአመፅኞቹ መሀል መኖራቸው። ሚስቱን ከራሱ በላይ ያፈቅራታል። ለአባትዋ ያላትን ስስትና ፍቅርም ያውቃል። ተኩሱ እንዳለቀ በደመነፍስ ነበር በደም ወደተጥለቀለቁት ሽማግሌዎች የበረረው። ይፈልግ ጀመር - የሚስቱን አባት። አገኛቸው - እግራቸው ቆስሎ። እግዚአብሄርን አመሰገነ። በደስታ ራሱን መቆጣጠር አቃተው። እንደምንም ከወደቁበት ደግፎ አነስቶአቸው በሬሳ መሀል ሲያቋርጥ አዛዡ ሻምበል ታምሩ

ያየዋል፤

- ምን እያደረግክ ነው መቶ አለቃ አክሊሉ?፡-

- አማቹ ናቸው - ይላል በልመና ስሜት፡፡

- አብዮት ልጅዋን ትበላለች፤ ጣለውና ጨርሰው -

- ጉዋድ ሻምበል እባክዎ ዛሬን ይዋሱልኝ፡፡ በህይወቴ እከስዎታለሁ፡-

- ግደለው፤ ትእዛዝ ነው፡-

አክሊሉ አማቹን ለቀቃቸው፡፡ አይኖቹ ግን ሻምበሉን ይማፀኑ ነበር፡፡

- ግደለው፡-

- አይሆንልኝም ጉዋድ ሻምበል፡-

ሻምበሉ ሽጉጡን መዞ የሽማግሌውን ግምባር ለሁለት ገመሰው፡፡ ሽማግሌው በአፍጢማቸው ተደፉ፡፡ መቶአለቃ አክሊሉ ራሱን አላወቀም፡፡ ጣቱን የጠመንጃው ምላጭ ላይ አሳረፈ፡፡ ሳበው ... ሳበው ... አልለተቀቀውም፡፡ አስራ አምስት የክላሽንኮቭ ጥይት በሻምበሉ ደረት ላይ ጠቀጠቀ፡፡ እና እጁን ለመንግስት ጠሰ፡፡

አኖሌ የአስረኛውን መቶ አለቃ ታሪክ በመደነቅ ሰምቶ ሲያበቃ፤

- በጥፋትህ ምን እንደተፈረደብህ አውቀሀል?፡- ሲል ጠየቀው፡፡

- ሞት፡- አለ፤ ገፅታው ላይ የተቃጠለ ስሜት እየተነበበ፡፡

- መቼ ነው ታዲያ ቅጣቱ ተፈፃሚ የሚሆነው?፡-

- የፊታችን አርብ ከሰአት - ካለ በሁዋላ - እየሱስም አርብ ነበር የተሰቀለው - ሲል አከለበት፡፡ በእሳት የተለበለበ ግንድ የመሰለ ገፅታው በድንገተኛ ተስፋ ተሞላ፡፡

- አሁን ምን ይሰማሀል?፡-

- ደስተኛ ነኝ፡-

- ለምን?-

- ሚስቴ የሆነውን ሁሉ ከሰማች በሁዋላ አንድም ጠብታ እንባ አልወጣትም አሉ፡፡ ጠጉርዋን ሹሩባ ተሰርታ፤ እጥርጥር ለብሳ የእለቱ እለት ኲምቢሽታቶ ላይ መታየትዋን ስሰማ ደስታ ተሰማኝ፡፡ በህይወቴ ቢያንስ አንድ መልካም ተግባር ፈፅሜያለሁ፡-





- ኢትዮጵያን እንደከዳህ አይሰማህም?፡-

- በጭራሽ፡-

- እንዴት?

- እዚህ ያሉት ሰዎች ደጋጎች ናቸው፡፡ ይሄም ቢሆን የተፈጠሩበት መሬት ነው፡፡ በገዛ መንደራቸው ምን ፍጠሩ ነው የምንላቸው? ጠሩ ደግሞ አይናገርም እንጂ ማንም ቢሆን ኢርትራ መቆየት አይፈልግም፡-

- ማነው ስምዋ ሚስትህ?፡-

- ምዕላል - ካለ በሁዋላ - በጣም ነው የምትወደኝ፡፡ ወላጆችዋ የሸዋ ሰው አታግቢ ብለው አስቸግረዋት ነበር፡፡ የወንድምሽን ገዳይ እንዴት ታገቢያለሽ? ይሉዋት ነበር፡፡ ተቀይመዋትም ነበር፡፡ አሁን ሞት ለምን እንደተፈረደብኝ ሲሰሙ ግን መጥተው ይቅርታ ጠየቁኝ፡፡ በተለይ አንድ አጐትዋ ጉብ ሰጥተው እንዲያነጋግሩኝ ሲፈቅድላቸው 'ላመንክበት አላማ መሞትህ ጀግንነት ነው፡፡ ከሳህል ጀግኖች ለይቼ አላይህም' ብለው በጆሮዬ ነገሩኝ፡፡ ግንባሬ ላይ ስመው ጭምር ተሰናበቱኝ፡፡ እንዲህ ሲሉኝ ተንሰቅስቄ አለቀስኩ፡፡ ከንቱ ሞት አለመሞቴ ታወቀኝ፡፡ ደሞ አንድ ወንድ ልጅ አለኝ፡፡ ልጁ በኔ ታሪክ የሚደሰት ይመስለኛል፡፡ እዚህ ያሉት ውሾች ፖሊሶች ግን ከሰው የተፈጠሩ መሆናቸውን እጠራጠራለሁ፡፡ እኔ ገና ሳልገደል በሚስቴ ውበት ተማርከው ለጋብቻ ጠየቁዋት፡፡ እስክገደል እንኳዋ ቢታገሱ ምናለ? ግን እኔ ከተገደልኩ ሚስቴ እዚህ ስለማትመጣ ያንጊዜ አናገኛትም ብለው ሰግተው ይሆናል፡-

- ባለቤትህ ትጠይቅሃለች?፡-

- እስክረሽን ድረስ በቀን ሰላሳ ብር ጉቦ እየተከፈለ ለሁለት ደቂቃ እንድንገናኝ ዘመዶችዋ አመቻችተውልናል፡፡ አሁን እንኳዋ ሁለት ቀን ነው የቀረኝ፡-

- የትውልድ መንደርህ የት ነው?፡-

- አታውቀውም፡-

- ንገረኝ አውቀው ይሆናል፡-

- ጋሱሬን ታውቃታለህ? - አለ አክሊሉ ፈገግ ብሎ፡፡

- የት ነው ልጄ?፡-

- እንዲት የጉራጌዎች የገጠር ቀበሌ ናት፡- ብሎ ትክዝ አለ፡፡

አኖሌ ከተሰጡት ፋይሎች መካከል የሞት ፍርድ

የተፈረደባቸውን የጦር ሰራዊት አባላት ቅድሚያ ሰጥቶ ነበር ያነጋገራቸው:: ፀረ-አንድነት ግጥም ፅፎ በግብር ቤቱ በራፍ ላይ ከሚገኘው የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፉ ሞት የተፈረደበት ወጣትም ትኩረቱን ስለሳበው ከመቶ አለቃ አከሊሉ ቀጥሎ እንዲቀርብለት ያዘዘው እሱን ነበር:: ለአኖሌ በረዳትነት የተመደበው ሙማዬ ይህን እስረኛ ላለማቅረብ አንገራግሮ ነበር::

- እብድ እኮ ነው ጌታዬ:-

- ይሁን አምጣው!:-

- በወሬ ያደርቆታል:: አራት ነጥብ አያውቅም:-

- ሻለቃ ባሻ ያዘዝኩህን ብቻ ፈፅም:- ብሎ ሲቆጣው እንደ እርጉዝ ፈረስ የተለጠጠ ሆዱን እያወዛወዘ ውልቅ አለ:: ባሻው ቀኑን ሙሉ ስለስጋ አውርቶ አይታክትም:: ከአኖሌ ጋር ሲተዋወቅም!

- አገልጋይዎ ሆኜ ተመድቤያለሁ:: የቢላዋው ስለት ስጋውን ያሳምረዋል እንዲሉ ስራዎ እንዲሳካ ብልት ብልቱን አሳይዎታለሁ:- ሲል ነበር የጀመረው::

አኖሌ ውፍረቱና ቃላቱ ስለተገጣጠመበት ከልቡ ነበር የሳቀው:: ስድቡም 'አኛ ስጋ! ጅማታም የመሳሰሉ ሲሆኑ ሲያደንቅም 'ሙማዬ! ፍርምባዬ' ማለት ይቀናዋል:: ለአስመራ ጄኔራሎች የአመት በአል በግ በመግዛት ዝናን አትርፏል:: በግ ሲመርጥ ከበጉ ድድ ጀምሮ ሆዱ ውስጥ ጭድ አለመስግሰጉን! ኩላሊቱን! ብልቱን! ኮቴውን! የጠጉር ቀለሙን! አገላብጦ ይመረምራል:: የተማረና ያልተማረ የሚላቸው በጉችም አሉት:: ከተማ ውስጥ ወረቀት እየበሉ ያደጉትን በጉች የተማሩ በጉች ይላቸዋል:: እንደሱ እምነት ስጋቸው አፈር አፈር ይላል:: የቅርጫ ወሬ ከተሰማ ከተፍ ነው:: ገንዘብ ከሌለው ከሻኛው አንድ ጉርሻ ቀምሶ ይመለሳል:: ቅፅል ስሙም ሙማዬ ሆኖ ቀርቶአል:: አኖሌ ስለዚሁ ስጋ ወዳድ ረዳቱ በተመስጦ እያሰበ ሲገረም ነበር እብድ የተባለውን እስረኛ ይዞለት ከተፍ ያለው::

- ይሄው ጌታዬ ... እንግዲህ ቢላውም ሰንጋውም ይኸው:: ችግር ከፈጠረቦት ግን ይንገሩኝ:: እዚሁ አለሁ:- ብሎ ውልቅ አለ:: ሞት የተፈረደበት ምስኪን ወጣት ጭብጥ ብሎ ወንበሩ ላይ ቢቀመጥም አይኖቹ ግን እንደ እባብ አይን ያለማረፍ ይካለቡ ነበር:: ጤነኛ አይመስልም:: ለመናገር እንዳቆበቆበም ይታወቅበታል::

- ምን አጥፍተህ ታሰርክ? - ሲል ጠየቀው::

- መልካም!:- ብሎ ተመቻቸ - ከስር መሰረቱ ልናገር?:-





- ቀጥል:-

- ተራራው ክፍለጦር በ1973 ሲመሰረት ከአዲሳባ ነው ወደ ውትድርና የገባሁት:-

- የህይወት ታሪክህን ተወውና የታሰርክበትን ምክንያት ብቻ ንገረኝ:-

- የታሰርኩትማ በማይረባ ግጥም ነው:: ዞሮ ዞሮ ግን ይህን ሁሉ ተንኮል የጉነጉነው ሌጊዮን ነው:-

- ማነው ሌጊዮን?:-

- ጋኔን ነዋ!:-

አኖሌ በርግጥም የወጣቱ አእምሮ መነካቱን ተገነዘበ:: እና በርጋታ ያወጋው ጀመር ...

- በል ቀጥል ... ከጋኔን ጋር ደሞ ምን አጋጫችሁ?:-

- እኔ ዲያቆን ነበርኩ:: ድንግሊትዋን ቅድስት ማርያምን ለማገልገል ቅሌን ጨርቄን ሳልል በልጅነት ነው ወደ ገዳም የገባሁት:: ለካ ሌጊዮን ይከታተለኛል:: የድንግሊቱ ቀንደኛ ጠላትና ስም አጥፊ እንደመሆኑ እምዬ ማርያምን ማገልገሌ አብከንክኖት ኖሮአል:: አንድ ቀን አገኘኝ! ያለወትሮዬ አስረሽ ምቺው ጠጅ ቤት ቁጭ ብዬ ስጠጣ ቆየሁ:: በመካከሉ ፊኛዬን ከፉኛ ይዞኝ እከፍላለሁ ብዬ በጉዋሮ በር ብቅ አልኩ:: ፊኛዬን ስለያዘኝ ሩቅ መሄድ አቃተኝና በጉርድ በርሜል ከቅንጭቡ አጥር ስር ከተቀመጠ የጠጅ አተላ ላይ መሽናት ጀመርኩ:: ለካ ሌጊዮን በርሜሉ ውስጥ ተቀምጦ የጠጁን አተላ እየተስገበገበ ይውጥ ኖሮአል:: የሚያቃጥለውን የጠጅ ሽንት ገበቴ በሚያህል ጆሮው ስለቀበት በርግጎ የአተላውን በርሜል እግሬ ስር ደፍቶ ከማድቤቱ ግድግዳ ተላተመ:: እኔ ምናገባኝ ብዬ ሽንቼ ስመለስ ተከትሎኝ መጣና!

- ማን እንደሆንኩ ታውቃለህ? - አለኝ

- ማንም ሁን! ችግርህ ነው:- አልኩት::

- ሌጊዮን የምባለው ሀይለኛው ጋኔን እኔ ነኝ - አለኝ::

- ችግርህ ነው:- ብዬው ሂሳቤን ከፍዬ ውልቅ ልል ስል! ጠጅ ቀጅዋ ሁለት ብር ሰጥቼያት አንድ ነው የሰጠኸኝ ብላ ካደች:: ያኔ ገባኝ:: ሌጊዮን አንዱዋን ብር ሰቦአት ኖሮአል:: እኔ ታዲያ ወደሰፈሬ ስመለስ ልክ ልኩን ነገርኩታ:-

- የት አገኘኸው?:-

- የሱን ማምሻ ደሞ አጣሁት!? ሴተኛዳሪዎቹ ሰፈር ሲያቃጥር አይደል እንዴ የሚያመሸው? ሰው ከጠጣለትና ከተዳራለት ክንፍ ያለው ነጭ እሀያ ላይ ሉጋም አስሮ በደስታ ሲጋልብ ያድራል:: ታዲያ ልክ ልኩን ነገርኩታ! ቂራ ላይ ብዙ ተባባሪ ስላለው ሁሉም ይስማና ይለይለት ብዬ - ፍፃሜ መጥቶአል! - እያልኩ ጮህኩ:: - መወርወሪያ የሌለሽ ሴት - መቋቋሚያ የሌለህ ወንድ - ሌጊዮንን አስደስታለሁ ብለህ ካቅምህ በላይ አረቄ ተግተህ ከደም ጋር የተቀላቀለ ትውከት በየጉዳናው ያዘረበረብህ ሁሉ ወዮልህ! ደም ታራለህ! ዘመኑ ሰዎች ደም የሚያፍሩበት ዘመን ነው:: የአዳም ዘር፤ የሄዋን ዘር መልአከ ሞት አንዣቦብሻል ... ከሌጊዮን ጋር ያበርሽ ሁሉ ታውቆብሻል:: አስራ ሶስት ክንፍ ያለው መልአከ ሞት ተልኮብሻል:: ሞት ጥቁር ክንፉን ሲዘረጋብሽ ሰማያዊ የሀር ብርድ ልብስ እስኪመስልሽ ድረስ ትዘናጊያለሽ ከየመስኪያው ጭላጭ አረቄ አንቃረሽ ፍትወት ያማረሽ ሴት ወዮልሽ! መጋረጃሽን ከልለሽ በድብቅ የሰራሽው ያልታየ መስሎሻል - ጉድፍሽ ሁሉ ተገልጦአል ... ከድሃው በገፈፍሽው ገንዘብ ወሰራ ዶሮ ገዝተሽ አንገትዋን እንደታጠበ ጋቢ እየጠመዘዝሽ ለሌጊዮን የገበርሽ - ወደሲኦልሽ ተብለሻል:: አይኔም አይራራ ብር ስትይ እም-ብር-ትሽ ይተረተራል - አይንሽም ይበራል - አንቺ በር አፍ ተብለሻል ... እያልኩ ድፍን ቂራን አሳደምኩበት:: በዚህ ተናዶ እስከእለተ ሞቴ እንደማይለቀኝ ምሎ ተገዝቶ በህልም ነገረኝ:: ይኸው እስተዛሬ ይዞኛል:-

- ስነፅሁፍ ትወዳለህ?:-

- ኧረ እኔ እቴ ... ዜማ እንጂ ግጥም እምብዛም ነኝ:-

- ፀረ - አንድነት ግጥም በመፃፍ ነው የተወነጀልከው?:-

- አዎን! ያቺ መዘዘኛ ግጥም ናት ጉድ የሰራቺኝ:: እኔ ገጣሚ አይደለሁም:: ሌሊት ጨረቃዋ እንደ ወትሮው ሳትደምቅ ብትቀር ጊዜ 'ምን ሆነች?' ብዬ ብዙ አሰብኩ:: ሁዋላ 'ወይዘሪት ዝምታ' አልኩዋት:: ድንገት ሌጊዮን ሲያስተኝ ደሞ የመጣልኝን ግጥም ቢጤ ጫጫርኩና ኪሴ አኖርኩዋት:-

- ግጥሙን ታስታውሰዋለህ?:-

-የማይረባ ነውኮ:: ትንሽ ናት:-

- ካስታወስከው እስኪ ንገረኝ?:-

ንኩ ወታደር በጥሩ ዜማ በቃሉ ያምበለብለው ጀመር፤

*እንደምን አመሸሽ - ወይዘሪት ዝምታ*

*ዛሬስ ምን አገኘሽ - ፀዳልሽ ተፈታ*





*ፋናሽ ተሙዋሙዋተ - ሀሴትሽ ተገታ*

*ደከመ ፈገግታሽ - ገፅታሽ ፈዘዘ*

*ብርሃንሽ ባይጠፋም - ሳቅሽ ደበዘዘ*

*ጆሮዬም ላይ አለ - የትካዜሽ መዝሙር*

*እየጠቀጠቀ - ልብን የሚነዝር*

*ምንድር ነው ምክንያቱ - ያዘንሽበት ጉዳይ*

*ምን አየሽ ጨረቃ - ኤርትራ ወይ ትግራይ*

*በተራሮች አናት - የደም ጉርፍ አለወይ?*

*ይለማል ወይ ጨኸት - እንጉርጉሮ መሳይ*

***ወይንም ይታያል ወይ - ሸገር እምብርቱ ላይ***

***እዚያ መሀል አገር - ይታያል ወይ ደስታ - እስከስታ ፍንደቃ***

***ይሰማል ወይ ሆታ - የታምቡር ድለቃ***

*ድሪያና ዳንኪራ - የውድቅት ሙዚቃ*

*እስኪ ተናገሪ - ምንም ሳታስቀሪ - ወይዘሪት ጨረቃ*

ግጥሙ እንግዲህ ይሄ ነው:: ማርያምን! ዕፌ ኪሴ ነበር ያኖርኩት:: በሶስተኛው ቀን ሌጊዮን ግጥምዋን ከኪሴ መንትፎ ግብር ቤቱ ደጃፍ ላይ ካለው የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለጠፈው:: ጠዋት ወታደሩ ሁሉ አነበበው:: ግማሹ ገለበጠው:: እኔ ፈርቼ ዝም አልኩ:: 'ማነው?' ሲባልም አልተናገርሁ:: ሁዋላ ሁሌ ግጥም ይፅፍ የነበረ ዝማሙ የሚባል የብቸና ልጅ ተይዞ ሲታሰር መቼም ክርስቲያን ነኝ፤ ሌላው ቢቀር በኔ ጦስ ሰው ሲጉዳ የማምናት ድንግሊቱ ምን ትለኛለች ብዬ 'እኔ ነኝ' የፃፍኩት አልኩ:: አዛዡም ግልፅነቴን አይተው አንድ ወር ያለ እረፍት ከባድ ስራ እንድሰራ አዘዙ:: ቅጣቴን ጥርሴን ነክሼ ጨርሼ ነበር:: ዳሩ ምን ያደርጋል ሌጊዮን ነገር ጉነጉነብኝ፤

- ቅጣትህን ከጨረስክ በሁዋላ ታዲያ እንደገና ለምን ታሰርክ? ሞት ሊፈረድብህስ እንዴት ቻለ?:-

- ወታደሮቹ አባባሉታ:-

- እንዴት?:-

- የሰከሩ ሌሊት ምሽጋቸው ውስጥ ሆነው ሚስቶቻቸውን፤

ልጆቻቸውን፣ ወላጆቻቸውን ዘመዶቻቸውን፣ መንደራቸውን ሲያስታውሱ ጨረቃን እያዩ 'ወይዘሪት ጨረቃ ... ወይዘሪት ዝምታ .. ዝዋይ ላይ አማትረሽ ... ደሴ ላይ አማትረሽ ... ጅማ ላይ አማትረሽ ... ሞጆ ላይ አማትረሽ ... ከሰማሽም መርዶ ... ወይም እንጉርጉሮ ... የትካዜ መዝሙር ... ባክሽ ተናገሪ ... የስንታችን ሚስቶች በናፍቆት ጠቆሩ? የስንቶቻችንስ ለሌላ ተዳሩ? የስንታችን ልጆች ሳይበሉ አደሩ? ወይዘሪት ዝምታ ... ባክሽ ተናገሪ ... ምንም ሳታስቀሪ ... ቅንጣት ሳትጨምሪ ... እያሉ አባባሉት:: አንድ ቀን ስሌዳው ላይ 'ወይዘሪት ጨረቃ ሆይ! ለእናቴ በላክሁት ገንዘብ አዲሳባ ላይ ቤት የሰራው ጄኔራል ማን እንደሆነ አይተሽ ንገሪኝ?' የሚል ፅሁፍ ተለጥፎ አደረ:: በሌላ ቀን ደግሞ አንድ የሰከረ ወታደር ማታ ላይ' ወይዘሪት ጨረቃ! ሚስቴ በዚህ ሰአት ከማን ጋር እየተዳራች ነው?' ብሎ ሲጮህ፣ ሲያለቅስ ቆየና ራሱን ገደለ:: እየቆየ የጨረቃን መውጣት ወታደሮች በናፍቆት ይጠብቁ ጀመር:: ከዚያ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው 'ወይዘሪት ዝምታ ... ልጆቼ ራት በልተው ይሆን?' ሲሉ ይጠይቃሉ:: ታዲያ ሁኔታው ሲባባስ የኰሩ አዛዥ በዚሁ ጉዳይ ላይ ጦሩን ሊያነጋግሩ መጡ:: ወታደሩን በሙሉ ሰብስበው ማታማታ ከጨረቃ ጋር የሚደረገው መነጋገር መታገዱን ገለፁ:: ይኸኔ አላንጉ የሚባል አንድ የወላይታ ልጅ እጁን አውጥቶ፣

- ይህ ችግር አሳሳቢ ከሆነ ለአብዮታዊ መንግስታችን የሚሳነው ነገር ስለሌለ ጨረቃዋ ወደ ግምባር እንዳትመጣ ለምን አትታገድም?:- ብሎ ሲጠይቅ ጦሩ ሁላ በጣም ሳቀ::

ስብሰባው እንዳለቀ አላንጉና እኔ ታሰርን:: እሱ ማምሻውን ተገደለ:: እኔ እስካሁን ቆይቻለሁ:-

«የኤርትራን መገንጠል በመደገፍ» በሚል ምክንያት የታሰረ አንድ ተራ ወታደር አስጠርቶም አነጋግሮ ነበር:: ከእስረኛው ጋር የግማሽ ሰአት ቆይታ ካደረገ በሁዋላ ግን ከልብ አዘነ:: ያዘነው ለስርአቱ አራማጆች እንጂ:: በድብደባ ብዛት ለእስረኛው አልነበረም:: ራሱን በመሳት ላይ ያለ ከሚመስለው እስረኛ ጋር ያደረገው ቆይታ ይህን ይመስል ነበር፣

- ስምህ ማነው?:-

- የኔ ስም?:-

- አዎ ያንተ ስም?:-

- ስሜ እንኩዋ ... መኩዋንንት:-

- የትውልድ ቦታህ?:-





- የተወለድኩት?:-

- እህ:-

- ምንጃር፣ ነዋሪነቱ ግን ሞጆ:-

- ፋይልህ ላይ ግን አያሌው የሚል ስም ያነበብኩ ይመስለኛል:- አለ እኖሌ እየተጠራጠረ::

- ልክ ኖት:: በመኩዋንንት የሚጠራኝ የለም:: 'አያሌው ሞኙ' ነው የሚሉኝ:: በቅፅል ስሜ መጥራት ነው የለመዱት:: ጥንት አያሌው የሚባል ሞኝ ነበረ ይላሉ:: እኔንኩዋ አላቀውም:-

- አንተን ለምንድነው 'ሞኝ' የሚሉህ?-

- የሞኝነት ጣጣ ከልጅነቱ ነው የተከተለኝ:-

- **እንዴት? እስኪ አብራራልኝ?:-**

- **እኔ አልተማርሁም:: ያልተማረ ደሞ ከተማ ከገባ ስራ አያገኝም:: ሸክም ነው:: እኔም ታዲያ ከምንጃር መጥቼ ሞጆ ላይ እሸክም ነበር::** የሞጆ ሰው ሁሉ ትዳር ይዞ ሲያልቅ እኔስ ከማን እንሳለሁ ላግባ ብዬ ስነሳ ሴቱ ሁሉ አሻፈረኝ አለ:: ሴቱ ተሸካሚ አናገባም አለ::

ከዚያ የገዘሆኔ ህመም የተጠናወታት ፈት አገኘሁና ተስማማች፣ አገባሁዋት:: ድፍን ሞጆ ጉድ አለ:: በአለም ላይ እኔን የመሰለ ሞኝ ተፈጥሮ እንደማያውቅ በቀን ሀያ ጊዜ ይነግሩኛል:: ያገባሁዋት ሚስቴ አከታትላ ሁለት ወለደችልኝ:: ወንድና ሴት:: እንደገና ጉድ ተባለ:: 'አባት መኮኑ ነው ወይ?' አሉኝ:: ሞጆ ያለውን ይበል ብዬ የልጆቼን ስም 'ንጉሱ' እና 'ልእልት' ብዬ ጠራሁ:: 'ወገኛ!' እያሉ አፌዙ:: 'ቂላቂል' እያሉ ተዘባበቱብኝ:: ሚስቴ ታዲያ ድህነቱ አቅም አሳጣትና አረፈች:: ጥቂት ሆነን ቀበርናት:: ከሚስቴ እረፍት በሁዋላ ጉጆዬ ጨለመችብኝ:: መላ ባገኝ ብዬ ለምክር ወደ መንደራችን ቄስ ሄድኩ:: 'መምሬ ደስታ' ይባላሉ:: የሀይማኖቱን ስርአት ስለማያከብሩና ንክ ናቸው ስለሚባል 'መምሬ አብደላ' እያለ ነው ነዋሪው ሁሉ የሚጠራቸው:: እሳቸው ዘንድ ሄጄ፣

- ልጆቼን ምን ላብላ፣ ቸገረኝ - አልኩዋቸው::

- እኔን አማክረህ ነው ወይ የወለድካቸው?:- አሉኝ::

- ከቄስ አንደበት ይሄ ቃል ይወጣል ወይ?:- አልኩዋቸው::

- እሱን ሂድና ለናትህ ንገራት:- አሉኝ::

- እርስዎ ግን ሰባራ ጋን ቢጤ ኖት:- አልኩዋቸው::

- አንተ ደሞ የእህያ ወገብ ነህ፦ አሉኝ።

በዚሁ ተለያየን። ቢቸግረኝ ነገር አለሙን እርግፍ አድርጌ ትቼ ወታደርነት ተቀጠርኩ።

- ልጆችህስ?፦ ሲል ጠየቀው አኖሌ።

- ትቻቸው ጠፋሁ። በቂ ገንዘብ ባልተውላቸውም የሚያኮራ 'ስም' ሰጥቼያቸዋለሁ። 'ንጉሱ' እና 'ልእልት' የሚባሉት ስሞች የትም አይገኙም፦

- ወታደርነት ከተቀጠርክ በሁዋላ ልጆችህ ትገዛ ብለውህ ያውቃሉ?፦

- በጭራሽ፦

- ለምን?፦

- ትገዛ ቢሉኝ ምን አመጣለሁ? አላበላቸው አላጠጣቸው፦

- ለምን ወሰድክ ታዲያ?፦

- ሁሉም ይወልዳላ! በቅሎ አይደለሁ ከሰው ተለይቼ ሳልወልድ የምቀረው?፦

- በል ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ። የኤርትራን መገንጠል መደገፍህ ነው የሚገለፀው ይሄ እውነት ነው፦

- አንድም ሀቅ የለውም!፦ ሲል ጮኸ እስረኛው።

- በምንድነው ታዲያ የታሰርከው?፦

- በአንድ ክፉ ቀን ስብሰባ ተብሎ ከየምሽጋችን ተጠራን። ተሰበሰብን። 'ካድሬ ንግግር ያደርጋል' ተባለ። 'እሺ' አልን። ካድሬ ስለ ኤርትራ ተናገረ። ተናገረ። ተናገረ። እኛ ሰማን። ሰማን። ሰማን። በመጨረሻ 'ታዲያ ኢትዮጵያ አንገትዋ ተቆርጦ ያለባህር በር መኖር ትችላለች ወይ?' ብሎ ጠየቀን። እኛ ስራችን መስማት ስለሆነ ዝም አልን። እሱ ግን 'ያዙኝ ልቀቁኝ' አለ። 'ኢትዮጵያ ሀገሬ'! ያለባህር በር ትኖራለች ወይ!?' እያለ እንባው ሁሉ ወረደ። ካሁን አሁን ጋብ ይላል ብንል ባሰበት። 'ንገሩኝ! ንገሩኝ! የባህር በራችንን ለማቆየት ከመዋጋት ሌላ ምን አማራጭ አለ!? ንገሩኝ!? ንገሩኝ!? ንገሩኝ!?' እያለ ሲትከነከን እጄን አወጣሁ። ይኸኔ ማልቀሱን ትቶ 'አንተ እጅህን ያወጣኸው፤ ተናገር! አለኝ። ልናገር ስነሳ ወታደሮቹ 'ቁጭ በል! ቁጭ በል!' እያሉ ጮሁ። እላፊ ይናገራል ብለው ሰግተው ኖሮአል። መልሼ ቁጭ ስል ካድሬው ጮኸ። ወታደሮቹንም ወረደባቸው። 'የኢትዮጵያ ጀግኖች የቁጣ





ስሜታቸውን ለመግለፅ ፈቃድ ሲጠይቁ እንዴት ይከለከላሉ?' አለና ደነፋባቸው። ከዚያ ተነሳሁ።

- በል ተናገር?፦ አለኝ።

- ከመዋጋት ሌላ አማራጭ ያለት ነገር ከነገሩኝ መላ ቢጠ ከሆነ ብዬ ነው፦ አልኩ።

- ቀጥል! ቁጣና ቁርጠኝነትህን መግለፅ መብትህ ነው፦ አለኝ።

- የኔ አሳብ'ንኩዋ። ችግሩ የባህር በር ከሆነ፤ ወሃ እንደሁ ሞኝ ነው። በቀደዱለት ቦይ ይፈሳልና፤ እንዲያው ሆ ብለን አንዷ ተዚህ ተቀይባህር ቁፋሮ ብንጀምር ወደቡ ደሴ አይደርስም ወይ?፦ አልኩ። ያሸልመኛል ብዬ የተናገርኩት ለእስር ዳረገኝ። 'እረ ሞኝ ነኝ!' ብል ማን ሰምቶ። 'አንተን ብሎ ሞኝ! የገንጣይ አስገንጣይ ቅጥረኛ! ከሀዲ! የእናት ጡት ነካሽ!' ያልተባልሁት የለም። በስድቡ ቢበቃ ደህና። ዱላው! እንደ ራፊ እያገላበጡ ያበራዩኛል። ገራፊውን 'እኔ እኮ ገብስ አይደለሁለም። እየኝ! አያሌው ሞኙ ነኝ' አልኩት። እሱ እቴ! ልቡ እስኪወልቅ ይውልብኛል። ሁዋላ ስጠይቅ 'መግረፍ ስራው ነው' አሉኝ። እንግዲህ የኒያ ህፃናት ግፍ ይሆናል ለዚህ ያበቃኝ። የምድሩ እንዲህ የከፋ የሰማዩማ ምን ሲሆን እንደሁ የቀደሙት ይወቁ፦

- የሰማዩ ሩህሩህ ነው አይዞህ፦ ብሎ አሰናበተው። አያሌው ሞኙ እያነከሰ ወጣ። አስተሳሰቡ መናጋቱን አኖሌ አልተጠራጠረም።

አኖሌ ዋቆ ብርድ ሲቆነጥጠው ማስታወሻ ደብተሩን አጣጥፎ ወደ ክፍሉ ገባ። ጃኬቱን ደርቦም ወደ ሆቴሉ ባር አመራ። አሳቡን የሚበታትንለት የታላቅዋ ብሪጣንያ ጂን አስፈልጎታል። የሎንደን ጎርደን ጂን፤ በአስመራ በረዶና ሎሚ። ሮዛን አስታወሰ። ሮዛ - ጉዋል አስመራ። 'ፊትህ ላይ የማይረሳ ነገር አለ' ያለችውን አስታወሰ። እና ሞቀው። ለምን እንደሞቀው ግን አላወቀም። ግራሴ ሮዚና - ሲል አጉተመተመ።

- 2 -

በነጋታው አኖሌ ሁለት ጉዳዮች ነበሩት። ከባድ ስብሰባና የሮዛ ቀጠሮ። ከማለዳው ሶስት ሰዓት ጀምሮ የሁለተኛው አብዮታዊ ሰራዊት የወታደራዊ ደህንነት ኤክስፐርቶች በአካባቢው የፖለቲካ ሁኔታዎች ላይ ማብራሪያ ሊሰጡት ቀጠሮ ይዘውለታል።

በሰአቱ የጦር ሰራዊቱ ማእከል ከሆነው ቃኘው ደረሰ።

ከፍተኛ መኮንኖቹ አንዲት ሰከንድ ሳይቀድሙና ሳይዘገዩ ነበር-አስር ሰው ከሚይዘው ያማረ የስብሰባ ሳሎን የደረሱት፡፡ ከአኖሌ ሌላ ተሰብሳቢዎቹ አምስት ነበሩ፡፡ ከአምስቱ ሁለቱ ኮሎኔሎች ሲሆኑ፣ የተቀሩት ሶስቱ ሻለቆች ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው በአካባቢው ሀገሮች ጉዳይ ላይ የየራሳቸው የስራ ክፍፍል ቢኖራቸውም በየጊዜው እየተሰበሰቡ መረጃዎቻቸውን እየጨመቁ አጠቃላይ ግንዛቤያቸውን ስለሚያዳብሩ እየተደጋገፉ በማብራራቱ ረገድ የተሻለ ልምድ አዳብረዋል፡፡

ስብሰባውን የከፈተው አኖሌ ነበር፡፡

በቀጥታ ከፕሬዝዳንት መንግስቱ ሃይለማርያም ተልኮ መምጣቱን ከገለፀ በሁዋላ፣ የእለቱን ስብሰባ አላማ ባጭሩ አስረዳ፣

«...ሁላችሁም እንደምታውቁት የስነ ልቦና ጦርነት ከውጊያ ስልቶች አንዱ ነው» ሲል ተንደረደረ «... የስነልቦና ጦርነትን ልዩ የሚያደርገው በጦር ክፍሎች ላይ ብቻ አለማተኮሩ ነው፡፡ በዚህ ስልት የአንድ ሀገር ህዝብ የሀገር ፍቅር ስሜቱን እንዲያጣ፣ ሞራሉ እንዲወድቅ፣ መንፈሱ እንዲላሽቅ፣ የበታችነት ስሜት እንዲሰማው፣ ባለው መንግስት ላይ እምነት እንዲያጣ፣ ድጋፍ እንዳይሰጥና እንዲያምፅ፣ ከአላማው እንዲዘናጋ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ ስልት በፖለቲካ፣ በማህበራዊ በኢኮኖሚያዊና በወታደራዊ መስኮችና በተለያዩ ዘዴዎች የሚነዛ አደገኛ መሳሪያ ነው፡፡ የስነልቦና ጦርነት ቀዳሚ ተግባር የጠላትን የውጊያ መንፈስ አስቀድሞ ማላሸቅ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በአሁኑ ሰአት ጠላቶቻችን በሚያካሂዱብን የስነልቦና ጦርነት ከፍ በልጠው ይገኛሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ሰራዊታችን በአላማው ፀንቶ ለማን? ለምን? እንደሚዋጋ ሊያውቅ አልቻለም፡፡ ስለሆነም ድል ማድረግ ተስኖታል፡፡ አሁን እኛ የምናካሂደውን የስነልቦና ጦርነት በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የኛን ሰራዊት ሞራል ጠብቆን፣ የህዝባችንን ድጋፍ ለማግኘት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የወንበዴውን ተዋጊ ሃይል ለማዳከም ብሎም ሻእቢያን ከኤርትራ ህዝብ ሙሉ በሙሉ መነጠል በሚሉት መሰረታዊ ነጥቦች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የዛሬው ስብሰባችን አላማም ለዚህ ጥናት አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ተጨባጭ አካባቢያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ከእናንተ ለማግኘት ነው» ብሎ አምስቱንም ከፍተኛ መኮንኖች ገረመማቸው፡፡

አኖሌ የመግቢያ ገለፃውን ሲያበቃ መኮንኖቹ ርስበርስ ተያዩ፡፡ ከሰከንዶች በሁዋላ አኖሌ፣

«ከሱዳን የውስጥ ሁኔታ ብንጀምር» ብሎ በመካከለኛ እድሜ ላይ ለሚገኘው ለኮሎኔል በቀለ ፈገግታ አሳየው፡፡





ኮሎኔል በቀለ የጭልፊት አይኖች ያሉት እርጋታን የማያውቅ አይነት ሰው ነው፡፡ በስለታም ድምፁ ስለሱዳን መንግስት ማብራራት ጀመረ፡፡

ሱዳን የደቡቡን የአገሪቱ ክፍል አመፅ ለማፈን ከምእራቡና ከአረብ አገሮች ወታደራዊ እርዳታ ለማግኘት ጥረት ላይ እንደሆነች ተነተነ፡፡ ጆርዳን፣ ሳውዲት አረቢያ፣ ኢራቅ ፣ ሊቢያ ኩዌትና ግብፅ ይረዱዋታል፡፡ ብዛታቸው ያልታወቁ ሮኬቶች፣ ሳውንቸሮች፣ ታንኮች ብረት ለበሶች የመገናኛ ሬድዮኖችና ጥይቶች ማግኘትዋንም አብራራ፡፡ ሱዳን ውስጥ በተፈጠረው የነዳጅ ውድነት የኢኮኖሚ ድቀትና አለመረጋጋት መታየቱን በጥቅሉ ካስረዳ በሁዋላም «ሱዳን በጠላት ደረጃ የምትታይ ሀገር ናት» ብሎ ሊያጠቃልል ሲል አኖሌ «ሱዳን ለምን ጠላታችን ሆነች? በሚለው ጥያቄ ላይ ዝርዝር ማብራሪያ ቢሰጥ ለሚካሄደው የስነልቦና ጦርነት ጠቃሚ ነገር ሊገኝበት የሚችል ይመስለኛል» አለ፡፡

ኮሎኔሉ «ልመጣበት ነው» ብሎ ጉሮሮውን ሳለ፡፡

የሱዳንን ጉዳይ ጠቅልሎ ስለነበር 'ልመጣበት ነው' በሚለው ምላሹ አኖሌ ተገርሞ ፈገግ አለ፡፡

«የሱዳን መንግስት ጠላትነት በቀጥታ በስልጣን ላይ ካለው መንግስት ሳይሆን ከሀገሪቱና ከህዝቡ ጋር ነው» በሚል መንደርደሪያ ማብራራት ጀመረ፡፡ «በርግጠኛነት ለመናገር በኢትዮጵያ ውስጥ መንግስታት ቢለዋወጡም እንኳዋ የሱዳን ጠላትነት ይቀጥላል፡፡ የጠላትነታቸውም መንስኤ የአባይ ወንዝ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በካርቱምና በወዲሀልፋ መካከል ከወንዙ ምእራብና ምስራቅ በመስኖ የሚለማው እርሻ ለህዝቡ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡ ነጭና ጥቁር አባይ ከሚገናኙበት ከካርቱም ደቡብ የሚገኘው የገዚራ ጥጥ እርሻ ፕሮጀክት ብዙ ሱዳኖች ከዘላንነት እንዲላቀቁ አድርጓአል፡፡ በ1952 በግብፅና በሱዳን መካከል በተደረገው የአባይ ውሃ አጠቃቀም ስምምነት በሱዳን የኤልሮሳረስና የካሽም ኤልጊርባ ግድቦች በመሰራታቸው ሱዳን 20500 ሚልዮን ኩቤክ ሚትር ውሃ ታገኛለች፡፡ የግብፅና የሱዳን መንግስታት ይህን ውሃ ከህዝቦቻቸው ህይወት ጋር የተያያዘ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ላይ ሰላም ከሰፈነ የልማት ስራ ይጀመራል፡፡ የግብፅና ሱዳን ዋና ስጋት ያ ነው፡፡ የአባይ ውሃ መጠን እንዲቀነስ አይፈልጉም፡፡ ስለዚህ ተቃዋሚዎችን በሙሉ ፍላጐት ይረዳሉ፡፡ ሱዳን ጠላታችን የሆነችበት ዋናው ምክንያት ይሄ ቢሆንም ሌሎች ጥቃቅን ምክንያቶችም ይኖራሉ...»

አኖሌ «... የሱዳን ውስጣዊ ሁኔታ ምን ይመስላል? ቅድም በጥቅሉ የተገለፀ አለ፡፡ ዘርዘር ብሎ ቢቀርብ?» ሲል ጠየቀ፡፡

ኮሎኔሉ ሲጋራውን ስቦ ቀጠለ፡፡ «... ሱዳን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ወታደራዊ ቀውስ አለባት፡፡ የደቡብ ሱዳን ጦርነት አለ፡፡ በህዝቡ መካከል የሚደረገው የዘር፣ የሀይማኖትና የአስተዳደር ልዩነትም ሌላ ችግር ነው፡፡ በዳርፉርና በኩርዶፋን ክፍለሀገር የሚገኙ ብሄረሰቦችም የማመፅ ዝንባሌ ይታይባቸዋል፡፡ የካርቱም መንግስት በውስጥ የተወጠረ ነው፡፡ ዘወትር ግን ከውስጥ ውጥረት ሲበረታ የችግሩን አቅጣጫ ለመለወጥ ጎረቤት አገሮችን መወንጀልና መተንኮስ ያዘወትራል፡፡»

አኖሌ «... ዋነኛ የሚባሉትን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ደካማ ጎኖቻቸውን ለይተህ ልታብራራልኝ ትችላለህ?» የሚል ጥያቄ አስከተለ፡፡

«... የሱዳን ዋነኛ የፖለቲካ ችግር የተለያዩ ብሄረሰቦች አመፅ መስፋፋቱ ሲሆን፣ አስተዳደሩ ሀይማኖታዊ መሆኑም ሌላው ድክመታቸው ነው፡፡ በአጠቃላይ በሱዳን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች አሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሱዳን አስራ ሶስት ቢልዮን ዶላር የውጭ እዳ አለባት፡፡ በአመት የዚህ ብድር ወለድ ክፍያ 482 ሚልዮን ዶላር ነው፡፡ ይህ የካርቱሙን መንግስት ጭንቀት ላይ ጥሎታል፡፡ ስራ አጥነት ተባብሶአል፡፡ ምዝበራ ተንሰራፍቶአል፡፡ ወንጀል ቅጥ አጥቶአል፡፡ ህዝቡና መንግስትም ሆድና ጀርባ ሆነዋል፡፡» ብሎ ግንባሩን በመሀረም ጠረገ፡፡

«ጠንካራ ጎኖቹስ?» አለ አኖሌ፡፡

«እንግዲህ የሱዳን መንግስት የአረብ ሊግ አባል በመሆኑ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ካላቸው የአረብ አገሮች እርዳታ ሊያገኝ ይችላል፡፡ የሱዳን የደህንነት ክፍልም እጅግ ጠንካራና የተራቀቀ ነው፡፡ በዚያ በኩል አይታሙም፡፡ ፊጣኖችና - ሁኔታዎችን በቅድሚያ የማወቅ አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ከሊቢያ የአየር ድጋፍ ያገኛሉ፡፡ ሌላው የካርቱሙ መንግስት የጉሳዎችን የርስበርስ ግጭት ለራሱ ጥቅም በማዋል የተካነ ነው፡፡ የኢትዮጵያን መንግስት የሚቃወሙትን በማስተባበር የሚያገኙት ውጤትም አደገኛ ነው፡፡ በፕሮፓጋንዳውም፣ በወታደራዊ እገዛውም በስፋት ይሰሩበታል፡፡ የተቃዋሚዎች መጠናከር የኢትዮጵያን ውስጣዊ ሁኔታ ስለበጠበጠው የሱዳን መንግስት ከዚህ ሁለት ጥቅም ያገኛል፡፡ በኛ መንግስት የሚደገፉት የደቡብ ሱዳን አማፅያን ይዳከማሉ፡፡ ሌላው ደግሞ የአባይ ወንዝ ያለችግር መፍሰሱን ይቀጥላል ... የሱዳንና የግብፅ የጋራ`መከላከያ ስምምነት ሌላው ጥንካሬያቸው ሲሆን፣ በደቡብ ሱዳን የተገኘው የነዳጅ ክምችት ጥቅም ላይ ከዋለም ኢኮኖሚውን ሊያረጋጋ ይችላል፡፡»





አኖሌ «በሱዳን የሚደገፉ ኢትዮጵያውያን የወንበዴ ቡድኖች እነማን ናቸው? ከሱዳን መንግስት ጋር ያላቸው ግንኙነትስ ምን ይመስላል? ... እኔ የማተኩረው በቀጥታ ሻእቢያ ላይ ቢሆንም ለግንዛቤ እንዲረዳኝ ዙሪያ መለሱ ቢዳሰስ?» ሲል ጠየቀ፡፡

«እኔ የሚመለከተኝ በአብዛኛው የሱዳን ጉዳይ ነው፡፡ ፀረ አብዮተኛ ወንበዴዎችን በተመለከተ ሻለቃ ሙሉጌታ በተሻለ ሊያብራራው የሚችል ይመስለኛል» ብሎ መድረኩን ለወጣቱ መኮንን ለቀቀለት፡፡

ወጣቱ መኮንን ከአኖሌ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ መስጠት የጀመረው «ብዙ የፀረ አብዮተኛ ወንበዴ ቡድኖች አሉ» በማለ መንደርደሪያ ነበር፣

«... ዋነኞቹ ግን ሻእቢያ፣ ህወሀት፣ ኢድህ፣ ኢህአፓ፣ ኦነግ፣ የአፋር ወንበዴ ቡድን ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አስጊ እንቅስቃሴ ያላቸው ሻእቢያና ህወሀት ቢሆኑም ኦነግም ቢሆን የሚናቅ አይደለም፡፡ በህወሀት ስር ኢህዴን የሚባል ድርጅት አለ፡፡ የወያኔ የአማራው ክንፍ ነው፡፡ በወሎና በጎንደር ይንቀሳቀሳል፡፡ ኢድህ የመሳፍንቶች ርዝራዥ ሲሆን እንቅስቃሴው በምእራብ ጎንደርና በሱዳን የተገደበ ነው፡፡ ኢህአፓ በጎጃምና በጎንደር ምእራባዊ ክፍል በመንቀሳቀስ ፀረ ሰፊራ ፕሮፓጋንዳ ነው የሚያካሂደው፡፡ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ከሱዳን ግዛት በመነሳት የኦሮሞ አካባቢዎች ላይ ውጊያ ይሞካክራል፡፡ በርግጥ ብዙውን ጊዜ ሰራዊታችንን ፊት ለፊት የመግጠም ስልት አይጠቀምም፡፡ እያደፈጠ በአንዳንድ ተቋማት ላይ ጥቃት ይፈፅማል፡፡ ፕሮፓጋንዳም በጥቂቱ፡፡ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ ግን ከሻእቢያ ጋር ያለውን የቀረበ ግንኙነት ይበልጥ ማጠናከር ጀምሮአል፡፡ የአፋር ወንበዴዎች በአውሳ አውራጃ በተለይ በአዲስ አበባ አሰብ መንገድ በተመላላሽ ተሽከርካሪዎች ላይ አደጋ ይጥላሉ፡፡ ይህ ሃይል በሻእቢያ እንደሚደገፍ መረጃ ደርሶናል፡፡ ለወያኔ መንገድ በመምራት እንደሚተባበሩም ተደርሶበታል፡፡»

ቀጣዩ የአኖሌ ጥያቄ፣ «የኤርትራ ህዝብ ስለ ኢትዮጵያም ሆነ ስለ ኤርትራ ታሪክና ህዝብ ያለው እውቀት ምን ይመስላል?» የሚል ነበር፡፡

ሁለተኛው ኮሎኔል ነበር ለዚህ ጥያቄ ምላሽ መስጠት የጀመሩት፡፡ ወፍራምና ራሰ በራ ናቸው፡፡ በእድሜ ገፍተዋል፡፡ ገራገር ቢጤ ይመስላሉ፡፡ ኮሎኔል ወልዴ ይባላሉ፡፡

ኤርትራ የሚለው ስም በጣሊያን ከመሰጠቱ በፊት ያ ተራራማ አገር ምድረ ሀማሴን፣ ምድረ ባህረ ነጋሲ፣ ምድረ አግአዚያን በመባል

ይታወቅ እንደበር አስረዱ። አገሩ የሚተዳደረውም በባህረ ነጋሲዎች እንደነበር ከገለፁ በሁዋላ 'ኤርትራ ነፃ ሀገር መሆን አለባት' የሚለው አመለካከት በእያንዳንዱ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጅ ደም ውስጥ የተረጨ መርዝ መሆኑን አስገነዘቡ። የወንበዴዎቹን ጥፋት ህዝቡ 'ትግል' እያለ እንደሚጠራው ወንበዴዎቹን ደግሞ 'ታጋይ' እንደሚላቸው አብራሩ።

የአኖሌ ቀጣይ ጥያቄ «የሻእቢያ አመሰራረት ምን ይመስላል?» የሚል ነበር።

ኮሎኔሉ ማስታወሻ ደብተራቸውን ሲያተረማምሱ ቆይተው ማብራራት ጀመሩ፣

«ሻእቢያ ከጀብሀ ተገንጥሎ ከመውጣቱ በፊት በኤርትራ ውስጥ የተደራጁ የተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ይካሄዱ ነበር። የአብዛኞቹ አላማ ኤርትራን ከኢትዮጵያ በመገንጠል ነፃነትዋን እንድትቀዳጅ ለማድረግ ነበር።

ከጀብሀ መቋቋዋም ቀደም ሲል ከነበሩት ቡድኖች መካከል «ማህበር ሸዋዓተ» ሊጠቀስ ይችላል። የማህበር ሸዋእተ መሪዎች ወልደአብ ወልደማርያምና አብድል ቃድር ካቢሬ የሚባሉ ነበሩ። የማህበሩ አባላት ሰባት ሰባት በመሆን ኤርትራ ነፃነትዋን እንድትጎናፀፍ ለህዝቡ ቅስቀሳ ያደርጉ ነበር። መቀጠል ግን አልቻሉም። በኢትዮጵያ መንግስት መታደን ስለጀመሩ ወደ ሱዳንና እንግሊዝ ሀገር ኮብልለው ገቡ። በውጭ ሀገርም ሆነው ቅስቀሳ ማካሄዱን ቀጠሉ።

«ከዚህ በሁዋላ በረሃ ቀርተው የነበሩ አስራ አምስት ያህል ዲሞክራት ነን የሚሉ ኤርትራውያን «ንሀናን አለማናን» በሚል መጠሪያ እራሳቸውን ሰይመው እንቅስቃሴ ጀመሩ። መሪያቸው አብርሃም ተወልደ ይባል ነበር። አላማቸውን ለማስራጨትም ምቹ ነው ብለው ወዳሰቡት አከለ ጉዛይ አውራጃ አላ በተባለ አካባቢ መንቀሳቀስ ያዘወትሩ ነበር።»

አንድ መሀመድ እድሪስ አወተ የሚባል ገበሬ ብረት ይዞ በኤርትራ ውስጥ በመዘዋወር ከመንግስት ጋር እየተጋጨ ብዙ ጀብድ ይፈፅም ስለነበር ብዙ ተከታዮች ማግኘት ችሎ እንደነበር ጭምር ኮሎኔሉ ተናገሩ።

«ይህ ሰው አያሌ ዴሞክራት ታጋዮች ነን ባይ ወጣት ኤርትራውያንን ከኤደን በመርከብ በመጫን ወደ ደንከል እንዲገቡ አድርጉአል። ይህን ያደረገበት ምክንያት ወጣቶቹ ወደ ኤርትራ ምድር በሌላ ቦታ መግባት ስለማይችሉና በበረሃ ከሚገኙት ቡድኖችጋር





ግጭት እንዳይፈጠር በማሰብ ነበር።

በዚሁ ጊዜ ዛሬ ሻእቢያ እየተባለ የሚጠራውን ድርጅት የመሰረቱ ሀይሎች ከጀብሀ በመገንጠል «ህዝባዊ ሀይልታት» በሚል ስያሜ ደንከል በረሀ ገቡ። ደንከል የገቡት እነዚሁ ወጣቶች አብረው መዝለቅ አልቻሉም። 'ከደንከል እንውጣ' ና 'ደንከል እንቆይ' በሚል ጥያቄ አለመግባባት ፈጥረው በሁለት ቡድን ተከፈሉ። ሁለቱ ቡድኖች 'ቀዳማይ ወገን ህዝባዊ ሀይልታት' እና 'ካልአይ ወገን ህዝባዊ ሀይልታት' የሚል ስያሜ ያዙ። 'ቀዳማይ ወገን' የተባለው ደንከል ሲቆይ 'ካልአይ ወገን ...' ወደ ሰሜናዊ ሳህል አውራጃ አመራ። ዳሩ ግን በጉዞ ላይ ከጀብሀ ጋር ግጭት ፈጥረው ከካልአይ ወገን ህዝባዊ ሀይልታት ብዙ ሰዎች ሞቱባቸው። ከሞት የተረፉት ወደ ሰሜናዊ ሳህል በመግባት በአብራሃም ተወልደ ከሚመራው ቡድን ጋር ግንኙነት ፈጠሩ።

«የቀደማይ ወገን ህዝባዊ ሀይልታት መሪ የነበረው መስፍን ሀጐስ ይባል ነበር። ለማንኛውም ለብዙ ጊዜ ቀዳማይ ወገንና ካልአይ ወገን እየተባሉ ቆዩ። በደንከል ኡበል የሚባልም ሌላ ቡድን ነበር። እዚህ አካባቢ ትንሽ የሚያምታታኝ ነገር አለ። ዞሮ ዞሮ እነዚህ ሶስት ቡድኖች ማለትም፤ ቀዳማይ ወገን ህዝባዊ ሀይልታት፣ ካልአይ ወገን ህዝባዊ ሀይልታትና ኡበል ግንኙነታቸውን ሲያጠናክሩ ቆይተው የጋራ ግንባር በመፍጠር በ1970 እ.ኤ.አ ህዝባዊ ሀይልታት ሀርነት ኤርትራ በሚል ስያሜ ተቀሳቀሱ።

ኡስማን ሳላህ ሳቤ ከውጭ የሚልኩላቸውን መሳሪያም እኩል ይካፈሉ ጀመር። ውጊያ ሲኖርም የጋራ ግንባር በመፍጠር ነበር የሚዋጉት። የእነዚህ ሶስት ቡድኖች በሶስት መሪዎች መታዘዝ ግን ለአመራር አመቺ ባለመሆኑ፤ ለጠላትም አመቺ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ብለው በማሰብ መስከረም አንድ 1974 አንድ ወታደራዊ ሀይልና አንድ መሪ አቋቋሙ፤ ሰራዊቱ ተወሀደ፤ የድርጅቱ መሪዎችም ተመረጡ። በወቅቱ በአመራርነት ከተመረጡት መካከል፤ ኢሳይያስ አፍወርቂ፤ ሮመዳን መሀመድ ኑር፤ መስፍን ሀጐስ፤ ሰለሞን ወልደማርያም፤ አሊ ሰይድ፤ አብደላ አደም፤ አቡአጃጅ፤ አቡጠያራ፤ አብርሃም ተወልደና ሳላህ ጠጠው ጥቂቶቹ ነበሩ። የሻእቢያ አመሰራረት ከሞላ ጐደል ይህን ይመስል ነበር።»

አኖሌ ጥያቄውን ቀጠለ፣

«ህዝቡ ከመነሻው ጀምሮ ለሻእቢያ ድጋፍ ነበረው ማለት ይቻል ይሆን?»

ኮሎኔሉ ለሰከንዶች በዝምታ ከቆዩ በሁዋላ «... ህዝቡ የሻእቢያን አላማ ጠንቅቆ አውቆ ሳይሆን በስሜትና በጠባብ ብሄርተኝነት አላማ

ነበር የሚገፋው:: የሻእቢያ አባላት በአብዛኛው ከደጋው ክርስትያን ወገን በመሆናቸው መብታችንን ሊያስከብርልን የሚችለው ሻእቢያ ብቻ ነው የሚል ስሜት ከትግርኛ ተናጋሪዎች በኩል ይንፀባረቅ ነበር:: የሻእቢያ መሪዎች የተማሩ ስለነበሩ ለኤርትራ ህዝብ መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ የሚል ተስፋም ነበር:: ጀብሀ ከመነሻው አድሀሪ አዝማሚያ ስለነበረው ከዚህ ድርጅት የተገነጠለው የሻእቢያ ሀይል ዴሞክራት ሊሆን ይችላል የሚል መላምት ነበር በህዝቡ ውስጥ::»

ኮሎኔሉ ንግግራቸውን ገታ አድርገው ከቆዩ በኋላ

«ከሞላ ጐደል የድርጅቱን አቋዋም ብታውቅ ለስራህ እንደሚያግዝህ እገምታለሁ» ብለው ማብራራታቸውን ቀጠሉ «... ሻእቢያ እንደሚለው - ኤርትራ እ.ኤ.አ ከ1889 ጀምሮ በኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ስር ስትማቅቅ ቆይታ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ጣሊያን ድል ተመትታ ስትወድቅ፤ ሀምሳ ሁለት አመታት ያህል በኤርትራ የቆየው ቅኝ ግዛታቸው እ.ኤ.አ በ1941 አክትሞአል:: ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ስትወጣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤርትራ በእንግሊዝ ሞግዚትነት ለጥቂት አመታት እንድትቆይ በወሰነው መሰረት እንግሊዝ ኤርትራን ማስተዳደር ጀመረች:: ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በሁዋላ በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ አገሮች በቀጥታ ነፃነታቸውን ሲጐናፀፉ ኤርትራ ይህን እድል መነፈግዋ ትክክል አይደለም:- ይላል ሻእቢያ::

ሌላው የሻእቢያ ቀንደኛ አቋም - አራቱ ሃያላን መንግስታት ማለትም አሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝና ሶቪየት ህብረት ሁለተኛው የአለም ጦርነት እንዳበቃ የኢጣሊያን ቅኝ ግዛቶች በሚመለከት ስብሰባ አድርገው፤ ሊቢያና የኢጣሊያ ሶማሌ ላንድ ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ሲወስን የኤርትራ ጉዳይ ግን የብዙ አገሮች ፍላጐት ስለነበረበት መወሰን አቅቶአቸው ጉዳዩ ለተመድ ቀረበ:: እ.ኤ.አ በ1950 የተመድ ጠቅላላ ጉባኤ በአምስተኛ ስብሰባው በአሜሪካ ተፅእኖ ለኤርትራ ህዝብ ፍላጐት ደንታ ሳይሰጥና ህዝቡ ሳይጠየቅ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትዋሀድ ተወሰነ:: ተመድ በቻርተሩ በመጀመሪያው አንቀፅ ያስቀመጠውን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በመጣስ የወሰነው ውሳኔ ትክክለኛ አይደለም:: አሜሪካ ኤርትራ ውስጥ የጦር ሰፈር ለማግኘት ከኢትዮጵያ ጋር ቀደም ብላ በመስማማትዋ ምክንያት የተሸረበ ሴራ ነው:: ማንም አገር ከቅኝ ግዛት ነፃ ሲወጣ ራሱን ቻለ እንጂ ከሌላው ጋር ይቀራረባል እየተባለ እንዲጣመር አልተደረገም:: ስለዚህ ኤርትራ እ.ኤ.አ በ1952 በፌዴሬሽን መቀላቀሏ ትክክል አልነበረም:- ብለው ያምናሉ ወንበዴዎቹ::

ሌላው ልታውቀው የሚገባ አቢይ የሻእቢያ አቋም - ኤርትራ





በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ከተሳሰረች በሁዋላ ለማተዳደሪያ የወጣው ህግ በተግባር አልተተረጐመም:: የኤርትራ ሸንጐ እ.ኤ.አ ህዳር 14 ቀን 1962 ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ውህደቱን ያሳለፈው ግማሹ በገንዘብ ተደልሎ፣ ከፊሉ ደግሞ ተገዶ ነው:: በመሰረቱ መሆን የነበረበት በህዝብ ውሳኔ ነበር:: ስለዚህ ይህም ትክክለኛ አይደለም:- ይላል የሻእቢያ ሰነድ:: ተመድ የራሱን ቻርተር የሚቃረን ውሳኔ በማሳለፍ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድንቀላቀል ከማድረጉም በላይ የኢትዮጵያ መንግስት በሀይል ተጠቅሞ የራሱ አካል ሲያደርገን ተመድ ባለመቃወሙ ውሳኔው ለኛ አይሰራም:: ለኤርትራ የራሷን እድል በራስዋ የመወሰን መብት መስጠት አለበት:: ይህም በኢትዮጵያ መንግስት ወይም በሻእቢያ ሳይሆን በገለልተኛ ሀይል ለህዝቡ የውሳኔ ህዝብ እድል ይሰጠው:- እያለ ነው ሻእቢያ ህዝቡን ያሳመነው፤ እስምንም እያደናገረ ያለው»

ገለፃው በዚሁ መልኩ እስከ እኩለ ቀን ከቀጠለ በሁዋላ ርእስ ጉዳዮቹ ባለመጠናቀቃቸው ቀጣዩ ስብሰባ ከሶስት ቀን በሁዋላ እንዲካሄድ ወስነው ተለያዩ::

* * *

እኖሌ በዚያን እለት ተሲያት ወደ አዲሳባ የሚልከውን ሪፖርት ሲያጠናቅር ከቆየ በሁዋላ ሮዛን ለማግኘት ወደ ባር ኢምፔሮ ገሰገሰ:: በሰአቱ ነበር የደረሰው:: ስድስት ሰአት ከምሽቱ በአስመራ የሰአት አቆጣጠር:: ለአይን ያዝ አድርጐአል:: የኩምቢሽታቶ ዘምባባዎች በምሽት ታይተው አይጠገቡም:: በረንዳው ላይ ተቀምጦ ማኪያቶ አዘዘ:: ረጅም ግራጫ ጃኬትና ከውስጥ ስስ ጥቁር እንገተ ሙሉ ሹራብ፣ ነጣ ካለ ሱሪ ጋር ለብሶአል:: አንገት ልብሱን እንገቱ ላይ የጠመጠመ ሲሆን መነፅር አድርጐአል - ውብ መነፅር::

የአስመራ አየር ቀዝቀዝ ብሎአል::

በኩምቢሽታቶ የሚመላለሱትን ሰዎች አንድ ባንድ ያጤን ጀመር:: አብዛኞቹ የመሀል አገር ሰዎች መሆናቸውን በአለባበሳቸው ለያቸው:: ኤርትራውያን ኩምቢሽታቶ ላይ የሉም:: እኖሌ ፈገግ አለ:: በርግጥም ኤርትራውያን ኩምቢሽታቶ ላይ አለመታየታቸው ምን ያስደንቃል? በስደት ወይም በትግል ላይ ናቸው:: በኩምቢሽታቶ የሚታዩ ኤርትራውያን ገፅታ ላይም ቢሆን መረጋጋት አይታይም:: የአገሬው ሰዎች በኩምቢሽታቶ ጐዳና እንደ ቀይ ባህር የምሽት ማእበል መገማሸር ሲገባቸው ፖሊስ እንደሚከተለው ሰው እየተጣደፉ ሲመላለሱ ነው የሚታዩት ...

«እኖሌ - ወዲ እሮም!» የሚል ድምፅ አባነነው::

ሮዛ ትከሻውን ያዛው ፊቱ ቀማለች:: ከተቀመጠበት ፊጥኖ ተነስቶ ያስማት ጀመር - ጉንጭ ለጉንጭ::

«ሮዛ አንቺ ኖረሻላ!?» እያለ በረጅሙ ሳቀ::

ሮዛ እንደ አብዛኞቹ ኤርትራውያን ሴቶች ቀጭን ነበረች:: የደስ ደስ አላት:: የአይን መነፅርዋን በየስከንዱ ገፋ ታደርገዋለች:: ከአኖሌ ጋር ተሳስመው ሲያበቁ!

«እንሂድ» አለችው «... እናቴ እየጠበቀችህ ነው»

በእግር መንገድ ጀመሩ::

«አስመራን እንዴት አገኘሀት?» ስትል ጠየቀችው::

«የቀድሞ ውበትዋን የምታንጉራጉር የሀብታም ግቢ ትመስላለች» ሲላት ሮዛ ከልብዋ ሳቀች:: ስቃ ስታበቃም!

«ለማደግ ግን ተስፋ ያላት ከተማ ናት:: አስመራ ያለብዙ ድካም ታላቅ ከተማ መሆን ትችላለች:: የናንተው ፊንፊኔ ግን የከተማ ቅርፅ ለመያዝ እያሌ ወጪ ትጠይቃለች:: በርግጥ አየርዋ ቀረጥ ቢከፈልበትም አይቆጭ...»

አኖሌ በድንጋጤ ጨው ሆነ:: ቃል አልተነፈሰም:: ግራ በመጋባት ሮዛ ላይ አፈጠጠ:: ያስደነገጠው 'ፊንፊኔ' የሚለው ቃል ነበር:: ይህን ቃል ለመጨረሻ ጊዜ አዲስ አበባን ወክሎ ሲጠራ የሰማው ጀርመን ሳለ ነበር - ከአንግ አባላት አንደበት:: ሮዛ ቃሉን ከየት አመጣችው? ሲል ራሱን ጠየቀ::

«ምን ሆንክ?» አለችው -

«ምንም ...»

«ዝም ስትል ግራ አጋባኸኝ:: መጥፎ ተናገርኩ?»

«በጭራሽ»

«የአዲሳባ አየር ቀረጥ ቢከፈልበትም አይቆጭ ማለቴ ይሆን ያስገረመህ? እውነቴን ነውእኮ:: አየርዋ ምግብ ነው:: ከተማ መስራት የሚችሉ ሰዎች ጠፉ እንጂ የአዲስ አበባ አየር በየትኛውም አለም ኩሶ የሚገኝ አይመስለኝም::»

«ፊንፊኔ የሚለውን ስም የት ሰማሽው?» ሲል ጠየቃት - እንደዋዛ::

«እንጃ!» አለች ሮዛ «... ግን የአዲሳባ የቀድሞ ስም ፊንፊኔ





እንደነበር! ቃሉ የኦሮምኛ ስለሆነ 'ለዋና ከተማነት አይመጥንም' ተብሎ እንደተለወጠ አንድ ሰው ነግሮኛል:: ከዚያ ወዲያ ብዙ ጊዜ ፊንፊኔ የሚለውን ስም መጠቀም ያስደስተኛል:: ግን ለምንድነው ፊንፊኔ የሚለው ስም ለዋና ከተማነት አይመጥንም የተባለው? መጥፎ ትርጉም አለው?» ስትል ጠየቀችው::

አኖሌ ሳያስበው ስሜታዊ ሆነ::

«የስርአቱ ሰዎች ዘረኞች ስለሆኑ እንጂ ችግሩ ቃሉ ላይ አይደለም ያለው:: ጭሮን አሰቡተፈሪ! ብሾፍቱን ደብረዘይት! አዳማን ናዝሬት! እያሉ ለውጠው የለ? የከተሞችን ስም ለመለወጥ በቂ ምክንያት አልነበራቸውም:: አሳማዎች ስለሆኑ ነው ያን የፈፀሙት»

ሮዛ ወደ ጆሮው ጠጋ ብላ አንሾካሾከችለት::

«ፖለቲካ ውስጥ አትግባ:: እዚህ አገር አሸዋና ጠጠሩ ሁሉ ሰላይ ነው::»

አኖሌ በእሺታ ራሱን ላይ ታች ወዘወዘ:: በሮዛ ግልፅነት ይበልጥ መደሰት ጀመረ:: ፊንፊኔ የሚለውን ስም ስለወደደችው ደግሞ የማያውቀው የደስታ ስሜት ወረረው:: በመገረም ያያት ጀመር:: የመጣላትን የምትናገር የዋህ ሰው መስላ ታየችው:: ግን ደግሞ 'ፖለቲካ ውስጥ አትግባ' ያለችውን አስታውሶ ግራ ተጋባ:: መልሶ ደሞ ምክንያትዋን ሊረዳላት ሞከረ:: ህዝቡ ሁሉ ተጠራጣሪ ሆኖአል:: ምክንያቱም ሰው ያለ ፍርድ ይገደላል:: 'ግን ይህን የዋህና ደግ ህዝብ ማስቃየት ለምን አስፈለገ?' ሲል ራሱን ጠየቀ:: 'የዋሆች ጠንካራ ተዋጊዎች መሆን ይችላሉን?' ሲል መልሶ ለራሱ ተጨማሪ ጥያቄ አቀረበ:: የበርሃ ሰዎች ታጠሱት:: ጦር ያዘው መትረየስ ሲገጥሙ የተዘጋጁ ልበ ሙሉ አርሞዎች - ግን ደጋጎች! የዋሆች::"

«ምን ሆነሀል አኖሌ?» አለች ሮዛ ተጨንቃ::

«ምን ሆንኩ ሮዛ?»

«የተከፋህ ትመስላለህ?»

«ያላገኘሁትና ያጣሁት ነገር ያለ ይመስላል ብለሺኝ አልነበር? እንዳልሺው እርካታ የራቀኝ ሰው ሳልሆን አልቀርም:: ሳማ እንዳለው እንደ ኦሮሞ ዱር አራዊቶች አይደለሁም:: እኒያ እንስሳት 'ሰው አይደላችሁም' ቢባሉ ምንም አይመስላቸውም:: ምክንያቱም ሰው አይደሉም:: ይገርምሻል ሮዛ ይህ ከርፋታም ስርአት እኛ ኦሮሞዎችን እንደሰው አያየንም:: ግን ደህና ... ይህን መሰል ጉዳይ ማውራት ተገቢ አይደለም:: ሮዛ ረበሽኩሽ?»

ታክሲ ይዘው ቲራቮሎ ወደሚባለው ሰፈር ነጐዱ። ከደቂቃዎች በሁዋላ ታክሲው ከነሮዛ መኖሪያ ቤት ደርሶ ቆመ። ሂሳብ ከፍለው ከታክሲው ወረዱ። ሮዛ እየመራች ወደ አንድ ቪላ ይዛው ገባች። የውጭው በር ግምብ ላይ በወርቃማ ቀለም «ይስሀቅ አስመሮም» የሚል ፅሁፍ ግምቡ ውስጥ ተቀብሮ ይነበባል።

«ይስሀቅ አባትሽ ነው?» ሲል ጠየቃት።

«አያቴ ነው። አባቴ ኤፍሬም ይባላል።» ካለች በሁዋላ «ሞቶአል ብለን እንገምታለን።» ብላ አንሾካሾከች።

«የት ነው ያለው?»

«አይታወቅም። ከአዲስ አበባ ወደ ናይሮቢ መሳፈሩን ብቻ ነው የምናውቀው። ከዚያ ወዲያ ኤፍሬም ይስሀቅ የውሃ ሽታ ሆኖአል። እናሳዝንም?» አለችው።

ዝም አላት። ይህን መሰል ወሬ ለምን እንደምትነግረው አልገባውም። ወደ ሰፊ ሳሎን አስገብታ ካስቀመጠችው በሁዋላ፣

«የሳሚ ጉዋደኛ ስለሆንክ ነው ሆዴን የነገርኩህ» አለችው።

«ይገባኛል! ይገባኛል!» ብሎ ፈገግታ አሳያት።

«ሳሚ እንደኔ እዩት ብሎናል። እንመንክ?»

«በጣም እንጂ ሮዛ። ወንድማችሁ ነኝ።»

«የጦር ሰራዊት ደጋፊ ነህ?»

ጥቂት አመነታ።

«ደጋፊም ተቃዋሚም አይደለሁም። ብዙውን ጊዜ በስራዬ ላይ ብቻ ነው የማተኩረው።»

«ሃይማኖትህስ?»

«አላውቀውም!» አለ ጭፍንግግ ብሎት።

«የቤተሰብህ ሃይማኖት ምንድነው?»

«ቤተሰቤን አላውቅም። ያለኝ መረጃ ኦሮሞዎች እንደነበሩ ብቻ ነው። ከዚያ በተረፈ አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ 'መልካም ሰው' መሆን ከቻለ በቂ ይመስለኛል።»

ራስዋን ላይ ታች ወዘወዘችና ...

«እኛ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ነን። ማማ በተለይ ማርያምን በጣም ታምናታለች። ሆኖም ባህርይዋ እግዚአብሄርን





በመፍራት፣ እግዚአብሄር የሚወዳቸውን ነገሮች በማድረግ ላይ የተመሰረተ ነው። በጣም ትፀልያለች። ምን ብላ እንደምትፀልይ ልንገርህ?»

«ንገሪኝ?»

«አታሳስረኝም?»

ከልቡ ሳቀ። በጣም ሳቀ።

«ምን አሳቀህ?»

«ቅን ነሽ። ለአለም ቅን ሰዎች በእጅጉ ያስፈልጉዋታል። ስለዚህ አላሳስርሽም ንገሪኝ?»

«ማማ ዘወትር ፀሎት ታደርጋለች። ብዙውን ጊዜ አምላክን ክፉዎች እንዳይበረቱ አድርግ፣ ብላ ትማፀነዋለች። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ድምፅዋን ዝቅ አድርጋ ለማርያም አስመረይቱ 'በረሃ ያሉት ለቤታቸው እንዲበቁ አስቢያቸው' ትላታለች»

አኖሌ ስሜቱ ከልብ ተነካ። ሮዛን በፍቅር ያስተውላት ጀመር። ግልፅነትዋን ወደደው። ስላመነችው ቢደሰትም ይህ ባህርይ ግን ቤተሰቡን በሙሉ አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል አምኖ ስጋት አደረበት። ሮዛ፣

«ማማን ጠርቼ ላስተዋውቅህ» ብላው ወጣች።

በሳሎኑ ግድግዳዎች ላይ የተሰቀሉትን ስእሎች ማስተዋል ጀመረ። በሙሉ መንፈሳዊ ናቸው።

* * *

አኖሌ ምሽቱ ጥሩ ሆነለት። የሮዛ ዘመዶች ሁሉ ተስማሙት። መልካም ራት ቀረበ። ቡና ተፈላ። ከበው ሲያጫውቱት አመሹ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ሳሙኤል ከአዲሳባ ደወለ። ሳሙኤል ከምሽቱ አራት ሰአት ላይ ነበር የደወለው። መጀመሪያ አኖሌ በአጋጣሚው በእጅጉ ተደስቶ ነበር። ሳሙኤል ግን «በአጋጣሚ አይደለም የደወልኩት፣ አንተን ፈልጌ እንጂ» አለው።

አኖሌ ግራ ተጋብቶ፣

«እዚህ መሆኔን በምን አወቅህ?» ይለዋል።

«ሆቴል አጣሁህ። ምናልባት እዚህ ካለህ ብዬ ነው» ሲል መለሰለት በጀርመንኛ።

አኖሌም መልሶ በጀርመንኛ ቋንቋ፣

«ምንድነው?»

«እንዴት እንደምነግርህ አላውቅም። ጉዳዩን የሰማሁት በአጋጣሚ ነው»

አኖሌ «ምንድነው ንገረኝ!?» ሲል ጮኸ።

«መከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ የሚሰራ አንድ ዘመድ አለኝ። በአጋጣሚ ሻለቃ ጉተማ የሚባል ሰው አንተን በተመለከተ ስለፃፈው ሪፖርት አጫወተኝ።»

«ጉተማ ... የቡርቃው? ምን ብሎ ፃፈ? ይህ ክብት! ከክብት ምን ይጠበቃል ... እበት ካልሆነ?»

«ጉዳዩ እንደምታስበው እንኳ ቀላል አይደለም። በእነግ አባልነት ወንጅሎሀል። ለማንኛውም የራስህን እርምጃ ለመውሰድ ያመችህ ዘንድ የደብዳቤውን ፎቶ ኮፒ ልኬልሀለሁ። ነገ ይደርስሀል። በነገራችን ላይ ጉዳዩ በጥንቃቄ እንዲታይ ደብዳቤው ለደህንነት ሚኒስትሩ ተመርቶአል። ይህን ከደብዳቤው ላይ ነው ያየሁት። እንድትጠነቀቅ እመክርሀለሁ። ሁኔታዎች ጥሩ አልመሰሉኝም። ለማንኛውም ደብዳቤውን ካየህ በሁዋላ ራስህ ብትወስን መልካም ነው። ይህ መንግስት ሰው የመናቅና የማነቅ ሱስ ስላለበት ነው ስጋቴ የጨመረው። ምን ይመስልሀል?»

አኖሌ ረጋ ለማለት ሞከረ። «ደብዳቤውን መጀመሪያ ባየው ደስ ይለኛል» የሚል ምላሽ ሰጠው።

«ነገ ይደርስሀል። እንደደረሰህ ግን ደውልልኝ» አለው ሳሙኤል።

በርግጥም በነጋታው ማታ ካረፈበት የእምባሶይራ ሆቴል ደርሶ ክፍሉን ሲከፍት በበሩ ስር የተወረወረ ፖስታ አገኘ። በችኮላ ፖስታውን ከፍቶ የሻለቃ ጉተማን የቡርቃ አመፅ ሪፖርት ያነብ ጀመር። በጣም ገረመው። የሻለቃው ነገር ጠምዛዥነት አናደደው። ደግሞም አሳዘነው። ከሆቴሉ በረንዳ ላይ ወጥቶ በጨለማ የተዋጠችውን አስመራ እያስተዋለ ይተክዝ ጀመር። የማያስደስቱት ነገሮች እየበረከቱ መምጣታቸውን አስተዋለ። አደገኛ ሁኔታዎችም መከሰት ጀምረዋል ...

የሀወኒ መሰወር አንዱ ነው። ያፈቅራታል። ከልብ ያፈቅራታል። በእምባገነንነትና ሰብአዊ መብትን በመጣሱ ወደሚታወቀው ስርአት ሰተት ብሎ የገባው ሀወኒን ማግኘት ከተቻለ የስርአቱን ብልሹነት ችዬው እኖራለሁ ብሎ በማሰቡ ነበር። ግን





ሀወኒ የውሃ ሽታ ሆና ቀርታለች። ስደት ላይ ናት፤ አለያም ሞታ ሊሆን ይችላል። ሌላው አባቱ ናቸው። ሞተዋል። ከዚህ ውጭ ደግሞ ባልጠበቀው ጥልፍልፍ ውስጥ ተዘፍቆአል። ከኦሮሞ ገበሬዎች ጋር ያደረገውን ንግግር በምስጢር የቀረፀው ሰላይ ሹፌር በየእለቱ 'ገንዘብ' እያለ ይነተርከዋል። አስመራ ከመምጣቱ በፊት አምስት ሺህ ብር ሰጥቶት ነበር። ቀሪውን ደግሞ ከአስመራ መልስ እንደሚሰጠው ነግሮት ነበር። ሰላዩ ሾፌር ግን ሀሳቡን መለወጥ ጀምሮአል። 'በርካሽ ነው የተስማማሁልህ' ማለት ጭምር አምጥቶአል።

በዚህ ላይ ደግሞ ሀልውናውን እንኩዋ ማረጋገጥ ላልቻለ ስርዓት ማገልገሉ አልተዋጠለትም። የአስመራ ገጠመኙም ሀሲናውን እያቆሰለው ይገኛል። የኢሰፓ መንግስት የአገዛዝ ስልት እያንቀጠቀጠው ነው። ሞት የተፈረደባቸው ወታደሮች ፊቱ መጥተው ይደቀናሉ። ከመሞታቸው በፊት ሲያነጋግራቸው ችሎአል። አሁን ግን በህይወት የሉም። በእለተ አርብ ተረሽነዋል። እንደ እየሱስ ክርስቶስ አለ - መቶ አለቃ አክሊሉን አስታውሶ። አብርሀ ፀሎትንም አስታወሰ። 'ወታደሮች ልጃገረዶችን መድፈር ማቆም አለባቸው' ያለውን። ጮማዬም ትዝ አለው። ልጃገረዶችን አስገድዶ መድፈር ለጮማዬ እጅግ ተራ ነገር ነው። ብርቱካን ልጦ እንደመብላት። አሁን ደግሞ አንድ ሌላ ጠላት ተፈጥሮአል። ሻለቃ ጉተማ። ለመከላከያ ሚንስቴር ባቀረበው ሪፖርት አኖሌ ለቡርቃ ገበሬዎች ስላደረገው ንግግር አጣሞና አወላግዶ ተርኩአል።

አኖሌ በፍርሀትና በጭንቀት ተወረረ። ማድረግ ያለበትን አላወቀም። እንዲሁ ብቻ ከወዲያ ወዲህ ይንጉራደድ ያዘ።

## - 3 -

አምስቱ ከፍተኛ መኮንኖች ቃኘው በሚገኘው የስብሰባ ሳሎን በቀጠሮው ሰአት ቢገኙም አኖሌ አስር ደቂቃ ዘግይቶ ነበር የደረሰው።

ይቅርታ ጠየቃቸው።

«ምንም አይደለም» አሉ ሽማግሌው ኮሎኔል።

አኖሌ ማስታወሻ መያዣያ አጀንዳውን ገላልጦ በቀጥታ ከሶስት ቀን በፊት ወዳቆመበት ርእሰ ጉዳይ ዘለቀ ...

«... ባለፈው ስብሰባችን የሱዳንን ውስጣዊ ሁኔታ ካየን በሁዋላ ስለተቃዋሚ ቡድኖች ነበር መረጃ ያገኘሁት። የኤርትራ ክፍለ ሀገር ህዝብ ስለ ኢትዮጵያ ያለው አመለካከት ላይም የተወያየን ይመስለኛል። ሻእቢያ የመገንጠልን ጥያቄ ለማሳመን የሚያነሳቸውን ነጥቦች ጭምር ተመልክተናል። ዛሬ በተቻለ መጠን ሻእቢያን በሚመለከቱ ጉዳዮች

ላይ ጥልቅ ማብራሪያ ማግኘት እፈልጋለሁ:: በተለይ የድርጅቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በግልፅ ባውቃቸው ለስራዬ ስለሚያግዘኝ በዚያ ላይ ብታተኩሩ እመርጣለሁ» ብሎ መኮንኖቹን አንድ ባንድ በፈገግታ ቃኛቸው:: በዚህ ጊዜ ሻለቃ ሙሉጌታ፣

«የሻእቢያን ውስጠ ሚስጥር አብጠርጥሮ የሚያውቀው እንኳዋ ሻለቃ ቡልቻ ነው» ብሎ በረጅሙ ሳቀ::

ሻለቃ ቡልቻ ራሰ በራ ቀጭን ጉልማሳ ነው:: በመጀመሪያው ስብሰባ ምንም አስተያየት ሳይሰጥ በማለፉ አኖሌ «አሻቢ» ቢጤ አድርጎ ነበር የወሰደው:: ለአኖሌ በእጅጉ የሚያስፈልገው የሻእቢያ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን የመረዳት ጉዳይ በዚህ በተናቀው ሰው ላይ በማረፉ አኖሌ ራሱን ሳይታዘብ አልቀረም:: በርግጥም ሻለቃ ቡልቻ የሚናቅ ቢጤ አልነበረም:: ከሌሎቹ ሁሉ የተሻለና በራሱ የሚተማመን መሆኑን አኖሌ የተገነዘበው ገና ከንግግሩ መግቢያ ነበር፣

ሻለቃው «ወንበዴዎቹ ተራ ዘራፊ ዱርዬዎች አይደሉም:: እንዲያ የሚያስቡት የማስታወቂያ ሚኒስቴር ጋዜጠኞች ናቸው» ሲል ነበር የጀመረው:: በዚህ አነጋገሩ ከፍተኛ መኮንኖቹ በሆታ አውካኩ:: አኖሌ ፈገግ አለ በመገረም::

ሻለቃ ቡልቻ ማብራሪያውን ቀጠለ ...

«... ወንበዴዎቹ ከጉዋድ መሪ እስከ ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ድረስ በየደረጃው በሴሚናርና በስብሰባ መልክ ከውጊያ በፊትና ከውጊያ በሁዋላ እየተወያዩ ስትራቴጂና ስልታቸውን ይቀይሳሉ:: በዚህ ውይይት አበይት ስህተቶቻቸውን ከተመክሯቸው በመነሳት በስልጠናና በልምምድ ያስወግዳሉ:: በደረቅ ልምምድም የግንዛቤያቸውን መጠን ይለካሉ:: ይህ ለእንቅስቃሴያቸው ቅንጅትና ፍጥነት ዋስትና ይሆናቸዋል:: በውጊያዎች የተሳካ ድል የሚያገኙትም ለዚህ ነው:: ውጊያ ከመክፈታቸው በፊት የሚፈፅሙትን የቅንጅት እንቅስቃሴ፣ የሌሊትና የቀን የህብረት ውጊያ ልምምድ ከጉዋድ መሪ ወደላይ ላሉ የአመራር አካላት የሰጡትን ሴሚናር አንድ ባንድ ገምግመናል:: ከግምገማችን ወንበዴዎቹ ባለሙያ፣ ብልህና፣ ባለአላማ መሆናቸውን ነው መገንዘብ የቻልነው::

«ወንበዴው በእግረኛና በሜካናይዝድ ክፍለጦር መደበኛ ውጊያ ማለት Conventional War ሲያካሂድ፣ የአካባቢ ታጣቂ፣ የኮማንዶና የመሀንዲስ ብርጌዶች ደግሞ ሽምቅ ውጊያውን ያግዙታል:: ሁለቱንም በተጉዋዳኝ ወይም በተናጠል መፈፀማቸው ጥበባቸው ከኛ መሻሉን ያሳየኛል::»





ሻለቃው ቀና አለና «ማስታወሻ እየያዝክ ነው?» ሲል አኖሌን ጠየቀው::

«በጣም! በጣም!»

አኖሌ ባንኖ ነበር ምላሽ የሰጠው::

በሻለቃው የአቀራረብ ብስለት እየተደነቀ ነበር ገለፃውን የሚያዳምጠው::

«የኤርትራ ወንበዴዎች ከማንኛውም ፀረ-ኢትዮጵያ መንግስት አቋም ካለው ወገን ጋር ሁሉ ይተባበራሉ:: ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ አረብ አገሮች፣ ህወሀት፣ ኦነግ ከመሳሰሉት ድርጅቶችና አገሮች ጋር ጥብቅ ወዳጅ ናቸው:: ካልመሰላቸው ግን ፖሊሲያቸውን ይለውጣሉ:: ለምሳሌ 'ለአርነት ከሚታገሉ ህዝባዊ ታጋዮች ጋር ሁሉ እንተባበራለን' የሚል ጠንካራ አቋም ነው ያላቸው:: ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ለማስከበር የሚታገሉትን የሱዳን መንግስት ተቃዋሚዎች ግን እንኳን ሊያግዙዋቸው መልሰው ይወጉዋቸዋል:: ጠንካራ አቋማቸውን እዚህ ላይ ሲደርሱ ለምን ሻሩት? ምክንያቱ ግልፅ ነው:: ለጊዜው ሱዳን ታስፈልጋቸዋለች:: ከሱዳን ቢጋጩ ደግሞ ያለጥርጥር ኮሎኔል ጆን ጋራንግን ሳህል ያስጠሩታል:: ማየት ያለብን ወንበዴዎቹ አላማቸውን ከግብ ለማድረስ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሰይጣን ጋር ሊሻረኩ መቻላቸውን ነው:: ከማንም ጋር ያላቸው ወዳጅነት አላማቸውን እስከጠቀመ ብቻ ነው:: አላማ ስንል ጊዜያዊ ጥቅም አይደለም:: አሻግረውም ያያሉ - እንደ ትንቢተ ኢሳይያስ:: ለዚህ ነው የርእዮተ አለም ካባቸውን የሚለዋወጡት::

«የሚገርማችሁ ነገር» አለ ሻለቃው ሲጋራ እየለኮሰ «... ወንበዴው የኛን ጦር ደካማና ጠንካራ ጐን አውቆ እንዴት እንደሚዋጋ ካጠና በሁዋላ ጠንካራውን ተዋጊ ሃይል መርጦ ልምምድ ያደርጋል:: በመጨረሻ ጦሩን ያዝናናዋል:: መዝናናት ሲባል ስነስርዓት ያለው ድግስ ተደርጎ ነው:: የቪዲዮ ፊልም፣ ትያትር፣ ሙዚቃ፣ ምግብ፣ መጠጥ ይቀርባል:: ተዋጊው ሰራዊት በልቶ፣ ጠጥቶ፣ ዘፍኖ፣ ተስካሩን በልቶ ለኤርትራ ህይወቱን እንደሚከፍል ቃል ገብቶ ነው የሚዘምተው» ብሎ ዙሪያ ገባውን ያስተውል ጀመር:: ሁሉም በተመስጦ ያዳምጡታል::

«ሌላው እንግዲህ ለክቡር የአገር ውስጥ ጉዳይ ተወካይ የሚጠቅመው ጉዳይ፣ ሻእቢያ ስለሚያካሂደው ሳይኮሎጂካል ምርፌር ነው:: ወንበዴዎቹ አይበገሬነታቸውን ሲለፍፉ ነው የሚውሉት:: የጦርነቱ ሚዛን ለእነርሱ ያጋደለ መሆኑን፣ አሸናፊነትም የማይቀር የታሪክ ሂደት መሆኑን ይናገራሉ:: የጠራችንን ብሶቶችም ያካሉ::

ይህ ስልታቸው በጣም አደገኛ ነው። በሬድዮ፣ በበራሪ ወረቀት፣ በተባባሪዎች በወኪሎችና በሌሎች ፀረ-አብዮት ሃይላት በኩል ይለፍፋሉ። አባቶቻችን 'ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው' እንደሚሉት ሆነናል። ጄኔራሎች ሳይቀር በሻእቢያ ፕሮፓጋንዳ ይበረግጋሉ። እነዚህ ሰዎች ጄኔራል ታሪኩ አይኔ በመንግስት ትእዛዝ የተገደለ እለት በሬድዮናቸው «ጀግና» ሲሉ አሞግሰውታል። ብልህነታቸውን እዩት። በሚያዘጋጁዋቸው መፃህፍት ግን ይህቺን ቃል አይደግሙዋትም። ምክንያቱም መፅሀፍ ለታሪክ የሚቀር ሰነድ ነው። የሬድዮ ወሬ ግን ፕሮፓጋንዳ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች ታሪኩን ጀግና የሚሉት የሞተ አይጐዳም ብለው አይምሰላችሁ። ሰራዊቱን ለመከፋፈል ነው። ከመንግስት ለመነጠል ነው። ደሞ ተሳክቶላቸዋል። የኛ ጦር 'ሻእቢያ ጄኔራል ታሪኩን ጀግና አላቸው። ሀቅ ነው።' እያለ ከጫፍ ጫፍ ተንሾካሾከ። የሻእቢያ ሬድዮ ታማኝነትን አገኘ። 'አይዋሹም' የሚል ሚዳይ አገኙ። የኛ መንግስት «ጀግኖችን ይገድላል» የሚል ስያሜ ሊከናነብ፤ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ደግሞ ያን ቀን ምሽት 'ስንዴ ከካናዳ መንግስት በእርዳታ ተገኘ' የሚል ዜና ነው ይናገር የነበረው» ሲል ከፍተኛ መኰንኖቹ ጠባብዋን የስብሰባ ሳሎን በሳቅ አፈረሱዋት። እኖሌም አብሮ ይስቅ ጀመር። ሻለቃው ሲጋራውን መጦ ተረኮሰውና ቀጠለ።

«ከወንበዴው ጠንካራ ጐኖች ሊጠቀስ የሚገባው ሌላው ጉዳይ የመረጃ ስራቸው ነው። ብታምኑም ባታምኑም በመንግስት ደረጃ የተያዙ ብሄራዊ ምስጢሮችን ያገኛሉ። እኔ ለዚህ በቂ መረጃ አለኝ። ይህ ከባድ ጉዳይ ነው። የመረጃ ክፍላቸው ከሶስት መቶ በላይ የሰለጠነ የሰው ሃይል ያለው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ! ማለት በመተንተኛ ኰምፒውተር የተጠናከረ የጠለፋ ክፍል ስላለው የወገንን መልእክቶች ሙሉ በሙሉ መጥለፍ ይችላሉ። ይህ የመረጃ ስራም ኢሳይያስ ቁጥር ሁለት ተብሎ በሚጠራው ጴጥሮስ ሰለሞን የሚመራ ነው። እኛ ግን የነሱን ሳይፈር መድፈር አቅቶናል። አንድ አብነት ለማንሳት! የኛ ጦር በአብዛኛው በውጊያ ወቅት መልእክት በግልፅ ይለዋወጣል። ፈንጂ ለማለት 'ድንች' ታንክ ለማለት 'ኤሊ' መንገድ ለማለት 'መቀነት' ጥይት ለማለት 'ቆሎ' የሚሉት ናቸው የጦሩ የተለምዶ የኰድ ቃላት። ይሄ በእውነቱ በጣም ያሳፍራል። ከፈረንሳይ ሰራዊት ጋር አይደለም የምንዋጋው። አማርኛ ቋንቋን አቀላጥፈው ከሚናገሩ ሰዎች ጋር እንደምንዋጋ ጨርሶ ረስተነዋል። እዚህ ዘንድ የሚዛን ጉድለት ይታያል። በተቀረ በረሃ ውስጥ የመድሃኒት፣ የጥይት፣ የጦር መሳሪያ፣ የልብስ፣ የጫማ ፋብሪካዎች አሏቸው። ሳህል ውስጥ በአፍሪካ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ዘመናዊ ጋራዥ አላቸው። ይሄ እውነት ነው። ሌላው ሊነሳ የሚገባ ነጥብ፤ እነዚህ ሰዎች በባህርያቸው አይለምኑም።





አለመለመንን ባህል አድርገውታል። በውነቱ አለመለመን ፀጋ ነው። ከልመና ይሰውረን ማለትም ታላቅ ፀሎት ነው።

«ሌላው የውጭ ሀገር ጋዜጠኞችን በማሳመን፣ አስፈላጊ ሲሆን በገንዘብ በመደለል የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ዘመቻም ይለቁብናል። እኛ አፀፋውን ለመመለስ ቀርቶ ግንዛቤውም የለንም።

«... ስለ ጠንካራ ጐኖቹ ይህን ካልን ይበቃናል። ደካማ ጐኖቹን ደግሞ ልጠቃቅስ፣ እንኀዲህ በሃይማኖት በዘርና በባህል በመሳሰሉት ምክንያቶች በኤርትራ ቆላማ መሬትና በደጋማው አካባቢ በሚኖሩት መካከል የቆየ ቅራኔ አለ። የቆላው ህዝብ ልብ አሁንም ከጀብሃ ጋር ነው። ሌላው የአፋር ህዝብ ፍላጐት ደግሞ የራሱን አስተዳደር መስርቶ ከኢትዮጵያ ጋር ዝምድና መፍጠር በመሆኑ እዚያም አካባቢ አለመግባባት ይታያል። ይህ ሁኔታ አሰብን ከኤርትራ አውራጃዎች ለመነጠል ያመቸናል። ጀብሃ የሚጠናከርበትን መንገድ መፈለግም በአንፃራዊ መልኩ ሻእቢያን ማዳከም ነው። ጅሃድ የተሰኘ እንቅስቃሴም በምእራባዊ ቆላ አካባቢ አለ። ይህ ለሻእቢያ ትልቅ ውጋት ነው። ሻእቢያ በእስልምና ሃይማኖት በኩል የሚመጣበትን ችግር በቀላሉ ስለማይፈታው ያንን ቁስሉን እንዳይነኩበት ዘወትር እንደተንፈራገጠ ነው። የሻእቢያ መሪዎች ጅሀድና ጀብሀ የሚባሉትን ቃላት መስማት አይፈልጉም። ስለዚህ እዚያ አካባቢ ደጋግሞ መጮህ ያስፈልጋል። ሌላው ዴምሀኤ በሚል ስያሜ ማለትም ዴሞክራቲክ ምንቅስቃስ ሀርነት ኤርትራ የተሰኘ አምስት ሻምበሎች ያሉት ቡድን ተቋቁሞ በትግራይ ድንበር አካባቢ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ምናልባትም ይህ ሃይል በህወሀት እየተረዳ ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ አንድ የግሌ ጥርጣሬ አለኝ። ህወሀት ሻእቢያን ለማስፈራራት ይቃጣ ይሆን? ይህ አልዋጥ ይለኛል። ህወሀት ከሻእቢያ የሚያገናኘው ገንዘብ የማይገዛቸው አያሌ ወታደራዊ አገዛዞች አሉ። ወያኔዎች እኒያን ማጣት አይሹም። ይህ ከሆነ ህወሀት ዴምሀኤን በነፃ መሬቱ እንዲጠለል ለምን ፈቀደለት? ምናልባት ይህም የሻእቢያ የራሱ መርሀግ ተንኮል ይሆን? እዚህ አካባቢ ፍተሻ ያስፈልጋል። ቂላቂሎቹ የዴምሀኤ ሰዎች ሳያውቁት በትግራይ ምድር የቁም እስረኛ ሆነው ይሆን? ምናልባትም ቀለብ የሚሰፍርላቸው ሻእቢያ ራሱ ሊሆን ይችላል። ይሄ እውነት ከሆነ ሙቼም የዘመናችን ታላቅ ቀልድ ተብሎ ይመዘገባል» ብሎ በሳቅ ይንከተከት ጀመር። ሌላ የሳቀ አልነበረም። ብቻውን ስቆ ሲያበቃ ማብራሪያውን ቀጠለ «... ይቅርታ ጉዋዶች። ነገሩ በጣም ያስቅ ነበር። ለምን እንዳልሳቃችሁ አልገባኝም። በአገራችን ባህል ጉዋደኛ ሳቅን ቀርቶ ለቅሶንም ይጋራ ነበር» ሲል ተሰብሳቢው ሁሉ በሳቅ ጮኸ። ይሁን እንጂ ሻለቃው በተራው ሳይስቅ ቀረ። ሳቁ ጋብ ሲል ጠብቆ ቀጠለ፣ «ለማንኛውም

ቀዳዳውን ጉርጉሮ በህወሀትና በሻእቢያ መካከል ያለው መተሳሰር እንዲላላ ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ነው።

«ሌላው የሻእቢያ ደካማ ጎን የመገንጠልን ጥያቄ ማራመዱ ነው። ይህን አቋሙን የማይደግፉትን በውጭ ሀገር የሚኖሩ ተቃዋሚ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ማስተባበርና በነርሱ በኩል ውጥረት መፍጠር ያሻል። የጦርነቱ መራዘምም በሻእቢያ ተዋጊዎች ላይ መሰላቸትን ማስከተሉ ስለማይቀር ያንንም ቀዳዳ መጠቀም ተገቢ የሚሆን ይመስለኛል።»

ይህን ብሎ ሻለቃው ማስታወሻ ደብተሩን አጠፈ። ውይይቱም በዚሁ መልክ እንደተለመደው እስከ እኩለ ቀን ቀጠለ።





# ቼንቶ ፔር ቼንቶ!

# ጉዋል ኤሬ - ሮዚና!

## ምእራፍ ሰባት

### - 1 -

በክፍሉ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደ ሮዛን ይጠብቃት ጀመር። ትእግስት አጥቶአል። በተምታታ የሀሳብ ኩሬ ውስጥ እየተንቦራጨቀ ነው። ሁኔታዎች አላማሩትም። በስጋት ተይዞአል። ስጋቱ ምክንያተ ቢስ አልነበረም። በተለይም መከላከያ ሚኒስትሩ ወደ ደህንነት ፅህፈት ቤት የመሩት ደብዳቤ ከማስገረም አልፎ አስግቶታል። ስለጉዳዩ ጂብሪልን በቀጥታ መጠየቅ ስላልደፈረ ዳርዳር ብሎት ነበር።

'ሻለቃ ጉተማ እኔ ላይ ያቀረበው ክስ ይኖር ይሆን?' ነበር ያለው እንደዋዛ። 'እስካሁን የለም' የሚል ነበር የጂብሪል ምላሽ።

አኖሌ አላመነውም። እንደደበቀው ገመተ። ሌላው ተጨማሪ ስጋት የሰላዩ ሹፌር ማስፈራሪያ ነበር። እየደወለ ይነጫነጫል። በተዘዋዋሪ 'ህይወትህ በመዳፌ ላይ ናት' እያለ ሊያስፈራራ ይቃጣዋል። ሀወኒም የለችም። አባቱ ሞተዋል። ስራው ከእለት እለት እየቀፈፈው ነው።

የአስመራ ቆይታው የኢሰፓ መንግስት መሰረት እየተናደ ለመሆኑ ወሰል ብሎ ያይ ዘንድ ረድቶታል። እነዚህ ምክንያቶች አለመረጋጋትን ፈጥረውበታል። እና ቢቻል ከዚህ ከተወሳሰበ ሁኔታ ገለል የሚልበትን መንገድ መፈለግ እንዳለበት አምኖአል።

ግን እንዴት?

ጥናቱን ጨርሶ ወደ አዲስ አበባ መመለስ አልታየውም። ከዚሁ ከአስመራ ወደ ውጭ ሀገር መውጣት የሚችልበት መንገድ ካለ ማየት ነው የፈለገው። በዚህ ጉዳይ ላይ ማነጋገር የሚችለው የቅርብ ሰው ግን አልነበረውም። ይህን የመሰለ ጨዋታ ከሳሙኤል በቀር የሚጋራው የለም። ሳሙኤል ደግሞ ሩቅ ነው - አዲሳባ። ከሁለት ቀናት በፊት በስልክ የተገናኙ ጊዜ 'ሮዛን ማንኛውንም ነገር ታግዝህለችና ቅረባት' ብሎት ነበር። ሌላ አማራጭ አልነበረውም። ሮዛ የአስመራ ነዋሪ በመሆንዋ የከተማዋ ወጣቶች ወደ ሱዳን የሚሾልኩባቸው ቀዳዳዎች ልታውቅ ትችል ይሆናል ብሎ ገምቶአል። አውጥቶ አውርዶ የደረሰበት መደምደሚያ ይኸው ነበር - ፍርጥ አድርጐ ሊነግራት። በዚሁ ጉዳይ ላይ ሊያዋያት ዛሬ እኩለ ቀን ላይ ደውሎላት ነበር። ለጥብቅ ጉዳይ እንደሚፈልጋትና ሆቴሉ ድረስ እንድትመጣ ሲጠይቃት ጥቂት አመንትታ ነበር። 'ምን ሆነህል?' ብላ ደጋግማ ስትጠይቀው በቴሌፎን ሊነግራት እንደማይችል ገለፀላት። እያቅማማች 'ከምሽቱ ሰባት ሰአት - በአስመራ አቆጣጠር እመጣለሁ' አለችው።

እና አሁን ሰአቱን አየ። አስር ደቂቃ አልፎአል። 'መቅረትዋ ይሆናል' ብሎ ሲያስብ የክፍሉ በር በቀስታ ተቆረቆረ። አኖሌ ተጣድፎ ሄዶ በሩን ከፈተው። ሮዛ ነበረች። ጥቁር መነፅር አድርጋለች። አናዋን በአንገት ልብስ ሸፍና ነበር። ሙሉ ጂንስ፣ ነጭ ስኒከር።

«እንኳዋን ደህና መጣሽ ሮዛ»

ቀድማ ስትጨብጠው፣ ስቦ ሳማት። ሮዛ ፈጥና መነፅርዋንና የአንገት ልብስዋን አወላልቃ አልጋው ላይ ወረወረች።

«እየሰጋሁ ነው የመጣሁት አኖሌ» አለች።

«ምን ተፈጠረ?»





«የናንተ ሰዎች ጣጣ ምን ማለቂያ አለው? በሰበብ አስባቡ መታሰር፣ መገደል ይበዛል። ሰዎቻችሁ መግደል ይወዳሉ። ከመጠየቅ ማሰር ይቀናቸዋል» ብላ ፈገግታ አሳየችው።

ይህን ብላ ሰአትዋን መልከት አደረገች፣

«በል መሸቶአል፤ ወደ ጉዳያችን እንግባ» አለችው።

አኖሌ ጥቂት አመነታ። ከምን እንደሚጀምር ጨነቀው።

«አንድ ከባድ ጉዳይ ላዋይሽ ፈልጌያለሁ» ሲል ጀመረ።

በእሺታ ራስዋን ላይ ታች ወዘወዘች።

«የልቤን የማወጋው ሌላ ሰው ባለመኖሩ ነው አንቺን የመረጥኩት። በዚህ ላይ በኔና ባንቺ መካከል ሳሚ አለ ብዬ ስለማስብ ነው።»

እንደገና በመስማማት ራስዋን ወዘወዘች።

«አሁን የማነሳልሽ ጉዳይ አደገኛ ስለሆነ ከኔና ካንቺ ውጭ ሌላ ሰው ሊሰማው ከቶ አይገባም። ማለቴ የምጠይቅሽ ጉዳይ የማይሳካ ከሆነ ...»

ሮዛ ድንገት አቋረጠችው፣

«አኖሌ ... የጋብቻ ጉዳይ ከሆነ ከወዲሁ ባናነሳው እመርጣለሁ። ማማ እንዳየሀት ብቸኛና ደካማ በመሆንዋ ረጅም አመታት ከጐንዋ የምለይ አይመስለኝም።»

አኖሌ በመገረም ያስተውላት ጀመር። አስመራ ከመጣ ጀምሮ ሶስት ጊዜ ብቻ ነው የተገናኙት። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የጋብቻን ጉዳይ ያነሳል ብላ ማሰብዋ አስገረመው፣ ይህን ንግግር ከሮዛ እንደበት መስማቱም አጠራጠረው።

«እንዴት እንዲህ አሰብሽ ሮዛ?» አላት በሞቀ ድምፅ።

«እዚህ አገር ስጋብቻ መጠየቅ በጣም የተለመደ ስለሆነ ነው። ይቅርታ» አለችው።

«ምንም አይደል» ካለ በሁዋላ እንደገና ወደ ርእስ ጉዳዩ በቀጥታ ለመግባት ያምጥ ጀመር።

«ስሚኝ ሮዛ ... ላማክርሽ የፈለግሁት ከዚህ አገር መውጣት ስለሚቻልበት መንገድ ነው። አሁን በዝርዝር ልነግርሽ በማይቻለኝ ምክንያቶች ከዚህ አገር የግድ መውጣት አለብኝ። ጉዳዩ ከባድ ነው። ግን አንድ ነገር ልግለፅልሽ። ህይወቴ አደጋ ላይ ናት።

ከዘገየሁ የኔ ነገር ሊያከትም ይችላል። ስለዚህ እንድትረጂኝ እፈልጋለሁ። ከአስመራ በርካታ ወጣቶች ወደውጭ እንደሚኮበልሉ ይታወቃል። ያንን የመሸሎኪያ ቀዳዳ ደግሞ ከእናንተ ከአገሬው ተወላጆች በቀር ሊያውቀው የሚችል ከቶ አይኖርም። ስለዚህ ከልብሽ እንድትረጂኝ እማፀንሻለሁ ...» ብሎ በተስፋ ያስተውላት ጀመር።

ሮዛ ስትደነግጥ አስተውሎአታል። ግን በጥሞና ነበር ያዳመጠችው። ተናግሮ ሲያበቃም በረጅሙ ተንፍሳ፣

«እንዳልከው ከባድ ርእስ ነው አኖሌ!» አለች።

«ይገባኛል። ግን አጣብቂኝ ውስጥ ነኝ። ሳሚ እንደነገረኝ ከሆነ ከዚህ ከኤርትራ ለመውጣት የሚቻልባቸው አንዳንድ መንገዶች አሉ። አንቺን እንዳማክርሽም ጠቁሞኛል።»

«ምን መሰለህ አኖሌ፣ እንዲህ ያለ ነገር መነጋገር የሚቻለው ወይም የሚሞከረው ለህይወታቸው በማይሳሱ፣ ቃላቸውን መጠበቅ በሚችሉ ሰዎች መካከል ብቻ ነው። ነገ በኔም ሆነ በቤተሰቤ ላይ ሞት ከሚያስፈርድ ጨዋታ ውስጥ መግባት ይከብዳል።»

«እኔ ምስጢር የመጠበቅ ብቃት ያለኝ አልመስለሽም?» አለ ግልፍ ብሎት። ፊቱ ባንድ ጊዜ ጉብት መሰለ።

«እንዲያ አላልኩም አኖሌ! ይህን ያህል የማናግርህም ስላመንኩህ ነው። ግን ሀገር የሚያስለቅቅ ምን ችግር ይገጥምሀል ብዬ አስቤ ነው?»

«በጣም አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነኝ ሮዛ!»

ሮዛ ለሰከንዶች ያህል ተደምማ ከቆየች በሁዋላ

«ወጣቶች ከአስመራ እንዲወጡ የሚረዳ አንድ ሰው አውቃለሁ። እሱን ላግኘውና ነገ ልመለስ ...» ስትል ተነፈሰች።

ይህን ብላም ፈጥና ከተቀመጠችበት ተነስታ በመነፅርዋና በአንገት ልብስዋ ራስዋን ሸፋፍና ለመልስ ጉዞ ተሰናዳች።

«ልሸኝሽ?» ሲል ጠየቃት አኖሌ።

«እዚሁ ቆይ! ካንተ ጋር መታየት አልፈልግም» ስትል ተከላከለች። እጅዋን እንደያዛት ቆመ። ውስጥ እጅዋ ፈጀው። አጥብቆ የያዘው መዳፍዋ ሙቀት እየጨመረ ሄደ። ሮዛ በተረበሸ መንፈስ አይን አይኑን ስታየው ቆየች። ምን ማድረግ እንዳለበት ተደናገረ። ቀስ ብሎ ለቀቃት፣





«ሮዚና!»

«ደህና እደር አኖሌ» ብላ እብስ አለች።

* * *

በነጋታው በቀጠሮው ሰአት ነበር የክፍሉ በር የተቆረቆረው። አለባበስዋ በእጅጉ አስገረመው። ዛሬ እጅግ ተውባለች። ሽቅርቅር ብላ በአስመራ ጉዳናዎች ላይ የሚታዩትን ኮማሪዎች መስላለች።

አኖሌ «እንዴት ሆነ ጉዳዩ?» የሚል ጥያቄ ያቀረበላት በችኮላ ነበር።

«ያልኩህን ሰው አገኘሁዋለሁ። ብዙ ከተወያየን በሁዋላ አሳምኜዋለሁ። የደህንነት ሰራተኛ መሆንህን ስነግረው አንቀ ሊገድለኝ ደርሶ ነበር። እንደምንም አበረድኩት። በመጨረሻ ሊያገኝህ ወስኖአል። ሰውየው እንደሚለው ከሆነ አንተን በሁለት መንገድ ከአስመራ ማስወጣት ይቻላል። የመጀመሪያው በገንዘብ ሃይል ነው። ሁለተኛውን አልነገረኝም። የገንዘቡ ካልተሳካ ብቻ ነው ወደ ሁለተኛው አማራጭ የምንገባው ይላል»

«ገንዘቡን ምን ያህል ይላሉ?»

«መቶ ሺህ የኢትዮጵያ ብር።»

«አብደሻል!?» ብሎ ጮኸ።

«በየጊዜው የሚፈፅሙት ነው አኖሌ። የመንግስት ሰዎች በተዋረድ የሚከፋፈሉት መሰለኝ። ይህ ሁሉ ለአንድ ሰው የሚሰጥ ገንዘብ አይደለም። የሚገርምህ ይህ የምነግርህ ሰው ከዚህ ገንዘብ ሁለት ሺህ ብር ብቻ ነው የሚያገኘው። ከባድ ስራ ይመስለኛል።»

ወዲያው ተስፋ ቆረጠ። እና ሌላ መንገድ ማሰላሰል ጀመረ።

«ያን ያህል ገንዘብ አይኖርህም?» ስትል ጠየቀችው።

«እየቀለድሽ ነው!?»

«ምን ያህል ይኖርሃል?»

«ይህን ርእስ እንርሳው ሮዛ! እንኳዋን እዚህ አዲሳባ ያለኝ ጥሬ ገንዘብና ንብረት ቢሸጥ መቶሺህ አይሞላም።»

«በአስቸኳይ ገንዘብ ሊልኩልህ የሚችሉ ሰዎች ካሉ፣ ሳሚ ጥቂት እንዲጨምርልህ ማድረግ ይቻላል። በርግጥ አደጋ ላይ ከሆንክ አይናችን እያየ መሞት አይኖርብህም ...» አለች።

በሁለት እጁ ከንዶችዋን ጨምድዶ ይዞ በፍቅር አስተዋላት:: ጭንቀትዋ ውስጡ ገባ:: ግን ምንም መፍትሄ የለውም:: የባዶ ሜዳ ህልም ሆነበት::

ከቆይታ በሁዋላ አስታወሰና፣

«ሁለተኛው አማራጭ የተባለውስ ምንድነው?» ሲል ጠየቃት::

«እሱን አልነገረኝም:: ከራስህ ጋር ካልተነጋገረ በቀር ለኔ ሊገልፅልኝ እንደማይችል ነው የነገረኝ:: ምናልባት ገንዘቡን የሚቀንስበት ሁኔታ ካለ ራስህ ለምን አታገኘውም?»

«ታማኝ ሰው ነው?»

«ቹንቶ ፔር ቹንቶ!» አለች ሮዚ:: መቶ በመቶ ማለትዋ ነበር::

«ምን ማረጋገጫ አለሽ?»

«ከሀያ በላይ ወጣቶችን ያለችግር ሱዳን እንዳደረሳቸው አውቃለሁ:: በዚህ ላይ የብሌን ተወላጅ ነው:: ብሌኖች በክህደት ጨርሶ አይታሙም:: ይህ በድፍን ኤርትራ የታወቀ ነው:: አንድ ጊዜ ታስሮ ተገርፎ ነበር:: በድብደባ ብዛት ስድስት ወር ካልጋ አልተነሳም:: ግን አላመነም:: ስባሪ ምስጢር ሳያወጣ ሲቀር ለቀቁት»

«እና እንዴት ላገኘው እችላለሁ?»

«ቀጠሮ ልያዝልህ:: ነገ በዚህ ሰአት ...»

«ጥሩ:: የት?»

«እዚሁ ይመጣል:: ከምሽቱ ስምንት ሰአት - በኛ አቆጣጠር:: በርህን ሶስት ጊዜ ብቻ ይቆረቁራል:: ያን ጊዜ እሱ መሆኑን ታውቃለህ:: ስሙ አዶናይ ይባላል::»

ከዚያም ለመሄድ ተነሳች:: ሊሸኛት ከቃጣ በሁዋላ እንደምትከለክለው ተረድቶ ቆም ሲል ...

«ዛሬ ረጅም መንገድ ትሸኘኛለህ::» አለችው::

«ምን ተገኘ?» አለ በመገረም::

«ምናልባት ለዘልአለሙ የምንለያይበት ቀን ሊሆን ይችላል» ብላ ፊትዋ በሀዘን ጉም ሲዋጥ አየና እሱም ስሜትዋ ተጋብቶበት ተረበሸ::

«ተስፋ ማድረግ ሁልጊዜ ጠቃሚ ነው» አላት::

ከሆቴሉ ወጥተው የአስፋልቱን ዳር ይዘው በዝግታ ያዘግሙ





ጀመር::

«ሮዚና»

«እህ!»

«ተግባብተን ነበር .. አይደለም?»

«ነበር!»

«እጮኛ አለሽ?»

«የለኝም::»

«ለምን?»

«አጋጣሚ!» ብላ ፈገግ አለች::

«መቼም ኤርትራዊ የማግባት ሀሳብ ነው የሚኖርሽ» አላት:: ኤርትራውያን በትዳር ላይ ያላቸውን ግትር አቋም አሳምሮ ያውቃል::

«ምን መሰለህ እኖሌ ... እኛ የኤርትራ ሰዎች እኮ ዘረኞችና ጠባቦች አይደለንም:: በርግጥ በበርካታ ኤርትራዊያን ላይ ጋብቻን በተመለከተ ተመሳሳይ እምነት ሊኖር ይችላል:: ምክንያቱ ግን ብዙዎች እንደሚገምቱት ዘረኝነት አይደለም:: ማንነትህን ላለማጥፋትና ኤርትራዊነትን ጠብቆ ለማኖር የሚደረግ ተጋድሎ ነው:: ኦሮሞዎችና አማራዎች በቁጥር ብዙ ናችሁ:: ባህላችሁና ማንነታችሁ በቀላሉ ሊዋጥ አይችልም:: እኛ ግን ሶስት ሚልዮን አንሞላም:: ይህቺም በዛች ተብላ በየእለቱ በቦምብና በጥይት የሚያልቀውን ህዝብ አስብ:: እልቂቱ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ መንግስትም እንደሚፎክረው በጅምላ ሊያጠፋን ከቃጣ ኤርትራዊ የሚባል ዜጋ ለዘልአለሙ ሊጠፋ ይችላል:: በርግጥ ከዚህ የተሰደዱ ኤርትራውያን ከአንድ ሺህ አመት በሁዋላም ቢሆን ወደ አባት መሬታቸው ይመለሱ ይሆናል:: ይህ ጭንቀት ታዲያ በእያንዳንዱ ኤርትራዊ ጭንቅላት ውስጥ የታተመ ነው:: ስንወለድ ጀምሮ ኤርትራዊ መሆናችንን፣ በማንነታችን መኩራት እንደሚገባን፣ በጋብቻም ቢሆን ርስ በራሳችን መጋባት እንዳለብን ወላጆቻችን ያስተምሩናል:: ይህ እምነት በውስጣችን ህግ ሆኖአል:: እኔን በተመለከተ ግን ኤርትራዊ ባይሆንም የወደድኩትን ላገባ እችላለሁ» ከዚያም ፈገግ ብላ «... በርግጥ የወደድኩት የሌላ አገር ሰው ከሆነ አንድ ግዴታ አስገባዋለሁ» አለች፣

«የምን ግዴታ?»

«የልጆቹ ማንነት ጥያቄ ላይ ...»

«እንዴት?»

«ኤርትራዊ መሆን ይኖርባቸዋል ብዬ አምናለሁ»

«አይከብድም? ላይፈልጉ ቢችሉስ?»

«ዋናው አስተዳደግ ነው:: እኛን ቤተሰቦቻችን የሚኮተኩቱን ገና ህፃን ሳለን ነው:: በዚህም ምክንያት ሳታውቀው ጤናማ ትምክህት ይይዝሃል:: ያን ጤናማ ትምክህት ደግሞ በምብና ቃጠሎ አያጠፋውም::» ካለች በሁዋላ፣ «በጣም ለፈለፍኩ? እና የሻእቢያ ካድሬ መሰልኩ? ደሞም ብዙ አመንኩህ? እንዳታሳስረኝ አደራ...» ብላ ጣፋጭ ሳቅ አሰማችው::

አኖሌ ሳቀና እጁን ትከሻዋ ላይ አሳርፎ ጉንጩዋን ሳማት:: ቁና ሙሉ አየር ስትተነፍስ ሰማ:: ሰውነቱዋ ማተኮስና መንቀጥቀጥ ጀመረ::

«ተመችተሺኛል» አላት የዜኒትን አነጋገር አስታውሶ::

«እውነት?»

በድጋሚ ሳማት - ጉንጭዋን::

«የምንገናኝ ይመስልሻል?»

«እግዚአብሄር ያውቃል::»

«እኔስ ከዚህ አገር በሰላም የመውጣቱ ጉዳይ ይሳካልኝ ይሆን?»

«ቼንቶ ፔር ቼንቶ» አለችው::

«እውነት?»

«አኖሌ ሙት! አዶናይ የተረገመ ሰው ነው»

በጨለማ ውስጥ አስር ደቂቃ ያህል እንደተጉዋዙ፣

«በቃህ ተመለስ» ብላ አቆመችው::

እጅ ለእጅ ተያይዘው በፀጥታ ቆሙ:: አኖሌ እጆችዋን እያሻሸ፣

«ወደ አስመራ ስመጣ ቀበጥ ልጆችን ጠብቄ ነበር» አላት::

«እንደ አሮማይዋ ፊያሜታ?» ብላ ሳቀች::

«አዎን ... ፊያሜታ ፅብቅቲ ... ጉዋል አስመራ» አለ::

«በነገራችን ላይ» አለች ሮዛ «... ፊያሜታ ኢትዮጵያዊት እንጂ ኤርትራዊት አይደለችም:: ማንም ኤርትራዊ ይህንኑ ይነግርሀል::»

ኤርትራን አገር አድርጋ በማውራትዋ አኖሌ አልተገረመም:: በሳሙኤል ሰምዶታል:: ይልቁን፣





«ፊያሜታን ለምን እንዲያ አየሻት?» ሲል ጠየቃት::

«በበኩሌ ኤርትራዊት ወጣት ሴት እንደ ፊያሜታ ስታስብ ጨርሶ ሰምቼና አይቼ አላውቅም:: ፊያሜታ ኢትዮጵያዊት ናት ብለን ልንቀበል ግን ይቻለናል::»

«... ቢያንስ ከሀዲ ኤርትራዊት ለምን አትያትም?» አላት አኖሌ እየታዘባት::

«ከሀዲ ኤርትራዊ አለ ብዬ አላምንም» ስትለው አኖሌ የፌዝ ፈገግታ እያሳያት፣

«ጭፍን አስተሳሰብ ነው ሮዛ:: ካንቺ ይህን ከቶ አልጠብቅም::» አላት::

«አውቃለሁ» አለች ሮዛ በፈገግታ ተውጣ «... በአማራ ገገሮች ላይ ባለኝ ገደብ አልባ ጥላቻ የተፈጠረ ባህርይ ይመስለኛል:: ስሜቱ ቢያንስ ኤርትራዊነቴን በከፍተኛ ሁኔታ ጠብቄ ለማቆየት ያግዘኛል:: ሌላውን እስካልጉዳሁና እስካልናቅሁ ድረስ ደግሞ የኤርትራዊነት ስሜቱ ስማይን ጥሶ ቢሄድ አደጋ የለውም ብዬ ነው የማስበው»

እየተያዩ ጥቂት ቆዩ::

አኖሌ ወደ ደረቱ አስጠግቶ አንገትዋ ስር እየሳማት፣

«ቢያንስ የመንፈስ ጥንካሬሽን አደንቀዋለሁ» ሲል አንሾካሾከ::

መልስ አልሰጠችውም::

«አልረሳሽም» ሲል አከለ::

«እኔም» ስትል ተነፈሰች::

በዝምታ አይን አይኑን ታየው ቀጠለች::

ከንፈርዋ ላይ ሳማት:: አልተከላከለችውም:: ቀዘቀዘው ከንፈርዋ፣

«በርዶሻል?» ሲል ጠየቃት::

ወደ ጆሮው ጠጋ ብላ:-

«ህዝባችን ሁሉ በርዶታል» አለችው፣ እያይዛም «ይቅናህ:: ከእንግዲህ ልታገኘኝ አትሞክር» ብላ በሁለት እጆችዋ አቅፋ ሳመችው:: አሁን ግን ከንፈሮችዋ ፈጁት::

ሮዛ ይህን ፊዕማ ከመቅስበት ጥላው ነጉደች::

ቆሞ ቀጭንዋን ልጅ ከጀርባዋ ተመለከታት::

... ሮዚና እያንጉራጉረች ነጉደች::

የፀሀይቱ ባራኪን አለያም የበረከትን አልነበረም የምታቀነቅነው:: ወይ ደሞ የየማን ባርያን መቸ ሆኖ? የወዲትኹልን አለያም የፊሂራን አልነበረም የመረጠችው:: ጨርሶ ዘፈንም አይደለም - ግጥም እንጂ:: የግጥሙን ደራሲ አታውቀውም:: ድንገት ነበር በድምጺ ሀፋሽ ሬዲዮ ሲነበብ ያደመጠችው፤

*... ነዚ ምድሪ ቀሰይ ኢልኩም ርገፁዎ*

*መን ይፈልጥ ደም ተጋዳላይ ለለዎ*

*ነዚ መሬት ተጠንቲቅኩም ከዑዋቱዎ*

*መንይፈልጥ አዕፅምቲ ጅግና ሂዙሉ*

*ዝረገፅኩም መሬት አከብሩዎ*

*ብደም ሰማእታት ቅዱስ ኰይኑሉ*

ግጥሙ ሲነበብ በሚያንቀጠቅጥ ስሜት ነበር ያዳመጠችው - ከበረሃው የሻእቢያ ሬድዮ:: በቃልዋ ይዛዋለች:: መበርታት ስትፈልግ ዘወትር በዜማ ታንጐራጉረዋለች ...

ቀጥታ ትርጉሙ፤

*ይህን ምድር ቀስ ብላችሁ ርገጡት*

*ማን ያውቃል የተጋዳይ ደም አለበት*

*ይህን መሬት ተጠንቅቃችሁ ቆፍሩት*

*ማን ያውቃል የጀግኖችን አፅም ይዞአል*

*የረገጣችሁትን መሬት አክብሩት*

*በሰማእታት ደም ቅዱስ ሆኖአል - ማለት ነበር::*

- 2 -

በሩ በዝግታ ተቆረቆረ ...

አኖሌ በዝምታ በር በሩን ያስተውል ጀመር:: ተደገመ፤ ተሰለሰ:: ከዚያ ቆርቆራው ቆመ:: አኖሌ ጥቂት ጠበቀ:: አራተኛ ባለመቆርቆሩ ተነስቶ ከፈተው:: ወፍራም ጃኬት የለበሰ ጢሙን በቀጭኑ የተላጨ ሰው ቆሞአል:: አፍንጫው ከመርዘሙ የተነሳ ሌላውን የሰውነት ክፍሉን ጋርዶታል:: ራሰ በራ ጀመር ያደረገው፤ ቀጭን መካከለኛ ቁመት ያለው፤ ርጋታ ገፅታው ላይ የሚነበብበት ሰው ነበር::

«አኖሌ ...» ብሎ እጁን ዘረጋለት::





«አዶናይ እባላለሁ ... ሮዛ ልካኝ ነው::»

«እኔም እየጠበቅሁ ነበር!» ብሎ ወደ ውስጥ ይገባ ዘንድ ጋበዘው::

ሰውየው ገብቶ ተቀመጠ:: አኖሌ አልጋው ጫፍ ላይ አረፍ ብሎ ... ምን አይነት ወሬ እንደሚጀምር እየጨነቀው፤

«ምን ይምጣልህ?» ሲል ጠየቀው::

«ምንም አልፈልግ ... ቶሎ መመለስ አለብኝ» ብሎ ሰአቱን አየ:: ቁጥብነት ይታይበታል::

«መልካም ... ሮዛ በዝርዝር ነግራህ እንደሆን አላውቅም::»

«ጫፍ ጫፉን አንስታልኛለች ...» አለና መልሶ ዘና አለ::

«በግልፅ እንነጋገር ታዲያ?»

«ጥሩ ... ከተጀመረ ግልፅ መሆን ይሻላል:: እዚህ አገር በርካታ አጠራጣሪ ነገሮች አሉ:: አንተ ወይም እኔ የመንግስት ሰላይ ልንሆን እንችላለን:: ምንም ማረጋገጫ የለም:: ለጊዜው ግን ሁለታችንም ሮዛን አምነን እንነጋገር::»

አኖሌ ጭንቀት ሰፈረበት:: ይህን ባለጐራዱ አፍንጫ የግድ ማመን እንዳለበት አሰበ:: ከዚህ ወዲያ ማፈግፈግ አይችልም:: ከሞት አደጋ ጋር ቁማር ጀምሮአል:: ላፈግፍግ ቢልም አይችልም:: አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶአል:: እና ቀጠለ ...

«እኔም ሮዛን አምኜ ነው የማናግርህ» ካለ በሁዋላ «... ባጭሩ ስለኔ እንዳጫወተችህ ነግራኛለች:: መንግስት ወደ አስመራ ለስራ ልኮኛል:: ስራዬን አጠናቅቄ እንደጨረስኩ ግን ከዘጠና በመቶ በላይ ጥሩ ሁኔታ ላይገጥመኝ ይችላል:: በዚህ ምክንያት ከኢትዮጵያ መውጣት እሻለሁ:: ቀደም ሲል ጀርመን ነው የነበርኩት:: አመጣጤ የተሻለ ሁኔታ ይገጥመኛል ብዬ ነበር:: አባቴንና ፍቅረኛዬን ለማግኘት ጓጉቼም ነበር የመጣሁት:: አሁን ግን ሁኔታዎች እንደጠበቅሁት አልሆኑም:: የምሰራው ስራ አልተስማማኝም:: አባቴም ሞቶአል:: ፍቅረኛዬን አላገኘሁዋትም:: ያለችበትን እግዚአብሔርም አያውቀው:: በዚህ ላይ መንግስት በፖለቲካ አመለካከቴ ጠርጥሮኛል:: የማያስፈራሩኝ የደህንነት ሰዎችም አሉ:: ይህ ሁኔታ ከሀገር እንድለቅ ያስገድደኛል:: ስለዚህ ሀገር ለቆ መውጣት በሚቻልበት መንገድ ላይ እንድንነጋገር ነው የምፈልገው»

አዶናይ ራሱን ላይታች ሲወዘውዝ ከቆየ በሁዋላ፤

«አሁንስ እየተከታተሉህ ሊሆን አይችልም?» ሲል ጠየቀው::

«ሊሆን ይችላል:: እስካሁን ግን ፍንጭ አላየሁም:: ምናልባት የትም ሊሄድ አይችልም ብለው ሊዘናጉ ይችሉ ይሆናል:: በየእለቱ

ሪፖርት ስለማደርግም ሳይጠረጥሩኝ ይችላሉ።»

«በአስመራ የተመደብክበትን ስራና ሃላፊነትህን ልትነግረኝ ትችላለህ?»

«አስፈላጊ ነው?» አለ አኖሌ።

«በጣም!» አለ አዶናይ «ግዴለህም እመነኝ። ፍላጐትህ ሙሉ በሙሉ እንዲሳካ መተማመን ነው ያለብን። በዝርዝር ንገረኝ የስራ ተግባርህን»

ቀስስተኛ ይመስል የነበረው ሰው ድንገት በራስ የመተማመን፣ የማዘዝ መንፈስ ሲያድርበት አኖሌ አስተዋለ። እና እንደታዘዘው ያብራራ ጀመር፣

«በደህንነት መስሪያ ቤት ውስጥ ከፍተኛ ኤክስፐርት ነኝ። ባብዛኛው ጥናት ነክ ተግባራት ላይ ነው የምሰማራው። ወደ አስመራ የመጣሁት በሻእቢያ ላይ ሳይኮሎጂካል ዎር ፌር ለማካሄድ መነሻ የሚሆን ጥናት ለማቅረብ ሲሆን፤ እዚህ በምቆይባቸው ሶስት ወራት ዶክመንቶችን የማየት፤ ማንኛውንም እስረኛ የማነጋገር፤ ከከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖችና ጄኔራሎች መረጃዎችን የመሰብሰብ ሙሉ ፈቃድ ተሰጥቶኛል። በተረፈ አንድ ረዳት፣ መኪናና፣ ቢሮ አለኝ። ስለከተማው ህዝብ ስሜት ለማጥናት እንዲመቸኝ ሆቴል እንድሰነብት ያቀረብኩትን ሀሳብም ስለተቀበሉት እዚህ ሆቴል ማረፍ ችያለሁ።»

«ስላንተ ይበቃኛል!» አለ አዶናይ «... ከኢትዮጵያ ስለምትወጣበት ሁኔታ እንነጋገር። እንግዲህ አስተማማኝ የሆነና አስተማማኝ ያልሆነ የማምለጫ መንገዶች አሉ። የትኛውን እንደምትመርጥ መቼም ግልፅ ነው። ሆኖም ገንዘቡን አትችለውም። በእጅህ ምን ያህል ብር አለህ?»

አኖሌ የፌዝ ፈገግታ አሳየው።

«ምንም አልያዝክ?»

«አዲስ አበባ ባንክ ጥቂት ገንዘብ አለኝ።»

«ምን ያህል?»

«ሰላሳ ሺህ»

«በተንቀሳቃሽ ሂሳብ ነው?»

«የለም። በደብተር ነው»

አዶናይ ራሱን ግራ ቀኝ ወዘወዘና፣





«የአዲሳቦውን ገንዘብ ተወው። አሁን በእጅህ ያለውን ንገረኝ?»

«ሺህ አምስት መቶ።»

«ይሄማ ትርጉም የለውም።»

«አዝናለሁ። ወዲህ ከመምጣቴ በፊት ከኢትዮጵያ የመውጣት እቅድ አልነበረኝም። በገጠሙኝ ሁኔታዎች ተስፋ መቁረጥ የጀመርኩት አስመራ ከመጣሁ በሁዋላ ነው»

«እንግዲህ የገንዘቡ ነገር ተስፋ የለውም ማለት ነው» ካለ በሁዋላ፣ መልሶ፣

«ሮዛ ልትረዳህ አትችልም? ቤተሰቦችዋ አቅም ያላቸው ይመስለኛል» አለው።

አኖሌ ለምላሽ ፈጠነ፣

«ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ከነርሱ ስባሪ ሳንቲም አልጠይቅም። የትያውቁኛል? ሌላው ቀርቶ ከእንግዲህ መገናኘት እንደሌለብን ነው የሚገባኝ። አደጋ ላይ እንዲወድቁ አልፈልግም።» ካለ በሁዋላ «... ይልቅ ሮዛ 'ከገንዘብ ውጭ ሌላ አማራጭ መኖሩን ነግራኝ ነበር። ምንድነው እሱ?» ሲል ለመስማት ጉዋጉቶ ጠየቀው።

አዶናይ ከንፈሩን በልጠጥ አደረገና ችላ እንደማለት አለ።

«ምንድነው ጉዳዩ?» አለ አኖሌ።

«እሱ እንኩዋ መስዋእትነትን ይጠይቃል» አለው።

«ምን አይነት መስዋእትነት?»

«ሰላሳ በመቶ ያህል አደገኛ ሊሆን ይችላል።»

«... ገሙሉ አደጋ ውስጥ ያለሁ ሰው ነኝኮ» አለ አኖሌ። አያይዞም «ይልቅ ጉዳዩን ንገረኝ» አለ ተቻኩሎ።

«ይሄ እንኩዋ ከኔ ቁጥጥር ውጭ ስለሆነ በቅድሚያ ሌሎች ሰዎችን ማነጋገር አለብኝ።»

«እና ውጤቱን መቼ ትነግረኛለህ?»

«ነገ ልክ በዚህ ሰአት» ብሎ ከተቀመጠበት ተነሳ። ሲሰናበተውም «... ሳትረበሽ ስራህን እንደወትሮው አከናውን። ምንም አይነት ለጥርጣሬ የሚያበቃ ፍንጭ እንዳትተው» ሲል መከረው።

* * *

በነጋታው ብሩ ሶስት ጊዜ በዝግታ ሲቆረቆር አኖሌ ፈጥኖ

ተነስቶ በረገደው:: ትእግስት አጥቶ ነው የቆየው::

በጥቁር ሱፍ ያሸበረቀ መልከ መልካም ጉልማሳ በሩ ላይ ቆሞአል::

«ማንን ፈለጉ?» አለ ተደናግሮት::

«አዶናይ ነኝ» አለው::

የትናንቱ መጥረቢያ መሳይ አፍንጫ የለም:: አኖሌ የገዛ አይኑን ማመን አቃተው:: በደመነፍስ ነበር እንዲገባ በሩን የከፈተለት::

«ሰው ሰራሽ ነበር አፍንጫህ?» ሲል ጠየቀው::

በእምንታ ራሱን ላይ ታች ወዘወዘና ፈገግ አለ::

«ማመን አይቻልም!»

«ምን ይደረግ?» ብሎ በርጋታ አኖሌን ያጤን ጀመር::

«ወደ ጉዳያችን እንግባ!» አለ አኖሌ:: አያይዞም «ውጤቱ ምን ሆነ?» ሲል ጠየቀው::

«ተስፋ አለው» የሚል ነበር አዶናይ የሰጠው ምላሽ::

«እውነት?»

አኖሌ ጉዋጉዋ::

«እድለኛ ነህ እንዲያውም:: ዛሬ ቀኑን ሙሉ ባንተ ጉዳይ ላይ ስነጋገር ነው የዋልኩት:: አጋጣሚ ሁኔታውን ከልምድ አንፃር ስናየው ያለችግር የማምለጥ እድልህ ወደ ዘጠና በመቶ አሻቅቦአል:: ያለምንም ጥርጣሬ ከሃያ ቀን በሁዋላ ቦን ወይንም ጄኔቭ ትገባለህ::»

«አላምንም!» አለ ህልም እየመሰለው::

«አትጠራጠር:: ጥቂት ድፍረት ብቻ ነው የሚያስፈልግህ»

«መልካም! የሚጠበቅብኝን ጉዳይ ልወቀዋ!»

«በቅድሚያ ጥቂት ጥያቄዎችን ላቅርብልህ» አለ አዶናይ:: አያይዞም ቀጠለ፣

«ትናንት ስለ ስራህ ስትገልፅልኝ እስረኞችን ማነጋገር ስለመቻልህ አንስተህ ነበር ልበል?»

«አዎን» ሲል መለሰ አኖሌ::

«ማንኛውም እስርቤት እንደልብ የመግባት ፈቃድ አለህ?»





«አዎን አለኝ» አለ፣ ምን ሊጠይቀው እንደፈለገ እያውጠነጠነ፤

«በየትኛውም ሰአት?»

«እስካሁን በስራ ሰአት ብቻ ነው የምገባው»

«ማምሻውን የመግባት ፈቃድ ማግኘት ትችላለህ?»

«በቂ ምክንያት ካለኝ ማስፈቀድ የሚገድ አይሆንም::»

«እስካሁን ከእስረኞች መካከል ማን ማንን አነጋግረሀል?»

«ብዙ ናቸው:: ወታደሮች፣ መኮንኖች፣ የሻእቢያ ሰላዮች፣»

«ከሻእቢያ ሰላዮች ማንን አነጋገርክ?»

«አብርሀ ሀለጎ ይባላል::»

«እንግዲህ ቦን ወይም ጄኔቭ ድረስ ልንሸኝህ የምንችለው አብርሀ ሀለጎ የተባለው እስረኛ እንዲያመልጥ ጥቂት እርዳታ ካደረግህ ነው:: ኦፕሬሽኑ በቀላሉ ይፈፀማል:: አንተም በቀላሉ ይህን ሀገር ትለቃለህ:: ይህን ተግባር ለፈፀምክበት ሻእቢያ ከአስመራ ውስጥ እንዲትም ልምጭ ሳያርፍብህ አንጠልጥሎ ያወጣሀል! ቅንጣት አትጠራጠር:: እንፈፅመዋለን! መስዋእትነትን ጭምር እንከፍላለን - ኦፕሬሽኑ እንዲሳካ:: ላንተ ብለን ብቻ ሳይሆን ድርጅቱ የሚፈፅማት እያንዳንድዋ ተግባር ከታማኝነቱ፣ ከህዝባዊነቱ፣ ከብቃቱም ጋር ስለሚጣበቅ የማንፈፅመውን አንናገርም:: የተናገርነውን ደግሞ እንፈፅመዋለን»

አኖሌ ብቸር አለበት:: አይኖቹን እንደ እንቁራሪት አፍጥጦ ነበር አዶናይን የሚያስተውለው፤

«አንተ የሻእቢያ ሰው ነህ?»

«ነኝ አዎ!»

ግራ ተጋባ:: እንዴት ማሰብ እንዳለበት አላወቀም:: እንደ ጣራውን፣ መልሶ መሬቱን፣ ደሞ ወደ አዶናይ አፈጠጠ፣

«ለመሆኑ» አለ አኖሌ «... ባቀረብከው ጥያቄ ባልስማማ ምን ታደርጋለህ?» ሲል ጠየቀው::

«ለፖሊስ ጠቁመህ እንዳታሲዘኝ ዛሬውኑ አገር ጥዬ እጠፋለሁ» አለው አዶናይ ስሜቱ ባልታወቀ ሁኔታ አኖሌን እየገረመመ::

«አስመራ ውስጥ የሻእቢያ አባላት በብዛት አሉ ማለት ነው?»

«አራት መቶ ሺህ ያህል!» አለ አዶናይ በፈገግታ እንደተዋጠ::

ፊገግታ ይታይበት እንጂ ውስጡ ግን በጭንቀት ሲፈነዳ ምንም አልቀረውም፣ አያይዘም፣ «ህዝቡ ሁሉ ደጋፊያችን ነው። እያንዳንዱ ዜጋ ተባባሪያችን በመሆኑ ነው በሙሉ ልብ እንደምታመልጥ የምነግርህ»

አኖሌ በተመስጦ ማሰብ ጀመረ። አደገኛ ወጥመድ ውስጥ መግባቱን አመነ። ግን ምን የተሻለ ምርጫ አለኝ ሲል ራሱን ጠየቀ። ስለ ሳሙኤል አሰበ? ያንን ወረቀት ከመከላከያ እንዴት አገኘ? የሮዛ የአይን መነፅርና የአንገት ልብስ? የሮዛ ክብረት የጠነከረ መንፈስ ... የአዶናይ አፍንጫ ... የሮዛ እናት ፀሎት ... በሚስጢር ቁልፍ የተከረቸሙት ከተማ ... እንደ ባቢሎን ለመፍረስ የቀረበች ሀገር ... እንደ ናቡከደናሶር ሳር መጋጥ የሚገባቸው መሪዎች የዘገሰባት ሀገር ... በፍርሀት የተከበበ ትውልድ ...

አኖሌ ለመሞት ወይም ጨርሶ ከዚህ የጭንቀት ሀገር እጅግ ለመራቅ ተመኘ ...

«ምን ይመስልሀል ታዲያ?» የሚለው የአዶናይ ጥያቄ አባነነው።

«መልካም ነዋ! ዝርዝሩን እንነጋገር!»

አዶናይ ያመቀውን የጭንቀት አየር ለቀቀው። በደስታ መጮህ አምሮት ነበር ...

* * *

«ሰንበት ደረሰኮ ጌታዬ። ጠቦት ቢጤ አላማሮትም? አዋጥተን እንረድና ፍርምባውን ለይቼ ለርሶ ምሳ እንዲዘጋጅ አደርጋለሁ። ስራ ብቻ ደሞ ሰው ይገላል። ነገ ሰንበት ነው። ጮማ የሆነ አሳብ አይመስሎትም?»

«ጠቦት ዋጋው ስንት ነው?»

«መቶ ሀምሳ ይገኛል። ያስጠስጠ።»

«እና ሰባ አምስት ታዋጣለህ?»

«ይመኑኝ።»

«ፍርምባውን ቃል ገብተሃል!» አለው እየሳቀ።

«ይመኑኝ እያልኩዎ!»

አይኖቹ በደስታ ስሜት ደመቁ።

«በል ወደ ስራ እንግባ ...»

«የት ነን ዛሬ»





«ወንበዴውን ነው ማነጋገር የምፈልገው»

«ድጋሚ!? ጋግርታም ነው ... ይመኑኝ ዛሬ ይስድቦታል። መሞት ስለሚፈልግ በጣም ያሳደባል። ለነገሩ ከድብደባው ሞት ይሻለው ነበር።»

«ግዴለም እንሂድ!» ብሎ ጃኬቱን ለብሶ ወጣ።

ጮማዬ ዛሬም እንደወትሮው የባጥ የቆጡን እየቀባጠረ ነበር ማርያም ግምቢ ያደረሰው። በር ጠባቂ ፖሊሶቹ የአኖሌን የፈቃድ ወረቀት አገላብጠው ከመረመሩ በሁዋላ ሁለቱንም ፈትሸው አስገቡአቸው። ግቢው ሰፊ ነው። ከጥበቃ በሩ ሀምሳ ሜትር ርቀት ላይ ካለው ሺላ ከዛፉ በላይ አደገኛ እስረኞች ታጉረዋል። አብዛኞቹ በሻእቢያ አባልነት ወይም ሰላይነት ተጠርጥረው የታሰሩ ይሁኑ እንጂ ከእስረኞቹ መካከል እጅ ከፍንጅ የተያዘ፣ እስያም ያመነ የለም - ከአብርሃ ሀሎት በቀር።

በርግጥም ከእስረኞቹ መሀል የአብርሀ ሀሎትን ያህል ተፈላጊ ሰው ሳይኖር ይችላል። አብርሃ ሀሎት ከመንግስት ጋር ቢተባበር የሻእቢያ የሰላላ መዋቅር ብትንትኑ ሊወጣ እንደሚችል የደህንነት ሹማምንቱ አልተጠራጠሩም። እስካሁን ግን ድብደባና ማስፈራሪያ፣ አለያም ማባበያ ሊበግረው አልቻለም። የደህንነቱ ባለስልጣኖች ወደ ከፍተኛ የማሰቃያ ስልቶች ለመሸጋገር በተዘጋጁበት ጊዜም ነበር አኖሌ እስመራ የገባው። አኖሌ የስነ ልቦና ሳይንስ ምሁር በመሆኑና በቀጥታ ከፕሬዝዳንቱ ቢሮ መላኩ የደህንነት ሹማምንቱን ስሜት አልሰረቀውም። 'እስኪ ይሞክረው እናየዋለን' በሚል ስሜት ነው ችላ ብለው አብርሃ ሀሎትን ለጊዜው የለቀቁለት።

በማርያም ግምቢ ማጎሪያ ግቢያ በር ላይ በየእለቱ ሁለት ፖሊሶች ይቆማሉ። አብርሀ ሀሎት ከታሰረበት ልዩ ክፍል ደጃፍ ላይም አንድ ወታደራዊ ፖሊስ ዘወትር በንቃት ይጠብቃል። በረጅም ግንብ ከታጠረው ግቢ፣ በየማእዘኑ ላይ የጥበቃ ማማዎች ከነባውዛቸው አውቶማቲክ መትረየስ ደቅነው ቀንና ሌሊት በንቃት ይጠብቃሉ። ወደዚህ ማጎሪያ በልዩ ትእዛዝ ካልሆነ በቀር ማንም ጠያቂም ሆነ ባለጉዳይ ዝር ሲል አይፈቀድለትም።

አኖሌ ወደውስጥ ዘልቆ እንደገባ የልዩ ወህኒው አዛዥ ሙሉ መቶ አለቃ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ነበር የተቀበለው፣

«ተስፋ ሳትቆርጥ ተመለስክ እንዴ?»

«ግዴለህም - ይሸነፋል» አለ በጉራ።

«የሚሆንልህ አይመስለኝም። ጊንጥ ነው።»

«ግደሉስም አንዳንድ ዘዴዎችን እንጠቀማለን።»

«በል ልፋ እንግዲህ ... ሰውዬው እንደሁ የተረገመ ነው። ከፈሱ የተጣላ ሰይጣን። በስቴፕለር ቅንድብና ቅንድቡን አጣብቀን አስቃየነው! ገረፍነው! ተሰተልነው! የተንኮሉ ብዛት የስቃይ ድምፅ እንኳዋ አያሰማም። ኰሎኔል ዝናው ለመጨረሻ ጊዜ ሲያናግሩት 'አልገድልህም! ስጋህን ከትፌ እበላዋለሁ' ሲሉ ዛቱበት። ወዲያ ቢገደል በተሻለ» እያለ ነበር ወደታሰረበት ክፍል የሸኘው።

እኖሌ ከልዩ ጠባቂው ፖሊስ ጋር አብርሀ ፀሎት ብቻውን ወደተዘጋበት ክፍል እንደገባ «የእግሩና እጁ ሰንሰለት ይፈታ!» ሲል አዘዘ። ፖሊሱ ከያዘው ከምር ቁልፍ መርጦ ከፈተና በእስረኛው እግሮችና እጆች ላይ ያሉትን ሰንሰሎቶች አወለቃቸው። አብርሃ ፀሎት ሰውነቱ ቢዳከምም አይኖቹ ንቁ ናቸው። በእሳሪዎቹ ላይ ንቀት ይታይበታል። እኖሌ በጀርባ በኩል ያሉት መስኮቶች እንዲከፋፈቱ ፖሊሱን አዘዘው። እንደታዘዘው ፈፀመ!

«እንግዲህ ብቻዬን ልቆይ!» አለ እኖሌ።

ፖሊስ «መልካም» ብሎ በሩን መለስ አድርጐ ወጣ።

አብርሃ ፀሎት ፍራሹ ላይ እግሩን አኰራምቶ ተቀምጦ እኖሌን በጥንቃቄ ያስተውለዋል!

ሙግዬ በሩን ከፍቶ ብቅ አለ።

«ዝጋውና ደጅ ጠብቀኝ» ሲል አዘዘው።

«አብሬም ልሁን?»

«እዚያው ቆይ ደህና ...»

ሙግዬ በሩን ቀስ አድርጐ ዘግቶ ወጣ። እኖሌ ቁራጭ ወረቀትና ብእር ካወጣ በሁዋላ!

«እዚህ ክፍል ድምፅ መቀጃ መሳሪያ የተገጠመ ይመስልሃል?» ሲል ፅፎ ወረቀቱን ወደ አብርሃ አቅርቦ አሳየው።

አብርሃ ፀሎት በመደነቅ ወረቀቱን ተቀብሎ በችኮላ ካነበበ በሁዋላ ወደ እኖሌ ቀና ብሎ! መልሶ አቀረቀረ።

እኖሌ መልስ ፈልጐ ነበር። አብርሃ ፀሎት ግን በመጠራጠር እንደ ወረቀቱን መልሶ እኖሌን ያስተውል ጀመር።

እኖሌ የክፍሉን ዙሪያ ገባ ያስተውል ጀመር። ጥጋ ጥጉን ጭምር ፈታተሸ። ምንም አጠራጣሪ መሳሪያ አልነበረም። መርፌ መሰል የድምፅ መቅጃ መሳሪያዎች በጣራው ላይ ካልተገጠሙ በቀር





ሌላ ድምፅ መቅጃ መሳሪያ ሲኖር እንደማይችል አመነ። የኢትዮጵያ የስለላ ቴክኖሎጂ ያን ያህል እንደማይራቀቅ ደግሞ እኖሌ ይገምታል። እና ወደ ተግባሩ ዘለቀ።

«ዘጠና ዘጠኝ አባላሁ» አለው ዝቅ ባለ ድምፅ።

የአብርሃ ፀሎት አይኖች ሲደምቁና ሲደናገጥ አየ። የደረቁ ከንፈሮቹም ተንቃነቁ። እና እንደምንም ብሎ!

«በቁጥር የሚጠራ ሰው ሰምቼ አላውቅም» የሚል ምላሽ ሰጠው።

«አንተ ማነህና! ለሰባት አመታት ዘጠና ዘጠኝ አልነበርከም?»

አብርሃ ፀሎት በመጠራጠር እኖሌ ላይ አፈጠጠ። ይህን ኮድ የሚያውቀው አንድ ሰው ብቻ መሆኑን አብርሃ ያውቃል። ያ ሰው ተይዞ ቢሆን እንኳዋ ይህን ሲናገር አይችልም።

ሲያምን ፈለገ። ሙሉ ልቡን መስጠት ደሞ ፈራ። የማረጋገጫ ጥያቄዎችን ለመወርወር ተገደደ!

«ዘጠና ዘጠኝ ምን ማለት ነው?»

«ቦሎኛ የሚመረት ስእት» አለ እኖሌ ፈገግ ብሎ።

አብርሀ ፀሎት ረጅም አየር ካስወጣ በሁዋላ!

«አማራ ነህ?» ሲል ጠየቀው።

«ኦሮሞ ነኝ።»

«ከማን ጋር ነበር የተገናኘኸው?»

«አዶናይ መሆኑን ከገለፀልኝ ሰው ጋር»

«የኰድ ቁጥሩን ነግሮሀል?»

«ቁጥሩን አልነገረኝም። ሁለት ቃላት ብቻ ነው የነገረኝ»

«ምን አለህ?»

እኖሌ እንደማሰብ አለ። ቃላቶቹን የረሳቸው መስሎት ነበር። አስታወሰ!

«ነቢያት - ቦቼፊሊያ» አለ።

አብርሃ ፀሎት አይኖቹን በሰፊው ሲበለጥጥ አስተዋለው። ወዲያው ስሜቱን ላለማሳወቅ እየጣረ!

«ለኔ ምን እንድትነግረኝ ነው የፈለገው?» አለ ጨርሶ ግራ

የመጋባት ስሜት ጭምር እየታየበት።

«እንድታመልጥ ዝግጅት ጀምረናል። ተስፋ የሚያሳድር እቅድ ነው።» ብሎ የታሰበውን በዝርዝር ያብራራለት ጀመረ። አብርሀ ፀሎት የአኖሌን ገለፃ በጥንቃቄ ሲያዳምጥ ከቆየ በሁዋላ በመስማማት ራሱን ነቅንቆ አንዳንድ ማስተካከያዎችን አከለበት። በመጨረሻ፣

«ለመሆኑ በዚህ ኦፕሬሽን ላይ ያንተ ፍላጐት ምንድነው?» ሲል በርጋታ ጠየቀው።

«መንግስት ሲተናኮለኝ ጀምሮአል። ቀድሜ መሸሽ እፈልጋለሁ።»

«ልንያዝ፣ ልንገደል እንደምንችል አውቀሃል?»

«ድብብቆሽ እየተጫወትኩ እንዳልሆነ ይገባኛል! ግን አማራጮቹ ጠበብ ያሉ ናቸው። እግሬ አዲስ አበባን ከረገጠ በሁዋላ መንፈራገጥም አይቻል ይሆናል። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ እድልን መማፀን ያስፈልግ ይሆናል»

«እቅዱ እንኳ ምንም አይወጣለትም። ሆኖም ሁልጊዜ በታቀደው መሰረት ማከናወን አያጋጥምም። እምነህበት ግባ። በዚያ መንፈስ ከገባህ የተሻለ ውጤት እንደማትፀፀትም አረጋግጥ! በዚያ መንፈስ ከገባህ የተሻለ ውጤት ሊመጣ ይችላል። ባመነታህባት ደቂቃ ግን እንደምትገደል እወቅ!»

አኖሌ «ገብቼበታለሁ! ወደሁዋላ አልመለስም» ሲል አረጋገጠለት። በዚህ ጊዜ አብርሀ ፀሎት ሊተኮርበት የሚገባ በሚላቸው ነጥቦች ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ሰጠው። አኖሌም የራሱን አስተያየት እያከለ በእቅዱ ላይ በጥንቃቄ ደግመው ደጋግመው ተወያዩበት።

* * *

«ይመኑኝ ፍርምባውን ለብቻ አሰራልዎታለሁ!» አለ ጮማዩ ማርያም ግምቢን ለቀው እንደወጡ።

«ኰሎኔል ዝናውን ማግኘት ስላለብኝ ፈጠን ብለህ ንዳ!» አለው ሰአቱን በችኰላ እያየ።

«አ ... ኰሎኔል ሸንኩርት!» ብሎ ሳቀ ጮማዩ።

«የምን ሸንኩርት?» አለ ገርሞት።

«ሸንኩርት አያቁም? ነግሬውት አልነበር እንዴ?»

«የወታደሮች ቋንቋ ረቂቅ ነው ...» ብሎ አፌዘበት።





«እዚህ አገር ሸንኩርት ነው የሚባሉት ትንንሶቹ ሴቶች» ካለ በሁዋላ ከት ብሎ ሳቀ። አኖሌ ገረመው።

«ታዲያ ኰሎኔሉን ለምንድነው ሸንኩርት የምትለው?»

«ይወዷሉ! ሸንኩርት ካላገኙ እንደ እብደት ነው የሚያደርጋቸው። መሳደብ መቆጣት ነው። አንዳንዴማ ያስገዋራቸዋል። ሸንኩርት ያጡ ቀን ያንዱን አስረኛ ሞተር ያጠፋሉ።»

«የምን ሞተር?»

«ልብ ነዋ። ስለ አባባል ምንም አያቁም ልበል? እዚህ አገር ሰው ሲሞት 'ሞተር አጠፋ' ነው የምንለው። ታዲያ ኰሎኔል እንዳይቆጡ ሸንኩርት እንፈልጋለን። አንዴ አይረሳኝም ሸንኩርት ሳያገኙ ሰነበቱና ንዴታቸው ጡሜቦ የሚባል ተራ ወታደር ላይ አረፈ። ልጁ እንኳዋ ምንም አላጠፋም ነበር። ግፍ ነው! ጡረታ ፈረምክ ብለው ነው የወሰኑበት። እስካሁን አይኔ ላይ አለ - ያ ምስኪን ...»

«የምን ጡረታ ነው የሚፈርመው? ተራ ወታደር ነው አላልከም?»

«ጡረታ መፈረም አያቁም? ወረቀት ላይ መስሎት እንዴ? በጓደኛው እግር ላይ ነው የፈረመለት»

«ምኑን?»

«በጥይት ነዋ! እግሩን ቀለበሉት። ተዋውለው ነበር። ጉዋደኛው ግን አውቆ መታኝ ብሎ እሪ አለ። ጡሜቦ ለጓደኛው ውለታ በሰራ ሸቤ ገባ። ኰሎኔል ታዲያ ሸንኩርት ሳያገኙ ሰንብተው ነበርና ቁጣ ቁጣ ሲላቸው እኔን ጠርተው የዚያን ከይሲ ሞተር አጥፋ ሲሉ አዘዙኝ። ወስጄ ኩዋድሮውን ስነቅልበት አለቀሰ። እንጀቴን በላኝ። ደረቱ ላይ ስፈርምለት ሽብረክ አለና እንደ ክረምት አባብ ዝርግት ...»

አኖሌ ዝም አለ። ወሬው ቀፈፈው። ጮማዩ ቀጠለ ...

«የምር ሸንኩርት ቀምሰው አያውቁም?»

መልስ ስላልሰጠው ቀጠለ፣ ... «እኛ መችም ግፍ ነው የሰራነው። ቀለድንባቸው ከረዶቹን። እነሱም ጊንጥ ናቸው። አንድ ጊዜ አንዱ ሃምሳ አለቃ ሸንኩርት ይዞ ያድራል። በራስዋ ቤት። ሌሊት ተነስታ መፃፊያውን በቢላ ቆርጣው ጠፋች። እሱ ጠጥቶ እንሰሳ ሆኖ ነበር።»

«እጁን?» አለ አኖሌ ግራ ገብቶት፡

«እረ በጠቅላላው! - መፃፊያ እጅ ሆነ እንዴ ደሞ? ተክለወልድን ነውንጂ:: የወንድ ነገርዬውን ..»

«አሃ!» አለ አኖሌ::

«ታዲያ ወታደሩ ሁሉ ፈራ:: ማደር ተወ:: ፃፍ ፃፍ አድርጐ እዚያው ሞተርዋን አጥፍቶላት ይመጣ ጀመር:: አዬ ኤርትራ! ሞት - ፍቅር - ቁርጥ - ግፍ ሁሉን አየን:: ይገርሞታል አንዳንድ ቀን ወደፊት የሚበቅሉት ዛፎች የሰው ልጅ ጣትና አፍንጫ ያበቅሉ ይሆን? ብዬ አስባለሁ:: መሬቱ እኮ የሰው ደም ጠግቦአል:: የኤርትራ እናቶችም ታዲያ እልህ የያዛቸው ነው የሚመስሉት:: ላይ በላይ ይወልዳሉ:: የሞተውን ያህል ተክተው ያድራሉ ...»

አኖሌ በትእዝብት ያጤነው ጀመር:: በመስማቱ ብቻ አፈረ:: ጮማዬ ግን የየእለት ወሬው ስለሆነ ያለመጨነቅ ነበር የሚያወጋው:: ስለ ኰሎኔል ዝናውም መተረኩን ቀጠለ ...

«... እሳቸውኮ ሽንኩርት ሲያዩ ፍርምባ ያዩ ያህል ፊታቸው ይፈካል:: ለነገሩ ከአስመራ ወጣ ሲባል ያለው ውበት ያጉዋጉዋል:: ቅመም ናቸው:: ለዚሁ የተፈጠሩ ነው የሚመስሉት:: የአዋሽ ዳር ሽንኩርት ናቸው - ቀይ የሀበሻ ሽንኩርት:: በአዋሽ ዳር ቀይ ሽንኩርት የተጠበሰ የበግ ስጋ ቀምሰው ያውቃሉ?»

አኖሌ መስማት አቁሞ ነበር::

ኰሎኔል ዝናው ቢሮ እንደደረሱ በችኰላ የመኪናውን በር ከፍቶ ወደ ደህንነት ሹሙ ቢሮ ተጣደፈ::

አኖሌ አብርሀ ፀሎትን አስመልክቶ ለኰሎኔል ዝናው ሰፊ ማብራሪያ ይሰጥ ጀመር:: ሲናገር በስሜት እየተወራጨ ነበር:: 'አብርሃ ፀሎትን ማንበርከክ ችዬአለሁ::' የሚለውን ዜና በወኔ ነበር የገለፀው:: 'የራሴ ጥረት ብቻ ነው ማለት ደግሞ አይቻልም' የሚል ማካካሻም አከለ:: ቀደም ሲል በተካሄደው ምርመራ አብርሀ ፀሎት እንደተዳከመ አብራራ:: 'አሁን ግን ድል ተገኝቶአል' ሲል ደነፋ አኖሌ:: 'ዛሬ የተጠቀምኩበትን የማግባባት ስልት ከቀጠልንበት የአስመራን የስለላ መዋቅር ማግኘት ብቻ ሳይሆን የሳይኰሎጂካል ምር ፌር በማካሄዱ ሂደት ላይ አብይ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አያጠራጥርም' ሲል ለደህንነት ሹሙ አረጋገጠለት:: የደህንነት ሹሙ ሲጋራውን በዝግታ እየማገ የአኖሌን ገለፃ አዳምጦ ሲያበቃ፣

«ማመን የማይቻል ተአምር ነው:: በርግጥ ከአስር ቀን በፊት ብልቱን እንደማስቆርጥ ነግሬው ነበር:: ፈርቶ መሆን አለበት:: ይህ ጉረኛ:: ደሞ እፈፅመው ነበር:: ከስሩ ልገርዘው ወስኜ ነበር ...» ብሎ ከልቡ በሳቅ ተንከተከተ::





እየሳቀም ይቀልድ ጀመር፣

«ብልቱ እንደሚቆረጥ ሲነገረው ወኔው ተሰለበ! ገምቼ ነበር:: ማንም ወንድ ቢሆን በቁሙ ወንድነቱን ከሚያጣ ሞትን ይመርጣል:: አትጠራጠር አኖሌ፣ ውጤት የተገኘው በዚህ ምክንያት ነው:: ደሞ ይገርምሀል፤ ይሄን ስልት እንደ ማስቃያ ተጠቅመንበት አናውቅም ነበር:: ያን ቀን ግን እንደለመደው ሲሰድበኝ ድንገት ነው አፌ ላይ የመጣብኝ:: 'ብልትህን ነው የማስጐምደው' አልኩት:: ድንጋጤ ገፅታውን ሲያለብሰው አይቻለሁ:: ይህን ያህል ፍርሀት ውስጥ የሚያስገባው መስሎ ግን አልተሰማኝም ነበር:: አጀብ ነው! ድንቅ ነው!»

ኰሎኔሉ ወደ ዝና ሽሚያ መግባቱን አኖሌ ተረዳ:: እና እቅዱ እንዳይበላሽበት ሰጋ:: ፈጥኖ የማስተካከያ ርምጃ ወሰደ፤

«ሙሉ በሙሉ ፈቃደኛ አልሆነም ኰሎኔል:: ተስፋ ነው የሰጠኝ:: የእስር ቤት አኑዋኑዋሩ እንደሚሻሻልለት ቃል ገብቼለታለሁ:: የሚያውቀውን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ በወረቀት እንደሚያሳፍር እሱም ቃል ገብቶልኛል:: አንተ በተለይ አምርረህ እንደምትጠላው ነው የሚሰማው:: ስለዚህ አንድ ጊዜ፤ ነገም ሊሆን ይችላል፤ አብረን ብቅ ብለን እናጫውተው:: እንዳይቀብጥ ከዚያ ማውጣት ተገቢ አይደለም:: ከነገ ጀምሮ ግን አኑዋኑዋሩ ላይ ማሻሻያ ይደረግለት»

«እንዴት ያለ ማሻሻያ?» አለ ኰሎኔሉ::

«ሻል ያለ ምግብ ...»

«ይቻላል::»

«ህክምና::»

«እሱም ቀላል ነው::»

«ጠዋት ፀሀይ እንዲሞቅ ማድረግ፤ ሰንሰለቶቹ ቢወልቁለት፤ ሬድዮ ደግሞ ቢገባለት::»

«ይህም ቢሆን አያስቸግርም::»

«ለኔ ለስራዬ እንዲረዳኝ ደግሞ መጠጥ በየእለቱ እንዲገባለት ቢደረግ:: ህይወት እንድታጉዋጉዋው ሱሰኛ ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው:: ሰዎችን እንዳሻን ልናሽከረክራቸው የምንችለው በቀላሉ ሊያገኙት በማይችሉት ሱስ ሲጠመዱ ብቻ ነው:: ለልማዳቸው ሲሉ በቀላሉ ይጐተታሉ:: ጠርሙስ ዊስኪ ከነገ ጀምሮ እንዲገባለት ቢደረግ»

«ሀሳቡ ጥሩ ነው። ለዊስኪ ግን በጀት የለንም።»

«ምን ይሻላል ታዲያ ኰሎኔል? ለሶስት ጠርሙስ ዊስኪ ብዬ ፕሬዚዳንቱ ቢሮ መደወል አለብኝ?»

ኰሎኔሉ አመነታ፣

«መልካም እስኪ! ጠቃሚ መስሎ ከታየህ አንዳንድ ዘዴዎችን እንጠቀማለን። ግን አንዳንድ ወረቀቶች ላይ የምትፈርም ከሆነ ነው። ለኛም እንዲተርፍ ማድረግ ይቻላል» ብሎ ኰሌኔሉ በረጅሙ ሳቀ!

«ግዴለም። ያሻህ ሰነድ ላይ ፊርማዬን አኖራለሁ። እኔ ውጤቱ ነው እየታየኝ ያለው።»

አኖሌ ጉዳዩን አጠናቅቄያለሁ ለማለት የማስታወሻ ደብተሩን አጠፈ።

«ዛሬ ማምሻውን ልጋብዝህ?» አለ ኰሎኔሉ።

«ግራሲ!»

- 3 -

ይህ በሆነ በሶስተኛው ቀን፣ በእለተ አርብ፣ ለአይን ያዝ ባደረገበት ምሽት ሁለት ሰዎችን የያዘች አንዲት ሰማያዊ ፊያት 124 መኪና ማርያም ግምቢ ማጐሪያ ደርሳ ቆመች።

የጥበቃ ፖሊሱ በሩን ከመከፈቱ በፊት ብቅ ብሎ «ማን ልበል?» የሚል ድምፅ አሰማ።

አኖሌ ነበር ቀድሞ ምላሽ የሰጠው፣

«እኛ ነን። አኖሌ ዋቆ እባላለሁ»

«መግባት ክልክል ነው!»

እሁንም አኖሌ እድሉን ለኰሎኔሉ አልሰጠም። ለምላሽ ተሽቀዳደመ፣

«ቀዋሚ የመግቢያ ፈቃድ እንዳለኝ አልተነገራችሁም እንዴ?» ካለ በሁዋላ ወደ ኰሎኔሉ ዞሮ «... ፈቃድ የተሰጠኝ ከነረዳቱ ነው። ዘወትር ግን አዲስ ይሆናሉ። ማታ መግባት ክልክል ነው ይላሉ። ሲያሻቸው ደግሞ ረዳቴን ይከለክሉታል። እኔ ለግቢውም ሆነ ለሀገሪቱ አዲስ ነኝ። ያለረዳት ልንቀሳቀስ ከቶ አልችልም።»

በዚህ መካከል የጥበቃ ፖሊሱ ኰሎኔል ዝናውን በማየቱ እንደ ጥይት ተተኩሶ የማጐሪያውን ግቢ በር ወለል አድርጐ ከፈተው።





ኰሎኔሉ መኪናውን ቦታ አስይዞ ነቃመ በሁዋላ! ፖሊሱን በቁጣ ጠርቶ ያምባርቅበት ያዘ፣

«ሞተርህ እንዲጠፋ ትፈልጋለህ? አንተ የቀበሮ ጭራ!»

«ከስራ ሰአት ውጭ እስረኛን ማነጋገር በጥብቅ በመከልከሉ ነው ጉዋድ ኰሎኔል። እናንተ መሆናችሁን አላወቅሁም ነበር ...»

«መመሪያ ማክበር ጥሩ ነው» አለ ኰሎኔሉ «... ይሄ የስራ ባልደረባችን ግን ባሻው ሰአት ቢመጣ ትብብር ይደረግለት። አኖሌ ዋቆ ይባላል። ይሄን መመሪያ ለተረኞች ጭምር አስተላልፍ። ረዳቱ ጭምር እንዳይከለከል። አዳምጠሀል!?»

ተያይዘው ወደ አብርሃ ፀሎት የእስር ክፍል አመሩ። በመንገዳቸው ላይ አኖሌ ያለማቋረጥ ይለፈልፍ ነበር፣

«... ብዙ ለውጥ እምጥቶአል ኰሎኔል። ዋስትና ነው የሚፈልገው። የልባችንን እንዳቀረብነው ማረጋገጥ ይፈልጋል። በተለይ አንተን በጣም ይጠራጠርሃል። እንድገደል ከፍተኛ ግፊት የሚያደርገው ኰሎኔል ዝናው ነው ብሎ ያምናል። ዛሬ እንደተራ ጉዋደኛ አብረነው ዊስኪ ጠጥተን አጫውተነው ብቻ እንመለስ። ለአንድ ሳምንት ያህል ማታ ማታ መጠጣት መልመድ አለበት። ያኔ ህይወት ትጣፍጠዋለች። የመኖርን ጣእም ያስታውሳል። ልቡ ይሸነፋል። ይሄ በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በህዝብ ላይም የሚሰራ ስልት ነው። በቅርቡ በራሳቸው በኰሎኔል መንግስቱ ታዝዤ አንድ ጥናት አጥንቼ ነበር። 'የኤርትራን ህዝብ ልብ እንዴት ማግኘት ይቻላል?' የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሰፊ ጥናት አካሂደናል። እኔ ያቀረብኩት ሀሳብ ኤርትራ ላይ የልማት ስራ መጀመር አለበት የሚል ነው። ለአብነት አከለ ጉዛይ ላይ አንድ ትልቅ ሆስፒታል መስራት መጀመር። ህዝቡ ይህን ሲያይ ተስፋ ያሳድራል። የሻእቢያ ወንበዴዎች አላማቸው ጥፋት ስለሆነ ያንን ማፍረሳቸው አይቀርም። መንግስት እንደገና ግንባታውን ይጀምር። ለአይሮፕላን ጥይት መግዣ የሚውለውን ግንባታ ላይ ማዋል። ህዝቡ እየተለወጠ ይመጣል። የጂት ቦምብ ከህዝብ አራርቆናል። የሻእቢያን ወንበዴዎች አይሮፕላን አያገኛቸውም። ህዝቡ ላይ ነው እሳቱ ሁሉ የሚያርፈው። ህዝቡ ላይ አንድ ፈንጂ በወደቀ ቁጥር መቶ ሺህ ኤርትራዊ እናጣለን። የአይሮፕላንና የቦንቡን ወጪ ለኤርትራውያን ማህበራዊ ችግሮች መፍቻ ማዋል አለብን። ያኔ ሻእቢያ ከህዝቡ ይነጠላል። መንግስት የሰራውን ሆስፒታል ሻእቢያ ማፍረሉ በሰፊው ይነዛል። ይሄ ህዝቡን ያስቆጣዋል። ያኔ የወንበዴው ቡድን ከህዝቡ እየተነጠለ ይሄዳል ...»

ኰሎኔሉ ግን በተቃውሞ ራሱን ግራ ቀኝ ወዘወዘ፣

«የኤርትራን ህዝብ አንተ አታውቀውም። ትእቢታቸውና ንቀታቸው። መሀይሞች - ጥሬ ስጋ የሚበሉ - ቅንዝረኞች - እያሉ ነውኮ የሚሰድቡን። እንዲህ ሲሉ ታዲያ እልህ ይይዝሀል። ሆስፒታል ቢሰሩላቸውም ንቀታቸው ይቀጥላል» ካለ በሁዋላ «ግን ጉዋድ ፕሬዝዳንት ያቀረብከውን ሀሳብ ተቀብለውታል?» ሲል ጠየቀው።

«በሚገባ! ጥናቱን ካነበቡት በሁዋላ ጠርተው አቅፈው ሳሙኝ! 'ከሁሉም አዲስ አሳብ ለመሰንዘር ያለህን ድፍረት አደንቃለሁ' አሉኝ። እኔ ጀርመን ነው የኖርኩት። ግዴለኝም። በግልፅ ያሻኝን መናገር ለምጄያለሁ።»

«ለነገሩኮ ሀሳቡ ጥሩ ነው። ግን ህዝቡ እባብ ነው።»

የአብርሃ ፀሎትን ክፍል የሚጠብቀው ፖሊስ ኰሎኔል ዝናውን በማየቱ መሽቆጥቆጥ ጀመረ። የአብርሀ ፀሎትን ክፍልም በችኰላ ከፈተላቸው፤

አኖሌ ወደ ኰሎኔሉ ጆሮ ጠጋ አለ፤

«ጥበቃው ከኛ ጋር ይጠጣ!» ሲል ሀሳብ አቀረበ።

«ለምን?»

«ለጥንቃቄ አጠገባችን ቢሆን አይከፋም!»

ኰሎኔሉ ሳቀ፤

«እኛ እኮ ከማንደ ተምረናል። አይኑ ላይ አሳይተን ቆለጡን ነው የምናፈነዳለት። ላንተ ግን ...» ብሎ ሳቀበትና በሀሳቡ ተስማማ። እናም ሶስቱም ዊስኪ ጠርሙሳቸውን ከብርጭቆዎች ጋር ይዘው አብርሃ ፀሎት ክፍል ገቡ።





# እንደምን አደርሽ

# ኖራህ!?

## ምእራፍ ስምንት

### - 1 -

**በነጋታው ቅዳሜ ነበር እለቱ ...**

**ከምሽቱ ሁለት ሰአት ላይ አኖሌና የወታደር መለዮ ልብስ የለበሰ፣ ኡዚ የታጠቀ፣ ሽንጣ ያንጠለጠለ ሰው መኪናቸውን ማርያም ግምቢ ደጅላይ አቁመው በእግር ወደ ወህኒ ቤቱ ደጃፍ ተጠጉ ...**

**«ማነው!?»**

**«እኛ ነን! አኖሌ ነኝ።»**

**«እርሶ ኖት? ታዲያ መኪናችሁን አታስገቡም ኖሮአል?»**

«የኤርትራን ህዝብ አንተ አታውቀውም። ትእቢታቸውና ንቀታቸው። መሀይሞች - ጥሬ ስጋ የሚበሉ - ቅንዝረኞች - እያሉ ነውኮ የሚሰድቡን። እንዲህ ሲሉ ታዲያ እልህ ይይዝሀል። ሆስፒታል ቢሰሩላቸውም ንቀታቸው ይቀጥላል» ካለ በሁዋላ «ግን ጉዋድ ፕሬዝዳንት ያቀረብከውን ሀሳብ ተቀብለውታል?» ሲል ጠየቀው።

«በሚገባ! ጥናቱን ካነበቡት በሁዋላ ጠርተው አቅፈው ሳሙኝ! 'ከሁሉም አዲስ አሳብ ለመሰንዘር ያለህን ድፍረት አደንቃለሁ' አሉኝ። እኔ ጀርመን ነው የኖርኩት። ግዴለኝም። በግልፅ ያሻኝን መናገር ለምጄያለሁ።»

«ለነገሩኮ ሀሳቡ ጥሩ ነው። ግን ህዝቡ እባብ ነው።»

የአብርሃ ፀሎትን ክፍል የሚጠብቀው ፖሊስ ኰሎኔል ዝናውን በማየቱ መሽቆጥቆጥ ጀመረ። የአብርሀ ፀሎትን ክፍልም በችኰላ ከፈተላቸው፣

አኖሌ ወደ ኰሎኔሉ ጆሮ ጠጋ አለ፣

«ጥበቃው ከኛ ጋር ይጠጣ!» ሲል ሀሳብ አቀረበ።

«ለምን?»

«ለጥንቃቄ አጠገባችን ቢሆን አይከፋም!»

ኰሎኔሉ ሳቀ፣

«እኛ እኮ ኮማንዶ ተምረናል። አይኑ ላይ አሳይተን ቆለጡን ነው የምናፈነዳለት። ላንተ ግን ...» ብሎ ሳቀበትና በሀሳቡ ተስማማ። እናም ሰስቱም ዊስኪ ጠርሙሳቸውን ከብርጭቆዎች ጋር ይዘው አብርሃ ፀሎት ክፍል ገቡ።





# እንደምን አደርሽ

# ኖራህ!?

## ምእራፍ ስምንት

### - 1 -

**በነጋታው ቅዳሜ ነበር እለቱ ...**

**ከምሽቱ ሁለት ሰአት ላይ አኖሌና የወታደር መለዮ ልብስ የለበሰ፣ ኡዚ የታጠቀ፣ ሻንጣ ያንጠለጠለ ሰው መኪናቸውን ማርያም ግምቢ ደጅላይ አቁመው በእግር ወደ ወህኒ ቤቱ ደጃፍ ተጠጉ ...**

«ማነው!?»

«እኛ ነን! አኖሌ ነኝ።»

«እርሶ ኖት? ታዲያ መኪናችሁን አታስገቡም ኖሮአል?»

«ደህና ስለማንቀይ ነው፡፡ ደህና አመሸህ?»

«ደህና! ደህና! ይግቡ ...» እጅ እንደመንሳት አለ፡፡

አኖሌና ታጣቂው ረዳቱ ወደ ግቢው ዘለቁ፡፡ ፖሊሱ እጅ መንሳቱን ቀጠለ ...

«ትናንት ወዳጅህ አስቀናህ መሰለኝ!» አለው አኖሌ፡፡

«ዊስኪ ነው!?» ብሎ ፖሊሱ ከልቡ ሳቀ፡፡ «ለኛም አንድ ቀን ይደርሳል፡፡»

አኖሌ ከሻንጣ ውስጥ ግማሽ ጠርሙስ ዊስኪ አውጥቶ ሰጠው፡፡

«ደብቀህ ተጠቀም፡፡ እንዳትቀና ብዬ ነው፡፡» አለው፡፡

በደስታ ተቀበሎ፣

«ያኑርልኝ ጌታዬ ... ያኑርልኝ፤ ብርዱን ያባርርልኛል፡፡ ጭንቀቴን ሁሉ ይገፍልኛል፡፡»

«ትናንት ሁለት አልነበራችሁም እንዴ? የታለ ታዲያ ወዳጅህ?»

«አመሻሽቶ ይመጣል፡፡ እዚሁ ነው፡፡»

«ስክረህ እንዳታስወቅሰኝ ደሞ፡፡ እኔን የሚነካኝ የለም፡፡ አንተ ግን መቀመቅ ትወርዳለህ፡፡»

«ይመኑኝ፤ ከሶስት ጉንጭ በላይ አልወስድም!»

አኖሌና መለዮ ለባሹ ወደውስጥ ዘለቁ፡፡

ሁለቱም ቃል ሳይተነፍሱ ወደ አብርሃ ፀሎት ልዩ የእስር ክፍል ደረሱ፡፡

«ማነው!?» የአብርሀ ፀሎት ልዩ ጠባቂ ነበር፡፡

«አኖሌ ነኝ!»

«ዛሬም ተመልሰው መጡ እንዴ?» ብሎ ብድግ አለ፡፡

«የትናንቱ ዊስኪ አልተስማማህም መሰለኝ?» ሲል ቀለደ፡፡

«እረ ምን ሲደረግ ... ስለትናንቱ እግዚአብሄር ያክብርልኝ፡፡ ሙቀት ለቆብኝ ሳይቆፈንነኝ አደረ፡፡ መቼም እግዚአብሄር ያክብርልኝ፡፡»

«ግዴለም ሰሞኑን ያልፍልሀል፡፡ በል ዛሬም እኛ ዘንድ ግባ፡፡»

ፖሊሱ የአብርሀ ፀሎትን ክፍል በፍጥነት ከፍቶ አስገባቸው፡፡





ሬድዮ በከፍተኛ ድምፅ ይጮህ ነበር፡፡ ፖሊሱ እንደትናንቱ ከዊስኪው ሊቀዋደስ ረዳቱን ተከትሎ ገባ፡፡ የአኖሌ ረዳት በያዛት ሻንጣ ላይም አይኑን ተከለ፡፡ የዊስኪ መያዥያ መሆንዋን ተገንዝቦአል፡፡ አልተሳሳተም፡፡ ከሻንጣዋ ውስጥ ዊስኪ ወጥቶ ተቀዳ፡፡ ወግ ተጀመረ፡፡ የሬድዮው ድምፅ ከፍ በማለቱ ግን መደማመጥ አልተቻለም፡፡

ፖሊሱ ግራ ተጋባ ... 'ሬድዮውን ይህን ያህል ማጮህ ለምን አስፈለገ?' ሲል ራሱን ይጠይቅ ጀመር፡፡

* * *

በር ላይ የቆመው ጠባቂ በሶስት መለኪያ አላበቃም፡፡ አምስተኛው ላይ ደርሶአል፡፡ ሞቅ ሲለው ደስታና በራስ የመተማመን ስሜት ተሰማው፡፡ ሆኖም እንቅልፍ ሞከረው፡፡ ደነገጠና ከተቀመጠበት ብድግ አለ፡፡ ሽለብ ቢያደርገው የሚደርስበትን ቅጣት ያውቃል፡፡ እና ከወዲያ ወዲህ ሲንጐራደድ ድምፅ ሰማ፡፡ ቀና አለ፡፡ አብርሃ ፀሎት ከታሰረበት ክፍል አካባቢ የመታፈን አይነት ድምፅ መሰለው ...

ማዳመጥ ጀመረ፡፡ ከሚሰማው የሬድዮ ድምፅ በላይ የሁለት ሰዎች ከፍተኛ የማስካካት ድምፅ ተከተለ፡፡

«እየተጫጫሱ ነው» ሲል አሰበና ወደ ዊስኪ ጠርሙሱ አመራ፡፡

አንዴ መጐንጨት አማረው፡፡ እናም ተጐነጨ፡፡

አስመራ ፀጥ ብላለች፡፡ ከዋክብት ሰማዩ ላይ ፈስሰዋል፡፡ ወታደሩ ማንኪያ የተባሉትን ክዋክብት ይፈልግ ጀመር፡፡ የማንኪያው ጭራ ዘወትር የሰሜንን አቅጣጫ እንደሚያመለክት በማሰልጠኛ ጣቢያ ተምሮአል፡፡ የማንኪያው ጭራ አስመራን ያመለክታል ... ኤርትራን ይጠቁማል ... የጦርነት ምድርን ለዘልአለሙ ያሳያል ...

የእግር ኰሽታ ሰምቶ ዘወር አለ፡፡

«መጣችሁ እንዴ ጉዋድ አኖሌ ...»

«መጣን! ነገ ደሞ እንገናኝ ... ከጄኔራል ሁሴን ጋር እንመጣለን፡፡ ብርቱ ዘብ መሆንህን እነግራቸዋለሁ፡፡ ያውቁሀል አይደለም?»

«ወየው ጉድ! ደሞ ጄኔራሉ እኔን ይወቁኝ!? እርስዎ ሆነው አከበሩኝ፡፡» ብሎ ተቅለሰለሰ፡፡

«አለቀብህ እንዴ ውስኪ!?»

«እረመቸ ተነክቶ?»

«እንዳትጨርሰው ... ከነገ ወዲያ ነው የማመጣልህ!»

«ለዚህውም ያኑርልኝ ጉዋድ አኖሌ ... ያኑርልኝ ...»

«በል ደህና እደር»

«በሰላም ያሳድርልኝ»

ከግቢው ወጥተው መኪናቸውን አስነስተው ነጉዱ::

አስር የጭንቀት ደቂቃዎች::

ካራቫል ሬስቶራንት ደረሱ:: አንድ አሮጌ ማርቸዲስ በሩ ላይ ቆማለች:: መኪናቸውን አቁመው ወረዱ:: ጊዜ አላጠፉም:: ወደማርቸዲስዋ ገሰገሱ:: አኖሌ ከሾፌሩ ጐን ያለውን በር ከፍቶ ገባ:: አብርሀ ፀሎት ደግሞ ከሁዋላ::

ማርቸዲስዋ ተነስታ ተፈተለከች::

አዶናይ መኪናዋን እያሽከረከረ ይጮህ ነበር፤

«ኩፉ አላምንም ... አብርሃ:: አይኔን አላምንም... ውድ ጉዋደ::»

«አኖሌን አመስግነው:: ቃልህን መጠበቅህንም አረጋግጥ» አለው አብርሃ ፀሎት::

«አታስብ ... ከአራት ሰአት በሁዋላ ሁለታችሁም ርቃችሁ ትሄዳላችሁ::»

«ወዴት?» አለ አብርሃ ፀሎት::

«ሳህል ...»

አዶናይ መኪናዋን ከአንድ ሆቴል ጉዋሮ አስገብቶ አቆማት:: ከካራቫል ሆቴል የአስራ አምስት ደቂቃ መንገድ ብቻ ነበር የተጉዋዙት:: አካባቢው ጨለማ ነው:: ሆቴሉ የደከመ በመሆኑ እምብዛም ግርግር አይታይበትም:: ተስተናጋጆቹ በረንዳው ላይ ሻይ የሚጠጡ ጥቂት ወጣቶች ነበሩ::

«አብሮኝ የገባው ሰው የማምለጥ ተስፋው ምን ያህል ነው?» ሲል ጠየቀ አኖሌ::

ምላሽ የሰጠው አልነበረም፣

«ወይስ አብርሀ ፀሎትን ተክቶ ይሰዋል?» ሲል መልሶ ጠየቀ::





አዶናይ ምላሽ ሰጠው፣

«አኖሌ ... ይህን ጥያቄ ደግመህ አታንሳው:: ዝርዝር ነገሮችን ለጊዜው ልንነግርህ አንችልም:: አብርሀ ፀሎትን ተክቶ እንደማይሰዋ ግን አረጋግጥልሀለሁ - መቶ በመቶ::»

ፀጥታው አስፈሪ ነው:: ለሰአታት በፀጥታ መኪናቸው ውስጥ ቆዩ:: አኖሌ ፍርሀት አደረበት:: ሰአቱን አየ:: ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት:: በያንዳንድዋ ደቂቃ አደጋ ሊደርስ ይችላል:: ሞት! ልቡን እፍን አደረገው:: ለምን ይህን መሰል ችግር ውስጥ ገባሁ? ብሎ ራሱን ጠየቀ::

በእጁ ያለው አማራጭ ይኸው ነው ሲል ለራሱ ምላሽ ሰጠ:: እድልን ይማፀን ጀመር:: ህይወትና ሞት:: ሞት ምን ይመስል ይሆን? ሲል አሰበ:: አለመኖር ... የአኖሌ አለመኖር ... አለም እንደሁ አኖሌ ለሚባል አንድ ሰው ኩፉ ምንም ግድ አይኖራት ... አኖሌ ቀረ ሄደ ምን ለውጥ አለው? ሞት ጨለማ ይሆን? ለምን በዚህ ዘመን ተፈጠርኩ? ለመሆኑ እኔ ማነኝ?

ሰአቱን አየ:: ዘጠኝ ተኩል ...

አንድ ጥላ ወደ መኪናቸው ሲጠጋ ሰስቱም ተመለከቱ:: አኖሌ ቀልቡን ሲስት ምንም አልቀረው:: ልቡን ሰወረው:: ሌሎቹ አልተንቃነቁም:: የተጠጋው የሰው ቅርፅ ያለው ጥላ ተመልሶ ሄደ:: በሰከንዶች ልዩነትም አንዲት ቶዮታ ላንድ ክሩዘር ወደ ሆቴሉ ጉዋሮ ዘልቃ ገባች:: አኖሌ በጨለማ ውስጥ ከመኪናዋ ጐን ላይ የቀይ መስቀል ምልክት ታየው ...

* * *

የቀይ መስቀል አርማ ያለባት ላንድ ክሩዘር ከአየር ሃይል ግቢ ደጅ ላይ ደረሰች:: ከተረኛ ኤርፖሊሶች አንዱ እንደተለመደው ፍተሻውን በጥንቃቄ ያካሂድ ጀመር:: ከበሩ ግራና ቀኝ ታጥቀው በተጠንቀቅ የሚጠብቁ አራት የጥበቃ ኤርፖሊሶች ይታያሉ:: የአስር አልቅነት ማእረግ ከንዱ ላይ ያንጠለጠለው ፖሊስ ወደ ላንድ ክሩዘርዋ ጠጋ ብሎ ከውስጥ ያሉትን ሰዎች አንድ ባንድ ካስተዋለ በሁዋላ፣

«ጤና ይስጥልኝ ዶክተር!» አለ በፈገግታ::

«አንተው ኖረሃል? ማነው ብዬ እኔ ደሞ?» አሉ ሀኪሙ::

«ዛሬ ደግሞ ጉዋዝ አበዙሳ? ቁስለኛ አለ እንዴ?»

«የለም ... ኖራህ ደሴት ላይ ተሰቦ ገብቶ ነው።»

«ምነው? አሁንም ውሃ አልወጣም?»

«ከየት በመጣ አቅም?» አሉት የይለፍ ወረቀቱን እያቀበሉት። በወረቀቱ ላይ ካሉት ስሞች በተራ ቁጥር አንድ ላይ የሰፈረውን የዶክተሩን ስም ዘሎ የሌሎቹን እየጠራ መታወቂያቸውን ያመሳክር ጀመር፣

«የራሺያ ሀኪሞች ኖራህ ደሴት ላይ አሉ አይደለም እንዴ ዶክተር?»

«የመቼሁን? ለቀቁኮ።»

«በሉ መልካም ጉዞ ...»

ከዚያም ወደ ኤር ፖሊሱ ዞሮ አለ፣

«... በሩን ክፈት!»

መኪናዋ ሰተት ብላ ወደ ግቢው ዘለቀች። በመኪናው ውስጥ ያሉት ሶስት ሰዎች ረጅም አየር አስወጡ።

«እብደት ነው!» ሲል አጉረመረመ አኖሌ።

ሌላ ቃል የተነፈሰ የለም።

ዶክተሩ መኪናዋን በከፍተኛ ፍጥነት ያበሩአት ጀመር። ሰአታቸውንም ደጋግመው ያያሉ።

ድንገት ወታደራዊ መኪና ከሁዋላ ተከተላቸው። ዶክተሩ በመረበሽ በሁዋላ መመልከቻ መስታወት ይመለከቱ ጀመር። መኪናዋ ኡዋዝ ጂፕ መሆንዋን በፊት መብራቶችዋ አወቁ። ጂፕዋ ከመፍጠንዋ የተነሳ በአጭር ሰከንዶች ውስጥ ትቀርባቸው ጀመር። በግምት ሰላሳ ሜትር ርቀት ላይ እንደደረሰች ረጅም መብራት አበራች። ዶክተሩ ዝግ አደረጉ። የኡዋዝ ጂፕዋ መብራት ብልጭ ድርግም ይል ጀመር። ምልክቱ ለርሳቸው ስለነበር ፍሬን ያዝ አደረጉ። በሁዋላ መመልከቻው እያዩም፣

«ተረጋግታችሁ ተቀመጡ። የመደናገጥ ምልክት እንዳያዩባችሁ። መጥተው ቢያነጋግሩዋችሁ ትድም ያልኩዋችሁን ብቻ መልሱ» ሲሉ አዘዙ።

ዶክተሩ ይህን ይናገሩ እንጂ ድምፃቸው እየተቆራረጠ ነበር መኪናቸውን አቁመው የወረዱት።





ጂፕዋ ተጠግታ ቆመች።

አብርሃ ፀሎት ሽጉጡን ከመኪናው ወንበር ስር መዘዘ። አኖሌ ግንባሩ በላብ ተጥለቀለቀ። ሶስተኛው የዶክተሩ ረዳት የተኛ መስሎ ተንጋለለ።

አኖሌ «ምንድናቸው?» ሲል ወደ አብርሃ አንሾካሾከ።

«አላወቅሁም» ብሎ በንቃት ይጠብቅ ጀመር።

ከሶስት ደቂቃ በሁዋላ ኡዋዝ ጂፕዋ ሞተርዋን አስነስታ ወደሁዋላ ተመለሰች። የዶክተሩ የተጣደፉ የጫማ ኮቴ ድምፅም እየቀረበ መጣ።

«ምንድነው ዶክተር!»

አብርሃ ነበር ቀድሞ ጥያቄ ያቀረበው።

**«አንድ ሙሻ ወታደር ነው። ወደኖራህ ደሴት ሲጋራ እንድወስድለት ነው የሚለምነኝ። የዛሬው ምሽት ተረኛ መኮንን መሆኑ ነው»** ብለው መኪናቸውን አስነስተው ተፈተለኩ።

«ታዲያ?»

«ተስማምቼለታለሁ። ኖራህ ደሴት ላይ ከፍተኛ የሲጋራ እጥረት አለ።»

ከዚያም ቃል ሳይተነፍሱ ከአየር ማረፊያው ሜዳ ደረሱ። በድጋሚ ሰጥበቃዎች ወረቀቶቻቸውን አሳዩ። ይሄኔ ዶክተሩ ጥድፊያ ጀመሩ።

«ካርቶኖቹን ጫኑ ልጆች!» ሲሉም አዘዙ «... መፍጠን አለብን ... ቶሎ በሉ!»

**በአይናቸው ግን የሄሊኮፕተርዋን አብራሪ እያሰሱ ነበር። በአካባቢው ስላጡት ግራ ተጋብተው ይገላመጡ ጀመር። ከጨለማው የግራር ዛፍ ስር ድንገት ድምፅ ሰሙ፣**

**«እዚህ ነኝ ዶክተር!»** የሚል።

**ድምፅ** ወደሰሙበት አቅጣጫ በችኮላ ሄዱ። ፓይለቱ የተደራረቡ ቡሉኬቶች ላይ ተቀምጦ አገኙት፣

«እንደምን አለህ እስክንድር?»

«ደህና አመሹ?» ብሎ ከጨበጣቸው በሁዋላ «ሰዎችዎ መጡ?» ሲል ጠየቃቸው።

«መጥተዋል!»

«ዶክተር ... ህይወቴን ከሚያሳጣኝ ችግር ውስጥ መግባት እንደማልፈልግ ያውቃሉ። ጉዳዩ ከተጋለጠ በጦሱ እንደማልገባ ይወቁ።»

«አንተን ማንም አይጠይቅህም። ጥያቄ ከቀረበልህ ግን ከኔ ጋር ሶስት ረዳቶች እንደነበሩ ትገልፃለህ። ፍተሻ ያንተ ተግባር አይደለም። ከባድ አይደለም እስክንድር። ወደ ጂዳ መሻገር የሚፈልጉ ሁለት ምስኪን ወጣቶች ናቸው። ይልቁን ለሚስትህና ለልጆችህ በቂ መተዳደሪያ አስቀምጥ። አንተ በየትኛዋም ደቂቃ ሙዋች ነህ።» አሉና እጃቸውን ወደ እጅ ቦርሳቸው ሰደው የታሰሩ ብሮች አወጡ።

«ምን ያህል ነው ዶክተር?»

«ሃምሳ ሺ።»

«አልቀበልዎትም ...»

«ምነው?» አሉ ስሜታቸው በድንጋጤ እየተኮማተረ።

«ሚስቴና ልጄ ገንዘብ ምን ያደርግላቸዋል? እኔን ነው የሚፈልጉኝ።»

ዶክተሩ ግራ በመጋባት ፓይለቱ ላይ አፈጠጡ። ሁለት ጊዜ በገንዘብ ተመሳሳይ ስራ ሰርቶላቸዋል። 'ዛሬ ድንገተኛ የባህርይ ለውጥ ለምን አመጣ?' ብለው ማሰብ ሲጀምሩ ጂፕዋ ሲጋራ ጭና ከተፍ አለች።

«ምንድነው ዶክተር?» አለ እየተደናገጠ።

«... አንድ ውሻ መኮንን ነው። ሲጋራ ወደ ኖራህ ደሴት መላክ ይፈልጋል» ብለው አረጋጉት።

ሲጋራ የሞሉ ካርቶኖችን የያዘው መስመራዊ መኮንን ከጥበቃ ኤር ፖሊሶቹ ጋር መጨቃጨቅ ጀመረ።

ፖሊሶቹ የይለፍ ወረቀት እየጠየቁት ነበር። ሻምበሉ በከፍተኛ ድምፅ ሲደነፋ ቆይቶ እጁን ወደ አንዱ ፖሊስ ዘረጋ። ሁሉም ነገር አለቀ። ፖሊሶቹ የፈለጉትን ሲያገኙ ይለፍ መጠየቁን ትተው ካርቶኖቹን በመሸከም አገዙት። ዶክተሩ የጉቦ ቅብብሉን ትርኢት በአንድናቆት ሲያስተውሉ ቆይተው፣ ወደ ሄሊኮፕተር አብራሪው ዘወር አሉ፣

«አልገባኝም እስክንድር» አሉት ጥቅል ብሩን እንደዋዛ ወደ ቦርሳቸው እየመለሱ።





«ሁለቱ ሰዎችም ጂዳ መሄድ የሚፈልጉ ተማሪዎች ናቸው ብዬ አላምንም። በግልፅ እንነጋገር። ከተያዝን ሁላችንም አይቀርልንም።»

«ላንተ ምን ልዩነት ያመጣል እስክንድር?»

«ማወቅ አለብኝ።»

«ገንዘብ ይጨመርልህ?»

«ገንዘብ አልፈልግም።»

«ምንድነው ታዲያ የምትፈልገው?»

«አስመራን መልቀቅ እፈልጋለሁ። ሚስቴና ልጆቼ ዘንድ ደብረዘይት መመለስ እሻለሁ።»

«ይህን ለማድረግ እንደማልችልማ ታውቃለህ!»

«ይችላሉ ዶክተር! ለሻለቃ ማሞ የፈፀሙላቸውን አውቃለሁ።»

ዶክተሩ ለጥቂት ሰከንዶች አቀረቀሩና ፊታቸውን የሲጋራ ካርቶን ወደሚያመላልሱት ጥበቃዎች መልሰው፣

«ተውት! የኔ ልጆች ይጭኑታል።» ሲሉ አዘዙ።

ተረኛ መኮንኑ ወደ ዶክተሩ በፍጥነት ቀርቦ «እንግዲህ አደራ!» ሲል ተማፀነ።

«ደህና!» አሉት

ተረኛ መኮንኑ ወደ ጂፑ ተቻኮለ።

ዶክተሩ እጃቸውን ወደ ቦርሳው ከተቱና የተጠቀለለውን ሃምሳ ሺህ ብር አወጡ፣

«ያልከውን እፈፅምልሃለሁ! ይህን ደግሞ ልጅህን አስተምርበት። እንዳንተ ሄሊኮፕተር ነጂ ባይሆን ይመረጣል» ብለው ቀለዱበት።

ብሩን ተቀብሎ የዶክተሩን እጅ በምስጋና እየጨበጠ፣

«ይመኑኝ ዶክተር! ይህ ጉዞ የተሳካ እንዲሆን አደርጋለሁ!» ሲል በሞቀ ወኔ ቃል ገባ።

ዶክተሩ ግን በልባቸው 'ሞኞ! ከዛሬ ወዲያ እኔን የት አግኝተኸኝ?' ሲሉ አላገጡበት።

ሄሊኮፕተርዋ ምድርን ለቀቀች። ገና አልነጋም። አኖሌ በጨለማው ውስጥ አስመራን ቁልቁል አያት - በብርሃን ደምቃ። እፎይታ ግን አልተሰማውም። ልክ ሲነጋ ኖራህ ደሴት ያርፋሉ።

ከዚያ የሚጠብቃቸውን አኖሌ አያውቅም፡፡

የልብ ምቱን ያዳምጥ ጀመር ...

- 2 -

ጂብሪል አሊ ቅዳሜ ማምሻውን ሲጠጣ ስላመሸ እሁድ ማለዳ ድካም ጣለው፡፡ ቢሆንም ነቅቶ ነበር፡፡ ታናሽ እህቱ ጀሚላ የመኝታ ክፍሉን በር ቆርቆራ!

«ውሃ ሞቆልሃል!» ብትለውም ሰነፈ፡፡

የባጥ የቆጡን ሀሳብ እያነሳ ሲጥል! ከአርብ ጀምሮ ከአኖሌ ጋር በስልክ እንዳልተገናኙ ትዝ አለው፡፡ እና ተንጠራርቶ ቴሌፎኑን አነሳ፡፡ አስመራ ይሞክር ጀመር፡፡ አራተኛው ላይ አምባሶይራ ሆቴል ጠራለት፡፡

«አኖሌ ዋቆ ...» አለ፡፡

«የሉም!» አለው የወንድ ድምፅ፡፡

ሰአቱን አየ፡፡ ረፍዶአል፡፡

'ማልዶ ወጥቶ ነው? ወይስ ደጅ አድሮ?' ሲል አሰበ፡፡

«ማን ልበል?» የሚል ጥያቄ ተከተለ፡፡

«ጓደኛው ነኝ ... መልእክት ይንገሩልኝ፡፡»

ኦፕሬተሩ መልስ ሳይሰጠው ሲንሾካሾክ ሰማና ደነገጠ፡፡

«እሺ ... ማን ልበል?» አለ በተደናገረ ድምፅ፡፡

«ምን ሆነሀል? ችግር አለ እንዴ?» ሲል ጠየቀው፡፡

«ምንም ችግር የለም! ስምዎን ይንገሩኝ? ከየት ልበለው?»

ጂብሪል በጣም ደነገጠ፡፡ ኦፕሬተሩ መርበትበቱና ሌላ ሰው እያዘዘው እንደሚናገር በግልፅ ታወቀው፡፡ ከአልጋው ዘልሎ ወረደ፡፡

«የኔ ወንድም እኔ ጂብሪል እባላለሁ፡፡ ከአዲስ አበባ የህዝብ ደህንነት ፅህፈት ቤት ነው የምደውለው፡፡ ችግር ካለ ብታስረዳኝ?»

«ቆይ ይጠብቁ!» አለ፡፡

ከጥቂት ሰከንዶች በሁዋላ አንድ ወፍራም ድምፅ በስልኩ መስመር መጣለት፡፡

«ጤና ይስጥልኝ ጓድ ጂብሪል!»





«ጤና ይስጥልኝ ... ማን ልበል?»

«የአስመራ የህዝብ ደህንነት ክፍል ባልደረባ ነኝ፡፡ መቶ አለቃ ደግሰው እባላለሁ፡፡ እኔ እንኩዋ አውቅሀለሁ፡፡» ካለ በሁዋላ «አኖሌ የተባለውን የስራ ባልደረባችሁን ለአንዳንድ ጥያቄዎች ፈልገነው ነበር፡፡ ካረፈበት ሆቴል አላገኘነውም፡፡»

«ሌላ ቦታ አድሮ ይሆናላ፡፡ ዛሬ እሁድ ነውኮ፡፡ የተፈጠረ ችግር አለ እንዴ? ለምን ፈለጋችሁት?» አለ ግራ በመጋባት፡፡

«ዝርዝር ጉዳዩን አላውቅም፡፡ አስቸኳይ ትእዛዝ የተላለፈልን ግን ከአንድ ሰአት በፊት ነው - ከኮሌኔል ዝናው ቢሮ፡፡ አኖሌ ምናልባት ወደርሶ ከደወለ ቢያሳውቁን መልካም ነው፡፡»

«ደህና!» ብሎ ስልኩን ዘጋው፡፡

እጁ እየተንቀጠቀጠ ወደ ኮሌኔል ዝናው ቢሮ ሞከረ፡፡ ተይዞአል፡፡ የእውር ድንበሩን ማስታወሻ ደብተሩን ይፈልግ ጀመር፡፡ አገኘው - የኮሎኔሉን ልዩ መስመር፡፡ ደወለ፡፡ ተይዞአል፡፡ ሲረጋጋ ቢሞክርም አልቻለም፡፡ እጁ እግሩ ይንቀጠቀጣል፡፡ አኖሌ ታፍኖ ይሆን? ሲል አሰበ፡፡ ታፍኖ መሆን አለበት! ከአርብ ጀምሮ ያልደወለው ለዚህ ይሆን? ማሰብ ጀመረ፡፡ በርግጥ ጊዜው የጦርነት ነው፡፡ ግን ሻእቢያ አኖሌን ለምን ያፍነዋል? ምስጢር ፍለጋ? ምን ምስጢር ያገኛሉ ከአኖሌ?'

ወደ ሚኒስትሩ ቢሮ ሊደውል አሰበና አመነታ፡፡ ሰሞኑን ገሸሽ አድርገውታል፡፡ ወደ ወሎ ክፍለሀገር ሃየሎም የተባለውን የወያኔ ኮማንደር እንዲገድል የተላከው ሰው ከድቶ በወያኔ ሬድዮ ከለፈለፈ ወዲያ ስሜታቸው ጤናማ አልነበረም፡፡ አሁን ደሞ ሌላ ጣጣ - ሌላ ችግር - አኖሌ!

ስልኩን አንስቶ ይሞክር ጀመር፡፡ ድንገት ጠራለት፡፡ የልቡ ምት ቀጥ ሊል ነበር፡፡ በጉጉት ይጠብቅ ጀመር፡፡

«ሀለው!» የሚል ችኩል ድምፅ፡፡

«ኮሎኔል ዝናው አለ?» ሲል ጠየቀ፡፡

ከኮሌኔሉ ጋር ጀርመን አብረው ስለተማሩ በሚገባ ይተዋወቃሉ፡፡ ሆኖም ኮሎኔሉ ብዙ ጊዜ በጂብሪል ላይ የበላይነቱን ለማሳየት ይጥራል፡፡

«ማን ልበላቸው?» አለ ኤዲሲው፡፡

«ጂብሪል .. ከአዲስ አበባ፡፡»

ከሰከንዶች በሁዋላ የኮሎኔል ዝናው ድምፅ መጣለት - ቀዝቃዛ

ድምፅ::

«ምንድነው ዝናው?» አለ - ከሰላምታ በፊት::

ፈጣን ምላሽ ግን አላገኘም:: የኰሎኔሉ ድምፅ ቀዘቀዘበት::

«በቅድሚያ እንደምን አደርክ?»

«እንደምንነህ? ስለ አኖሌ ምንድነው የምሰማው?»

«ምን ሰማህ?»

«እምባሶይራ ሆቴል ደውዬ ነበር:: ባንተ ትእዛዝ እየተፈለገ መሆኑን አንድ ፖሊስ ነገረኝ:: የተፈጠረ ችግር አለ እንዴ?»

«አንዳንድ ችግሮች አሉ:: በእዝ ጠገጉ መሰረት ወደ በላይ አካል አስተላልፈናል:: ጉዳዩ በከፍተኛ ሁኔታ እየታየ ነው»

«ምንድነው የተፈጠረው?!» ሲል ጮሆ ጠየቀው::

«ላንተ ሪፖርት ማቅረብ አለብኝ እንዴ ጂብሪል?» ሲል አንጉዋጠጠው::

ጂብሪል ቀዝቀዝ አለ:: እንደምንም ስሜቱን አምቆ ይቅርታ ጠየቀው፣

«ላስቀይምህ ብዬ አይደለም:: ጉዳዩ በቀጥታ እኔን ስለሚመለከትና አኖሌ ሊደርስበት የቻለውን አደጋ ስገምት በመስጋት ነው:: እባክህ ይቅርታ አድርግልኝና እንነጋገር ...» ሲል ተማፀነው::

«ለማንኛውም የላክኸው ልጅ የሻእቢያ ወኪል ሆኖ ተገኝቶአል:: ከድቶናል:: ያውም አብርሃ ፀሎት የተባለውን ቀንደኛ የሻእቢያ እስረኛ ከእስር ቤት እንዲያመልጥ አድርጎ ነው የተሰወረው::»

የጂብሪል ትንፋሽ ስርግ አለ::

ቃል መተንፈስ አቃተው:: በቴሌፎን መስመር የተላለፈለትን አስደንጋጭ ዜና ማመን ቸገረው:: ማመን ግን አለበት:: ህልም አይደለም:: እንደደነዘዘ የሻለቃ ዝናውን በእብሪትና በንቀት የተሞላ ዲስኩር ማዳመጥ ቀጠለ፣

«... ሁልጊዜ ጣልቃ ትገባላችሁ:: ውጤቱን እዩታ! የስለላ ስራ ፍልስፍና አይደለም:: መፅሀፍ እያነበቡ እንደ ተውኔት የሚጠና ተግባር አይደለም:: ቅልጥፍና፣ ታማኝነትንና ድፍረትን የሚጠይቅ ጥበብ ነው:: ሙሉ ሃላፊነት ሰጥታችሁ የላካችሁት ሰው የፈፀመው እንግዲህ ይህንን የክህደት ተግባር ነው:: ለነገሩ ማንቁርቱን እንደምይዘው አልጠራጠርም:: እገባበት ገብቼ ጉሮሮውን እንቀዋለሁ::





ያን ጊዜ በዶላር ተገዝተው የሚተባበሩት ከሀዲዎች ማን ማን እንደሆኑ ይናዘዛል ...»

ጂብሪል ለአሽሙራዊ ንግግሩ አልተጨነቀም...

«... ሊደበቅ የሚችልበትን ፍንጭ አጊኝታችሁዋል?» ሲል ጮሆ ጠየቀው::

«ስራውን በምስጢር ብይዘው እመርጣለሁ!» አለው በበላይነት መንፈስ::

«ልረዳህ የምችለው ጉዳይ ስላለኝ ነው!» አለ ጂብሪል አንድ ነገር እያስታወሰ::

«ካለ ንገረኛ! ...» አለ ኰሎኔሉ::

«እዚህ አዲስ አበባ አንድ የልብ ጉዋደኛ አለው:: ሳሙኤል የሚባል ኤርትራዊ ነጋዴ:: ከጀርመን ጀምሮ ይተዋወቁ እንደነበር ገልፆልኛል:: ከዚህ ከመሄዱ በፊትም በቅርብ ይገናኙ ነበር:: የሳሙኤል እጅ ሊኖርበት ስለሚችል እሱ ከተያዘ ፍንጭ ሊገኝ ይችላል::»

«ጊዜ አትስጠዋ! በአንድ ሰአት ጊዜ ውስጥ አስመራ ያለውን የዘመዶቹን አድራሻ ግለፅልን:: በውነቱ ይህን ካደረግህ ዋነኛ ተጠቃሚው አንተ ትሆናለህ::»

«ግን እንዴት ሊያመልጥ ቻለ? ጥበቃ የለም እንዴ?»

«እኛም እንቆቅልሽ ሆኖብናል:: አኖሌ ከአንድ ታጣቂ ረዳቱ ጋር ማታ ማሪያም ግምቢ ገብቶ ተመልሶ ወጥቶአል ነው የተባለው:: ረዳቱ ሲጠየቅ ትናንት ማምሺያውን ከአኖሌ ጋር አለመገናኘቱን ገልፆአል:: እስከ ሶስት ሰአት ከምሽቱ የምግብ ኰሚቴ ስብሰባ ላይ እንደነበር ተረጋግጦአል:: እንግዲህ የአኖሌ ረዳት የተባለው ማነው? አይታወቅም:: የአብርሀ ፀሎት ልዩ ጠባቂ ተገድሎ ነው የተገኘው:: አብርሃ ፀሎት በየት እንደወጣ አይታወቅም::»

ጂብሪል ስልኩን ዘግቶ ያወጣ ያወርድ ጀመር:: ሚኒስትሩ ዘንድ ሊደውል አሰበና ተወው:: ኰሎኔል ዝናው 'የበላይ አካላት እንዲያውቁ ተደርጉአል' ያለውን አስታወሰ:: ሚኒስትሩ የሚሰማቸውን ሊያስብ ሞከረ:: ግን ጊዜ የለም:: አኖሌ እንዲያዝ የሚያደርግ ፍንጭ ካገኘ በሁዋላ በሙሉ ልብ ራሱን ነፃ ለማውጣት ሊከራከር ይችላል:: በቅድሚያ ግን ሳሙኤል መያዝ አለበት::

ግን ጂብሪል ደንዝዞ ነበር:: ማመን አቅቶታል:: 'አኖሌ ከሻእቢያ ጋር እንዴት ይተባበራል?' እያለ ራሱን እየጠየቀ ነበር::

አኖሌ ከመከላከያ የተባፈ የክስ ደብዳቤ ይኖር እንደሆነ የጠየቀውን ድንገት አስታወሰና ጥርጣሬ ሸው አለበት። አሳቡ እንደገና ወደ ሳሙኤል ዞረ። የሳሙኤል እጅ ሊኖርበት እንደሚችል አመነ። የሳሙኤል አድራሻ የት ይገኛል? ትዝ አለው - ናዝሬት የተገናኙ ጊዜ ፒያሳ የልብስ ሱቅ እንዳላቸው አኖሌ አጫውቶት ነበር። የሱቁን ስም ጭምር ነግሮታል። ማን ነበር? ሸገር ቡቲክ? ዘጠና ሰባት ደውሎ ጠየቀ። ሰጡት። ደወለ። ይጠራል ... ይጠራል ... የቀጭን ሴት ድምፅ መጣለት ... ረጋ ለማለት ሞከረ።

«ሳሙኤል ይኖራል?»

«በዚህ አይገኝም!»

«ቆየት ብዬ ልደውል ይሆን?»

«ዛሬ ሱቅ ዝግ ነውኮ! ደሞ እዚህ አልፎ አልፎ ነው የሚመጣው።»

«እሃ ... ቤት ይኖራሉ»

«ይኖር ይሆናል .. ይሞክሩ።»

«የኔ እህት እባክሽ ቁጥሩን ስጪኝ ...»

«ቆይ ...» አለች።

ከሰከንዶች በሁዋላ ቁጥሮቹን አንድ ባንድ ጠራችለት።

«አመሰግናለሁ የኔ እህት።»

«ምንም አይደል።»

እየተቻኮለ ደወለ።

እንደ እንደጠራ ልጅ ቢጤ ስልኩን በችሎላ አንስቶ «ማንን ፈለጉ?» አለ።

«ሳሙኤልን ያቅርቡልኝ።»

«ቆይ እስኪ ...» አለ ትንሹ ልጅ።

ጂብሪል አመነታ። እንደቀረበ ሊዘጋው ፈለገ። ከዚያም በቴሌፎን ቁጥሩ መሰረት አድራሻውን ከቴሌኮሙኒኬሽን አጣርቶ በቁጥጥር ስር ማዋል። ይህን እያሰበ ድንገት የሴት ድምፅ መጣለት።

«ሳሙኤል የለም!» አለች።

«የት ሄደ ባክሽ የኔ እህት? ቀጠሮ ነበረን።»

«ከኢትዮጵያ ውጭ ነው።»





ትንፋሹ ቁርጥ አለ። ጨለመበት። አላመናትም።

«የሚሸጡ ልብሶች በቡቲኩ ስም እንዳመጣለት አዞኝ ነበር። መቼ ይመለስ ይሆን?»

«የቱ ቡቲክ?»

«ሸገር ቡቲክ» አለ።

«ተሳስተዋል። ሳሙኤል እዚህ ቤት ተከራይ እንጂ ከሱቁ ጋር ግንኙነት የለውም።»

«ታዲያ ለምን እንዲያ አለኝ? መቼ ነው የሄደው?»

«ከትላንት ወዲያ ነው የተሰናበተን። ከሃያ ቀን በሁዋላ ይመለሳል።»

«ዶቅርታ የኔ እህት - ዘመድ ናችሁ አይደለም? እቃውን ወደ አስመራ ቤተሰቦቹ ዘንድ ልትልኩልኝ ትችላላችሁ?»

«አልለመኝም መሰለኝ። ቤት ተከራይ ነው። ዝርዝር ነገሮችን አናውቅም .. ሲመለስ ቢደውሉ ይሻላል።»

«እሺ አመሰግናለሁ!»

ስልኩን ዘግቶ በመኝታ ቤቱ መስኮት ወደ ደጅ አማተረ። ወኔው ሲከዳው ተሰማው። በህይወቱ ለሁለተኛ ጊዜ በፀፀት የሚያንገበግብ ስህተት መስራቱን አመነ። የመጀመሪያው ስህተት የዘጠኝ አመት ፍቅረኛውን ከመጠን ባለፈ ቅናቱ ማጣቱ ሲሆን ሁለተኛው ...

ድንገት በሩ ተንኳኳ። ዘወር ብሎ በተከፈተው የመኝታ ቤት በር በኩል አሻግሮ ተመለከተ። በሩን በዝግታ ገፋተው ሁለት ሲቪል የለበሱ ጐልማሶች ሲገቡ አየ። አወቃቸው። የደህንነት ማስጠራዊ ፖሊሶች ናቸው። በቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሉ አመሩ።

«ጉዋድ ጂብሪል እንደምን አደርክ?» አለ አንደኛው ፖሊስ።

«እንደምን አደራችሁ?»

«በቁጥጥር ስር እንድትውል ታዟል። ልብስህን ለባብስና ተዘጋጅ»

የሌሊት ልብሱን እየቀየረ ለራሱ ብቻ በሚሰማ ድምፅ አጉረመረመ።

«... ሁለተኛው ስህተት ይህን እብድ መንግስት አምኜ ወደ ሀገር ቤት መመለሴ ነው...»

## - 3 -

ቀይ ባህር በውጥረት ታፍናለች።

የአውሮፓ ነዳጅ ጫኝ መርከቦች ባህሩን በፍጥነት እየሰነጠቁ ውር ውር ይላሉ። በባህረ ሰላጤው ጦርነት የባስራ ወደብ የተደበደበባት ኢራቅ ሳትቀር የጆርዳንን ወደብ በመጠቀም ዘይትዋን የምታመላልሰው በዚሁ በቀይ ባህር ላይ ነው። ራሺያዎችና አሜሪካኖችም በቀይ ባህር ዙሪያ የስለላ መሳሪያዎቻቸውን ተክለው ተፋጠዋል።

ቀይ ባህር ተከባለች ...

የሶማሊያ ኪስማዩና በርበራ የባህር ሃይል ሰፈሮች በፀጥታ ተውጠዋል። ግብፅ ግን እረፍት የላትም። የባህረ ሰላጤው ጦርነት የሚያመጣውን ማንኛውንም ችግር ለመቋቋቋም በመርሳ ማትሩህና ፖርት ተውፊቅ ወደቦችዋ ከሃያ ሺህ በላይ የባህር ሃይል አሰልፋ የበላይነት ስሜትዋን አረጋግጣ የአካባቢውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ታስተውላለች። እስራኤል በሃይፋና አሽዶድ፤ ኬንያም በሞምባሳ የባህር ሃይል ሰፈሮቻቸው ጦራቸውን ወደ ቀይባህር አነጣጥረዋል። ሳኡዲ አረቢያም ከአልዋጅህ፣ ከአልዳማምና ከበረስ አልሚሻብ የባህር ሃይል ሰፈሮችዋ የኢትዮጵያን እንቅስቃሴ ታጥና እንጂ አራት ሺህ የሰው ሃይል ላለው የኢትዮጵያ ባህር ሃይል ራስምታት የሆኑበት የኤርትራ ፈጣን የውጊያ ጀልባዎች ናቸው። በመርሳ ጉልቡብ የተፈጥሮ ወደብ ላይ ቅጠል ተሸፍነው ትእዛዝ የሚጠብቁት የሻእቢያ ቶርፒዶ ተሸካሚ መርከቦች ቢሆኑ ዘወትር የደርግን ባህርሀይል እንቅልፍ እንደነሱ ነው። በዚህ ላይ የቀይ ባህር ሙቀት የመርከበኞቹን ናላ ያዞረዋል። ሌሊት መተኛት አይቻልም። አሸዋ ያዘለ አውሎ ነፋስ እየተነሳ የሚያሳቅቅ የነፋስ ድምፅ በመርከበኞቹ ጆሮ እንደ ቢምቢ ያምማል። በነፋሱ ምክንያት መርከበኞቹ መስማትና ማየት ይሳናቸዋል። በዚህ አስቃቂ የአየር ሁኔታ ውስጥ የኤርትራ ምድር እምቢተኞች ከፋይበር ግላስ በተሰሩ ጀልባዎቻቸው፤ በማንኛውም ደቂቃ ደርሰው አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ። የባህር አውሎ ነፋስ መነሳት ሲጀምርም ቀይባህር የጭንቅ ይመሳሰላል። የደርግ ባህር ትሆናለች። የነፋሱና የጥይት ድምፅ ይመሳሰላል። የደርግ የባህር ሃይል መርከበኞች በእንያንዳንድዋ ደቂቃ ሞት ሊከሰት እንደሚችል ያውጠነጥናሉ።

ከወደብ ጥበቃ ውጭ ያሉ የባህር መስመሮች ላይ የንጋት ኮከብ ብርሃን ይንቦገቦጋል። የጠረፍ ከተሞችና መንደሮችም እንደ እንቁ ደምቀዋል። በርቀት ይታያሉ። የኤሌክትሪክ ብርሃናቸውም እንዲሁ ያብረቀርቃል። ዳህላክ አርቺ ፔላጎ፣ መርሳ ጉልቡብ፣





መርሳ ተክላይና ጢኦ ላይም እስትንፋስ አለ። ቀኑንና ሌሊቱን ሙሉም የደርግ ባህር ሃይል የቅኝት መርከቦች ባህሩን እየሰነጠቁ ያልፋሉ። አጥቂና አሳሽ መርከቦች ሞተራቸውን አላጠፉም። ሰብ መሪኖች፤ ተዋጊ አይሮፕላኖችና ሄሊኮፕተሮች በተጠንቀቅ ላይ ናቸው።

ይሁን እንጂ በደርግ መርከበኞችና ወታደሮች ልብ ውስጥ ፍርሀት አለ። የመመልከቻና የማዳመጫ መሳሪያቸው ዘመናዊ ቢሆኑም መርከበኞቹ በማዳመጫው የልብ ትርታቸውን ነው የሚቆጥሩበት። በመመልከቻው ደግሞ መሀል አገር ያሉ ዘመዶቻቸውን ሊያዩበት ይጥራሉ...

* * *

ሄሊኮፕተርዋ ዝቅ ማለት ስትጀምር ዶክተሩ ሰአታቸውን አዩ ...

አስር ደቂቃ ዘግይተዋል። ተቁነጠነጡ። ኖራህ ደሴትን ከሄሊኮፕተርዋ ቁልቁል አዩዋት። ወታደሮች የማለዳውን የሰውነት እንቅስቃሴ ለማጠናቀቅ ግማሽ ሰአት ብቻ ቀርቶአቸዋል። ወደ ፓይለቱ ተጠግተው «መፍጠን አለብህ!» አሉት። ፓይለቱ በእሺታ ራሱን ላይ ታች ወዘወዘ።

ዶክተር አበራ የቀዶ ጥገና ህክምና ስፔሻሊስት ናቸው። ሻእቢያ በትምህርት ላይ እያሉ ነበር በአባልነት የመለመላቸው። ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ ሳህል ለመሄድ የነበራቸው ጉጉት ከፍተኛ ነበር። ሆኖም ወደ አስመራ እንዲመለሱ ሲነገራቸው ጆሮአቸውን ተጠራጠሩ። አብዱልከሪም - አባላሰሁ ብሎ ሮም ላይ የተዋወቃቸው ሰው የሻእቢያ ማእከላዊ ኮሚቴ አባል መሆኑን አልሸሸጋቸውም። የስራ ተግባራቸው ሮም ላይ ነበር የተገለፀላቸው። በማንኛውም ቅፅ ላይ ብሄረሰባቸውን አማራ ብለው እንዲሞሉና በቀይመስቀል ስር አስመራ እንዲመደቡ ሁኔታዎች እንደሚመቻችላቸው ሲነገራቸው «ለውዲትዋ ሀገሬ የሚከፈል መስዋእትነት» ብለው ነበር የአዲስ አበባን ትኬት የቆረጡት። በርግጥም አስመራ ተመድበዋል። አስመራ ላይ ስራ በጀመሩ በሶስተኛው ወር እዚህ ግባ የማይሉት አንድ ግንባራም ሰው መጥቶ የኮድ መጠሪያቸው 'አርባ አራት' መሆኑን ነገራቸው። ከዚያም ለመስማት የሚያስደነግጡ ተግባራትን እንዲፈፅሙ መመሪያ ይሰጣቸው ጀመር።

እነሆ ሶስት አመታቸው።

ከስምንት ቀናት በፊት ግን ያው ግንባራም ሰው መጥቶ «ይህ

የመጨረሻ ተግባር ነው!» አላቸው:: እያይሀም «... ከዚህ በሁዋላ ወደ ሳህል ታልፋለህ» ሲላቸው ልባቸው በደስታ ሞቀ:: «መቼና እንዴት ነው የምሄደው?» ሲሉ ጠየቁ::

«በቅርቡ ከኖራህ ደሴት ...» ይላቸዋል:: ዝርዝር አቅዱንም አስጠናቸው:: ይኸው የመጨረሻ ተግባራቸው ግን ጥቂት አስግቶአቸዋል::

ሄሊኮፕተርዋ ኖራህ ደሴት አረፈች::

በሄሊኮፕተርዋ ማረፊያ ሜዳ ዳርቻ ባለች የእንጨት የዘብ ጥበቃ ማማ ላይ በጨው የተቦጫጨቀ ፋቲግ የለበሱ፣ ለአመታት ያለለውጥ ኖራህ ደሴት ላይ በመቆየታቸው ሞራላቸው የወደቀ ሁለት ወታደሮች ብቻ ነበሩ:: የሻእቢያ ተዋጊዎች ኖራህ ደሴት ላይ ጥቃት ሰንዝረው ስለማያውቁ፣ መሰላቸትና መዘናጋት ይታይባቸዋል::

ዶክተሩ ከሄሊኮፕተርዋ ሲወርዱ ሁለት ካርቱኖችን ይዘው ነበር:: ግዴለሾቹ ወታደሮች ላይም አንባረቁ፣

«ፈዛቹሃልሳ! የሄሊኮፕተሩ እርግብግቢት ጆሮአችሁን እንዳይበጥሰው ነው? በሉ ይህን ያዙ:: ፍጠኑ ... ያዝ አንተ! ይህን ለአስተዳደር አድርሰህ አምስት ወታደሮች ይዘህ ተመለስ:: ያዝ አንተ ደግሞ - ወደ ክሊኒክ ቀጥል! እቃ የሚሸከሙ ይዛችሁ ተመለሱ ... ፍጠኑ ... ጠመንጃችሁን አስቀምጡ!»

ወታደሮቹ በታዘዙት መሰረት ሩጫቸውን ተያያዙት:: ዶክተሩ ወደ ሄሊኮፕተሩ መለስ ብለው ምልክት ሰጡ:: አኖሌ፣ አብርሃና የዶክተሩ ረዳት ካርቶኖችን ተሸክመው ወረዱ::

በአምስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ እቃቸውን አጠናቀው አውርደው የሄሊኮፕተሩን አብራሪ ተሰናበቱት:: እጁን አወዛውዞላቸው የኖራህን ደሴት ምድር ለቀቀ:: ሄሊኮፕተርዋ ከፍ እንዳለች ዶክተሩ ፈጠን ብለው መመሪያ ይሰጡ ጀመር፣

«የቆመው አለት ይታያችሁዋል?»

«ይታየናል!» አሉ አብርሀ ፀሎትና አኖሌ::

አኖሌ በውርጩ መተንፈስ አቅቶታል::

«በሱ ትይዩ ሸጡ ስር ሁለት ጀልባዎች ይጠብቁዋችሁዋል::





የምትሄዱበትን ባህረኞቹ ታጋዮች ያውቃሉ::»

«እናንተስ?» አለ አብርሀ ፀሎት ዶክተሩንና ረዳታቸውን በስጋት መንፈስ እያጤነ፣

«የኛ መንገድ በሌላ አቅጣጫ ነው:: በሉ አሁን ገስግሱ:: መንገድ ላይ አሳ አጥማጆች ከነጠመዋችሁ የእርዳታ ስንዴ እየተሰጠ እንደሆነ ንገሩዋቸው:: በተቀረ ፍጥነት ያስፈልጋችሁዋል»

የወዳደቁ ኮንቴይነሮችና የተበላሹ መኪኖችን አቋርጠው ጭው ባለው በረሃ ላይ የሩጫ ያህል ገሰገሱ:: ውርጩ አኖሌን አሰቃየው:: ውው ... ውው ... የሚል ድምፅ ጆሮው ውስጥ ያምማል:: ነፋሱ የሚፈጥረው ነው:: መጠናቸው ከጤፍ የማይበልጠው ዛጎሎች አየሩን ሞልተውታል:: አኖሌ በአፉ የሚገቡትን ዛጎሎች እየተፋ አይኑን ጨፍኖ እጁን ሲያወራጭ አብርሃ ፀሎት እየጎተተው ይሮጣል...

ከደሴቱቱ ደርቻ ደረሱ:: አልዘገዩም:: እየተንደረደሩ ወደ ባህሩ ጥግ ቀረቡ:: ገደል ነው:: አፉን የከፈተው ጥቁር ገደል ስር ሁለት ከፋይበር ግላስ የተሰሩ ባለሞተር ጀልባዎች በማእበሉ ይጫወታሉ:: አኖሌ በየጀልባዎቹ ላይ ሶስት ታጣቂዎችን አየ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ተዋጊ ታጋዮችን በማየቱ አንዳች ስሜት ሰውነቱን ወረረው::

ባህረኞቹ በትግርኛ ይናገራሉ...

«ምንድነው የሚሉት?» አለው አኖሌ አይኑን ለመግለጥ እየታገለ::

«በሀረጉቹ ላይ ተንጠላጥላችሁ ውረዱና አሸዋው ላይ ዝለሉ ነው የሚሉት» ብሎ የአኖሌን እጅ ይዞ ወረደ::

«ቅደም!» አለው አኖሌን::

በሀረግ ተንጠልጥሎ መውረዱ ለአኖሌ አልከበደውም:: የቡርቃ የልጅነት ጨዋታውን አስታወሰ:: ተከታትለው አሸዋው ላይ ወደቁ::

የባህሩ ሞገድ መነሳት ጀምሮአል:: ሃይለኛ ውርጭ አለ:: ውርጩ አይንና ፊትን ያጠናፍራል:: ባህረኞቹ በትግርኛ ይለፈልፋሉ፣

«ምንድነው የሚሉት አብርሃ?»

«መንገዳችን ለየቅል ነው አኖሌ:: እኔ ወደ መርሳ ተክላይ ነኝ:: አንተ ወደ መርሳ ጉልቡብ:: በል ደህና ሁን ...»

«ምንድናቸው አሁን ያልካቸው?»

«ወደቦች ናቸው።»

ተቃቅፈው ተሳሳሙ።

አብርሃ ፀሎት አኖሌን አቅፎ ጆርባውን እየጠበጠበው፣

«እንገናኛለን! አልረሳህም አኖሌ ... ጀግንነትህን አደንቃለሁ። ለትግላችን ላበረከትከው አስተዋፅኦ ብድር መላሽ ያድርገን ... እመነኝ ... ኤርትራ ብድርዋን ትመልሳለች ...» አለው።

ጀልባዎቹ ጉዞ ጀመሩ።

አኖሌ በአብርሃ ፀሎት ጉንጮች ላይ እንባ ያየ መሰለው። እጁን እያወዛወዘለት «አኖሌ ... አኖሌ ..» ብቻ ሲል ሰማው።

*   *   *

«እንኩዋን ከህዝባዊ ግንባር የባህር ሀይል የኮማንዶ ቡድን ጋር በሰላም ለመቀላቀል አበቃህ» በማለት እጁን ለሰላምታ ከዘረጋለት በሁዋላ «... ከአሁን በሁዋላ በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ ነህ» ብሎ አጥብቆ ጨበጠው። ከሶስቱ ባህረኞች ክላሽንኮቭ የታጠቀው ነበር ይህን ያለው።

«አማርኛ ትችላላችሁ እንዴ?» አለ በመገረም።

«ባህርዳር ተወልጄ ያደግሁ ኤርትራዊ ነኝ» አለው ጥርት ባለ አማርኛ። ቀሪዎቹ ሁለቱ አፋሮች መሆናቸውን አኖሌ ተረዳ። የጀልባዋን መሪና መድፉን የያዙት አፋሮቹ ሲሆኑ አማርኛ የሚችለው ታጋይ ከክላሽንኮቩ በተጨማሪ የመገናኛ ሬድዮም ትከሻው ላይ አንግቦአል። ትውውቁ በዚህ አብቅቶ ጉዞው በፍጥነት ቀጠለ።

«ወደ ደሴቲቱ እንዴት መጠጋት ቻላችሁ? ጥበቃ የለም ማለት ነው?» ሲል ጠየቀ አኖሌ።

«ሌሊቱን በንቃት ይጠብቃሉ። ሆኖም ከደሴቱቱ ዳርቻ ላይ ለመድረስ አንድ ኪሎ ሜትር ሲቀረን የጀልባዋን ሞተር አጥፍተን እየቀዘፍን ነው የተጠጋነው።»

«መንገድ ላይ የመንግስት የባህር ሃይል ቢያገኙንስ?» ሲል ጠየቀ መልሶ።

«ከተከታተሉን እንተኩስባቸዋለን። ካልሆነ ግን እየተደበቅን ነው የምንሄደው። ፍጥነት ስላለን ግን አይደርሱብንም። ሁለት ሰአት ያህል በፍጥነት ያለ እንቅፋት ከተጉዋዝን ግን የእኛ ክልል ውስጥ ስለምንገባ ችግሮች አይኖሩም»

አኖሌ መረጋጋት ጀመረ።





«ይቺ ጀልባ ዩርፕ ውስጥ መዝናኛ ናት» አለ በመገረም ዙሪያ ገባዋን እየተመለከተ።

«የፈረንሳይ ስሪት ናት።» አለ ታጋዩ በኩራት «... መድፍ ግን እዚህ ነው የገጠምንላት። የደርግ መርከቦች አይቋቋሙዋትም። ለቶርፒዶ ተሸካሚ መርከቦችም ሆነ ለአሳሽ መርከቦች ራስ ምታት ነው የሆነችባቸው። አይጥ የገዘሆንን አፍንጫ እየነከሰች ስታሰቃየው ማለት ነው። አየህ ... ደርግ የባህር ሃይሉን ያዋቀረው ለተደራጀ የባህር ላይ ውጊያ ነው። የኛ ውጊያ ስልት ግን በአለም አቀፍ ደረጃ ከተለመዱት ውጊያዎች የተለየና ምንም መከላከያ ያልተዘጋጀለት ስልት ነው። የደርግ መርከቦች አንድ ስናይፐር ጠመንጃ እንኩዋ የላቸውም። እኛን በመቶ ሰላሳ ሚሊ ሜትር መድፍ ሊመቱን ይሞክራሉ። አንዱ የሚባክነው ጥይት ግን አምስት የዚህ አይነት ጀልባ ይገዛላቸው ነበር ...» ብሎ ከልቡ ይስቅ ጀመር።

አኖሌ ስላልገባው ደፋ ቀና የሚለውን የማለዳ ባህር ያስተውል ጀመር። ሃይለኛ ነፋስ ይነፍሳል። የነፋሱ አቅጣጫ በደቡብና በምስራቅ መካከል ሲሆን የደቡብ ሞንሱን ወራት ባህሩ ላይ አነስተኛ ማእበል እንዲከሰት አድርጎታል።

አኖሌ መረጋጋት ይጀምር እንጂ ስጋቱ ጨርሶ አልለቀቀውም። አይኖቹን ግራ ቀኝ ያማትራል። የጀልባዋን ለሆሳስ የሞተር ድምፅና የውርጬን መዚቃ ያዳምጣል። ጀልባዋ ከሁዋላዋ እያደራች የምታልፈው አረፋ ላይ አይኑን ተክሎ ቀጥሎ አደጋ ሊመጣ ይችል ይሆን? እያለ ያውጠነጥን ጀመር። በመሆኑም ፍርሃቱን ለማስወገድ ሲል ጥያቄዎች ጣል ያደርግ ጀመር ...

ጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ እንደተጉዋዙ አንድ ጥቁር ነገር በርቀት ታያቸው ...

«ምንድነው!?» አለ አኖሌ በተረበሸ መንፈስ።

መድፉን የያዘው አፋር በጦር ሜዳ መነፅሩ አሻግሮ ከተመለከተ በሁዋላ በትግርኛ አንዳች ነገር ተናገረ፣

«ምንድነው?» አለ አኖሌ።

«የንግድ መርከብ ሊሆን ይችላል ... ሲቀርብ እናውቀዋለን» አለውና ከዚያም የጦር ሜዳ መነፅሩን ከአፋሩ ታጋይ ተቀብሎ ይመለከት ጀመር። አይቶ ሲያበቃ ወደ አኖሌ መለስ ብሎ፣

«የንግድ መርከብ ነው!» ሲል አረጋጋው።

አኖሌ ተንፈስ አለ። እንደገና መረጋጋት ጀመረ።

«ስምህ ማነው?»

«ዶልፊኖ። ያንተስ?»

«አኖሌ ዋቆ» ካለ በሁዋላ «ትክክለኛ ስምህ ዶልፊኖ ነው?» ሲል ጠየቀው።

«ባህር ላይ ስለምሰራ የሰጡኝ ስም ነው። የቀይ ባህር ዶልፊኖችን እወዳቸዋለሁ። እንደ ኤርትራ ህዝብ የዋህና ጠንካራ ናቸው። አንዳንዴ ከነሱ ጋር እጫወታለሁ» ሲል መለሰለት።

እንደገና ሌሎች ሁለት መርከቦች ብቅ አሉ። አኖሌ መልሶ በጥያቄ ወጠረው። ዶልፊኖ የአኖሌን ስጋት ስለተረዳ፣

«... በባህረ ሰላጤው ጦርነት ምክንያት ይህ መስመር ተጨናንቆአል» ሲል ያብራራለት ጀመር። «ቀይባህር ጉሮሮ ሆናለች። በዚህ ላይ ዘይት የጫኑ መርከቦች ሲመላለሱ ነው የሚውሉት። በዚህ ላይ የስለላ መርከቦች አሉ። የአካባቢው አገሮች አይናቸውን ለሰከንድም ቢሆን ከዚህ ባህር ላይ መንቀል አይፈልጉም። ለእንግሊዞች፣ ለፈረንሳዮችና ለአሜሪካኖችም ቢሆን የቀይባህር የጂኦ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው። ራሺያና አሜሪካ በስለላ የተፋጠጡት እዚሁ ባህር ላይ ነው።»

«ሻእቢያ ብዙ ወደቦች አሉት?» ሲል ጠየቀው።

«አሰን» አለ በኩራት። «አምስት ያህል ወደቦች አሉን። ከራስ ካሳር እስከ ባፅእ ያለው የባህር ዳርቻ ባብዛኛው ሜዳማ ነው» ሲል አስረዳው።

በኮራል የተሸፈነች አንዲት ድንጋያማ ደሴት ታከከው ሲያልፉ አኖሌ አካባቢውን በመደነቅ ማስተዋል ያዘ። አስመራ ላይ ገለፃ ያደረጉለትን የመረጃ መኮንኖችም አስታወሰ፣

«በዚህ ባህር ላይ ጉልበት ያላት ግብፅ ናት። ታግዛችሁዋላች?» ሲል ጠየቀው።

«ጨርሶ!» ሲል ፈጥኖ መለሰ «ግብፆች በቀይ ባህር ላይ የሚሰማቸው የበላይነት ትምክህት ጨርሶ ባዶ ነው። በታሪክ ብቻ ራሱን የቆለለ መንግስት ነው! ድሮ ግብፆች የአባይ ወንዝን አምላክ ከሰማይ በባልዲ የሚደፋላቸው ይመስላቸው ነበር» ብሎ በሳቅ ይጮህ ጀመር።

«የስልጣኔ ምንጭ ናት ግብፅ» አለ አኖሌ በዶልፊኖ ፌዝ ባለመስማማት።

«የባህር ላይ ውጊያን በተመለከተ ግን ጉራ ብቻ ነው





የተሸከሙት!» አለ ዶልፊኖ በግድየለሽነት።

በኮራል ከተሸፈነችው ደሴት ሁለት ኪሎ ሜትር እንደራቁ የዶልፊኖ ፊት በደስታ እያብረቀረቀ፣

«ከእንግዲህ ያለው የባህር ክልል በህዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤሪትሪያ ቁጥጥር ስር ነው። ከማንኛውም አደጋ አምልጠናል። ይህ የኛ ነፃ ባህር ነው» ሲል ጮኾ ይነግረው ጀመር።

ይህን ብሎም የሬዲዮ ግንኙነት ለማድረግ ይታገል ጀመር።

አኖሌ ተመቻችቶ ተቀመጠ። ሞትን እንዳለፉት አመነ። ከደርግ መንግስት ቁጥጥር ውጭ መሆኑን ሲያስብ ማመን አቃተው። በሀሴት ፈነደቀ። ሮዛና አዶናይን አሰባቸው። ወደዳቸው። ተመካባቸው። በደስታ መጮህ አማረው። 'የማንፈፅመውን አንናገርም። የተናገርነውን እንፈፅማለን' ያሉትን አስታወሰ። 'እውነትም እነዚህ ሰዎች Pragmatic! ናቸው' ሲል ለራሱ አንሾካሾከ። መንግስቱ ሃይለማርያም ስለሻእቢያ ሰዎች ሲናገር 'እንደታጠቅነው መሳሪያ ቢሆን ኖሮ ወንበዴዎቹ ገና ድሮ እንደ ሰጉንዋ አንገታቸውን አሸዋ ውስጥ መቅበር ነበረባቸው' ያለውን አስታወሰ። በኤርትራውያን ጥበብና ድፍረት ተደነቀ። ከመደነቅም አልፎ ወገናዊነት ተሰማው። ድንገት የታጋይነት ስሜት አደረበት። ስለመታገል ማሰብ ጀመረ - ለኦሮሞ ህዝብ።

«የኢትዮጵያ ወታደር ነበርክ?» ሲል ጠየቀው ዶልፊኖ።

«አይደለሁም። ሲቪል ሰራተኛ ነው የነበርኩት»

«ይህ ዘመቻ በጣም ተሳካልን። አንዳንድ ጊዜ ከባድ ፈተናዎች ...» ከማለቱ ሰማዩ ለሁለት የተቀደደ እስኪመስል ድረስ ሁለት ሚጎች ቀይባህር ላይ ተወንጭፈው አለፉ።

አኖሌ ህሊናውን ሊስት ምንም አልቀረው። ታጋዮቹ በትግርኛ ይነጋገሩ ጀመር። ጀልባዋን አቀዘቀዙዋት። ወዲያው ግን አቅጣጫ ቀይረው ተፈተለኩ። ዶልፊኖ ወደ አኖሌ ዞሮ፣

«የናንተ ማምለጥ ተደርሶበታል ማለት ነው። ያልተለመደ አሰሳ ነው» ብሎ እየጮኸ ይነግረው ጀመር።

አኖሌ «ቦንብ ይጥሉብን ይሆን? ተመልሰው ይመጡ?» እያለ ይወተውት ጀመር።

አይኑን ወደ ሰማይ ሲልከም ፀሀይ አጥበረበረችው። የሰማዩን ቀለም መለየት አይቻልም። አመድ የተነሰነሰበት ሰማያዊ ብረት ምጣድ መስሎአል።

እንደገና ድምፅ ሰሙ::

ሚጉቹ ወደ ባህሩ ዝቅ ብለዋል::

«አጉንብስ!» ሲል ጮኸ ዶልፊኖ:: «አትደንግጥ! ግንባርህን ብቻ ደብቅ! ግንባርህን ደብቅ!»

አኖሌ የጆሮው ታምቡር የተቀደደ መሰለው::

ሁሉም ቀና አሉ::

በመቶ ሜትር ርቀት ላይ ከባድ ፍንዳታ ባህሩን አናወጠው:: ውሃው ተንቦራጭቆ አለበሳቸው::

አፋሩ ጀልባ ነጂ በከፍተኛ ፍጥነት ከፋይበር ግላስ የተሰራችውን ጀልባ ያስጋልባት ጀመር:: ሰአቱን አየ:: አይኑንም ማዶ ተከለ:: ዶልፊኖ እንደገና ሰማይ ሰማዩን እያየ «አይተውናል ... ግን ኢላማቸውን ስተዋል!» ሲል በጩኸት ተናገረ::

«እንደገና ይመጣሉ?» ሲል አኖሌ ጮኸ ጠየቀ::

«ጊዜ የላቸውም:: ግን እንጃ:: ሁለቱም በምባቸውን አራግፈው ካልሆነ እንደኛዋ ተመልሳ ለመምጣት የሚያስችል ጊዜ ይኖራታል» አለው::

ሆኖም ግን ሁለቱ ሚጉች ሳይመለሱ ቀሩ::

አኖሌና ባህረኞቹ እንደገና በእፎይታ የተነፈሱት የባህሩን ዳርቻ ማየት ሲጀምሩ ነበር::

«በየቀኑ በዚህ መልክ ያስሳሉ?» ሲል አኖሌ ጠየቀ::

ድንጋጤው ጨርሶ አልለቀቀውም::

«የዛሬው ለየት ይላል:: ብዙውን ጊዜ የተረጋገጠ መረጃ ሲያገኙ ብቻ ነው ተዋጊ አይሮፕላን የሚልኩት:: ካልሆነ ሄሊኮፕተሮች ቅኝት ያደርጋሉ:: ለማንኛውም አሁን ከአየር ጥቃት ራሳችንን መከላከል እንችላለን:: የባህር ዳርቻ ሽጦቹ ከሄሊኮፕተርም ሆነ ከተዋጊ ጀቶቹ ሊለዩ አይችሉም::»

ለጥቂት ደቂቃዎች የኤርትራን ምድር ጠረፍ በርቀት እያዩ በኤርትራ ባህር ላይ በዝምታ ተጉዋዙ::

ዶልፊኖ በዚህ ድንገተኛ ክስተት መብገን ፊቱ ላይ እየተነበበ ለራሱ ይሁን ለአኖሌ ባልለየ ሁኔታ፣

«ማሽነፋችን እንደሁ አይቀር!» ሲል ጮኸ::





አኖሌ መልስ አልሰጠውም::

«ቆርቆንዳዎች!» ሲል እንደገና ጮኸ::

ይህን ብሎ ወደ አኖሌ እየተመለከተ «... አይመስሉህም?» ሲል ጠየቀው::

«ምን?»

«ቆርቆንዳዎች ናቸው::»

በመስማማት ራሱን ላይ ታች ወዘወዘ::

ሙቀቱ ይበልጥ እየተሰማቸው መጣ:: ዶልፊኖም የሙቀቱ መጠን ሰላሳ ስምንት ዲግሪ ሴንቲግሬድ መድረሱን ለአኖሌ ነገረው:: የሚያስቅቅ የነፋስ ድምፅ በጆሮዋቸው ያምም ጀመር:: አሸዋ ያዘለ አውሎ ነፋስ እየተነሳም ከኤርትራ ምድር ዳርቻዎች ወደ ባህሩ ይራገፋሉ:: የታጠቁ አፋሮች ከወገባቸው በላይ እርቃናቸውን እንደሆኑ አሳ ሲያጠምዱ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ሲያራግፉ ለአኖሌ ይታዩት ጀመር::

«ሞትን ስንት ጊዜ አመለጥኩዋት?» አለ አኖሌ - ሊሞት የሚችልባቸውን በርካታ አጋጣሚዎች ማለፉን በመገረም እያሰበ::

ባህረኛው ዶልፊኖ ከልቡ ሳቀ::

«እየቆየህ ትለምደዋለህ:: አሸናፊነት እንጂ ተሸናፊነት አይሰማህም:: ብትሞትም ግድ አይኖርህም:: በተለይ ለሀገር ነፃነትና ለምትወደው ህዝብ መታገል የሚሰጠው ውስጣዊ ደስታ አይቻልም::» ካለ በሁዋላ የጦር ሜዳ መነፃሩን ለአኖሌ እያቀበለው፣

«የመርሳ ጉልቡብ ወደብ ማለት ያውልህ! ጉዞአችንን በድል አጠናቀናል!» ሲል ጮኸ::

# «የሰሜኑ ኰከብ»

# ለመጨረሻ ጊዜ ...

## ምእራፍ ዘጠኝ

- 1 -

የኢህአዴግ ድምፅ በእጅጉ አየለ ...

ጆሮዎች ወሬ ፍለጋ ተቀሰሩ፡፡ የኢህአዴግን የድል ዜና ማድመጥ ልብ ያቆም ጀመር፡፡ ሬድዮ ነክቶ የማያውቅ ጭምር ማምሻውን የታጋዮችን ድምፅ ፍለጋ ሬድዮኑን መጉርጉር የጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡ የደርግን ውድቀት አይቀሬነት ማስተባበል ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደረሰ፡፡ የለውጥ አየር ይነፍስ ጀመር፡፡ ህዝቡ የኢህአዴግን የድል ጉዞ በግልፅ መደገፍ የጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡

ገበሬውና ታጋዮቹ ልብ ለልብ ተገናኙ:: ህይወቱን እየከፈለ የሚገስግሰው ተጋዳይ ጉሮሮውን የሚያርስበት ውሀ በቀጥታ ከገበሬው ያገኛል:: ምግብ ይቀርብለታል:: «እንኳዋን መጣችሁልን!» የሚል እልልታ ማድመጥ ጭምር ለታጋዮች እንግዳ አልሆነም:: እንቀላፍተው የከረሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ከአውሮፓና ከአሜሪካ በከፍተኛ ድምፅ ይናገሩ ጀመር:: ደርግ 'ኢህአዴግ ማለት ወያኔ ማለት ነው:: ወያኔ ደግሞ ፀረ-ኢትዮጵያ የወንበዴ ቡድን ነው' የሚል እሪታውን ደጋገመ:: አማራው በትግሬ ላይ ይነሳ ዘንድ በግልፅ እስከመጠየቅ ደረሰ:: ይህን መሰል ቅስቀሳ የያዙ በራሪ ወረቀቶችን በሄሊኮፕተር ለገበሬው ይበትን ጀመር:: ከህዝቡ ግን የድጋፍ ምላሽ ሊያገኝ አልቻለም::

የአማራው ገበሬ ደርግ በሄሊኮፕተር ለሚበትነው በራሪ ወረቀት ምላሽ የሚሰጠው በተለመደው የግጥም ዘይቤው ነበር::

*- መንግስቱ ሲዳከም ሲታየው ድቀት፣*

*አይሉት ሰላምታ አይሉት ናፍቆት፣*

*ይነሰንስ ጀመር ብጣሽ ወረቀት::*

*ደብድቤስ ለመፃፍ የኔም ልብ ይመኛል፣*

*ታዲያ ወረቀቱን ማን ያደርስልኛል?*

*አትጨነቅ ደርጉ አይሸበር ሆድህ፣*

*አትርጭ ወረቀትህን በወዲያ በወዲህ፣*

*እጅን የሚያወጣ እጅ ነው እንግዲህ፣*

*ኢህአዴግ ሳይተውህ እኛም ሳንሰድህ - እያለ ያሳግጥበት ያዘ::*

ሁኔታዎች ለደርግ ጨለሙ:: የድሆች ቁጣ አየለ:: የአርሶ አደሮች ክንድ ጠነከረ:: የተጋዳዮች ግስጋሴ ፈጠነ:: መጪውን ዘመን ለመረዳት ነቢይ መሆን አስፈላጊ አልነበረም ...

* * *

... ሀወኒ ታጋይ ሆናለች::

ለመጀመሪያ ጊዜ በውጊያ የተሳተፈችው ሰሜን ሸዋ ላይ «አንበሳው» ሶስተኛ ክፍለጦር ሲደመሰስ ነበር:: አንበሳው ክፍለጦር በቀለበት ውስጥ የመግባቱ ዜና ታጋዮችን ከዳር እዳር ሲያጨዋጭህ፤ሀወኒ ምክንያቱ ጨርሶ አልገባትም ነበር:: ሀየሎም እየቀለደ አጫወታት፣





«አንድ ተናካሽ አንበሳ አለ:: ደርግ ስሙን ለማይ ጥግ ለቅሎት ነው የኖረው:: ዛሬ ግን እጃችን ላይ ገብቶአል:: አንበሳው ማን እንደሆነ መራኛ ትመሰክራለች::»

«መቼ ነው ውጊያው የሚጀመረው?» ስትል ጉጉትታ ጠየቀች::

«በዚሁ ሳምንት» አላት:: አያይዞም «... ግን በቅድሚያ እኛ አይደለንም ወደ ውጊያ የምንገባው:: የሳሞራ ሀይል ነው የሚገጥማቸው» ብሎ ሲጋራውን ላይ በላይ እየማገ በእልህ ወዲያ ወዲህ ይንጉራደድ ጀመር::

«አብሬ መሆን እፈልጋለሁ» አለች ሀወኒ::

«ትችያለሽ::»

«ግን ሳሞራ ማን ነው?»

«አታውቂውም?»

«እንጃ!»

ሳቀና፣ «አንቺም እንደ ደርግ 'ሀየሎም' የሚለውን ስም የሙጥኝ ብለሽ ይዘሽ ነዋ:: እንዲያውም እዚያም ሄደሽ ሰራዊቱና አመራሩን ማየት አለብሽ:: ኩማንደሩ ሳሞራ የኑስ ይባላል:: የሞዛምቢኩን ታጋይ የመጠሪያ ስም ተውሶ በመታገል ላይ ያለ መሪ ነው:: እንዲያውም እሱን ስትተዋወቂ እኔን ትተይኝና እንገላገላለሁ»

ሲቀልድባት ቆይቶ ማምሺያውን የሳሞራ የኑስ ሰራዊት ወደሚገኝበት ስፍራ ላካት::

ሰሚ ላይ የ203ኛ አየር ወለድ በአውራሮ፣ በመቅደላና በላባደር ክፍለ ሰራዊቶች ሲመታ ነበር አንበሳውና ሌሎች ጥቂት የደርግ ሀይሎች ወደ ሰሜን ሸዋ የተንቀሳቀሱት:: አንበሳው በጉጉፍ በኩል አድርጉ ካራምሽግ አካባቢ ሰፈረ:: አሳቡ የሀየሎምን ክፍለ ሰራዊት ጨፍልቆ አለም ከተማን ለመቆጣጠር ነበር:: በሀየሎም የሚመራው የታጋዮች ሰራዊት ውጊያ ላይ ስለሰነበተ በቀጥታ ከአንበሳው ጋር ብቻውን መላተም አልፈለገም:: አንበሳው ገፍቶ እንዳይሄድና መላወሻ እንዳያገኝ ግን ዘግቶ ያዘው::

ደርግ አጥብቆ የሚመካበት ሶስተኛው አንበሳ ክፍለጦር መራኛ ሲገባ ከጀርባው እንዳይቆረጥ ጥንቃቄ ተደርጉ ነበር:: አጅባር ከተባለ ስፍራ የአንበሳውን ጀርባ የሚጠብቅ ሀይል ተመደበ:: ይህን የተገነዘቡት የኢህአዴግ ኩማንደሮች ሃይላቸውን ወደ አጅባር አንቃነቁ:: አጅባር ያለው የደርግ ሀይል ከተመታ የአንበሳው ጀርባ እርቃኑን እንደሚቀር ተረድተው ነበር:: አሉላ፣ አግአዚና አቃቂ

ክፍለ ሰራዊቶች ወደ አጅባር ተወርውረው በአንድ ቀን ውጊያ የአንበሳውን ጀርባ ጠባቂ ሀይል ድምጥማጡን አጠፉት:: በነጋታው ጉጉፍ የነበረውን የደርግ ሀይል ደመሰሱት:: መራኛ ተከበበ:: አንበሳው ኩቶ መሸሽ በማይችልበት ቀለበት ውስጥ ገባ::

ይህ ሁኔታ የኢህአዴግ ፖሊት ቢሮ አባላትን በከፍተኛ ሁኔታ ሲያስደስት ኰሎኔል መንግስቱ ሀይለማርያም በበኩሉ ድንጋጤና ሽብር ውስጥ ገባ:: ከጭንቀቱ የተነሳም በቀጥታ ከአንበሳው ክፍለጦር አዛዥ ጋር የሬድዮ ግንኙነት አድርጐ 'ለሰራዊቱ ክብር ሲባል አንበሳው ጠንክሮ እንዲከላከል' ተማፀነ:: የደርግ ባለስልጣናት የዚህ ስመጥር ክፍለጦር ስም እንዳይዋረድና በዚህ ምክንያት የአጠቃላይ ሰራዊቱ ሞራል እንዳይነካ ከዳር እዳር ተነቃነቁ:: ሰማይ በአይሮፕላን ተሞላ:: አንበሳው ከአየር ትጥቅና ስንቅ ይዘንምለት ጀመር::

መራኛ በሳቅ ፈነዳች!

የድል ነጥብ ለመያዝ ጭምር ተዘጋጀች:: የሞትና የህይወት ጨዋታው ሊጀመር ሆነ:: አሸናፊው የድል ዋንጫ ያገኛል:: ዋንጫው ላይ የአንበሳ ምልክት አለ:: ጨዋታውን መሰረዝ አይቻልም:: ምርጫው መጋጠም ብቻ ነው:: ኢህአዴግ ግጥሚያውን የመሰረዝ እድል ነበረው:: አንበሳው ግን አንድ እድል ብቻ ነው ያለው - መጋጠም::

በወታደራዊ ጥበብ ሙያው ብቃቱና ተፈጥሮአዊ ጀግንነቱ ተደጋግሞ የተነገረለት፤ ሀንድ ድረስ ተጉዞ የውትድርናን ጥበብ እንደ ውሀ ጠጥቶ መመለሱ የሚወራለት ኰሎኔል ሰረቀብርሃን በሀየሎምና በሳሞራ በሚመሩ ታጋዮች ተከቦአል::

በሳቅ ትጮሀለች - መራኛ!

ያሳቃት የሰማዩ ትርኢት ነበር:: መራኛ የሄሊኮፕተር አይነቶችን አይታ ጠገበች:: መራኛ ስለ ፓራሹት በወሬ ሰምታ እንጂ በአይን አይታ አታውቅም ነበር:: ዛሬ ግን አለፈላት:: ያለምንም ክፍያ ድንቅ ትርኢቶችን ትኰመኩም ያዘች:: ደጅዋን ረግጦ የማያውቀው ኰሎኔል መንግስቱ በጦር ሜዳ ሬድዮ ሲጮህ ጭምር ሰማች::

በኤርትራና በትግራይ ምድር በተደረጉ ውጊያዎች አንበሳነቱን ማስመስከሩ የተነገረለት የእሳት ወንድ ልጅ፤ በገዛ ደረትዋ ላይ እንደ ብቅል ተሰጥቶ ሲንኰራደድ መራኛ በአይንዋ በብረቱ አየችው::

እነሆ የውጊያው ሰአት ደረሰ ...

ፊሽካ ሊነፋ ምንም አልቀረው:: በሳሞራ የኑስ የሚመሩት





ታጋዮች ከአንበሳው ጋር ፊት ለፊት ለመጋጠም እጅግ አስቸጋሪ ገደሎችን መውጣት ነበረባቸው:: እኒያን አስቸጋሪ ገደሎች እየቡዋጠጡና እንደ ጦጣ እየተንጠለጠሉ ለመውጣት ግን የግድ የጨለማ ሽፋን መጠቀም ነበረባቸው:: አለያ በጠራራ ፀሀይ ቢሞክሩት ገደል ላይ የተንጠላጠሉ ታጋዮችን በጥይት መቅለብ ለአንበሳው ቀርቶ ለማንም ቢሆን ተራ ጨዋታ ነበር:: ሌሊቱን ታጋዮቹ ያንጠጡትን ገደሎች ተሻግረው ለውጊያ ዝግጁ ሆነው አደሩ::

ሀወኒ ታሪክ ፀሀፊ ናት ...

በውድቅት የተፈፀመውን አስደናቂ ትርኢት ሁሉ ስትመዘግብ አደረች:: እንደ እሳት ነበልባል የሚንቀለቀለውን የሰራዊት ስሜት ወረቀት ላይ ለማስፈር ቃላት ጭምር አጣች::

«አንችልም አይለም» ብላ ነበር ስለ ሌሊቱ ዘመቻ ማስፈር የጀመረችው::

«... የታዘዙት ግን ምናልባት የማይቻለውን ነው:: መዝሙራቸው ውስጥ 'የማንወጣው ተራራ የለም' የሚል ስንኝ አለ:: የዘመሩትን ሊፈፅሙ ተዘጋጅተዋል:: ኰማንደራቸው ሳሞራ የኑስ ይባላል:: ቀጭን፣ ጠይም ነው:: ተግባቢና ትህትና የተላበሰ:: ከተራ ተዋጊዎቹ ጋር አፍለአፍ ገጥሞ ሲመካከር በመካከላቸው የአዛዥና ታዛዥ ግንኙነት አልነበረም::

እነሆ ባልተጠበቀ መንገድ ዝነኛውንና ጉረኛውን አንበሳ ለመግጠም መክረው አብቅተዋል:: ጥርሱ ላይ ያለውን ደም በምላሱ ለመጥረግ እየታገለ ዙሪያ ገባውን በጥርጣሬ የሚያስተውል አንድ ግዙፍ አንበሳ መራኛ ሜዳ ላይ ተጋድሞ ይታየኛል::

ሲነጋ አንበሳው ወዮለት!

ባልጠበቀው አቅጣጫ ታጋዮቹ ገደሉን እየወጡት እንደሆነ ማን በነገረው!? ሲገጥሙት የተዘጋጁት ቀጫጭን ታጋዮች ርስበራስ እንደሚዋደዱ! መዋደዳቸው ደግሞ ሀይልና ብርታት እንደሚሰጣቸው ማን ባጫወተው!?

«... ሰሜን ሸዋ ላይ ጨለማ ወድቆአል:: ጨለማው ግን ከወትሮው ይለያል:: አንድ ምስጢራዊ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት ሌሊት ነው:: ነገ ማለዳ የአማራው ምድር ሰማይ በጥይት ይታረሳል:: ከባድ ግጥሚያ ይደረጋል:: ሲነጋ ዝነኛው አንበሳ ወዮለት:: የሚዋረድበት ሰአት ደርሶአል:: የማስመሰያ ለምዱ የሚገፈፍበት ደቂቃ ሞልታለች:: የአንበሳው ለምድ ሲገፈፍ ከውስጥ አንድ ባህታዊ መገኘቱ አይቀሬ ነው - የቀበሮ ባህታዊ::»

በነጋታው ታጋዮቹ በስድስት ሰአት ውጊያ የአንበሳውን ክፍለጦር ወታደሮች ከነ መሪያቸው ማረኩዋቸው:: በዚያን እለት አስራ ዘጠኝ የደርግ ብርጌዶች ተደመሰሱ:: ይህ ሁሉ ሲፈፀም ሀወኒ እዚያው ነበረች:: ማምሻውን ታዲያ ከሳሞራ ጋር ሻይ እየጠጡ ጥቂት አወጉ፤

«ሁላችሁም ተመሳሳይ ናችሁ ልበል?» አለችው::

«የአላማው አስፈፃሚዎች ነን፤ ሀወኒ» አላት::

አያይዞም ጥቂት ቃላትን አከለ፤

«አንቺም እኮ እንደኛው ነሽ::»

* * *

ሀወኒ ታጋይ ናት ...

ሰራዊቱን ተከትላ ድል አብሳሪ መሆንዋን ቀጠለች:: ምስል ቀረፃውም ሆነ ለሬድዮ ጣቢያው የውጊያ ሪፖርት የመላኩን ተግባር ወድዳዋለች:: ይህን መሰል ተግባር በማይከናወንበት ጊዜ ደግሞ ወደ ሰራዊቱ እየገባች የጦርነት ገጠመኞቻቸውን ትሰበስባለች:: ታጋዮቹ ቢጋለ የትግል መንፈስ ያወጉዋታል:: እኒያን ስሜቶች በጥንቃቄ ትመዘግባቸዋለች:: የጀግንነት ታሪኮችን እንደተራ ገጠመኝ ሲያወጉዋት ተመስጣ ታዳምጣቸዋለች:: አንዳንዴ በግራሚ ደንገዞ ማስታወሻ መያዙን ጭምር ትዘነጋዋለች:: ያን የጀግንነትና የመስዋእትነት ታሪክ ለአለም ሁሉ የማሳወቅ ሃላፊነት እስዋ ላይ የወደቀ ሆኖ ጭምር ይሰማታል::

ሀወኒ ራስዋን እንደ ተራ ታሪክ መዝጋቢ ብቻ አትቆጥርም:: ባለአላማ መሆንዋ በጥልቀት ይሰማታል:: ውጊያዎች ሲደረጉ ከግንባር ቀደም ታጋዮች ጋር ለመግባት ትሽቀዳደማለች:: በርግጥ በውጊያዎች ሁሉ ይህን እንዳትፈፅም ብዙውን ጊዜ ሀየሎም እንቅፋት ይሆናል:: ይነታረካሉ! ስሜታዊ ሆና እሪታዋን ታቀልጠዋለች:: ወደ ባህርዳርና ጉንደር ግን እንደናዳ ሀየሎም ያስገድዳታል:: ወደ ባህርዳርና ጎንደር ግን እንደናዳ ከሚወረወሩት የኤርትራና የኢትዮጵያ ታጋዮች እኩል ለመግባት ችላለች:: ሀየሎምን በቅርብ ማወቅ ብቻ ብቁ ታሪክ መፃፍ እንደማያስችላት ስለተረዳች ትኩረትዋ ወደ ሰራዊቱ ሆኖአል:: ወታደራዊ ሚስጢሮችን ጭምር ታውቅ ዘንድ ተፈቅዶላት ከአመራሩ አልተለየችም:: ያን ማወቅዋ ብቻውን ግን አላረካትም:: እንባና ሳቅ እያቀላቀለ የሚያስደንቅ ታሪክና ገጠመኝ የሚገኘው ተራ ተጋዳዮች አካባቢ መሆኑን ትገነዘባለች:: ከእኒያ መስዋእትነትን በፈገግታ ከሚቀበሉት ታጋዮች ጋር መዋልና መጉዋዝ የፈጠረባት





የእርካታ ስሜት በምንም ሊተካ የማይችል እየሆነ ሄደ:: ብዙዎቹ 'ሀወኒ - ጉዋል ኦሮሞ' እያሉ ነው የሚጠሩዋት:: እንዲህ ሲሉዋት እንዳች የማታውቀው የብርታት ስሜት የሰራ አካልዋን ይወረዋል:: እንዳይደክማት ይንከባከቡዋታል:: ከምግባቸው የተሻለውን ያቀርቡላታል:: ያከብሩዋታል:: ጥይት እንዳይመታት ይጠነቀቁላታል:: ሀወኒ ግን ያንን እንዳያደርጉ ታስቸግራቸዋለች:: ስታስቸግር ይስቁባታል:: አንድ ቀን አንዱ ታጋይ እስከ አንገቱ ጥይት ያዘለ ብሬይኑን ከአንገቱ አውልቆ «እንኪ ያዢ» አላት:: በወኔ ተቀበለችው:: ግን አልቻለችም:: በአፍጢምዋ ልትደፋ ነበር:: በሳቅ አውካኩ ታጋዮቹ:: «ወታደራዊ ስልጠና ስላልወሰድሽ አካላዊ ጥንካሬ የለሽም:: የመንፈስ ጥንካሬሽ ግን ከኛ ይበልጥ እንደሆነ እንጂ አያንስም» እያሉ ሲያጫውቱዋት በብስለታቸው በእጅጉ ትደነቃለች::

ሀወኒ ... ታሪክ ፀሃፊና ተጋዳሊት ሆናለች::

የታጋይነት ክብር ሞቆአታል:: ታጋይ ንብረት የለውም:: የግል ኑሮ የለውም:: ለራሱ አይኖርም:: ታጋይ ታጋሽ ነው:: ታጋይ አይዋሽም:: ታጋይ ጉረኛና ቁጡ አይደለም:: በታጋዮች መካከል መበላለጥ የለም:: ታጋይነት ተፈጥሮአዊ ውበት ነው:: ታጋይነት አላማ ነው:: ባማረ ግንብ ውስጥ የራስን ደስታ ፈጥሮ መኖር ማለት አይደለም - ታጋይነት:: ተጋዳላይ ለህዝብ ፍቅር አለው - ገደብ የሌለው ፍቅር::

ወደ ባህርዳር ገስግሰው ከገቡት ታጋዮች ጋር አብራ የገባችው ሀወኒ በዚያ ዘመቻ ትእግስትን ነበር በዋነኛነት የተማረችው:: የኢህአዴግን አላማ በቅጡ ያልተገነዘቡ! እለያም በደርግ ካድሬዎች የተደራጁ የከተማው ነዋሪዎች በድል አድራጊው የኢህአዴግና የሻዕቢያ ሰራዊት ላይ የስድብ፤ የርግማንና የድንጋይ ዶፍ ሲያወርዱ አልተሸማቀቀችም:: 'እነዚህ ሁሉ ነገ ለዚህ ትግል ይሰዋሉ' ስትል ለራስዋ አንሾካሾከች:: ታጋዮች ከታንክ ጋር ተጋፍጠው ድል ከጨበጡ በሁዋላ እንገታቸውን ደፍተው! ጠመንጃዎቻቸውን አዘቅዝቀው ተሸናፊ ሲመስሉ ሀወኒ ተመካችባቸው:: አይንዋ እንባ ሞላ:: ሀወኒ እልፎ እልፎ ራስዋን እንደ ታሪክ ፀሀፊ ብቻ ታያለች:: ራስዋን ዳር አኑራም በታጋዮች ድርጊትና ባህርያት ትመሰጣለች:: ታጋዮችን 'እነርሱ' እያለች ትጠራለች - ራስዋን እንደ ፈጣሪ ገንጥላ አውጥታ:: ታዲያ ሀላፊነቱ ይከብዳታል:: ይህን መሰል የጀግንነት ታሪክ በኢትዮጵያ ቀርቶ በአለም እንኩዋ አልፎ አልፎ የተፈፀመና ሊፈፀም የሚችል መሆኑን ታውቃለች:: ይህ በዝርዝር መፃፍና

ለቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ እንዳለበት ይሰማታል::

ባህርዳር በተያዘችበት እለት ለሀየሎም አንድ ጥያቄ አቀረበችለት፤

«መታገስ ይከብዳል መሰዋት?» የሚል::

አጭር መልስ ሰጣት፤

«መታገስ!»

ይህን ብሎ ፈገግ አለ - ደብዛዛ ፈገግታ::

ማብራሪያ አልጠበቀችም:: አልፈለገችምም:: ሀየሎም ልክ ነው::

ሀወኒ ጉዞዋን ቀጥላለች ...

የኢህአዴግ ሰራዊት ወደ ታሪካዊትዋ ጎንደር ከተማ ያደረገው ጉዞ ታሪካዊ ነበር የሆነላት:: አንድ አመት ታስራ የስርአቱን ክርፋት ያየችው በጎንደር ከተማ ነበርና ድርብ ስሜት ነበር ያደረባት:: በመምህርነት ወደቆየችባት የጎንደር ከተማ የምስል መቅረጫ መሳሪያዋን አንግባ ከግንባር ቀደም ታጋዮች ጋር ወደመሀል ከተማ ስትዘልቅ ህዝቡ በከፍተኛ እልልታ ነበር ኢህአዴግን የተቀበለው:: የእናቶች ለቅሶ በርክቶባት የከረመችው ጎንደር፤ እልልታዋን አቀለጠችው:: የቴዎድሮስ ከተማ ጎንደር፤ ጥንታዊ ብትሆንም ተረስታና ተጥላ የቀረችው ጎንደር፤ በደርግ በትር ክፉኛ የተቀጠቀጠችው ጎንደር፤ አያሌ ታጋዮችን ያፈራችው ጎንደር፤ ልብ በሚነካ የእናትነት መንፈስ ነበር ድል አድራጊውን ሰራዊት የተቀበለችው:: ይኸው ተሰምቶት ነው መሰል የኢህአዴግ ሬድዮ ገና በማለዳው፤

«መላኩ ተፈራ የእግዜር ታናሽ ወንድም፤

የዛሬን ማርልኝ ሁለተኛ አልወልድም»

የሚለውን ጉደኛ የጎንደር የእናቶች እንጉርጉሮ ያስታወሰው::

በዚህ መቸ አበቃ:: «ጎንደር እንዳሻሽ ውለጂ» ሲል ኢህአዴግን ወክሎ አወጀ::

ሀወኒ ሰራዊቱን ተከትላ ጎንደር ገባች::

ኩንጉ ጫማዋ ተስማምቶአታል:: «ጉባኤ» በሚል መጠሪያ የሚታወቀው ሱሪና ሸሚዝዋ አምሮባታል:: ማማር ታጋይ መሆን ነውና የታጋይነትን መልክ አላብሶአታል:: ባለማንገቻ ሬድዮ ትከሻዋ ላይ አንጠልጥላለች:: ሽጉጥ ታጥቃለች:: የታጋይነትን የአመለካከት





መንፈስ ሰንቃለች:: አላማ አላት:: ባለአላማ ነች:: የቀመችለትን አላማ በጥልቀት ታውቀዋለች::

ምን ቀረ? ምንም!

ምስል መቅረጫዋን አንግባ እንደ ናዳ ከሚወረወሩት ታጋዮች ጋር እንደወፍ በረረች:: ናዳዎችና ወፎች:: አእዋፋትና ናዳዎች ...

የጎንደር ተማሪዎችና እናቶች በአስፋልቱ ዳር ግራና ቀኙን ተገጥግጠው በጭብጨባና በእልልታ ታጋዮችን አጀቡዋቸው:: ታፍኖ የኖረው የጎንደር ህዝብ ስሜቱ ገንፍሎ ከድል አድራጊ ታጋዮች አላማ ጋር በመንፈስ ተዋሃደ:: በጉዞ ላይ ሳሉ ድንገት ከህዝቡ መካከል ስምዋ ሲጠራ ሰማች:: ተማሪዎች ነበሩ:: ተማሪዎችዋ! አወቁዋት! ይንጫጩ ጀመር፤

«ሀወኒ!»

«ቲቸር ሀወኒ!»

«ሀወኒ!»

አንድ እርምጃ በተራመደች ቁጥር ስምዋን የሚጠሩ ተማሪዎች ቁጥር ይጨምር ጀመር:: «የታሪክ መምህራችን ነበረች፤ ታስራ ነበር» የሚሉ ንግግሮችን ጭምር ጆሮዋ ጠለፈ::

ሰራዊቱን ተከትላ ገሰገሰች ...

- 2 -

«ሀወኒ ... የምስራች!»

«ምስር ብላ ... ምን ተገኘ?»

«ከሶስት ቀን በሁዋላ ሰራዊታችን የአባይን ወንዝ ተሻግሮ የወሊጋን ምድር ይረግጣል!

ጩኸትዋን ለቀቀችው::

ፊትዋ ላይ የሚረጨውን የደስታ ርችት ሲያዩ ሀየሎም፤ ራሱን በሀወኒ ቦታ አኑሮ ይደሰት ጀመር:: ከዘመቻ ቴዎድሮስ ቀጥሎ በሁለተኛው ረድፍ በተያዘው በዚህ ዘመቻ ወሊጋንና የኢሉባቡርን የተወሰኑ ክፍሎች በአጭር ጊዜ ነፃ ለማውጣት እንደታሰበ አጫወታት:: ይህም አዲስ አበባን ለመክበብ እንደሚያስችል ጠቆማት:: ሶስተኛው ደግሞ ዘመቻ ዋለልኝ በሚል ስያሜ እንደሚጠራና ከደሴ እስከ ደብረብርሃን ያለውን ሃይል በሙሉ እንደሚጠርግ ገልፆላት ሲያበቃ የመጨረሻውን አዲስ አበባን ለመያዝ

የሚደረገውን ዘመቻ ለማካሄድ ጭምር አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መደረጉን አወጋት:: ይህን መሰል ተከታታይ ዘመቻ ማካሄድ የደርግ ሃይል እንደገና ለመደራጀት በቂ ጊዜ እንዳይኖረው እንደሚያደርግ፤ ዋናው ሃይል በዚህ መልኩ መመታቱም አዲሳባ ላይ ምንም ግጭት እንዳይደረግ ያግዛል' ሲል አብራራላት::

በዚህ እለት አግአዚ ኦፕሬሽንን በተመለከተ ሊያወጋት ቃል ገብቶላት ስለነበር ወቅታዊውን ሁኔታ ተጨዋውተው ሲያበቁ ሀወኒ ዋና ወዳለችው ርእሰ ጉዳይዋ ሰተት ብላ ገባች፣

«ዛሬ ጥቂት ፋታ ያለህ ይመስለኛል - ስለ ኦፕሬሽኑ ግለፅልኝ» አለችው::

ሀየሎም ርእሱ በመነሳቱ ያለመደሰት ስሜት ታየበት:: የቀጣዩን ዘመቻ ዝግጅት አጠናቀናል:: በርግጥም ዛሬ ፋታ አለው:: ቢሆንም የቆየውን የአግአዚ ኦፕሬሽን ታሪክ አንስቶ የመተረክ ስሜትና ወኔ አልነበረውም:: ጊዜው እንዲሸጋገርለት ፈለገ:: ሀወኒ ግን ገና ሀሳቡን ሲያነሳ ቡራ ከረዩ አለች::

እንደማትለቀው ሲያውቅ ግን በማዘዣ ጣቢያው ለጊዜው በተዘረጋው አልጋ ላይ ጋደም ብሎ ሲጋራውን እየሳበ አይኖቹን ወደ ጣራ ሳከ፣

«ከየት ጀምሬ እነግርሻለሁ? ዘመቻው ከባድ ነበር:: በደርግ ቁጥጥር ስር የወደቁ እስረኞችን ሰቆቃ መቼም ታውቂዋለሽ:: የአብዛኞቹ መጨረሻ ሞት ነበር:: ከመገደላቸው በፊት እጅግ አስከፊ በሆነ ኢሰብአዊ ሁኔታ እንዲሰቃዩ ይደረግ ነበር:: ይህን ጉዳይ ድርጅታችን በጣም ሲያስብበት ከቆየ በሁዋላ ነው አግአዚ ኦፕሬሽን የታቀደው» ብሎ ዝም አለ::

«ዋና አላማው ምን ነበር - የአግአዚ ኦፕሬሽን?» ስትል ጠየቀችው::

«.. ሀወኒ እባክሽ ይህን ሌላ ቀን ላጫውትሽ:: ዛሬ ስለ አይበገሬዎቹ የአርሲ ኦሮሞዎች ተርኪልኝ ...»

ይህን ሲላት ጮኻ ከተቀመጠችበት ተነሳች

«እውነቱን ነው ሀወኒ:: በጣም አስቸግረሺኛል»

«አላስቸገርኩህም» ብላ አንቃ ያዘችው «... ሁላችሁም ቢሆን ያለፋትን የትግል ታሪኮች የምታውቁትን ያህል ለመናገር ዝግጁ መሆን አለባችሁ:: አለያ ይህ የትግል ታሪክ አፈታሪክ ሆኖ ነው የሚቀረው» ካለች በሁዋላ፤ የማስታወሻ ደብተርዋን እያመቻቸች፣





«... ለመሆኑ የአክሱም ሀውልት በዚያን ዘመን እንዴት ሊቆም የቻለ ይመስልሀል?» ስትል ጠየቀችው::

መልስ አልሰጣትም::

እስዋ ቀጠለች፣

«... ማንም ቢሆን እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይችልም:: መላ ምት ነው ያለው:: 'በገዘሆን ተገነቶ' የመሳሰሉ:: ከአክሱማውያን የተገኘ የፅሁፍ ማስረጃ የለም:: አርኪዮሎጂስቶች ሲቆፍሩ የገዘሆን ጥርስ አገኙ:: ገዘሆን ገነቶ አቆመው የሚለውን አመኑ:: የአፈታሪክን አደጋ ልታጤነው ይገባሀል ...»

ሲጋራውን እየማገ ትረካውን ቀጠለ፣

«... እንዳልኩሽ ድርጅታችን ይህን ጉዳይ ሲያስብበት ቆየ:: በእስር ቤቱ የኛ የከተማ አባሎች ቢኖሩም የተማረኩ ታጋዮቻችን፤ ባብዛኛው ደሞ ሲቪሎች ይገኙ ነበር:: ስለዚህ እርምጃው በቅድሚያ በሺህ የሚቆጠሩ እስረኞችን ህይወት ለማዳን እንደሚያስችለን፤ በሁለተኛ ደረጃም ትልቅ የፖለቲካ ድልን የሚያቀዳጀን እንደሆነ ተረዳን:: ጊዜውን ከመወሰናችን በፊት ግን አንድ ሁለት የሙቶ የሚሆኑ ኮማንዶዎችን አሰለጠንን:: ከዚያም እስረኞቹ ያሉበት ወህኒ ቤት አቀማመጡ ምን እንደሚመስል፣ እንዴት ወደዚያ ዘልቆ መግባት እንደሚቻል፣ የምሽጉን ጥንካሬ፣ የተኩስ አቅሙንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ማጥናት ጀመርን:: ጥናቱም በሁለት መንገድ መካሄድ እንዳለበት ወሰንን:: አንደኛ ከውስጥ አባሎቻችንና ከደርግ ከተማረኩት በመቀሌ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ እስረኞች መረጃዎችን ማግኘት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የኛን ታጋዮች አመሳስለን ወደ ከተማ በማስገባት መረጃ ማቀናጀት ነበር::

በዚህም መሰረት ሁለት ታጋዮች መለመልኩኝ:: ባግባቡ ጉዳዩን እንዲያጠኑ ካደረግሁ በሁዋላም ዝግጅት እንዲደረግላቸው ተደረገ:: የማገዶ እንጨት ይዘውና አርሶ አደር መስለው እንዲገቡ ነበር ያሰብነው:: በተሰጣቸው ተልእኮ መሰረትም ያላንዳች መሳሪያ የመርዝ መድኃኒት በቴትራሳይክሊን ማሸጊያ ውስጥ አስገብተን ሰጠናቸው:: ምናልባት ቢያዙ ምስጢር እንዳያወጡና ራሳቸውን እንዲሰው ነው ይሄ የተሰጣቸው::

ዋናው ችግር ደርግ መቀሌ እንዳትያዝ ለመከላከል ሶስት ዙር የውጊያ ምሽግ ነበር ያሰራው:: ሶስቱም ዙሮች ደግሞ ኬላዎች አሉዋቸው:: በየኬላውም ፍተሻ መደረግ አለበት:: ስለዚህ በቀላሉ መስረግ ያዳግታል:: ይሁንና ሰዎቻችን ያላንዳች ችግር እንጨት ተሸክመው አህያቸውን እየነዱ ገቡ:: ከገቡ በሁዋላ ለአራት ቀናት

ከተማዋን ባጠቃላይ፣ በተለይ ደግሞ የጠሩን አሰፋፈር፣ የተኩስ አቅሙን፣ መጠኑንና መግቢያ መንገዶቹን በዝርዝር አጥንተው መጡ::

እንደመጡ የእነሱን ቃል ተቀብዬ አንድ አይነት ስእል ወሰድኩኝ:: ከዚህ በሁዋላ በአሸዋ ገበታ መሬት ላይ ቅርፁን እንዲሰሩ አደረኩዋቸው - የቤቶቹን ቁጥር ሳይቀር በጭቃ ሰሩልኝ:: ቤቶቹን ለመስራት ወዳንድ ወር ያክል ፈጀብን:: በጠቅላላ ከሃምሳ በላይ ቤቶች ነበር የሰራነው:: በመጨረሻ ልክ የመቀሌ ወህኒ ቤትን የሚመስል ቅፅር ግቢ ሰራን::

ይህን ሰርተን ካጠቃለልን በሁዋላ ስልጠና ጀመርን:: በመጀመሪያ የአካል ስልጠና ነበር ያካሄድነው - ለሁለት ሳምንት:: ከዚያ በሁዋላ ጠላት እንዳለበት በመቁጠር ትንሽ ጄኔሬተር ተጠቀምን:: እንግዲህ በየጠላት ምሽግ መብራት (የአምፖል) እንዲኖር አደረግን ማለት ነው:: ቀጥለን ደግሞ የእስረኞቹን አምሳያ በየቤቱ እንዲቀመጥ አደረግን:: ልምምዱ የሚደረገውም እስረኞቹን ሳንጐዳ በሌሊት እንዴት ጠላትን በአጭር ጊዜ ለይተን በማጥፋት እስረኞቹን ነፃ እንደምናወጣ ነበር:: ይሄ የውስጡን ስራ የሚመለከት ነው:: ወህኒ ቤቱ ከተማዋ ውስጥ ቢሆንም ከከተማዋ ዙሪያ ያሉት ሶስት ዙር ምሽጐች ነበሩ - በጣም አደገኛ መሰናክሎች:: እነዚህን ሶስት ምሽጐች በርጋታ እንቅስቃሴ ማለፍ ነበረብን:: እንዴት?

ይህን ጉዳይ ስንመረምር በየምሽጉ ከሀያ እስከ ሰላሳ ሜትር ርቀት ድረስ ክፍት ቦታዎች እንዳሉ ተረዳን:: ክፍተቶቹ ቢለያዩም ሃያውን ሜትር እንዴት እናልፋዋለን የሚል ጥያቄ አነሳን:: ልምምዱን ልምምድ ማድረጉን ነበር በቅድሚያ የመረጥነው:: ልምምዱን ጀመርን:: ሳይነቃባቸው ክፍተቱን ማለፋቸውንና አለማለፋቸውን የምናረጋግጠውም በሁለት ሜትር አይናቸውን የተጨፈኑና በድምፅ የሚከታተሉ ታጋዮችን እያስቀመጥን ሰራዊቱ በዝግታ በሰልፍ እንዲገባ በማድረግ ነበር:: ይህ እንደተሳካላቸውም በሃምሳ ሜትር፣ በአርባ፣ በሰላሳ አምስት ሜትር ርቀት በተቀመጡ ሁለት ጉዋዶች መሀል እንዲያልፉ በማድረግ መፈፀም መቻሉን አረጋገጥን::

ቀጥለን ደግሞ ሰራዊቱ ወደ ውስጥ ከገባ በሁዋላ እንዴት ይከፋፈላል? እንዴትስ ማጥቃት ይጀመራል? ማጥቃቱስ ባንዴ እንዴት ይጀምራል? የሚለውን መፍታት ነበረብን:: በዚህም ረገድ ያንድ ወር ያህል ልምምድ ከተደረገ በሁዋላ የመጨረሻ ሙከራ አድርገን ተልእኮአችንን በአስራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ልናከናውን እንደምንችል አረጋገጥን::





ይህ ሁሉ ልምምድ ግን በምስጢር ይካሄድ ስለነበረ ከኮማንደሮቹ ከፊሉ 'ይሄ የከተማ ጥላን ነው፤ በቀርበ የሚጠቃ ከተማ አለ ማለት ነው ሲሉ አንዳንዶቹ ደሞ 'ይሄ የሚመስለው ሆስፒታል ነው:: ያለብንን የመድኃኒት እጥረት ለማቃለል ሆስፒታል ውስጥ ገብተን እንድንወስድ ስለተፈለገ ነው ይላሉ:: እኛም ስወደፊቱ የከተማ ውጊያ ልምድ ለማዳበር ያህል የሚደረግ ትምህርታዊ ልምምድ ነው በሚል ጓዶቹን እንሸፋፍንባቸው ነበር::

ከዚህ ሁሉ በሁዋላ ግን አንድ ከባድ ችግር ደግሞ ፊታችን ተደቀነ:: ይኸውም በመቀሌ 119ኛ ብርጌድ የሚባል ሃይል ሲኖር የዚህ አባል የሆነ የ16ኛ ክፍለ ጦር ተወርዋሪ ጦር አለ:: ወህኒ ቤቱ የሚገኘው ይህ ጦር ከሚገኝበት ብዙም አይርቅም:: በዚህ ላይ ከተማዋ ዙሪያ ከአስር ሺህ በላይ ሰራዊት አለ፣ ቢኤምቾች፣ መድፎች፣ ታንኮች፣ ዙ-23ቶች አሉ::

ከባድ ፈተና!

ሁኔታውን መገምገም ነበረብን:: የደረስንበት ድምዳሜም አንደኛ ውጊያው በወህኒ ቤቱ ብቻ ከሆነ ምንም እንኳ ወህኒ ቤቱን ተቆጣጥረን እስረኞቹን ብናወጣቸውም ጠላት በሰው የተኩስ አቅም የበላይነት በመጠቀም ተኩሶ ሊፈጅብን ይችላል:: ሁለተኛ ገደ ውጊያው በወህኒ ቤቱ አካባቢ ብቻ ከሆነ ያ ተወርዋሪ የሚባለው አንድ ብርጌድ ቶሎ ደርሶ ውጊያው ከመጠናቀቁ በፊት አለያም ውጊያው እንደተጠናቀቀ ሊደርስብን ይችላል:: በዚህ የደርግ አመራር አካል እዚያው የሚገኘው - የኮር አዛዡና የትግራይ እዝ አዛዥ ሳይቀሩ ይህን ጥቃት ስንሰነዝር የነርሱ አንድ ቦታ መሆን ደግሞ ለአመራር ይመቻቸዋል:: ስለዚህ እንደመፍትሄ በእቅድ ያስቀመጥነው 'ጠላት የመቀሌ አካባቢን እንደምናጠቃ ማወቅ የለበትም' የሚል ነው:: ስለዚህ ጠላት ሌላ ቦታ የምናጠቃ መስሎት ተወርዋሪ ሃይሉን ወደ ሌላ ቦታ የሚያንቀሳቅስበትን ሁኔታ መፍጠር ነበረብን:: ስለዚህም ውጅራት የምትባለዋን ስትራቴጂክ ቦታ ማጥቃት ከጀመርን ያ መቀሌ ያለው ብርጌድ ውጅራት ያለው ሃይሉ እንዳይደመሰስበት ማንቀሳቀሱ አይቀርም:: ይህም ከሆነ ወህኒ ቤቱን ስናጠቃ በተወርዋሪነት ገብቶ ስራችንን የሚያደናቅፈው ሃይል አይኖርም:: ሁለተኛም ደግሞ ጥቃታችን በወህኒ ቤቱ ላይ ብቻ መሆኑ ቀርቶ በመቀሌ ዙሪያ ባንዣራዊነት በጣም ቁልፍ የሆኑ ቦታዎችን በማጥቃት የማታለል ውጊያን ማካሄድ ይሆናል አልን:: ይህን አይነቱን ውሸንብር ከፈጠርን በኋላም ወህኒ ቤቱን ጥሶ እጥቅተን ለመውጣት እንችላለን የሚል ድምዳሜ ላይ ደረስን::

ሌላው ችግር እስረኞቹን በሰላም ሰስቱን ዙር የጥበቃ ምሽግ

አሳልፎ ማውጣቱ ነው:: ይህን ለማሳካት የኮማንዶ ሃይላችን በክፍተቶቹ በፀጥታ ተጉዞ ወህኒ ቤት መድረሱን ካረጋገጥን በሁዋላ በማድፈጥ መሸጉ የያዘውን ሃይል በማጥቃት ለእስረኞቹ መውጪያ የሚሆን ቀዳዳ ከፍቶ መቆየት አለበት የሚል መፍትሄ አስቀመጥን:: በመጨረሻም የጥቃት እንቅስቃሴያችንን በሙሉ ካቀናጀን በሁዋላ በተለያዩ አቅጣጫዎች እንቅስቃሴ አደረግን::

በኔ ግንባር ያለው ሃይል ሶስት ቀን ያክል እየተደበቀ መጉዋዝ ነበረበት:: ይሁንና በመካከሉ ትልቅ ችግር ገጠመን - የምስጢር ጉዳይ:: አንድ ከመቀሌ እንዲረዳን ያመጣነው ልጅ የልምምዱን ቦታ እንዳየ የሚጠቃው የመቀሌ ወህኒ ቤት መሆኑን አወቀ:: ታዲያ አንድ ቀን ከተጉዋዝን በሁዋላ ለኮማንዶዎቹ አሁን የምንሄደውና ልምምድ ያደረጋችሁትም የመቀሌ ወህኒ ቤትን ለመያዝ ይመስለኛል:: ስለዚህም ሀሳብ ልስጣችሁ ብሎ (የእሸዋ ገበታ) ሲሰራ ልክ ያቺን ለልምምድ በሳር የተሰራችውን የመቀሌ ወህኒ ቤት ቁጭ አደረጋት:: ታጋዩ ይሄኔ መቀሌ ወህኒ ቤትን እንደምናጠቃ ተረዳ:: ይኸኔ እኔ በአጋጣሚ ስገባ የተሰራውን እየሁ:: አንድ የመቶ ያክል ናቸው የተሰበሰቡት:: በጣም ደነገጥኩኝ:: ሁለት ቀን ያክል ሲቀረን ነው ይህ የሆነው:: ሌላ አማራጭ ስላልነበረኝ አንድዋ የኮማንዶ የመቶ በሌላዋ እንድትታሰር አደረግሁ:: መንገድ ላይ ሳለን 'እነዚህ ወንጀለኞች ናቸው! ብዙም ችግር ፈጥረዋልና አታነጋግሩዋቸው በእስር ይቆዩ' ስል መመሪያ ሰጠሁኝ:: በዚሁ መሰረት ቡድንዋ መቀሌ አጠገብ እስክንደርስ ድረስ ታስራ ነው የሄደችው::

እስቀድመን ስለደረስን ሌሊቱን እዚያው መቀሌ አጠገብ ካለች በረሃ አሳለፍን:: ከዚያም ልክ ከጠዋቱ ሶስት ሰአት አካባቢ ከውጅራት ጋር በሬዲዮ ተገናኘሁ:: ያ ተወርዋሪ ሃይል ውጅራትን ለማዳን እንቅስቃሴ መጀመሩን ሰማሁ:: በጣም ተደሰትኩ::

በመጨረሻ ከቀኑ ስምንት ሰአት ላይ የታሰረችውን መቶ ትጥቁዋ እንዲመለስላት አድርጌ ለሰራዊቱ መግለጫ ሰጠሁኝ:: ተልእኮአችን ምን እንደሆነና በልምምዱ መሰረትም እንዴት መስራት እንዳለብን፣ መቼ እንደምንሰራው፣ ምን አይነት ሁኔታ እንዳለ፣ ተወርዋሪው ሃይል ከመቀሌ የወጣልን መሆኑንና በዲሲፕሊን መስራት እንዳለብን አስረዳሁ::

ታጋዩ እስረኞችን የማውጣት እቅድ መሆኑን ካወቀ በሁዋላ በጭብጨባ፣ በመፈክርና በጣም በተለየ ስሜት ተቀበለኝ:: ምንም አይነት ችግር ቢፈጠርም ሊወጡት እንደሚችሉ መገመት አላዳገተኝም:: ጉዞ እንደተጀመረ የስኳድ አመራርና የቡድን



አመራሮችን ይዤ በመቅደም ወደ ከተማዋ ተጠጋሁ:: ከተማዋን በሜዳ መነፅር በሩቁ ቃኘናት:: ወደ አስራ አንድ ሰአት ተኩል ሲሆን ግን ጉዞ ጀመርን:: ይህን ያደረግንበትም ምክንያት ከምሽቱ በሁለት ሰአት ጥቃቱ መጀመር ስላለበት ነው:: ከዚያ ብንዘገይ ውጅራት የሄደው ሃይል ተመልሶ ሊመጣብን ይችላል::

እናም ለማደናገር ተኩስና ውጊያ የሚከፍቱትን በአዲጉዶ፣ በእንዳየሱስ ላይ ተኩስ እንዲከፍቱ አደረግኩ:: እነሱ ተኩስ ሲጀምሩ ያ ሾልኮ የሚገባው የኮማንዶ ሃይላችን በዝግታ ሶስቱን ዙር ምሽግ አልፎ ወህኒ ቤት አካባቢ ተጠጋ:: ሰአረ የያዛት ሻለቃ ደግሞ መውጪያ በሮችን ወደምትከፍትበት አቅጣጫ ደረሰች:: ይኸኔ ጥቃቱን እንዲጀምሩ አዘዝናቸው::

በአንድ ጊዜ አምስቱም የወህኒ በሮች ላይ ተኩስ ተከፈተ::

ዘበኞቹ አምስቱ መውጪያ በሮች ላይ ሆነው መትረየሶቻቸውን እንደጠመዱ ነበር በሩቅ ጥበቃ የሚያካሂዱት:: ወህኒ ቤቱ መከከላቸው ነው ያለው:: ተኩሱ ሲጀመር እንንግዲህ እነኚህ መትረየስ የያዙት የደርግ ወታደሮች በአር ፒጂና በእኛ መትረየስ በተተኮሰ ጥይት ባንዴ ተመቱ:: ለተወሰነ ጊዜ የተንጣጡት መትረየሶች ፀጥ አሉ:: ሁዋላ የቀሩት ክላሽንና ኤም-14 ነበሩ:: እነሱንም በእጅ በእጅ ውጊያ ተጠግተው ተኩስ ከፈቱባቸው:: ውጊያው በአስራ ሁለት ደቂቃ ውስጥ ተጠናቀቀ::

ቀደም ብሎ ግን የገጠመን ችግር ነበረ:: አንደኛዋ ቡድን በግራ በኩል ስትሄድ በተለያዩ የቀለማት መብራቶች ግራ ተጋባች:: መብራቱ አዲስ ነበር:: ለቡድንዋ ጭርሱኑ ወህኒ ቤቱን መለየት አቃት:: ሆኖም በባትሪ የመብራት ምልክት ስሰጣት በሩቅ ያለውን መብራት እየተከተለች ወደ ከተማ ውስጥ መግባት ጀመረች:: እንደገና ግን ሶስት ጉዋዶች የሰገራ መጠራቀሚያ ጉድጉዋድ ውስጥ ገቡ:: ቢሆንም መሳሪያ እየተቀባበሉ ሁለቱ ወዲያውኑ ወጡ:: አንዱ ግን በመቆየቱ መንቀሳቀስ አልቻለም:: ስለዚህ ሁለቱ እሱን ተሸክመው እንዲቆዩ ተደረገ:: ይህቺ ቡድን በመዘግየትዋ አራቱ ቀድመው ተኩስ እንደጀመሩ ግን አምስተኛዋም ቡድን መደነጋገሩን ትታ የራስዋን ጥቃት ከፈተች::

ወህኒ ቤቱን የተቆጣጠሩት ሰዎች ባጠቃላይ ስድሳ ስምንት ይሆኑ ነበር:: ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ አስራ ስድስት ሰዎች የያዘች አንዲት ጉዋድ ለማደናገር መናኸሪያ የሚባለውንና አውቶቡሶች፣ የመንግስት መኪናዎች የሚያሰባስቡባትን ቦታ እንድታጠቃ አድርገን ነበር:: በአዲጉዶም መስመር የመጣችው ቡድንም በተመሳሳይ በሩቅ ተኩስ ከፈተች:: ይኸኔ ታዲያ ጠላት

ተኩሱ ወዴት እንደሆነ እንኩዋን መረዳት አልቻለም:: የታችኛው
ወደላይኛው መልእክት እስኪያስተላልፍ ከአስራ አምስት ደቂቃ
በላይ አለፈ:: ጄኔራሎቹና ኰሎኔሎቹ ሲነጋገሩ እሰማ ነበር::
ግራ እንደተጋቡ አስራ ሁለት ደቂቃ ነጐደ::

በኛ በኩል ቀጥሎ የቸገረን የእስር ቤቱን ክፍሎች ቁልፎችን ማግኘቱ ነበር:: ሆኖም እስረኞቹ ባለቡት የኛ ሰዎች የሚነጋገሩትን ውስጥ ሳሉ ይሰሙ ስለነበር መዝጊያውን በሃይል ሰበሩት:: እንደወጡም ሁኔታው ተገልጦላቸው 'በምንላችሁ በታዎች እኛን ተከትላችሁ ነው የምትሄዱት፤ መበታተን የለም' ተባሉ:: እነሱም በሰልፍ ልክ እንደ ታጋይ በዝግታ መጉዋዝ ጀመሩ:: ነጭ ልብስ ከመልበሳቸው በስተቀር ድምፃቸው ፈፅሞ አይሰማም ነበር:: ያም ሆኖ ግን በድል ተወጥተነዋል ያልነው ያቺ የተከፈተችውን በር ሲያልፉ ነበር::

ከዚያ ርቀን እንደሄድን እስረኞቹን ስናያቸው ግን አብዛኞቹ ጫማ የላቸውም:: እግራቸው በሙሉ ጠቁሮአል፤ ሆኖም አይሰማቸውም:: ከሁሉም በጣም ያስገረመኝ ጉዳይ ትንሽ ሄደው መቆማቸው ነበር:: ወደኋላ መለስ ብለው ከተማዋን ያዩአታል:: በሁዋላ ፈዘው ይቆያሉ:: ከዚያ ደግሞ ባንነው ሩጫ ይጀምራሉ:: የተለየ ነበር ስሜታቸው:: ከከተማዋ አንድ ሰአት ተኩል ጉዞ ካደረግን በሁዋላ አንድ ትንሽ ወንዝ ዳር እንዲያርፉ አደረግን:: ውጅራት የነበረው ሃይል እንዲያፈገፍግ ከተማዋ መሀል የሚገኘውም እንዲሁ እንዲያደርግ ተደረገ:: በዚህ ውጊያ አንድ ሰርፀ የሚባል ጉዋድ ተሰዋብን:: አንድ ሻማ የሚባል የአንድ ቡድን አመራር የነበረም እንዲሁ ባላወቅነው ሁኔታ አልተገኘም:: የምንጠረጥረው ምናልባት የሰገራ ማጠራቀሚያ ውስጥ ከገቡት ጉዋዶች ጋር ሳይገባ እንዳልቀረ ነው::

ከእረፍት በሁዋላ ከሰሜናዊ አቅጣጫ ወደ ደቡባዊ ምእራብ አቅጣጫ በመለወጥ ሌሊቱን ሙሉ በእግር ሄድን:: በማግስቱ ሄሊኮፕተሮች በብዛት ሆነው አካባቢውን ሲያስሱ ዋሉ:: እኛም እስረኞቹን ደብቀን ውለን በነጋታው ሳምሪ ገባን::

ነፃ ካወጣናቸው አንድ ሺህ ሶስት መቶ እስረኞችም ግማሹ ወዲያውኑ ከኛ ጋር ሲቀላቀሉ፣ የቀሩት ግን ወደሱዳን ሄዱ:: ሆኖም ከነሱም ውስጥ ወደ ሰላሳ በመቶ ያህሉ ተመልሶ ከኛ ጋር ሊታገል ተቀላቀለ:: እንግዲህ አግአዚ ኦፕሬሽን ባጭሩ ይህን ይመስል ነበር ሀወኒ ፅበቅቲ - »ሲል አጠቃለለ::

«የሚገርም ታሪክ ነው» አለች::





«በወቅቱ እስረኛ ከነበሩት መሀል ያነጋገርሽው ሰው አለ
ሲል ጠየቃት::

«የለም:: ወዲ አስመራ ዛሬ ነገ እያለ ልቤን አውልቆኛል

«ሞርታር' የምንለው አንድ ታጋይ አለ:: እሱን ጠይቂ
የማስታወስ ችሎታው ጥሩ ነው:: ትናንት ነው ወዲህ የመጣ
ወደ ወሰጋ የሚደረገው ዘመቻ ሲጀምር ግን ወደ ጉንደር ስለሚ
አታገኚውም» አላት::

«አሁኑኑ አነጋግረዋለሁ» አለች ሀወኒ «... የትነው የማገኘው

ነገራት::

በረረች - እንደ ወፍ:: እንደ አሮሚያ አእዋፍት ...

... ሞርታር እጅግ ተባባሪ ሆኖ አገኘችው:: ካረፈበት
ደርሳ ጥያቄውን ስታቀርብለት ምንም እንኩዋ አጣዳፊ ስራ
የነበረ ቢሆንም ሀየሎም እንደላከትና ጉዳዩ ትኩረት እንደሚያ
እንስታ ስታጣድፈው የተወሰኑ ደቂቃዎች ሊተባበር ዝግጁ
በእርግጥም የማስታወስ ችሎታው ድንቅ ነበር:: የእስራቱ
ትናንት የተፈፀመ ያህል ጥቃቅን ሁኔታዎችን ሳይቀር አ
አጫወታት:: ሞርታርም እንደ ሀየሎም «ጊዜው መጥፎ ነበር»
ነበር የጀመረው::

«... ዘወትር ከምሽቱ አስራ አንድ ሰአት ሲል በእስር
ደወል ይደወል ነበር:: የደወል ድምፅ ሲሰማ ዱላ የያዙ ፖሊ
በቆመጥ እየደበደቡ፤ ቁርጭምጭሚታችን እየቆለመሙ ያጉሩ
በዚያች ሰአት ታዲያ ራት ደፍሮ የሚበላ እስረኛ የለም:: ሁ
የቀረበለትን ለኩፍ እያደረገ ይተወዋል:: ከምሽቱ አንድ
ሲሆን ጭንቀት ይጨምራል:: ሰስት ሰአት ላይ የልብ
ይጨምራል:: ፀጉር ይቆማል፤ ንደት፣ ፍርሃት፣ ቁጭ
የተቀላቀለባቸው ስሜቶች ይስተዋላሉ:: ያኔ የወህኒ ቤቱ መብ
ከጠፋ አሰየው ነው:: የሁሉም ልብ ያርፋል:: መብራቱ ከ
ግን ነገር እንዳለ ይገባናል:: ያኔ የአንዳንዱ ልብ በፍርሀት ይ
የቆረጠ የቆረጠው ደግሞ በእልህ ይጠባበቃል:: በፍርሃትና
መሀል ሆኖ የጭንቀትና የቁጣ ሲቃ ቀላቅሎ የሚያምጥም
ያም ሆነ ይህ አይቀርም:: እኩለ ሌሊት አካባቢ የመኪናዎች ድ
ይሰማል:: ያኔ ልባችን ይከፋፈላል:: ከፊሉ «የሚያልፉ መኪና
ድምፅ ይሆናሉ» በሚል ራሱን ያፅናናል:: ገሚሱ ስራ
ያጠብቃል:: የፅናት ፈገግታ ያሳያል:: አካሉ የሚንቀጠቀጥ
ይታያል:: ሲርገፈገፉ ይታያሉ:: በመካከሉ የበር መከፈት ሃ
ድምፅ ይሰማል - የትልቅ በር:: በር ይንኩዋኩዋል::

የወታደሮች ኮቴ። ቅጭልጭል የሚል የቁልፍ ድምፅም ይከተላል። ከዚያም በሩ ተበርግዶ የስም ዝርዝር መነበብ ይጀምራል። የትግራይ ምድር ስሞች...

ሀወኒ አቋረጠችው፣

«ስማቸው የሚጠራ እስረኞች ምን አይነት ስሜት ይታይባቸው ነበር?»

ሞርታር ፈገግ አለ፣

«ሁሉም አይነት ስሜት ይታይ ነበር። ጭንቅላታቸውን እንዳቀረቀሩ የሚወጡ ይታያሉ። እየፎከሩ የሚወጡም አሉ። እያፌዙ የሚወጡም ይታያሉ። እየተንቀጠቀጡ መውጣትም ነበር። እንዳልኩሽ ሁሉም አይነት ስሜት ይታያል። የሰው ልጅ ልጆቹንና ሚስቱን መውደዱ የግድ ስለሆነ 'ሚስቴን ... ልጄን!' እያለ የሚወጣም ነበር።

ከዚያ ወዲያማ ምን አለ? የፊጥኝ እየታሰሩ መኪና ላይ መጫን ነው። ካስፈለገ ዱላም ይታከላል። ወደ ሞት የሚጉዋዝ የዱላ ስንቅም ይመረቅለታል። የመጀመሪያው ግብአተ መሬት መፈፀሚያ ቦታ ውጫሌ ነበር። ያኔ ሀያ ሶስት የሚሆኑ የትግራይ ምሁራን ቤንዚን ተርከፍክፎባቸው ተቃጠሉ። ከዚያ በሁዋላ ሰው አላረፈም። ስአትዋ የተለመደች ሆነች። ዘወትር እኩለ ሌሊት ላይ ይመጣሉ። ሰዎች ይታረዳሉ - የትግራይ ልጆች። ... እኒያ የተራራው አገር ሰዎች ... ይታረዳሉ! ወደ ደብሪ ይወሰዳሉ። ወደ ኢላላ እንዳ እየሱስ ይጋዛሉ። ይህ ሁሉ እንግዲህ ከ1968 እስከ 1969 ባለው ጊዜ የተፈፀመ ነው። ከሌሊቱ ስድስት ሰአትም የሞት ሰአት መሆንዋ ትለመድ ጀመር። 1970 አመተ ምህረት የገባውም የሞት ድግሱን ይበልጥ እያፋፋመ ነበር። በአንዲት ጠባብ ቅጥር ውስጥ 700 የምንደርስ እስረኞች ታጭቀናል። እለተ ሞታችንን እንጠብቃለን።

ጊዜው መጋቢት ወር ነው።

1970 ኢ.ም። እለቱን መቶ አለቃ ደስታ ታደሰ ሲኰፈስብን ዋለ። የተሻለ ዘር፣ የተሻለ ዜጋ፣ የተሻለ ሰው መሆኑን ሊነግረንሞከረ። ይሁና! እኛ እንድናዳምጥ እሱ እንዲናገር ህጉ ይፈቅዳል። 'እንደመፅሀፍ ቅዱስ ንግርት ... ያመነ ምህረትን ያገኛል፤ የከዳ ደግሞ ሰይፍ ይጠብቀዋል' አለን። ማምሻውን ደሞ ተመለሰና 'እነዚህን ሬሳዎች አምጥተህ ካላስጉተትካቸው መቼ ይናገራሉ?' ብሎ ደነፋ። እስረኛው ሁሉ እነዚህ ንግግሮች ምን ማለት እንደሆኑ ይገባዋል ...»





«ምን ማለት ነው?» አለች ሀወኒ።

«ግድያ ይኖራል ማለት ነው» አለና ሞርታር ትረካውን ቀጠለ «... እና ያን ቀንም መሸ። ቢመሽም ግን አልተኛንም። አይኖቻችን ፈጠዋል። ምን አይኖቻችን ብቻ፣ ልባችን ... ቀልባችን ... ጆሮአችን ... በረከት መንግስተአብ እንደሚለው ሁሉም ህዋሳቶቻችን ነቅተዋል። ያሰብነው አልቀረም። እኩለ ሌሊት ላይ አስር ሰዎች ተወሰዱ። ከግቢው ብዙም ሳይርቁ ወስደው እንደገደሉአቸው ሰማን። ጀርባቸው ላይም ወረቀት ተለጥፎ ጉዳና ላይ ተዘረጉ።

ሚያዝያ ደግሞ መጣ። የወሩ አጋማሽ ይመስለኛል። እስረኛው ተረጋግቶ ተኝቶ ነበር። መቶ አለቃ ደስታ ድንገት ነበር የመጣው። ካድሬዎችን አስከትሎ ነበር የገባው። ወታደሮቹ በበሽታ የደቀቀውን እስረኛ ባለበት ይረግጡት ጀመር። ራሳችንን ... ሆዳችንን ... ያገኙት ቦታ ... የተመቻቸው ላይ ያላጉን ያዙ። 'ተነሱ!' እያሉ ያምባርቃሉ። ይጮሀሉ። ዛሬ እያንዳንዳችን ጉርጉዋድ እንደምንገባ ነገሩን። መቶ አለቃ ደስታ በጣም ይቆጣ ነበር። ግን ምን ሆኖ ነበር? ሁላችንም ተነሳን። መቶ አለቃው ስም ዝርዝር ያነብ ጀመር። የሰላሳ ሁለት የትግራይ ምድር ስሞች ተጠሩ። ስማቸው ከተጠራው ውስጥ የተለመደው የወኔ፣ የፅናት ስሜት የሚነበብባቸው ነበሩ። የተጠሩት ሰዎች ከወጡ በሁዋላ ተኩስ ሲዘንም ሰማን። ሞቱ ማለት ነው ...»

ሞርታር ይህን ብሎ ሲጋራ ለኰሰ። ፊቱ ሲለዋወጥ ሀወኒ ተመለከተች። ባንድ አፍታ አውሬ መሰለ። እንደገና ሲቀጥል ድምፁ ሻክሮ ነበር «... በርጡብት በፈነደቁበት ቀዬና ጉዳና ሬሳቸው ተሰጣ። ይህ የሆነው እኩለ ሌሊት ላይ ነው። የእኩለ ሌሊቱ ርሸና ያለማቋረጥ ቀጠለ - እስከ ሰባዎቹ መጨረሻ ዘለቀ። ቀናት ሄዱ ... ሮጡ ... ሁኔታዎችም መለዋወጥ ጀመሩ። ደርግ መረጋጋት የጀመረ መሰለ። በህዝቡ ልብ ውስጥ በቂ የፍርሀት ፈንጂ መቅበሩን አመነ። ስለዚህ ርሸናውን በቀን ለማካሄድ ደፈረ። በ1971 መጀመሪያ ላይ እኩለ ቀን ላይ እስረኞች ይወሰዱ ጀመር። ግን ብዙ አልገፉበትም። ምናልባት በጠራራ ፀሀይ የሰው ደም ምች ስለሆነ ይሆናል። ግድያውን ወደ አመሻሹ ላይ አደረጉት። ፀሀይ ማሽቆልቆል ስትጀምር የሞት ፍርድ ደብዳቤ የያዘች የክፍለ ሀገሩ አስተዳደር መኪና ተጣድፋ ትመጣለች። ቀይ የብረት ቆብ የደፉ ወታደራዊ ፖሊሶችም በሙሉ ልብ ዱብ ዱብ ሲሉ ይታያሉ። ያኔ ወህኒ ቤቱ ይታመሳል። ሁሉም ስለ ራሱ ያስብ ይሆናል። እኔም 'ተራዬ ደርሶ ይሆን?' ብዬ ማሰቤ አልቀረም። ከሚጠሩት መሃል መፈክር የሚያሰሙ፤ እንደ ነበልባል የሚንቀለቀል ወኔ ያላቸው ወጣቶች ይታዩ ነበር ...»

«መፈክሮቹ ምን የሚሉ ነበሩ?» ስትል ጠየቀች ሀወኒ።

«'ድል ለህወሀት!' 'ድል ለህዝብ!' 'ሞት ለፋሽስት ደርግ!' የመሳሰሉ ናቸው:: ቀሪው እስረኛ ከንፈሩን ይነክሳል:: አንጀቱ ያራል:: ቀጣዩ ተረኛ መሆኑንም ያውቃል - እኔም:: ይህ ድርጊት አላቋዋረጠም:: እስከ ጥር 1978 ድረስ በዚሁ ሁኔታ ቀጠለ:: ተስፋችን የመነመነ ነበር:: እንዲህ እያለ ጥር ሰላሳ መጣ:: እለቱ አርብ ነበር:: በዚህ እለት ሁላችንም የእስረኞችን ስራ እየሰራን ነበር:: የሚያስተምረው፣ የሚጠልፈው፣ ሽማ የሚሰራው፣ ልብስ አጥቦ የሚተኩሰው ... የሚሰፋው ሁሉም ጉድ ጉድ ሲል ዋለ:: ፀሀይ ስታቆለቁል እንደተለመደው የእስረኛው ስጋት ተቀሰቀሰ:: ግን ደሞ ባልተለመደ ሁኔታ ስእትዋ በሰላም አለፈች:: አምን ደሞ መሸ:: የመግቢያ ደወልም ተደወለ:: ሁሉም በየእስር ጉሬው ገብቶ ተቆለፈበት:: ምሽት ላይ ብዙ ትርኢት ይታያል:: የትግራይ ምድር ሰዎች ጥግጥጉን ይዘው ሲተክዙ፣ ሲያወጉ፣ ከፊሉ በመኝታ ቦታ ሲጨቃጨቅ ይታያል:: የሚስቅም አለ:: አምን ሰዎች በችግር ግዜም ቢሆን ከልባቸው ሊስቁ ይችላሉ:: የመግደያዋ አስራ አንድ ሰአት ስላለፈች የእፎይታ መንፈስ ይታያል:: የዛሬው ካታለፈ መቸ አነሰና? ግን ድንገት «ጎ» የሚል ድምፅ ሲሰማ የእስረኛው ልብ ሁሉ ቀጥ ይላል:: በዚህ እለት ቀስ በቀስ እስረኞች ይተኙ ጀመር:: ጥግ ላይ የሚተኛ አንድ ልጅ እግር፣ ቀጭን ወጣት ግንባሩን ጉልበቶቹ መካከል ወሽቆ ያንጉራጉር ነበር ...»

ህወኒ አቋዋረጠችው፣ «እንጉርጉሮው ምን ነበር?»

ሞርታር አመነታ፣ «... የማን ዘፈን መሆኑን ዘንግቼዋለሁ:: ብቻ እኔም ተጋደምሁ:: እኔ ከተኛሁ በሁዋላ ያ ቀጭን ወጣት እንጉርጉሮውን አቆመ:: እሱም መተኛቱ ነው ...»

ሞርታር ትረካውን አቋዋርጦ ሲጋራውን እየሳበ ፈገግ ሲል ህወኒ አስተዋለችው:: ገፅታው ባንድ አፍታ ደመቀ:: አንፀባረቀ::

«... እኩለ ሌሊት ላይ ድንገተኛ የተኩስ ድምፅ አስበረገገን:: ተኩሱ አላባራም:: እንደነጐድጓድ ይወርድ ጀመር:: ሞት ጉዋዙን እያንዳንዳችን ከእንቅልፋችን ባንነን ተነሳን:: ክፍላችን ተተራመሰ:: ጠቅልሎ መምጣቱን እርግጠኛ ነበርን:: ትልቁ የወህኒ ቤት በር ግን ደግሞ ድንገት ተኩሱ ቆመ:: ሲከፈትም ሰማን:: የበሩ አከፋፈት ግን ከወትሮው የተለየ ነበር:: የወታደሮች ጫማ ድምፅም አልተከተለም:: ይልቁን፣ 'ህሎ! ሀሰንጋይ!' የሚል ያልተለመደ ድምፅ ሰማን! የተለመደው የቁልፍና የሰንሰለት ድምፅ ሳይሆን 'ሲጢጢጢጥ የሚል





የመዝጊያ ፍንቀላ ድምፅ ቀጠለ:: ሌላም ድምፅ ተከተለ:: አምን ይህ ድምፅ ለዘልአለሙ አእምሮዬ ላይ ተመርጉአል::

'እኛ ህወሀት ነን! ከአሁን በሁዋላ ነፃ ናችሁ! ቶሎ በፍጥነት ወጡ!' የሚል ድምፅ በትግርኛ መጣ:: አምን በተራራማዋ ምድር ቁዋንቁዋ ... በተወለድንበት ... በዘፈንንበት ... በሳቅንበት ... ባለቀስንበት ... በተጣላንበት ... በተፋቀርንበት ... ቁዋንቁዋ የነፃነትን ድምፅ ሰማን:: ግን አላመንንም:: እኔ ህልም ነበር የመሰለኝ:: 'ቅዥት ነው ገሃድ?' የሚሉ ድምፆች ከየማእዘኑ ተደመጡ:: የደስታ እንባቸው እንደ ጅረት የሚወርድም ነበሩ:: የእስረኞች ፊት እንደንጋት ፀሀይ ደምቆ ይታይ ነበር:: በጆሮአችን በገባው ጣፋጭ ሙዚቃዊ ድምፅ ሰክርን ... እኔ በበኩሌ 'የሚገድለን ብቻ ሳይሆን ነፃ የሚያወጣንና የሚያከራን ወገን አለን ለካስ?' በሚል መንፈስ ሰውነቴ በደስታ ግሎ ነበር::»

ህወኒ ተከዛ ብዙ ቆየች::

ጥያቄ አልነበራትም:: ዝም ብላ ብቻ ሞርታርን አይን አይኑን ታየዋለች:: ማስታወሻ ደብተርዋንም አጣጠፈች:: ሞርታር ስሜቱን አየት አደረገና የሚያውቀውን ተናግሮ ማጠናቀቁን ገለፀላት::

«አሁን ህየሎምን ስታየው ወይም ስለሱ ስትሰማ ምን ይሰማሃል?» የሚል ጥያቄ አቀረበችለት:: ሞርታር ፈገግ አለ፣

«አንድ ድምፅ ወደ አእምሮዬ ይመጣል!» አላት::

«የምን ድምፅ!?»

«'እኛ ህወሀት ነን! ከአሁን በሁዋላ ነፃ ናችሁ' የሚል ድምፅ» ካላት በሁዋላ እንደመተከዝ ብሎ «... ታውቂያለሽ ህወኒ! እኔ ከሚሳር ነኝ:: ከተሞችን ስንቆጣጠር በርካታ ህዝብ እየሰበሰብኩ ንግግር አደርጋለሁ:: ብዙውን ጊዜ 'እኛ ህወሀት ነን' ብዬ ነው የምጀምረው:: በዚህ ጊዜ ስሜቴን እንኩዋ መቆጣጠር ያቅተኛል:: አምን ህወሀት ነኝ! የትግራይ ምድር ሰው ነኝ! ለህዝቦች ነፃነት መስዋእትነት ለመክፈል የምታገል የተራራማዋ አገር ሰው ነኝ!' ብዬ አስባለሁ:: ስሜቱ ይሞቃል:: በእጅጉ ይሞቃል» ብሎ ፈገግ አለ::

አመሰገነችው:: ከልብ ደጋግማ አመሰገነችው::

*　　*　　*

ሞርታር ዘንድ ቆይታ ወደ ማረፊያዋ ስትመለስ ጨልሞ ነበር:: ከሶስት ቀናት በሁዋላ ወደ ኦሮሚያ ምድር ስለሚደረገው ዘመቻ እያሰበች በስሜት ተዋጠች:: አባይን ከሚሻገሩት የመጀመሪያዎቹ

ታጋዮች ጋር የመጉዋዝ ፍላጎት አደረባት:: ለመጀመሪያው ኦሮሞ ገበሬ ነፃነት መጥታለች፤ ይህን ሂድና ለኦሮሞ ገበሬዎች ሁሉ ንገር' ማለት አሰኛት:: ይህንኑ ቃል ደግሞ የኦሮሚያ ተራሮች ያስተጋቡታል:: ባቱ ተራራ ስታላቂ ካካ፤ ካካ ለጭላሎ፤ የአርሲው ጭላሎ ለዝቋዋላ ያቀባብሉታል:: የኦሮሚያ አእዋፍት ደግሞ የነፃነቱን ዜና ከተራሮቹ እየተቀበሉ በእያንዳንዱ ኦሮሞ ጐጆ ያዳርሱታል:: «የአባይን ወንዝ ተሻግሮ የኦሮሚያን ምድር መርገጥ» የሚለው ስሜት አንድ ታሪክ አስታወሳት:: የትግል ታሪክ:: ያነበበችው ታሪክ:: የቻይና ታጋዮች ድንቅ የትግል ታሪክ ...

ሀዩሎም በሚገኝበት የማዘዣ ጣቢያ በኩል ስታልፍ በሀዩሎም ክፍል መብራት በርቶ ተመለከተች: ደጃፉ ላይ ታጋዮች ራት በመመገብ ላይ ነበሩ:: ብቅ ማለት አስፈለጋት:: አባይን ከሚሻገሩት የመጀመሪያዎቹ ታጋዮች ጋር አብራ ለመሄድ ይፈቅድላት ዘንድ ሀዩሎምን መማፀን ፈለገች:: ይህን ሊከለክላት እንደማይገባ ደግሞ አመነች::

ራት በመመገብ ላይ የነበሩት ታጋዮች እንድትቀላቀላቸው ጋበዙዋት:: በርግጥም ርቦአት ነበር:: ጠንከር ያሉ አምስት ጉርሻዎችን አነሳስታ ወደ ሀዩሎም ስታመራ፣ አንዱ ታጋይ፣ «ስብሰባ ላይ ሳይሆኑ አይቀሩም» አላት:: መለስ አለች::

«የለም:: ጨርሰዋል» አለ ሌላው ታጋይ::

ሀወኒ በሩን ገፍታ ስትገባ ክፍሉ በሲጋራ ጢስና በሻይ ሙቀት ወላፈን ታፍኖ ነበር:: አራት ደማቅ የኩራዝ መብራቶች ተንጠልጥለው ብርሀን ይሰጣሉ:: በአንድ አሮጌ ጠረጴዛ ላይ ካርታ ተዘርግቶአል:: ሀዩሎምና ሶስት ሌሎች ኮማንደሮች በካርታው ዙሪያ ከበው በከፍተኛ ድምፅ ይጨዋጨዋሀሉ:: በሩ ሲከፈት አራቱም ዘወር ብለው ተመለከቱ፣

«ሀወኒ ምን ፈለግሽ?» ሲል ጠየቀ ሀዩሎም::

«ስራ ላይ ናችሁ፤ ነገ ልመለስ?»

«ንገሪኝ ደህና::»

«የስራ ጉዳይ አይደለም»

ሀዩሎም ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ደጅ ወጣ:: በጨለማው ውስጥ ብቻቸውን ሆኑ፣

«ተመለስ ወደ ስራህ»





«ሞርታሯን አገኘሽው?»

«አዎን አገኘቼዋለሁ:: ጥሩ ነግሮኛል:: አሁን የፈለግሁህ ግን አባይን ከሚሻገሩት የመጀመሪያዎቹ ታጋዮች ጋር አብሬ መሄድ እንደምፈልግ ልነግርህ ነው::»

«ትችያለሽ:: ከባህል ክፍል ጉዋዶች ጋር ተነጋገሪ:: ሀይሌ ያመቻችልሻል::»

ስሜትዋ በደስታ ክንፍ አውጥቶ በረረ - እንደ ወፍ:: አባይን ተሻግሮ አየር ላይ ቀዘፈ - ንፁህ አየር ላይ - ነፋሻ ሰማይ ላይ - የኦሮሚያ አየርና ሰማይ::

«ስሜቴን አልቻልኩትም፤ ሀዩሎም»

«ይገባኛል፣ ሀወኒ::»

«አባይን የመሻገሩ ሁኔታ ምን እንዳስታወሰኝ ልንገርህ?»

ሀዩሎም አላስጨረሳትም::

«የቻይና ታጋዮችን - ፈጣን የድል ጉዞ ሊሆን ይችላል» አላት::

በደስታ ጩኸትዋን አቀለጠችው::

«ቻው ሀወኒ» አላት ሊለያት እየቸኰለ::

«ያን ያህል ተግባብተናል?»

«አሁን ካጠገቤ ጥፊ! ችግር የገጠመሽ መስሎኝ እንጂ አጣዳፊ ስራ ላይ ነኝ»

«ለመስዋእትነት የሚሽቀዳደሙት እኒያ የቻይና ታጋዮች ትዝ ይሉሀል?»

«አዎን እኛም እነዚያን የመሰሉ ጀግኖች አሉን:: ቻው ሀወኒ:: ከዚህ በሁዋላ ነቀምቴ ነው የምንገናኘው:: ተረዳኢኪ?»

«እወ»

ፊቱን አዙሮ ሊሄድ ካለ በሁዋላ፣

«ለመሆኑ ኦህዴድ ነቀምቴ ላይ ለታጋዮቹና ለአካባቢው አዋቂዎች አንድ ኮንፈረንስ እንደሚያዘጋጅ ሰምቼ ነበር:: አንቺ አትሳተፊም እንዴ?»

«ኧረ ወረቀት አቀራቢ ነኝ» አለችው::

«እውነት? ጥሩ ነዋ! በምን ርእስ?»

«'ዳዴሱሶ - በነፍጠኛው ላይ ያለው አይታ' በሚል ርእስ።»

«ከባድ ርእስ ነው። ተዘጋጅተሸበታል?»

«ብያለሁ እንግዲህ»

«ኦሮሚኛ ብችል እሳተፍ ነበር።»

«አዲስ ነገር አይኖረውም። የነፍጠኛውን ድርጊቶች መቸ አጣኸውና።»

«ያንቺን አቀራረብ ባይ ደስ ይለኛ ነበር። የሚሰብ እንደሚሆን መቸም እገምታለሁ። ለመሆኑ ካንቺ ሌላ ማን ማን አለ! ሌላ ተናጋሪ?»

«ሰለሞን ዲሳሳ የዳዴሱሶን ፕሮግራም ያስተዋውቃል። ኩምሳ! ወደፊት የሚመሰረተው ህዝባዊ መንግስት ምን አይነት ባህርያት እንደሚኖሩት በቀጥታ ከዳዴሱሶ አላማዎች ጋር አስተሳስሮ ያቀርባል። የኩምሳ እጅግ ጥሩ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ። የኦሮሞ ህዝብ ከመቶ አመት በሁዋላ ራሱን ማስተዳደር መጀመሩን ማንሳቱ አይቀርም። ርእሰ ጉዳዩ ራሱ በጣም ደስ ይላል። አሊ ኢብራሂም በበኩሉ 'የምኒልክ የወረራ አላማዎች' ላይ ተዘጋጅቶአል።»

«በርቱ እንግዲህ!»

ሀየሉምን ተሰናብታ የባህል ክፍል ባልደረቦችዋ ወደሚገኙበት ገሰገሰች። በመንገድዋ ላይ አንድ እንጉርጉሮ ወደ አእምሮዋ መጣ። የጥንትዋ ፊንፊኔ በአጤ ምኒልክ ወራሪ ሰራዊት ስትጥለቀለቅ የአካባቢው ኦሮሞ ገበሬዎች ያሰሙ የነበረው እንጉርጉሮ፣

*Inxooxxoo dhaabba tanii*

*Cafee gadi ilaaluun hafe*

*Finfinne loon geessanii*

*Hora obaa suun hafe*

*Tullou Daalatii irratti*

*You iin Gullalle hafe*

*Gafrassatti dabranii*

*Koraan Cabsuunis hafe*

*Hurufa boombii irratti*





*Jabbille yaasuun hafe*

*Bara jarri dhufani*

*Loon keenyas ni dhmani*

*Iddo Mashashaan dhufe*

*Birmadummaanis hafe.*

ትርጉሙ የሚከተለው ነበር፦

*እንጦጦ ላይ ሆኖ*

*ለምለሙን መስክ ወደታች ማየት ቀረ።*

*ከብቶቹን ፊንፊኔ ወስዶ*

*ሆራ ማጠጣቱ ቀረ።*

*በዳለቲ ላይ*

*የጉለሌዎች መሰብሰብ ቀረ።*

*ገፈርሳ ሄዶ*

*እንጨት መሰበሩም ቀረ።*

*በሁሩፋ በምቢ ላይ*

*ጥጆችን ማገድ ቀረ።*

*ሰዎቹ እንደመጡ*

*ከብቶቻችን አለቁ*

*መሸሻ ከመጣ ወዲህ*

*የኛ ነፃነት ቀረ።*

እነሆ አሁን አዲስ ዘመን ሊወለድ ነው። ከአርባ ስምንት ስአት በሁዋላ በኦሮሚያ ምድር ላይ የነፃነት ርችር የሚተኰስ ይመስላል። ከተተኰሰ የርችቱን ተኩስ ድምፅ የኦሮሚያ ተራሮች እየተቀባበሉ ማስተጋባታቸው አይቀርም ...

- 3 -

«ሀየሉም ... የምስራች!»

«ምስር ብዬ ... ምን ተገኘ?»

ሀወኒ ነበረች የምስራች ነጋሪዋ። ነቀምቴ በተያዘች በሰስተኛው

እለት ገና በማለዳው ካረፈበት ቤት ገብታ ነበር «የምስራች!» ያለችው። በእጆዋ ወረቀቶች ተሸክማለች። የደስታ ፀሀይ ፊትዋ ላይ አንፀባርቆአል። ሀየሎም ገፅታዋን አጢኖ ብቻ ልትቆጣጠረው ባልቻለችው አስደሳች ስሜት መዋጥዋን ተረዳ። «ምን አገኘሽ ይሆን?» ሲል አሰበ።

«ምስር ብዬ ሀወኒ ... ምን ተገኘ?»

«እውነተኛ የኦሮሞ ህዝብ ታጋይ ሆንኩ» አለች።

ሀየሎም ግራ ተጋባ፣

«እስከዛሬ ምን ነበርሽ፣ ሀወኒ?»

«ያንተ ታሪክ ፀሀፊ።»

ድንጋጤ ገፁን አጠናፈረው። ትክ ብሎ ተመለከታት። እንባዋ ጉንጩዋን ባንድ አፍታ አለበሰው። ሀየሎም ቃል ሳይተነፍስ ከቆየ በሁዋላ፣

«እስኪ ምን እንደተሰማሽ አጫውቺኝ?» አላት።

አጫወተችው።

ታሪክ ፀሀፊነትዋን እርግፍ አድርጋ ትታ የኦሮሞን ህዝብ በቀጥታ ለማገልገል የወሰነችው ትናንት ማምሻውን ቢሆንም በቀጥታ ለማገልገል የወሰነችው ትናንት ማምሻውን ቢሆንም ስሜቱ የተፀነሰው ግን የኦሮሚያን ምድር ከረገጠችበት እለት ጀምሮ ነበር። ያን እለት የስራ አካላትዋን የናጠ ህዝባዊ ስሜት ሲያድርባት ታወቃት። ከግንባር ቀደሞቹ ታጋዮች ጋር አባይን ተሻግራ የኦሮሚያን ምድር እንደረገጠች ተንበርክካ መሬቱን ሳመች። እንባዋ መሬቱ ላይ ተንጠባጠበ። ወላጆችዋን አሰበች። በንጉሱ ስርአት ፖሊሶች ጥይት ተደብድበው የተገደሉ እምቢ ባዮች። በአሳብ ርቃ ነጐደች። ወገኖችዋንና መንደርዋን አስታወሰች። ዋቆ አባዱላ። ቡርቃ። የኦሮሞ ህዝብ። የተዋረደ ህዝብ። ለህገሩ ባእድ እንዲሆን የተፈረደበት ህዝብ። ለመቶ አመታት በጨቋኞች ገዢዎች በትር የተቀጠቀጠ ህዝብ።

በዚያች ደቂቃ የኦሮሞ ህዝብ ከልጆቹ የሚፈልገውን ተመስጣ ማሰብ ጀመረች። በሩጫ ከአለም አንደኛ መውጣት? የፕሮፌሰርነትን ማእረግ መልበስ? በአለም የተደነቀ የታሪክ ፀሀፊነትን ካባ መከናነብ? እነዚህ ሁሉ መልካም ናቸው። ለሀወኒ ግን አላጠግብ አሉዋት። የኦሮሞ ህዝብ ከዚያም ባሻገር ኑሮውን የሚኖሩለት፣ ችግሩን የሚያዳምጡለት ልጆቹን ይሻል። ከድህነቱ ይወጣ ዘንድ የሚያግዙትን ይፈልጋል። የጣፈጠ አማርኛ ስለቻሉ





ከነፍጠኛው ጉያ ስር ተሸሽገው አብረው የሚያሙትን አይሻቸውም። የኦሮሞ ህዝብ የሚፈልገው ከአብራኩ ወጥተው መልሰው የሚጨቁኑትን፣ የሚዘርፉትንና የሚያዘርፉትን አይደለም። «ነብር ይቦጭቅህ አንበሳ?» የሚል ጥያቄ ይቀርብለት ዘንድ አይፈልግም። የኦሮሞ ህዝብ በማንም መቦጨቅ አይሻም። የኦሮሞ ህዝብ የሚፈልገው፣ ድህነቱን የሚያስወግዱ፣ ክብሩን የሚያስጠብቁ፣ ትምህርት ቤት የሚገነቡ፣ መንገድ የሚሰሩ፣ ክሊኒክ የሚያንፁ ኦሮሞዎችን ነው። ገንዘቡን እየገፈፉ ቦርጫቸውን የሚያሰፉ፣ የምድሪትዋን ሀብት እየቦጠቦጡ ጭልጥ ብለው የሚቀሩ፣ ተሽማቀው የሚያሽማቅቁትን ኦሮሞዎች አይደለም የሚሻው። የኦሮሞ ህዝብ የዝነኛ ኦሮሞ ችግር የለበትም። ዝነኞችማ ሞልተውታል። ሩዋጮች፣ ጀግኖች፣ ዘፋኞች፣ የአማርኛ ባለቅኔዎች፣ ፕሮፌሰሮች ሞልተውታል። እነዚህ ሁሉ መልካም ኦሮሞዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ሊከበሩ ይገባም ይሆናል። በቀጥታ ህዝባቸውን በማገልገል የሚጠቀስላቸው ተግባር ግን ከቶ አይኖርም። የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ሲነሳ ስለአለማቀፋዊነት እየደሰኮሩ ራሳቸውን የሚያታልሉ ኦሮሞዎች አያሌ ናቸው። ሀወኒ ከኒያ መሀል መሆን እንደማትፈልግ ነበር የተረዳችው። ኦሮሚያ እውነተኛ የኦሮሞ ህዝብ ልጆችን አጥብቃ የምትፈልግበት ወቅት መሆኑን ነበር የተገነዘበችው። የሀየሎምን የጀግንነት ታሪክ ፅፋ ለአለም ስታቀርብ ኦሮሞዎች በሩዋጭነቱ ገናና ስም ካለው አበበ ቢቂላ ለይተው እንደማያዩዋት ነበር የተሰማት። ይህን ስታስብ የስራ አካላትዋ ብርድ የመታው ያህል ተንዘፈዘፈ።

ትናንት ሌሊት ታዲያ ነቀምቴ ላይ ለሚካሄደው ኮንፈረንስ ዕሁፏዋን ስታዘጋጅ ስለወደፊት ጉዞዋ አጥብቃ አሰበች። የታሪክ ፀሀፊነት ስሜትዋ ጨርሶ እንደሞተ ተገነዘበች። ጥሪዋን አገኘችው። የቡርቃው አድባር የዋቆ አባዱላ አርእድ አንቀጥቅጥ ዲስኩር ወደ ጆሮዋ እየመጣ ተጥለቀለቀ። ኦሮሚያ አዲሱን ጉዞዋን በምትቀድስበት በዚህ ጊዜ ከአንድ ህዝባዊ አላማ ካለው ኦሮሞ የሚጠበቀው ተግባር ወለል ብሎ ታያት። ያለማመንታት - ወሰነች። የግለሰብንም ሆነ የድርጅትን የትግል ታሪክ ለመሰብሰብ የምታደርገው ጥረት እውነተኛ ፍላጐትዋ እንዳልሆነ በጥብቅ ተረዳች። ኦሮሚያን በሚመለከት ቀጥተኛ ጉዳይ ላይ መሳተፍ ቀዳሚ አላማዋ ሊሆን እንደሚገባው አመነች።

ይህንኑ አጫወተችው - ለሀየሎም።

በጋለ ስሜት ነበር የምትናገረው። ሀየሎም በጥሞና አዳምጦአት ሲያበቃ፣

«ትክክለኛ፣ ጤናማና በግሌ ስፈልገው የነበረ ውሳኔ ላይ ነው

የደረስሽው!» ሲል በሞቀ ስሜት አበረታታት:: እውነተኛና ቅን መሆንዋን ጭምር ነገራት:: ጥንካሬዋ ደረጃ በደረጃ መታየቱ ራሱ እውነተኛነትዋን እንደሚያሳይ አረጋገጠላት:: ከዚህ በላይ ግን አልቀጠለም:: ሀወኒ የኰንፈረንሱ ሰአት ደረሰባት:: ቀሪውን ማምሻውን እንደሚጨዋወቱ ተነጋግረው በቀጠሮ ተለያዩ::

... ሀወኒ ወደ አዳራሹ በረረች::

በረረች እንደ ኦሮሚያ ወፎች:: ነፃ አእዋፋት... ዘማሪዎች... ንፁህ ልብ ያላቸው ውብ ዘማሪ አእዋፍት...

* * *

ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በሰአቱ ተገኝተዋል:: የነቀምቴ ማዘጋጃ ቤት የስብሰባ አዳራሽ አልጠበባቸውም:: ተሰብሳቢዎቹ በሙሉ ኦሮሞዎች ናቸው:: አብዛኞቹ የነቀምቴ ከተማ ነዋሪዎች ሲሆኑ ጥቂት የዳዴአኦ ታጋዮችም አሉ::

ኰንፈረንሱ በሰአቱ ተጀመረ ...

የዝግጅት ኰሚቴው አስተባባሪ የሶስት ቀኑን ፕሮግራም ማስተዋወቅ ጀመረ:: የዳዴአኦ ዋና ፀሀፊ ኰንፈረንሱን በንግግር ይከፍታል:: ከዚያም ከምሳ በፊት ባለው ጊዜ የዳዴአኦ ማእከላዊ ኰሚቴ አባል የሆነው ሰለሞን ዲሳሳ የድርጅቱን ፕሮግራም ያስተዋውቃል:: ከምሳ በሁዋላ ታጋይ ሀወኒ ዋቆ «ዳዴአኦ - በነፍጠኛው ላይ ያለው እይታ» በሚል ርእስ አንድ ዝግጅት ይኖራታል:: በነጋታው በተመሳሳይ መልኩ ከምሳ በፊትና ከምሳ በሁዋላ «የኢህአዴግን ቀጣይ ጉዞና የምኒልክ ወረራዎች አላማ» ላይ የድርጅቱ ሁለት የማእከላዊ ኰሚቴ አባላት ንግግር ያደርጋሉ:: ተሰብሳቢው በማንኛውም ጉዳይ ላይ የመጠየቅ ሙሉ መብት አለው:: ሶስተኛው እለት የዳዴአኦ ዋና ፀሀፊ ኰንፈረንሱን በንግግር የሚዘጋበትና የባህል ትርኢት የሚታይበት ይሆናል::

የዝግጅት ኰሚቴው አስተባባሪ የሶስቱን ቀን ፕሮግራም አስተዋውቆ ሲያበቃ የዳዴአኦ ዋና ፀሀፊ የመግቢያ ንግግር ያደርግ ዘንድ ወደ መድረክ ጋበዘው::

ዝግጅቶች በተያዘላቸው ፕሮግራም ቀጠሉ ...

የማለዳው ፕሮግራም ተጠናቆ የተሲያቱ ተጀመረ:: ሀወኒ መድረክ ላይ መቅረቡ አላስጨነቃትም:: ከመምህርትነት ሙያዋ በቂ የመድረክ ልምድ ቀስማለች:: ይልቁን ኦሮሞዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በራሳቸው ጉዳይ ላይ ለመነጋገር በግልፅ በተሰበሰቡበት በዚህ አጋጣሚ ተሳታፊ መሆን መቻልዋ የፈጠረባትን የደስታ





ስሜት መቆዋቆዋም ነበር ያቃታት::

የኦሮሞን ህዝብ በቀጥታ ማገልገል መጀመርዋን ደግማ ደጋግማ እያሰበች እንደመባነን ያደርጋታል::

አኖሌን ጭምር መልሳ መላልሳ አሰበችው:: «ምነው አብነቤ በኖረ» ብላ ተመኘች:: በኦሮሞ ጥያቄ ላይ ተመሳሳይ አመለካከት እንደሚኖራቸው ትገምታለች:: በዋቆ አባዱላና በአይበገሬው የቡርቃ ህዝብ መካከል ተኰትኩተው በማደጋቸው የዚያን ጀግና ህዝብ በራስ የመተማመን ባህል መውረስ መቻላቸው ይሰማታል::

ሰአቱ ቀረበ...

«እንግባ!» አላት ሰለሞን::

ተያይዘው ወደ መድረክ ወጡ:: ከሺህ በላይ ሰዎች:: የኦሮሚያ ምድር ሰዎች:: ከሁለት ሺህ በላይ አይኖች:: ከመቶ አመት በሁዋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሳቸው ጉዳይ ላይ በነፃነት ለመነጋገር የተሰባሰቡ ኦሮሞዎች...

ሰለሞን ስለቀጣዩ አጀንዳ ካስተዋወቀ በሁዋላ ማይክራፎኑን ወደ ሀወኒ ገፋው:: ሞከረችው! ይሰራል:: አሳምሮ ይሰራል::

የተመሰገነ የኦሮምኛ ቋንቋዋ በውብ ድምፅ ይፈስ ጀመር - እንደ ዋቢሸበሌ ወንዝ...

«ውድ ወገኖቼ ... እንኳዋን ለዚህ አበቃን!»

የሀወኒ በራስ የመተማመን ስሜት ገና ከንግግርዋ ጅማሬ ተንፀባረቀ!

«የተሰጠኝ ርእስ 'ዳዴአኦ - በነፍጠኛው ስርአት ላይ ያለው እይታ' የሚል ነው:: ትናንት ማታ አንዳንድ አስፈላጊ ነጥቦችን ለማስታወስ ብዬ ማስታወሻ ስይዝ ስሜቴን መቆጣጠር ስላቃተኝ ተንሰቅስቄ አለቀስኩ:: የሀያ ዘጠኝ አመት ሰው ነኝ:: በዚህ እድሜዬ እንደትናንት ማምሺያ ስሜታዊ የሆንኩበት አንድም እለት አልነበረም»

አይኖችዋ በእንባ ቢሞሉም ስሜትዋን እንደምንም ገድባ ቀጠለች!

«...አቦ ሮባን ስንቶቻችሁ ታውቁዋቸዋላችሁ?»

ይህን ብላ በአዳራሹ የሞላውን ህዝብ ከዳር እዳር ቃኘች:: ድምፅ አልነበረም:: ብዙዎች ይተያዩ ገቡ::

ሀወኒ ፈገግ አለች - ውብ ፈገግታ::

ድምፅዋ እየጐላና እየተዋበ መጣ...

«... ደህና! ስለ አርሲው ሮባ ዳዲ ትንቢት ቀስ ብዬ እገልፃለሁ:: እኔና እናንተ ኦሮሞዎች ነን:: እኔ የአርሲ ኦሮሞ:: እናንተ ደግሞ (ሁላችሁም ላትሆኑ ትችላላችሁ) አብዛኞቻችሁ የወለጋ ኦሮሞዎች ናችሁ:: ነፍጠኞች ባለፉት ዘመናት ሁሉ ከፋፍለው ገዝተውናል፤ ከፋፍለው ዘርፈውናል፤ ከፋፍለው ከፋፍለው ገድለውናል፤ ከፋፍለው ሰብእናችንን ሊያጠፉ ሞክረዋል::

እናንተ የወለጋ ኦሮሞዎች፤ በአጋጣሚ የታሪክ ሰው ነኝና እናንተ የወለጋ ኦሮሞዎች፤ በአጋጣሚ የታሪክ ሰው ነኝና ታሪካችሁን ላስታውሳችሁ:: የኔና የናንተ አባቶች፤ (ጥንት ማለቴ ነው) ኦዳ ነቤ በተባለች ቦታ አብረው ይኖሩ ነበር:: ኦዳ ነቤ ግን ጠበበቻቸው:: ስለዚህ ሰፊ ምድር ፍለጋ ወደተለያየ አቅጣጫ ሊጎዋዙ ወሰኑ:: የሚሄዱበትን አቅጣጫ ለማወቅም እጣ ጣሉ:: ቱለማዎች በእጣው የሚጫ ልጆች እድል ወደ ዛሬዋ ወለጋ ሆነ:: ቱለማዎች በእጣው መሰረት ወደ አዋሽ በላይ ነጐዱ:: የኔ አባቶች ደግሞ አርሲና ባሌ ቀሩ:: እነዚህ አባቶቻችን ለጉዞ ሲሰናዱ ተላቅሰው ነበር:: ተማምለውም ነበር:: የተማማሉት፤ ላይረሳሱ፤ ላይከዳዱ፤ ላይከፋፈሉ፤ ርስበራስ ላይዋጉ ነበር:: ምክንያቱም ይህ ታሪክ በተፈፀመበት ዘመን ምድር ሰፊ ነበረች:: ዛሬ ግን ጠባለች:: ደምቢዶሎ የገዘቀዋላው ኦሮሞ የጭላሎውን በቀላሉ ያገኘዋል:: ደምቢዶሎ የተወራው በአንድ አዳር እካ ይደርሳል:: ለዚህ ነው ዛሬ ግንባር ለግንባር ተገናኝተን በራሳችን ጉዳይ ላይ መነጋገር መቻላችን:: አንድ የምንሆንበት ጊዜም ቀርቦአል:: ምስጋና ለዋቃዮና ለህዝባዊው ትግል:: በንግግሬ መግቢያ 'እንኳዋን ለዚህ አበቃን!' ማለቴ ለዚህ ነው::»

የመድፍ ተኩስ የመሰለ ጭብጨባ አዳራሹ ውስጥ አስገመገመ!

ሀወኒ ቀጠለች፣

«... ወደ ተሰጠኝ ርእስ በቀጥታ ከመዝለቄ በፊት በአፈ-ታሪክና በሰነድ ደረጃ ያለ ታሪካችንን ቀንጨብጨብ ማድረግ እሻለሁ:: ስለኦሮሞ ህዝብ አመጣጥ በተለያዩ ጊዜያት እንደ አሸዋ የበዙ መላምቶች ተነግረዋል:: በፅሁፍም ሰፍረዋል:: አብዛኛው በጥላቻና በንቀት የተሞላ ነው:: እኒያን ሁዋላ የምናያቸው ሆኖ፤ የኦሮሞ ህዝብ ግን በሺህ ለሚቆጠሩ ዘመናት በምስራቅ አፍሪካ የኖረ ህዝብ መሆኑን በጥቅሉ ማስቀመጥ ይገባል:: እንዲያውም አንዳንድ ታሪክ ፀሀፍት 'ኦሮሞ ጥንታዊ ዝርያና እንጋፋ ተወላጅ መሆኑን፤ ምናልባትም ለበርካታዎቹ የምስራቅ አፍሪካ ህዝቦች የዘር ግንድ ነው' ሲሉ ያረጋግጣሉ::





ኦሮሞዎች በዋቢ ሸበሌና በጁባ ወንዝ መካከል ቤናዲር በተባለ አውራጃ ለአያሌ አመታት መኖራቸው በኦሮሞ አፈ-ታሪክ ይነገራል:: በዚያ ቆይታቸው ባንቱ ከሚባል ነገድና ከሶማሌዎች ከፍተኛ ጥቃት ይሰነዘርባቸው ነበር:: በአካባቢው የሚደርስባቸው ጥቃት ሲበረታ ደግሞ ወላቡ ወይም አሁን መዳወላቡ ወደምትባለው ውብ ምድር አልፈው አያሌ አመታትን በአካባቢው አሳልፈዋል:: በአስረኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኦሮሞዎች አብያ፣ ህዲ፣ ዳዲ በሚባሉ የባሌ ወረዳዎች ላይ ይኖሩ እንደነበር የሚገልፁ ማስረጃዎችም አሉ:: ይህም ዘመን ለአቢሲኒያዎች የዛጉዌ ዘመነ መንግስት ይመስለኛል:: ዛሬ የክፍለሀገር ወይም የጐሳ መጠሪያ ሆነው የሚታወቁት እንደ ከረዩ፣ ወሎ፣ ቱለማ፣ ሜጫ፣ በጠቀስኩት አካባቢ የተወለዱ የኦሮሞ አያቶች ናቸው:: ራያ፣ ቤቶን፣ ኢቱን የተባሉት ልጆችን የወለደው ደግሞ ከረዩ ነው - አያንቱን አግብቶ:: ቱለማም አልኮን አግብቶ አብቹን፣ ዳጭን፣ ሶዶን ወልዶአል:: በወቅቱ ፈረሰኞች የነበሩት ጀግኖች አያቶቻችን ዛሬ የሰፈሩባቸውን ቦታዎች ሁሉ የሞሉት ኑሮአቸው ሰላማዊ ስለነበር ነው:: የአያቶቻችን የአኑዋኑዋር ስርአት ዛሬ ከፖለቲከኞች አንደበት ሁሉ እንደማይጠፋው ቃል 'ዴሞክራሲያዊ' ነበር:: ኦሮሞዎች በስልጣን ፍለጋ መነሾ ርስበራስ የተገዳደሉበት አንድም ዘመን አልነበረም:: ዛሬም እንዲኖር አንሻም!»

እንደገና አዳራሹ በጭብጨባ ተነቃነቀ::

ሀወኒ ግማሽ ሰአት ያህል በኦሮሞ ህዝብ ታሪክ፤ ባህል፤ የአስተዳደር ስርአት ላይ ማብራሪያ ከሰጠች በሁዋላ ወደ ተሰጣት ዋነኛ ርእስ ጉዳይ ዘለቀች::

በነፍጠኞች የዘወትር አጀንዳ ነበር ንግግርዋን የጀመረችው:: «ኢትዮጵያዊነት» ኢትዮጵያዊነት በተባለው ካፖርት ስር ስለተሸሸገው አመለካከት በስፋት ተነተነች:: ከኢትዮጵያዊነት በፊት የብሄረሰቡን ስም የሚያነሳውን ሁሉ «ጠባብ፣ ጐጠኛ፣ ዘረኛ» የሚል ስያሜ ስለሚያከናንቡበት ምክንያት ጭምር አብራራች::

«ይሁን እንጂ እኛ ኦሮሞዎች» አለች ሀወኒ «ዘረኞችና ጐጠኞች አይደለንም:: በርግጥ እንደ አመለካከት ጠባብነት ሊከሰት ይችላል:: ይህ ባህርያዊ ነው:: በቅድሚያ መነሳት ያለበት ግን 'ጠባብነት መከሰት የለበትም' የሚለው ሳይሆን 'ጠባብነት እንዴት ተከሰተ?' የሚለው ነው ሊሆን የሚገባው:: ጠባብነትን የፈጠርነው እኛ ኦሮሞዎች አይደለንም:: ጠባብነት ተፈጥሮአዊ አይደለም:: በጋራ በምንኖርባት በዚህች የምስራቅ አፍሪቃ ምድር የዘር ልዩነትና የብሄር ጭቆናን ያመጣው የነፍጠኛው ስርአት ነው::

አብነቶችን እንስተን በዝርዝር እያየን መሄድ እንችላለን::

የነፍጠኛው ስርአት አገልጋይ የነበሩት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የሚባሉ አንድ ትምክህተኛ አሉ:: ዛሬ በህይወት ያሉ የአማራው ገዢ መደብ አባላት ባለንበት ዘመን ጭምር እኒህን ሰው ያደንቁዋቸዋል:: በአርአያነት ይጠቅሱዋቸዋል:: እኒህ «ስመጥር» ሰው ባዘጋጁት የአማርኛ መዝገበ ቃላት «ጋላ» የሚለው ቃል ኦሮሞን ወክሎ ገብቶአል:: በነጭ ወረቀት ላይ ሰፍሮ የሚገኘውን ላንብብላችሁ «ጋላ - ያማራ ጠላት፤ ደመኛ፤ በግና ተኩላ፤ አማራና ጋላ፤ ጋሌ በማለት ፈንታ ጋላን ገድሎ ምነው ገለሌ ማለት ነበር» ይላል:: ወገኖቼ! ሁላችንም እንደሚገባን ኦሮሞ ራሱን ጋላ ብሎ ጠርቶ አያውቅም:: ስያሜው የባእድ ነው:: ማንም ቢሆን ኦሮሞ ራሱን «ጋላ» ብሎ የተጠቀመበትን ጊዜና ዘመን በማስረጃም ሆነ በአፈታሪክ ደረጃ ሊያቀርብ አይቻለውም:: ይህን ቃል ነፍጠኞች ራሳቸው የፈጠሩት የኛ ያልሆነ ስያሜ ነው:: የእኔ ስም ሀወኒ ነው:: ማንም መጥቶ «ሀና» ቢለኝ የኔ ባለመሆኑ ይኩስኩሰኛል:: ስለዚህ አልቀበለውም::»

ምንነቱ ያልታወቀ ማጉረምረምና ሳቅ አዳራሹን ሞላው:: ሀወኒ ቀጠለች፣

«... አለቃ ኪዳነ ወልድ ባዘጋጁት መዝገበ ቃላት 'ጋላን ገድሎ ምነው - ገለሌ ማለት ነበር' ሲሉ አኑረዋል:: 'ጋላን መግደል' ለምን አስፈለገ? ቁም ነገሩ እዚህ ላይ ነው ያለው:: የኦሮሞ ህዝብ ከወራሪው የምኒልክ ሰራዊት ጋር ባደረገው ውጊያ በአይበገሬነት ስለተጋደለና አልንበረከክ ብሎ ከባድ ጭንቀት አሳድሮባቸው ስለነበር ነው አለንበት ዘመን ድረስ ጥላቻቸውና ርግማናቸው የተከተለን:: በወቅቱ በተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ኦሮሞዎች ተሸንፈዋል:: የታገሉትና የተፋለሙት ሲወለዱ ጀምሮ ሊኖራቸው የሚገባውን መብት ላለማጣት ነበር:: ዳሩ አያቶቻችን ራሳቸውን የሚከላከሉበት ዘመናዊ መሳሪያ አልነበራቸውም:: የአማራ ገዢዎች ደግሞ በእንግሊዝና በፈረንሳይ መንግስታት ይረዱ ነበር:: ክርስትናን የማስፋፋት አላማ የነበራቸው አውሮፖውያን የኦሮሞ ህዝብ የሚጨፈጨፍበትን ዘመናዊ መሳሪያ በገፍ አቅርበዋል::

አለቃ ኪዳነ ወልድ ኦሮሞና አማራን 'በግና ተኩላ' ብለው በምሳሌ አቅርበዋል:: የርሳቸው አመለካከት ተሸካሚዎች ደግሞ ዛሬ 'ሁኔታዎች እንደቀድሞው መቀጠል አለመቻላቸውን ሲረዱ 'ተዋልደናልና ያለፈውን አታንሱ' ይሉናል:: መዋለድ ሌላ፤ ታሪክን ማወቅና መብትን ማስከበር ደግሞ ሌላ:: አጀንዳው የመዋለድና ያለመዋለድ ጉዳይ አይደለም:: አዎን ተዋልደናል:: በጋብቻ ስም ግን ነፍጠኛው የፈፀመውን ግፍ እንዳናነሳ መሞከር አደገኛ ነው::





«ዳዶአኦ ህዝብና ህዝብን የሚጋጨት ግብ የለውም:: ነፍጠኞች በኦሮሞ ህዝብ ላይ ገደብ የሌለው ግፍ ፈፅመዋል:: ይህ ሀቅ ነው:: ይህን ሀቅ መካድ አይቻልም:: ለማድበስበስ መሞከሩም ግብዝነት ነው:: ሀቁን አውቆና አምኖ ተከባብሮ አብሮ መኖር ብቻ ነው መፍትሄው::

ጐንደር ሳለሁ አንድ የማይገርም ሁኔታ ገጥሞኝ ነበር:: በአንድ ሆቴል ውስጥ ምሳ ላይ ሆኜ ይመስለኛል አጠገቤ ተቀምጠው የነበሩ እንግዶች በወሬያቸው መካከል 'ባጫ' የሚለው ስም ስድብ እንደሚመስል ሲያወሩ ሰማሁ:: በወቅቱ በስምቼ ክልብ አዘንኩ:: ባዶ ትምክህተኞች አሲያም አላዋቂዎች እንደሆኑ ግልፅ ነበር:: ደካሞች ይህን መሰል ነገር ሲናገሩ ብናደምጥ አያውቁምና ልናስተምራቸው ይገባል:: መማር የማይፈልጉ ከሆኑና በትምክህት የሚያብጡ ከሆነ ደግሞ ደብረብርሀን አካባቢ 'ሸናባቸው' የሚባል አሳፋሪ የሰው ስም መኖሩን ገልፀን እንግረመንገዳችንን ደግሞ 'ባጫ' የሚለው ስም ለኦሮሞዎች እጅግ ውብ ስም እንደሆነ አጫውተናቸው ማለፍ ይገባናል:: ይህን በመፈፀም ፈንታ ሰልጺ 'ኩራባቸው' የሚል ስም የሚያወጣ ኦሮሞ፤ በድን ነው! ሙት ነው!» ጭብጨባው አዳራሹን ደበላለቀው:: ሀወኒ ቀጠለች፣

«ዳዶአኦ የብሄር ጭቆና መኖሩን ሲያምን እፍአዊ አይደለም:: ደርግ እንደፈፀመው ኦሮምኛ ቋንቋዋ በራዲዮ በመልቀቅ ብቻ የኦሮሞን ህዝብ መብት መጠበቅ አይቻልም:: የኦሮሞ ህዝብ ቋንቋው በሬድዮ ባለመነገሩ አይደለም የተበደለው:: በቋንቋው ያሻውን አለመናገሩ ነው ዋነኛ ችግሩ:: በኦሮምኛ እንማር፣ በኦሮምኛ እንዳኝ ነው ጥያቄያችን:: ባህልና መብታችን ይከበር፣ ራሳችንን እናስተዳድር ነው ጥያቄያችን:: ባለፉት ዘመናት አማርኛ መናገር ለሚቸግረው እንደ ኦሮሞ ግመድ አፍ የሚል ስያሜ ያሸክሙት ነበር - ነፍጠኞች:: እስኪ እነርሱ ኦሮምኛ ይናገሩና ይሞክሩት:: አማርኛ ማወቅ እንደ እውቀት ተቆጥሮ ባለፉት ዘመናት ሁሉ አፈር ድሜ በልተናል:: እድለኛ የተባልን ጥቂቶችም ቋንቋውን እንደምንም ለመድን:: አማርኛ ሊያገለግለን የቻለው ግን እስከ ስድስተኛ ክፍል ብቻ ነበር:: ሰባተኛ ክፍል ላይ ተሸመድምዶ ወገቡን ይዞ ለእንግሊዘኛ አስረከበን:: ያን ጊዜ ታዲያ ኢትዮጵያ በምትባለው ሀገር የምንኖር ብሄር ብሄረሰቦች ሁሉ ለእንግሊዝኛው ግመድ አፍ ሆንን::»

ድንገተኛ ሳቅ አዳራሹን አነቃነቀው::

ሀወኒ ቀጠለች፣

«የኦሮሞ ህዝብ 'የራሱን እድል እስከመገንጠል ድረስ በራሱ ይወስናል' ሲባል 'ከኦሮምኛ ቀጥሎ ሁለተኛ ቋንቋዎችን ምን ይሁን?'

ቢባል ጭምር ያሻንን መወሰን እንደምንችል መረዳት አለብን:: ምናልባት እውቀትን ለማሻሻል የተሻለ አቅም ያለውን እንግሊዝኛን ልንመርጥ እንችል ይሆናል:: እዚህ ድረስና ከዚህም በላይ ሙሉ መብት ይኖረናል::

ዳዴኡኦ - ለህዝቦች ያልተገደበ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እንዲሰጥ ይታገላል ስንል የሌሎችን ሕዝቦች መብት እያፈነ አለመሆኑን ግን በጥንቃቄ መገንዘብ ይገባናል:: ምክንያቱም ጊዜው የበቀል አይደለም:: ሌላው ቀርቶ በክልላችን የሚኖሩ ኦሮሞ ያልሆኑ ወንድሞቻችን በኦሮምኛ ይናገሩ ዘንድ ልናስገድዳቸው አይገባም:: የነፍጠኛው ስርአት እኛን አማርኛ እንድንናገር አስገድዶናል:: ያንን በግልባጩ መፈፀም አይጠበቅብንም:: ያንን ከፈፀምን በቀል ነው:: የኦሮሞ ህዝብ ደግሞ ብቀላ ባህሉ አይደለም:: ከጭቁኑ ያማራ ህዝብ ጋርም ጠብ የለንም:: ነፍጠኝነት ስርአት ነው:: ቅድም እንደገለፅኩት 'ኦሮሞ' የሚል ስማችንን 'ጋላ' በሚለው ተክቶ የሚናገር አንድ ማስቲካ ሻጭ አማራ ቢገጥመን 'ነፍጠኛ' ልንለው ከቶ አይገባንም:: ያ ሰው አላወቂ ብቻነው:: ከስርአቱ መወገድ ጋር በሂደት የሚጠፉ ብጥስጣሽ አመለካከቶች ስሜታዊ ሊያደርጉን አይገባም::»

ሀወኒ አምቦ ውሀ ተጐንጭታ ንግግርዋን አራዘመች፣

«... የነፍጠኞች ትምክህት መገለጫው አያሌ ነው:: በአንድ ወቅት አልንበረከክ ብሎ ቁምስቅል ያሳያቸውን ጀግና የኦሮሞ ህዝብ ለማጥላላትና ስም ለማጥፋት ብዙ ተናግረዋል፤ ፅፈዋል:: ጥቂቶቹን ለመጥቀስ፣ የኦሮሞ ህዝብ በ14ኛው ክፍለዘመን ከኢሲያ እንደፈለሰ፣ ከዚያም ማዳጋስካር ላይ እንዳረፈ፣ ከማዳጋስካር ደግሞ በሞምባሳ በኩል አሁን ኢትዮጵያ ወደምትባለው አካባቢ መምጣቱን የነፍጠኛው ስርአት ደብተራዎች ፅፈዋል:: ይህ ኦሮሞን መጤና ባእድ ለማድረግ የሚደረግ ጥረት ነው::

«... የአማራ ገዢ መደብ 'ምሁራን' እኛን ጋላ፣ ጨካኝ፣ ተከላ፣ ጭፍራ፣ አረመኔ፣ ከባህር የወጣ፣ ብለውን ሲያበቁ፤ ራሳቸውን ደግሞ አማራ፣ አምሀራ፣ የተመረጠ፣ ነፃነት ያለው ህዝብ፣ ሀራ - ሁር - ጨዋ፣ ነፃነት ያለው ወገን - አሽናፊ - ድልነሺ - ዋና አለቃ ሲሉ በመዝገበ ቃላታቸው ገልፀውታል:: ይህ የምላችሁ በነጭ ወረቀት ላይ የታተመ ነው:: እነዚህ ሰዎች አምባገነን ብቻ ሳይሆኑ ቂሎችም ነበሩ:: ትምክህታቸውን በሚመስል መንገድ ማንፀባረቅ እንኳ አልቻሉበትም:: እዚህ ላይ ለያይተን ማየት የሚገባን ቁም ነገር የአማራው ገዢ መደብ ለአማራው ጭቁን ህዝብ የቆመ እንዳልነበር ነው:: የነፍጠኛው





ስርአት ገገርዎች የጠጅ ቤት አግዳሚ ወንበር ላይ ተደርድረው፤ ጠመንጃቸውን እየወለወሉ 'አማራ -ሀራ - ሁር - አም - ሀም- ሀራ- ' ሲሉ ነው እድሜያቸውን የገፉት::»

ግማሽ ሰአት የእረፍት ጊዜ ተሰጠ::

በእረፍት ሰአት የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች ሀወኒን ከበው አድናቆታቸውንና ምስጋናቸውን ያጐርፉላት ጀመር::

«በኦሮሞነታችን ክብር እንዲሰማን አደረግሽ» የሚሉ አስተያየቶችን ጭምር አዳመጠች:: ይህን መሰሉ ፖለቲካዊ ትንታኔ በመፅሀፍ መልክ ተዘጋጅቶ ለኦሮሞ ህዝብ ሁሉ ቢዳረስ ጠቃሚ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ጭምር ገለፁላት፣

ከእረፍት በሁዋላ ሀወኒ ካቆመችበት ቀጠለች፣

«እኛ የዳዴኡኦ - ኢህአዴግ አባላት አማራ ጨዋ አይደለም፤ ጀግና አይደለም የሚል እምነት የለንም:: አማራ ጀግናና ጨዋ ህዝብ ነው:: የዚህ የዘፈን ካሴት ሲገለበጥ ግን ኦሮሞን 'ጨካኝ፣ አረመኔ' እያለ ማዘኑም የለበትም ነው የኛ ጠንካራ እምነት::»

ጭብጨባው ከዳር እዳር አስተጋባ::

«የነፍጠኛው ስርአት አራማጆች የኦሮሞን ህዝብ ከጭቁኑ የአማራ ህዝብ ለማጋጨት በአያሌው ጥረዋል:: ምክንያታቸው በጣም ግልፅ ነው:: ጭቁኑ የአማራው ገበሬ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ካልተጋጨ የነፍጠኛው ስርአት ሀይል ያጣል:: አይበገሬውን የኦሮሞ ህዝብ ለመቀጥቀጥ መሳሪያ የሚያደርጉት ከኦሮሞ ገበሬ ያልተሻለ ህይወት የሚገፋውን ምስኪን የአማራ ህዝብ ነው:: የኛን ሀይል ለመቁዋቁዋም የአማራውን ገበሬ በባዶ ትምክህት ሰማይ ጥግ ሊሰቅሉት ጥረዋል:: በኦሮሞ ላይ የበላይነት ስሜት ያድርበት ዘንድ በሀይማኖቱ በኩል ሳይቀር ሰበካ ያካሂዱ ነበር:: ዛሬ በጥንቃቄ ልናጤነው የሚገባን ጉዳይ ቢኖር ታዲያ፤ ነፍጠኞች ለቀበሩት አሳሳች መርዝ መጠቀሚያ እንዳንሆን ነው:: ጭቁኑ አማራ ትምክህተኛ ገዢዎች የቀበሩትን የተንኮል መርዝ እንዲገነዘብ ማድረግ አለብን:: ያን ጊዜ አጋራችን ይሆናል:: ይህን የምላችሁ በሚቀጥሉት አመታት ሳይሆን ወራት ውስጥ ደርግ ወድቆ የኦሮሚያ ህዝብ ራሱን በራሱ ማስተዳደር እንደሚጀምር ስለማምን ነው::

«...ትምክህተኞች ሰይጣናዊ ባህርይ የተላበሱ እኩዮች ስለሆኑ በነርሱ የንቀትና የጥላቻ ዝባዝንኬ እየተገፋን የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም በሚጐዳ አፍራሽ መንገድ እንዳንጉዋዝ መምከር እሻለሁ:: ከንግዲህ ነፍጠኞች ከፃፉት በላይ ሊናገሩ እንደማይችሉ ከወዲሁ ማመን

አለብን። ምናልባት በ«ራዕየ ማርያም» ያሰፈሩትን ብቻ ባነሳላችሁ የትምክህተኞችን መረን የለቀቀና የከረፋ አመለካከት በቅጡ መገንዘብ ያስችላችሁዋል። የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን 'ማርያም መገንዘብ ያስችላችሁዋል። የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን 'ማርያም የታያት ራእይ' ብላ በ1960 ባሳተመችው በዚህ መፅሀፍ 'ያንዱ ነፍስ፣ በአንዱ ላይ ሲወድቅ አየሁ። እኔም 'ምንድን ናቸው?' ብዬ ልጄን (እየሱስን) ጠየቅሁት። እርሱም 'አራስ መርገም፣ ደንቆሮ፣ እስላም፣ ጋላ፣ ሻንቅላ፣ ፈላሻ፣ ናቸው። ፈረስ፣ አህያና ግመልን በወሲብ የሚገናኙ...' እያለ ይቀጥላል...»

አዳራሹ በድንገተኛ ድንጋጤ ተመታ።

የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች ጆሮአቸውን የተጠራጠሩ ያህል እየተዘዋወሩ ርስበራስ ይታያዩ ያዙ። የሰሙትን ባለማመን ወይም 'የት ነው ያለነው?' በሚል ስሜት ግራ የተጋቡ ገፅታዎች ታዩ። 'ትምክህተኞች በኦሮሞ ላይ ያላቸው ጥላቻና ንቀት ይህን ያህል የገፋ ኖሮአልን?' የሚል ጥያቄ በተሰብሳቢዎቹ ገፅታ ላይ አረብቦ በግልፅ ተስተዋለ።

ሀወኒ ረገብ ባለ ድምፅ ቀጠለች፣

«... ትምክህተኞች እነዚህ ናቸው። ተራ መሀይሞችም ናቸው። የእስለም ክርስትያኖች ሁሉ የሚቀበሉትን ቃል እንኳዋ ማክበር አልቻሉም። እየሱስ ክርስቶስ እንደነርሱ ዘቅጦ ኦሮሞን የሚሰድብ አድርገው አዩት። የአምላካችን ልጅ የሚሉትን መሲህ የሚሰድብ አድርገው አዩት። የአምላካችን ልጅ የሚሉትን መሲህ ከነርሱ ጋር የጠጅ ቤት ወንበር ላይ አኑረው 'አማራ - ሀራ - ሁር- ሀም-' የሚለውን ዜማ ሊያዘፍኑት ሞከሩ። መፅሀፍ ቅዱሳቸውን ወርውረው ሌላ የጥንቆላ ቃል መፃፍ ጀመሩ። ኦሮሞን የሚንቅ እየሱስ ፈጠሩ። ጣኦት አመለኩ። መልሰው ግን እኛን 'ሀይማኖት የለሽ ሊሉን ይሞክራሉ። የነርሱ አምላክ ማነው? እየሱስ? እግዚአብሄር? አይደለም! የነርሱ አምላክ ትምክህታቸው ነው። የባዶ ትምክህታቸው መድረሻ ደግሞ ሄዶ ሄዶ ኦሮሞን ለይቶ የሚንቅ፣ አማራን ለይቶ በሚያከብር እየሱስ በመፍጠር ተጠናቀቀ። ይህ ሀቅ ነው።

ይህ ሀቅ ግን መሀይምነት እንጂ ሌላ ስም ሊሰጠው አይችልም። እኔ በግሌ ትምክህትን ራሱ በሁለት እከፍለዋለሁ። ደንቆሮ ትምክህተኞችና የሰለጠኑ ትምክህተኞች። ጥሎብን ለመቶ አመታት በደንቆሮ ትምክህተኞች ጠመንጃ ስር ወደቅን። ምንም እንኳዋ የትምክህት ጥሩ ባይኖረውም፣ ዛሬ ኦሮሚያ ነፃነትዋን ስትቀዳጅ ከደንቆሮዎቹ ትምክህተኞች የምትረከበው በሺህዎች የሚቆጠሩ አረቄ ቤቶችን መሆኑ ሲታሰብ ከልብ ያሳዝናል። ያንገበግበናል። ይህ በኦሮሞዎች ላይ ብቻ የደረሰ በደል አይደለም።





ጉጃም ብትሄዱም የአማራው ገበሬ ከኦሮሞ ገበሬ ያልተሻለ ህይወት ሲገፋ ነው የምታገኙት። ትግራይ ደሞ የከፋ ሁኔታ ታያላችሁ። የትግራይና የአማራ ህዝብ ከነፍጠኛው ያገኙት ገፀ በረከት ቢኖር 'ሰው' መሆናቸው ስለታመነላቸው ብቻነው። በተቀረ ሌላው ሁሉ ያው ነው። ዛሬ ቢጋራ የምንታገለውና መታገል ያለብንም ለዚህ ነው»

ወረቀቶችዋን ስታገለባብጥ ቆይታ፣ ደሞ ቀጠለች፣

«...ምኒልክና የነፍጠኞቹ ስርአት የኦሮሞን ህዝብ ብቻ ሳይሆን የደቡብ ህዝቦች ወገኖቻችን ላይ ጭምር የከፋና የመረረ በደል አድርሰዋል። የወላይታ ህዝብ በማንነቱና በባህሉ የሚኮራ ህዝብ ነበር። ምንም እንኳዋ በወቅቱ በነበረው የቦና አገዛዝ 'ፍትሀዊ አስተዳደር' ነበር ለማለት ባንደፍርም የወላይታ ህዝብ በራሱ ሰው መተዳደር መቻሉ አብይ ትርጉም ነበረው። ቢያንስ ህዝቡ በማንነቱ እያፍርም ነበር። መሬቱም የወላይታ መሬት ስም መሆኑ ይታወቃል። ህዝቡ ጀግናና ቅን ነው። ወላይታዎች በአካባቢው ገናና ነበሩ። በወቅቱ ምኒልክ ወላይታን ሲወር በህዝቡ ላይ የፈፀመው ግፍ በአይነቱ እጅግ አሰቃቂ ነበር ሊባል ይችላል። ጉጂ ያቃጥሉ ነበር። የማረኩትን ሰው ሁሉ አርደዋል። ህዝቡን ጨፍጭፈው ሲያበቁ እንስሳትን ይወርሱ ነበር። ጦና በተማረከበት ውጊያ ብቻ 18ሺህ እንስሳት ከህዝብ መዘረፉ ተመዝግቦአል። የወላይታ ህዝብ የተበገረው ዘመናዊ ጠመንጃ ከታጠቁ ወራሪዎች ጋር በተራ ጦር በመግጠሙ እንጂ የህልውናው መሰረት የሆነውን ራሱን የማስተዳደር መብቱን ለማስከበር ህዝቡ እጅግ ከባድ መስዋእትነትን ነበር የከፈለው። ነፍጠኞች በጀግናው የወላይታ ህዝብ ላይ የፈፀሙት ግፍ በከብት ዘረፋና በገደላ ብቻ አላበቃም። ሁለት ሺህ ያህል የወላይታ ወጣቶችን ከየጉጆአቸው መንትረው እያወጡ በባርነት ሸጠዋቸዋል። ይህ ድርጊት 'የጥንት ታሪክ' ተብሎ የሚታው አይደለም። በዛሬው የወላይታ ህዝብ አመለካከት ላይ ከባድ ተፅእኖ ማሳደሩ መታሰብና መነገር አለበት። በብሄረሰቡ አባላት ላይ ማንነትን የመሸሽ ዝንባሌ የሚታየው የነፍጠኞች ስርአት በፈፀመው መረን የለቀቀ ግፍና የስነ ልቦና ጦርነት ምክንያት ነው። ነፍጠኞች፣ ዘርፈውና ገድለው ወደ መጡበት ቢመለሱ ደግ ነበር፣ ግን አልሆነም። ሰብእናን የመግደል ክፉ ልማድ ነበራቸው። አንዳንዶቻችን የወላይታን ህዝብ ታሪክ ባለማወቅ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ 'ወላሞ' እያልን ስንጠራቸው ነበር። የወላይታ ህዝብ 'ወላሞ' የሚለውን ስያሜ አለመቀበል ብቻ ሲሆን ቃሉን ሲሰማው ጭምር ክፉኛ ይቆጣል። ምክንያቱ ግልፅ ነው። 'ወላሞ' የሚለው ቃል «ዋ! ላሞ» ከሚለው የመጣ ነው። ነፍጠኞች «ከብቶች ናችሁ! ላሞች ናችሁ» ሲሉዋቸው ስለፈለጉ እንደዘበት የብሄረሰቡ አባላት ላይ የለጠፉት የንቀት ስያሜ

ነው፡፡ ምኒልክና ነፍጠኞቹ የፈለሰፉትን ይህን ስድብ የሀይለስላሴ ስርአት እንዳለ ተቀብሎ ነበር ያስተናገደው፡፡ ደርግም 'ጃንጀሮ' የሚለውን ስያሜ ተቀብሎ አሁን ድረስ ይጠቀምበታል፡፡ 'ጃንጀሮ' በሚል ስያሜ የሚጠራው ብሄረሰብ ትክክለኛ ስም 'የም' ነው፡፡ ጃንጀሮ የተባሉት ተራራ ላይ ወጥተው ወራሪያቸውን በድንጋይ ስለፈጁት ነው፤ ዝንጀሮ ለማለት 'ጃንጀሮ' የሚል ስያሜ ሰጥተው ህዝብን ያህል ነገር በደንታ ቢስነት የሚያዋርዱት፡፡ የነፍጠኛው ስርአት ክርፋት እዚህ ድረስ ጠልቆ ሊሰማን ይገባል፡፡ 'ነፍጠኞች ይሄን ያህል ኦሮሞ ፈጅተዋል' ስንል መሳሳት የሌለበን አንድ ታላቅ እውነት አለ፡፡ የቀረው ግን ከሞት አምልጦአል ማለት አይደለም፡፡ ቀሪውንማ በቁሙ ለመግደል ነው የተሞከረው፡፡ አንድን ህዝብ ደግሞ በቁም ከመሞት የከፋ አደጋ ከቶ ሊገጥመው አይችልም፡፡ ግን አልተቻላቸውም፡፡ እነሆ የጭቁን ህዝቦች አመፅ በርትቶ ጠራርጎ እያጠፋቸው ነው፡፡ የነፍጠኛውን አመለካከት የተሸከመው የፋሺስት ስርአት ዛሬ በመቃብሩ አፋፍ ላይ ይገኛል፡፡

«እስካሁን የገለፅሁትን የማጠቃልለው የነፍጠኛው ስርአት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ህዝቦች ላይ ጭምር በደል ያደረሰ «ስርአት» መሆኑን፤ በደል ስንል ደግሞ ስለተገደሉ ብቻ ማንጎራጎር እንደሌለብን፤ ከፍተኛ አደጋ የደረሰው ከሞት ተርፈው የስነልቦና ቀውስ በደረሰባቸው ወገኖቻችን ላይ መሆኑንና በዚያን ጊዜ የተዘራው መርዝ ደግሞ በኛ ላይ ሳይቀር ተፅእኖ እንደሚያሳድር ተገንዝበን፤ ያንን ክፉ ነቀርሳ ነቅለን ለመጣል፤ በቅድሚያ እያንዳንዳችን በግለሰብ ደረጃ በማንነታችን የመኩራትን ባህል ማዳበር እንደሚገባን በመግለፅ ነው፡፡ ድል የሚገኘውም ሌሎችን በመርገምና በመጥላት ሳይሆን ማንነታቸውን በማክበር ብቻ ነው፡፡ እንግዲህ ወገኖቼ ለአዲሱ ጉዞ እንዘጋጅ፡፡ እኛ ማንነታችንን ካከበርነው ሌሎች ያከብሩናል፡፡ ራሳችን ያልተንከባከብነውን ማንነታችንን ግን ሌሎች ውሀ እያጠጡ ሊኮተኩቱልን እንደማይችሉ ማጤን ይገባናል፡፡»

... ውይይቱ በዚህ መልኩ በሰፊው ቀጥሎ ከዋለ በሁዋላ ከተሰብሳቢዎቹ ጥያቄዎች እየተሰነዘሩ ምላሽ ሲሰጥባቸው ቆየ፡፡ ህወኒና ሰለሞን እየተጋገዙ ማብራሪያዎችን ሰጡ፡፡ በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ የተነሳች አንድ ጥያቄ ግን በተለየ ሁኔታ ትኩረት ሳበች፡፡ ጥያቄውን ያነሳው ነቀምቴ ላይ በመምህርነት በማገልገል ላይ የነበረ አንድ ጉልማሳ የሸዋ ኦሮሞ ነበር፤ በኮንፈረንሱ ስርአት መሰረት ስሙን ተናግሮ ሲያበቃ፣

«ህወሀት የእኩልነትን መንፈስ እስከመጨረሻው ጠብቆ ያኗኗል' ብላችሁ እንድታምኑ ያደረጋችሁ መሰረታዊ ነገር ምንድን





ነው?» የሚል ጥያቄ አቀረበ፡፡

ሰለሞን ምላሽ ሰጠ፣

«... በጋራ የምንጉዋዘው ተመሳሳይ አላማና ግብ ስላለንና እስካለን ድረስ ብቻ ነው፡፡ ስለተማማልን ወይም ስለተዛመድን አይደለም፡፡ ህወሀት በፕሮግራም የሚመራ የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ ለትግራይ ህዝብ የቆመ ድርጅት ነው፡፡ ዳዴኡአም እንዲሁ ለኦሮሞ ህዝብ ይሰራል፡፡ የሚያማክለን ደግሞ የኢህአዴግ ፕሮግራም ነው፡፡ በኢህአዴግ ፕሮግራም የተቀመጠው አሰራርና እምነት ከተጣሰ ግን ኢህአዴግ የሚባል ድርጅት አይኖርም፡፡ በተጨማሪ ከደርግ መንግስት መውደቅ በሁዋላ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ህገመንግስት ያፀድቃሉ፡፡ ህገመንግስቱ የኦሮሞን ህዝብ ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች መብቶች ያከብራል ብለን እናምናለን፡፡ የህዝብ ራስን በራስ የማስተዳደር ዋስትና ህዝቡ ራሱ ተወያይቶ የሚያፀድቀው ህገመንግስት ነው፡፡ የግለሰቦችና የፖለቲካ **ድርጅቶች ቅን ልቦና ለማንም ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲያ ማሰብም ተገቢ አይደለም፡፡»**

ሰለሞን ተናግሮ ሲያበቃ ህወኒ ተጨማሪ አስተያየት ለመስጠት እንደምትፈልግ ገልፃ ቀጠለች፣

«ዳዴኡኦ ከህወሀት ጋር ግንባር ፈጥሮ እየሰራ ይገኛል፡፡ 'ከህወሀት ተፅእኖ ምን ያህል ነፃ ነው?' የሚል መሰለኝ የወንድሜ ጥያቄ፡፡ ጥያቄውን ግልፅ ካደረግነው ለምላሽ አያስቸግርም ብዬ ነው፡፡ ተሳስቼ ይሆን?»

«ልክ ነው!» የሚል ድምፅ ተሰማ፡፡

ህወኒ ቀጠለች፡፡

«በቅድሚያ በራሳችን ልንተማመን ይገባናል፡፡ 'ተከታይ ነን' የሚል ስሜት ከአእምሮአችን ይውጣ፡፡ ይህ አመለካከት እንዴት ሊከሰት እንደቻለ ይገባኛል፡፡ የዛሬ አይደለም፡፡ የመቶ አመት ውጤት ነው፡፡ ጥያቄውን ያቀረበው ሰው ካልተሳሳትኩ ስሙን 'ይታገሱ' ያለ ይመስለኛል፡፡ 'ይታገሱ' የኦሮሞ ስም አለመሆኑ ሁላችንም ይገባናል፡፡ አባቱ ወይም እናቱ የአማራ ስም ለምን እንዳወጡለትም እንረዳለን፡፡ ይታገሱ ምናልባት በቀጣዩ ዘመን ስሜን ወደ 'ሀጐሲ' እንድለውጥ እገደድ ይሆናል ብሎ ቢሰጋም አይደንቀኝም»

አዳራሹ በድንገተኛ ሳቅ ከስሩ የተነቀለ መሰለ፡፡

ሳቁ በቀላሉ አልበርድ አለ፡፡ ህወኒ ፀጥታ ይሰፍን ዘንድ አጨበጨበች፡፡ ውካታው ጋብ ይል ጀመር፣

«በእኔ እምነት ይታገሉ ያቀረበው ጥያቄ የኛ ስጋት ሲሆን አይገባም። ሰለሞን እንደገለፀው ከደርግ ውድቀት በሁዋላ ኦሮሚያ ራስዋን የምታስተዳድረው በግለሰቦች ወይም በድርጅቶች ቸርነትና ፈቃድ አይደለም። በመሰረቱ ደርግን ጠራርጐ ሲያጠፋው የተቃረበውን የህዝብ ትግልና ቁጣ የፈጠረው ጭቆና እንጂ ስልጣን የማግኘት ፍላጐት አይደለም። በምኒልክ ዘመን የነበሩት የአርሲው ሮባ ዳዲ ዛሬ ጊዜው የኛ አይደለም። አይበገሬነታችንን ግን አሳይተናል። ልጆቻችን ወራሪውን ጠላት አርበድብደው የሚያባርሩበት ጊዜ ግን ሩቅ አይደለም። ያ ዘመን እንደሚመጣ ደሞ እርግጠኛ ነኝ ብለው ነበር። ይህን ያሉት ነብይ ስለሆኑ አልነበረም። ህዝቦችን ለዘልአለሙ በባርነት መግዛት ከቶ የማይቻል እውነታ መሆኑን ስለተገነዘቡ ይመስለኛል። ሮባ ዳዲ እንደተነበዩት የጨቋኞች ጊዜ አክትሞአል። የህዝብ ሀይል በርትቶአል። ዛሬ ህወሀት በነፍጠኛው መንገድ ሊቀጥል ቢፈልግ እንኳ አይቻለውም። የኦሮሞ ህዝብ ያቀመዋል። ዋለልኝ መኮንን እንዳለው ወደድንም ጠላንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሶማሌ ብሄርም ይኖራል። ከሶስት ሚሊዮን የማይበልጠው የሶማሌ ብሄረሰብ ከሀያ ሚሊዮን በላይ ከሚሆነው የኦሮሞ ህዝብ እኩል መብት ይኖረዋል። ይህንን ፅንሰ ሀሳብ ነው ልንገነዘብ የሚገባን። ምክንያቱም ህወሀትም ሆነ ዳዴኡኦ እየታገሉ ያሉት በብዛትና በሀይል የሚገኝ የበላይነት ያከትም ዘንድ ነው ብዬ አምናለሁ። ይህ ተቀልብሶ ሌላ መልክ ከያዘ ግን አብረን የምናየው ይሆናል።

ማሰብ ያለብን ግን የዳዴኡኦ ህልውና የሚከበረው በህወሀት መልካም መሆን ወይም አለመሆን ሳይሆን ለኦሮሞ ህዝብ ባለው ታማኝነት ብቻ መሆኑን ነው። የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችን ያሰባሰባቸውም የፀረ ጭቆና አቋማቸው ነው። አባል ድርጅቶቹ በመራራው ትግል ውስጥ፣ በመስዋእትነት መድረክ ላይ በአላማ የተሳሰሩ እንጂ ጠላ ቤት ተገናኝተው ማህበር ያቋቋቁዋሙ ታላላቅ እድሮች አይደሉም ...»

አዳራሹን ያናጋው ሳቅ የጀመረችውን ሳያስጨርሳት ቀረ። ስሜታዊነትዋ ለራስዋም አሳቃት። ሳቁ ፈጥኖ አላባራም ...

በዚያን እለት ማምሻውን ሀወኒ ሀየሎም ካረፈበት ጊዜያዊ ማዘዣ ጣቢያ ስትደርስ ያልጠበቀችው ትርኢት ነበር የገጠማት። በሞቀ ወሬ ላይ ቤቱ በኢህአዴግ አመራር አባላት ተሞልቶአል። እጁን ነበሩ። በጨለማው ውስጥ ክንፈ ገብረመድህንን አየችው። እዱ እያወራጨ ይናገር ነበር። ኩምሳም አለ። አባዱላ ገመዳ፣ አዲሱ ለገሰ፣ አሊ ኢብራሂም፣ ሁሉም የኢህአዴግ አመራር አባላት ናቸው።





«ገቢ» አላት በጥበቃ ስራ ላይ የነበረው ታጋይ «...አንቺን እየጠበቁሽ ነው።»

ዘልቃ ገባች።

የኢህአዴግ መሪዎች ከየተቀመጡበት እየተነሱ የሞቀ ሰላምታ አቀረቡላት።

በምሽቱ ተሰባስበው የሚያወጉት በእለቱ ስለተካሄደው ኮንፈረንስ ነበር። ሀወኒ ስምዋ ሰማይ ጥግ ደርሶ ጠበቃት። የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች በሀወኒ ማብራሪያ መመሰጣቸው፣ አቀራረብዋ በእጅጉ ሳቢ እንደነበር እያነሱ ሲያወጉ አመሹ።

- 4 -

ግንቦት 13 ቀን፣ 1983 ኰሎኔል መንግስቱ ሀይለማርያም አገር ጥሎ ሸሸ። የአለም ሚዲያዎች ይህንኑ ርእሰ ወሬ ከዳር እዳር ነዙት። ትኩረት ወደ ኢትዮጵያ ሆነ። የኢህአዴግ ስም በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እየተነሳ ይወገዝና ይወደስ ገባ። ህዝቡ የለውጡን አየር ሙሉ በሙሉ ይተነፍሰው ያዘ። የኢህአዴግን ማንነት በቅጡ የማያውቁ ሳይቀሩ «ከጭራቁ ደርግ የማይሻል ከቶ አይኖርም» በሚል ስሜት ኢህአዴግን በተስፋ ለመቀበል ተዘጋጁ።

ወሬው ባሻው መንገድ ይጉዋዛል ...

የመሀል አገር ሰዎች «የኢህአዴግ ተዋጊዎች አንድ ፍሬ ያከክሳሉ» እያሉ አዳነቁ። «የሰላም ጥሪ» የመሳሰሉ ቃላት መደመጥ ጀመሩ። በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን «ሰላማዊ የፖለቲካ ውድድር» የመሳሰሉ ቃላትን ማነሳሳት ጀመሩ።

አዳዲስ ቃላት ፈሉ ...

«ሀሳብን በነፃ መግለፅ» «ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብት» የመሳሰሉ ጉዳዮች ከተረሱበትና ከተወረወሩበት ብቅ ብቅ አሉ። «ኤርትራ» ርእሰ ወሬ ሆነች። «የባህር በር ማጣት» የሚያስተክዝ አጀንዳ ነው ሲሉ የሚወተውቱ ሰዎች ተደመጡ። «እናንት አስመሳይ ተከላዎች! በባህር በር ስም ፈጃችሁን! በኢትዮጵያ አንድነት ስም ጨረሳችሁን! ደማችንን እንደ ሽንኮራ አገዳ መጠጣችሁት! መብቶቻችንን ነፍጋችሁ በራስ የመተማመን ወኔያችንን ሰለባችሁት! ሆዳሞች! አሁን ከአባይ ወንዝ የረዘመ ምላሳችሁን ሰብስቡ! በቃችሁ! ጊዜው የጀግና ታጋዮች ነው! ጊዜው የህዝብ ልጆች ነው!» የሚሉ ስሜታዊ ቁጣዎች እዚህም እዚያም አስተጋቡ።

ኢህአዴግ በርግጥም በድል ደጃፍ ላይ ነበር ...

በሰላም በትግል - በፋና ኢ.ህአዴግ - በዘመቻ ቴዎድሮስ - በዘመቻ ቢሉሉማፍ ወልቂጡማ - በዘመቻ ዋለልኝ ጉዞዎቹ የድልን አዝመራ አፍሶ በወርሀ ግንቦት ማብቂያ አዲስ አበባን ቀለበት ውስጥ አስገባት:: የኢትዮጵያን መንግስት አስተዳደር በጊዜያዊነት ለመረከብ ተዘጋጀ:: ወደ አዲስ አበባ የሚያስገቡ በሮች በሙሉ በቁጥጥር ስር ዋሉ::

* * *

ሀወኒ ዋቆ በዚህ ታሪካዊ ከበባ ላይ መገኘት ሳትችል ቀረች:: በዳግም የአምቦ ማጥቃት በክላሽንኮቭ ጥይት ተመታች:: ሀየሉም ይህን ክፉ ዜና ሲሰማ በእጅጉ ደነገጠ፣

«ተሰዋች!?» ሲል ጮኸ::

አለመሰዋትዋን ገለጡለት:: ወዳለችበት በርሮ ሲደርስ ወደነቀምቴ ሊወስድዋት መኪና ላይ ሲጭኑዋት ደረሰ::

«ሀወኒ!»

ፈገግ አለች - የደከመ ፈገግታ::

አይኖችዋ ግን ብሩህ ነበሩ:: ሀየሉም ወደ ታጋዩ ሀኪም ዘወር አለ፣

«እንዴት ናት?»

«ሆድዋ ላይ ነው:: ደህና ናት:: ደም ግን ፈሶአታል!»

«አትረበሽ!»አለችው - ሀወኒ «... ደህና ነኝ::»

«ወደፊት አትለፊ ብዬሽ ነበር» ሲል አልጐመጐመ::

«ሀየሉም!» አለች::

መልስ አልሰጣትም::

ያንኑ ሲጋራውን ላይ በላይ እየማገ ተወራጨ::

«አንድ ግጥም ልንገርህ?»

አሁንም መልስ አልሰጣትም::

የመኪናዋ ሞተር ሲቀሰቀስ ሀየሉም ተጠግቶ ጉንጭዋ ላይ ሳማት::

በጆሮዋም፣ «ኦሮሞዎች ይፈልጉሻል:: መሞት የለብሽም» አላት::

* * *





... አዲሳባ ተከባለች::

የአዲስ አበባ በሮች በታጋዮች ታጥረዋል:: አዲስ አበባን የከበበውን ጦር አማክለው የሚመሩት ማዘገዣ ጣቢያቸውን ለገዳዲ ላይ ያደረጉት ፃድቃን ገብረተንሳኤና አበበ ተክለሀይማኖት (ጆቤ) ነበሩ:: ታምራት ላይኔ መለስ ዜናዊን ተክቶ በበላይነት ይመራል:: በየበሮቹ ያሉት የኢ.ህአዴግ ከፍተኛ አመራር አባላት የመጨረሻዋን መመሪያ ከለገዳዲ ይጠብቃሉ:: በደብረዘይት መንገድ ሳሞራ የኑስና በረከት ስምዖን፤ በአምቦ ሀየሉም አርአያና አለምሰገድ ገብረአምላክ፤ በሰንዳፋ ምግበና ገብረኪዳን እንዲሁም ሀይሌ ጥላሁን፣ አዲሱ ለገሰ፣ ባጫ ደበሌ እና ሌሎችም የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት አዲሳባን አሸግረው እያማተሩ፤ የጦርሜዳ መገናኛ ሬዲዮኖቻቸውን ከበዋል::

ስዬ አብርሀ ትግራይ - ሀገረ ሰላም ነበር:: መለስ ዜናዊ ለንደን:: በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የአፍሪካ ጉዳይ ሀላፊ ሚስተር ኸርማን ኮሆን ደርግ፣ ኢ.ህአዴግና ኦነግን ለማደራደር በጠራው ስብሰባ ላይ ለመገኘት ከትግራይ በረሀ ወደ ለንደን አቅንቶ እዚያው ነበር:: ስዬ ከለገዳዲና ከለንደን ያለማቋረጥ ግንኙነት ያደርጋል:: አይሮፕላኖች አዲሳባ ላይ እንዳያርፉና ከዲሳባም እንዳይነሱ የኢህአዴግ መሪዎች ጥብቅ ትእዛዝ በመስጠታቸው እያንዳንድዋ ደቂቃ ትንፋሽ ታሳጥራለች:: የአለም ሚዲያ ትኩረት አዲስ አበባ ዙሪያ ላይ አነጣጥሮአል:: አዲስ ነገር ሞልቶአል:: ደግና ክፉ አዳዲስ ነገሮች ...

ወሩ ወርሀ - ሙዋርት ነው::

አዲሳባ የሞቃዲሾና የሞኖሮቪያ እድል እንደሚገጥማት ሁሉም ተንብዮ አብቅቶአል:: የሲጋት ወሬ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ጆሮ የሚያቃጥልበት ጊዜ ነበር:: የኢ.ህአዴግ ባላንጣዎች 'የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት - እስከመገንጠል' የሚለው አንቀፅ ተግባራዊ ከሆነ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር እንደሚያከትምላት እየወተወቱ የድፍን ኢትዮጵያን ህዝብ አስጨነቁ:: መገንጠል በኤርትራ እንደማያበቃ፤ የኦሮሚያ ጉዳይ ራሱ ያለቀለት መሆኑን አወጁ:: 'ሻእቢያና ወያኔ ኢትዮጵያን የማጥፋት ድብቅ አጀንዳ አላቸውና የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ አይንህን ክፈት' ሲሉ አስጠነቀቁ:: በዚሁ ሰሞን ታዲያ የኤርትራ ህዝብ ታጋዮች መሪ ኢሳይያስ አፍወርቂ ስለ ተቃዋሚዎች ተጠይቶ አንድ አጭር ምላሽ ሰጠ::

«... ውሾቹ ይጮሀሉ... ግመሉ ጉዞውን ቀጥሎአል::»

* * *

... አዲሳባ ተከባለች::

እለቱ ግንቦት 19 ቀን ነው - 1983:: በወታደራዊ የሰአት አቆጣጠር 16:30:: የኢህአዴግ ዋና ፀሀፊ የመለስ ዜናዊ መልእክት የህወሀት አመራር ዋሻ ከሚገኝበት ሀገረሰላም ደረሰ - በሳተላይት:: መልእክቱ የለንደኑ ድርድር መፍረሱንና የመጨረሻው ዘመቻ እንዲፈፀም የሚያዝ ነበር - ዘመቻ ውጋጋን:: ስዬ አብርሀ ከለገዳዲ ጋር ተገናኘ:: እና አጭር መመሪያ::

ለገዳዲ ከፍተኛ ኮረብታ ላይ የነበረው ጻድቃን ገብረትንሳኤ በጦር ሜዳ የመገናኛ ሬድዮው በየበሮቹ ያሉትን ኮማንደሮች ይፈልግ ጀመር::

እነሆ ... ወገግ ከማለቱ በፊት ዘመቻ ውጋጋን ይጀመራል:: ከሚቀጥለው ቀን ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ በአይነቱ ልዩ የሆነ ውጋጋን መታየቱ የማይቀር ነው:: ውጋጋኑ መታየት ሲጀምር ደግሞ የኢህአዴግ ሬድዮ አብዛኛው ህዝብ በድል አብሳሪነትዋ የሚያውቃትን «የሰሜኑ ኮከብ» የተሰኘችውን የትግል ሜዳ ዘፈን ለመጨረሻ ጊዜ ያስደምጣል:: ለመጨረሻ ጊዜ ...





# ሰማዩም

# የኦሮሞዎች ነው

## ምእራፍ አስር

### - 1 -

የኢህአዴግና የኤርትራ ተዋጊዎች የደርግን ሰራዊት እንደ አቡዋራ አቦነኑት:: የኤርትራና የኢትዮጵያን ምድርም ከጥግ እስከ ጥግ ነፃ አወጡዋቸው:: ሊማረክ የፈቀደውን ማረኩት:: አሻፈረኝ ያለ በደረቱ ሙሉ ጥይት ታቀፈ:: እጅግ አብሪተኛ የነበሩትና ራሳቸውን ከፈጣሪ በላይ የሰየሙት የደርግ ሹማምንትም በራዲዮ የተደረገላቸውን ጥሪ ያለማወላወል ተቀብለው ወደ ወህኒ በሰልፍ ሲገቡ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ለህዝብ ታየ::

በርግጥ የጦር መሳሪያው ጦርነት አልቆአል:: ሰላማዊው

የትግል መድረክ ግን ተከፍቶአል፡፡ ሆኖም የጦር መሳሪያው ትግል ስለማለቁና ሰላማዊ መድረክ ስለመከፈቱ እርግጠኛ ያልሆኑ አያሌ ነበሩ፡፡

በተለይም በብሄር መደራጀት የፈጠረው ስጋትና ውዥንብር ማንኛውም ዜጋ ጆሮውን አንቅቶ የሚከሰተውን እንዲያዳምጥ አድርጎታል፡፡ ከዚህ ቀደም እምብዛም በግልፅ ያልተሰሙና ያልተለመዱ ስሜቶች በአደባባይ ፀሀይሞቁ፡፡ የአማራነት ... የኦሮሞነት ... የትግራዋይነት ... የወላይታነት... ስሜቶች! እንደሰደድ እሳት ይያያዙ ጀመር፡፡

*   *   *

አስመራ ከተማ በታላቁ ቤተመንግስት በተዘጋጀው ልዩ የራት ግብዣ ላይ አኖሌ ዋቆ የተከበረ ስም ይዞ ተገኝቶአል፡፡ የኤርትራ፣ የኢህአዴግና የኦነግ ከፍተኛ ባለስልጣናት የግብዣው ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ ግብዣው የኤርትራ ህዝብ ለነፃነቱ ያደረገው ትግል በድል መጠናቀቁን አስመልክቶ እንደተዘጋጀ ይነገር እንጂ ድብቅ ተልእኮ እንዳለው ግልፅ ነበር፡፡ ይህን በመሰሉ የመገናኛ መድረኮች በርካታ ቁምነገሮች እንደሚፈፀሙ ፖለቲከኞቹ አሳምረው ያውቃሉ፡፡ የዚህን ግብዣ ትኩሳት የጨመረው የኤርትራው ኢሳይያስ አፍወርቂ፣ የኢትዮጵያው መለስ ዜናዊ እንዲሁም የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መሪዎችና ታላላቅ ዲፕሎማቶች በመገኘታቸው ብቻ ሳይሆን ወቅቱ ራሱ በርካታ ውዥንብርና አከራካሪ ሀሳቦች ያሉበት በመሆኑ ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ ከሰሜን አሜሪካና ከአውሮፓ ተጠርተው የመጡ ምሁራንም ጥቂት አልነበሩም፡፡

የኢህአዴግ ሰዎች የእንግዶቹን አመለካከት ይፈትሻሉ፡፡ የኢህአዴግ ሰዎች እንግዶች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ብቃታቸውን ይገመግማሉ፡፡ እንግዶች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ብቃታቸውን ይገመግማሉ፡፡ እንግዶች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ብቃታቸውን ይገመግማሉ፡፡ እንደልብ እንዲያወጉ ሲባል በግብዣው አዳራሽ ጥቂት መቀመጫዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ይህም ትኩሳቱን አናረው፡፡ ማንም ሰው ወደ ኢሳይያስም ሆነ ወደ መለስ ጠጋ ብሎ ማዳመጥና ሀሳብ መሰንዘር ይችላል፡፡ የሁለቱ ሀገሮች የፀጥታ ሰዎች ረጃጅም ጆሮዎቻቸውን የቀሰሩበት! አይናቸውን እንደባውዛ ያበሩበት ግብዣ ነበር፡፡

አኖሌ ዋቆ ለወጣትነቱ የሚስማማ ቀላል ጃኬት ለብሶአል፡፡ ጂንቶኒኩን እስኪደጋግም ድረስ እጅግ ቀላል ጉዳዮችን ከተለያዩ የፖለቲካ ሰዎች ጋር ሲጨዋወት ቆየ፡፡ በተለይም በአስመራ ስለፈፀመው ጀብዱ የኢህአዴግ ሰዎች ሲያነሱለት «እንዴት አወቁ?» የሚል ግራሚ ሳያሳድር አልቀረም፡፡





የተፈፀመውን ሁኔታ እንደዋዛ ማብራራት ሲጀምርም አድማጩ ከሁለት ወደሶስት እያለ ይሰፋ ጀመር፡፡ አብርሃ ፀሎት ዊስኪ የሞላ ብርጭቆውን ይዞ ድንገት ከተፍ ሲል አኖሌ ንግግሩን ገታ አደረገ፡፡ አብርሃ እንደደረሰ ይቅርታ እንኳዋ ሳይጠይቅ ጣልቃ ገብቶ የአኖሌን አጭር ግለ ታሪክና ጀብድ ያምበለብለው ያዘ፡፡ በአለም ላይ ከዚህ በላይ ጀብዱዎች እንደሚፈፀሙ አብርሃ ፀሎት ካብራራ በሁዋላ «የአኖሌን ልዩ የሚያደርገው ግን በዚህ አይነት ሙያ ምንም ስልጠና ባለመውሰዱ ነው» ሲል አወደሰው፡፡

«አንድ ጊዜ ላቁዋርጣችሁ!» አለ አንድ ሰው፡፡

ገፁ ላይ ግርማ ሞገስ የሚነበብበት፣ ጠይም፣ ሽበት የወረረው ሙሉ ሰው ሲሆን የለበሰው ግራጫ ሱፍ ሰውነቱ ላይ ተስማምቶአል፡፡ ንግግሩን በርጋታ ጀመረ

«ወንድሜ በቅድሚያ ብንተዋወቅ!» አለው አኖሌን፡፡

«አኖሌ ዋቆ» አለ፡፡

«ዶክተር ቡልቻ ዋቅጋሪ እባላለሁ፡፡ የOLF ሰው ነኝ» ካለ በሁዋላ «... እስካሁን ስላንተ የተነገረውን ታሪክ እንደማደምጠው ከሆነ፣ ጀርመን ሀገር ተምረሃል ... ከዚያም እንደማንኛውም ቅን ዜጋ ኢትዮጵያ የምትባለዋን ሀገርህን ለማገልገል ብለህ ተመለስክ፡፡ ተያይዞም አርሲ - ቡርቃ ያሉ ኦሮሞዎች አመፅ ሲያነሱ ውስጥህ ተዳፍኖ የነበረው የፖለቲካ ወይም የብሄርተኝነት እሳት ተጫረ፡፡ ቢጫርም ግን የትላይ ማቀጣጠል እንደነበረብህ አልገባህም፡፡ ሁዋላ የደርግ ሰዎች ሊተናኮሉህ ሞከሩ፡፡ ይህ ግን አልተስማማህም፡፡ የላቀ ጀብዱ ፈፅመህ አሳግጠህባቸው አመለጥክ፡፡ እንደ ቼ ጉቬራም ለሌሎች ህዝቦች አርነት ታገልክ፡፡ ማለትም ለኤርትራ፡፡ ይህ ሁሉ እጅግ ድንቅ ታሪክ፣ የሚያኮራ ተግባር ነው፡፡ እዚህ ያለነው ሁሉ ይህን ወጣት ከልብ እንደምናደንቀው ይሰማኛል ...»

ዶክተሩ ይህን ብሎ በአኖሌ ዙሪያ ያሉትን ሁሉ ገረመመ፡፡ ከዚያም ቀጠለ፡፡ «... በዚህ መቼም እንስማማለን፡፡ ልጅ አኖሌ! አሁን እንደማየው ግን ያለፈ ታሪክህ መልሶ ለራስህ የመሰጠህ ይመስለኛል፡፡ እዚህ ላይ ተቃዋሚህ ነኝ፡፡ አንተ ኦሮሞ ነህ፡፡ እንደ ኦሮሞነትህ ግን ወገኖችህን የሚያኮራ ተግባር እስካሁን አልፈፀምክም፡፡ ጀብድ አያኮራም፡፡ የሚያኮራው ህዝባዊ ተግባር ነው፡፡ የደርግን ደምበኛን ጄኔራሎች አታለልክና ምን ይጠበስ? ይሄ ለኦሮሞ ህዝብ ምኑ ነው? ቡርቃ ያሉት ኦሮሞዎች አስመራ ላይ የፈፀምከው ጀብድ ቢነበብላቸው የሚያጨበጭቡልህ ይመስልሃል? ስለ ዝምተኛው ቡርቃም የነገርከን የሚመስጥ ተረት አለ፡፡ ዋቆ አባዱላ ቡርቃ

አንገቱን ስለደፋበት ምስጢር ያወረሱህን ታሪክ አጫውተኸናል:: አንገቱን ስለደፋበት ምስጢር ያወረሱህን ታሪክ አጫውተኸናል:: እና ቡርቃ አንገቱን የደፋው ጀግና አሮሞ! ጀብደኛ አሮሞ ባለማየቱ ይመስለሃል? በግለሰብ ደረጃ ጀግና የነበሩ አሮሞዎችማ ሞልተዋል:: አንዱ ራስ ጉበና ነው:: ራስ ጉበና ለኦሮሞ ህዝብ አልሰራም እንጂ ጀግናማ ጀግና ነበርኮ:: የቡርቃ ወንዝ ታዲያ በራስ ጉበና ጀግንነት ተማርኮ ለምን ቀና አላለም? ኦሮሞው አበበ ቢቂላ በሩጫው አለምን ጉድ ሲያሰኝ ቡርቃ ለምን እንዳቀረቀረ ቆየ? አብዲሳ አጋ ፋሺስት ጣሊያንን ሲያንቀጠቅጥ ቡርቃ ለምን ከዝምታው አልተላቀቀም? ለዚህ ጥያቄ መልስ እፈልጋለሁ::» ብሎ ፈገግ አለ::

ዊስኪው ይዞራል:: ጂን ቶኒክ ይቀዳል:: ጣፋጭ ብስኩት ይሸከረከራል::

በአኖሌ ዙሪያ ያሉት የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ሰዎች እርስ በርስ ይተያዩ ጀመር:: አኖሌ የወረደበትን የወቀሳ ዶፍ በትእግስት ካዳመጠ በሁዋላ፣

«እኔ የፈፀምኩት ተግባር ለኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል አላልኩም:: ይህ ማንኛውም ሰው ስለገጠመኝ ... 'የኦሮሞ እንደሚያወጋው ድንገት የተነሳ ቀላል ጨዋታ ነው:: 'የኦሮሞ ህዝብ ምን ይፈልጋል?' የሚለው ጥያቄ ሌላ አጀንዳ ነው:: የኦሮሞን ህዝብ ጥያቄ አስመልክቶ የግል አቋም እንደሚኖረኝ የኦሮሞን ህዝብ ጥያቄ አስመልክቶ የግል አቋም እንደሚኖረኝ የሚስቱት አይመስለኝም::» ብሎ ፈገግ ካለ ግን ዶክተር ቡልቻ የሚስቱት አይመስለኝም:: ምን ይመስል በሁዋላ «... የሆነስ ሆነና የቡርቃ ህዝብ ቁጣ ምን ይመስል እንደነበር ቅድም አጫውቼያችሁዋለሁ:: ምርጫ ስላልነበረኝ ... ወገኖቼ ከከንቱ እልቂት እንዲተርፉ! የቁጣቸው ነበልባል ላይ ስለቻለስኩት ቀዝቃዛ ውሀ ጭምር በግልፅ ቅድም ገልጫለሁ:: ለኦሮሞ ህዝብ እንደሚታገል ከገለፀ እንኩዋ ሀያ አመት የተጠጋው OLF ይህን ሁሉ አመታት ምን ሲሰራ እንደከረመ ያስረዱኛል?»

ሳቅና ጉምጉምታ ተከተለ::

አኖሌ ሞቅታ ተሰማው:: ዶክተር ቡልቻ ግን የዋዛ ሰው አይደለም:: የአኖሌን ጥያቄ በቀልድ ሊያልፍ ሞከረ:: አጠገቡ የነበረውን ሰው ገርመም አድርጎ ...

«የኢህአዴግ ኦሮሞዎች 'OLF' ን መውቀስ ስለሚያስደስታቸው ለዚህ ጥያቄ በቅድሚያ ማብራሪያ ይሰጡ ዘንድ እድሉን ለእነርሱ ከሰጠን በሁዋላ እኔ ብናገር ሳይሻል አይቀርም:: አይመስልህም እንዴ ኩምሳ!» አለው::

አኖሌ «ኩምሳ» ወደተባለው ሰው ተመለከተ:: ጉልማሳ





ነው:: ጠይም:: የሚናገር አይመስልም:: ሲያዳምጥ ነበር የቆየው::

ኩምሳ ቀላል ፈገግታ አሳይቶ ንግግር ጀመረ፣

«የዳዴኦኦም ሆነ የኢህአዴግ አሲያም የኦነግ ታሪክ ግልፅ ነው:: አንዱ ትግሉ ተሳክቶለት ሊሆን ይችላል:: ሌላው እንደታሰበው ላይገፋ ቢችልም በትግል ጀማሪነት አክብሮት ሊቸረው ይችላል:: ዞሮ ዞሮ ለተሳኩትም ሆነ ላልተሳኩት የተለያዩ ምክንያቶች ሊሰነዘሩ ይችላሉ:: ምክንያቶቹ ላይ ላንግባባ እንችላለን» ካለበሁዋላ እንደወዛ ንግግሩን አራዘመ::

«... ወደፊት ለምናደርገው ሰላማዊ ትግል ግን ያለፈ የትጥቅ ትግል ታሪካችን ብቻውን ድል አያመጣልንም:: በቀጣዩ አመታት የኦሮሞ ህዝብ በፈፀምነው ጀብዱ ላይ ማርክ ለመስጠት ጊዜና ፍላጎት የሚኖረው አይመስለኝም:: አስታዊና ተጨባጭ ድርጊታችንን ማየት ይፈልጋል:: አንድ ህዝብ ሃምሳ አመት ታግሎ ነፃ ያወጣውን የፖለቲካ ድርጅት አልፈልግህም ሊለው ይችላል:: በርግጥ 'ህዝብ ያልደገፈው ታግሎ ያሸንፋል ወይ?' የሚለው ራሱ አከራካሪ ሊሆን ይችላል:: ህዝቡ መስሎት ወይም ምርጫ አጥቶ ደገፈ ቢባል እንኩዋ አሸናፊው የፖለቲካ ፓርቲ ከድል መልስ ለህዝቡ ተጨባጭ ለውጥ ካላመጣ ህዝቡ አሽቀንጥሮ ሊጥለው ይችላል:: ስለዚህ ኦነግና ዳዶኦኦ በታሪካቸው ሳይሆን በተጨባጭ ድርጊታቸው በሚታገሉለት ፕሮግራም የሚመዘኑ ይመስለኛል:: ይልቁን ግን አኖሌ ስለ ቡርቃ አርሶ አደሮች የገለፀው ታሪክ በጣም መስጦኛል:: ይህን መሰል የህዝብ ስሜቶችና ታሪኮች ተሰፋ ያሳድራሉ...» ሲል አሳረገ::

የኩምሳ ንግግር ውጥረቱን አረገበው:: በአኖሌ ዙሪያ የተሰባሰቡት እንግዶችም ቀስበቀስ ተበታተኑ::

ዶክተር ቡልቻም በሌላ ሰው ተጠርቶ ገለል አለ:: በመጨረሻ አኖሌ፣ አብርሃ ፀሎትና ኩምሳ ቀሩ::

አብርሃ ፀሎት ወደ ኩምሳ እያመለከተ፣

«የኦህዴድ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ነው» ሲል ለአኖሌ አስተዋወቀው:: ከዚያም ትቶአቸው ዘወር አለ:: አኖሌና ኩምሳ ብቻቸውን ቀሩ::

አኖሌ ነበር ጨዋታ የጀመረው፣ በኦሮምኛ::

«የህወሀት ጥገኛነታችሁን፤ እንደ አመራርም ብቃት የሌላችሁ መሆናችሁን አንስተው የሚወቅሱዋችሁ አሉ» አለው በርጋታ::

ኩምሳ ፈገግ አለ፣

«የሚገርመኝ ባይወቅሱን ነበር። የዳዴኦ አላማ በፕሮግራሙ ተቀምጦአል። ያን አይቶ መነጋገር ይቻል ይመስለኛል። በተቀረ ግን የሰው ሀይልን በተመለከተ አሁን ያለው አመራር የመሪነት ቦታውን በርስትነት አልያዘውም። የሰው ሀይል ይለዋወጣል። ፕሮግራሙ ግን ዘላቂ ነው» ካለ በሁዋላ «አይተኸዋል ፕሮግራሙን» ሲል ጠየቀው።

አኖሌ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ።

«እንዴት አየኸው ታዲያ?» አለ ኩምሳ ጉዋጉቶ።

«ጥሩ ነው» አለ አኖሌ «... በርግጥ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ልዩነት አለኝ። በተለይ አደረጃጀት ላይ»

«አልገባኝም» አለ ኩምሳ።

አኖሌ ሩቅ ሲያስብ ቆየና፣

«መልካም! የዳዴኦ ፕሮግራም ጥሩ ነው። በትጥቅ ትግሉም መጠነኛ ልምድ አካብቶአል። ሆኖም ዳዴኦ በርግጥ የኦሮሞን ህዝብ ያለተፅእኖ በማገልገል ላይ መሆኑን በተጨባጭ ራሱን እንዲመዝን፤ውስጣዊ ጥንካሬውንም ከራሱ ያገኝ ዘንድ ለምን ከኢህአዴግ አባልነት ራሱን ነፃ አያደርግም?»

ኩምሳ ለጥቂት ሰከንዶች በዝምታ ቆይቶ ምላሽ ሰጠ፣

«ከኢህአዴግ አባልነት መውጣት ይቻላል። ግን ለምን? በቂ ምክንያት ያስፈልጋል።»

«ሁለት ምክንያት ልስጥህ» አለ አኖሌ «የመጀመሪያው ኢህአዴግ ማለት ከፍተኛ አቅም ባላቸው የትግራይ ሰዎች እጅ ያለ ድርጅት ነው። ስለዚህ የዳዴኦ ታዛዥነት አይቀሬ ይሆናል። በራስ የመተማመን ወኔያችሁ እየሙዋሙዋ ይሄዳል። የአባላቱ አስተሳሰብ እያስፈቀዳችሁ የምትሰሩ ከሆነ አታድጉም። የአባላቱ አስተሳሰብ የቀጭጭና ድርጅቱ የኦሮሞን ህዝብ በአግባቡ የማገልገል አቅም እንዳያጣ እሰጋለሁ።»

ኩምሳ በፈገግታ ተጥለቅልቆ ነበር ለምላሽ የተዘጋጀው፣

«ውድ አኖሌ...» ሲል ጀመረ «... የሰነዘርከው አስተያየት በትክክል ለኦሮሞ ህዝብ ከማሰብ የመጣ ነው ብዬ ከልብ አምናለሁ። ስጋትህ ግን እውን እንደማይሆን አንዳንድ መረጃዎችን ልስጥህ። የመጀመሪያው የኢህአዴግ አሰራር ነው። በአገራችን ፕሮግራሙ ላይ ያስተመጠውን ሁሉ ሳያዛንፍ በመፈፀም ላይ የሚገኝ የፖለቲካ ድርጅት ቢኖር ኢህአዴግ ብቻ መሆኑን አረጋግጥልሀለሁ። እኛ





የኢህአዴግ አባላት የብሄር ብሄረሰቦች መብት ስንል፤ ሰብአዊ መብት ስንል፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ስንል አፍአዊ አይደለም። የኢህአዴግ አባላት ትልቁ ሀብታቸው ነፃነታቸው ነው። እምነታቸውን ያለመሸማቀቅ ማራመድ መቻላቸው ነው። ወደፊት ኢህአዴግ ወይም ሀወሀት የኦሮሚያ የውስጥ ጉዳዮች ላይ እጃቸውን እያስገቡ እንዳሻቸው ሊያሽከረክሩ የሚችሉበት እድል ከቶ አይኖርም። ምክንያቱ ህግ ስለማይፈቅድ ብቻ አይደለም። የህወሀት ትግል ራሱ የራስን መብት ለማስከበር የተደረገ ተጋድሎ በመሆኑ ነው። ራስን አለማስተዳደር የሚያስከትለውን አደጋ የህወሀት ሰዎች ከማንም በላይ ያውቁታል። የኢትዮጵያን ህዝብ ከኢህአዴግ ታጋዮች በላይ ቀርቦ የማያውቅ አለ ብትለኝ ላሳር ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ህገ መንግስት ይኖራል። የኦሮሞ ህዝብ የወሳኝነት መብቱን በህግ ካረጋገጠ፤ ስልጣን በህዝብ እጅ ከሆነ በሌሎች ህዝቦች ላይ ለመፈንጨት የሚሻ ሀይል ሁሉ የግድ ይዳከማል። አሁን የምናወጣው ህግና የሚተገበረው አሰራር ነፍጠኛውን ለማዳከም ብቻ አይደለም - የሚያገለግለው፤ የዘመናችን ማንኛውም የፖለቲካ ሀይል ጨቁዋኝ ፍላጉቱን በስራ ላይ እንዳያውል የሚቆጣጠር ህግና አሰራር ነው የሚኖረው። የኢህአዴግ ሰዎች ባብዛኛው እድሜያችንን ያጋመስን ነን። ትውልድ ያልፋል። ትውልድ ይተካል። ለኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች የሚቀርላቸው ፀጋ ህጉ ነው። ጉዳዮችን በዚህ መልኩ ሰፋ አድርገን ማየት አለብን። ዛሬ በስራ ላይ የሚውለው ህግና አሰራር ወደፊትም የኦሮሞ ህዝብ በጨቋኞች ቀንበር ስር እንዳይወድቅ የሚጠብቀው ዋስትናው ይሆናል ብለን ነው የምናምነው። ለኦሮሞው ብቻ አይደለም። ለጋምቤላ፣ ለትግራይ፣ ለአማራ፣ ለሶማሌ ለሁሉም ህዝቦች ማለት ነው። ስለዚህ ስጋትህ ተገቢ አይመስለኝም። ተጨባጩ እውነታ ጨርሶ አጠራጣሪ አለመሆኑን ነው ላረጋግጥልህ የምሻው።»

አኖሌ የጥርጣሬ ምላሽ ነበር የሰጠው፣

«ተግባራዊ የሚሆን ህግና አሰራር? አይመስለኝም»

«አንተ የዳዴኦ መሪ ብትሆን በተፅእኖ ትሰራለህ?» ሲል ጠየቀው።

«አልሰራም።»

«እንግዲያው ወደ ድርጅታችን ግባና እየው። እንዳንተ አይነት የተማረና በኦሮሞነቱ የሚኩራ ሰው በእጅጉ ይጠቅመናል። ግባና ታየዋለህ። ዳዴኦ አሻንጉሊት ድርጅት ከሆነ እኔን ናቀኝ። ያን ጊዜ ቀና ብዬ ፊትህን ለማየት አልደፍርም።»

«አላምንህም።»

«እኔን ላለማመን በቂ ምክንያት የለህም፣ አኖሌ?»

አኖሌ በተቃውሞ ራሱን ግራቀኝ ናጠ፣

«ዴሞክራሲያዊ የሚመስል ነፍጠኝነት በኦሮሞ ህዝብ ላይ እንዳይጫን ስጋት አለኝ» አለ።

«ነፍጠኝነት ላይ የተለያየ እምነት ያለን ይመስለኛል» አለ ኩምሳ «... ነፍጠኝነት ስርአት እንጂ ዘር ወይም ሀይማኖት አይደለም - ለኔ። ስልጣን በነፍጠኛው እጅ እንዳይገባ የምንከላከልበት መንገድ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በማስፈን ብቻ ነው። ዴሞክራሲያዊ ስርአት እስካለ ድረስ የህዝብ መብት ይታፈናል ብዬ አላስብም»

«ዴሞክራሲ» ብሎ ፈገግ አለ አኖሌ «... እኔ ዴሞክራሲን የችግር መፍቻ ቁልፍ አድርጌ አላየውም። ዴሞክራሲ ባህርይ - ባህል - ልማድ ነው» ካለ በሁዋላ ከአስተናጋጁ ላይ ብርጭቆ የሞላ ጉርደን ጂን ተቀብሎ ቶኒክ ሳይቀላቅል ባንድ ትንፋሽ ግማሽ አደረሰው።

ኩምሳ ግራ በመጋባት ያስተውለው ጀመር፤ አኖሌ ቀጠለ፣

«... ዴሞክራሲያዊ መብት ሙሉ በሙሉ በህግ ተከብሮም መብትን መገፈፍና መዋረድ አለ። የሚንቅህን ክንድህን ጭምር ማቅመስ አለብህ። ያኔ ዝም ይላል። ህግ ብቻውን የተሙዋሙዋተውን የኦሮሞ ብሄረተኝነት ስሜት ወደቀድሞ ስፍራው አይመልሰውም። የኦሮሞ ህዝብ መቶ አመት የተገፈፈውን ኩራትና ክብሩን መልሶ የሚያገኘው በህግ ነው? በገዛ መሬትህ ላይ ሆኖ የሚያዋርድህን ትምክህተኛ ፍርድ ቤት ወስደህ ልትገትረው ነው? እና 'ህግ ሰፈነ' ሊባል ነው? እኔ ይሄን አልቀበልም። ለአብነት 'ጋላ' አትበሉኝ ብያለሁ። 'ጋላ' ብሎ የሚሰድበኝን ምንድነው የማደርገው? እንድከሰው ነው የምትመክረኝ? ምክርህ ይህ ከሆነ የኦሮሞ ብሄርተኝነት ስሜት ጭርሱኑ ይዘቅጣል። መፍትሄው መክሰስ ሳይሆን በጥሩ ቡጢ አፍንጫውን መስበር ነው። ለዚህ ነው ኦሮሞነት ይሰማችሁ ዘንድ ከኢህአዴግ አባል ድርጅትነት ውጡ ብዬ የምመክራችሁ..»

ኩምሳ በመደነቅ አፍጥጦ ሲያየው ቆይቶ፣

«... ይህ አመለካከትህ ብጥብጥ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የህግ ስርአቶች መጣስን ነው የሚፈጥረው» ሲል በአፅንኦት ተቃወመው «.. በዚህ ደግሞ የመጀመሪያው ተጐጂ ራሱ የኦሮሞ ህዝብ ነው የሚሆነው። ምክንያቱም ማንኛውም ግጭት በራሱ





መሬት ላይ ነው የሚካሄደው። መቶ አመት የተገነባን ስርአት በአንድ አዳር ማፍረስ ደግሞ ከቶ አይቻልም»

አኖሌ የጂን ብርጭቆውን አጋብቶ ሌላ ጠየቀ፤

«... በዚህ ወቅት የትግራይና የኤርትራ ህዝቦች ለምን በኩራት መራመድ እንደጀመሩ ታውቃለህ? የትምክህተኛውን የደነደነ ትከሻ ስላደቀቁት ነው» ከዚያም ወደ ኩምሳ ጆሮ ጠጋ ብሎ «እኛስ?» ሲል ጠየቀው «... በባዶ ሜዳ መንታ መላስ ያለው ጦር ሰብቀን ጃሎታ እናሰማ አላልኩህም። ቢያንስ ግን ከማንም ያልተጠጋጋ ከበላዩ የኦሮሞ ሰማይ ብቻ ያለው የኦሮሞ ድርጅት ያስፈልገናል። የሚቆጣ አለቃ ይዘህ፣ እጅህን ይዞ ፖለቲካ ያስተማረህን፣ ከተጣልክበት አንስቶ በህልምህ እንኳዋ የማታስበውን ስልጣን ያጐናፀፈህን የሌላ ብሄር ጌታ ይዘህ እንዴት ነው ስለዴሞክራሲ የምታወራልኝ?»

ኩምሳ በአኖሌ ንግግር እምብዛም አልተመሰጠም፤ ረጋ ብሎ ውይይታቸውን የሚገታ ሀሳብ ይሰነዝር ጀመር፣

«... የተፈጠረው ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ማንንም ያታግላል። ዳዶኦአ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ነው። አነግ ሌላ ነው። አንተ ደግሞ ሌላ ድርጅት ልታቋቁም ትችላለህ። የኦሮሞ ህዝብም የተሻለ የምርጫ እድል ይኖረዋል። የእኔ ታላቅ ምኞት የኦሮሞ ህዝብ የሚሻለውን የፖለቲካ ድርጅት መምረጥ የሚችልበት እድል እንዲፈጠር ብቻ ነው። በዚህ በጣም አምናለሁ...» ብሎ ትክዝ ካለ በሁዋላ፣ «... እኔ እንደ አህዴድ አመራርነቴም ሆነ እንደ ግለሰብ ታጋይነቴ የማስበው ህዝቡ መልካም የኑሮ እድል ይገጥመው ዘንድ እንጂ ምቾት ስላለው ወንበር አይደለም። እመነኝ አኖሌ - የዳዶኦአ አባላት ሁሉ እንዲህ ነው የምናስበው። ከዚህ ውጭ ስለ ወንበር ማሰብ የጀመርን ቀን ግን እንደግለሰብ አሊያም እንደድርጅት እየከሰምን እንሄዳለን። በድን እንሆናለን። ቅን አላማ ይዞ መታገል እንደሚገባ አምናለሁ። ከህዝቡ በላይ ብልህ የለም። ሆኖም ቢያንስ አሁን በያዝከው ብጥብጥንና ጦርነትን በሚጋብዝ መንገድ ተከታይ እንደማይኖርህ አረጋግጥልሀለሁ።

ውድ አኖሌ ... ልብህ በበቀል መሞላቱን ተግንዝቤያለሁ። እኔም የነፍጠኛው ስርአት ያንተን ያህል ያቅረኛል። ካንተም በላይ ይክረፋኛል። ሆኖም ሀላፊነት ሊሰማን ይገባል። አንድ ሰው አማራ ስለሆነ ብቻ ነፍጠኛ ነው ወደሚል መደምደሚያ እንዳንደርስ በእጅጉ ልንጠነቀቅ ይገባል። ውጤቱ እጅግ እጅግ አደገኛ ነው የሚሆነው። የህወሀትን አገዛዝ ቢሆን በቅንነት ተመልከተው። እነዚህ ሰዎች ደርግን ለማንበርከክ ባደረጉት ሰፊ የትግል አስተዋፅኦ አያሌ ወንድምና እህቶቻቸውን አጥተዋል። ስለዚህ ደርግን አንበረከክን ብለው ሲደንሱ

ከሚያነጉበት ሁኔታ ውስጥ አይደለም:: መስዋእትነት የከፈሉ ጉዋደኞቻቸውና በድህነት የሚማቅቅ ህዝባቸው እንቅልፍ ይነሱዋቸዋል:: በየደቂቃው ያስቡዋቸዋል:: ስለዚህ ቀጣዩ ህልም ሌሎች ህዝቦችን ማፈን ሊሆን አይችልም:: የእኒያ ታጋዮች መስዋእትነት ተገቢ የሚሆነው የተዋረደውንና በድህነት የሚማቅቀውን ህዝባቸውን ከድህነት ካወጡት ብቻ ነው:: አሲያ ያ ሁሉ መስዋእትነት ከንቱ ይሆናል:: ትግሉ የመዝናኛ ፊልም አይደለም:: ለክብር፣ ለጉራ፣ ለዝናና ለታሪክ ሽሚያ የተካሄደ አይደለም:: እውነታው ይህ ከሆነ የህወሀት ታጋዮችን የምንሸሽበትና የምንጠራጠርበት ምክንያት ምንድነው - አናሌ? የህወሀት ታጋዮች በአማራው ገዥ መደብ ምትክ የትግራይን የበላይነት የመጫን ዝንባሌ እስካላሳዩ ድረስ፤ በሁለቱ ህዝቦች መካከል ጥላቻ የሚዘራበት ምክንያት ከቶ አይገባኝም::

የትግራይ ታጋዮች ታግለው አታግለውናል:: ይሄ ምን ይከዳል? ከዚያም አልፎ በርካታ የአማራው ብሄር አባላት ባሉበት ድርጅት ውስጥ እያሉ ኦሮሞዎች በግለሰብ ደረጃ እየታገልን ነበር:: በተደረገው የጋራ ትግል አኩሪ ተግባር ነው የተፈፀመው:: ተደጋግፈን ነው እየተጉዋዝን ያለነው:: በጋራ መታገላችንም የኦሮሞን የብሄርተኝነት ስሜት እንዴት እንደሚያቀጭጨው ከቶ አይገባኝም:: ብሄርተኝነት ስንልም ስለዴሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ነው ማሰብ የሚገባን:: ሌሎችን የሚጎዳ ብሄርተኝነት ዘረኝነት ነው ሊባል የሚችለው:: ምናልባት ዳዴኡኦ ከኢህአዴግ አባልነት እንዲወጣ የምታቀርበው ጥያቄ ከበታችነት ስሜት፤ አሊያ ከባዶ ጥርጣሬ የመጣ ይመስለኛል::»

አናሌ ስሜታዊ ሆኖ ምላሽ ይሰጥ ጀመር፣

«ሀቁን መስማት ከፈለግህ ስለዴሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት የተናገርከው ያጠናኸውንና የተማርከውን እንጂ በእምነት ደረጃ የተዋሀደህ ሀሳብ አለመሆኑ ይታወቃል:: ሳይንስ ህይወት ያለውና ህይወት የሌለው ተብሎ ለሁለት ሊከፈል ይችላል:: ብሄርተኝነትን በዚህ ቀመር አንዛር አትየው:: ብሄርተኝነት ዴሞክራሲያዊና ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ተብሎ አይከፈልም:: ብሄርተኝነት እሳተ ገሞራ ነው:: ይፈነዳል:: እንዳሻው ይፈነዳል:: ከፈነዳ በሁዋላ ያን እምቅ ሀይል፤ ያን የሚንቀሳቀል እሳት ለበጎ ተግባር አሊያም ለጥፋት ማዋል ይቻላል:: ለሁለት የሚከፈለው ከፈነዳ በሁዋላ እንጂ በድን ሳለ አይደለም:: የኦሮሞ ብሄርተኝነት እንዳይፈነዳ አፍነህ ስለዴሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት መስበክ በኔ እምነት ጨቅላነት ነው:: ሌላ ስም ከቶ የለውም:: የትግራይ ሰዎች ትግል ሲጀምሩ የትግራይ ብሄርተኝነት፣ ትግራዋይነት ያስነደብ





እንዲፈነዳ ነው ያደረጉት:: በከፋ ጫና ወደ ጥላቻ እስኪለወጥ ድረስ ህዝባቸውን ቀስቅሰውታል:: የማይበገር ሀይል መሆኑን ካረጋገጡ በሁዋላ ግን ያን ስሜትና ሀይል ወደ ረጅሙ ግባቸው ይመሩት ጀመር:: አንተ እንዳታምፅባቸውም ብሄርተኝነትን ለሁለት ከፍለው አስተማሩህ:: ስለምትተማመኑም ቀሎ ገባህ:: እና ጆሮውን ደፍኖ በዝምታ ለተቀመጠው የኦሮሞ ህዝብ እነሱ የነገሩህን ደሰኮርክ:: በርግጥ የሰማህ የለም:: የሚሰማህም አይኖርም» ካለ በሁዋላ ጂኑን ጨልጦ «... ክብረነክ ቃላት ተጠቅሜ ከሆን ይቅርታ» ብሎ የፌዝ ፈገግታ አሳየው::

«... ደግነቱ» ሲል ነበር ኩምላ ንግግሩን የጀመረው «...ትግሉ ከስሜታዊነት እንርቅ ዘንድ በመልካም ሁኔታ ገርቶናል:: ባንተ ስድብ አዘል ንግግር ያልተቆጣሁትም ለዚህ ነው:: ቢያንስ ግን ጥቂት ነገሮችን ብቻ ልንገርህ ይገባኛል:: ስማኝ አናሌ ... የኦሮሞ ህዝብ ጦርነት ሰልችቶታል:: ምክንያቱም በጦርነት ሰዎች ይሞታሉ:: በአንድ ጆምበር ሀያሺህ የሰው ልጅ ሬሳ በተራራ ላይ እንደ እንሰሳ ተነጥፎ ሊታይ ይችላል:: ጦርነት ማለት ይሄ ነው:: የኦሮሞ ህዝብ አንተ እንደምታስበው ፍልስፍና አልጠማውም:: ንፁህ ውሀ - መንገድ - ክሊኒክ ነው የሚፈልገው:: የኦሮሞ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ መብቶቹ፣ ባህሉ እንዲከበርለት ይሻል እንጂ የሌሎች ህዝቦችን መብት የማፈን ምኞት ኖሮት አያውቅም:: አንተ በቀል ነው ያረገዝከው:: የኦሮሞ ህዝብ ግን ብቀላ ባህሉ አይደለም:: በተቀረ የተናገርካቸው አብዛኞቹ ረጃጅም ዝባዝንኬ ተረቶች ናቸው:: የፖለቲካ ልምድ ማጣትም ይታይብሃል:: 'የአንድ ፖለቲከኛ ብስለት የሚለካው የሌሎችን መብት ለመጠበቅ ቅድሚያ ሲሰጥ ብቻ ነው' የሚል ፅኑ እምነት አለኝ:: ዞሮ ዞሮ ኤርትራውያን ባዘጋጁት በዚህ የደስታቸው ግብዣ ላይ የግድ መግባባት ላይኖርብን ይችላል:: ሁሉንም ወደፊት የምናየው ይሆናል:: ግልፅነትህን ግን ሳላደንቅ አላልፍም:: ምናልባት ወደ ኢትዮጵያ ከመጣህም በድጋሚ ተገናኝተን እንጨዋወት ይሆናል:: ደግመህ ደጋግመህ ብታስብበት፤ መልሰህ መላልሰህ ከሰዎች ጋር ብትወያይ ደግ ነው:: ወደፊት ላለመፀፀት ሞክር::

በአፅንኦት የምመክርህ ሌላ ቁም ነገርም አለ:: ይህም በጉልበት መጠቀም መፍትሄ አለመሆኑን ነው:: ከኦነግ ጋር ያለን ልዩነትም ይኸው ነው:: የኦሮሞ ህዝብ አካባቢውን ማስተዳደር ይጀምራል:: የመብቱና የኢኮኖሚው ተጠቃሚ ይሆናል:: ባህልና ቋንቋውን ማሳደግ ይጀምራል:: ይህ ከሆነ በኛ እምነት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በጋራ መኖር የማንችልበት ሁኔታ የለም:: የመገንጠል ጥያቄም የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ከሆነ በህዝብ ውሳኔ ይስተናገድ ባይ ነን:: የኦነግ መሪዎች ግን ትላንት ነፍጠኛው ያደርግ እንደነበረው በህዝብ

ደም መክበር ነው የሚሹት። በዚህ ከፍተኛ ልዩነት አለን። አንተም ሳታውቀው የኦነግ አመለካከት ተሸካሚ የሆንክ ይመስለኛል»

ኩምሳ ይህን ብሎ በአንገቱ የስንብት ሰላምታ አሳይቶት ተለየው።

አኖሌ የተተረማመሰ አሳብ ውስጥ ተዘፈቀ። ድንገት ወደ ጀርመን የመመለስ ሃሳብ መጣበት። ራሱን እንዳልተሳካለት የኦሮሞ ታጋይ መቁጠር ፈለገ። እና ስደት? ጀርመን?

እንደገና ወደ ጀርመን!?

ሊሙህ ቃጣው!

ከጋና! ከናይጀርያ! ከሴኔጋል! ከኢትዮጵያና ከጋምቢያ የመጡ ስደተኞች የታጨቁባት ጀርመን ፊቱ መጥታ ድቅን አለች። እኒያ የሀገራቸው ድህነት - ጉስቁልናና ሰብአዊ መብት ረገጣ መሮአቸው የመጡ ሰዎች የታጐሩባት ጀርመን!

አድካሚ ስራ የሚሰሩ - በድካም ሀሊናቸውን የሚስቱ - የመኖሪያ ቤት ኪራይ መክፈል አቅቶአቸው! አውቶብስ ላይ የሚያድሩ- በሰአት ስድስት የጀርመን ማርክ እየተከፈላቸው! ከእለት ጉርስ የማያልፍ ስራ እየሰሩ ከምንም ነገር በላይ ከባድ የሆነውን የጀርመኖች ትምክህት ተሸክመው የሚኖሩ አፍሪቃውያን - ትዝ አሉት።

ሊሙህ ቃጣው!

ለራሱም ቃል ገባ።

«አልሰደድም! እኔ ኦሮሞ ነኝ። ለኦሮሞ ህዝብ እታገላለሁ። ለኦሮሞ ህዝብ ምንም ፋይዳ የማያመጡትን የፖለቲካ ድርጅቶች ጭምር እታገላቸዋለሁ?» እያለ ለራሱ ቃል ገባ።

**- 2 -**

'ይስሀቅ ኤፍሬም' የሚል ፅሁፍ ደጁ ላይ ከሚነበበበት ያማረ ግቢ ውስጥ! በሚንቀለቀል የጣውላ እሳት ዙሪያ ሁለት ሰዎች ተቀምጠዋል። ነበልባሉ ከፀጥተኛው ምሽት ጋር የዝምታ ህብረትርኪት ፈጥሮ ምሽቱን አስውቦታል። ሁለቱ ሰዎች አኖሌና ሮዛ ናቸው። ሮዛ ዛሬ ደስተኛ አይደለችም። ምክንያቱም በዚህ ምሽት አኖሌ ዋቆ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመለስ የመጨረሻውን ቁርጥ አድርጐ ነግሮአታል። አኖሌ ኤርትራ እንዲቀር ስትወተውተው ብትሰነብትም ሳይሳካላት መቅረቱ ነው።





«ግብገሮው ታዲያ እንዴት ነበር?» ስትል ወሬ ሰወሰች።

«የጨረባ ሰርግ ነበር» አላት።

«አልተደሰትክም?»

«ከዳዬኦአ ሰዎች ጋር አልተግባባንም።»

«ማናቸው እነሱ?»

«በኢህአዴግ ውስጥ ያሉ ኦሮሞዎች። የኦነግ አመለካከት ተሸካሚ አድርገው ቆጠሩኝ። ኦነግን ስለሚጠሉት! ከእነሱ የተለየ አሳብ ያለውን ሁሉ በዚያ መነፅር ነው የሚመለከቱት። የኦነግን መሪዎች ከኔ በላይ የሚያውቃቸው የለም። ሰባት አመት ሙሉ አውቃቸዋለሁ። በአውሮፖ ምድር ሲዝናኑ ነው ጊዜያቸውን የፈጁት። እንደነርሱ ጨዋኂ አድርገው ቆጠሩኝ...»

ሲጋራውን የሚንቀለቀለው እሳት ላይ ለኮሰ።

«ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰህ እንዴት ለመኖር ነው ያሰብከው?»

«ገና አልወሰንኩም»

«አይተኸው ካልተስማማህ ትመለሳለህ?»

«አልመለስም። እዚያው እሞታለሁ! »

ጨፍጋጋ ስሜት አድሮበታል።

«ሞትን ምን አመጣው ታዲያ?» ብላ ጠጉሩን ታሻሽው ጀመር።

ረጋ ብላም እንዲህ አለችው፤

«እየውና ካልተስማማህ ወደኛ ተመለስ። እዚህ በጣም ይመችሀል። ይህ የኔ ፍላጐት ብቻ አይምሰልህ። የአብርሀ ፀሎት ጭምር ነው። ዶክተር አበራም እዚህ እንድትቀር ይፈልጋል። አዶናይም እዚህ ከቀረህ በቂ ስራና ምቹ የኑሮ ሁኔታ እንደሚዘጋጅልህ ነግሮኛል። በርግጥ 'አትጫኑት፤ ፍላጐቱን ይፈፅም' ብሎኛል። ልንጫንህ አንሻም። ከኛ ጋር ብትሆን ግን በጣም ደስተኛ ነኝ። ማማ እንዴት እንደምትወድህ አይተሀታል? እናት ደሞ የለህም አይደል? ማማ ያንተም እናት ትሆናለች። ሌላ የምስራች ደሞ ልንገርህ። ባባ በህይወት መኖሩን ትናንት ሰማን። በሀቡአ ሱዳን ውስጥ ሲንቀሳቀስ ነበር። በደስታ ልናብድ ደርሰን ነበር ብታይ። ከእስር ቀን በሁዋላ አስመራ ይመጣል። ትተዋወቀዋለህ። እርግጠኛ ነኝ ይወድሀል። ባባ ሰው ይወዳል»

ሮዛ እንዲህ እንዲህ እያለች በደስታ ታጫውተው ጀመር።

አኖሌ የሚንቀሳቀሰው እሳት ላይ አይኖቹን ተክሎ በሀሳብ ርቆ ነጉዶ ነበር።

«ሮዚና ... ስለወደዳችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ» ሲል ተነፈሰ «... በህይወቴ ሙሉ የናንተን የመሰለ ቤተሰብ ውስጥ ጠልቄ ገብቼ አላውቅም። የማይረሳ ቤተሰባዊ ፍቅር ስላስተማራችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ። ኤርትራ የምቆይበት ምክንያት ግን አይታየኝም። እናንተ ኮምቢሽታቶ ላይ ከበሮ ይዛችሁ እይታየኝም። ... ቀጥሉ። ይገባችሁዋልም። እኔም ወደ ቡርቃ መጨፈራችሁን ቀጥሉ። ይገባችሁዋልም። እኔም ወደ ቡርቃ አመራለሁ። ወገኖቼ በየደቂቃዋ ስሜን ያነሱ ይሆናል» ብሎ ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ተዋጠ።

እንደገና መናገር ሲጀምር ድምፁ ጉርንኖ ነበር፣

«እዎን መሄድ አለብኝ። የምሄደውም ነገ ነው። ነገ በማለዳ ወደ ሀገሬ እመለሳለሁ። እኔ ለኤርትራ ህዝብ አልታገልኩም። ልታገልም ሆነ ላገለግል አልፈልግም። ለኤርትራ ህዝብ የማገለግልበት ምንም በቂ ምክንያት የለኝም። የራሴ ህዝብና አገር ያለኝ ሰው ነኝ። ኤርትራውያንም ቢሆኑ ቼ ጉቤራን አይፈልጉትም። የራሳቸው ቼ አላቸው። ብዙ ሺህ ቼዎች አሉዋቸው...»

«ነገ ልትሄድማ አትችልም!» ስትል ጮኸች።

«ምነው?» አላት።

«በኔ ሰርግ ላይ መገኘት አለብህ።»

አኖሌ ፈገግ አለ።

«ልታገቢ ነው እንዴ?»

«እዎን።»

«ማንን?»

«አዶናይ»

«እውነት?»

«የምንስማማ አይመስልህም?»

«ጥሩ ምርጫ ነው። መቼ ወሰናችሁ ለመጋባት?»

«ከሰባት አመት በፊት» አለች።

«የዋቀዮ ያለህ» ብሎ ጮኸ።





«ረጅም ጊዜ ነው» ብላ ፈገግ አለች።

«ያኔ የተገናኘን ጊዜ ግን ፍቅረኛ እንደሌለሽ ነግረሽኝ ነበር»

«ያኔ ዋሽቼህለሁ።»

«ለምን ዋሽሽኝ ሮዚና?»

«በወቅቱ ልነግርህ አልችልም ነበር። ምክንያቱም ካንተ ጋር የምንገናኘው ድርጅታዊ ተልእኮ ይገፉ ነበር። ባህርይህን አላውቀውም። ምናልባት እንደወታደሮቹ ወሲብ የምትወድ ከሆነ ፍላጐትህን ለመፈፀም ጭምር ተዘጋጅቼ ነበር።»

አኖሌ ተገርሞ ጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ቆየ።

«ግን በወቅቱ አደገኛ ድርጊት መፈፀምሽ ይገባሽ ነበር?» ሲል ጠየቃት፣ ሁኔታውን ለማስታወስ እየሞከረም «... እናትሽም አንቺም አደጋ ውስጥ ነበራችሁ። እንዴት በዚህ መንገድ የስለላ ስራ ይሰራል? በወቅቱ መኖሪያ ቤትሽን ለኔ ማሳየት ጀግንነት ሳይሆን ቂልነት ነበር።»

ሮዝ ጭንቅላትዋን ግራቀኝ ስትወዘውዝ ቆይታ፣

«ከባድ እንደነበር ይገባኛል። ሆኖም ሰብአዊነት እንደሚያጠቃህ ሳሚ ነግሮን ስለነበር ነው ያንን የወሰንነው። ጥርጣሬ ልብህ ውስጥ እንዳይኖር ለማድረግ ነበር ያን የፈፀምኩት። ያን ማድረጌ አደገኛ ቢሆንም ውጤት ግን አጊኝተንበታል። ግን እኔ በግሌ ስሜታዊም ነበርኩ።

«ለምን?»

«ተልእኮውን ያለ እንከን የማሳካት ከፍተኛ ፍላጐት ነበረኝ»

አኖሌ በአሳብ ርቆ ሄዶ ነበር፣

«አንድ ነገር ልጠይቅሽ ሮዚና?»

«ምን?»

«በተሰነባበትንበት የመጨረሻ ቀን፣ ስመሽኝ ነበር። በአይንሽ ሙሉም ልክ እንዳሁኑ እንባ ሞልቶ ተመልክቼ ነበር። ይህ ሁሉ ድራማ ነበር?»

«አይደለም!» አለች ቅጭም ብላ «... የድርጅቱን አላማ ለማስፈፀም ብዙ የማስመሰል ስራ ሰርቻለሁ። ያንቀን ግን የልቤን ነበር ያን ያደረግሁት። ልቤ ለሁለት ተከፈለ። አብርሀን ከሞት ለማትረፍ የመጨረሻ ተስፋ አንተ ብቻ ነበርክ። እኝሬሽኑ ካልተሳካ

ደግሞ አንተም አብርሀም እንደምትገደሉ አውቅ ነበር:: ያንን አሰብኩ:: ድንገት ውስጤን ሀዘን በላው:: የአብርሀን ህይወት ለማዳን አንተን ገፋፍተን ወዳላሰብከው ቀለበት ውስጥ ካስገባንህ በሁዋላ ህይወትህን ብታጣ፤ እድሜ ልኬን ከፀፀት አልወጣም ነበር:: እና የስንብት ነበር የሳምኩህ::»

«ገፋፍታችሁኛል እንዴ ሮዚና?» ሲልጠየቃት፤ ገፋፍተን አስገብተንህ ያለችው ከንክኖት::

«አዶናይ አልነገረህም?»

«ምኑን?»

«ያለፈ ታሪክ ስለሆነ እንደማታዝንብን ተስፋ አደርጋለሁ» አለች እጁን እያሻሸችው::

«ንገረኝ ምንድነው?»

«ከመከላከያ ሚኒስቴር የተገኘ ብሎ ሳሚ የላከልህን ዶብዳቤ እዚሁ አስመራ ውስጥ እኛው ነን ያዘጋጀነው:: ሀሳቡን ያመጣው ግን ሳሚ ነበር...»

ከማያውቃት ሴት ጋር እያወራ መሆኑን ተጠራጠረ::

«እብዶች ናችሁ! » ሲል ተነፈሰ::

ሌላ ቃል አልጨመረም:: ቅሬታ ግን አላደረበትም:: ዞሮዞሮ ከደርግ ካምፕ በጥሩ ጊዜ መውጣት መቻሉን ወዶታል:: ከዚያም በላይ በቂ የትግል ልምድ ለማግኘት ረድቶታል::

«አኖሌ ... በቃ ወሰንክ?»

«ምኑን?»

«ወደ አዲሳባ መመለሱን?» አለች ትክዝ ብላ::

የማይለወጥ አሳብ መሆኑን ከገለፀላት በሁዋላ ድንገት አንድ የቆየ ነገር አስታወሰ::

«ፊንፊኔ የሚለውን ስም ተውሽው ማለት ነው?»

ሮዛ ፈገግ አለች::

«በመጀመሪያ የተገናኘን ቀን ፊንፊኔ የሚለውን ስም መጠቀሜ ትገዝ ብሎህ ነው?»

«እህ!»

«ይገርምሀል በወቅቱ የአዲስ አበባን ስም በፊንፊኔ ተክቼ





የተናገርኩት በአዶናይ ታዝዤ ነበር:: እኔ ቃሉንም ሰምቼው አላውቅም ነበር::»

«ለምን አላማ?» አለ ተገርሞ::

«ያንተን የብሄርተኝነት ስሜት ለመመዘን የተሰነዘረች የፍተሻ ተኩስ ነበረች:: ውጤቱ ታዲያ ጥሩ ነበር የሆነልን:: ታስታውስ እንደሆን ስሜታዊ ሆነህ ነበር:: የእለቱ እለት ለአዶናይ ሪፖርት ሳደርግለት ከጠበቅነው በላይ ኦሮሞ ነው ነበር ያለኝ::»

አኖሌ በመደነቅ ራሱን ግራ ቀኝ ናጠ::

«ምን አሰብክ ታዲያ?» አለች የሚያቃጥል መዳፉን እያሻሸችው::

«ሚዲስፒያቼ ሮዚና... ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ወደአዲስ አበባ እሄዳለሁ:: ዛሬውኑ ደውለሽ ለአብርሀ ለአዶናይና ለሳሚ ንገሪያቸው::»

በነጋታው ተሲያት ላይ አስመራን ለቆ ወደ አዲስ አበባ በረረ ...

አስር ያህል የሻእቢያ ታጋይ ወዳጆቹ ከአይሮፕላን ማረፊያው ድረስ መጥተው ሸኙት:: አብርሀ ፀሎት አምስት ሺህ ዶላር በፖስታ አሽጐ ሰጠው፤

«ምንድነው ይሄ?» አለ አኖሌ ግራ ተጋብቶ::

«ሶስት ሺ. ዶላር ህዝባዊ ግንባር የመደበልህ ነው:: ለድርጅቱ አስተዋፅኦ በማድረግህ:: የተወሰነልህ ክፍያ ግን አይደለም:: አዲስ አበባ እንደደረስክ ቢያንስ እንዳይቸግርህ በማሰብ የተደረገ ነው:: ሁለት ሺውን ጣሊያን የሚኖር ታናሽ ወንድሜ የላከልኝ ገንዘብ ነው:: እንደ ኪስ ገንዘብ ተመልከታት::»

«አመሰግናለሁ!» አለ - ፊቱ እየቀላ:: ባሳዩት ፍቅር ልቡ ተነካ:: ከአብርሀ ፀሎት ጋር ተቃቅፈው ሲሰነባበቱ፤

«በደስታም ሆነ በሀዘን ጊዜያት የጠበቀ መተሳሰብ እንዲኖረን እመኛለሁ» አለው::

ዶክተር አበራም በሞቀ ሁኔታ እየሳሙ ሲሰናበቱት፤

«ለኤርትራ ትግል አንድ ድንጋይ ወርውረሀል:: የወረወርከት ድንጋይ ኢላማዋን መትታለች:: ኤርትራ የፈፀምክላትን ውለታ ለዘልአለሙ አትረሳውም:: ውለታህን ለመክፈል ጭምር ምንጊዜም ቢሆን ዝግጁ ናት» አሉት::

አኖሌ በቀዘቀዘ ስሜት፤

«ለኤርትራ ብዬ ሳይሆን ለራሴው ስል የፈፀምኩት ስለሆነ ያን ያህል አያኩራራኝም» ሲል መለሰላቸው:: ዶክተሩ ፈገግ አሉ:: ትህትናውን አደነቁ::

ከሳሙኤል ጋር ሲሰነባበቱ፤ በሳሙኤል አይኖች እንባ ሞልቶ አኖሌ ተመለከተ::

«ተንኮለኛው ወዳጄ፤ ይሄ ሁሉ መረበሽ ምንድነው?» አለው::

«በልብህ ቂም ይዘህብኝ ይሆን?»

«እመነኝ ሳሚ:: አላማ ያለህ ሰው በመሆንህ ምንጊዜም አከብርሃለሁ:: 'ሳይደግስ አይጣላም' ይባሉ አማሮች:: ዞሮ ዞሮ ውጤቱን ብቻ እንመልከተው::»

ከሳሙኤል በሁዋላ ሮዛን ተሰናበታት፣ ደረቱ ላይ ልጥፍ አለች:: ጉንጮችዋ ባንዴ ታጠቡ::

«ከላ! እድለኛ አይደለሁም:: ከምወደው ሰው መለየት አልችልም::» አለችው::

«ምንጊዜም አልረሳሽም» አላት በጆሮዋ::

ቀጥሎ የተሰናበተውን ሰው ግን አላወቀውም:: ፊቱ ትዝ ይለዋል:: የት እንዳየው ግን ሊመጣለት አልቻለም:: እቅፎ በስንብት እየሳመው፣

«የት ነበር የምንተዋወቀው ጓል?» ሲል ጠየቀው::

«አብርሀ ፀሎትን አስፈትተህ እኔን ማሳሰርህን ጨርሶ ረስተኸዋል ወይስ ሞተአል ብለህ ደምድመህ ነበር?»

«የዋቀዮ ያለህ!» ብሎ ጮኸ:: «አንተው ኖረሀል? ለመሆኑ እንዴት አመለጥክ ከዚያ ግቢ? እንደማየው የጭልፊት ክንፍ የለህም::»

ጉልማሳው ሰው ፈገግ አለ፣

«የእስር ቤቱ ወጥ ቀቃይ ነበርኩ! እናንተ ከወጣችሁ በሁዋላ እያፋዋጨሁ ወደ ስራዬ ገባሁ:: በዚያን ምሽት ደስተኛ ስለነበርኩ፤ በነጋታው ለእስረኞቹ የቀቀልኩት ወጥ እጅ የሚያስቆረጥም ነበር:: ይታይህ ወዳጄ ... ሻእቢያ የሚባል የተረገመ ድርጅት ለእስረኞች መልእክት እንዳደርስ በመፈለጉ ሰባት አመት ሙሉ የእስር ቤት ወጥ ቀቃይ ሆኜ እንድቆይ አዞኝ እዚያው ከረምኩ::»

የአኖሌ ሾኚዎች በሳቅ አውካኩ::





በመጨረሻ ፈንጠር ብሎ ቆሞ የነበረውን ሰው ተሰናበተው:: አዶናይ! ከአዶናይ ጋር ተቃቀፉ:: በሞቀ ሁኔታ ጀርባ ለጀርባ እየተጠባጠቡ ቆዩ:: መሰነባበቱ ከበዳቸው:: ስሜቱን እንዳልቻሉ ታወቀባቸው:: በእምባሶይራ ሆቴል ያደረጉዋትን አስጨናቂ ቆይታ አስታውሰው ይሆን? የአዶናይን እንጃ! አኖሌ ግን በአሳብ የሁዋሊት ተጉዞ ነበር:: ሄዶ ሄዶ በዚያች አስጨናቂ ደቂቃ ላይ አረፈ:: ያቺን ወሳኝ ደቂቃ ሲያስብም ስትከነክነው የከረመችውን አንድ ጥያቄ ለአዶናይ ለማቅረብ ተገፋፋ::

«አንድ ነገር ልጠይቅህ፤ አዶናይ?»

አዶናይ ምላሽ ሳይሰጥ አይን አይኑን ያየው ጀመር::

«እምባሶይራ ሆቴል በኔ ክፍል ለመጨረሻ ጊዜ ስንነጋገር ባቀረብከው አሳብ ባልስማማ ኖሮ በርግጥ ሀገር ጥለህ ትጠፋ ነበር?»

አዶናይ ምላሽ በመስጠት ፈንታ፤ ፈገግ ብሎ አይኖቹን ወደ ሰምበል አቅጣጫ አሻገረ፣

«ነገረኝ? ዘወትር ስለምትከነክነኝ ነው ማወቅ የፈለግሁት:: ደሞም ያለፈ ታሪክ ነው» አለው::

«ሀገር ጥሎ የመጥፋት ጉዳይ እንኩዋ የሚታሰብ አልነበረም» ሲል መለሰ አዶናይ:: ያልፈለገው ርእስ እንደተነሳ ገፅታው ላይ ታወቀበት::

«ታዲያ ምን ታደርግ ነበር?»

«ምን ማድረግ ይገባኝ እንደነበር መቸም አንተም የምትገነዘበው ይመስለኛል::»

አኖሌ የአዶናይን ጭንቀት ሲያይ በምላሹ ላይ አገዘው፣

«በርግጥ ትፈፅመው ነበር?»

«አማራጭ አይኖርም ነበር፤ አኖሌ::»

አኖሌ አልደነገጠም:: የጠበቀው ነበር::

«አውቃለሁ አዶናይ» አለ በደበዘዘ ፈገግታ ተውጦ «... አውቃለሁ የተናገራችሁትን ትፈፅማላችሁ ...»

የኢትዮጵያ አየር መንገድ አይሮኘላን ከአንድ ሰአት ሰላማዊ በረራ በሁዋላ አዲስ አበባ ተቃርቦ ማዘቅዘቅ ጀመረ:: አኖሌ በአይሮኘላኑ መስኮት አረንጉዋዴ ስጋጃ የለበሰውን የኦሮሚያ መሬት ሲመለከት ከጥቂት አመታት በፊት ከአባቦሩ ጋር የተለዋወጣቸውን ጥቂት ቃላት አስታወሰ፣

- አኖሌ ልጄ?-

- አቤት አባቴ-

- ያንን ሰማይ ታየዋለህ! ?»

- የቱ!?-

- እስከ አድማስ የተዘረጋውን፡-

- አዎን አባቴ፡-

- እንኩዋን መሬቱ ሰማዩም የኦሮሞዎች ነው፡-!

# ክፍል - ሶስት

# የቡርቃ ቁጣ!

# ዝምተኛው ቡርቃ

## ምእራፍ አስራ አንድ

- 1 -

ዘመኑ የመሸጋገሪያ ዘመን ነው። የአዲሳባ ፖለቲካ ጤናማ አይመስልም። ቁልፍ የስልጣን ቦታዎችን የያዘው ኢህአዴግ ግን ጉዳዮችን እንደ አመጣጣቸው ለማስተናገድ ሲጥር ይስተዋላል። የፖለቲካ ትኩሳቱ በርትቶአል። ዘረፋው አይሎአል። በኮሚቴ የሚሰሩ ተግባራት ማለቂያ የላቸውም። አመራር ላይ ያለ አንድ የኢህአዴግ ሰው በአንድ ጊዜ የሶስት ኮሚቴ አባል ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው የሁለት መስሪያ ቤቶች ሚኒስትር ሆኖ ይሾማል።

የታማኝ ሰው እጥረት አለ።

ችሎታና ታማኝነት ደግሞ አዘውትረው አይገጣጠሙም:: ዘመኑ አንድ ሰው ሁለት ጉዳዮችን በአንድ ጆሮው የሚያዳምጥበት ዘመን ነው:: ምሳ እየተመገበ ስብሰባ የሚመራ፤ ቢሮ ውስጥ አልጋ የሚዘረጋ የኢህአዴግ ባለስልጣን ጥቂት አይደለም:: ሀላፊዎች የመታወቂያ ወረቀት ሲያሰሩ 'የስራ መደብ' በሚለው ቦታ 'ስብሰባ' ብለው ማስፈር ይቃጣቸዋል:: በመዲናዋ አዲስ አበባ ሌሊት ተኩስ ማድመጥ ተለምዶአል:: ኡኡታም አለ:: የተደራጁ ሌቦች ከተሞችን ሲያምሱ ያድራሉ:: የኦሮሞና የአማራ ተቃዋሚ ድርጅቶች ያጉረመርማሉ:: ፈንጂ የትም ይፈነዳል:: በየወሩ ከስብ በላይ መፅሄቶች እየወጡ ሀገሪትዋን በወሬ ሰደድ ያቀጣጥሉዋታል:: በመሆኑም ጊዜው የእፎይታ ይሁን የሽብር ለይቶ ለመናገር አስቸጋሪ ነበር::

* * *

በፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ ልዩ ትኩረት የተሰጠው አንድ ጉዳይ አለ:: ይህም የክልሎች የፀጥታ ጉዳይ ነው:: ይህንን ችግር ለመፍታት በበላይ ሆኖ የሚመራና የሚቆጣጠር አንድ ኮሚቴ ተዋቅሮአል:: ይህ ኮሚቴ ደግሞ የተለያዩ ሌሎች ግብረ ሃይሎችን እያቋቋመ ዘመቻውን በስፋት ተያይዞታል:: ሆኖም ችግሩ እንደታሰበው በቀላሉ የሚፈታ አልሆነም:: ከሁለት መቶ ሺህ በላይ የፈረሰው የደርግ ጦር ወታደሮች ከነመሳሪያቸው ተበትነዋል:: ደሞዝ የላቸውም:: የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ማንኛውንም ተግባር ለመፈፀም ዝግጁ ነበሩ:: በመሆኑም ኮሚቴው በስራ ተወጥሮአል:: በቀን ሃያ አራት ሰአት ይማስናል:: በየእለቱም የኮሚቴው እንቅስቃሴ ለፕሬዚዳንቱ ይቀርባል:: ስራው ሱሪ ባንገት ሆኖአል ...

በተከታታይ የተለያዩ ግብረ ሃይሎችን እያቋቋመ ሲያስማራ የሰነበተው ክንፈ ገብረመድህን በእርግጥም ለዚህ አይነት ፈታኝ ተግባር ብቁ ይመስላል:: የትግራይ ሰው ነው:: የህወሀት ፖሊት ቢሮ አባል:: በአመራሩ ጥሩ ተሰሚነት አለው:: ተሰሚነቱ ከብቃት የመነጨ መሆኑን ማንም ያምንለታል:: ፈጣንና ቁጡ ነው:: ቁጡነቱ አንዳንዴ እንደ በምብ ሲፈነዳ ያስደነግጣል:: ዲፕሎማሲያዊ አቀራረብን ጨርሶ የማያውቅ ያስመስለዋል:: ቁጣው እንደ መብረቅ እየተንተገተገም ቢሆን ግን ተወደጅነትን ያተረፈ ሰው ነው:: ሰው አክባሪነቱና ቀለል ያለ አቀራረቡ ድንቅ ነው:: ቀጭንና ረጅም ነው፤ መልከ ቀና:: 'ግልፅ ሰው ነው' ይሉታል አብረውት የሚሰሩ ሁሉ:: ያልተለመደ ግልፅነቱ አይጐረብጥም:: ፍቅር ያሳድራል:: ታዲያ





ሲያወጋ ምንም ሳያስቀር የልቡን የተናገረ ይምሰል እንጂ ሆዱ ጫካ ነው:: ወደሚዲያ ጨርሶ አይቀርብም:: በፀጥታ ጉዳዮች ላይ ቃለምልልስ ቢሰጥ እንኳ የበታቾቹን ፎቶግራፍ ነው የሚያስለጥፈው:: ሾፌርና አጃቢ የለውም:: የሲቪል ፕሮቶኮል ልብስ ለብሶ ያየውም ቢሆን ከቶ አይገኝም:: የሚያየው ታዲያ ማመን የማይችሉ ውጊያዎችን መርቶ የመጣ፣ የደህንነት ሚኒስትር ነው ብሎ ከቶ አያስብም::

... ክንፈ ሰሞኑን ተዋክቦአል::

የተጣለበትን ከባድ ሃላፊነት ለመወጣት ብቃት ያላቸውን ታጋዮች እየመረጠ ነው:: ዛሬም እነሆ አንድ አስቸኳይ ስብሰባ ያደርጋል:: ሰአቱን አየ:: ከቀኑ ስምንት ሰአት:: ተሰብሳቢዎቹ ከስብሰባው አዳራሽ ገብተው መሆን አለበት:: ስልኩን አንስቶ ፀሃፊውን ያነጋግራት ጀመር...

«መጥተዋል» አለችው::

ተነስቶ ወደ ስብሰባ አዳራሹ አመራ::

ተሰብሳቢዎቹ ወደ አስር ይጠጋሉ:: አንዱ ኮማንደር ሃየሎም አርአያ ነበር:: የፖሊስ አዛገዩም አለ:: ሁለት የአህዴድ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትም የስብሰባው ተካፋይ ናቸው:: የመከላከያ ሰራዊት ባልደረቦችም ይታያሉ:: ሀወኒ ዋቆና አብርሃ ፀሎት ጭምር በተሰብሳቢነት ተገኝተዋል:: በሙሉ የኢህአዴግ ታጋዮች ናቸው - ከአብርሃ ፀሎት በቀር::

የሰላምታና የቀልዳ ቀልድ ልውውጡን ባጭሩ ቀጭቶው በቀጥታ ወደ እለቱ አጀንዳ ዘለቀ:: ክንፈ ማስታወሻ ደብተሩን ሲገላልጥ ቆይቶ፤ እንዲህ ሲል ስብሳባውን ከፈተ፣

«... በምስራቅ ሸዋ፣ በአዋሳና በባሌ አካባቢዎች የሚፈፀሙ የሽብር ተግባራትን ለመግታት አንድ ጠንካራ እንቅስቃሴ ማድረግ አስፈልጐአል:: የአካባቢውን ፀጥታ ማስጠበቅ የደቡብ ሰራዊት ድርሻ ቢሆንም ዛሬ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሰጥተን ልናይ የፈለግንበት አንድ ምክንያት አለ» ካለ በሁዋላ፤ ንግግሩን ገታ አድርጐ «በቅድሚያ ግን ልገልፅ የሚገባኝ አንድ ነገር አለ:: ሀወኒና አብርሃ ፀሎት የኮሚቴው አባላት አይደላችሁም:: በዚህ ስብሰባ እንድትገኙ የፈለግነው ለኮሚቴው የሚጠቅሙ አንዳንድ መረጃዎችን ትሰጡናላችሁ በሚል ነው» ብሎ ወደ ጀመረው ማብራሪያ ገባ::

«ምሽጉን ናዝሬት፣ አሰላ፣ ወይም አዲስ አበባ ላይ ያደረገ አንድ የዝርፊያ ቡድን ተቋቁሞአል:: የዚህ ቡድን የመጠሪያ ስም 'የቡርቃ

ዝምታ ይባላል» ሲል ሀወኒ ደንገጥ አለች።

አይኖችዋ ከንፈ ላይ አተኮሩ። ጆሮዋ የተሳሳተ መስሎአት ጭምር ነበር። የቡርቃ ስም መነሳት ነበር ያስደነገጣት። ስለ ትንቢተ - የቡርቃ ዝምታ አያሌ ታሪኮችን ታውቃለች። ማነው ታዲያ በዚያ ትንቢት ስም የተደራጀው?

ከንፈ ሀወኒን እንደዋዛ አጢኖአት ገለፃውን ቀጠለ፤

«ቡድኑ ግን እንደስሙ ዝምተኛ ሳይሆን ጥቂት የፖለቲካ ስሜት የተቀላቀለበት ዘረፋ ላይ ያተኮረ ነው። የደህንነት ፅህፈት ቤቱ ከፖሊስ ሃይል ጋር በመተባበር ባደረገው ከፍተኛ ክትትል የዚህ ቅሚያ ቡድን አለቃ» ብሎ የማስታወሻ ደብተሩ ላይ ስም ይፈልግ ጀመር «... አኖሌ ዋቆ ይባላል!»

ሀወኒ ተስፈንጥራ ከመቀመጫዋ ተነሳች።

ተሰብሳቢዎቹ ደነገጡ። **ወይም የደነገጡ መሰሉ**። ሁሉም ትንፋሽዋ እየተቆራረጠ **ለመናገር ያቀበቀበችው** ሴት ላይ አፈጠጡ ...

ሀወኒ «እርግጠኛ ነህ ... **አኖሌ ዋቆ** ነው!?» ነበር ያለችው በሚንቀጠቀጥ ድምፅ።

ከንፈ «የተሳሳትኩ **አይመስለኝም** ...» ብሎ ትክ ብሎ አስተዋላት።

ሀወኒ «አኖሌ ዋቆ ሞቶአል!» **ስትል በስሜት ተናገረች**።

«ማነው አኖሌ ዋቆ?» ሲል በርጋታ ጠየቃት ከንፈ። አያይዞም

«የትና እንዴት ሞተ?» ሲል አከለ።

ሀወኒ መቀመጫዋ ላይ በእርጋታ አረፈች፤

«አኖሌ ማለት ወንድሜ ነው። ለኔ ከዚያም በላይ ነው። የአንድ እናትና አባት ልጆች አይደለንም። ሁለታችንም ግን ወላጅ አልባ ስለነበርን በድፍን አርሲ በአባዱላ ማእረግ የሚታወቁት ዋቆ ናቸው ያሳደጉን። ዋቆ አባታችን ነበር የሚመስሉን። አኖሌም ወንድሜ ነበር የሚመስለኝ። ሁዋላ እንድንተጫጭ ተደረገ። በመካከሉ ግን አኖሌ ወደ ጀርመን ስለሄደ ግንኙነታችን ተቋረጠ። ሃየሎም ረስተኸው ካልሆነ ስለ ጀርመን ሀገር እጮኛ እንዳለኝ ነግሬሀለሁ። አኖሌ ዋቆ ማለት እሱ ነው። ኢህአዴግ አዲሳባ ሲገባ ቡርቃ ሄጄ ነበር። አኖሌ ከጀርመን ተመልሶ እንደነበርና ከአባታችን ሞት ጋር ተያይዞ





**በተነሳ አመፅ ምክንያት ደርግ እንደገደለው የቡርቃ ገበሬዎች ነግረውኛል። በገበሬዎቹ መረጃ ብቻም አላበቃሁም። ዜኒት ከምትባል የትምህርት ቤት ጉዋደኛዬ ተመሳሳይ መረጃ አግኝቼያለሁ። አኖሌ በደርግ ተይዞ መሰወሩን ታውቃለች። ዳፋው ጂብሪል ለተባለ ጉዋደኛው ጭምር እንደተረፈ አጫውታኛለች። አሙዋሙዋቱን በግልፅ ባላውቅም መሞቱን ግን እምኜ እርሜን አውጥቼያለሁ። ሀየሎም ስለዚህ ጉዳይ ጫፍ ጫፉን አልነገርኩህም? ረስተኸው ካልሆነ ነግሬሀለሁ? 'አኖሌ' ምን ማለት ነው ብለህም ጠይቅኸኝ ነበር ...»**

ሀየሎም «ዛሬ ስብሰባው ላይ እንድትገኚ የፈለግነው በዚሁ ምክንያት ነው። ምናልባት የስም መመሳሰል እንዳይኖር ጥርጣሬ ነበረኝ» አለ።

አብርሃ ፀሎት መናገር ይፈቀድለት ዘንድ ከጠየቀ በሁዋላ፤

**«እኔም የስም መመሳሰል እንዳይኖር እሰጋለሁ» ሲል ጀመረ «እስመራ በድርጅታችን አማካይነት ወደ ሜዳ ወጥቶ ደርግ እስኪወድቅ ድረስ ሲታገል የቆየ አኖሌ ዋቆ የሚባል ሰው አውቃለሁ። ይሄ ሰው ከስድስት ወራት በፊት ወደ አዲስ አበባ ተመልሶአል።» የሚል መረጃ ሰጠ።**

የሀየሎም አይኖች ሀወኒ ላይ፤ መልሶ ደግሞ አብርሃ ፀሎት ላይ ሲሽከረከሩ ቆዩ። ከንፈና ሀየሎም እየቆዩ ይተያያሉ። መልሰው ደግሞ አይኖቻቸውን ወደ ሀወኒና አብርሃ ፀሎት ይመልሳሉ።

ሀየሎም «የአኖሌ ፎቶግራፍ ይኖራል?» ሲል ጠየቀ።

**ከንፈ በአወንታ ራሱን ነቅንቆ ከአጀንዳው መካከል አንዲት ጉርድ ፎቶግራፍ አወጣ።**

**ሀወኒ በችኮላ ፎቶውን ከከንፈ ተቀበለችው።**

**«ራሱ አኖሌ ነው» ብላ ጮኸች።**

ይህን ብላ ፎቶግራፉን ለአብርሃ ፀሎት ስታቀብልም በተስፋ ነበር። ኤርትራ የሰነበተው አኖሌ ይኸው ይሆን ዘንድ ተመኘች።

«ይሄው ራሱ ነው!» ሲል አብርሃ አረጋገጠ።

እንባዋ ከአይኗዋ እንደ ጅረት ቢወርድም ፊትዋ ላይ ግን የደስታ ስሜቶች ታጭቀው ታዩ። ሀየሎም ወደጣራው ቀና አለ። ጥሎበት አይሆንለትም የሀወኒ ነገር። ቅንነትዋን ይወድላታል። እንደ መፅሀፍ ተገልጦ ፊትዋ ላይ የሚነበበው ፍላጐትዋን መመርመርና ማስተዋል የሚፈጥርበት የደስታና የሀዘን ስሜት አለ።

ክንፈ ሰአቱን እየና - ቸኩል ብሎ እንዲህ አለ ...

«... ሀወኒ እጮኛሽ ወይም ወንድምሽ ባለመምጣቱ እንኳን ደስ ያለሽ:: ሁላችንም የደስታሽ ተካፋይ እንደምንሆን ታምኚያለሽ:: እዚህ ስብሰባ ላይ መገኘትሽም መልካም አጋጣሚ ነው:: እኔ እንኩዋ አኖሌ ወንድምሽ ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ነበር:: የዚህ ሰው የትውልድ አካባቢ ቡርቃ በመሆኑ አንዳንድ ጠቃሚ መረጃዎችን ካንቺ እናገኛለን በሚል ነበር በስብሰባው እንድትካፈይ የፈለኩት:: ዞረም ቀረ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች መግባት አለብን:: አኖሌ ዋቆ ወንድምሽ ነው:: ባይጐዳ ደስ ይለናል - አንቺም:: ሆኖም በሆነው ደቂቃ በፖሊስ ጥይት ሊሞት ይችላል:: ስለዚህ ከዚህ ተግባሩ እንዲገታ በሚደረገው የፖሊስ ስራ ላይ ለመሰማራት ያለሽን ፍላጐት ባውቀው ደስ ይለኛል!»

«በጣም ፈቃደኛ ነኝ! በጣም!» ጮኸች ሀወኒ::

«እንግዲያው እንቀጥላለን::»

ክንፈ ማብራሪያውን ካቆመበት ቀጠለ::

«... የቡርቃ ዝምታ በሚል ስያሜ ዘረፋ የሚፈፅመው ይኸው ግለሰብ ከሌሎች ቀማኞች የሚለየው ለወሰዳቸው ንብረቶች ወይም ጥሬ ገንዘቦች ደረሰኝ መስጠቱ! እንዲሁም ዝርፊያው ፖለቲካዊ መልክ እንዲይዝለት የሚያደርገው ጥረት ነው:: አኖሌ ከፈፀማቸው ወንጀሎች ማሳያ የሚሆኑትን ኢብራሂም ያብራራቸዋል» ብሎ የአዲሳባ ፖሊስ አዛዡን መልከት አደረገ ...

ኢብራሂም ወረቀቶቹን አስተካክሎ ያብራራ ጀመር::

«... አኖሌ ዋቆ የሚባለው ሰው የሚመራው ቡድን እስካሁን ከገጠሙን የተደራጀ ዝርፊያ ከሚፈፅሙ ቡድኖች የተለየ ባህርይ አለው:: የመጀመሪያው ልዩ ነገር ለወሰደው ንብረት ደረሰኝ መስጠቱ ነው:: ናሙና ይዤያለሁ» ብሎ በፖስፖርት ቅርፅ የተቆራረጠ ብራና አወጣ::

«ይህ ብራና በየትኛውም የፅህፈት መሳሪያ መደብር ውስጥ በሽያጭ አይገኝም:: ወደ ሀገራችን በውጭ ምንዛሪ የሚገባ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ በዚህ ወረቀት የሚጠቀመው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ነው:: መጠኑ ጥቂት ይሁን እንጂ በየማተሚያ ቤቶቹም ይገኛል:: በምስክር ወረቀቱ ላይ የተፃፈውን ላንብብላችሁ::

'ለአቶ ባለሀብት'





**እምላክ ለኦሮሞዎች በሰጣቸው ለምለም ምድር፣ ወንጀና ሀይቅ ለማይደና የተፈጥሮ ሀብት አላግባብ በመጠቀም ካካበቱት ንብረትና ገንዘብ የመጀመሪያውን ዙር ተመላሽ በማድረግዎ ምስጋናችንን እየገለፅን መልእክተኞቻችን በሁለተኛው ዙር ሲመጡ ይህ የምስክር ወረቀት ፊት ለፊት በሚታይ ቦታ ተሰቅሎ መገኘት እንደሚገባው እናሳስባለን::**

**- ቡርቃ አባዱላ'**

ቀማኞቹ በዚህ የምስክር ወረቀት መሰረት ከአዲሳባ፣ ከናዝሬት፣ ከአሰላና ከአካባቢው በድምሩ ሁለት ሚልዮን ብር የሚገመት ንብረትና ገንዘብ ዘርፈዋል:: ይህን የምስክር ወረቀት የሚሰጡት ድርጊታቸውን ፖለቲካዊ መልክ ለመስጠት ነው የሚል እምነት አለን:: ቡርቃ አባዱላ የሚለው ስያሜ እንዲገን ይፈልጋሉ:: ወንጀለኞቹ የታጠቁ ናቸው:: ድርጊቱን ከመፈፀማቸው በፊት በቂ ጥናት እንደሚያደርጉ መገመት ችለናል:: ከዝርፊያ ፍላጐታቸው ጐን ኦሮሞዎች በሌላው ብሄር ላይ በቀጣ እንዲነሳሱ ይሻሉ:: የሚበትኑት የምስክር ወረቀት ኦሮሞዎችን ለአመፅ ይቀሰቅሳል ብለው ያስባሉ:: ባለሀብቶች እየበረገጉ ክልሉን ጥለው እንዲወጡ የሚሹ ይመስለኛል:: በሚፈጠረው የፖለቲካ አለመረጋጋት በመጠቀም የገንዘብ ጥማታቸውን የማርካት ዝንባሌ ይታይባቸዋል:: ከዚህ ያለፈ አላማ አይኖራቸውም:: ቡድኑ አንድ ውስን ቦታ ጣቢያ ያለው አይመስለኝም:: ተንቀሳቃሽ ነው:: ባደረግነው ጥብቅ ክትትል የምስጢር ስማቸው 'የቡርቃ ዝምታ' የሚባል ሲሆን የቡድኑ ፊታውራሪ 'አኖሌ ዋቆ' እንደሚባል አረጋግጠናል:: ቡርቃ ሄደን ነበር:: እንቅስቃሴ የለም:: በዚያ መንደር ስም እየተጠቀሙ ጣቢያቸውን ቡርቃ ያደርጋሉ ማለት እንኩዋ ዘበት ነው:: በርግጥ የቡርቃ አካባቢ ገበሬዎች ለፖሊሶች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም:: ቀደም ሲል በነፍጠኛው ስርአት በደረሰባቸው ግፍ ሳቢያ ተጠራጣሪ ቢሆኑ አያስደንቅም:: ዝርፊያ የተፈፀመባቸው ግለሰቦች እንደሚገልፁት የሚመጡት «የቡርቃ ዝምታ» ወይም የቡርቃ አባዱላ ተከታዮች ፊታቸው ላይ ግር የሚያሰኙ ሁኔታዎች አሉ:: ትክ ብሎ ለሚያያቸው ተፈጥሮአዊ ያልሆነ የሚመስል - ግምባር አፍንጫ ቅንድብ ከንፈር ቢያም ማስተዋል ይቻላል:: አይጨዋጨዋሁም:: የሚዘርፉትን ሰው ረጋ ብለው ያናግራሉ:: በቅድሚያ ለማሳመን ይሞክራሉ:: ካልሆነ እስከ መግደል ሊሄዱ እንደሚችሉ እንገምታለን:: ከባንክ አካባቢ መረጃዎች እንደሚያገኙም ተደርሶበታል:: '150ሺህ ብር ከባንክ በጥሬ ገንዘብ ባወጣሁበት ቀን ማታ ቤቴ መጡ' ሲሉ በምሬት የገለፁልን ቡና ነጋዴ ዘራፊዎቹ ከባንክ ቤት መረጃ ካላገኙ በቀር ማንም ሊነግራቸው እንደማይችል ይገልፃሉ:: ሌላው 'ገንዘቡን ምን ያደርጉበታል' የሚለው ጥያቄ

ነው መመለስ ያለበት:: ከግምት በቀር የተጨበጠ መረጃ የለንም:: ምናልባት የጦር መሳሪያ እየገዙበት ሊሆን ይችላል:: አለያም እዚሁ አፍንጫችን ስር ታላላቅ ህንፃዎች እየገነቡበት ሊሆን ይችላል:: የሚያምታቱ ነገሮች አሉ:: የምስክር ወረቀታቸው ይዘት በሚዲያ እንዲነገርላቸው አጥብቀው ይፈልጋሉ:: ይህ ፍላጐታቸውም ከዝርፊያው ጀርባ የፖለቲካ ግፊት እንዳለ ያስገነዝባል:: ምናልባት የሚደግፋቸው ሃይል ሊኖር ይችላል:: ከኦነግ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚችል ጥርጣሬ አለ:: መረጃ ግን የለንም»

ኢብራሂም ገለፃውን አበቃ::

ከንፈ ረጅም አየር አስወጥቶ ወደ ሀወኒና አብርሃ ፀሎት በየተራ እየተመለከተ እንዲህ አለ፣

«ያለኝ መረጃ እንደሚያመለክተው አብርሃ ፀሎት ከአኖሌ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበረህ:: ማለት የምትችለው ካለ እንስማ? ሀወኒም አስተያየት እንደሚኖርሽ አምናለሁ:: አኖሌን በቅርብ ከማወቃችሁ አንፃር የናንተ አስተያየት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል::»

ሁለቱም ግን ለመናገር አልቻሉም:: ይተያዩ ጀመር:: አብርሃ ፀሎት «በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር» በሚል ምክንያት በአስቸኳይ አስመራን ለቆ አዲሳባ ሲገባ፤ የተፈለገበት ጉዳይ አኖሌን በተመለከተ ይሆናል ብሎ ጨርሶ አልገመተም ነበር:: አሁን ጉዳዩን ሲረዳ ሀዘን ወረረው:: ስለ አኖሌ ያለውን በጐ ስሜት አጥብቆ ማሰብ ጀመረ:: በደርግ እስር ቤት ተስፋ የቆረጠባትን የመጨረሻ ደቂቃ ደጋግሞ አስታወሳት:: አኖሌ ረድቶት ነበር:: መሰዋእትነትን ከፍሎለት ነበር:: ያን አስታወሰ:: እና አሁን ሊረዳው ፈለገ:: እርዳታው ግን አኖሌ ህገወጥ ድርጊቱን ትቶ ሰላማዊ ትግል እንዲጀምር በማገዙ በኩል መሆን እንደሚገባው አመነ::

ሀወኒ በበኩልዋ ሩቅ ተጉዛ ነበር - በሀሳብ:: በአንድ ወቅት 'ፈረንጅ አገር ተመችቶት ረሳኝ' ብላ ያማችው አኖሌ! ሞተ ብላ ሀዘንዋን ያወጣችለት እጮኛዋ፤ የልጅነት ፍቅረኛዋ አጣብቂኝ ውስጥ መግባቱን ስታስብ 'ከኔ ሌላ ማን አለው?' ብላ ራስዋን ጠየቀች:: 'ለኔስ ማን አለኝ?'

አኖሌን አጥብቃ ፈለገችው:: ናፈቃት፣

«አኖሌ ... የት ነህ?»

* * *





«የቡርቃ ዝምታ» ተብሎ በሚጠራው ቡድን ላይ የተጀመረው ውይይት በነጋታውም ቀጥሎ ዋለ:: ሀወኒና አብርሃ ፀሎት መረጃዎቻቸውን በዝርዝር አቀረቡ::

የሀወኒ መረጃዎች ትኩረት የሳቡ ነበሩ ...

ሀወኒ ስለቡርቃ ወንዝና ስለ አካባቢው ገበሬዎች ስትተርክ የኮሚቴው አባላት በመደነቅ አዳመጡዋት:: ገበሬዎቹ ስለቡርቃ ወንዝ ያላቸው እምነት አደገኛ መሆኑን የኮሚቴው አባላት አመኑ:: ገበሬዎቹ 'አኖሌ በዋቆ አባዱላ ለመሪነት የተመረጠ ነው' ብለው ማመናቸውም ቢሆን እንደዋዛ አልታየም::

ሀወኒ ትረካዋን ቀጠለች ...

ስለዋላጆቻቸው አሙዋሙዋት ስታወጋ ሀዮሎም ገፅታ ላይ ያየችው ጭንቀት ቢያባብትም እንደምንም ስሜትዋን ለመገደብ ታገለች::

ናዝሬት ትምህርት ላይ ሳሉ ተማሪዎች 'አኖሌ ዋቆ' በሚለው ስም ምትክ 'አኖሌ - ኦሮሞ' ይሉት እንደነበር፤ ይህን ስያሜ ማግኘት የቻለው ደግሞ ከኦሮሞዎች ጋር በኦሮምኛ ማውራትን በመምረጡና በክፍል ውስጥ መምህር በሌለበት ክፍለ ጊዜ ከተማሪዎች ፊት ወጥቶ ዋቆ አባዱላ ያወሩ የነበሩትን የጦርነት ታሪኮች እያወራ የተማሪዎችን ስሜት ይቆጣጠር እንደነበር፤ በዚህም በተማሪዎች መወደድን እንዳተረፈ፤ ዘርዝራ ለኮሚቴው አብራራች::

አብርሃ ፀሎት በበኩሉ አኖሌን ከተዋወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአስመራ የፈፀማቸውን ተግባራት በዝርዝር ገለፀ::

አኖሌ ሳመነበት ነገር ታማኝ መሆኑን አብነቶችን እየጠቀሰ አቀረበ:: ከዚያም ከአስመራ ከወጣ በሁዋላ በበረሀ ቆይታው የነበረውን አመለካከትና የትግል ተሳትፎ ዘረዘረ:: አኖሌ በበረሃ በአንድ አካባቢ ያለስራ ተወስኖ ጊዜውን አላሳለፈም:: ከሻእቢያ ሰራዊት ጋር ወደ ጡጊያ ቀጠና እየገባ ልምድ ቀስሞአል:: ወደ ምርኮኞች ማእከል ተጉዞ የኦሮሞ ተወላጆችን አነጋግሮአል:: ሱዳን እየሄደ ከኦነግ ወኪሎች ጋር ይገናኝ ነበር:: አኖሌ በበረሃ ቆይታው ራሱን በስፖርት ያንፅ ነበር:: ወታደራዊ ስልጠና ወስዶአል:: የሻእቢያን የትግል ታሪክ ከእንግሊዝኛ መፃህፍት ላይ አንብቦአል:: ሬድዮ ማዳመጥ ዋነኛ ተግባሩ ነበር:: የኢህአዴግ፣ የደርግ፣ የኦነግ፣ የኦህዴድ፣ አንዳቸውም አይቀሩትም:: የቬትናም የኩባና የቻይናን የትግል ታሪኮች አንብቦአል:: በኢትዮጵያና በአፍሪቃ ቀንድ ፖለቲካ ላይ ከኢሳይያስ አፈወርቂ ጀምሮ ከበርካታ የፖለቲካ ሰዎች ጋር እየተገናኘ ተወያይቶአል:: በበረሃ ቆይታው የፖለቲካ ግንዛቤ አድማሱን

ለማስፋት ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበር:: ይሁን እንጂ የወደፊት ፍላጐቱን ላለማሳወቅ ይጠነቀቅ እንደነበር መታዘቡን አብርሃ ፀሎት አብራራ::

የኦሮሞን ህዝብ በተመለከተ ያነሳቸው የነበሩትን አንዳንድ ነጥቦች ግን እያስታወሰ ተናገረ::

አኖሌ ብዙውን ጊዜ ለኦሮሚያ የሚያስፈልጉዋት መሪዎች በኦሮሞነታቸው የበታችነት ስሜት የማይሰማቸው መሆን አለባቸው ይል ነበር:: 'የኦሮሞዎችን ክብር ለማስጠበቅ ነፍጠኞች መረን ሲለቁ በወይራ ዱላ መቀጥቀጥ ያስፈልጋል' የሚል እምነት ነበረው:: 'የሞተውን የኦሮሞ ብሄርተኛነት ስሜት በህግ ብቻ ማነሳሳት አይቻልም' ብሎም ያምናል:: አኖሌ የመገንጠል ጥያቄ መፍትሄ ነው ብሎ አያምንም:: የመገንጠል ጥያቄ በመብት ደረጃ ከተቀመጠ በቂ ነው ይላል:: ኦሮሚያ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ተገንጥሎ የትም ሊሄድ አይችልም የሚል እምነት አለው:: ሆኖም የኦሮሞ ህዝብና ምድር ከመላው ኢትዮጵያ ከግማሽ በላይ በመሆኑ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያን በበላይነት መምራት ማረጋገጥ ይገባቸዋል' ባይ ነው:: አልፎ አልፎ ደግሞ 'ነፍጠኞች የኦሮሞን ክንድ ማወቅ አለባቸው:: ትምህርት ማግኘት አለባቸው' የሚል የጥላቻ ስሜት ያንፀባርቅ እንደነበር አብርሀ ገለፀ:: 'ኦሮሞዎች በኦሮሞነታቸው አንድነት ፈጥረው መታገል ይኖርባቸዋል' - **ይል** ነበር ደጋግሞ:: 'የኦሮሞዎች አንድነት አንገብጋቢ ጥያቄ ነው' ባይ ነበር::

ከማብራሪያዎቹ በሁዋላ በአኖሌ እምነቶች ላይ ሰፊ ውይይት አካሄዱ:: የተለያዩ አስተያየቶች ተሰነዘሩ:: ኩምሳ በአንድ ቃል «አኖሌ ወጥ የሆነ እምነት የለውም:: የራሴ የሚለው እምነት አልያዘም:: ተምታቶበታል:: የዝና ጥማት ሊኖርበትም ይችላል:: የአባቱ ተረት ደሞ አልፎ አልፎ ያባንነዋል:: አነግንም ሆነ ኦህዴድን ለምን እንደሚቃወም አያውቅም» ሲል አስተያየት ሰጠ::

ክንፈ ከኩምሳ የተለየ አስተያየት አልነበረውም::

ሀየሎም ግን ጥቂት ለየት ያለ ስሜት ነበረው፤

«ያላችሁት ሁሉ እንዳለ ሆኖ» ሲል ጀመረ «... መፍትሄው ላይ ግን አፅንኦት ሰጥቼ መግለፅ የምፈልገው ነጥብ አለ:: ከአኖሌ ጋር መወያየት ያስፈልጋል:: በግሌ አኖሌን ማሳመን ይቻላል ብዬ አምናለሁ:: አኖሌ ጀብደኛ አይመስለኝም:: ነፍጠኛው ላይ ያለው መራራ ጥላቻ ይሆናል የዚህ አይነት ስሜት ያሳደረበት::





'ይኸን ስሜት በጤናማው ጐኑ ማየት ይቻላል' ብዬ አምናለሁ:: 'አኖሌ ኦህዴድን ቀርቦ ቢያየው ይጠላዋል?' ያልተመለሰ ጥያቄ ይመስለኛል::»

ኩምሳ የሀየሎምን አሳብ ተቃወመ፤

«ኤርትራ ላይ አግኝቼው በኦህዴድ ዙሪያ ሰፊ ውይይት አድርገናል:: ግትር አቋዋም አለው:: 'ኦህዴድ ከኢህአዴግ አባል ድርጅትነት መውጣት አለበት' ይላል:: በቂ ምክንያት ግን አያቀርብም:: 'ወደ ድርጅታችን ግባና ኦህዴድን በነፃነት የመምራት እድል እንሰጥሀለን' አልኩት:: አላመነኝም:: የአቢሲኒያ ገዢዎችን ስር የሰደደ የተንኮል መንፈስ እያሰበ ብቻ የሚበረግግ ይመስለኛል::»

«ሀየሎም ያቀረበው ሀሳብ ተገቢ ይመስለኛል» አለች ሀወኒ «... አኖሌን መቅረብና ማወያየት ያስፈልጋል:: እኔ በበኩሌ ለዚህ ተግባር ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነኝ:: አኖሌን ማሳመን የሚቻል ይመስለኛል::»

አብርሀ ፀሎት በበኩሉ የሀየሎምን አሳብ ደግፎ አስተያየት ሰጠ:: አኖሌ በውይይት የሚያምንና ካመነበት ደግሞ ለእምነቱ የሚሞት ጠንካራ ሰው መሆኑን በሞቀ ወኔ ገለፀ::

ውይይቱ በዚሁ ነበር የተደመደመው::

* * *

ተሰብሳቢዎቹ የሰብሰባ አዳራሹን ለቀው መውጣት ሲጀምሩ አብርሃ ፀሎት፣ ሀወኒና ሀየሎም ወደ ሁዋላ ቀሩ:: ክንፈ ነበር እንዲቆዩ የነገራቸው:: ሁዋላ ሲቀሩም፤ ሀወኒና አብርሀ ፀሎትን፣

«እኔ ቢሮ ጠብቁኝ፤ እፈልጋችሁዋለሁ» አላቸው::

ሀወኒና አብርሃ ፀሎት ተያይዘው ሲወጡ ክንፈና ሀየሎም ቀሩ:: ሁለቱም የተማከሩ ይመስል ሲጋራቸውን አወጡ:: አኩል ለኩሱ:: አኩል መማግ ጀመሩ:: በማንኛውም ነገር እንዲሁ ይግባባሉ:: የሚያስቡት ጭምር ይቀራረባል:: በታላላቅ ውጊያዎች ጭምር አብረው ሰርተዋል:: እጅግ እጅግ ቅርብ ናቸው፣

«ምን አሰብክ?» ሲል ጠየቀ ክንፈ::

«አኖሌ ሳያውቀው ታላቅ አደጋ እየፈጠረ ነው::»

«ሳያውቀው ነው ብለህ?» አለ ክንፈ::

«ውጤቱ ምን ሊያስከትል እንደሚችል የገባው አይመስለኝም::»

ክንፈ ጫን ባለ ድምፅ፣

«የአኖሌን ጭራ መያዝ ያስፈልጋል።» አለ።

«የተደበቀበት ቦታ ፍንጭ የላችሁም?» አለ ሀየሉም።

«ምንም!» አለ ክንፈ ሲጋሩን ባለ በሌለ ሀይሉ እየመጠጠ። ንዴቱ ቅርብ ናት። እልሁ ባሩድ ናት። እንቅልፍ አይተኛም - ያሰበውን ሳይፈፅም። ሲጋራቸውን እየማገ ይተያዩ ጀመር፣

«አዲሳባ ያለ ይመስልሀል?» ሲል ሀየሉም ጠየቀ።

«ይመስለኛል። ሌላ ቦታ ሊደበቅ አይችልም።»

«ፎቶውን በቴሌቪዥን ብንለቅስ?»

«ምን ብለን?»

«ዘራፊ፣ ወንጀለኛ ተብሎ ነዋ!»

ክንፈ በመቃወም ራሱን ግራቀኝ ወዘወዘ።

«ይህን ካደረግን አኖሌን ፈጥነን ልንይዘው እንችል ይሆናል። ከጀርባው ያለው ግን ለዘላለሙ ራሱን ይሰውራል? አኖሌን አሳዶ መያዝ አይከብድም። ዋናው ጉዳይ ግን ከጀርባው ያለውን ማወቅ ነው። ስለዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቴሳውን መርገጥ አለብን።»

«ከጀርባው ማን ይኖራል?» ሲል ጠየቀ ሀየሉም።

«ማን ያውቃል?»

«አነግ? ጀርመኖች? ወይስ? ...» ሀየሉም የጀመረውን ሳይጨርስ አንጠልጥሎ ተወው።

«ይህን ለማወቅ ቴሳውን መርገጥ አለብን። ከተደበቀበት ዋሻ ብቅ እንዲል አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብናል ...»

የክንፈ አይኖች በድንገተኛ ብርሃን ተሞሉ። ፈገግታ ታየበት። ሀየሉም የክንፈን ገፅታ በማየት ብቻ ተስፋ አደረገ። አዎን ክንፈ አንድ ድንቅ መላና መፍትሄ ሲያገኝ አይኖቹ ይበራሉ።

«ምን አሰብክ?» አለ ሀየሉም፣ የክንፈን አሳብ ለመስማት በእጅጉ ጉዋጉቶ።

«አኖሌ አዲሳባ ነው ብለን እንመን። አዲሳባ የት? ቤት ተከራይቶ? ሆቴል ውስጥ? ቤት ገዝቶ? ዘመዶቹ ቤት? ወይስ እንጦጦ ዱር ውስጥ? እኔ እንደሚመስለኝ ቤት ተከራይቶ ወይም





ገዝቶ ነው ሊሸሽግ የሚችለው። ዘመድ የለውም። እንጦጦ ባህርዛፎች ውስጥ አይታሰብም። ሆቴል ለመቆየት አይደፍርም። ምናልባት አራትም አምስትም የተከራየው ቤት ሊኖረው ይችላል። ከቤት ቤት እየለዋወጠ ሊሆን ይችላል ድርጊቱን ሁሉ የሚፈፅመው። ታማኝ ተከታዮች ሊኖሩትም ይችላሉ። ይህ እውነት አይመስልህም?»

«ሊሆን ይችላል።»

ክንፈ ሲጋራውን ተረኩዋኩሶ፣ በችኮላ ሌላ ለኩሰ። አይኖቹ ይበልጥ ደመቁ፣

«... አብርሃ ፀሎት ቅድም ሲገልፅ አኖሌ ሚዲያ የመከታተል ልማድ ማካበቱን አንስቶ ነበር። ስለዚህ የአይጥ ጉሬ ውስጥም ይደበቅ አለያም ሰማይ ላይ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን መከታተሉ አይቀርም። አይመስልህም?»

«ሊሆን የሚችል ነው!» አለ ሀየሉም። ክንፈ ምን እንዳሰበ አልገባውም።

«እንግዲያው በተከታታይ በሚካሄድ የስብሰባ ዜና ላይ ሀወኒና አብርሃ ፀሎት ተደጋግመው እንዲታዩ ይደረግ። ያን ጊዜ የአኖሌ ጭንቅላት ይበጠበጣል። እንቅልፍ ያጣል። ሀወኒ በጣም ታፈቅረዋለች። አኖሌም ከጀርመን የተመለሰው ሀወኒን ፈልጉ ጭምር እንደነበር ከአብርሃ ማብራሪያ የሰማሁ ይመስለኛል። በጣም ይፋቀራሉ። ከእጮኝነት በላይ ልጅነታቸውን ተጋርተዋል። ወንድምና እህት ናቸው። ፍቅረኛሞች ናቸው። አኖሌ በቴሌቪዥን መስኮት ሲያያት ስሜቱን ጨርሶ መቆጣጠር አይችልም። እሰዋን ለማግኘት ይበልጥ እንዲነሳሳ ደግሞ ሀወኒና አብርሃ ፀሎት ጉን ለጉን ተቀምጠው ሲንሾካሾኩ ቀራጩ ለሰከንድ ያህል ይቅለባቸው። አኖሌ እቅሉን ይስታል። አይጠራጠርም። ከቶ ሳይጠራጠር ከሁለት አንዱን ለማግኘት ጥረት ማድረጉ አይቀርም። በተለይ አብርሃን ያምነዋል። ህይወቱን አድኖታል! ስለዚህ አሳልፎ እንደማይሰጠው እርግጠኛ ይሆናል። ሀወኒን ሲያይ ደግሞ ሰው ነውና ውስጡ የታመቀው ናፍቆት እንደሚበጠብጠው ጨርሶ አይጠረጠርም። የቴሌቪዥን ሰዎች ስብሰባው በነጋታውም እንደሚቀጥል ግልፅ ያድርጉ። በነጋታው አኖሌን ወይንም ወኪሉን በአካባቢው እናጣውም ...» ብሎ ፈገግ አለ።

ሀየሉም «የተረገምክ!» ብሎ ረጅም ሳቅ አሰማ።

ተቻኩለው ወደ ክንፈ ቢሮ አመሩ። ክንፈ ጊዜ አላጠፋም። ወደ ቴሌቪዥን መምሪያ ሀላፊው ደወለ። አምስት ደቂቃ ያህል

ተነጋገሩ። ክንፈ ስልኩን ዘግቶ፣

«ተከታታይ የስብሰባ ዜና የላቸውም!» አለ። አያይዞ «መጠበቅ ሊኖርብን ነው?» አለ በቅሬታ።

«የለም!» አለ ሀየሎም፤ አንድ አሳብ ብልጭ እያለለት፣ «የሀሰት ዜና መፍጠር እንችላለን።»

«እንዴት አድርገን?» አለ ክንፈ «... በነጋታው በምንጠቅሰው ስፍራ የግድ ሰብሰባ መኖር አለበት። ተሰብሳቢዎች በቴሌቪዥን ሲታዩ ደግሞ ከሀወኒና ከአብርሃ ሌላ ተሰብሳቢ የግድ መታየት አለበት። አለያ እኖሌ ድራማ መሆኑ ይገባዋል። ያልተለመደ የዜና አቀራረብ ልንከተል ደሞ አንችልም።»

«ይቻላል!» ሲል ሀየሎም ደግሞ አረጋገጠለት። «... እንዲያውም ከኤርትራ ጊዜያዊ ፅህፈት ቤት ጋር መነጋገር ይቻላል። ከዚህ በፊት የተቀረፁ መጠነኛ ሰው ያለባቸውን የስብሰባ ፊልሞች መጠቀም ይቻላል። ጉዳዩን ከኤርትራ ጋር ካያያዝነው የአብርሃ ፀሎት መታየት የበለጠ አሳማኝ ይሆናል። የዜናውን ርእስ ጉዳይ የሁለቱን ሀገሮች ህዝቦች ለማቀራረብ ወደፊት ስለሚካሄዱ የሙዚቃ ፌስቲቫሎች ሊሆን ይችላል። ውይይቱ በነጋታው በዚያው በኤርትራ ፅህፈት ቤት እንደሚቀጥል ሊገለፅ ይችላል። ዜና ላይ፣ ሰብሳቢና ተሰብሳቢዎችን ከቆየ ፊልም መጠቀም። በየመካከሉ ሀወኒና አብርሃን ጉላ እያደረጉ ማቅረብ ይቻላል።»

ክንፈ በመስማማት ራሱን ላይ ታች እየወዘወዘ፣

«ልክ ነህ ይቻላል።» አለ «...ግን ለአብርሃና ለሀወኒ አቅዱን በግልፅ ልንነግራቸው ይገባል። አላማውን ጭምር እንዲያምኑበት ማድረግ ያሻል።»

## - 2 -

በምሽቱ የሚተላለፈው ዜና በሀየሎምና በክንፈ እቅድ መሰረት ይዘጋጅ ዘንድ ለታጋይ ጋዜጠኞች መመሪያ ተላለፈ። ፊልም ቀራጮቹ የአብርሃና የሀወኒን ምስል ቀርፀው የማስመሰያ ቅንብራቸውን ለመስራት ኢህአዴግ ፅህፈት ቤት ወደሚገኘው ስቱዲዮ ተጣደፉ። ቀረፃው ካለቀ በሁዋላ ክንፈ «ማምሻውን ጉዳይ አለሽ እንዴ?» ሲል ለሀወኒ ጥያቄ አቀረበላት። አብርሃ ቀደም ብሎ ሄዶ ነበር።

«የለኝም። ትጋብዙኝ ዘንድ ካሰባችሁ ፈቃደኛ ነኝ» አለች





እየሳቀች።

ተያይዘው ወጡ።

በመንገዳቸው ላይ ሀወኒ እኖሌን በተመለከተ እንደዋዛ አንዳንድ ያልተጠበቁ አስተያየቶችን ትሰነዝር ጀመር፤ በክንፈ መኪና ነበር የደብረዘይትን መንገድ ይዘው መጉዋዝ የጀመሩት፣

«በነገራችን ላይ» አለች ሀወኒ «... እኖሌ በኦህዴድ ላይ ያሳደረው እምነት ከፊል እውነታ እንዳለው አታምኑም?»

ከመቅፅበት ተያዩ - ሀየሎምና ክንፈ።

ዱብ እዳ ነበር የሆነባቸው። ከስብሰባው ይህን መሰል እምነት ይዛ ትወጣለች ብለው አልጠበቁም ነበር። ለእኖሌ ያላት ወገናዊነት አድልቶ እንጂ ተጨባጭ ነገር ይኖራታል ብሎ ባለመገመቱ፣ ክንፈ ቀጥሎ የምትናገረውን ለመስማት እየጉዋጉዋ ነበር፣ «የእኖሌ ከፊል እውነታ ምንድነው?» የሚል ጥያቄ ያቀረበላት።

«በስራ አስፈፃሚ ደረጃ ያሉ መሪዎቻችን መባለግ ጀምረዋል። ኦሮሚያን ርስታቸው ለማድረግ መሩዋሩዋጥ የጀመሩ ከፍተኛ ባለስልጣናት ብቅ ብቅ እያሉ ነው። የሌላውን አላውቅም። እኔ ግን የቅርብ አለቃዬን በተመለከተ በቂ ማስረጃ ላቀርብላችሁ እችላለሁ። አጋጣሚ ቀጥተኛ አለቃዬ በመሆኑ ዝርዝር ነገሮችን ጭምር ማወቅ ችያለሁ። የሚያሳፍር ስራ እየሰራ ነው ያለው። ይሸረሙጣል። ጉቦ ይወስዳል። ሌላም ሌላም ... ስለማን እንደማወራ መቼም ገብቶአችሁዋል። ከኔ ጋር በተደጋጋሚ አይታችሁት ሊሆን እንደሚችልም እገምታለሁ። ምስጢሮቹን ሁሉ ስለማውቅበት በጣም ይፈራኛል። እኔ ለርሱ አፈርኩ። መሪዬ ነው ብዬ መቀበል ጭምር አቃተኝ። ይህ በሽታ እየተዛመተ ከሄደ አደገኛ ይመስለኛል። በአመራር ደረጃ ብትነጋገሩበት ጥሩ ነው። እርግጠኛ ነኝ የኢህአዴግ አመራር አባላት በየጊዜው እየተገናኙ ውስጣቸውን ይፈትሻሉ። አይደለምንዴ?»

«አሁን ያልሻቸው ተጨባጭ ናቸው?» አለ ክንፈ።

«ማስረጃ የለኝም። ማስረጃ መሰብሰብ የሚገባኝ ግን አይመስለኝም። አንድ አካል መኖር አለበት ይህን መሰል ጥቆማዎችን የሚቀበል ...»

«ግምገማዎች ላይ ማንሳት ተገቢ ይሆናል» አለ ሀየሎም። «ካልተሳሳትኩ ስለ ሰለሞን ዲሳሳ ነው እየተናገርሽ ያለሽው።» አለ ክንፈ።

«አዎን - ስለእሱ ነው የማወራው!»

«በግል አነጋግረሽው ነበር?»

«አንስቼለት ነበር»

«ምናለሽ?»

«ካደ። ቅድም ዜኒት ብዬ የገለፅኩላችሁን ልጅ በፍቅረኛ ደረጃ ይዞአታል። እኔ ዘንድ ስትመጣ ነው የተዋወቃት። ልጅቱ ትምህርት ቤት ሳለን ጉዋደኛዬ ነበረች። እኔ ወደ ዩኒቨርስቲ ስሄድ እሰዋ ንግድ ጀመረች። አሁን እሳት የላሰች ነጋዴ ወጥቶአታል። ጥሩ ያልሆነ ባህርይ የያዘች ይመስለኛል። ይኸው የኛው ሰው ታዲያ አብሮአት ያብዳል። እዚሁ አዲስ አበባ ቤት እንድታገኝ ጭምር አድርጉአል። ሌላም ... ሌላም ብዙ ነገሮች እሰማለሁ። ከልጅቱ ጋር ግንኙነት ከጀመረ ወዲህ ታጋይ ሚስቱን ፈትቶአታል። ተገቢ እንዳልሆነ ነገርኩት። 'የተሰመደ ነው' የሚል ምላሽ ነው የሰጠኝ። 'ብዙዎች እየፈቱ ነው' አለኝ። እንዲህ ሲለኝ ላንቀው ነበር። አበድኩ። ናቅሁት። 'ሌሎች ስለፈቱ ነው መፍታት ያሰብህ ወይስ ስላልተግባባችሁ?' ስለው 'ይህን ያህል የምትንገበገቢው በርግጥ ለሚስቴ አዝነሽ ነው ወይ?' አለኝ። ከአንድ መሪ ይህ ንግግር አይጠበቅም»

«ቀንተሽ እንዳይሆን!» አላት ሀየሎም።

ሀወኒ ጨኸትዋን ለቀቀችው። ወደ ሀየሎም ተጠግታ ታንባርቅበት ጀመር።

«ሀየሎም! የልብህን ነው? እኔ እንደዚያ ነኝ!?»

ድምፅዋ ዝግትግት አለባት። ክንፈና ሀየሎም እየተቀባበሉ ይስቁባት ጀመር። የምር መናደድዋን ሲያይ ሀየሎም

«ቀልዴን ነው ሀወኒ!» አላት።

«የልብህን ከተናገርክ ወዲያ?»

«ስጋ ብዖት!» ሲል ማለ።

አመነችው። ሀየሎም 'ስጋ ብዖት' ካለ አይዋሽም።

«እኔ አነጋግረዋለሁ» አለ ክንፈ።

ሀወኒ ቀጠለች።

«ዜኒት ማለት አደገኛ ሴት ናት - ክንፈ። የኢህአዴግ ትግል ለርስዋ Adventure ብቻ ነው። ታጋይነት ማለት ለዜኒት ስኁራ የሚያገለግል ታፔላ ብቻ ነው። ሹም ማለት ደግሞ ፈላጭ ቆራጭ። ከሹም መጠጋት ማለትም መከበር ማለት ነው - ለዜኒት። አታምኑኝም! ሰለሞን ታጋይነቱን ስንራ ማዋል ጀምሮአል። የሚያስደነግጥ ነገር ጭምር ለዜኒት ነግሮአታል። የእናቱ አባት አማራ መሆናቸውን አጫውቶአታል። ይህን ሁሉ ምን አመጣው? ቁራጭ የአማራ ደም ፍለጋ ወደ አያቱ ምን አሻገረው? በኦሮሞነቱ ያፈረ ይመስለኛል። ለኦሮሞነቱ ክብር የሌለው ሰው ደሞ አለቃ ሊሆነኝ ቀርቶ የኔ ድርጅት አባል ከቶ ሊሆን አይችልም። ይህን አይነት ሰው ከአመራር መባረር አለበት። አዲሳባ ተወልዶ እንዳደገ ጭምር ይናገር ጀምሮአል። አዲሳባ መወለድ ታላቅነት መሆኑ ነው? ከአራዳ ልጅ ካምፕ ራሱን መቀላቀሉ ይሆን? አዲሳባ ራሱ የኦሮሚያ መሆኑን እያሰበ ሊሞቀው ይገባ ነበር።»

«የትግል ልምድ ማጣት ሊከስታቸው የሚችሉ አያሌ ጉድለቶች ይኖራሉ። ኦህዴድ ቀስ በቀስ ውስጡን እያጠራና እየጠነከረ መሄድ ይጠበቅበታል» አለ ሀየሎም።

ሀወኒ ተቃወመች!

«ሰለሞን የትግል ልምድ እጥረት የለበትም። እንደማውቀው ስድስት አመታት ታግሎአል። የኦሮሞነት ስሜት ነው የሌለው። ከኦሮሞነቱ እየሸሸ ነው። ሸሽቶ የት ይደርሳል? አለያ ደሞ ኦሮሞ ላይሆን ይችላል።»

«በቅርቡ ግምገማ ነበራችሁ አይደለም?» ሲል ጠየቃት ክንፈ «... በዚያ ላይ የተነሱ ነገሮች የሉም?»

«እሱን ግምገማ እንኳዋ ተወው ክንፈ። ቀልድ ነበር። የበረሀዋ ባህል ድምጥማጥዋ የጠፋችበት ግምገማ ነበር። ብዙ የሚነገር አለው። ግን የሆነ ያልሆነውን ከመናገሬ በፊት በቅድሚያ ኩምላን በስፋት ሳናግረው ፈልጌያለሁ። በዳዴኦአ ውስጥ አደገኛ አዝማሚያዎችና ችግሮች ይታዩኛል።»

«በህወሀትም ቢሆን ከዚህ የከፋ አመለካከቶች የተከሰቱበት ጊዜ ነበር። በትግል ነው ያን የአደጋ ጊዜ ማለፍ የሚገባው» ክንፈ ነበር።

«በግለሰብ ደረጃ በየትኛውም የኢህአዴግ ድርጅት ውስጥ ተመሳሳይ መዝቀጥ ሊከሰት ይችላል። መፍትሄው እያጠሩ መሄድ ነው»

እየተቀባበሉ አስተያየት ይሰጡ ጀመር። ሀየሎምና ክንፈ ሀወኒን ራት ጋብዘው ሲያበቁ ቤትዋ ድረስ ሸኙዋት። የዜና ሰአት

ላይ ነበር የደረሰችው:: ሶስተኛው ዜና አኖሌን ለማጥመድ የተዘጋጀው የእለቱ ቅንብር ነበር:: የተቀጣለት ቅንብር:: ፊልም ቀራጮ! ሀወኒና አብርሃን በበቂ ሁኔታ አሳይቶ ወደ ሌሎች ተሰብሳቢዎች ተሻገረ:: ዜና አንባቢው ስብሰባው በነጋታው ከማለዳው ሶስት ሰአት ጀምሮ በኤርትራ መንግስት ጊዜያዊ ፅህፈት ቤት ቀጥሎ እንደሚውል ገልፆ ወደ ቀጣዩ ዜና ተሻገረ::

ሀወኒ ሳታውቀው ሆድዋ ግልብጥብጥ አለባት:: በረዳት:: መንፈስዋን በረዳት:: እንባዋ እንዳይቀድም ጣራ ጣራ ማየት ጀመረች:: ውስጥዋ ግን እንደልማዱ ይጮሀል ...

«አኖሌ ... እወድሀለሁ!»

- 3 -

አብርሃ ፀሎት በኤርትራ ጊዜያዊ ፅህፈት ቤት ደጃፍ ላይ ቁሞ ሰው የሚጠብቅ መስሎ ሰአቱን ደጋግሞ ያይ ጀመር:: 2:45 ይላል:: ሀያ ደቂቃ ብቻ በዚህ መልኩ ቆይቶ ወደ ፅህፈት ቤቱ ቅፅር ግቢ እንዲገባ ነው የተነገረው:: እሱ እንደገባ ደግሞ ሀወኒ እንዲሁ ሃያ ደቂቃ ያህል ከፅህፈት ቤቱ አጠገብ ባለው ሬስቶራንት ቆይታ እስዋም ወደ ፅህፈት ቤቱ ቅፅር ግቢ ትገባለች:: ለሁለቱም መልእክት ማስተላለፊያ ረቂቅ መሳሪያ ኮዋሌታቸው ላይ ተያይዞላቸዋል:: የሚያዩትን ከአኖሌ ጋር የተያያዘ ነገር ሁሉ በዝቅተኛ ድምፅ መናገር ብቻ ይበቃቸዋል:: የሚያስተላለፉት እያንዳንዱ መልእክት በሶስት ደቂቃ ውስጥ በፅህፈት ቤቱ ዙሪያ ሲቪል ለብሰው በእግርና በመኪና ለፈሰሱት የደህንነት ሰዎች ይደርሳል::

አብርሃ ፀሎት በተነገረው መሰረት ሰአቱን እያየ ከወዲያ ወዲህ ይንጐራደድ ጀመር!

«አምስት ሳንቲም!» አለው አንድ ጐልማሳ ለማኝ::

እስር ሳንቲም አውጥቶ ሰጠው:: ለማኙ አመስግኖ ሄደ::

«ስለ አብርሃሙ ስላሴ!» አለ ሌላ ሽማግሌ ለማኝ::

«እግዜር ይስጥልኝ!» አለ አብርሀ::

«ሲጋራ! ማስቲካ!» አለ ሱቅ በደረቴ::

ዝም አለው::

«የአረቡ ሮዝማን አለኝ:: ዊንስተን ... ጦርና ሱፐር ሚኒት ማስቲካ!» አለ::





«አልፈልግም!»

«ጫማ ልጥረግ አባባ» አለ ልጅ እግር ሊስትሮ::

«ደህና ተወው!»

«ቆሽሾአል ልጥረግልዎት ...»

«አያስፈልገኝም አልኩህ» አለ ቆጣ ብሎ::

«እዚህ አገር እንደ አስመራ ውድ አይደለም ጋሼ:: ዘጠና ዘጠኝ ሳንቲም ብቻ ነው የማስከፍልዎ:: የቦሎኛ ቀለም አለኝ::»

አብርሃ ፀሎት በድንጋጤ ራደ:: ቃል ሳይተነፍስ እግሩን አነሳ:: ሊስትሮው ጫማ መወልወል ጀመረ:: ትንፋሹን እንደምንም ሰበሰበ፣

«ማነው የላከህ?» ሲል ጠየቀው::

«ስማቸውን አልነገሩኝም::»

«ረጅም፣ ጠይም ናቸው?»

«አይደሉም:: ቀላ ይላሉ:: ራሰበራና አጭር ናቸው::»

«የት ነኝ አሉህ?»

«እሱንም አልነገሩኝም::»

«ምን እንድትነግረኝ ላኩህ?»

«የርሶን ወይም የሀወኒን ስልክ ቁጥር::»

አብርሃ አመነታ:: አኖሌ መያዝ እንዳለበት አመነ:: ካልተያዘ አንድ ቀን ባጭሩ ይቀጫል:: ተይዞ ሰላማዊ ትግል መጀመር አለበት:: በህቡእ የሚታገልበት ምክንያት ለአብርሃ አልታይህ አለው:: ተገቢ ያልሆነ መስዋእትነት መክፈል እንደማይገባው አመነ፤

«ቁጥሩን እሰጥሀለሁ:: ታዲያ የት አገኘተህ ነው ለራሰበራው ሰው የምትሰጠው?»

«ቀጥረውኛል::»

«የት?»

«ሜክሲኮ አደባባይ::»

«ስንት ሰአት ነው ቀጠሮአችሁ?»

«እንደጨረስክ ነው ያሉኝ።»

«ታዲያ በቃልህ ቁጥር መያዝ ትችላለህ? ወይስ ስክርቢቶና ወረቀት ልስጥህ?»

«በቃሌ እይዘዋለሁ ይንገሩኝ።»

አብርሃ ፀሎት የሀወኒንም የራሱንም የስልክ ቁጥሮች አንድ በአንድ ነገረው።

«ይዘሀቸዋል?»

«አዎን ይገኖቸዋለሁ።»

«እስኪ ጥራቸው?»

ሊስትሮው ቁጥሮቹን ጠራለት። አልተሳሳተም። እንዲያውም አልተደነቃቀፈም።

«ሊስትሮ ነህ የውነት?»

«አዎን!»

«እኔን እንዴት አወቅኸኝ ታዲያ?»

«በፎቶግራፍ!»

«ማን አሳየህ የኔን ፎቶ?»

«ወንድምዎ ኖትዋ! ራስበራ ያልኩዎ።»

'ፎቶዬን የት አገኘ?' ሲል አሰበ አብርሀ።

አብርሃ ፀሎት አንድ ብር አውጥቶ ለሊስትሮው ሰጠው። አብርሃ ፀሎት አንድ ብሩን ኪሱ ጨምሮ፤ የሊስትሮ ሳጥኑን አንከብክቦ ልጁ አንድ ብሩን ኪሱ ጨምሮ፤ ወደ ላሊበላ ሬስቶራንት አቅጣጫ ማዝገም ጀመረ።

አብርሃ ፀሎት ጊዜ አላጠፋም።

«መረብ 91 ነኝ» ሲል ኮዱን ከተናገረ በሁዋላ መልእክቱን በችኮላ ያስተላልፍ ጀመር፤

«ጫማዬን የጠረገልኝ ቀይና ኮስማና ሊስትሮ ከአኖሌ የተላከ ነው። የኔንና የሀወኒና ስልክ ቁጥር ተቀብሎኛል። ሜክሲኮ አደባባይ ከአኖሌ ወኪል ጋር ቀጠሮ ይዞአል። እንደሚመስለኝ ሊስትሮው በቀጥታ ከአኖሌ የተላከ አይደለም። ስለዚህ ሊስትሮውን በቀጥታ ከአኖሌ የተላከ አይደለም። ራስበራ፤ አጭርና የተገናኘውን ሰው በቀጥታ መያዝ አይገባም። ራስበራ፤ አጭርና ቀይ ነው ሊስትሮውን የላከው ሰው። መረጃው ስህተት ሊሆንም





ይችላል። እንደሚመስለኝ ከሊስትሮው ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ሰዎች አኖሌ ዘንድ እስኪደርሱ ድረስ ክትትል ቢደረግባቸው ጠቃሚ ይመስለኛል። አበቃሁ - መረብ 91።»

አብርሃ ይህን መልእክት አስተላልፎ ወደ ኤርትራ ጊዜያዊ ፅህፈት ቤት ገባ። ተግባሩን በተገቢው መንገድ ማጠናቀቁ ተሰማው። በአጋጣሚ ከሀወኒ ጋር ስልክ በመለዋወጣቸው ተደሰተ ...

* * *

ሶስት የደህንነት ሰዎች በተለምዶ 'ወያኔ' ተብላ በምትጠራው ቶዮታ መኪና ሊስትሮውን በሀምሳ ሜትር ርቀት ይከተሉታል።

ሊስትሮው እየተጣደፈ ይራመዳል። ደህንነቶቹ ታጥቀዋል። አይናቸውን ለሰከንድም ከሊስትሮው ሳይነቅሉ ተከታተሉት። የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ህንፃ አጠገብ መብራት ያዛቸው። ሊስትሮው ከጉናቸው ቀምአል። ያዩታል። እሱ አያያቸውም። መኪና ቀነስ ሲልለት በሩጫ አስፋልቱን ተሻግሮ በጥድፊያ ገሰገሰ። ግን ድንገት ቆም አለ። ከኪሱ ቁራጭ ወረቀትና ብእር አውጥቶ የሊስትሮ ሳጥኑን አስደግፎ ይፅፍ ጀመር። ፅፎ ሲያበቃ መንገዱን ቀጠለ።

የደህንነቶቹን መኪና መብራት ለቀቃት። በተለመደው ርቀት ይከተሉት ጀመር። ተከታትለው ሜክሲኮ አደባባይ ደረሱ። ሊስትሮው በአደባባዩ በስተቀኝ ባለችው ካፍቴሪያ አጠገብ ከተኮለኮሉት መስሎቹ መካከል ገብቶ ተቀላቀለ።

ደህንነቶቹ የመገናኛ ሬዲዮናቸውን ከፍተው ሪፖርት አስተላለፉ። ከንፈ አጭር መመሪያ ሰጠ፤

«ባለጉዳይ መስላችሁ አጠገቡ ቆዩ። በቃል ወይም በወረቀት የሚያስተላልፈውን መልእክት በጥንቃቄ ተከታተሉ። አጣራጣሪ ነገር ካያችሁ እስከ እኩለ ቀን ድረስ ጫማ የሚያስጠርጉትን በሙሉ ተከታተሉዋቸው። 6:30 ላይ ከመካከላችሁ አንዳችሁ ጫማ አስጠርጉ። እየጠረገ ሳለ ስልክ ቁጥሮቹን በአግባቡ አስተላልፎ እንደሆን ጠይቁት። ለምን አይነት ሰው እንደሰጠ ጭምር፤ መልእክቱን የተቀበለውን ሰው ካወቃችሁ በሁዋላ ሀይላችሁን ወደዚያው አሰባስቡ። አኖሌን ብትደርሱበትም እንዳትይዙት። ሃያ አራት ሰአት አትለዩት። የሚገባበትን ቦታና የሚገናኛቸውን ሰዎች የሚከታተሉ ሰዎች በፍጥነት ተመድበው የያንዳንዳቸው መድረሻ በዝርዝር ይጠና። ይሄ ለሶስት ቀናት በተከታታይ የሚቀጥል ስራ ይሆናል። የምትከታተሉዋቸው ሰዎች በጭራሽ

እንዳይጠረጥሩዋችሁ»

ዳሩ እንደታሰበው ሳይሆን ቀረ::

እስከ 6:30 ሲስትሮው የአራት ሰዎችን ጫማ ነበር የጠረገው:: ከአራቱ አንዱ የህወሀት ታጋይ ሆኖ ተገኘ:: ተከትለውት ነበር:: ሄዶ ሄዶ መከላከያ ሚኒስቴር ፅህፈት ቤት ገባ:: ሁለተኛዋ ወጣት ሴት ነበረች:: ታክሲ ይዛ ስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ገባች:: ሶስተኛው በእድሜ የደከሙ ሽማግሌ ነበሩ:: እዚያው ማኪያቶ አዘው ጫማ አስጠርገው የትም አልሄዱ:: እዚያው ማኪያቶ አዘው አሳፊ አግዳሚውን ይታዘቡ ያዙ:: የመጨረሻው መልከ መልካም ወጣት ነበር:: ባችኮላ አስጠርጐ እብስ አለ:: ፒያሳ ድረስ ተከተሉት:: ሲኒማ ኢትዮጵያ ገባ:: ከደህንነቶቹ አንዱ ሲስትሮው አጠገብ ያለውን የኤሌክትሪክ ምሰሶ ተደግፎ ደቃቃውን ጫማ ጠራጊ በጥንቃቄ ተከታትሎታል:: ከአንዳቸውም ጋር መልእክት አልተለዋወጠም:: ወረቀትዋንም አላስተላለፈም:: ደህንነቱ በመመሪያው መሰረት አምስተኛ ሰው ሆኖ ጫማውን አስጠረገ፤ በመካከሉ በተነገረው መሰረት፣

«ስልክ ቁጥሮቹን በአግባቡ አስተላለፍክ?» ሲል ጠየቀው::

«የምን ስልክ ቁጥር?» አለ ጫማ ጠራጊው፤ ስራውን በተረጋጋ ሁኔታ እያቀላጠፈ::

«ጠዋት እንድታደርስ የተነገረህን»

«ማነው የነገረኝ?»

«ጠዋት ስቴድዮም አልነበርክ?» ብሎ ጠየቀው ደህንነቱ እየተገረመ::

«ከዚህች ንቅንቅም አላልኩ::»

የገዛ ጆሮውን ማመን አቃተው::

ሲስትሮው ሽምጥጥ አድርጐ ሲክድ ከልብ ተደነቀ:: እንዲህም አለው፣

«ስማ አንተ ደቃቃ ፍጥረት! እኔ ፖሊስ ነኝ:: እውነቱን ካልነገርከኝ በቀጥታ ወደ እስር ቤት ትወሰዳለህ:: ትሰማኛለህ!? ጠዋት ስቴድዮም አካባቢ ጫማ ከጠረግህለት ሰው የተቀበልከውን የስልክ ቁጥር ለማን ነው ያስተላለፍከው?»

የሲስትሮው እጆች ሲንቀጠቀጡ ተመለከተ:: ቡሩሹ ከእጁ ላይ ወደቀበት:: በፍርሀት ቀና አለ:: አይን ለአይን ተጋጩ፣





«በል እውነቱን ተናገር:: ቁጥሩን ለማን ሰጠህ?»

«መንገድ ላይ ነው የተቀበሉኝ::»

«አትዋሽ!» ሲል አፈጠጠበት «... ከስቴድዮም ጀምሮ ተከታትዬሀለሁ:: መድን ድርጅት ህንፃ አጠገብ ስልክ ቁጥሮቹን ወረቀት ላይ ስታሰፍር ጭምር ተመልክቼሀለሁ:: ከዚያ ወዲያ እዚህ እስክትደርስ ድረስ ማንም አላነጋገረህም:: እውነቱን ካላወጣህ ወዮልህ! አሁኑኑ ከርቸሌ ትገባለህ!?»

«በእጃቸው አይደለም የተቀበሉኝ?»

«ታዲያ በምንድነው?»

«ፎቶ ቤቱ በር ላይ ስደርስ ወረቀትዋን መንገዱ ላይ ጥዬ ነው የሄድኩት::»

ደህንነቱ ውሀ ሆነ:: አሞሌ አምልጦአል! ከዚያ ወዲያ ለሲስትሮው ያቀረበለት ጥያቄ ለሪፖርቱ የሚያገለግለውን መረጃ ለማግኘት ብቻ ነበር ...

«የትኛው ፎቶ ቤት?» ሲል ጠየቀው::

«ቡናና ሻይ ህንፃ ስር ያለው::»

«ወረቀቱን ወደ ፎቶ ቤቱ ነው የጣልከው?»

«አይደለም:: እጄን ብቻ ነው የዘረጋሁት:: ወረቀትዋ ወደቀች:: እንደዚያ አድርግ ነው የተባልኩት::»

«ማነው ይሄን ያለህ?»

«የላከኝ ራሰበራ ሰው::»

«ሰውየው ወረቀትዋን አንስቶአታል?»

«እኔንጃ!»

«ለምን ዞረህ አላየህም?»

«ዞረህ እንዳታይ ተብያለሁ:: ወረቀትዋን ጥለህ መንገድህን ቀጥል ነው የተባልኩት::»

«አሁን ከኔ ጋር ፖሊስ ጣቢያ እወስድህና ይህንኑ ትናገራለህ:: አትታሰርም:: አትፍራ:: እሺ?»

«እሺ!?» አለ ሲስትሮው ፈራ ተባ እያለ::

ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ የሚያጠፋው የስራ ጊዜ አላሳሰበውም:: በማለዳዋ አጭርና ቀላል ስራ መቶ ብር አግኝቶበታል:: ደስታው ገና ከውስጡ አልጠፋም ...

- 4 -

ስልኩ ጮኸ::

ሀወኒ ልብዋን እፍን አደረጋት:: ደግሞ ጮኸ:: አቃሰተች:: 'ውዱ አኖሌ' ብላ መጮህ አሰኛት:: ተጠግታ እጅዋ እየተንቀጠቀጠ አነሳችው::

«ሀወኒ!» የሚል ጐርናና ድምፅ መጣላት::

«ነኝ» አለች:: «... እንደምነህ ሀየሉም::»

«አልደወለም?»

«እስካሁን አልደወለም::»

«ተዘግተሽ ዋልሽ ቀኑን ሙሉ?»

«ስልኩ ላይ ተተክዬ ዋልኩ» ብላ ፈገግ አለች::

«ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ብቅ እላለሁ:: ራት በልተሻል እንዴ?»

«ገና ነኝ::»

«እንግዲያው አብረን እንበላለን::»

«ደግ::»

ስልኩን አኑራ ወደ ወጥ ቤት ገብታ ሻይ ጣደች:: እስኪፈላ ድረስ መፅሀፍ ቢጤ ለመገላለጥ አስባ ወደ መፃህፍት መደርደሪያዋ ስታመራ የደጅ መጥሪያ ድምፅ ሰማች:: የአክሱማይት ልጅ ፀሀዬ ሊሆን እንደሚችል ገመተች:: ፀሐዬ የስድስት አመት ህፃን ነው:: ጐረቤት በመሆናቸው ዘወትር ማምሻውን ቴሌቪዥን ሊያይ ይመጣል::

በሩን ከፈተችው::

ይሁን እንጂ ጨለም ባለው በረንዳ ላይ ፀሀዬ አልነበረም የጠበቃት:: አክሱማይት ነበረች:: አክሱማይት የማህፈረ ሚስት::

«ግቢ አክሱም! እንደምን አመሸሽ?» አለቻት::

«ሰላም!» ብላ ወደ ውስጥ ዘለቀች::





«አልመጣም እንዴ ፀሀዬ?»

«ዛሬ አልመጣም?» አለቻት ገፅታዋን ትክ ብላ እያጤነች::

«ታች ወርዶ ከልጆች ጋር እየተጫወተ ይሆናላ!» ብላ ልትመለስ ስትቃጣ፣

«ቆይ ሻይ ጠጥተሽ ትሄጃለሽ:: እየፈላ ነው» ብላ እጅዋን ይዛ ከሳሎን አስቀመጠቻት::

አክሱማይት አልባሌ ጃኬት ለብሳለች:: ገፅታዋ ምጥጥ ብሎአል:: ጠጉርዋን ወደሁዋላ ቀጥፍራዋለች:: ፎቶግራፍ የማንሳቱ ስራ ባብዛኛው ስለተጠናቀቀ በመከላከያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ዶኪመንቴሽን ክፍል በጊዜያዊ ስራ ላይ ተመድባ በማገልገል ላይ ናት::

«ምን ሆንሻል አክሱም?» ስትል ጠየቀቻት ሀወኒ፣ ፊትዋን ትክ ብላ እያስተዋለቻት:: ስታነባ እንደቆየች ጠረጠረች:: አይኖችዋ በርበሬ መስለዋል::

«ምንም አልሆንኩ» አለች::

መዋሸትዋ ግን ታወቀባት:: የሚያንሰቀስቅ ስሜት ከወደ ሆድዋ ፈነቀላት:: ፊትዋን በሁለት እጆችዋ ሸፈን አደረገችና እንባዋን በቀጫጭን ጣቶችዋ አባበሰች::

ሀወኒ ደነገጠች:: ሀወኒ ስለ አክሱማይት ጥቂት ነገሮችን ታውቃለች:: አዎን ... ከምትወደውና ከሚወዳት ባልዋ ጋር ተለያይተዋል:: ከማህፈረ ጋር ተለያይተዋል:: ኢህአዴግ አዲሳባን ከተቆጣጠረ በሁዋላ ሲግባቡ አልቻሉም:: 'ቀድሜህ በተሰዋሁ' የሚሉ ንግግሮችም ተረስተዋል:: ሁኔታዎች ለአክሱማይት በእጅጉ ከብደዋታል:: ከማህፈረ የእብዮ ጋር 'የኔ ጀግና!' የተባባሉባቸው ዘመናት እንደ አክሱም ሀውልት ዘመን ርቀው ይታዩዋት ጀምረዋል::

ሀወኒና አክሱማይት ከተዋሩበቱ ወዲህ በተለይ ተቀራርበዋል:: ከሶስት ወራት በፊት ከማህፈረ ጋር እንደተለያዩ ስትነግራት አክሱማይት ጉዳዩን ቀለል አድርጋ ነበር ያወጋቻት:: 'መብቱ ነው' ነበር ያለቻት ለሀወኒ:: ከዚያ ወዲህም የማህፈረን ጉዳይ ጨርሶ አንስተው አያውቁም ነበር:: ስለ ትግሉ ነበር የሚያወጉት:: ምን ስለ ትግሉ ብቻ፣ አክሱማይት የሴቶችንም ጥያቄ ደጋግማ ማንሳት ያስደስታታል:: ለነገሩ ስለሴቶች መብቶች አክሱማይት አበጥራ ታውቃለች:: የአክሱማይት የእኩልነት ጥያቄ ግን እፍአዊ አይደለም:: በተግባር ከወንዶች በላይ ስለዋለች የእኩልነቱ ጥያቄ ከማንም በላይ

ይሰማታል:: ይህን መሰል ነገር መልሳ መላልሳ ለሀወኒ ታወጋታለች:: እጅግ አስደናቂ ከሆኑት ትረካዎችዋ ውስጥም የአክሱማይት ያለፈ የጀግንነት ታሪክ ደምቆ ታይቶአታል - ለሀወኒ::

አክሱማይት ባለፈው መራራ የትግል ዘመን ግንባራቸውን ካላጠፉት አንድዋ ነበረች:: ቀሚስዋ አላደናቀፋትም፤ ስህተት አይታ ባለማለፍ አክሱማይት ቀዳሚዋ ነበረች:: መራራው ትግል ቀጥቅጦ የሰራት ታጋይ ናት:: የትግል ፅናት ሲነሳ የአክሱማይት ጉዳይ ግልፅ ነው:: በደካማ ጐን የሚያማት የለም:: ደንብና መመሪያ በማክበር፤ አክሱማይትን የሚስተካከላት ከቶ የለም:: ደንብና መመሪያ አልፎ አልፎ ሊጣስ የሚችል ነገር አይደለም - ለአክሱማይት:: መፈፀም ያለበት ነው:: 'ግትር ናት' የሚሉዋት አሉ:: ያሉትን ቢሉ ግን 'ወይ ፍንክች' ናት:: ደሞ ማድረግ እንጂ መናገር መቼ ይሆንላታል? ጥራዝ ነጠቅ አይደለችም:: ስለሴቶች መብት በመጮህ ብቻ ተወስና ወጥ የምትረግጥ መቼ ሆና? አክሱማይት የምር ናት::

ከማህፈረ ጋር በመለያየትዋ ብዙ አልተጐዳችም ነበር:: 'መብቱ ነው' ነበር ያለችው:: ዛሬ ታዲያ ምን ሆነችና እንባዋ የተከዜን ሙላት መሰለ? አሁን ታዲያ ምነው ተበገረች? የምን እንባ መጣ ደሞ?

ሀወኒ ፍርሀት ፍርሀት አላት:: አስደንጋጭ ስሜት ወረራት? ምክንያቱን ማወቅ አስፈራት:: ይሁን እንጂ፣

«ምን ሆነሻል አክሱም?» አለቻት ደግማ::

አክሱማይት አንድ ነገር ልትናገር አለችና እንባዋ በአይንዋ ጥቅጥቅ ብሎ ሞላ:: ስላቃታትም ፊትዋን በሁለት እጆችዋ ሸፍና ከሆድዋ፣ ከልብዋ በተፈነቀለ የብሶት ስሜት ህቅ እያለች ትንሰቀሰቅ ጀመር::

ሀወኒ ተረበሸች::

የምትይዝ የምትጨብጠው ጠፋት:: ልታፅናናት አልደፈረችም:: ዳሩ አክሱማይት አፅናኝ ትፈልጋለች ብሎ ማን ያስባል?

«ምንም አልሆንኩ! እልህ ይዞኝ ነው:: የማህፈረ ጉዳይ ስሜቴን ጐዳው:: እኔ እንኳዋ አልቅሼ አላውቅም:: አሁንም የፀሀዬ ጉዳይ አንገብግቦኝ እንጂ ነገሩን ራሴ እቁዋቁዋመው ነበር» ብላ ስሜትዋን ለመቆጣጠር ታገለች::





አክሱማይት በተለይ በዳንሻ፣ በኩረም፣ በሽሬ ተጋድሎዎች
የተመሰከረላት ጀግና ናት:: ግራ ጉንጭዋ ላይ ጐራዴ መስለ
የተጋደመው የጠባሳ ምልክት እንደ ከረዩዎች ለጌጥ ያስቆረጠቸው
መች ሆኖ? የካሊበር ጥይት ነው የጉንጭዋን ስጋ ተልትሎ
ጠብሶት ያለፈው:: የምታነክሰውም እንደ ፒያሳ ቀንጃጆች በድመ
የአረማመድ ፋሽን ስትዘንጥ መች ሆኖ? ሽንጥዋ ላይ የተቀረቀረው
ጥይት እስካሁን ባለመውጣቱ እንጂ:: አክሱማይት በርበሬ ወጥ
አትበላም:: ግን እንደ ቦሌ ቀበጦች ምላስዋን ስለሚለበልባት መቼ
ሆኖ? ጨጉዋራዋ በመጐዳቱ እንጂ:: አክሱማይት ከስታለች:: እንደ
አዲስ አበቤዎች 'ቅጥነት ውበት ነው' ብላ አይምሰላችሁ:: የተጐዳ
ሰውነትዋ በቀላሉ መመለስ አቅቶት እንጂ:: አክሱማይት ለችግር
ተንበረከከች ብሎ ማንም አያማትም:: ግን ከብረት ተሰርታ መቼ
ሆኖ? ለትግሉ በነበራት ፅናት፣ ቆራጥነትና ብርታት እንጂ::

አክሱማይት ዘመድ ሞቶባት አይደለም የምታለቅሰው:: ከብዙ
አመታት በፊት ሁለት ወንድሞችዋ አጠገብዋ ሲወድቁ ቀናችባቸው
እንጂ አላለቀሰችም:: አክሱማይት ዘመድ አላት ብሎም ማንም
አያስብም:: የሱዋ ዘመዶች የትግራይ ገበሬዎች ናቸው:: የገበሬዎች
ጉዳይ ለአክሱማይት ርእዮተ አለም ብቻ አይደለም:: ለአክሱማዊት
ገበሬዎች የምር ፍቅር ናቸው::

አሁን ግን ተበግራለች:: እነሆ ከአንጀትዋ የሚገፋት የብሶት
ሲቃ ያንሰቀስቃታል:: አክሱማይትን አዲስ አበባ በገረቻት::
ፈተነቻት:: አሸነፈቻት::

ሀወኒ ቃል እንኩዋ መተንፈስ ስላቃታት በዝምታ ትቆዝም
ጀመር ...

ከደቂቃዎች በሁዋላ ፊትዋን በመሀረም አባበሳ::

«ሀወኒ ሀፍተይ ... ሬቢሼኪ ... ይቅርታ አድርጊልኝ» አለች::

«አክሱም ምን ሆንሽብኝ? በጣም አዝነሻል?»

ሀወኒ ይህን ብላ ሻዩን ለማምጣት ወደ ኩሽና ገባች::
የአክሱማይት ስሜት እንደተጋባባት ሻዩን ይዛ ተመለሰች:: ሻያቸውን
እያጣጣሙ አክሱማይት ብሶትዋን ትተርክላት ቀጠለች፣

«ሀወኒ ሀፍተይ ... የውልሽ ከማህፈረ ጋር ተለያይተናል
አይደለም? ይሄ ያለቀ ጉዳይ ነው:: ዛሬ እንዳሁ ስሜታዊ የሆንኩት
ግን ሊያገባ መሆኑን ስለሰማሁ ነው:: ማህፈረ ማግባት መብቱ
ነው:: ከኔ ተለያቶአል:: ከኔ መለያየት የፈለገው ግን የአዲሳባን

ቆንጃጅት ፈልጐ መሆኑን ዛሬ ነው የተገነዘብኩት:: ይህ አቀሰሰኝ:: ማህፈረ ሰርግ አስፈለገው:: ይህም አሳመመኝ:: ልጁን ረሳው:: በየወሩ ብቻ ገንዘብ ይልካል:: 'አባት ይናፍቀዋል' ብሎ ግን አያስብም:: ልጁ አባቱን በቴሌቪዥርን ያይና 'ማህፈረን ውሰጂ' እያለ ጉሮሮዬን ያንቀኛል:: እሱ ግን ደነዘዘና ልጁን እንኳዋ የመጠየቂያ ጊዜ አጣ:: በርግጥ ለሰርግ እየተዘጋጀ ስለሆነ ጊዜ አይኖረውም:: ሀወኒ ... ሀፍተይ የሴቶች ስብሰባ መደረግ እንደሚኖርበት እየተሰማኝ ነው...»

በር ተንኳኳኩዋ::

አክሱማይት ንግግርዋን አቋረጠች:: ተያዩ:: 'ማነው?' በሚል ስሜት፣

«ሀየሎም ነው» አለቻት ሀወኒ «... ወደ አንድ ግብዣ ለመሄድ ቀጠሮ ነበረን::»

«ምንም አይደል» አለች አክሱማይት ከተቀመጠችበት እየተነሳች፣ «... ነገ እመጣለሁ:: እንጨዋወታለን:: ጉዳዩ ተራ ስለሆነ አታስቢ:: እውነት መስሎኝ እንጂ ማህፈረ በአላማውም ቢሆን ፅኑ አለመሆኑን አስቀድሜ አውቅ ነበር:: ስጋው የሚያሸንፈው ሰው ነበር:: እንኳዋን አዲሳባ በረሀም ይህ ስሜቱ እየተፈታተነው በየግምገማው እንደተወቀጠ ነበር...» እያለቻት ነበር በሩ ዘንድ ደርሰው የከፈቱት::

ሀየሎምና አክሱማይት የሞቀ ሰላምታ ተለዋወጡ:: ሀወኒ ቤት ሲገናኙ ሁለተኛ ጊዜያቸው ነበር:: አክሱማይት ፊትዋን አይቶ ማልቀስዋን እንዳያውቅባት ፈጥና ተለየቻቸው::

... የአክሱማይት መኖሪያ ቤት ሀወኒ ካለችበት ህንፃ ላይ ስለነበር ፈጥና ነበር ቤትዋ የደረሰችው:: ፀሀዬን አላገኘችውም:: 'ህንፃው ላይ ከሚኖሩት ህፃናት ጋር እዚያው ደጅ እየተጫወተ መሆን አለበት' ብላ አሰበችና ወደ በረንዳው ወጥታ ከሰባተኛ ፎቅ ላይ በብርሃን ወደምታብረቀርቀው አዲስ አበባ አይንዋን ሰደደች::

አዲሳባን ጠልታታለች::.

ከሁሉም በላይ ግን ማህፈረን:: ሳታውቀው የበቀል ስሜት ውስጥዋ ማቆጥቆጥ ጀምሮአል:: የልጅዋ ነገር ነው ጥቂት ያሳሰባት:: ዘመድ የላትም:: በጦርነቱ በሙሉ አልቀዋል:: እናትዋም አባትዋም ህይወታቸው ያለፈው በአይሮፕላን ቦምብ





ነው:: ቢሆንም ማህፈረን ልትበቀለው ትፈልጋለች:: እሱን ብቻ ሳይሆን ሚስቶቻቸውን አላግባብ በሚፈቱት ላይ ሁሉ አስደንጋጭ በትር ለማሳረፍ ወሰነች:: እልህ ያንገበግባት ጀምሮአል:: ቀደም ሲል የማታውቀው ስሜት ተፈጥሮባታል:: 'ምነው ተሰውቼ በነበር' ብላ ተመኘች:: እንባዋ አልቆም አላት:: ግራ ገባት:: አታውቀውም ይህን ስሜት:: ግር አላት - እንባ በጉንጮችዋ ሲወርድ:: ባነባች ቁጥር የብሶትና የበቀል ስሜትዋ እያደገ ሲሄድ ተሰማት:: ማህፈረ ከስራው ተባርሮ' እስር ቤት ይገባ ዘንድ ተመኘች:: ግን ሊሆን አይችልም:: የምትወደው ድርጅትዋ ህወሀትም ቢሆን ይህን ለማድረግ ህጉ አይፈቅድለትም::

በረንዳውን ትታ ወደ መፀዳጃ ቤት ሄደች:: ለመጀመሪያ ጊዜ መልክዋን በመስታወት በጥሞና አጤነችው:: የራስዋ ገፅታ ለራስዋ አስደነገጣት:: አይኖችዋ አብጠዋል:: ተጨማደዋል:: የመከራ ታሪክ ይነበባል - ገፅታዋ ላይ:: በካሊበር ጥይት የተሰነጠቀው ጉንጭዋ ቁጡ አስመስሎአታል - ቁጡ ነበር:: ቁጡ ነበር መምሰል ለሚስትነት ውብት አይደለም:: የህመም ስሜት ገፅታዋ ላይ ይነበባል:: ጉንጭዋ ላይ ያለው ምልክት በትግሉ ወቅት ጀግንነትዋን የሚተርክ ነበር:: 'ዛሬ አስተያማነቴን ማንጉራጉር ጀመረ?' ብላ ለራስዋ አንሾካሾከች:: ይህ ስሜት መላ ሰውነትዋን ወባ እንደያዘው ሰው አንቀጠቀጣት:: 'ማህፈረ - ጨካኝ!' ብላ አሰበች 'ጨካኝ - ማህፈረ!'

መተንፈስ አቃታት - በስቃይ::

ከማህፈረ ጋር የተጋቡ ሰሞን 'የኔ ጀግና' እያለ የሚያቆላምጣትን አስታወሰች:: ዛሬ ግን ዘመኑ ተለውጦአል? 'የኔ ቆንጆ' የሚለው ቃል ተገቢ ሆኖአል? 'አክሱማይት ደግሞ ለዚህ ቃል የማትመጥን ሆና ተገኘች?' እያለች ከራስዋ ጋር ትሙዋገት ገባች:: የበቀል ስሜትዋ ባሰ::

በቀል ... በቀል ...

በሰርጉ እለት የሚፈፀም በቀል:: ከተራራ ወደ ተራራ የሚያስተጋባ በቀል:: የገደል ማሚቶዎች እየተቀባበሉ የሚያስተጋቡት ድምፅ ... በማህፈረ የሰርግ እለት የሚፈፀም በቀል ... አክሱማይት ወሰነች::

ውሳኔዋ ውስጣዊ ሙቀት ፈጠረላት:: ፈገግ አለች ...

ፈገግታዋን በመስተዋት አየችው::

ጥርሶችዋ ውብ ናቸው:: በጣም ውብ ናቸው:: የልብዋን ያህል

ግን ንፁህና ውብ አይደሉም።

የማህፊረን የሰርግ ቀን በዚያው ቅፅበት መናፈቅ ጀመረች። የስራ ባልደረባዋ እንደ ነገራት ከሆነ የማህፊረ ሰርግ አራት ወራት ይቀረዋል። አራት ረጃጅም ወራት። ከማህፊረ ጋር በመጨረሻ የተለዋወጡዋቸው ቃላት በአእምሮዋ እየተመላለሱ ይረብሹዋት ጀመር፣

አንድ ቀን አምሽቶ ገብቶ፣

- ትዳራችን መቀጠል አልቻለም። ጭቅጭቅ በዛ። ቤታችን የንትርክ ቤት ሆነ። ቀን ስብሰባ ውዬ ማታ ግምገማ መግባት ታክቶኛል። ስለዚህ እንለያይ - ይላታል።

- አታምሽ፣ አትጠጣ፣ አትማግጥ፣ ፀሀዬን ትምህርቱን ተከታተለው ነው ያልኩህ። ይሄን ለመፈፀም ምን ይቸግርሀል? መፍትሄውስ መለያየት ነው? - ብላ በተራዋ ትጮህበታለች።

- በቃኝ አክሱም - ሲል አምርሮ መለሰላት።

ከወትሮው በተለየ መቆጣቱን ስታይ ረገብ አለች። የመገረም ስሜት ጭምር አደረባት።

- ምን እያልከኝ ነው ማህፊረ?፡- ትላለች ቀዝቀዝ ብላ።

- እንለያይ!፡-

ማመን አቃታት። እንዲህ ያከርራል ብላ አላሰበችም ነበር።

- ከኔ ጋር ያለመኖር መብት አለህ። ሆኖም ... - ብላ ድምፅዋ ዝግት አለ። ተለማምጣ አድራ አታውቅም ነበር። አሁን በራስ የመተማመን ወኔዋ ቀስበቀስ ሲከዳት ተሰማት። እሁን ለፀሀዬ ስል እንዳሻህ እንደምንም ያሰበችውን ተነፈሰች። - ሆኖም ለፀሀዬ ስል እንዳሻህ እንዲኖር አልሻም። እተውሃለሁ። ልጃችን በፈረሰ ቤት ውስጥ እንዲኖር አልሻም። የሚያገዋግዋ ልጅ ነው። በትምህርቱ ጉበዝ ነው። እና ለፀሀዬ ስል ...

- አክስኩማይት - ሲል አቋረጣት - ትዳሩ በቃኝ ነው ያልኩሽ። የማመሸውም ነዝንዝሽ ታክቶኝ ነው። በባዶ ሜዳ ነው እየቀናሽ ያለሽው። ራስሽን ዝቅ አድርገሽ ስላሰብሽ ነው። ውጤቱን ደሞ ታይዋለሽ፡-

አክሱማይት መተንፈስ እንኳዋ አቃታት፣

- ሶስተኛ ሰው ያወያየን ... - አለች በጣር።





- ካልፈለግሁ አስራ አንደኛ ሰውም ካንቺ ጋር እንድኖር አያስገድደኝም፡-

- ከባድ ውሳኔ ነውኮ ማህፊረ -

- አውቃለሁ! አገናለሁም! -

- ለኔ ከባድ ነው ማህፊረ። እድሜዬ ገፍቶአል። ሀመሃምተኛ መሆኔንም ታውቃለህ። አንተንም ለብዙ አመታት ለምጄሀለሁ። አዲስ ኑሮ መመስረት አልችልም። ልታስብልኝ ይገባል፡-

- ሁሉም ነገር አክትሞአል። የውሸት ትዳር ላንቺስ ምን ይጠቅምሻል?፡-

- ጥቂት አስብበት ማህፊረ። እኔም ችግሮች ካሉብኝ ላስተካክል-

- አልችልም አክሱም -

ለደቂቃዎች ያህል በዝምታ ተደመመች።

- ችግሩ ይገባኛል ማህፊረ። ተጨቃጫቂ የሆንኩት ለትዳራችን ብዬ ነበር። ካንተ ተለይቼ ምን እሆናለሁ? ለፀሀዬስ አታዝንለትም? የሚያገዋግዋ ልጅ እየሆነ ነው። ከእናትና ከአባቱ ጋር አብሮ መኖርን አጥብቆ ይፈልጋል። እኛስ ምን ያህል እድሜ ቀረንና? የወጣትነት ጊዜያችንን በትግራይ በረሀ ነው ያሳለፍነው። የተሰዋን ትውልድ ነን። ከእንግዲህ ምን ኑሮ አለን? ማህፊረ እባክህ እንደሚዳው ሁን፡-

- ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር የለውም አክሱም። ፀሐዬ የኛን ጭቅጭቅ እየሰማ ቢያድግ ነው የበለጠ የሚጐዳው። ስለወደፊቱ አታስቢ፤እኔ ባግባቡ አሳድገዋለሁ። እኔና አንቺም በዘምድና እንጠያየቃለን። አንቺም አዲስ ኑሮ ለመጀመር የሚከብድሽ ነገር የለም -

ትእግስትዋ ተሙዋጥጦ አለቀ። ግንባርዋ ላይ ቡዋንቡዋ የሚያህል የደም ስር አፈጠጠ። ደምዋ ጠቆረ። ቁጣዋ አይኖችዋ ላይ ተነበበ። ትክ ብላ በጥላቻ አየችው ...

- መልካም! እንለያያለን። ፀሀዬንም አታገኘውም። ከእናቱ ጋር ይሻለዋል። በተረፈ፡- ብላ ረጅም የቁጣ ትንፋሽ እያስወጣች፣

- አሁኑኑ ከፊቴ ራቅ፡- ስትል አምባረቀች።

ደንግጦ ከተቀመጠበት ተነሳ። ጊዜ አልፈጀም። ከቁጣዋ ገለል አለ። ማህፊረ እንደወጣ ቀረ። አልተመለሰም። ያን ቀን

እክሱማይት ማህፈረ ሲወጣላት ጭንቅላትዋን ጉልበቶችዋ መካከል ቀብራ ስቅስቅ ብላ አልቅሳለች።

በርግጥም ማህፈረ ሳያውቀው በታላቅነት ህልም መዋጥ የጀመረ ሰው ሆኖአል። የተሰውትን ከመርሳቱ የተነሳ ግራ ትከሻውን ስለገነጠለው ጥይት ደጋግሞ መተረክ ያስደስተዋል። ማን አለብኝነት ይታይበታል። 'ኢህአዴግ ውለታዬን ከፍሎ አይጨርሰውም' ብሎ ከልቡ የሚያምን ሰው ሆኖአል። ሰው መናቅ ባህርይው ሆነ። ያለራሱ አዋቂ ሰው ያለ አይመስለውም። 'በሙስና ማንም አያማኝም' ብሎ በአደባባይ ሲፎክር ብዙዎች ሰምተውታል። እዚህ ላይ እውነቱን ነው። ስጦታ ግን ይቀበላል። የቤቱ ሶፋ፣ ማቀዝቀዣ፣ ቴሌቪዥን ሁሉ በስጦታ የተገኘ ነው። የሚያሞግሱት ሁሉ የልብ ወዳጆቹ ይሆኑ ዘንድ ያቀርባቸዋል። ያበረታታቸዋል። አመራር ከመስጠት ይልቅ ቁጣ ያበዛል። ሌሎችን ማማትና ጠልፎ መጣልም ልዩ ስጦታዎቹ ናቸው። መረብ ሰዎችን ጠልፎ ለመጣል ተጨንቆና ተጠቦ ነው የሚዘረጋው። ብዙውን ጊዜ አይሳካለትም። አንዳንዴ ግን ይፈፅመዋል። በራሱ የሚተማመን ሰው አይወድም። በተለይ የሱን ሀሳብ ያጣጣሉበትን 'ፀረ - ኢህአዴግ' የሚል ስያሜ ይሰጣቸዋል። በሄደበት ሁሉ ይህንኑ እያነሳ ያሳጣቸዋል። 'ሀሜት ይወዳል' እንዳይሉትም 'ፊቱም ቢሆን እናገራለሁ' ማለትን ያዘውትራል። ግን ሲያብል ነው። ፊት ለፊት መጋፈጥ ይፈራል - በተለይ ከታጋዮች ጋር። የቆየ ታጋይ ቢሆንም በረሃ ቀመስ ታጋዮችን ይፈራቸዋል። ጭብጥብጥ አድርገው ከያዙት ልስልስ ነው የሚለው። ደጋፊዎቹን 'ታፍ ሰዎች!' ሲል ሰው በተሰበሰበበት ያደንቃቸዋል። ታዲያ የራሱ ወሬ አቀባዮች አሉት። ከጀርባው ያሙትን ሁሉ በተቻለው መጠን ይመነጥራቸዋል። በዚህ ላይ ሴሰኛ ነው። መልከ ሸጋ ሴቶችን ሲያይ ቀልቡን ነው የሚስተው። ቢሮው የማይመጡ ወጣት ሴቶች የሉም። እንዳያሙት ታዲያ 'እንደልጆቼ ነው የማያቸው' እያለ ይናገራል። ፀሀፊዎቹና የበታች ሰራተኞቹ ያመኑት ይመስላሉ። ዘወር ሲል ግን ' ማህፈረ እንደልጁ የሚያያቸው ወንዶች ለምን የሉም?' ሲሉ ያሽሙዋጥጣሉ። ሌላ ጊዜ ደሞ ' ማህፈረ ሴት ልጅ ይወዳሉ' ሲሉ ይሳሳቃሉ።

እነሆ ማህፈረና እክሱማይት ከተለያዩ ወራት አልፈዋቸዋል። እክሱማይት ማህፈረን ለመርሳት ጥረት ማድረግ ጀምራ፣ እየተሳካላት ነበር። ወዳላሰበችው የበቀል ስሜት የገፋት ግን ዛሬ ማለዳ የስራ ባልደረባዋ ማህፈረ ስለሚያገባት አዲስዋ ሚስቱ በዝርዝር ከነገራት በሁዋላ ነበር። ታጋዩ እንዲህ ሲል ነበር





ያጫወታት፣

- ያን የመሰለ ውበት ታይቶ አይታወቅም። ከንፈርዋን ቀይ ቀለም ትቀባዋለች። ቢነኩዋት ትሰበራለች። አንድ ብረት ቀርቶ የማካሮቭ ጥይት ማንሳት የምትችል አይደለችም። የቆዳዋ ንጣትና ጥራት መስታወት ነው ማለት ይቻላል። ገና ያልተጋቡ ቢሆንም አብረው መኖር ጀምረዋል ነው የሚባለው። ማህፈረ ወደስራ ሲሄድ ሲል ታኩርፋለች አሉ። ሁለት እጆችዋን አንገቱ ላይ ጠምጥማ 'አትሂድብኝ፣ እናፍቅሀለሁ፣ እሞትብሀለሁ!' ትለዋለች አሉ። እንዲህ ስትለው የመጀመሪያ ቀን እውነት መስሎት ግማሽ ቀን ከስራ ቀረ። ከስራ ቀርቶ ሊመያየጣት ሞከረ። እስዋ ሆድዋን በሁለት እጅዋ ጥርቅም አድርጋ ይዛ ከአይኖችዋ እንባ እየወጣ ሳቀች አሉ። ስቃ ... ስቃ ስታበቃ 'ውሸቴን ነው አልሞትብህም!' አለችው። 'ውሸትሽን ለምን እንዲያ ትይኛለሽ?' ብሎ ቢጠይቃት 'ቅብጠት' አለችው። 'ምንድነው ቅብጠት?' ሲላት ትክክለኛውንና ተገቢውን ማብራሪያ መስጠቱን ትታ መሳቅ። ስራዋ ሁሉ መሳቅ ነው አሉ። ሲጨብጡዋትም መሳቅ። በቃ መሳቅ። ይሄ 'ቅብጠት' የሚሉት አደናቃፊ አመለካከት ግን ከግለኝነት ጋር ይመሳሰል ይሆን?፡-

*   *   *

. ከምሽቱ አራት ሰአት ሲል ነበር የተመለሰችው። ጥሩ ምሽት ነበር ያሳለፈችው - ከሀየሎም ጋር። በተለይም በኦህዴድ ዙሪያ ብዙ አወጉ። ጥቃቅን ጉዳዮችን ከድርጅቱ አቋምና የወደፊት እጣ ጋር ማያያዝ እንደማይገባት ሲመክራት ነበር ያመሸው። የእክሱማይትን ጉዳይ ስታነሳለትም ተመሳሳይ ምላሽ ነበር የሰጣት። አዳዲስ መድረኮች ሲፈጠሩ አዳዲስ አመለካከቶችና ችግሮች እንደሚወለዱ አብራራላት። እነዚያን እንቅፋቶች በትእግስትና በዘዴ ማለፍ ተገቢ እንደሆነ በርጋታ አጫወታት። በጥሩ ራትና በመልካም ወግ አለፈላት - ምሽቱ።

ስለመሽ ልብሶችዋን ማወላለቅ ጀመረች። በአለም ላይ ትልቁ የሚያደክማት ስራ ልብስ አውልቆ አጣጥፎ ማስቀመጥ ነው። ጂንስ ሱሪዋን ሳሎን ተወችው። ሸሚዝዋን መኝታ ቤት። ብርድ ካልሆነ የሌሊት ልብስ አትለብስም። አወላልቃ ... የውስጥ ሱሪና የጡት መያዣያዋ ሲቀራት 'የእንቅልፍ ኪኒን' ይሆናት ዘንድ አንድ መፅሀፍ አንጠልጥላ ወደ አልጋዋ ስትበር - ስልኩ ጮኸ።

«ከንፈ ወይስ አኖሌ?» ስትል ለራስዋ ጥያቄ አቀረበች።

አኖሌ ይሆን ዘንድ ተመኘች?

«ሀለው?»

«ሀወኒን ነበር እባክዎ?»

«ነኝ ማን ልበል?» አለች ልብዋ እየነጠረ።

«ይጠብቁ» አላት ደዋዩ።

አንድ ደቂቃ! ረጅም ደቂቃ!

ልብዋ ሊቆም ደረሰ ...

«እኔ አላምንም ሀወኒ የኔ ፍቅር!» የሚለው የአኖሌ የስቃይና የጭንቀት፣ የፍቅርና የናፍቆት ድምፅ በጆሮዋ ዘልቆ መላው ሰውነትዋን እንደ ኤሌክትሪክ ሃይል አነዘረው።

«አኖሌ! ....» ማለት ብቻ ነበር የቻለችው።

እንባዋ እየወረደ፣ መናገርና መተንፈስ አቃታት ...

* * *

ስልኩ ደጋግሞ ሲጮህ ከእንቅልፉ ባንኖ ሄዶ አነሳውና «ሀለው» አለ - ከንፈ ገብረመድህን።

ከዚያም በቀጭኑ ሽቦ ለመጣለት ድምፅ እንዲህ የሚል ምላሽ ይሰጥ ጀመር ...

«እንደምነህ ሀየሉም ... አይ ... አልደወለችልኝም ... አሀ ላንተ ደወለችልህ? ... ግን ዘገየች ... እኛ ጭራውን ይዘነዋል ... በዚህ ሰአት ሂልተን ሆቴል ሰላማዊ እንቅልፍ ላይ ነው ... እዚያ ክፍል የተከራየነው እኛ ነን ... እ ... አዎ አዎን ... ጉት ያለውን ክፍል የተከራየነው እኛ ነን ... ነገ ላጫውትህ ... ለጊዜው እንዳልኩህ ልንይዘው አልፈለግንም ... ነገ ላጫውትህ ... አዎን ከነገ ማለዳ ጀምሮ የኛ ሰዎች ጉዞውን ጥሩ አድርገው ያጅቡታል ... ለመሆኑ የት ነህ? ... በል ደህና እደር ...»





# ረጅም ጉዞ!

# ማን ማንን ይዞ?

## ምእራፍ አስራ ሁለት

- 1 -

ከጎተራ ወደ ቦሌ በሚያመራው የተፈረካከሰ የአስፋልት ጎዳና ላይ «ዶቭ ሀውስ ባር» የሚል ፅሁፍ ይታያል። አዲስ አበባ ስትጨልም ዶቭ ሀውስ ትንቦገቦጋለች። ዘፈኑ ወሲብ ነው። መጠጡ ወሲብ ነው። ዳንሱ ወሲብ ነው። ሁሉም ነገር ቃጠሎ ነው... ወንድ አበሾችና ነጮች እንዳይገቡ የተከለከለ ይመስል ቤቱ ዘወትር በአፍሪካውያን ዲፕሎማቶች እንደተጠቀጠቀ ነው።

እነሆ ዶቭ ሀውስ ...

አንድ የኢህአዴግ ማእከላዊ ኮሚቴ አባልና አንዲት ሙሉ ኮረዳ በቀለጠው መድረክ ተሰይመዋል::

አዳራሽዋ በመሳሳም ነድዳለች:: የአዲሳባ ቆንጆዎች ስስ ከንፈሮች እንደወልቂጡ ሚጥሚጣ ይፋጃሉ:: ቀጫጭኖቹ፣ ከንፈሮች እንደወልቂጡ ማጥሚጣ ይፋጃሉ:: ቀጫጭኖቹ፣ ቀያዮቹ፣ ጠይይሞቹ፣ ወሲባዊ ስሜትን የሚያንር ጫት መርጠው የቃሙት፣ መጠጥ እንደውሃ የጠማቸው፣ ፍትወት ያንበገባቸው፣ ትእግስት ያሳጣቸው፣ ቅዕል ስሜቸው «ጫጩት» የሆነ ትናንስ ኮረዶች ነፍሳቸውን ስተው ሰበር ሰካ ይላሉ:: አግረመንገዳቸውን ሲያልፉ ነካ ያደረጋቸውን አፍሪካዊ ከንፈር መጥምጠውት ያልፉሉ:: ልቡ እስኪቀልጥ... አይኑ እስኪደክም በእነዚያ ለስላሳና ቀጫጭን ጣቶቻቸው በስስ ቲሸርቱ ስር ደረቱን ዳስሰው ነፍሱን ያቀልጥዋታል::

«ምን ልታዘዝ ጌታዬ?»

ባለስልጣኑ መልስ ከመስጠቱ በፊት ውቢትዋ ኮረዳ ቀድማ አዘዘች::

«ለሱ ዋይት ሆርስ ደብል... ለኔ አሌክዛንደርያ ደብል!»

ይህንኑ ነው ዘወትር የምትጠጣው:: የሱንም አውቀለታለች::

«ተጫወት እንጂ... ፈዘዝክ?» አለችው::

አይኖቹ ግን ጠጉሩዋን ከጆሮ ግንድዋ በላይ ወይፈን የነጨው አክርማ አስመስላ የተቆረጠች አንዲት ጠይም ኮረዳ ላይ አርፈው ነበር::

«...ተጫወች አንቺም!» አለ እየተደናገረው::

«ትፈልጋታለህ?» አለችው::

«ማንን?»

«ልጅትዋን?» አለች ፈገግ ብላ::

«አብደሻል?»

«ምነው?»

«የበጉር አቆራረጥዋ ገርሞኝ ነው ያየሁዋት እንጂ ሌላ እኮ አይደለም»

«መገረም ምን ማለት ነው?» አለች::

ጥያቄዋ ስላላማረው «ኖኖ... ዘኒ... እንደዚያ ማሰብ የለብሽም:: አላደርገውም! አላስበውም...»





«ቀንቺ እኮ አይደለም» ሰለ፤ ከፈለግሃት...አንድ ጊዜ አውጣት! እኔ ላመቻችልህ:: ይህ ብልግና አይደለም:: እኔም ደስ ያለኝን ሰው ላወጣ እችላለሁ»

በጥፊ የተመታ ያህል ዞር አያት:: ቁና ተነፈሰ::

«አትገምትም ደዜን?» ብላ ሳቀች::

«እንጃ... እንዲህ ያለ ነገር አስቤ አላውቅም...»

«አለበለዚያማ መኖር ይሰለቻል!»

«እውነት!?» አለ::

ሆኖም ምን ማሰብ እንዳለበት አያውቅም ነበር:: አስተናጋጁ መጠጡን አቅርቦላቸው ተመለሰ:: ሙዚቃው ቀልጦአል:: አፍሪካውያን ዲኘሎማቶች ኮረዶችን እየመረጡ ይወዛወዛሉ:: ይተሻሻሉ:: ሱሪያቸው አብጦ ሊፈነዳ ደርሶአል:: ቁና ቁና እየተነፈሱ ይተሻሻሉ:: ተሰቃይተዋል:: ስቃዩን አልቻሉትም::

«Relax ሰል:: እኔ በጣም እመችሀለሁ»

ውስጡ በመደናገር ይታመስ ጀመር:: አዳዲስ ቃላት:: አዳዲስ የመደሰቻ ባህር:: ወይም በኢህአዴግ - አግዴድ ቋንቋ... «አዲስ መድረክ»... እያለ ማሰብ ጀመረ...

«መመቸት ምን ማለት ነው ዘኒ?»

ሳቀችና «ምን ልበልህ? ለምሳሌ አግባኝ ብዬ አላስቸግርህም... አልቀናም ... ሰለውጥ በየመካከሉ በጣም ቆንጆ ሴቶችን አስተዋውቅሀለሁ ... እኔን ደግሞ በፈለግኸኝ ጊዜ ሁሉ ታገኘኛለህ...»

በመደነቅ ያያት ጀመር::

«ይህ ምን አይነት ግንኙነት ነው ዘኒ?»

«ምኑ?»

«የኔና ያንቺ ግንኙነት ምን ሊባል ነው?»

እንደገና ሳቀች፣

«በወደቀው ስርአት አጠራር ውሽምና ... በዘመኑ ደግሞ Share holders ...» ብላ ክልብዋ ስትስቅ እምባዋ ከአይንዋ እየተፈሰመቀ ይወጣ ነበር የናዝሬትዋ ዜኒት::

የሰለሞን ዲሳሳ ልብ በፍጥነት ይመታ ይዞአል ...

አይኑ ደግሞ ልጅትዋ ላይ ቀርቶአል:: ያያታል:: በአይኑ ሊውጣት ምንም አልቀረው:: ጠይም ናት:: ቀጭን::: በዜኒት

የአነጋገር ዘይቤ ከንፈርዋ የሚመች:: ስትስቅ ጉንጭዋ የሚቀላ:: የወሲብ ብልቃጥ ...

«ፈልገሃታል?»

«አንቺ ልጅ አብደሻል!?»

«ታድያ ለኢህአዴግ አባልነት ልትመለምላት አሰብክ እንዴ?»

«አንቺ ልጅ ጤነኛ ነሽ?»

«አጠፋሁ? ግልፅ ስለሆንኩ? ስለቀርብኩህ? ስለወደድኩህ?»

«አሄሄ... አሳገባህም እያልሽ? ይሄኔ ሌላ አስበሻል!»

«ሶል እመነኝ ... እኔ አላገባም:: እንዲያውም ሌላ ጉዋደኛ ጭምር አልይዝም::: አንተ በሳምንት አንዴ አትጥፋ ብቻ!»

«በየቀኑ ብመጣስ?»

«ደስታውን አልችለውም»

«ታዲያ ለምን ትገፋፊኛለሽ?»

«ለሰውጥ ነዋ! ... ነፃ ከሆንክ የበለጠ እንደምትወደኝ ደሞ አውቃለሁ:: ልጥራት?»

«አብደሻል!» ብሎ ቢቆጣትም ድምፁ ግን የሰለለና የሞተ ነበር::

«እሷም አይንዋን ካንተ አልነቀለችም! ይህ ሴሰኛ አይንህ ነው የሴቶችን ልብ የሚበረግደው... ትምጣና ትጠጣ... ትጫወት ... ምንቸገረህ? ስንሄድ ተሰናብተናት እንሄዳለን::»

«ምንድናት ግን?»

«እንጃ! ብዙ ናቸው:: ሲዝናኑ የመጡ ነው የሚሆኑት:: ዱርዬ ግን አትመስልም::»

«ከፈለግሽ ጥሪያት... ግድ የለኝም» አለ::

ዜኒት ብድግ ብላ ወደበሩ አመራች:: ልትወጣ ስትልም ለልጅትዋ በአንገትዋ ምልክት ሰጠቻት::

ዜኒት በረንዳው ላይ ወዲያ ወዲህ እያለች ትንጐራደድ





ጀመር:: ከሶስት ደቂቃ በሁዋላ ልጅቱ ብቅ አለች::

«ጤና ይስጥልኝ... ዜኒት እባላለሁ»

«ኤሚ...» አለች ፈጠን ብላ::

«ኢሚ? ምን ማለት ነው? ያልተለመደ ስም» አለች ዜኒት::

«እመቤት ነው ስሜ:: ስሙ ስለሚያስጠላ ብዙ ሰዎች ኢሚ ነው የሚሉኝ»

«ወንድሜ ወዶሽ ሲሞት ነው:: ዝም ብለሽ አብረሽን ትጫወቺያለሽ?»

«ስንት ይሰጠኛል?»

ዜኒት እጢዋ ዱብ አለ:: አመነታች::

«እሱ እንኩዋ እንደዚያ ያለ ነገር አያውቅም»

«ታዲያ በነፃ?» አለች ኢሚ አይኖችዋ ፈጠው፣ «... ልሰጥ የመጣሁ መሰልኩሽ እንዴ?»

ዜኒት አቅማማች?

«ገንዘቡን እኔ እሰጥሻለሁ:: እሱ ግን ማወቅ የለበትም» ስትል አስጠነቀቀቻት::

«መቶ ሀምሳ ትሰጪኛለሽ?»

«አይበዛም?»

«ሁሉ የምንወጣበት ዋጋ ነው::»

«ደህና! ምን መሰለሽ ኢሚ... ይህን መሰል ስራ እንደምትሰሪ ጨርሶ ማወቅ የለበትም:: የኮሜርስ ኮሌጅ ተማሪ መሆንሽን ንገሪው:: ከጉዋደኞችሽ ጋር እንደመጣሽ ... መኪና እንደያዛችሁ ... አልፎ አልፎ ደግሞ አይኑ በጣም እንደሚያምር ንገሪው ... ቢበዛ ሶስት ጊዜ ንገሪው:: እሱ አብረን እንሂድ ካለ ብቻ ነው ከኛ ጋር የምትመጪው:: ያውም ጥቂት ትግደረደሪና እኔ አግባባሻለሁ:: በተረፈ ስጠራሽ ነው የምትመጪው»

«ካልፈለገስ? ጊዜዬ ሊቃጠል?»

ዜኒት ከጂንስ ሱሪ ኪስዋ ሃምሳ ብር አውጥታ አስጨበጠቻት::

«ፍላጐቱ ካልሆነ... ይህ ቲፕ ነው»

«አብሽር!» ብላ ፈገግ አለች «ትመቺያለሽ እሺ?»

ወደየቦታቸው ተመለሱ።

«ቆየሽ» አላት ሰለሞን ዲሳሳ።

«ወሬዋ ጣፈጠኝና ሳላስበው ዘገየሁ።»

«ምንድናት ልጅቱ?» አለ ቸኩሎ።

«የኮሜርስ ኮሌጅ ተማሪ ናት። ቤተሰቦችዋ ቂልቢ ገብርኤል ሲሄዱ አጋጣሚውን በመጠቀም ሊዝናኑ መጥተው ነው ...» ብላ አይንዋን ወደ ኤሚ ወርወር አደረገች። ፔፕሲዋን እየተጎነጨች ከጉዋደኞችዋ ጋር የጠፈ ወግ ይዛለች። ይህንኑ እያወራችላቸው መሆን አለበት።

«አልጠራሻትም?»

«አልጠራሁዋትም። የማውቅሽ መሰለኝ ብዬ ቀበጣጥሬ ተመለስኩ። ብጠራት ግን ትመጣለች። ግን ትንሽ ትቆይ። ደሞ የፈለግሁት መስሎአት እንዳትንጠባረር ...» ካለች ሁዋላ «... ስራ ታዲያ እንዴት ነው» ስትል ጠየቀችው።

«ደግ ነው» የሚል ምላሽ ሰጣት።

አይኖቹን ግን ከኤሚ አልነቀለም።

ከግማሽ ሰአት በሁዋላ ዶብ ሀውስ ባርን ለቀው ወደ ሎምብሬል ገሰገሱ። ኤሚን ይዘዋታል። ኤሚ ትችልበታለች። የሰለሞንን መስገብገብ አባሰችበት።

«ደረትህ ላይ ጠጉር አለ?» ብላ ፊት ለፊት ስትጠይቀው ዜኒት የምትገባበት ቀዳዳ ጠፍቶአት ነበር።

ሰለሞን ግን ጥያቄዋን እንደጋጠወጥነት አላየውም። ይልቁን ከልቡ ስቆ ግልፅነትዋን ያደንቅ ጀመር።

አያይዞም፣ «ይህን መሰል ግልፅነት የኢትዮጵያ ባህል መሆን አለበት!» የሚል ማሳሰቢያ ሰጠ።

ዜኒት እፎይ አለች።

እየቆየች ይገርማት ጀመር። የገረማት ሰለሞን የኤሚን ጋጠወጥነት ከኢትዮጵያ ባህል ጋር ለማያያዝ ጥረት ማድረጉ ነበር። ደካማ ጎኑን በትክክል ማግኘትዋን አመነች። ሰለሞን ወሲብ ላይ ይሸነፋል። እዚያ አካባቢ ማንኛውም ጉድፍ አይታየውም። ማንኛውም ስህተት ይሸፈናል። ይህ ግን አንድ





ሊዳጋ እንዳለው ታስባት። ለብቻዋ ከያዘችው ሌላ ሲለምድ ሊተዋት ይችላል። በሱዋው በኩል የተለያዩ «ጫጩቶችን» ካገኘ ግን ወደ ሌሎች ቀነጃጅት እያማተረ አይዘነጋትም። ይልቁን ምስጢረኛው፣ ጉዳይ ፈፃሚው፣ የልብ አውቃ ትሆናለች። ለበርካታ ሚስጢሮቹ ተሸሽገው መቅረት ሲል ደግሞ የማይፈፅምላት ጉዳዮች አይኖርም። ሚሊየኔር የመሆን ህልምዋ ያንጊዜ እውን ይሆናል!

ከኦሎምፒያ ወደ ተቻለ ጋራዥ በሚያደርሰው መንገድ ዳር ሎምብሬል ባር ይገኛል። ዶብ ሀውስ ያልሄዱ አፍሪካውያን ዲፕሎማቶች በጥንታዊትዋ ኮንጎ ውብ ጣዕመ ዜማ ከሎምብሬል አብረቅራቂ ወለል ላይ ይወዛወዛሉ።

ደጃፉ ላይ ከደመቀው የቡና ስነስርአት ዙሪያ የአራዳ ምድር ወጣት ደላሎች ከአፍሪቃውያን ዲፕሎማቶች ላይ አይናቸውን ያነከራትታሉ። የምሽቱ ትልቁ ጉዳይ የቀጭን ኩረዳ ጥያቄ ነው። እጥረት አለ። ዲፕሎማቶቹ ወፋፍራሞቹን ሴቶች ለአይናቸውም አይፈልጉዋቸውም። ቀጭን ከተገኘች ምንም ቢሆን ይከፍላሉ። ምንም ይሁን! ስለመልክ ቁንጅና ደንታ የላቸውም።

ሎምብሬል ላይ ህይወት በስብሳለች። እርካታ በረሃብ ሞታለች። መጥገብ የለም። እየበሉ ረሀብ - እየጠጡ ጥማት - ፍላጎት ዳርቻ የለውም። የፍላጎት ገደብ ማጣት ሎምብሬል ላይ ተንሰራፍቶአል።

ትልቁ ሰውና ቀጫጭኖቹ ኩረዶች ሎምብሬል ሲደርሱ የደላሎች አይን ሁለቱ ሴቶች ላይ አረፈ። ሲንጥቁ አሰፈሰፉ። እየተጉተተ የገባውን ሀበሻ ንቀውታል። በገንዘብ እንደሚያሸንፉት ከልምድ ያውቃሉ። የሎምብሬል ሴቶች የወርሀ-ጽዋግሜን ሴት ውሾች መሆናቸውን ደላሎቹ አሳምረው ያውቃሉ። ከደላላ የተጣላች ሴት ደግሞ ምን መግቢያ አላት?

ይወያዩ ጀመር።

«ምንድነው ይሄ ሰው፣ ታውቂታላችሁ?»

«አናውቀውም።

«መኪናዋን አይተሃል?»

«አላየሁም...»

ሶስቱ ደላሎች ተሯዋሩጠው ደጅ ወጡ። ወደ ሽማግሌው ዘበኛ ጠጋ ብለው፣

«አባት... አሁን የገቡት ሁለት ሴትና አንድ ወንድ በየትኛዋ መኪና ነው የመጡት?» የሚል ጥያቄ አቀረቡላቸው፡፡

«ያችው!» ብለው በከዘራ አመላከቱዋቸው፡፡

XL-TOYOTA COROLLA፡፡

ታርጋውን አየ፡፡ ከሰስቱ አንደኛው ፊቱን ጨለምደድ አደረገ፡፡

«አወቅኸው?» አለው ተሻኪለው፡፡

«አዎን?»

«ማነው?»

«ኢህአዴግ!»

ጉመን በጤና አይነት በርጋታ ወደግቢው ተመለሰ፡፡

ዛሬ ሎምብሬል ላይ የሚጨት እጥረት አለ፡፡

«ገፊ ቀን!» አሉ በልባቸው፡፡

... ኤሚ ተመችታቸዋለች፡፡ ሰለሞንን ሁለት ጊዜ ካልደነሰን ብላ ብታስጨንቀውም ዜኒት ከለከለችው፡፡

«ለክብርህ ጥሩ አይደለም - ሰው ሊያይህ ይችላል» ስትለው ሰለሞን ከልብ አደነቃት፡፡ 'ዘኒ የልብ አውቃናት' እያለ ያስብ ጀመር ...

ኤሚ «ሽንት ቤት» ብላ ወጣ ስትል ጠብቃ፣

«ወደድካት» ስትል ጠየቀችው፡፡

«ደስ ትላለች» አለ፡፡

«ታወጣታለህ?»

«ይቅርብኝ ዘኒ»

«አልወደድካትም?»

«ኖኖ... ማሰቡ ራሱ ብልግና ነው...»

«ካልመሰለህ ተወው...» አለች፡፡

«ባህርዩን በማጥናት ላይነሽ ልበል?» አላት፡፡

«በጭራሽ! ነፃ እንድትሆን ነው» ካለች በሁዋላ «...የሁልህ





ስለሆን እኔ በጣም እወድሃለሁ፡፡ ግን ትዳር የመመስረት ሀሳብ የለኝም፡፡ መቼም ቢሆን አላገባም፡፡ ምክንያቱም ህፃን ልጅ አልወድም፡፡ የልጅ ፍቅር ሳይኖረኝ ባገባና ብወለድ ውጤቱን አስበው፡፡ በተቀረ ግን አንተ የራስህ ምርጫ እንዲኖርህ እፈልጋለሁ፡፡ ማግባት ከፈለግህ ራሴ እድርሀለሁ፡፡ ሆኖም እየሰረቅህ እኔ ዘንድ ትመጣለህ»

ይህን ብላ ከልብዋ ሳቀች፡፡ ሲቃ ስታብቃ ወደ ጆሮው ጠጋ ብላ፣

«ስርቆት ሲጣፍጥ ልነግርህ አልችልም፡፡ ካላገባህ ደግሞ ከኔ ሌላ ማንንም አታውጣ ብዬ ራሴን ማታለል አልፈልግም፡፡ ከሆነ ላይቀር ደግሞ ለምን እኔ ራሴ አላመቻችልህም? ትንሽ መቅናቱ አይቀርም፡፡ የቅናት ስቃይ ግን ደስ ይለኛል፡፡» ካለች በሁዋላ «...አስደነግጥኩህ?»

ስትል ጠየቀችው፡፡

«እንዲህ የምታስብ ሴት ለምቼ አላውቅም» ብሎ ረጅም አየር አስወጣ፡፡

«ሀሳቡን ካልታተመ መፅሀፍ ላይነው ያገኘሁት» አለችው፡፡

«ምን አይነት መፅሀፍ?»

«ትኩሳት» አለች «...የስብሀት ገብረእግዚአብሔር»

«ለምን አልታተመም ታዲያ?»

«በደርግም በንጉሱም ዘመን 'የህብረተሰብን ስነምግባር ይበክላል' በሚል ምክንያት ታግዶ ውስጥ ለውስጥ ነው የሚነበበው፡፡ እኔንኩዋ እየጣመኝ ያነበብኩት መፅሀፍ ቢኖር 'ትኩሳት' ነው፡፡ ለነገሩ ከትኩሳት ሌላ መፅሀፍ የሚባል ጨርሶ አንብቤ አላውቅም፡፡ እንቅልፌ ይመጣል፡፡ 'ትኩሳት' ግን ...»

«አሁን ታዲያ ሊያሳትሙት ይችሉ የለምንዴ?»

«የወሲብ ነውኮ፡፡»

«ማሳተም መብታቸው ነው፡፡»

ዝም አለች፡፡ ቆየችና ግን፣

«የሆነው ሆነና ስለልጅቱ ምን ወሰንክ?»

«እንጃ!?»

«እንግዲህ ዛሬ መሞሸርህ ነው! ወንድሜ ነው ብዬአታለሁ፡፡

ቅድም በጆርዬ ስታንሾካሹክ አይተሀታል?»

«ምን ነበር የምትልሽ?

«የእውነት ወንድምሽ ነው ወይ?» ብላ ነበር የምትወተውተኝ

«ጠርጥራለች ማለት ነው?»

«አንተ ነህ! በደንብ አላዋራሀትምኮ»

«ጨዋታ ብዙ አትችልም! ውበትዋ ግን በውነቱ ግሩም ነው::»

«እኔስ?»

«አንቺ ሁሉንም ይዘሻል» ብሎ ሳም አደረጋት፣

«ኤሚ የት ነው የሄደችው?» አለ ወዲያው::

«መፀዳጃ ቤት:: ላነጋግራት አብራን እንድትሄድ?»

«ደስ እንዳለሽ» አለ አይንዋን እየሸሸ::

አያይዞም፣ «ግን የት ነው የምንሄደው? ቤቱ መቼም አልሞክራትም:: ጉረቤቶቼ በሙሉ ታጋዮች ናቸው::»

«ያለስራህ አትግባ:: እሱን መሰል ቲግባር በህዝብ ግንኙነት ሀላፊ የማይፈፀም ነው::» ብላ ኤሚን ፍለጋ በሚደንሱት ሰዎች መካከል ሰንጥቃ ሄደች::

በረንዳው ላይ ሶስት ደላሎች ኤሚን ከበዋታል:: ኤሚ ዜኒትን ስታይ ገንጠል ብላ መጣች:: ደላሎቹ አፈገፈጉ::

«ምንድነው?» አለቻት::

«ሶስት እንስጥሽ ነው የሚሉኝ፤ ለአንድ ኡጋንዳዊ::»

«እና ምን አልሻቸው?»

ዜኒት ብልጭ ቢልባትም ንዴትዋን ዋጥ አደገች::

«ከጨመርሽልኝ... እኔ ከጥቁር ጋር ከምወጣ ያገሬ ሰው ይሻለኛል::»

በጥፊ ልታጠናግራት ፈለገች:: ተንገበገበች:: ሉምብሬል መምጣትዋ ፀፀታት:: የሴቶቹ ባህርይ ገረማት፤ አናደዳትም።

«ጊዜያዊ ገንዘብ ለምን ያታልልሻል? ሰው አይበልጥምም?» አለቻት - ግንፍል ግንፍል እያላት::





«ቤት ክራይ ስለደረሰብኝ ነው እንጂ ለገንዘብ ብዬ አይደለም:: ያከራዩቺኝ አንድ አሮጊት ወንቋይ ናት:: አንድ ቀን ካለፈ እቃዬን አያወጣች ወደ ደጅ ትወረውረዋለች:: እኔ ደግሞ አየሽ የሚወስደኝ ካጣሁ ቤቴ ስለምገባ... አሁን ያሰሁበትን አካባቢ እፈልገዋለሁ:: አስፋልት ዳር ስለሆነ ኮንትራት ታክሲዎች አያስቸግሩኝም:: ከአስፋልት ወጣ ካለ እንደምታውቂው ባለታክሲዎቹ ገንዘብሽንም ተቀብለው... እንደገና እዚያው መኪና ውስጥ ተጫውተውብሽ ነው የሚለቁሽ:: ስለዚህ ነው ያመነታሁት:: ወይም ነገ ወንድምሽን ... በቅናሽ ልውጣለት ...»

«ምን መሰለሽ ኤሚ... ወንድሜ በገንዘብ እንደምትሰሪ ሳያውቅ በጣም ስለወደደሽ እንጂ ሌላ ልዩ ነገር ኖሮሽ አይደለም - አንቺን የመረጥነው:: እኔም እሱ ሳያውቅ ነው ካንቺ ጋር የተነጋገርኩት:: እንዲደሰት ብዬ እንጂ አቃጣሪ አይደለሁም:: ካወቀ በጣም ነው የሚጠላኝ:: እኛን ብለሽ መጥተሽ እዚህ ስትቀሪ ምን ይላል? በጣም ያዝንብኛል! እኔ ለገንዘቡ አይደለም:: ሶስት መቶ ቀርቶ ሌላም እሰጥሻለሁ:: ላንቺ ግን ጥሩ አይደለም:: ከገንዘብ ሰውን ማስቀደም ይሻላል:: ከሰው መግባባትና መተዋወቅ ይበልጥብሻል:: ይህን ስራ ትተሽ ሌላ የራስሽን የተከበረ ስራ ስለመጀመር መጣጣር ነው ያለብሽ:: ኤሚ ሙች ይህን ቅርፅና መልክ ይዘሽ... በዚህ እድሜ ብዙ መስራት ትችያለሽ:: ውበት ሀብት ነው:: ግን ረጋፊ ነው:: ከመርገፉ በፊት ልትጠቀሚበት ይገባል:: ለማንኛውም በሁዋላ ብዙ እናወራለን:: ብዙ የማጫውትሽም አለ:: እሺ?»

በእሺታ ራስዋን ነቀነቀች:: ተያይዘው ደናሾቹን እየገፈታተሩ ወደ ባንኮኒው ሲያመሩ፣

«ከዚህ ቀጥሎ የት ነው የምንሄደው?» ስትል ጠየቀቻት::

«ሂልተን::»

«ዋው! አሊጋው ይመቻል፤ እሺ?»

«እውነት?»

«አንቺ ግን እህቱ አትመስይም::»

«ደላላ እመስላለሁ?» አለች እየሳቀች::

«አዎን፣ እሺ?»

[illegible]

«ዋው! ጆሊ ነሽ፤ እሺ?»

«እንዴት»

«ነፃነሽ! ግን እንደሱ ከሆነ ከኛ ጋር እደሪ! ምናለበት? እኔ እንደዚያ ደስ ይለኛል። ሙቅ በጣም ይመቸኛል»

«ምነው?»

«ጆሴ እንሁን ... እንቺም ነይ»

«ሌሚ በፈጠረሽ እንዲህ ያለ ወሬ ተይ! ጨዋ ሆነሽ ብቻ አስደስቸው!»

«በጣም ሀርድ ትበጭቂያለሽ! እሺ?»

ዜኒት የዛሬን ብቻ በሰላም ለመገላገል በልብዋ ፀለየች። ዜኒት የዛሬን ብቻ በሰላም ለመገላገል በልብዋ ፀለየች። ዘባርቀው ደግሞ ለሌላው ደህና! ጠንክረው የማይገለብጥዎትን! ዘባርቀው ደግሞ ለሌላው ደህና! ጠንክረው የማይገለብጥዎትን ቀነጃጅት ትመለምላለች። የታጋይ ሰለሞን ዲሳሳ የማያዋርዱዎትን ቀነጃጅት ትመለምላለች። የታጋይ ሰለሞን ዲሳሳ የወሲብ ጥማትም መፍትሄ ያገኛል። ያንጊዜ እነዚያን ምስጢሮች ለመሸፈን ሲል በርካታ ጉዳዮችዋን ይፈፅምላታል። ህልምዋም እውን ይሆናል። ዜኒት ሚሊዩነር ሚሊዩነር ... ሚሊዩነር ... ሚሊዩነር ...

ህልም ሆኖ የቀየ ምኞት።

- 2 -

ሀወኒ ናዝሬት አዳማራስ መዋኛው ዳር ተቀምጣለች። የለበሰችው ጂንስ ሱሪና ጥቁር የቆዳ ኮት አምሮባታል። ጠጉርዋን እንደነገሩ ቁጥርራዋለች። ያዘዘችውን ሚሪንዳ በግማሽ ሰአት ውስጥ ሩቡን ያህል እንኳዋ አልነካችለትም።

የቀጠሮው ሰአት አልፎአል...

አኖሌ ግን የለም። ሰአትዋን ደጋግማ ማየት ብቻ ሆነ። አኖሌ ተወካዬ ወይም እኔ እንመጣለን ነበር ያላት። ተወካዩም ቢሆን ግን ብቅ አላለም። ሰግቶ ይሆን? ጠርጥሮኝ ይሆን? እያለች ራስዋን በጥያቄ ወጠረችው። ናፈቀችው። የልብ ምትዋ ፍጥነት ጨመረ ...

የሚያሰጋ ነገር ግን አልነበረም - እንደ ሀወኒ እምነት።

ከኮነሬ ጋር ግልፅ ውይይት ነበር ያደርጉት። የቱቀበለችው መመሪያም ውስብስብ አልነበረም። አኖሌ እጁን ለመሸጋገሪያው መንግስት እንዲሰጥ በአስር ቀን ጊዜ ውስጥ እንደምታሳምነው በርግጠኛነት ተናግራ ነበር። በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ





አኖሌ እጁን ካልሰጠ ግን ከአስራ አንደኛው ቀን ጀምሮ ሀወኒ የአኖሌን እንቅስቃሴዎች በሙሉ ለደህንነቱ መስሪያ ቤት ሪፖርት ማድረግ ትጀምራለች። እስከ ሀያ ቀን ሪፖርት ካላደረገች ግን ሀወኒ ከአቅም በላይ የሆነ አደጋ እንደደረሰባት ታምኖ መስሪያ ቤቱ የራሱን እርምጃ እንደሚጠቀም ነበር የተነጋገሩት።

ደግማ ሰአትዋን አየች።

አርባ ደቂቃ አልፎአል። እንደመንጠራራት ብላ ወደሁዋላዋ ዞወር አለች። ጥቁር መነፅርና ሰማያዊ ኮፍያ ያደረገ ጎልማሳ ሰው ተቀምጦ ቢራ ይጠጣል። ልብዋ ፍርስ አለ። ደግማ ዘወር አለች። ሰውየው ተረጋግቶ ተቀምጦ ቢራውን ያለሀሳብ ይስባል።

አኖሌ አይደለም።

«ተወካዩ ይሆን?» ስትል አሰበች። ከአኖሌ ሰዎች አንዱ እንደሚሆን ግን አልተጠራጠረችም። ራሱን ለመደባበቅ ጥረት እንዳደረገ በግልፅ ይታያል። ኮፍያውን ወደአይኑ ደፍቶታል። ደጋግማ ዘወር ብላ ብትመለከተውም ያላየት ለመምሰል ጥረት ሲያደርግ አስተዋለች። በጣም ገረማት።

«አይኖቼ እንኳዋ ወንዶችን ለማስደንገጥ በቂ ነበሩ። ምነው እኚህ ሰው ጨከኑ?» እያለች ከራስዋ ጋር ትቀልድ ጀመር።

ይለይለት ብላ ጠቀሰችው።

በመነፅሩ ውስጥ እንደሚያያት አልተጠራጠረችም። ሆኖም ያላየ መሰለ። ግራገባት። «አይነስውር ይሆናል» ስትል ከልብዋ አሰበች። አሊያ ሌላው ቢቀር የአንገት ሰላምታ እንኳዋ ሊሰጣት ይገባ ነበር። ወይም ደግሞ «ይቅርታ የኔ እመቤት እኔ ባለትዳር ስለሆንኩ አትድከሚ» ሊላት በተገባ። የአኖሌ መልእክተኛ ቢሆን ኖሮ ደግሞ ያነጋግራት ነበር። ከዚህ ሁሉ አንዱንም ባለመፈፀሙ አይነስውር ሲሆን እንደሚችል መቶ በመቶ ወደማመኑ አዘንብላ ተወችው።

እንደገና አስር ደቂቃ አለፈ ...

አኖሌ በገለፀላት መሰረት መጥቶ ያነጋገራት ሰው ግን የለም።

ራሱ አኖሌም ቢሆን ብቅ አላለም። መጨነቅ ጀመረች። ተስፋ አድርጋው ወደነበረው «አይነስውር ሰው» ዘወር አለች።

የለም! ... በቦታው የለም! የገዛ አይንዋን ተጠራጠረች። ከመቀመጫው ሲነሳ ድምፅ አለመስማትዋ አስገረማት። አይንዋን ከወዲያ ወዲህ እያንከራተተች ትፈልገው ጀመር። የትም የለም።

የማቅረቢያ ሳህን ይዞ ቆሞ ለነበረ አንድ ልጅ እግር አስተናጋጅ ምልክት ስትሰጠው ፈጠኖ መጣ፣

«እዚህ ከጀርባዬ ተቀምጦ የነበረው ኰፍያና መነፅር ያደረገ ሰው ወዴት ሄደ?»

«ስልክ ፈልጎት ወደ ሪሴፕሽን ሄዶአል»

ግራ ገባት። ተስተናጋጅ ከሆነ እንዴት ስልክ ሲፈልገው ይችላል? የአስተናጋጁ ምላሽ አልተዋጠላትም፤ ምናልባት 'ቋሚ የሆቴሉ ነዋሪ ይሆን?' ብላ አሰበች፤ ይህንኑ ጠየቀችው፣

«አይደለም!» አላት አስተናጋጁ በኦሮምኛ «...አንቺን እንዲከታተል ኢህአዴግ የመደበው የደህንነት ሰው ነው። አሁን ግን በቀላሉ ስላታስልነው ከግቢ ወጥቶአል። የኛ ሰዎች ስልክ ደውለው ከዚህ ገለል እንዲል አድርገውታል። ድንገጦ እግሩ የቻለለትን ያህል በመሸሽ ላይ ነው። ለማንኛውም ከአስር ደቂቃ በሁዋላ ሆቴሉን ለቀሽ ደጁ ላይ ከምትጠብቅሽ አረንጉዋዴ ማዝዳ ውስጥ ግቢ። እኔ 'የቡርቃ አባዱላ' መልእክተኛ ነኝ።»

አይኖችዋ እንደ እንቁራሪት ፈጠው ነበር፤ አስተናጋጁን የምታጻምጠው።

## - 3 -

«እኖሌና ሀወኒ እንዴት ናቸው?»

ሀየሉም ለክንፈ ያቀረበለት ጥያቄ ነበር።

«አብረው ናቸው። ትናንት እዚህ አዲሳባ ነበሩ። ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለዋውጠው ዋቢሸበሌ አደሩ። ታውቃለህ ሀየሉም... አሳዘኑኝ። ናፍቆቱ ሊወጣላቸው አልቻለም።» ካለ በሁዋላ ከመሳቢያ ውስጥ ፎቶግራፍ አውጥቶ አቀበለው።

ሀየሉም ግራ ተጋባ። በፎቶው ላይ ሌሎች ሰዎችን ነበር የሚያየው። «ራሳቸውን በሰው ሰራሽ አካላት ለውጠው ነው» አለው - ክንፈ።

ሀየሉም ፎቶግራፉን በመደነቅ ሲያይ ቆየ። እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲተያዩ ካሜራው ቀልቦአቸዋል። ፎቶግራፎቹን መለሰለት።

ክንፈ ቀጠለ፣

«...የዘረፈውን ገንዘብ ገና ጥቅም ላይ እንዳላዋለው





አረጋግጠናል። የት እንደቀበረው ግን አልደረስንበትም። የገንዘቡ ብዙ አላሳሰበንም። እኖሌ ምን እንደሚፈልግ ግን በግልፅ ማወቅ እንሻለን? 'ከጀርባው ማን አለ?' የሚለው ጥያቄ ደግሞ ዋነኛውና እንገብጋቢው ነው።»

«እስካሁን ምን ፍንጭ አገኛችሁ?»

«ምንም! ወደ ኦሮሞ ድርጅቶችም ሆነ ወደ ኤምባሲዎች ደጃፍ ዝርም አላለ፡ ምናልባት የሀወኒ ናፍቆት ሲለቀው ወደ አንዱ ድርጅት ወይም ኢምባሲ ይጠጋ ይሆናል። ያን ጊዜ የምስጢሩ ቁዋጠሮ ይፈታል?»

«ከማን ጋር ግንኙነት ያለው ይመስልሀል?»

«ምናልባት አነግ።»

«ከሀገሮችስ?»

«የሁለት ሀገሮችን ስም በግምት ማንሳት ይቻል ይሆናል። ፍንጭ ግን የለኝም።»

«ነፍጠኛውን በመጥላት በስሜት ብቻ የሚፈፅመው ይሆን?»

«አይመስለኝም። ያን ሁሉ የጥንቃቄ ጥበብ ከየት ያመጣዋል? ቀደም ሲል እዚህ አዲስ አበባ ተራ ኤክስፐርት ነው የነበረው»

«አብርሀ ፀሎትን ታምነዋለህ?»

«ብዙ አጠራጣሪ ነገር የለውም። እኛ ነን ያስጠራነው። ሆኖም ውለታ ሊውልለት ይፈልጋል። ይህን በግልፅ ነው የነገረኝ። የግል ስሜቱ ብቻ እንደሆነም አጫውቶኛል። የርሱን ግላዊ ፍላጎት ከስራ ጋር ልንቀላቅል እንደማንችል ነግሬዋለሁ። ዞሮ ዞሮ ስለ አብርሀ ፍላጎትም ቢሆን ርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም።»

«እኖሌና ሀወኒ አሁን የት ናቸው?»

«ሶደሬ እየዋኙ ነበር ከግማሽ ሰአት በፊት። ነገ ግን ወደአባቦኮ ኰረብታ እንደሚሄዱ ለሀወኒ ነግሮአታል»

«የት ነው አባቦኮ ኰረብታ?»

«አርሲ ውስጥ ነው። ካካ ተራራና ቡርቃ አካባቢ።»

ሀየሉም «እኖሌ ስራውን ተወው ማለት ነው?» አለ ፈገግ ብሎ።

«አይመስለኝም። ናፍቆታቸውን እየተወጡ ነው። ታውቃለህ

ግን ... ከልብ ስሜት ይነካሉ:: አፍ ለአፍ ገጥመው ሲንሾካሾኩ ነው የሚውሉት:: እንደሌላው ፍቅረኛ አይሳሳሙም:: ያወራሉ፣ ያወራሉ:: ይከራከራሉ:: አንዳንዴ ይጨቃጨቃሉ:: ደሞ ይሳሳቃሉ:: እጅ ለእጅ ተያይዘው እንደወፍ ይበራሉ»

«ሀወኒ እንደምትለው - እንደአርሚያ ወፎች» ብሎ ፈገግ አለ - ሀየሎም:: ይህን ብሎም «እንዳይያዙ ይጠነቀቃሉ ወይስ አምላክን አምነው ነው አለማቸውን የሚቀጩት?» ሲል ጠየቀው::

«በጣም ይጠነቀቃሉ:: አኖሌ ራሱን የሚለዋውጥበት የተለያዩ የኘላስቲክ አካላት ያሉት ይመስለኛል:: የሚናቅ ባላጋራ አይምስልህ::»

«ከሀወኒ ጋር የሚያወሩት ይታወቃል?»

ክንፈ ድንገት በሳቅ ፈነዳ፣

«ምን አሳቀህ?»

«አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ?»

«ምን?»

«የዋቢሸበሌ አዳራቸውን በሙሉ ቀርፀነዋል:: አንድ ሰአት ያህል ስላንተ ነበር የምታወራለት::»

«ምን እያለች?»

«እያደነቀችህ ትነግረው ነበር:: ሁዋላ ምን አላት መሰለህ?»

«ምን አላት?»

«ኢህአዴግን ነው የምትወጂው ሀየሎምን?»

ሀየሎም ፈገግ አለ፣

«ምን መለሰችለት ታዲያ?»

«ቂል አትሁን? ስትለው፣ ኰረኰማት መሰለኝ ሲጫዋጨዋሁ ነበር::»

«አኖሌ ሳይያዝ እስከመቼ ይቆያል?» አለ ሀየሎም::

«ማወቅ አለብን፤ ከጀርባው ያለውን:: የግድ ማወቅ አለብን::»

«ዘረፋውን ከቀጠለስ?»

«እናደናቅፍባቸዋለን - ያላወቅን መስለን»





«ተከታዮቹ ታወቁ?»

«አራቱን ደርሰንባቸዋል::»

«ተያዙ?»

«አልያዝናቸውም:: ሁለቱን አዚያው ገለበጥናቸው::»

«መገልበጥ ማለት?»

«አኖሌን እንዲሰልሉ መልሰን ቀጠርናቸው:: የደርግ መኮንኖች የነበሩ ናቸው::»

«የቀሩትንስ?»

«እስካሁን አላነጋገርናቸውም:: እየሞከርን ነው::»

«የሀወኒ ጉዳይስ? የግድ አብራው መክረም አለባት?»

«የተላከችበትን ጉዳይ መፈፀም አለባት ብለን እንጠብቃለን:: ሆኖም ከንግዲህ ከአምስት ወይም ከአስር ቀን በላይ አብራው መቆየት የለባትም:: እናስጠራታለን::» ካለበሁዋላ «... ባንተ በኩልስ ምን አዲስ ነገር አለ?» ሲል ጠየቀው::

«ባሌና አርሲ አካባቢዎች ጠመንጃዎች የጫነች አንዲት ላንድሮቨር ተይዛለች:: ንብረቱ የኦነግ መሆኑን አረጋግጠናል:: ዲንሾ የሚባል ቦታ ላይ ነው የተያዙት::»

ክንፈ አይኖቹን ፊታ ጠበብ አደረገ:: ሀየሎም ቀጠለ፣

«ከቡርቃ ዝምታ ጋር የተያያዘ ነገር እያነሱ ገበሬዎችን የሚያነሳሱ ሁለት የኦነግ ካድሬዎችም በቁጥጥር ስር ውለዋል::»

«ስለአኖሌ አንስታችሁላቸው ነበር?»

«እኔም ራሴ አነጋግሬያቸዋለሁ:: አኖሌ እንደላካቸው ያነሳሉ፤ እውነት ላይሆን ግን ይችላል:: ለማንኛውም ነገ ወደ አካባቢው እመለሳለሁ:: በአርሲና በባሌ አካባቢዎች የታመቀ ትኩሳት አለ:: ተቀብሮ የኖረ መቁዋሰል በግልፅ ታያለህ:: ይህን ስሜት በጥንቃቄ ማብረድ ካልተቻለ፤ ሀላፊነት የጐደለው ቅስቀሳ ከተጨመረበት ውጤቱ አስከፊ ነው የሚሆነው::» ካለ በሁዋላ «ለመሆኑ አኖሌ ወደ ቡርቃ ሄዶ ያውቃል?» ሲል ጠየቀው::

«አዎን ይሄዳል» አለ ክንፈ «... ቅድም እንደገለፅኩልህ ወደ አባቦኩ ኰረብታ በየጊዜው እንደሚመላለስ የሚገልፅ መረጃ ደርሶኛል:: ከገለበጥናቸው ሰዎች የተገኘ መረጃ ነው:: ምናልባት የዘረፈውን

ንብረት እዚያ ደብቆት ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ:: ንው እንደሚመስለኝ እኖሌ ሀይል ለመፍጠር በመንቀሳቀስ ላይ ነው ያለው:: በኮረብታው ላይ ጠመንጃ እከማችቶ ሊሆንም ይችላል::»

«ኮረብታው ለምን አይፈተሽም ታዲያ?»

«መቼም ቢሆን ይደርሳል:: አካባቢው በአይነ ቁራኛ እየተጠበቀ ነው:: ከእኖሌ ጀርባ ማን እንዳለ እስክናውቅ ድረስ እኖሌ መበርገግ የለበትም::»

ሀየሎም ሲጋራ እየለኰሰ::

«በርግጥ ከኦነግ ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን?»

«ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል:: ከበስተጀርባ ያለውን ገና አልደረስንበትም»

«ስለኦህዴድ ያለው አመለካከት ይታወቃል?»

«ኦህዴድ ላይ ጥርጣሬ አለው:: 'አመራሩ ከቶ ነፃ ሊሆን አይችልም' ይላት ነበር ለሀወኒ:: ሀወኒ ልታስረዳው ትሞክርና ትልበት ታጣለች:: ሰለሞን ዲሳሳን እያስታወሰች ነው መሰለኝ ደጋግማ 'የሰው እጥረት ነው የኦህዴድ ችግር! አመራሩ ቢጠናከር ...' እያለች ጥቂት ትገፋለች:: እሱ ደሞ 'ህወሀት የኦህዴድ አመራር እንዳይጠናከር ይፈልጋል'' ይላታል:: 'የህወሀት መሪዎች እነሀየሎም ናቸው:: ህዝቡ በድህነት ስለመዋረዱ፣ ፍትህ እጥተ ስለመበደሉ ጠልቆ የሚሰማቸው ሰዎች ናቸው:: በራሳቸው ላይ ደርሶ ያዩትንና ታግለው ያስወገዱትን የግፍ አገዛዝ ሌላው ላይ ሊጭኑ ከቶ አይፈልጉም:: አያስቡትም:: የህወሀት ሰዎች ያን የመሰለ ህሊናም ሆነ አቋም ከቶ ሊኖራቸው አይችልም' እያለች ትወተውተው ነበር:: እኖሌ መልሶ ያዳክማታል:: 'ህወሀት ድብቅ አጀንዳ አጀንዳ አለው' እያለ ሊያሳምናት ጥረት ያደርጋል:: 'ድብቅ አጀንዳ ሊኖራቸው አይችልም' ትላለች ሀወኒ:: 'ሶስት አመት ብቻ ታገሺ! በያንዳንዱ ኦሮሞ ሹም ስር የራሳቸውን ኦሮሞ ያልሆነ ሰው ሰግስገው የህዝቡን ስልጣን፣ ራስን የማስተዳደር መብት ይነጥቁታል' እያለ በእርግጠኝነትና በቁጭት ሲሰብከት ነው ያነጋው ዋቢሸበሌ ሆቴል::»

«ራሱ እኖሌ እንዲያ የሚያምን ይመስልሀል? ወይስ የሀወኒን እምነት ለመለወጥ ሲል የተናገረው ይሆን?»

«የሚያምንበት ነው የሚመስለው:: ሲናገር ስሜታዊ ነበር::»

«እውቆ ያላወቀ ካልመሰለ ድብቅ እጀንዳ እንደሌለን





ልናሳምነው ይገባል» አለ ሀየሎም

ክንፈ መልስ አልሰጠውም:: ሀየሎም ቀጠለ፣

«መሞከር አለብን:: እውነታውን እያወቀ ደጋፊ ለማግኘት ሲል ከሆነ እንዲያ የሚለው ምንም መድከም ሳያስፈልግ ይችላል:: እኔ እንደሚመስለኝ ግን እኖሌ የልቡን ነው የሚናገረው:: በርግጥም ድብቅ አጀንዳ አላቸው ብሎ እምኖአል::»

«እንጃ! » አለ ክንፈ::

«ግዴለህም በተሳሳተ መንገድ ነው የተገነዘበን:: አላወቀንም:: ጨርሶ አያውቀንም::»

አያይዞ ሀየሎም እንዲህ ሲል ጠየቀው፣

«ለመሆኑ የዋቢሸበሌ አዳራቸውን እንዴት መቅረፅ ቻላችሁ?»

«ደርግ ለስለላ ስራ የሰበሰበው መሳሪያ ተአምር ነው» አለ ክንፈ «ግን አልተጠቀሙበትም:: አንድን ሰው በትእግስት ተከታትለው ማንነቱን ከማወቅ ይልቅ እንዳሻቸው አስረው ነበር የሚገድሉት:: አሰራራቸው በዘፈቀደ ማሰርና መግደል ሆኖ ሳለ ይህን ሁሉ የረቀቀ ዘመናዊ መሳሪያ ለምን እንደሰበሰቡ አይገባኝም::»

ለጥቂት ደቃቂ በዝምታ ቆዩ::

ሀየሎም፣ «ሰለሞን ዲሳሳን አነጋገርከው?» ሲል ጠየቀው::

«እኔ አላናገርኩትም:: ለኩምሳ ነግሬው 'መረጃው አለኝ' ብሎኛል:: በራሳቸው የውስጥ ግምገማ አንስተውት ሰለሞን ወሬው ሀሰት መሆኑን እንደገለፀ ነው የነገረኝ::»

«ሀወኒ ርግጠኛ ያልሆነችበትን ነገር አትናገርም» አለ ሀየሎም::

«ሰነገሩ ከሌላ አካባቢም ወሬው ደርሶኛል:: ግን የግድ በራሳቸው መድረክ ነው ማየት የሚገባቸው:: ቀጥታ ጣልቃ ባንገባ ይመረጣል::»

«ጉዳዩን በኢህአዴግ መድረክ ማንሳት ይቻላል::»

«አይቀርም» አለ ክንፈ:: «... ግን አያስቸኩለንም ...»

ሲጋራቸውን እያጤሱ ጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ቆዩ::

«ሀወኒ ሪፖርት ማድረግ ለምን አልጀመረችም?» ሲል ጠየቀ ሀየሎም::

«አልገባኝም፡፡»

«አኖሌ ተጠራጥሮአት ይከታተላት ይሆን?»

«ሊሆን አይችልም፡፡ የዚያ አይነት ሁኔታ መከሰቱን የሚገልፅ ፍንጭ እስካሁን አልደረሰኝም፡፡»

«አብርሀ ፀሎትስ ወደ ኤርትራ መቼ ይመለሳል?»

«የመቆየት ፍላጎት አለው»

«ስራውን አልጨረሰም እንዴ?»

«ጨርሶአል፡፡ በአኖሌ ጉዳይ የሚረዳበት ነገር ካለ ለመተባበር እንደሚፈልግ ገልፆልኛል፡፡ እንዳልኩህ ድብቅ ፍላጎት ሊኖረው ይችላል ...»

ለሰከንዶች ያህል በፀጥታ ቆዩ፡፡

«ስራ ከጨረስክ ለምን አንወጣም?» ብሎ ብድግ አለ ሀየሎም፡፡

ክንፈ ሰአቱን አየ፡፡ ሶስት ተኩል - ከምሽቱ፡፡

## - 4 -

... ከሶስት ወራት በሁዋላ፡፡

የማህፈረ የሰርግ እለት፡፡ ወይም ደግሞ አክሱማይት ብቀላዋን የምትፈፅምበት አስፈሪ እለት...

ሰርጉ የሞቀና የደመቀ አልነበረም፡፡ ቤተዘመድና የስራ ባልደረቦቹ በሙሉ ቢገኙም ታጋዮች ግን ብቅ ሳይሉ መቅረታቸው በግልፅ ታየ፡፡ አልፎ አልፎ አልመጡም እንዳይባሉ ያህል ብቅ ብለው እልም የሚሉ ግን ነበሩ፡፡

ሰለሞንና ዜኒት ከሙሽሮቹ ቀጥለው የክብር እንግዳ ሆነው ቆዩ፡፡ ዜኒት ደስታ ፍንቅልቅል ሲያደርጋት ቢቆይም ሰለሞን ደስተኛ ሳይሆን ቀረ፡፡ በሰርጉ ላይ የታጋዮች በብዛት አለመገኘት ውስጥ ውስጡን ከነከነው፡፡ ምግብ ከተበላ በሁዋላም ዜኒትን «ቀድመሽ ውጪ እከተልሻለሁ» ሲል በጆሮዋ ነገራት፡፡

ተነስታ ወጣች፡፡

ከመኪናዋ እንደደረሰች ስራ አልፈታችም፡፡ ከቦርሳዋ ውስጥ ደብዳቤ አውጥታ ማንበብ ጀመረች፡፡

አምስተርዳም ያለው ፍቅረኛዋ ከበርካታ ልብሶች ጋር አያሌ





ገፅ ደብዳቤ ልኮላታል፡፡ ካቆመችበት ቀጠለች፡፡

- ...ናፍቆትሽ አስልስሎኝ ሲያም ሆኜልሻለሁ፡፡ ባስብበትሽ ቁጥር እምባዬ ይመጣል፡፡ ባገኘሽ ምን እንደማደርግሽ አላውቅም፡፡ ምናልባት ደረቴን ሰብሬ ልቤ አጠገብ ላስቀምጥሽ እሞክር ይሆን? ጭምቅ ዋጥ የማደርግሽም ይመስለኛል፡፡ ለመሆኑ ከድምፅሽ የበለጠ የሚያስደስተኝ ነገር እንደሌለ ታውቂያለሽ? ከዚያ ቀጥሎ ደብዳቤሽ፡፡ ከዚያ ቀጥሎ...፡- ስርዝ ድልዝ ስለነበረው - ከዚያ ቀጥሎ ምኔ ደስ ይለው ይሆን?፡- ብላ የተደለዘውን ለማንበብ ትጣጣር ጀመር፡፡

አልቻለችም፡፡

- የኔ ዜድ በጣም ያስቸገረኝ ነገር ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ከአንቺ ተለይቶ መኖር፡፡ አንቺ እኮ የጥንካሬዬ ምንጭ ነሽ፡፡ ህይወት በሰፊው የሚታየኝ አንቺ አጠገቤ ስትኖሪ ነው፡፡ ይህን ስል ግን ጨርሶ ተስፋዬ ተሙዋጦአል ማለቴ አይደለም፡፡ ሙቼም አላማ አለኝ፡፡ ዜድ ላንቺ ያልተገዛው የአካሌ ክፍል የትኛው ይሆን? ሀሳቤ ሳይቀር ያንቺ ሆኖአል፡፡ ግን ለምንድነው እንዲህ የተቆጣጠርሽኝ? 'ፍቅር ነው' መልሱ፡-

ራሱ ላቀረበው ጥያቄ ራሱ ምላሽ ሲሰጥ ዜኒት ፈገግ አለችና «ጅሎ ተሳስተሀል፡፡ ፍቅር ሳይሆን ወሲብ ነው፡፡ የሚያቃጥል ወሲብ» ብላ ማንበብዋን ቀጠለች - ... እግዜላክ ከሰማይ ወርዶ የተሰቀለው ለሰው ልጆች ባለው ፍቅር አይደል? አንቺኮ በህይወቴ አግኝቻቸው የማላውቃቸውን ነገሮች ሰጥተሽኛል፡፡ ጉዋደኞቼ አልቃሻ ይሉኛል፡፡ እንግዲህ ምን ይደረግ፡፡ የማለቅሰው የያዘ ይዞኝ ነው፡፡ ዜኒት ወደ ጆሮሽ ጠጋ ብዬ 'የኔ ቆንጆ' 'የኔ ወርቅ?' የምልሽን አስታውሺ፡፡ 'እንባዬ አማረኝ' የምልሽንም አስታውሺ፡፡፡-

«ሞዛዛ!» ብላ እየሳቀች ማንበቡዋን ቀጠለች፡፡

- ...ሌላው ያልነገርኩሽ ጥብቅ ጉዳይ መኪብብ ከዚህ የአሜሪካ ቪዛ ስላገኘ በቅርቡ የመላእክት ምድር ወደሆነችው አሜሪካ ሲሄድ ነው፡፡ እድለኛ አይደለም? ሰሞኑን ግን ታሞ ነበር፡፡ ከመኝ ፍራ በላይ ክሎራንፌኒከ እንደ ቆሎ ሲቅም...፡-

የመኪና ጡሩምባ ድምፅ ሰማችና ዘወር አለች፡፡ ሰለሞን ምልክት ሰጣት፡፡ ደብዳቤዋን አጣጥፋ በርሳዋ ውስጥ ጨምራ፤ መኪናዋን አስነስታ ተከተለችው፡፡ የአመስተርዳሙ የቆየ ፍቅረኛዋ የላከላትን አርባ ገፅ ደብዳቤ ማንበብ ከጀመረች አስር ቀን አልፎአታል፡፡ የናፍቆት ጩኸቱ በበረታ ቁጥር እየሰለቻት መጥቶአል፡፡ አሜሪካን የመላእክት ምድር በማለቱ ግን ከልብ ገረማት - ሳቀችው፡፡ ከልብ ሳቀችው፡፡

ለነገሩ ሁሉንም እንደናቀች ነው።

ዜኒት ከሰለሞን ጋር ያላትን ግንኙነት ጭምር መቀረጥ ፈልጋለች። ባጭር ጊዜ ውስጥ የምትፈልገውን አግኝታለች። አሁን ያለእረፍት መስራት ብቻነው የምትፈልገው። ህሊናዋን ሚቆነጥጣት አንዳችም ነገር የለም። ራሱ ሰለሞንም ቢሆን ከአንድ ሚሊዮን ያላነሰ ብር እንዲያገኝ አድርጋለች። በርግጥ እስዋ ሶስት እጥፍ አግኝታበታለች። ሰለሞን ግን ይህን አያውቅም። የሚያውቀው የንግድና የመኖሪያ ቤት እንድታገኝ መተባበሩን ብቻ ነው።

በተለይ ከጥቂት ሳምንታት ወዲህ ግንኙነታቸው እየተበላሸ መጥቶአል። ሰለሞንም ይህንኑ ተገንዝቦ መነጫነጭ አዘውትሮአል።

«ማንኛውንም ነገር በቀላሉ ስለፈፀምኩላት ንቃኛለች» እያለ ይብከነከናል።

በርግጥም ስሜቱን ገዝታ እንደልብ ስታሽከረክረው ነበር የሰነበተችው!

«ቤት ለምን አትፈልግልኝም?» አለችው አንድ ቀን። ፈለገላት። አገኘላት። ዜኒት በሌ መንገድ ላይ የቪላ ተከራይ ሆነች።

«ሶል»

«ዘኒ»

«የንግድ ቤት እፈልጋለሁ። ምክርልኝ።» አለችው ሌላ ቀን። ምከረ። ተሳካለት። ዜኒት ሱፐር ማርኬት ከፈተች - ስቴድየም ዙሪያ። እያደዛ የአጎቴ ልጅ ነው ብላ ባስተዋወቀችው አንድ መልከ ቀና ጎረምሳ በኩል የገንዘብ ህልምዋን እውን አደረገች። በርግጥም የዜኒት የአጎት ልጅ እሳትን በቁሙ የጠጣ ጮሌ ነበር። ቶሎ ተግባባው -ሰለሞንን። እና ብዙ ነገር አስተማረው - በተለይ ገንዘብ እንዴት እንደሚገኝ። ለምን አገልግሎት እንደሚውል ጭምር። ሰለሞን ገንዘብን አወቀ። ጣፈጠው። ሶስቱም ተነከሩበት። በአስራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ሚሊዩነር ሆኑ - በአየር ባየር ንግድ።

ከዚያ ወዲያ ሰለሞን ለዜኒት ሩጫውን የጨረሰ ሰባኪ ቁስ ሆነ። ብልህ አእምሮዋ ሹክ አላት - ሰለሞን እሷን ለማግባት ያለው ፍላጐት እየጨመረ መምጣቱን። ቅብጥብጥ ስሜትዋ





ደግሞ አስጠነቀቀቻት - ይህን ሰው ማግባት እንደማትፈልግ።

በመሆኑም ትርቀው ጀመር።

ሳምንት ያህል ጭልጥ!

አንድ ቀን እንደለመደው ተቆጣት።

«ዘኒ እንዲህ የምትጠፊ ከሆነ በዚያው ቅሪ... እሲያ በየእለቱ ላይሽ እፈልጋለሁ።»

በዚያው ጠፋች። አስራ አምስት ቀን ከረመችና ብቅ አለች - ቢሮው። ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ተንደረደረባት።

«መጠቀሚያ እያደረግሽኝ ነው?»

«ጠንቀቅ በል ሶል!» አለችው።

አይኑ ወህዋ አላማረውም። ፈራት። ቃላትዎችዋ አስደነገጡት። 'ጠንቀቅ በል - ምን ማለት ነው?' እያለ ራሱን ይጠይቅ ጀመር።

ዛሬ ታዲያ ወደ ማህፈረ ሰርግ አብራው ትሄድ ዘንድ ሲጠይቃት ፈጥና ተስማማች። ቁርጡን ልትነግረው ወስና ነበር። እሱም ቁርጥ ያለ ነገር መስማት ፈልጐአል። ከማህፈረ ሰርግ ፈጥኖ መውጣት የፈለገውም ለዚሁ ሲል ጭምር ነበር።

ቀበሪቾ ሬስቶራንት ወደሱ መኪና ተጋብተው እዚያው መኪና ውስጥ ውስኪ አዘው መጣጣት እንደጀመሩ ሰለሞን ርእስ ወሬውን አነሳ፣

«አንድ መልክ ያለው ነገር ብናደርግ ይበጃል ዘኒ» አለ ሲፈራ ሲቸር።

«ምን ሶል?»

«ትዳር መሳይ ነገር።»

«የምርህን ነው?»

«ታዲያ አኩኩሉ እየተጫወትኩ ነው!?»

«አያስቸግረንም?»

«ምኑ?»

«የእድሜያችን ጉዳይ ነዋ! አንተኮ ትልቅ ሰው ነህ...»

«እየሰደብሺኝ ነው! ?» ሲል ተቅበጠበጠ።

«ሶል! ረጋ በል እንጂ!» አለች ቆጣ ብላ::

ረጋ አለ:: ሌላ ምርጫ አልነበረውም::

«በይ እንነጋገር!?»

«ምን?»

«ምን እየሰራን እንደከረምን ነዋ! ስለኔ ምን ታስቢያለሽ!?»

«የእውነት ልንገርህ?»

«ውሸት ልሰማ የምፈልግ ይመስልሻል ታዲያ!?» ሲል በቁጣ ጮኸ::

«አትቆጣና እውነቱን ልንገርህ ... ቁጣ ግን ተው!»

ቁጣ ተው:: ቢቆጣ የትም እንደማይደርስ ገብቶታል::

«መልካም ... እውነቱን ንገሪኝ»

«በፈለግኸው ጊዜ ልታገኘኝ ትችላለህ:: ትዳር ግን አልፈልግም»

«እ!?»

«ቀደም ብዬም ነግሬሀለሁ:: እየቀለድኩ አልነበረም»

«ምን!?»

«እኔ ባል አላገባም:: ምክንያቱም ልጅና ትዳር ለኔ ሲኦል ናቸው::» ውስጥዋ በሳቅ ቢንተከተከትም ፊትዋ ላይ አይነበብም::

«ይሄ እንዴት ይሆናል ዘኒ?»

«ምናለበት? ይከፋሃል?»

መልስ አልሰጣትም:: ስለሀወኒ እያሰበ ነበር:: የሀወኒን ጣፋጭ ምክሮች አስታወሰ:: የሀወኒ ግልፅ ልብ:: የሀወኒ ብስለት:: የሀወኒ የማይጠገቡ ቀልዶች:: ልጅ ያላት ፍቅር:: ሀወኒ የበረሃ ማር ... ሀወኒ ... ሀወኒ ... ሀወኒ ... 'ይህቺ ልጅ መልካም ስነምግባር የላትም:: ተውት!' ብላው ነበር::

'በጉዋደኛሽ መቅናትሽ ተገቢ አይደለም' ሲል ነበር 'ያንጉዋጠጣት 'ሀወኒ አፍቅራኛለች' የሚል ስሜት ጭምር በልቡ አሳድሮ ነበር::

ድንገት ቀልቡ ነጉዶ - ወደሀወኒ::

ካለችበት በእግር በፈረስ ፈልጉ ሊያገኛት ተመኘ:: እግርዋ





ላይ ወድቆ መሰመን ተመኘ - ይቅርታን መሰመን::

«ምን እያሰብክ ነው?» አለችው ዜኒት::

«ምንም»

«ንገረኝ ሶል?»

«የምነግርሽ ምንም ነገር የለም::»

«ተቀይመሃል!?»

«በማን?»

«በኔ ነዋ»

«ለምን?»

«ውሰቃ ውስህልኛል፤ ሆኖም ተገቢ ምላሽ ከኔ አጥተሀል?»

«እረ በሞራሽ»

በጣም ሳቀ - ሰለሞን ድምፅ አውጥቶ ሳቀ:: የልቡን ነው የሳቀው:: ሲስቅ ንዴቱ እየበረደለት ሄደ:: ንዴቱ ሲጠፋ ቁሻሻ የሀፍረት ዶንያ አልብሶት የሄደ ያህል ተሰማው:: በራሱ ማዘን ጀመረ::

ለደቂቃዎች በዝምታ ሲዋጥ፣

«ሶል!» ስትል ጮኸች - ዜኒት:: 'ዘኒ' የሚል ምላሽ ግን አጣች::

«ዘኒ» ስላላላት አልተከፋችም:: እንዲቀርጥለት ትፈልጋለች:: ሰበብ መሆን አትሻም:: ሁሉም ነገር ከሱ ቢመጣ ትመርጣለች::

«የዛሬ ማታ ፕሮግራማችን ምን ይሁን?» የሚል ጥያቄ አቀረበችለት::

«ኮንኮርድ እንሂድ:: ራሴን መርሳት እፈልጋለሁ» አለ ለዛውን ባጣ ድምፅ::

«ተረብሸሀል?» ስትል ጠየቀችው::

«ደህና ነኝ»

አያይዞም የፌዝ ፈገግታ እያሳያት «... ይልቁን በመፈቢያቱ ወራት ለኔና ላንቺ ፀሎት አድርሺ:: ኢህአዴግ የሚባለው ሀጥተኛ ውቅያኖስ! ግምገማ የተባለ ማእበሉን ያነሳል የሚል ጭምጭምታ ይናፈሳል:: ማእበሉ ከጠረገ እኔን ብቻ ለይቶ ገደል የሚከተኝ አይምሰልሽ:: ዳፋው ወዳንቺም ሊሻገር ይችላል:: እኔም ብሆን

የሬዐምኩዋቸውን ህገወጥ ድርጊቶች ሁሉ ዝብዝበ አድርጌ መናገሬ አይቀርም። ስለዚህ ከመተኛትሽ በፊት ስሁለታችንም ፀልይልን። እግዚአብሔር እንደሁ እኔን አይሰማኝም። አርባ ቀንና ሌሊት ባለቅስ እንኳዋ ጆሮ አይሰጠኝም። ምክንያቱም ከአናቴ በላይ የህወሀት ሰዎች ብቻ መኖራቸውን ነው ሳምን የኖሩኩት...»

ኮንኮርድ ሲጨፍሩ አመሹ።

ሰለሞን በጫጩቶች ተከቦ ላይ በላይ ዊስኪውን ሰረገበ። ሲነጋ ሲልም ከጫጩቶቹ አንድዋ አብራው ትሄድ ዘንድ ራሱ ጠየቃት። ስሞዋ ሜሮን መሆኑን ነግራው ስታበቃ፣ አብራው ለመዋብ ሳታቅማማ ተስማማች። እያያዘ ግን እንዲህ አለችው፣

«ብር ግን ቅድሚያ ስጠኝ።»

«ምን ያህል?» አላት አነጋገርዋ እየሰቀጠጠው።

«አምስት»

«አምስት ምን?»

«አምስት መቶ ብር ነዋ»

ቆሌው ተገፈፈ።

«የምርሽን ነው?»

«ስለነጋ ነው እንጂ እንዲያውም እኔ በዶላር ካልሆነ አልወጣም።»

«ለመሆኑ!» አላት ሰለሞን ሁለት ደቂቃ ክንዶችዋን እንደብረት በጠነከሩ እጆቹ ጨምድዶ ይዞ፣ ወሲባዊ አይኖዋን፣ ወሲባዊ ጠባብ አፍዋን፣ ወሲባዊ ከንፈሮችዋን፣ ለወሲብ የተፈጠረ የሚመስል መላ ሰውነትዋን እያስተዋለ «ለመሆኑ» አላት፣

«...አንድ ወር ሙሉ እኔ ዘንድ ለመሰንበት አስበሻል ወይስ አንቺ ሁለት ኩንታል የአድአ ነጭ ጤፍ ነሽ?»

ዜኒት ይህን ሰምታ ከኮንኮርድ ጣሪያ በላይ ስትስቅ ተሰማ።

የፈፀምኩዋቸውን ህገ-ወጥ ድርጊቶች ሁሉ ዝክዝክ አድርጌ መናገሬ አይቀርም:: ስለዚህ ከመተኛትሽ በፊት ለሁለታችንም ፀልይልን:: እግዚአብሄር እንደሁ እኔን አይሰማኝም:: አርባ ቀንና ሌሊት ባለቅስ እንኳ ጆሮ አይሰጠኝም:: ምክንያቱም ከአናቱ በላይ የህወሀት ሰዎች ብቻ መኖራቸውን ነው ሳምን የኖሩኩት...»

ኮንኮርድ ሲጨፍሩ አመሹ::

ሰለሞን በጫጩቶች ተከቦ ላይ በላይ ዊስኪውን ሰረገበ:: ሲነጋ ሲልም ከጫጩቶቹ አንድዋ አብራው ትሄድ ዘንድ ራሱ ጠየቃት:: ስምዋ ሚርን መሆኑን ነግራው ስታበቃ፣ አብራው ለመዋብ ሳታቅማማ ተስማማች:: አያይዛ ግን እንዲህ አለችው፣

«ብር ግን ቅድሚያ ስጠኝ::»

«ምን ያህል?» አላት አነጋገርዋ እየሰቀጠጠው::

«አምስት»

«አምስት ምን?»

«አምስት መቶ ብር ነዋ»

ቆሌው ተገፈፈ::

«የምርሽን ነው?»

«ስለነጋ ነው እንጂ እንዲያውም እኔ በዶላር ካልሆነ አልወጣም::»

«ለመሆኑ!» አላት ሰለሞን ሁለት ደቂቃ ክንዶችዋን እንደብረት በጠነከሩ እጆቹ ጨምድዶ ይዞ፤ ወሲባዊ አይንዋን፤ ወሲባዊ ጠባብ አፍዋን፤ ወሲባዊ ከንፈሮችዋን፤ ለወሲብ የተፈጠረ የሚመስል መላ ሰውነትዋን እያስተዋለ «ለመሆኑ» አላት፣

«...አንድ ወር ሙሉ እኔ ዘንድ ለመሰንበት አስበሻል ወይስ አንቺ ሁለት ኩንታል የአድአ ነጭ ጤፍ ነሽ?»

ዜኒት ይህን ስምታ ከኮንኮርድ ጣሪያ በላይ ስትስቅ ተሰማ::



# በኦሮሞዎች ተከባችሁዋል!

# ወይም

# የሀየሎም ምስጢራዊ ደብዳቤ

## ምእራፍ አስራ ሶስት

## - 1 -

ወሬውን ማን የት ላይ እንደጀመረው በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም:: ይሁን እንጂ ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ በሆርዶፋ የሚመሩ ሰባት ወጣቶች በየገበሬው ጉጆ የመዞራቸው ጭምጭምታ አለ::

ታዲያ ገና በማለዳው፣

«ነፍጠኛን አርሲ ጂራ! ? ቆንጨራ ካስኔ ጭራ!» የሚል ቆረርቶ

ቡርቃን ያንቀጠቅጣት ያዘ።

ጃሎታውን የገደል ማሚቶ አቀባበለው። ካካ፣ ባቱና፣ ጭላሎ ተራሮች የቡርቃዎችን ቁጣና ቀረርቶ እየተቀባበሉ በድፍን የኦሮሞ ምድር ነዙት።

«ቡርቃቃቃቃ... ሲጋአአአአ» የሚል አስፈሪና አርአድ አንቀጥቅጥ ድምፅ የገበሬዎችን ልብ በረጋገደው።

«ጊዜው ደረሰ!» የሚል ጥሪ በየሸለቆው ናኘ።

ረፈድ ሲል ዘገራቸውን የሚነቀንቁ፣ ፈረሳቸውን የሚኮለኩሉ ገበሬዎች ቡርቃን አጥለቀለቁት። የሴቶች እልልታ ተሰማ። የሀወኒን ስም በጩኸት የሚጠሩ እናቶችና ልጃገረዶች ድምፅ! አኖሌን የሚያነሳሱ ኮበሌዎች ድምፅ - ቡርቃ ላይ ተጥለቀለቀ።

ለፍልሚያው አቅም አለኝ ያለ ሁሉ ቅሌን ጨርቁን ሳይል ጉጆውን የሁዋሊት ተወ። እርሻ ላይ የነበረ እርፉን ትቶ ባለመንታ ምላስ ዘገሩን አሊያም ጠመንጃውን ጨበጠ። ገና በማለዳው ጫት መቃም የጀመረ፣ የጌሾ ጥንስስ የመሰለ ጫቱን ከአፉ ተፋ። አፉን ደሞ በወፍራም ወተት ተጉመጠመጠው። ተጉመጥምጦ ሲያበቃ አይኑን እያጉረጠረጠ ከሰልፈኛው ተቀላቀለ።

ኦሮሞዎቹ ገበሬዎች ያልያዙት የመሳሪያ አይነት የለም።

ክላሽንኮቭ ጠመንጃ - ውጅግራ ጠመንጃ - አልቤን ጠመንጃ - ፋስ - ቢላዋ - መጥረቢያ - ድንጋይ - የወይራ ዱላ - ከአሀያ ጆሮ ተክል የተበጀ ጅቦ - ክብሪት - በጠያይምና በጠንካራ እጆቻቸው ጨብጠው ወደ ፍልሚያው ጋለቡ። ከቅዱስ ሚካኤል ደብር ባሻገር እጅግ ለም በሆነው የኦሮሞ ምድር ላይ የሰፈሩትን የአማራ ገበሬዎች ወደ አመድ ክምርነት ለመለወጥ ቸኮሉ። ቀረርቶው እዚህም እዚያም ይሰማል፣

- አስላማሌይኩም
ዋቀዮ መራንፍራ
ዲኒ ኬኛ - ቡርቃ ጂራ
አማሪ ኦሮሚያ ጂራ
ነፍጠኛን አርሲ ጂራ
ቆንጨራ ካስኔ ጭራ -





እኩለ ቀን ሲል እንደነጐድጓዋድ የሚያጉረመርም፣እንደማእበል የሚገላበጥ፣ የኦሮሞ ገበሬዎች ጉርፍ ችቦውን እሳት እያያያዘ፣ ጥይቱን እያንፈቀፈቀ ወደ ቅዱስ ሚካኤል ደብር አቅጣጫ እንደናዳ ሲወረወር ታየ ...

*   *   *

አማሮቹ ገበሬዎች በበኩላቸው ገና በማለዳው የኦሮሞዎቹን ንቅናቄ እንደሰሙ ወንዶቹ የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎቻቸውን ሸካክፈው ወደቅዱስ ሚካኤል ደብር ገስግሰው ተሰባሰቡ። አፍታም ሳይቆዩ የጐበዝ አለቃ መርጠው ምክክር ጀመሩ። ጊዜ እንደሌላቸው በማወቃቸው ወግ አላበዙም። ከመካከላቸው ሁለት ኮበሌ ፈረሰኞችን መርጠው የቡርቃ ገበሬዎች ፀብ መጫሬቸውን ለመንግስት ያሳውቁ ዘንድ ላኩዋቸው። ከዚያም የመከላከሉን ዘመቻ ይመሩ ዘንድ የተመረጡት የጐበዝ አለቆች ብዛት ያላቸውን የቡርቃ ገበሬዎች ማጥቃት ስለሚችሉበት መንገድ መላ መዘየዱን ተያያዙት።

ምክክሩ ብዙ ጊዜ ሳይወስድ ተፈፀመ።

«ኦሮሞዎቹ ደጃችን ላይ እስኪደርሱ ከጠበቅን ጐጆአችንን ያጋዩታል፣ ስለዚህ እኛ ቀድመን ወደእነርሱ እንገስግስ» ሲሉ መከሩ። ይህ ብቻ አልነበረም መላው።

«ወንድ የተባለ የቡርቃ ገበሬ ሁሉ መንደሩን ለቆ እየወጣ ስለሆነ የኛ ጥቂት ኮበሌዎች በካካ ተራራ ሸጦች ወደ መንደሮቹ ተጠግተው ጐጆዎቹ ላይ እሳት ይለኩሱ፣ ያን ጊዜ ለሴቶቻቸውና ለህፃናቶቻቸው ሲሉ ከፊሎቹ ወደ መንደራቸው ስለሚመለሱ ሀይላቸው ይዳከምልናል» ተባባሉ። በመጨረሻም የጐበዝ አለቃው እንዲህ ሲል አሳረገ።

«ለህይወታችን መሳሳት አይገባንም። ድል ካደረግን ሞት ምንም አይደለም። ህፃናቶቻችን ያድጋሉ። ዘራችንም ይቀጥላል። ቅዱስ ሚካኤል ደሞ ከቀኛችን ይሆናል።»

«እኩለቀን ከመሆኑ በፊትም ጠመንጃዎቻቸውን ወልውለው የቡርቃ ኦሮሞ ገበሬዎችን ጉርፍ ለመግታት ህፃናቶቻቸውን እየሳሙ ከመንደራቸው ወጡ።

ጉዞአቸው በፉከራ የተሞላ ነበር። በእድሜ የገፉ ገበሬዎች፣

«ኦርቶዶክስ አንገቷ ላይ ላሰራት ክር ሲል አጥንቱን ይከስክሳል! » ሲሉ ቀሰቀሱ!!

«ሃምሳ አመት የሚያስተኛ በትር እናቀምሳቸዋለን!» የሚሉ በቁጣ የተሞሉ ቀረርቶዎች ተደመጡ፣

ጃሎታው እየሞቀ ... እየደራ ... እየጋለ ... እየፈነዳ ... ሄደ ...

*    *    *

በዚያን እለት ተሲያት ላይ ቡርቃና አካባቢዋን ከሰማየ ሰማያት ለሚያያት የእሳት ከተማ መስላ ነበር። ጠመንጃዎች ነበልባል ተፉ። መንታ መላስ ያላቸው ጦሮች ቀሉ። የሴቶችና የህፃናቶች ጩኸት በአማራዎቹና በኦሮሞዎቹ መንደሮች ተሰሙ። ቆንጨራ በደም ታጠበ። የእሳት መላስ ህፃናቶችን ለበለበ። የመከላከያ ሰራዊት በፍልሚያዎቹ አካባቢዎች በሄሊኮፕተር ደርሶ እስኪገላግል ድረስ ቡርቃ ተንቀጠቀጠች...

በደም እየታጠቡ የሚፋለሙት አብዛኞቹ ገበሬዎች ግን የጠቡ ምክንያት እምብዛም አልተገለጠላቸውም ...

በርግጥ ምድሩ ለም ነው። ሰማዩም ከአመት አመት ውሀ ያመነጫል። መሬቱ ሰፊ ነው፤ ገበሬቹ ግን እፍኝ አይሞሉም። ያልታረሰው መሬት አያሌ ነው። ወፍ ዘራሹን ፍራፍሬ የሚለቅመው የለም። ማሩ የጉንዳን መጫወቻ ሆኖአል። እጣኑን ዞር ብሎ የሚያየው የለም። ምድሪቱ ሀብታም ናት። ገበሬዎቹ ግን ጥቂትና ድሆች ናቸው።

ርስ በራስ የሚፋለሙት ገበሬዎች ከሚለያዩባቸው ይልቅ የሚመሳሰሉባቸው ባህርያቶች ይበረክታሉ። አብዛኞቹ ደሀ ገበሬዎች የማንም የበላይ፤ የማንም የበታች መሆን ከቶ አይፈልጉም። ይሁን እንጂ ግጭቱ ተቀሰቀሰ ጉጆዎች በእሳት ጋዩ። ህይወት ጠፉ። ግን ለምን? የእብድ ገላጋይ በዝቶ ይሆን?

## - 2 -

ግጭቱ በተከሰተበት እለት ሀወኒ የደህንነት ሚንስትሩ ክንፈ ገብረመድህን ዘንድ ቀረበች። ክንፈ ከወንበሩ ተነስቶ የሞቀ ሰላምታ አቀረበላት። ስለጤንነትዋም አጥብቆ ጠየቃት። ቡና እስኪቀርብላቸውም ከአኖሌ ተለይታ ስትመጣ የገጠማትን ሁኔታ አጫወተቻቸው። ብዙ የመናገር ፍላጎት ግን አልነበራትም። ለአኖሌ አብራው መቆየት እንደማትችል በግልፅ ነግራው እንደተለየችው አጠር አጠር አድርጋ አወጋችው።

ቡናው ቀረበ ...





ክንፈ ፈጥኖ ወደዋናው አጀንዳ ዘለቀ። ማስታወሻ ደብተሩን እየገላለጠ፣

«የተላክሽበት ተግባር እንዴት ተፈፀመ?» የሚል የመግቢያ ጥያቄ አቀረበላት። ይህን ጥያቄ ሲያቀርብ ገፅታዋን በጥንቃቄ እያጤነ ነበር። አለመረጋጋትዋን ተገነዘበ። መረበሽ ይታይባታል።

«የተላክሁበትን ተግባር አልፈፀምኩም» ስትል መለሰች።

«ችግሮች ነበሩ?»

ሀወኒ መልስ ለመስጠት በመዘግየትዋ ክንፈ ቀጠለ፣

«ለነገሩ እጅግ ከባድ ተልእኮ ነበር። ለመሆኑ ቆይታሽ ምን ይመስል ነበር?»

«ችግሮች አልነበሩም ክንፈ። እኔ ራሴ በአቀዋሜ ፅኑ ወይም ርግጠኛ አልነበርኩም። በመወላወል ላይ ነበርኩ።»

ሀወኒ ይህን ብላ በሁለት እጆችዋ ፊትዋን በኃይል እያበሰች ትኩስና ረጅም ትንፋሽ አስወጣች። አለመረጋጋትዋና ትእግስት ማጣትዋ ገፅታዋ ላይ በግልፅ ይታይ ጀመር።

«ስማኝ ክንፈ ...» አለች ሀወኒ፤ በደከመና በተጐዳ መንፈስ።

«ተረብሸሻል?» አላት።

«አኖሌ አሁን ያለበትን ሁኔታ አባክህ ንገረኝ?»

ነገራት። አኖሌ አባቦኮ ኮረብታ ላይ በኢህአዴግ ሰራዊት ተከቦአል።

«ሊሞት ይችላል?» ስትል በጭንቀት ተነፈሰች።

«እጁን ከሰጠ አይሞትም።»

«እጁን እንኪዋ አይሰጥም ክንፈ። ሰውየውኮ አኖሌ ዋቆ ነው። ሌላ መንገድ ለምን አይፈለግም?»

«ምን አይነት መንገድ?» ብሎ ፈገግ አለ «... ወንጀለኛ ነው። እጁን መስጠት አለበት።»

«አኖሌ ወንጀለኛ አይደለም!» ብላ ጮኸች።

ክንፈ በመገረም ሲያስተውላት ቆይቶ፣

«ከሁለት ሚሊዮን በላይ ብርና ንብረት መዝረፉ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው። ይህን እንደፈፀመ አታውቂም?» ሲል ጠየቃት።

«... የአኖሌ ድርጊቶች በሙሉ ፖለቲካዊ እንጂ ከግል ጥቅም ጋር በተያያዘ የተፈፀሙ አይደሉም:: ህዝቡን ሲበዘብዙ ከኖሩ አረመኔዎች! ኦሮሚያ እየመገበቻቸው ኦሮሚያን ከሚንቁ ሆዳም ትምክህተኞች ከተወሰደው ገንዘብ ለግል ጥቅሙ ያዋለው ሰባራ ሳንቲም እንኩዋ የለም»

ክንፈ ፈጥኖ ምላሽ ሰጣት፣

«ዝርፊያ 'ፖለቲካዊ' የሚባል የክርስትና ስም የለውም:: ዝርፊያ ፖለቲካ አይደለም:: ፖለቲካም ዝርፊያ ሊሆን አይችልም» ሲል ለመጀመሪያ ጊዜ ከረር ያለ ምላሽ ሰጣት:: በግልባጩ ደግሞ ሀወኒ ረገብ ብላ መልስ ሰጠች::

«በአለማችን የተለመደ ድርጊት መሆኑን እንኩዋ አንተም አሳምረህ ታውቀዋለህ:: የተለያዩ ጥያቄዎችን ይዘው አመፅ የሚጀምሩ ቡድኖች ሁሉ ህጋዊ ባልሆነ መንገድም ቢሆን ገንዘብ ለማግኘት ይሞክራሉ:: የአኖሌ ድርጊት ከዚህ ተነጥሎ ባይታይ እመርጣለሁ»

ክንፈ ምላሽ አልሰጣትም:: እስዋም አልቀጠለች:: ለደቂቃዎች ያህል በዝምታ ተውጠው የየራሳቸውን አሳብ ሲያኙኩ ቆዩ:: ዝምታው ሲጫጫናቸው ሲጀምር ክንፈ ጠጉሩን ሁለት ጊዜ ወደሁዋላ ድጦ ሲያበቃ፣ ረጅምና የታመቀ አየር አስወጣ፣

«ሀወኒ ... ወደ ዋናው ጉዳያችን እንመለስ:: እስካሁን ካደረግናቸው ውይይቶች እንደምገነዘበው የአኖሌን ተግባራት የመደገፍ አዝማሚያ አይብሻለሁ:: ይህም የተላከሽበትን ተግባር አለመፈፀምሽንና ተባባሪው ሆነሽ መቆየትሽን ነው የሚያረጋግጠው:: እንደሚገባኝ አኖሌ በዝርፊያና ግጭቱን በመቀስቀስ ወንጀሎች የግድ ተጠያቂ ይሆናል ...»

ሀወኒ ክንፈን ትክ ብላ ተመለከተችው፣

«ከአኖሌ እምነቶችና አላማዎች የተጋራሁት ነገር አለ::» ስትልም ተነፈሰች «... ይህን አልክድም:: አደገኛ የሆኑና የምቃወማቸው አመለካከቶችም ነበሩት:: አብሬው በቆየሁባቸው ጥቂት ወራት እነዚህን ግትር እምነቶቹን እንዲለውጥ እየጣርሁ ነበር::»

የሚፋጅ አየር አስወጣች:: የተቃጠለ ፊትዋን በመዳፍዋ አሸችና ደሞ ቀጠለች፣

«ለሙቶ አመታት የተረገጠውን የኦሮሞ ብሄርተኝነት ስሜት ባፋጣኝ ማደስ ተገቢ መሆኑን ሁለታችንም አምነንበታል::





ብሄርተኝነቱን ማደስ በሚቻልበት መንገድ ላይ ግን ልዩነት ነበረን:: 'ከሀይል ውጭ ያሉትን አያሌ አማራጮች ማየት ይገባናል' እያልኩ ነበር:: በመካከሉ ያልታሰበ ግጭት ተቀሰቀሰ:: ግጭቱ በዚያ መንገድ እንዲነሳ አኖሌ ግፊት አድርጎአል ብዬ አላምንም:: የግጭቱ ቀስቃሽ አኖሌ መሆኑን መናገር ተገቢ አይደለም:: በተቀረ አሁን ለጊዜው ምን ማሰብ እንዳለብኝ እንኩዋ በቅጡ አላውቅም ...»

ክንፈ ከተቀመጠበት ተነስቶ ከቢሮው ወጣ:: አስር ደቂቃ ቆይቶ ተመለሰ:: ከፀሀፊው ቢሮ ስልክ ደውሎ በትግርኛ ሲነጋገር ሀወኒ ሰምታዋለች:: እንደተመለሰ፣

«... ሀወኒ አዝናለሁ!» አለ በተረበሸ ስሜት ተውጦ «... የስነስርአት ርምጃዎችን መውሰድ ይኖርብኛል:: ለጥቂት ጊዜያት ማረፊያ ቤት መቆየትሽ ነው:: መታሰርሽን አክብደሽ እንደማትመለከቺው እገምታለሁ:: ጥቂት ነገሮችን እስክናጣራ መፈፀም ያለበት ነው:: መቼም የድርጅታችንን ህገ - ደንብ በሚገባ ታውቂዋለሽ ብዬ አምናለሁ»

- 3 -

አባቦኩ ኩረብታ ከቡርቃ መንደር ሀያ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል:: አካባቢው የጫካማነት ባህርይ አለው:: በኩረብታው አካባቢ የገበሬ ጎጆዎች እምብዛም አይታዩም::

ኩረብታው ታሪክ አለው:: አፄ ምኒልክ አርሲን ሲወሩ በአካባቢው የአባቦኩነት ስልጣን የነበራቸው ሽማግሌ ኩረብታው ላይ ወጥተው «እጅን ለምኒልክ አልሰጥም» ብለው ማመፃቸው ይነገራል:: መከበባቸውና ማምለጫ እንደሌላቸው የሚገልፅ መልእክት ተላከባቸው:: አባቦኩ ታዲያ፣

«አላወቃችሁትም እንጂ እናንተም በኦሮሞ ህዝብ ተከባችሁዋል::» የሚል ምላሽ ላኩ::

ምላሹ ይህ ብቻ አልነበረም:: «መውጫና ማምለጫ የሌላችሁ እናንተ ናችሁ:: እኔማ በአባቴ ምድር ላይ ነኝ:: በዙሪያዬ ኦሮሞዎች አሉ:: እናንተ ስግብግብ ነፍጠኞች! እስኪ ዘወር ብላችሁ ከጀርባችሁ ያለውን አንድ የኦሮሞ ገበሬ ተመልከቱ:: አይኖቹ ደም ለብሰው፣ ፊቱ እንደነብር ተቆጥቶ ድርጊታችሁን ሁሉ ይመለከታል:: ከቻለ ነገ ማለዳ ያንቃችሁዋል:: ካልቻለ የፈፀማችሁትንና ማንነታችሁን ዘርዝሮ

ለልጁ ያወጋዋል፡፡ እናንት አዙራችሁ ማየት ያልቻላችሁ አረመኔዎች!፡፡ ልጅ ክባቱ በላይ ይቆጣል፡፡ ያን ጊዜ ልጆቻችሁ ወዮላቸው» የሚል ምላሽ መስጠታቸው ይነገራል፡፡

አባቦኩን የከበቡት የምኒልክ ጦር ሰራዊት አዛዥ ፊታውራሪ ሀብተስላሴ እምሩ ይባሉ ነበር፡፡ የአባቦኩ ምላሽ ሲደርሳቸው ለሰራዊታቸው ፈጣን ትእዛዝ ሰጡ፣

«እንበሶቼ! በአስቸኩዋይ የጋላውን ራስ ቆርጣችሁ አምጡልኝ!»

ከሁለት ሰአት ውጊያ በሁዋላ የአባቦኩ ራስ ጦር ላይ ተሰክቶ ቀረበላቸው፡፡

ሽበት የወረራቸው ሽማግሌ ራስ! ቁጣ የተቸከቸከበት ግንባር!

የፈጠጡ አይኖች!

አባቦኩ የሞቱ አይመስሉም ነበር ...

... ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የአካባቢው ገበሬዎች ኩረብታውን «የአባቦኩ ኩረብታ» ሲሉ ጠሩት፡፡

አኖሌ የተሸሸገው በዚህ ኩረብታ ላይ ነበር፡፡

ቡርቃ ላይ የአማራና የኦሮሞ ገበሬዎች ግጭት በተከሰተበት እለት አራት ሄሊኮፕተሮች በአባቦኩ ኮረብታ አናት ላይ ያንዣብቡ ጀመር፡፡ ከግማሽ ሰአት ማንዣበብ በሁዋላ ሜዳማውን አካባቢ መርጠው አረፉ፡፡

ከስድሳ የማይበልጡ የመከላከያ ሰራዊት አባላት አስር ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የአባቦኩን ኩረብታ ከበቡዋት፡፡ ሰራዊቱን እየመራ የመጣው የታጋዮቹ አዛዥ ሀየሎም ነበር፡፡ ሀየሎም አርአያ፡፡

ሀየሎም ሰራዊቱን በቀጥታ የሚመሩትን ሁለት የጋንታ መሪዎች አስጠርቶ መመሪያ ይሰጥ ጀመር፡፡ ኩረብታዋ ላይ «አኖሌ» ተብሎ የሚጠራ የአንድ ሀገወጥ ቡድን መሪ ጥቂት የሰው ሀይል ይዞ መሸሸጉን ከገለፀ በሁዋላ፤ እስካሁን ከኩረብታዋ አለመውጣቱን ጠቁሞ፤ 'ምናልባት መከበቡን ሲያውቅ ጥሶ ሊሸሽ ይሞክር ይሆናልና የማምለጫ ሽጦች በሙሉ በጥንቃቄ ይጠበቁ' ሲል መመሪያ ሰጠ፡፡





ጋንታ መሪዎቹ የታዘዙትን ለመፈፀም ፈጥነው ገሰገሱ፡፡ ሀየሎም ብቻውን አልነበረም ወደ አባቦኩ ኩረብታ የመጣው፡፡ አብርሀ ፀሎት አብሮት አለ፡፡ አኖሌ እጁን ይሰጥ ዘንድ ለማግባባት አብርሀ አወንታዊ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ገምቶ ነበር - ይዞት የመጣው፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች አካባቢውን ከፈታተሹ በኋላ ሀየሎምና አብርሀ በታጋዮች እንደታጀቡ በቅርብ ወዳለችው ሄሊኮፕተር አመሩ፡፡

«ምን አሰብክ?» ሲል ጠየቀው አብርሀ ፀሎት፡፡

«እጁን እንዲሰጥ ማግባባት አሰብን፡፡»

«እኔ ላሳምነው እችላለሁ» አለ አብርሀ፡፡

«ከዚያ በፊት ግን የአካባቢውን ገበሬዎች እንላክበት» አለ ሀየሎም፡፡

በግማሽ ሰአት ውስጥ አንድ ሽማግሌ ገበሬ ሀየሎም ዘንድ ቀረቡ፡፡

ሽማግሌው ሀየሎምን በጥርጣሬ አይን ይገረምሙት ያዙ፡፡

በአስተርጉዋሚ ያዋራቸው ጀመር፣

«እንደምን ዋሉ አባቴ!»

«ምስጋና ለዋቀዮ!» አሉ ሽማግሌው፡፡

«እንተዋወቅ፡፡ የኔ ስም ሀየሎም ይባላል፡፡»

«ባልቻ፡፡»

«የዚህ አካባቢ ነዋሪ ነዎት?»

«እዚሁ ነኝ» ብለው መለሱ፡፡

ቁጥብነት ይታይባቸዋል፡፡

«ይሄ ኩረብታ ማን ይባላል ስሙ?»

«አባቦኩ!»

«አኖሌን ያውቁታል?»

«እሱን የማያውቅ ማን አለ?»

«እዚህ ኩረብታ ላይ ነው ይባላል፡፡ እውነት ይሆን?»

«እኔ አላውቅም፡፡»

«እኛ ግን እዚህ መሸሸጉን አረጋግጠናል፡፡ ወደሱ መልእክት

ሊያደርሱልን ይችላሉ?»

ሽማግሌው መልስ ሳይሰጡ ዘገዩ።

«አባቴ ... እኔና ርስዎ እንደአባትና ልጅ እንጨዋወት። መቼም እንግባባለን። የምንግባባቸው እያሌ ቁምነገሮች አሉ። ሁለታችንም የነፍጠኛውን አገዛዝ አምርረን እናወግዛለን፤ ይሄ እውነት አይደለም?»

«ልክ ነው!» አሉ ሽማግሌው ጉሮሮአቸውን እየሳሉ፤

«ኦሮሞዎች በልማዳቸው መሰረት በሚያከብሩዋቸውና፤ እንደጥንቱ ባህል የራሳቸውን የአካባቢ አባቦኩ እየመረጡ መተዳደር ይኖርባቸዋል። በዚህስ እንግባባለን?»

«ይሄ ሁሉ እውነት ነው»

«የተናገርኩትን አምነውኛል?» ሀየሎም ጠየቀ።

«የሰው ልጆችን ልብ መመርመር የሚችለው ዋቀዮ ብቻ ነው» ሲሉ መለሱ ሽማግሌው።

«መልካም» አለ ሀየሎም ሲጋራ እየለኮሰ «... እኖሌ እጁን በሰላም እንዲሰጥ ወደኩሪብታው መልእክት መላክ እፈልጋለሁ። በዚህ ይተባበሩን። እኖሌ እንዲሞት አንፈልግም።»

«እኛም እንዲሞት አንሻም» አሉ ሽማግሌው።

«መልእክት ያደርሱልናል ታዲያ?»

«ይንገሩኝ መልእክቱን»

ሀየሎም ተደሰተ። ኩሪብታዋ መከበብዋንና እጁን ከመስጠት ሌላ ምንም አይነት አማራጭ አለመኖሩን የሚያስገነዝብ መልእክት በሽማግሌው ገበሬ በኩል ላከ።

ለአይን ያዝ ማድረግ በመጀመሩ ሀየሎም ፈጣን እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለበት ማሰላሰል ጀመረ። ከአብርሀ ፀሎት ጋር እኖሌን በተመለከተ እያወጉ የሽማግሌውን ገበሬ ምላሽ ይጠብቁ ጀመር። ከሀያ ደቂቃ በሁዋላ መልእክተኛው ተመልሰው መጡ።

«አደረሱ መልእክቱን?»

ሀየሎም በጉጉት ነበር ጥያቄውን ያቀረበላቸው፣

«አዎን አድርሼያለሁ።»





«ምን ምላሽ ሰጠዎት?»

ሽማግሌው ገበሬ ከቁምጣ ሱሪያቸው መታጠቂያ ስር የተጣጠፈች ቁራጭ ወረቀት አውጥተው አቀበሉት።

ሀየሎም ወረቀትዋን በችኮላ ገላለጣት። ለአይን ያዝ ቢያደርገም ለማንበብ አልተቸገረም።

«ተሳስተሀል» ይላል የእኖሌ ምላሽ ሲጀምር «... በጣም ተሳስተሀል ሀየሎም!። ያለኝ አማራጭ እጄን መስጠት ብቻ አይደለም። ተዋግቶ መሰዋትም ሌላ አማራጭ ነው።»

ሀየሎም ቃል እንኳዋ ሳይተነፍስ ከወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደ ደቂቃዎችን በዝምታ አሳለፈ፣

«ሀየሎም።»

«አብርሀ»

«ምን እያሰብክ ነው?»

«አንተ መሄድ አለብህ» ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ።

አብርሀ ፀሎትና ሽማግሌው ገበሬ ተያይዘው ወደ አባቦኩ ኩሪብታ አናት አቀኑ። ሀየሎም ሲጋራውን ላይ በላይ እየማገ ሄሊኮፕተሮቹ አካባቢ ወዲያ ወዲህ ይመላለስ ያዘ። በራሱ ሀሳብ መጠመዱ ግልፅ ነበር።

ከአንድ ሰአት በሁዋላ አብርሀ ፀሎትና ሽማግሌው ገበሬ ተመልሰው መጡ። አብርሀ ተርቦ ዳቦ የሚገምጥ ያህል ሲጋራውን እየመላለሰ ሲጐርሰው በድብዛዛው ምሽት ለሀየሎም ወለል ብሎ ታየው።

«አገኘኸው?»

አብርሀ  ዘግይቶ ነበር ምላሽ የሰጠው።

«አዎን ... አገኘሁት»

«ውጤቱስ?»

«ያው ነው» አለ ተስፋ በመቁረጥ።

ሽማግሌው ገበሬ በአካባቢው ከነበረ ቁዋጥኝ ላይ አረፍ ብለው ቀጥሎ የሚሰጣቸው ትእዛዝ ካለ ይጠብቁ ጀመር። ሀየሎም አይኖቹን የተጨማደደ ቁምጣ ሱሪ ለብሰው አለት ላይ በተቀመጡት ገበሬ ላይ ተከሉ፣

«እንዴት ማሳመን አቃተህ?» አለ::

«አልቻልኩም!» አለ አብርሀ ፀሎት «... ሲሰማኝ አልፈቀደም:: የኔን ዲስኩር ወደጐን እየተወ ጭርሱን ይቀልድብኝና ይስድበኝ ጀመር::»

«ምን አለህ?»

«...ትግሉ ሲያልቅ የአስመራ ምቹ ኑሮ ወኔህን ሰልቦት ይሆናል እንጂ አንተ እንኩዋ እንዲህ የምታስብ አልነበርክም አለኝ:: ቢቸግረኝ 'እጅህን መስጠቱ ይቅርና ከዚህ ኰረብታ የምታመልጥበትን መንገድ እንምከክር' አልኩት:: እንዲህ ስለው ሳቀ:: ከልቡ እየሳቀ 'ውለታ የመመለስ ግዴታ የለብህም:: ይልቁን አኖሌ ስለሚባለው ሰው እርግፍ አድርገህ ረስተህ ወደ አስመራ ተመለስና ሚስት አግባ:: ልጅ ውለድ:: የመጀመሪያ ልጅህ ወንድ ከሆነ ሳሙኤል በለው:: ምክንያቱም አንተ ከአስመራ እስር ቤት እንድታመልጥ ምክንያት የሆነው ሳሙኤል የተባለው ጉዋደኛዬ ነው:: ልጅህ ታዲያ ሳሙኤልን ያስታውስሀል:: ሳሙኤል ደግሞ እኔን:: ድንቅ ምክር አይመስልህም?' እያለ ቀለደብኝ::»

ሀየሉም በመገረምና በመደነቅ አዳምጦ ሲያበቃ ሲጋራውን ሜዳ ላይ ወርውሮ ጉማጁን በጫማው ደፍጥጦ አጠፋው:: ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ጨለማው ውስጥ በዝምታ ቆዩ!

«ሀየሉም»

«እሀ...»

«አንድ ነገር አድርግ:: አኖሌ መሞት የለበትም::»

ሀየሉም ምላሽ አልሰጠውም::

ለራሱ ብቻ በሚሰማ ድምፅ እጉተምትሞ ወደሄሊኮፕተርዋ አመራ:: አብርሀ ሲጋራውን ደግሞ ለኩሶ ወደሰማይ ቀና አለ:: ግማሽ ጨረቃ ሰማዩ ላይ ተለጥፋለች:: በረጅሙ ተንፍሶ ወደሄሊኮፕተርዋ ተመለከተ:: የሄሊኮፕተርዋ የውስጥ መብራት በርቶአል:: 'ሀየሉም ምን እየሰራ ይሆን?' ሲል ራሱን ጠየቀ:: ከአዲስ አበባ ሰዎች ጋር እየመከረ ይሆን?

መለስ ብሎ ስለአኖሌ ማሰብ ጀመረ:: የተገናኙባቸውን ጊዜያት! በእኒያ በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች... ተስፋ ባልነበረባቸው ...





... አብርሀ ፀሎት ለምን ያህል ደቂቃዎች እንደቆየ ባያውቅም ድንገት የሀየሉምን ድምፅ ሰምቶ ቀና አለ:: ሀየሉም ሄሊኮፕተርዋን ተደግፎ ቆሞአል:: በእጁ ነጭ ፖስታ መያዙን በጨለማው ውስጥ ተመለከተ:: የሀየሉም አጃቢዎችና ኦሮሚኛ ተርጉዋሚው ሽማግሌውን ገበሬ ጠርተው ወደ ሀየሉም ሲያቀርቡዋቸው፤ አብርሀ ፀሎትም አብሮ ተጠጋ፣

«አባቴ፤እንደገና ወደ አኖሌ ልልክዎት ነው::»

«ምን ገዶኝ» ሲሉ መለሱ::

«ይህን ፖስታ በእጁ ይሰጡታል::»

«ደህና::»

«ይህን ከፈፀሙ በሁዋላ ተመልሰው ወደኔ ይምጡና በትክክል ማድረስዎን ያረጋግጡልኝ::»

«ምላሽ አለው?»

«ምንም መልስ የለውም፤ አባቱ::»

ሽማግሌው ፖስታውን ይዘው ወደ ኰረብታው ገሰገሱ::

«አብርሀ::»

«እሀ::»

«ኰረብታዋ ላይ ምን ያህል የሰው ሀይል አለ?»

«ከስድስት አይበልጡም:: እርግጠኛ ግን አይደለሁም:: ቦታው ግን ለመከላከል ምቹ ነው:: ቢሆንም ከአንድ ሰአት በላይ ሊከላከሉ አይችሉም::»

ሀየሉም የጋንታ መሪዎችን በሬድዮ ተገናኝቶ በተዳከመ ድምፅ መመሪያ ይሰጣቸው ጀመር!

«... ልጁ እጁን ሊሰጥ ፈቃደኛ አይደለም:: ስለዚህ ሲነጋጋ ሲል በቁጥጥር ስር እናውለዋለን:: ተከታዮቹ ከአስር ወይም ከአስራ ሁለት የሚበልጡ አይደሉም:: ቢቻል ልንማርካቸው እንሞክር:: ከኛ ወገን ተኩስ የምንጀምረው ከነርሱ የመከላከል ተኩስ ከከፈቱ ብቻ ነው:: ቀድመን መተኩስ የለብንም:: ተኩስ ካልከፈቱ ምናልባት እጃቸውን ለመስጠት ወስነው ሲሆን ስለሚችል ከኛ ወገን እንዳይተኩስ:: ቃኚዎች ከሁሉም አቅጣጫ በቅድሚያ ወደ ኰረብታው ይላኩ::» የሚል መመሪያ ሰጠ::

እኩለ ሌሊት ላይ ከወደ አባቦኩ ኩረብታ አናት አምስት ጥይቶች በተከታታይ ሲተኮሱ ተሰማ። ኩረብታዎን የከበቡት ታጋዮችም «'የቡርቃ ዝምታ' መሪ ራሱን ገድሎ ይሆን?» ሲሉ ርስበርስ ተነጋገሩ።

## - 4 -

አይሮፕላን ለመጥለፍ የውስጥ ሱሪያቸው ውስጥ ሽጉጥ ሸሽገው ሊያልፉ ሲሞክሩ ከተያዙ ሁለት ወጣቶች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ነበር የታሰረችው። ሁለቱ የእስር ቤት ባልደረቦችዋ መስከረም እና ሀና ይባላሉ። እድሜያቸው ከሃያ አምስት አይበልጥም። መልከ መልካምና ቀጫጭኖች ናቸው። ያለማቋረጥ ይለፈልፋሉ። ማዳመጥ የሚችሉ አይመስሉም። አውሮፓ ወይም አሜሪካ የመሄድ ምኞት ናላቸውን ያዞራቸው የአራት ኪሎ ልጆች ናቸው። ሀወኒ ከሁለቱ እስረኞች ጋር የእለቱ እለት ተግባባች። ፋታ ሳይሰጡ ስምዋን ጠየቁዋት። ነገረቻቸው። በጣም 'የሚጥም' ስም መሆኑን ከገለፁላት በሁዋላ የስምዋን ትርጉም ማወቅ ፈለጉ። ምላሽ ሰጠች። 'ለምን ታሰርሽ?' የሚል ጥያቄ አስከተሉ። በቀላል ጉዳይ መታሰርዋን እንደዋዛ ተናገረች።

«ካያ ተይዞብሽ ነው?» አለች መስከረም።

«ምንድነው ካያ?» ሀወኒ ጠየቀች።

«ሀሺሽ ነዋ!»

እለመሆኑን ነገረቻቸው። 'ታዲያ ምን አጠፋሽ?' ሲሉ አፋጠጡዋት። የሀሰት ፓስፖርት ይዛ መገኘትዋን አጫወተቻቸው። አፍዋ ላይ የመጣላት ምክንያት ነበር። ቀኑባት። 'ቶሎ ትለቀቂያለሽ! እድለኛ ነሽ' አሉዋት። አያይዘው ስለ ራሳቸው መተረክ ጀመሩ። ቢያንስ አስራ ስምንት አመት እንደሚፈረድባቸው፣ የእስር ጊዜያቸውን የሚጨርሱትም በአርባ ሁለት አመታቸው እንደሚሆን ለሀወኒ ሲነግሩዋት፣ የሁለቱም እንባ ባንድ አፍታ ጉንጮቻቸውን እያጠበው ነበር፣

«አይሮፕላን መጥለፍ ምን አሳሰባችሁ?» ስትል ጠየቀቻቸው ሀወኒ።

የፍቅር ጉዋደኞቻቸው እንዳሳሳቱዋቸው አወጉዋት።

በዚህ መነሻ ተግባቡ።

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት እየተቀባበሉ ታሪካቸውን ያጫውቱዋት ጀመር። ስለመጀመሪያ ፍቅረኞቻቸው በሰፊው





ቀደዱላት። የመምህራኖቻቸውን መልክ፣ ቁመና፣ ልዩ ባህርይ እያነሱ ዘነጣጠሉዋቸው። ስለቀመሱትና ስላልቀመሱት የመጠጥ አይነት ወደ ማብራራቱ ተሸጋገሩ። ቀይ ቪኖን የመሰለ መጠጥ ግን በዚህ አለም ላይ እንደሌለ እየማሉ አረጋገጡላት። ሀወኒ እየሳቀች ታደምጣቸው ያዘች። እነርሱ ወጋቸውን ቀጠሉ - እየተቀባበሉ ስለ ሀሺሽ አጫወቱዋት። ለመጀመሪያ ጊዜ ሀሺሽ የወሰዱት የወሲብ ፊልም እያዩ መሆኑንና እለቱና ስሜቱ ጨርሶ እንደማይረሳቸው ተናገሩ። የሀሺሹ ሲያበቃ ወደ ጫት ዞሩ።

ሀና በተለይ ቀድማ ለመናገር ቸኰለች፣

«ስንት አይነት ጫት ትመሻል?» ስትል ሀወኒን ጠየቀቻት።

ቀምሳ እንደማታውቅ ሀወኒ ስትገልፅ፣ ሁለቱ የአራት ኪሎ ወጣቶች ስለጫት አይነትና ባህሪያቱ እየተቀባበሉ አስተማሩዋት፣

«ጫት ማለት 'አቡሚ ማር' ነው። ብው ያደርጋል» አለች ሀና።

መስከረም ቀጠለች፣

«'ጨንጌ' ደግሞ የጫት ባለጌ ነው። እሱን የቃመ ያው ነው። ማበድ፣ ሌሊቱን ሙሉ፣ በተለይ ለሴት ...»

«'ቁጦ' ግን ሰላማዊ ነው። ምግብ ማለት ነው። እኔ በበኩሌ አልወደውም።»

«'አወዳይ' ውድ ነው» አለች ሀና «... ልጥጦች ጉራቸውን የሚነሰንሱበት ካልሆነ አወዳይ ከማንም አይበልጥም»

«'ጉንችሬ' ደም ይመጣል። መዥገር ማለት ነው።»

አሳዎ - ሰልክ - ቡስጣኒ - እያሉ ሲያብራሩላት ሀወኒ በመደነቅ ነበር የምታደምጣቸው።

ይህን በመሰሉ ጨዋታዎች ሁለት የእስር ቤት ቀናት አለፉ ...

ሶስተኛው ቀን ተወለደ። ሀወኒ ለማዳመጥ ተዘጋጀች። ወጣቶቹ ግን እየተቀባበሉ በማውጋት ፋንታ በዝምታ ይተያዩ ጀመር፣

«አጫውቱኝ እንጂ?» አለቻቸው።

«ምን?» አሉዋት።

«ገጠመኞቻችሁን።»

«ጨርሰናል» አሉ።

«በቃ?» ብላ በመገረም ታያቸው ጀመር::

«የጫቱን እንድገምልሽ?» አለች ሀና::

«መድገም እንኳዋ ይሰለቻል:: ሌላ ያልነገራችሁኝ ካለ?» አለች - ሀወኒ::

ወጣቶቹ ማሰብ ጀመሩ::

ሀና አንድ የረሳችውን ማስታወስ ቻለች::

ናዝሬት አጐትዋ ዘንድ ለእረፍት የሄደች ጊዜ ምኒልክ በሚባለው ጣሳ ሙሉ ጠጅ መጠጣትዋን አነሳች:: ጠጁ ግን ወደራስዋ ሄዶ ከማሞቅ ይልቅ ቁልቁል ወርዶ ሁለት ጉልበቶችዋን እንደመዘመዛት ተናገረች:: ይህንኑ ለአጐትዋ ስትነግረው ሆዱን በሁለት እጆቹ ይዞ ግማሽ ሰአት ያህል እንደሳቀ አስታወሰች:: ጠጁ መዘዘኛ እንደነበረ ጭምር በቁጭት አነሳች:: በወቅቱ የፍቅር ጉዋደኛዋ ለነበረው ለአንድ የአማርኛ መምህር ልጅ ምኒልክ በሚባለው ጣሳ ሙሉ ጠጅ መጠጣትዋንና ሁለት ጉልበቶችዋን እንደመዘመዛት ስትነግረው በመሳቅ ፈንታ ተቆጥቶ 'ያገኘሽውን ሁሉ የምትሰረግቢ ልክስክስ' ብሎ እንደሰደባት፤ ምንም እንኳዋ ስድቡ ቢከነክናትም 'መሰርገብ ምን ማለት ነው?' ብላ እንደጠየቀችው፤ እርሱም 'ሂጂና የደስታ ተክለወልድን መዝገበ - ቃላት ተመልከቺ' እንዳላት ተረከች:: በዚሁ ሰበብ እንደተጣሉ፤ ሁዋላ ግን የጥላቸው መንስኤ ጠጁ ሳይሆን አንዲት የልጥጥ ልጅ አፍቅሮ መሆኑን እንደደረሰችበት፤ በዚህም ተናዳ 'ይመችህ!' እንዳለችው ዘረዘረች::

የሁለቱ ወጣቶች የመጨረሻ ትረካ ይኸው ነበር ...

በአራተኛው የእስር እለት ማለዳ መሰለቻቸት በመጀመራቸው፤ ሀወኒ ታሪክ መስማት ይወዱ እንደሆነ ጠየቀቻቸው:: ሁለቱ ወጣቶች ታሪክ ቀርቶ ቀርቀሮ ሲንኩዋኩዋ ቢሰሙ እንኩዋ እንደሚደሰቱ ገለፁላት::

ሀወኒ ያነበበቻቸውን መፃህፍት ለእነርሱ በሚስማማ መልኩ እያጣፈጠች ትተርክላቸው ጀመር::

## - 5 -

ከቡርቃ ግጭት በሁዋላ በተለያዩ የአርሲ አካባቢዎች በኦሮሞና በአማራ ገበሬዎች መካከል መጠነ ሰፊ ግጭቶች ይከሰቱ ጀመር:: ቃጠሎውና ደም መፋሰሱ ወደ ሳጉሬ - ጉና - አርባጉጉ - በቆጂ -ጐሮ - አገልጆ - ጃራ - ተዛመተ:: የመከላከያ ሰራዊት ግጭቶችን ለማስወገድ ከወዲያ ወዲህ መወርወር ዋነኛ ስራው ሆነ:: አርሲ በርግጥም የእሳት እቶን ሆነች::

የእግዚአብሄር አገልጋይ ከሆኑት አማልክቶች አንዱ የጋዜጠኝነትን ሚና ወስዶ ሁኔታውን ቢዘግብ ኖሮ መቸም እንዲህ ባለ ነበር፤

አርሲ ትታየኛለች ...

ገበሬዎች የጦር መሳሪያ ይዘዋል:: እሳት በፊታቸው ያስቀደሙ ጦረኞች በፈረሶቻቸው ሽምጥ ይጋልባሉ:: ተራሮች በነበልባል ተያያዙ:: ጠመንጃዎች አቅራሩ:: ሽምላ አብለጨለጨ:: የሰው ስጋ እንደ ሰም ቀለጠ - አፅሙ እንደ ዱቄት::

ጢስ ይታየኛል ...

ህይወት አሽልባለች:: በድን አካል ይጤሳል:: ህፃናት እንደሳር ደረቁ:: ገበሬዎች እንደ ጉጉት በፈረስ ቤት ተቀምጠዋል:: ሰዎች በሰዎች ላይ አሴሩ:: ራሳቸውን አዋቂ አድርገዋል:: እንደ ናቡከደነፆር ታብየዋል::

ገበሬዎች ይታዩኛል...

በማያውቁት፤ በማይመለከታቸው፤ ሳንጃ ለሳንጃ ይሞሻለቃሉ:: ደኖች እየጋዩ ነው:: ሀብታሙ ምድር ምድረ በዳነትን ናፈቀ:: እንደ ከበረ እንቁ የሚያብለጭልጩ ሳንጃዎች ወደ ሰዎች ሆድ ጠለቁ:: ልብ ፈረጠ:: የሰው ልጆች አካል የሸረሪት ድር መሰለ:: ጉልማሶች አሸለቡ:: ክብረት የጠነከረ ክንዳቸው ዛለ ...

ጭካኔ ይታየኛል ...

ቅጥፈት ይሰማኛል ...

ቆነጃጅት ሹሩባ አልተሰሩም:: መንደሮች አና ሆነዋል:: ኩበሌዎች ዘገር እየነቀነቁ ወደሚዳው እየገሰገሱ ነው:: ጐጆዎች በእሳት ስለተያያዙ ህፃናትና ሴቶች ገተታቸውን እየጐተቱ ተሰደዱ:: በአቅመ ደካሞች የተጨማደዱ ጉንጮች ላይ የእንባ ዘለላዎች ተንከባለሉ:: በአይኖቻቸው የቁጣ ነበልባል የሚተፉ፤ በየእጆቻቸው ካራ የጨበጡ፤ ከጉሮሮአቸው ደም እንደ አባይ ወንዝ የሚፈስ የቆሰሉ ነብሮች ይታዩኛል:: ይጠራጫሉ! ያጉዋራሉ!

የምእመናን ሰፈሮች ነደዱ:: መስጊዶች ተደረመሱ:: ቤተክርስትያናት በእሳት መላስ ተበልተው አመድ ሆኑ:: አርሲ

በጭንቅ ተይዛለች:: ሰደምና ጉመራን ታስታውሳለች::

እስኩ እነሆ ያቻትና!

ጉጆዎችዋ በእሳት ተያይዘዋል:: ከሰማንያ አምስት ሺህ በላይ ገበሬዎች ጉጆአቸውን ለቀው ተራሮቿን አልብሰውታል:: አራት ሺህ ያህሉ አማራዎች ናቸው - የቀሩት ደሞ ኦሮሞዎች:: ይላቀሳሉ:: ዋይታ ያሰማሉ:: ጉጆዎቻቸው ለምን እንደጋዩ አያውቁም::

እነሆ ጀጁ ትታየኛለች ...

የእሳት መላስ፤ የጥይት ቀረርቶ እያንቀጠቀጣት ነው:: ሰድሳ ሺህ ገበሬዎች ከነበልባሉ ለማምለጥ አውጭኝ እግሬ ሲሉ ይታዩኛል:: አርባ ሺህ ያህሉ ኦሮሞዎች ናቸው - የቀሩት አማራዎች::

መርቲና ጉናም ይታዩኛል ... በሺህዎች የሚቆጠሩ አማራና ኦሮሞ ገበሬዎች መንገዱንና ተራራውን ሞልተው ይጉዋዛሉ:: መድረሻቸውን አያውቁም:: ይራገማሉ:: ማንን እንደሚረግሙ ግን አያውቁም:: ዋይታ ያሰማሉ:: የእሪታቸው ድምፅ ሰማይ ጥግ ደረሰ:: ልብ የሚነካ እሪታ...

የለቅሶ ሸለቆ ይታየኛል ... አባራሪና ተባራሪ ይታዩኛል:: ተደበላልቆአል:: ተባራሪው አባራሪ ጭምር ነው:: አባራሪው አባረርኩ ይላል እንጂ ተባራሪ ነው ራሱ:: ቅጣንባሩ የጠፋ፤ ውል አልባ ትእይንት እነሆ:: ከአዳኞች እንዳመለጠች ሚዳቋ - የሚረግጡትን የማያውቁ፤ ወደቶሰሉት ነብሮች ይከንፋሉ:: የእሳት ራት ለመሆን ቸኩለዋል:: እልልታ ይሰማል - ዋይታም::

ምላሳቸውን እንደ እባብ የሳሉ፤ ከከንፈራቸው በታች የእፉኝት መርዝ የቀበሩ ሰዎች አበባ እንደሚቀስም ንብ ውር ውር ሲሉ ይታዩኛል:: ፍላፃው አልነካቸውም:: 'ከደሙ ንፁህ ነን' ይላሉ:: 'ለእውር አይን - ለአንካሳ እግር - ለደሀው አባት ነኝ' የሚል በረከተ:: መሰንቆ ለሀዘን ፣ እምቢልታም ለትካዜ መሆኑ ቀረ ...

በዚህ ታላቅ አደጋ ዙሪያ የፖለቲካ ድርጅቶች ርስበራስ ይወነጃጀሉ ያዙ::

ኢህአዴግ «በሁለቱ ብሄሮች መካከል የቆየ መሻከር ቢኖርም ለግጭቱ በዚህ መልኩ መከሰት የኦነግ እጅ አለበት» ሲል ገለፀ::





መግለጫው አያይዞ «... ኦነግ ከግጭቱ ፖለቲካዊ ጥቅም ለማግኘት አልሞ የነበረ ቢሆንም ውጤቱ ግን ህዝቡን ጉድቶአል:: ኦነግ የሰላምን መንገድ ያለመፈለግ ዝንባሌው ወደአደገኛ ደረጃ እየተሸጋገረ ነው...» ሲል አስጠነቀቀ::

መአህድ በበኩሉ «ግጭቱን ያስነሳው የኢህአዴግ የጉሳ ፖሊሲና የኦነግ ዘረኝነት ነው» ሲል መግለጫ አወጣ:: በመግለጫውም «በአርሲ የሚኖሩ የአማራና የኦሮሞ ገበሬዎች ላለፉት መቶ አመታት እጅና ጉዋንት ሆነው በፍቅር ኖረዋል:: አሁን በተነሳው ጠብም ዋነኛ ተጠቂ አማራው ነው» ሲል እሪታውን አሰማ::

ኦህዴድ ደግሞ፣

«የአማራውም ሆነ የኦሮሞው ጉዳት እኩል ነው የሚሰማን» ሲል መግለጫ አወጣ «... ምክንያቱም በሁለቱም ወገን የተጐዱት ጭቁኖችና ንፁሀኖች ናቸው:: የዚህ እሳት አቀጣጣዮች የአደጋው ሰለባ አልሆኑም:: እነሱ እዚህ ፊንፊኔ ቁጭ ብለው፤ አዳማ ላይ ቂብ ብለው አርባጉጉ ላይ እሳት ይለኩሳሉ:: አውሮፓ ቁጭ ብለው በክልሉ ላይ እሳት ይጭራሉ:: ገፈት ቀማሽ የሆኑት ሁለቱ ህዝቦች ናቸው:: ስለዚህ በሁለቱም ህዝቦች ላይ የደረሰው ጉዳት እኩል ይሰማናል:: በአማራው ላይ ብቻ ጭፍጨፋ ተፈፅሞአል ብሉ መአህድ የሚያቀርበውን ግን ፍፁም አንቀበለውም» አለ::

ኦነግ ደግሞ በፊናው፣

«ግጭቱን እኔ አልቀሰቀስኩም:: ጠመንጃም አላደልኩም:: የኦሮሞ ህዝብ ብሶት በራሱ ሀይል ፈንድቶአል:: ከእንግዲህ ደግሞ መቆሚያ ላይኖረው ይችላል» ሲል አስጠነቀቀ::

በርግጥ የሽግግር መንግስቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከእንካሰላንትያው ይልቅ የተፈናቀሉትን ገበሬዎች መልሶ ወደማቋቋቋም ተግባር አደሉ:: አስቸኩዋይ በጀት ተመድቦ የማረጋጋቱ ስራ በሰፊው ቀጠለ::

- 6 -

ቀናት በመልካም ሁኔታ ተገፉ ...

ሀወኒ ያነበበቻቸውን መፃህፍት ትዘረግፍላቸው ቀጠለች:: የቶልስቶይ - የዶስቶዮቭስኪ - የቼኾዋ አቼቤ - የኤርቪንግ ዋላስ - የጐርኪይ - የቼሆቭ ጠቦች - ምን የውጭ ብቻ ... የሀገር ውስጡም አልቀረ:: ካድማስ ባሻገር - አንድ ለናቱ - አልወለድም - አንድ ባንድ ተተረኩ:: ያልታተሙ ታሪኮችም አልቀሩዋት:: ስለካፋው ጋዜ

ሻረቻ አይበገሬነት - ስለአርሲ ኦሮሞዎች ተጋድሎ - የጨሰንቆ ጦርነት - የአኖሌ ጭፍጨፋ - ሁሉንም በየተራ አወጋቻቸው:: የሀየሎም አርአያ ስም ጭምር ተነሳ:: አግአዚ በተባለ ኦፕሬሽን ከመቀሌ እስር ቤት እንዲያመልጡ ስላደረጋቸው 1500 እስረኞች ስትተርክ አይናቸውን አፍጠው ትንፋሻቸውን ውጠው አዳመጡ::

ቀኑና ሌሊቱን መለየት እስኪሳናቸው ድረስ በሀወኒ ትረካ ተጠመዱ:: ሀወኒ በታሰረች በአስረኛው ቀን ማለዳ ትረካዋን አቁማ ወግ ጀመረቻቸው፣ ስለደከማት እረፍት ለማድረግ ያህል ነበር ያቋረጠችው፣

«በዚህ ሳምንት ካወራሁላችሁ ታሪክ የበለጠ የወደዳችሁት የትኛውን ነው?» የሚል ጥያቄ አቀረበችላቸው::

መስከረምና ሀና ይተያዩ ጀመር:: ሲያመነቱ ጥቂት ቆዩ:: ሀና ነበር ቀድማ አስተያየት የሰጠችው፣

«ፍቅረኛ ያጣችው አስቀያሚ ሴት ታሳዝናለች» አለች::

የጉርኪይን አንድ አጭር ልቦለድ ተርካላቸው ነበር::

«ግን እንደምንም አንድ መጥበስ እንዴት ያቅታታል?» የሚል ጥያቄ ለሀወኒ ያቀረበችው መስከረም ነበረች::

ሀወኒ ፈገግ አለች፣

«አልቻለችም» ስትል ታስረዳቸው ጀመር «... ምክንያቱም አንዳችም የሚስብ ነገር ገፅታዋ ላይ አልነበረም:: ታስፈራለች:: አይኖችዋ በሽተኞች ናቸው:: እግሮችዋና እጆችዋ ከተለመደው በላይ ወፋፍራሞች ነበሩ:: አፍንጫዋ የተዳመጠና ቀዳዳዎቹም ጥቃቅኖች ነበሩ:: ስለዚህ ወንዶች ሁሉ ሸሹዋት ...»

«ምን ሆና ነው ግን?» ስትል ጠየቀች - ሀና::

«ተፈጥሮ::»

ሀናና መስከረም በሀዘን ተዋጡ::

«ሌላስ የቱን ታሪክ ወደዳችሁት?»

«እስረኞችን ከመቀሌ እስር ቤት ያስፈታው ሰውዬ ታሪክም በጣም ደስ ይላል:: ግን እሱ ለምንድነው እንዲህ የሚለፋው?» አለች መስከረም::

«ለህዝብ ብሎ ነው» አለቻቸው ሀወኒ «... ህዝብ ሲባል ደግሞ እኔና እናንተንም ይጨምራል:: ለኛ ብሎ ነው





የሚታገለው::»

«እኛን የት ያውቀናል?» አለች ሀና::

«ፖለቲካ ታውቃላችሁ?» ስትል ጠየቀቻቸው::

ሁለቱ የአራት ኪሎ ወጣቶች ተያዩ:: ጥያቄው ከበዳቸው:: መስከረም ደፈር ብላ ለመመለስ ሞከረች፣

«ፖለቲካ ማለት በሬዲዮ የሚነገረው አይደለም?»

ሀወኒ በፈገግታ ተጥለቀለቀች፣

«ፖለቲካውን ተውት ደህና:: ስለደርግ ምን ታውቃላችሁ?»

ይሄ ጥያቄ ግን አልከበዳቸውም:: ይልቁን ምላሽ ለመስጠት ይሻሙ ጀመር፣

«ደርግማ መንጌ ናት!» አለች ሀና::

«መንጌ ደሞ ዝምቡዋቡዋ ጎበታለች!»

ይህን ካሉ በሁዋላ በተራቸው ደግሞ ለሀወኒ ጥያቄ ያቀርቡላት ጀመር፣

«አንቺ ግን ይሄን ሁሉ ታሪክ እንዴት በቃልሽ ያዝሽው? ማነው የሚነግርሽ?»

«አነባለሁ:: አንዴ ያነበብኩትን ደግሞ አልረሳም» ስትል መለሰች::

«አቻዮ ዲፈሮ ነሽ» አለቻት ሀና::

«ምንድነው አቻዮ ዲፈሮ»

«ሀርደኛ ማለት ነዋ!» አለች መስከረም::

ሀወኒ በእስር ቤት ጉዋደኞችዋ አነጋገር ትዝናና ጀመር:: ጥያቄአቸውን ቀጠሉ፣

«የምትነግሪንን ታሪክ ያነበብሽው ቡስጣኒ ቅመሽ ነው?»

«እኔ ጫት ቅሜ አላውቅም»

«ታዲያ እንዴት ለመድሽው?»

«ምኑን?»

«ድብርቱን ነዋ!»

«የምን ድብርት?»

«ቀኑን ሙሉ ምን ትሰሪ ነበር ታዲያ?»

«ስራ አለኝ:: እሰራለሁ::»

«ማን አገኘልሽ?» ሲሉ በአንድ ቃል ጠየቁዋት::

«ከዩኒቨርስቲ እንደጨረስኩ መንግስት ራሱ ስራ ሰጠኝ» ስትል መለሰችላቸው::

«ዩኒቨርስቲ ተምረሻል እንዴ?» ሲሉ በመገረም ጠየቁዋት::

«አዎን!»

«ጭረሻላ!» ሀና ነበረች::

«ምንድነው 'ጭረሻላ' ሀኒ?»

«ሀፒ መግጨት አታውቂም?»

ሀወኒ በሳቅ ትዘምር ጀመር:: ተቃቅፈው ባንድ ቃል እየተረዳዱ ሲያወሩ ሀወኒ በእጅጉ ተገረመች:: ሳቅዋን ማቁዋረጥ ጭምር አቃታት:: ሁለቱ ወጣቶች የሀወኒ የሳቅ መንስኤ ስላልገባቸው በመገረም ሲያስተውሉዋት ቆይተው፣

«አንቺ ግን 'ፋይን' ነሽ» የሚል አስተያየት ሰጡዋት::

«እንዴት?»

«ሳቅሽ እንደልብ ይመጣልሻል:: እኛ ግን የሚያስቅ ነገር ካላገኘን ብንሞት አንስቅም::»

«እናንተን የሚያስቃችሁ ምንድነው?» ስትል ጠየቀቻቸው::

«እኛ በብዛት የምንስቀው ፋዘሮቻችን ሲነቅሉ ነው::»

«ምንድነው የሚነቅሉት?»

«ስካር ነዋ!» አለች ሀና::

«በአባታችሁ ስካር መሳቅማ ነውር ነው::» አለች ሀወኒ::

ሁለቱ ወጣቶች ግን የሀወኒን ተግሳፅ ተቃወሙ፣

«ሲነቅል ባየሽው» አለች መስከረም ... «ቤታችን ከዩኒቨርስቲው አጥር ጋር ስለሚያያዝ አጥሩን ተደገፉ ይለናል::»

«ለምን?»





«ትምህርት እንዲገባን ነዋ!» እያሉ በሳቅ ይንፈራፈሩ ጀመር::

«እስከ ስንተኛ ክፍል ተምራችሁዋል!» ስትል ጠየቀቻቸው::

«እስከ ስምንት» ሲሉ መለሱ::

«ለምን አቆማችሁ ትምህርታችሁን?»

«ጭንቅ አንወድም» አሉ ባንድ ቃል::

ከዚህ በሁዋላ ሀወኒ ታሪክ ማውራትዋን ቀጠለች ...

ወጣቶቹ በጣም ከመገረማቸውና ሀወኒ በምታወራላቸው ታሪክ ከመመሰጣቸው የተነሳ እንደ ልዩ ፍጥረት ቆጠሩዋት:: ያን ሁሉ የአስገራሚ ታሪክ ጉድ በጭንቅላትዋ መያዝ በመቻልዋም አደነቁዋት:: ከተፈጠሩ ጀምሮ እንደዚህ አይነት ችሎታ ያለው ሰው ማየት ቀርቶ ይኖራል ብለው ገምተው እንኩዋ እንደማያውቁ አረጋገጡላት::

በአርባ ሁለት አመታቸው ከእስር እንደሚፈቱ አንስተው መሳቀሱን ረሱት:: ሀወኒን እንደ ፈጣሪ አመለኩዋት:: ከቤተሰብ ከሚመጣላቸው ምግብ እየተሻሙ ያጉርሱዋታል:: መሀላቸው አድርገዋት ይተኛሉ::

# ኢንተለቶ ሀወኒ

# ኤሳ ጅርታ!?

## ምእራፍ አስራ አራት

### - 1 -

አስደንጋጭ መርዶ!

አንድ አሸማቃቂ ዜና ከቡርቃ ገበሬዎች ዘንድ ደረሰ። ይህም የአኖሌ መሞትና የሀወኒ የመታሰር ዜና ነበር። ይህ ወሬ ቡርቃ የደረሰው በጀንበር ግባት ነበር። ወሬው እንደተሰማ የሴቶች ጉንጭ በእንባ ታጠበ። እንዲህ እያሉም ሲጣሩ ተሰሙ፤

«ኢንተለቶ ሀወኒ ... ኤሳ ጅርታ!?»

በዚያን እለት ምሽት ቡርቃ ላይ ያልተለመዱ ክስተቶች ታዩ:: ጨረቃዋ ደማቅ ቢጫ ሆና ወጣች:: ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ወደ ምድር ቀረብ ያለች ጭምር መሰለች:: በአድሜ የገፉ ገበሬዎች ታዲያ ከተፈጠሩ ጀምሮ ጨረቃዋን በዚህ መልኩ አይተዋት እንደማያውቁ እየማሉ ተናገሩ::

ምን ይህ ብቻ!

እንደ በረዶ የነጡ ከወደ ደቡብ የመጡ ዳክዮች ማምሻውን ሰማዩን ሞልተው በከፍተኛ ድምፅ እያስካኩ፣ በክንፎቻቸው አየሩን እየቀዘፉ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሲነጉዱ ታዩ:: በርግጥ በበልግ ወራት ይህን መሰል የዳክዮች ጉርፍ ማየት ያልተለመደ አይደለም:: የዛሬዎቹ ግን መጠናቸው ጨምሮአል:: ሰማዩን ሞልተው፣ ደሴት መስለው ቢጫዋን ጨረቃ መጋረድ ጭምር ቻሉ:: የቡርቃ ሰማይም የጨለመ መሰለ::

የቡርቃ ገበሬዎች እኒህን ልዩ ክስተቶች በቀጥታ ከሀወኒ መታሰርና ከአኖሌ መሞት ጋር አያያዙዋቸው:: ዳክዮቹ በከፍተኛ ድምፅ ሲንጫጩ ተሰሙ:: ይህ አስፈሪ የዳክዮች ድምፅ ለገበሬዎቹ ልዩ ትርጉም ሰጣቸው:: ለአያሌ አመታት እንደሚፈፅሙትም ሀማጋው ላይ ሰብሰብ አሉ:: ዳክዮቹ 'የዋቀዮ መልዕክተኞች ናቸው' ሲሉ ተጨዋወቱ:: የሚጠበቀው ታላቁ ጦርነት የሚጀመርበት ጊዜ መቃረቡን በዳክዮቹ ድምፅ መገንዘብ እንደሚቻል አወቁ:: በተለይም ሽማግሌዎቹ የቡርቃን ዝምታ ማብቃት ሳያዩ ሞት እንዳይቀድማቸው አምላክን ተማፀኑት:: የቡርቃ ገበሬዎች በዚያን ዕለት እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ የሚወዱዋቸውን ልጆቻቸውን ስም በማነሳሳት ቀረርቶና ሽሎታ አሰሙ::

በተሰበሰቡት ገበሬዎች መካከል በሽማግሌነታቸው የሚከበሩት አባቦሩ ነበሩ:: በመሆኑም በቀረርቶው ማሳረጊያ ላይ ንግግር ሊያሰሙ ብድግ አሉ::

«... ውድ ወገኖቼ!» ሲሉ ነበር የጀመሩት «... በቅርቡ የተነሳው ግጭት አያሌ የመንደራችንን ጉብዞች ቀጥፎአል:: እንደ አይናችን ብሌን የምንወደው ልጃችን አኖሌም እነሆ ሞተ:: የምንወዳትና ከአይናችን ብሌን በላይ የምንሳሳላት ልጃችን ሀወኒም ከዳግም - ነፍጠኞች የጨለማ ቤት ተወርውራለች ...»

የአባቦሩ የሚንቀጠቀጥ ድምፅ በቡርቃ ደን አናት ላይ ተጥለቀለቀ::





«... የቡርቃ ዝምታ ቀጥሎአል ወገኖቼ! የነካ ተራራ ጫፍ ላይ ወጥተን መጮህ አለብን:: ድምፃችንን በኦሮሚያ ምድር ሁሉ ማስተጋባት ይገባናል:: ኦሮሞዎች ሁሉ ቡርቃ ላይ ይሰብሰቡ:: ወገኖቼ! ልጃችን አኖሌ ለኛ ሲል በግፍ ተገድሎ፣ ሀወኒ ልጃችን ጨለማ ቤት ተወርውራ እኛ ወደ አፋችን እህል ይቀርባል!? ወፍራም ወተት ወደ ጉሮሮአችን ይንቆረቆራል? ንገሩኝ ወገኖቼ!?»

ሆርዶፋ እየተንሰቀሰቀ ሲያለቅስ ተሰማ:: ይህም ለቡርቃ እንግዳ ታሪክ ነው:: በጀግንነቱ ከተመሰገነው ከሆርዳፋ አይኖች እንባ ኩዑ እንዴት ይታያል?

አባቦሩ ንግግራቸውን ገታ አደረጉ:: በምትኩ የአራዊት ድምፅ ይሰማ ቀጠለ:: ከወፍራም ዛፎች ከርስ ውስጥ የተቆለለውን ቀይ ማር እየላሱ የሚንዣዣ ድምፅ የሚያሰሙ ነፍሳት::

«... ተስፋና ትእግስት አይለያዩም ወገኖቼ! የኛ ግን ትእግስታችን በዛ:: ተስፋችን ጤዛ ሆነ:: በለሰለሰ መስኮችን ላይ እየተንደባለልን ያለፋይዳ ማለፋችን ኩዑ እስከመቼ ይሆን ወገኖቼ!?»

ገበሬዎቹ ጠመንጃዎቻቸውን እያቀባበሉ ተኩሱን ያቀልጡት ጀመር:: ችቦዎች ተለኮሱ:: የሚንቀለቀል የእሳት ነበልባል ሀማጋውን ወገግ አደረገው ...

አኖሌና ሀወኒን አስመልክቶ ወሬውን ቡርቃ ላይ የነዛው ከፊንፊኔ መጣሁ' ያለው ጠጉረ ልውጥ ሰው እንዲህ ሲል ነበር ዜናውን ያዳረሰው፣

... አኖሌን ሌሊቱን ከአባቦኩ ኮረብታ ላይ ከማረኩት በሁዋላ - መንገድ ላይ ገድለው ዱር ውስጥ ቀበሩት:: ሀወኒን ደግሞ በሰንሰለት እጅና እግርዋን አስረው ጨለማ ቤት ውስጥ ቀረቀሩባት:: እርስዋንም በቅርቡ ይገድሉዋታል ...

- 2 -

.. በአስራ ሰባተኛው የእስር ቀን ሀወኒ እቃዎችዋን ጠቅልላ ወደ ክንፈ ገብረመድህን ቢሮ እንድትሄድ ተነገራት:: ይህን ዜና ይዛ ወደ እስር ጉዋደኞችዋ ስትመለስ በሀዘን ተውጣ ነበር:: ለወጣቶቹ አዘነች:: ላታገኛቸው ክፉ ልማድ ውስጥ እንደከተተቻቸው አሰበች:: ምርጫ ግን የላትም:: ከእስር መፈታትዋን ነገረቻቸው:: ሁለቱ ወጣቶች የሰሙትን ባለማመን ደንገዘው ፈገዘውና ባሉበት ደርቀው አይን አይንዋን ያዩዋት ጀመር:: ድንጋጤው ሲያልፍላቸው ግን ተቃቅፈው እዬዬአቸውን ያቀልጡት ጀመር:: ከእስር የሚፈቱት በአርባ ሁለት አመታቸው

እንደሆነ አስታወሰ። ሀወኒ ሆድ ቢብሳትም ቻል አድርጋ አፅናናቻቸው። ልብሶችዋንም ከሻንጣዋ አውጥታ አከፋፈለቻቸው። ጋቢዋን ተወችላቸው። እየመጣች እንደምትጠይቃቸው ጭምር ቃል ገባችላቸው። እንባቸውን እየጨማመቁ ኩርምት ብለው አይኖቻቸውን ከአይንዋ መንቀል አቃታቸው፣

«በሉ ደህና ሁኑ እህቶቼ። እወዳችሁዋለሁ» ስትል የሞት ሞትዋን ተነፈሰች።

መስከረም እንደምንም አንድ ነገር መናገር ቻለች፣

«የስንብት አንድ ታሪክ አውሪልን?»

ሀወኒ ሻንጣዋ ላይ አረፍ አለች።

«ሳልነግራችሁ የቀሩት ታሪኮች እጅግ ረጃጅም ናቸው። በሶስት ቀን ትረካ እንኳዋ አያልቁም። እነርሱን ለማውራት አሁን ጊዜ የለንም»

«ከአጫጭሮቹ አንዱን ድገሚልን» አለች ሀና።

«ሀየሎም እስረኞችን ከመቀሌ እስር ቤት እንዴት እንዳስለቀቀ ንገሪን!» አለች መስከረም፣ ፊትዋ ላይ ድንገት ተስፋ እያንፀባረቀ።

«እሱ ረጅም ነው» አለች ሀወኒ።

ከዚያ እየተቀባበሉ ያማርጡዋት ገቡ።

«ወይም በአንድ ክንድ መሬት ስለተቀበረው ገቤጋባ ሰው ታሪክ አውሪልን»

«የየዋሆቹን ቻይናውያን አባትና ልጅ ታሪክ ድገሚልን»

«የዱብሮቭ.ስኪይም ቢሆን ጥሩ ነው»

«ወይም የፑካቼቭ!»

«ስለሩህሩሁ ወንጀለኛ ሴማጋ ይሻላል»

«ወይም ፍቅረኛ ስላልነበራት መልከጥፉዋ ሴት»

«ካልሆነ ደሞ ለእግዚአብሄር ደብዳቤ ስለላከው ቅን ሰው»

«ስለ አማር ሴት ልጅ!»

«ለሚስቱ ከባድ ፈተና ስላዘጋጀው ቂል ግሪካዊ!»

ከዚህ ቀደም ያወራችላቸውን ታሪኮች እያነሱ ይንጫጩባት





ጀመር።

በመጨረሻ እንዲህ አለቻቸው፣

«እስከዛሬ ያወራሁላችሁ የሰው ልጆችን ታሪኮች ነው። ለመሰናበቻ ግን 'ጥፋት ፈፅመው የዘልአለም እስር ስለተፈረደባቸው አማልክት አወጋችሁዋለሁ' ስትላቸው ሁለቱ እስረኞች በደስታና በጉጉት ሊያዳምጡ ተዘጋጁ።

«ይህ ታሪክ በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ የሰፈረ ነው - በኦሪት ዘፍጥረትና በይሁዳ ላይ» ብላ ትረካዋን ጀመረች «... ከብዙ ሺህ ዘመናት በፊት፣ ምናልባትም ከብዙ ሚልዮን አመታት በፊት ... ስሙ እግዚአብሄር የተባለው የሰው ልጆች ፈጣሪ አማልክትን ለአንድ ተግባር ወደ ምድር ላካቸው። አማልክቱ እንደወትሮው የሰው ስጋ ለብሰው ወደ ምድር ወረዱ። የታዘዙትን ለመፈፀም በምድር ሲመላለሱም እጅግ ውብ የሆኑ ቆነጃጅት አዩ። ቆነጃጅቱ የሰው ልጆች ናቸው። አማልክቱ ግን አይተው ማለፍ አቃታቸው። ልክ እንደሰው ልጅ አሰቡ። 'እሸትና ቆንጆ አይታለፍም' የሚለው ተረትም ያንጊዜ ሳይሆን አይቀርም የተጀመረው። አማልክቱ ለየራሳቸው አንዳንድ መርጠው የወሲብ ጥማታቸውን አረኩ። 'ሀብታሞችና ባለስልጣኖች እንደሚያደርጉትም እጅግ ውብ የሆኑትን ነበር የመረጡት። ቆነጃጅቱም ከአማልክቱ ፀነሱ። የተፀነሱት ደግሞ ተወለዱ። ታዲያ የተወለዱት ልጆች በአባታቸው አማልክት በመሆናቸው፣ ሃይለኛ፣ ግዙፍና እንደ አባቶቻቸውም መንፈስ ያደረባቸው ሆኑ። እግዚአብሄር በዚህ ክፉኛ ተናደደ። ለአማልክቱ ብቻ የሰጣቸው መንፈስ ወደሰው በመተላለፉ ተቆጣ። ስለዚህ እኒያ ዝሙት የፈፀሙትን አማልክት ባስቸኩዋይ ወደ ሰማይ ጠርቶ 'ዘልአለማዊ' ወደተባለ እስር ቤት ከተታቸው። በሰንሰለት ታስረው በጨለማ ውስጥ እንዲኖሩ ፈረደባቸው። ከአማልክቱ የተወለዱት ልጆችም ዘራቸውን ከማባዛታቸው በፊት በጥፋት ውሃ ዘመን እንዲሞቱ አደረገ። ዝሙት የፈፀሙት አማልክት ግን አሁን ድረስ በጨለማ እስርቤት ተቀምጠዋል። እንግዲህ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ልክ እንደኛ ተረት እያወሩ ሊሆን ይችላል። ግን ያን ሁሉ ዘመን እንዴት ተረት ያወራሉ? ተረቱስ ከየት ይመጣል?» ብላ ፈገግ አለች።

ሀና ፊትዋ ላይ አመድ የተረጨ መሰሉ፣

«አማልክትም ጥፋት ይፈፅማሉ?» ስትል ጠየቀቻት።

«እንኩዋን የሰው ልጆች አማልክትም!» አለቻቸው።

ሀወኒ ቃልዋን ፈፅማለችና እየሳሙ ተሰናበቱዋት። ሀወኒ ከሄደች

በሁዋላ ብቻቸውን ቀሩ። ጉንጮቻቸውን መዳፎቻቸው ላይ አስደግፈው በአሳብ ሩቅ ነጐዱ። ምን እያሰቡ ይሆን?

## - 3 -

ከመቀመጫው ወጥቶ በሞቀ ሁኔታ ነበር እቅፎ የሳማት። እስዋም ቢሆን ሙሉ ፈገግታዋን ቸረችው። እጅዋን ይዞ ወደ እንግዳ መቀበያው አረንጉዋዴ ፎቴዎች ወሰዳት።

«እስር ቤቱ እንዴት ነበር ታዲያ?»

«እውቀት አግኝቼበታለሁ» አለች በደብዛዛው ፈገግ ብላ።

«ትንሽ ከሳሽ ልበል?»

«ይሆናል»

«ምን አገኘሽ ታዲያ እስርቤት?»

«በመሞት ላይ ያሉ ሁለት ምስኪን ወጣቶችን ተዋወቅሁ። አይሮፕላን ለመጥለፍ የሞከሩ...»

ከንፈ አስታወሳቸው።

«በፍርሀት ብቻ በቅርቡ ይሞታሉ» አለች።

«አይሮፕላን መጥለፍ ፋሽን ሆነኮ። አደገኛ ድርጊት ነው። ለነገሩ የነርሱ ጉዳይ ያን ያህል ከባድ አይደለም።»

ቡና እየጠጡ በወቅታዊ ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ሲጨዋወቱ ከቆዩ በሁዋላ፣

«ለመስማት የጉዋጉዋሁባቸው ሁለት ጥያቄዎች አሉኝ፣ ከንፈ» አለች ድንገት።

«ምንድናቸው?»

«እኔን በተመለከተ አጣርተህ ጨረስክ?»

«አዎን!»

«ውጤቱስ?»

«ነፃ ነሽ።» አላት፣ ፈገግ ብሎ።

ሀወኒ በሙሉ ልብ «ይህ እንደሚሆን እምነት ነበረኝ» ካለች በሁዋላ፣

«ሁለተኛው የአኖሌ ጉዳይ ነው። እንዴት ሆነ?»





ከንፈ መልስ ሳይሰጣት ዘገየ።

«ንገረኝ ከንፈ። ምንም ቢሆን ንገረኝ? ሞተ!?»

«አላወቅሁም፣ ሀወኒ»

«ታውቃለህ፣ ንገረኝ» አለች ጫን ብላ።

«አምልጦአል ነው የሚባለው» አላት እርግጠኛ ባልሆነ ስሜት።

«አይመስለኝም።» አለች ሀወኒ «አኖሌ አባቦኩ ኩረብታ ላይ በሀየሉም ከተከበበ በሁዋላ ሊያመልጥ አይችልም። የሆነውን በግልፅ ንገረኝ? ሞቶም ከሆነ አትደብቀኝ። ስጠብቀው የነበረ ነው ...»

«እኔን ካላመንሺኝ ሀየሉም ይነግርሻል!» አላት ትክ ብሎ እየተመለከታት።

«ሞቶአል!?» ስትል መልሳ ጠየቀችው።

ከንፈ ግን ምላሽ ሳይሰጣት ቀረ።

ሀወኒ ፊትዋን በሁለት እጅዋ ሸፈነች። ለደቂቃዎች ያህልም ግንባርዋን ጉልበቶችዋ ላይ ደፋች። ከንፈ በዝምታ ሲያስተውላት ቆየ።

ሀወኒ ቀና ስትል ፊትዋ የተቃጠለ አፈር መስሎ ነበር።

«መረጃ ስለሌለኝ ምንም ልነግርሽ አልቻልኩም።» አላት ከንፈ።

«እድለ ቢስ ነኝ» ስትል ተነፈሰች «... አኖሌን ማጣት አልፈልግም ነበር።»

«ሀወኒ እመኚኝ። አኖሌ ከአባቦኩ ኩረብታ ማምለጡን ነው የማውቀው።»

«ከንፈ አትቸገር። ከኩረብታው ሊያመልጥ አይችልም። አኖሌ ሞቶአል። አሁን ሌላ ሌላውን እንጫወት።»

ወሬያቸውን ሊቀጥሉ ግን አልቻሉም። በየራሳቸው አሳብ ተጠመዱ። ከንፈ ነበር ፀጥታውን የሰበረው።

«እኔም እንዳንቺ ግራ ተጋብቻለሁ ሀወኒ። አኖሌ ሞቶአል የሚል እምነት ግን የለኝም»

ሀወኒ ምላሽ ሳትሰጠው ቀረች።

«አላመንሺኝም?» አላት መልሶ።

«አላመንኩህም:: አኖሌ እንደቡርቃ ወንዝ መሬት ውስጥ ካልተቀበረ በቀር በቂ መረጃ የግድ ታገኛለህ:: በደንብ ታውቃለህ:: ልትነግረኝ ግን አልፈቀድክም:: ምናልባት ምን ብለህ እንደምትገልፅልኝ ተቸግረህ ሊሆንም ይችላል:: የሆነ ሆኖ ግን የተጎዳ ስሜቴን ለማስተካከል መጣር አለብኝ:: እንዳልኩት አልታደልኩም:: አኖሌን አፈቅረው ነበር ...»

ጉንጭዋን ማጠብ የጀመረ እንባዋን አባበሰች:: ግን አልቻለችም:: ፊትዋን በሁለት እጆችዋ ጋርዳ እየተንሰቀሰቀች ታለቅስ ጀመር:: ክንፈ በዝምታ አስተዋላት:: ከደቂቃዎች መንሰቅሰቅ በሁዋላ መልሳ እንባዋን ማባበስ ጀመረች::

«ሀወኒ»

«እሀ»

«ራት ልጋብዝሽ?»

እሺታዋን ራስዋን በመወዝወዝ ገለፀችለት::

ቢሮውን ለቀው ወጡ::

በተጨናነቀው ትራፊክ ውስጥ እንደምንም ብሉ የደብረዘይትን መንገድ ያዙ::

«ወዴት መሄድ ፈልገህ ነው?» ስትል ጠየቀችው::

«አንድ ዝምተኛ ቤት አሳይሻለሁ - እንደ ቡርቃ» አላት::

«የቡርቃ ዝምታ አብቅቶአል» አለች::

«አኖሌ ግን እንዳላበቃ ያምናል::»

«ኦሮሞዎች ያደረጉት ወደር የሌለው ተጋድሎ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸውን ለማስከበር ነበር:: ራስን በራስ ማስተዳደር ማለት ግን የነፍጠኛውን ጨቋኝ ስርአት አስወግዶ የራስ የሆነ ጨቋኝ ስርአት መተካት ማለት አይደለም:: የኢትዮጵያ ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ስርአት ተዘርግቶአል:: ይሁን እንጂ የእድል ወይም የአጋጣሚ ነገር ሆኖ እንደሁ አላውቅም፤ አብዛኞቹ የዳይሉኡ አመራር አባላት ጥንካሬና ብልህነት ይጎድላቸዋል:: ኦሮሞነትም ያጥራቸዋል:: በራስ ያለመተማመን ስሜቶችም ይስተዋልባቸዋል:: ይህ እንግዲህ የኛ የኦሮሞዎች የራሳችን የውስጥ ጉዳይ ነው:: ሰለሞን ዲሳሳና እሱን መሰሎች በእውነተኛ የኦሮሞ ልጆች የግድ መተካት አለባቸው ...»





ክንፈ በቅጡ አስተዋላት::

«ከዚህ ባሻገር» አለች ሀወኒ «... መስተካከል ያለበት አንድ ጎደሎ ነገር ይታየኛል:: እኛ ኦሮሞዎች የአቢሲንያ ሰዎችን ሙሉ በሙሉ አምነን አብረን መኖር እንድንችል ያለሞግዚት ራሳችንን እንድናስተዳድር፣ ደባና ተንኮል ያልታከለበት፤ የይስሙላ ያልሆነ ክልላዊ መንግስት ... መመስረቱን እንድናምን ጥረት መደረግ አለበት:: ቢያንስ ... ቢያንስ ኦሮሚያን የሚመሩት ሰዎች ኦሮሚያንና የኦሮሞን ህዝብ በመውደድና በብቃታቸው ቢያንስ መታማት የለባቸውም::»

«አጋነሽዋል ሀወኒ:: ስለ አመራሩ በጠቅላላ ነው እየገለፅሽልኝ ያለሽው? ወይስ ስለ አንድ ወይም ሁለት ግለሰቦች?»

ፈገግ አለች ሀወኒ - የደከመ ፈገግታ::

ክንፈ መኪናውን ከአንዲት ትንሽ ግሮሰሪ ደጅ ላይ አቆማት:: ከግሮሰሪዋ ደጅ ላይ የተቀመጠ አንድ ሀፃን ድምፁን ከፍ አድርጐ ይዘፍናል፣

*«አንዲት ልጅ ነበረች፣*

*ከራር የሚሉዋት*

*ድንጋይ ላይ ተቀምጣ*

*በሰንበት ጠዋት፣*

*ድንገት አንጠልጥሎ*

*ነፋስ ወሰዳት::*

ክንፈ በረጅሙ ሳቀ::

«ምናሳቀህ?»

«ዘፈኑ ሳንቲ ነው»

«ለምን ለኔ?»

«አንዳንድ ጊዜ የስሜት ነፋስ ወዳሻው አግጣጫ ያላጋሻል»

ሀወኒ ክፉኛ ተቃወመችው፤

«አትሳሳት ክንፈ። እኔ ሀወኒ ዋቆ ነኝ! ነፋስ አንጠልጥሎ የትም አይወስደኝም። ሰለሞን ዲሳሳ አለቃዬ ነው'ኮ። በሚሊዮኖች የወገኖቼ ህይወት ላይ እየወሰነ ያለው ሀያ አራት ሰአት በቅንዝር ተወጥሮ የሚውለው ሰለሞን ዲሳሳ መሆኑን አትዘንጋ - ክንፈ! ይሄ ምን ማለት ነው? የተማረ ሰው እንዳይመጣባቸው የሚፈልጉ የዳዴኦሕ አመራር አባላት አሉ። ጥቂት አይደሉም። ከነርሱ ጋር መታገል ከባድ ነው። ከሶየለት ደርግ ጋር የምታደርገው ትግል ይቀላል። የውስጥ መጠላለፍ ግን አደገኛ ነው። መንፈሱ ስስ የሆነ ሰው አብሮአቸው አይቆይም። ብቃት ያላቸውና ፖለቲካዊ ሰብዕናቸው የተጠበቀ መሪዎች የሉም ማለቴ አይደለም። ሚዛኑ ግን እጅግ አስደንጋጭ ነው። መጪውን አሻግሮ ማየት ያልቻለ ሰው ከዳዴኦሕ አንዳንድ የአመራር አባላት ጋር አስር ደቂቃ መነጋገር አይችልም። እኔ ነገሮችን ከጊዜያዊ ስሜቶች በላይ አሻግሬ ነው የማያቸው። ኦሮሚያ በዚህ ዘመን ያገኘችውን ይህን ወርቃማ እድል ለማንም አሳልፋ መስጠት የለባትም ብዬ ነው የማስበው። አቦ ሮባ እንዳሉት ጊዜው ደርሶአል ...»

ተያይዘው ወደ ግሮሰሪዋ ዘለቁ ...

ግሮሰሪዋ ጠባብ ትሁን እንጂ ንፁህና በጥቂት ሰዎች ብቻ የምትጎበኝ ትመስላለች። ወደጎዋዳ ገቡ። ምቹ ፎቴዎች ያሉበት ያማረ ሳሎን ተቀበላቸው። በሳሎኑ ውስጥ ቢራ እየተጎነጨ መፅሄት የሚያነብ አንድ ሰው ነበር። ቀና አለ። ሀወኒ ጮኸች።

«ሀየሉም!»

«ሀወኒ ... ጉዋል ኦሮሞ!»

* * *

ግብግቡ ቀጠለ ...

መልካም ራት ቀርቦ ተመገቡ። እየተመገቡ ወጋቸውን ቀጠሉ። የሞቀ ወግ። በክርክር የተሞላ። የፖለቲካ ወሬ። የስሜት ትኩሳት።

ክንፈ ሀወኒን እንዲህ እያለ ይመክራት ጀመር።

«... ሁለት ወይም ሶስት የኦህዴድ ታጋዮች ባለጉ ብለሽ በዚህ ደረጃ መወላወል አልነበረብሽም። በኦህዴድ ቀርቶ ብዙ





ልምድ ባለው በሀወሀት ውስጥ እንኳዋ እያሌ አደናቃፊ ሁኔታዎችና አመለካከቶች ይገጥማሉ። ትግል ከጠላት ጋር ብቻ አይደለም ሀወኒ። ከራስ ጋርም ትግል አለ። ከጠላት ጋር ከሚደረገው ትግል የውስጡ ይከብዳል። ውስብስብና ትእግስትን የሚጠይቅ ነው። የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጥንካሬ የሚለካው ውስጡን ለማዕዳትና ለማጠንከር በሚያደርገው ግልፅ ትግል እንጂ ጠላቱን ለመደምሰስ በሚያደርገው ተጋድሎ ብቻ አይደለም። ውስጡ የጠራና የጠነከረ፣ ህዝባዊ አመለካከት ያለው የፖለቲካ ድርጅት ምን ጊዜም የድል ባለቤት መሆኑ የማይቀር ነው።»

ሀወኒ በመስማማት ራስዋን ላይ ታች ናጠች ።

«አንድ ስጋት ግን አለኝ» አለች ሀወኒ ክንፈ ተናግሮ ሲያበቃ «... በኦህዴድ አባላት ስሜት ላይ እየተፈጠረ ያለው ራዕይ የማጣት አደጋ ውድቀታችንን እንዳያፋጥነው እሰጋለሁ። ነፍጠኛውንና አነግን በማውገዝ ጊዜያችንን እያባከንን ነው። ተናቅን፣ ተበደልን፣ ተረገጥን በሚለው ዘፈን ላይ ቆመን ቀርተናል። 'የኦሮሞ ህዝብ የስልጣኑ ባለቤት ሆኖአል' ተባለ። ከዚያም መሸ። ተኛን። አይነጋ የለም ነጋ። ማለዳ ስንነሳ የምንከፍተው ሙዚቃ ያንኑ 'ተናቅን' የሚለውን ሆኖአል። ወደሚቀጥለው ደረጃ ማደግ አልተቻለም። አመራሩ ይህን ስሜት ለማስተካከል ጥረት ማድረግ ነበረበት። የውስጥ ትግል ሊፋፋም የሚችለው፣ በመሰረቱ ራዕይ ሲኖርህ ነው። አንድ ወይም ሁለት የአመራር አባላት ባለጉ ብዬ አልወላወልኩም። ራዕይ የለንም ባይ ነኝ። ሰፋችንን ከመለወጥ፣ ያማረ አልጋ ልብስ ለመግዛት ከመሮጥ ያለፈ ህልም የለንም። ሰዎችን የምንለካበት መመዘኛ ምላስ ሆኖአል። ይኸ ነው እያስደነገጠኝ ያለው ...»

ቢራቸውን እየጠጡ ወጋቸውን ቀጠሉ፣

ክንፈ ድንገት ተነስቶ ወደ ደጅ ወጣ። የስራው ጠባይ ነው። አንድ የሚከታተለው ጉዳይ ሊኖረው ይችላል። መኪና ውስጥ ገብቶ የመገናኛ ሬድዮውን አነሳ፣

ሀወኒና ሀየሉም ብቻቸውን ቀሩ።

«ደቡብ ኢትዮጵያ ተስማማህ ታዲያ?» ስትል ዝምታውን ሰበረች - ሀወኒ።

«እኔ የትም ሄጄ ብኖር ግድ የለኝም። ሀገሬን እወዳታለሁ። ከህዝቡም ጋር ተቀላቅሎ መኖር እርካታ ይሰጠኛል። ትግል

ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ፣ በተለይም ከገበሬዎች ተለይቼ አላውቅም። የሚገርምሽ የትግራይም ሆነ፣ የአማራ፣ ወይም የጃንካ ገበሬዎች ከሚለያዩበት ይልቅ የሚመሳሰሉበት ይበረክታል። በገበሬዎች መሀል ከመኖር በላይ የሚያረካኝ ነገር የለም።» ካለ በሁዋላ ሲጋራውን ማግማግ አድርጐ «... ትግራይና አዲንብርአ.ድ ግን የእውነት ይናፍቁኛል» ብሎ ትክዝ አለ።

«ባለቤትህና ልጆችህስ?»

«ደህና ናቸው ሀወኒ።»

«ዳንኤል አደገ?»

«አሁንማ ጐርምሶአል» ብሎ ፈገግ አለ።

«ስሙን ግን ለምን ዳንኤል አልከው? 'ሙሴ' ማለት ነበረብህ።» አለችው።

«አ! ዳንኤልም ታጋይ ነው ሀወኒ። እኔን የፈጠረኝ ዳንኤል የተባለ ታጋይ ነው። ሰለክላኻ በተባለ ቦታ ተሰውቶአል»

«እውነት?» አለች።

ሀየሎም በአሳብ ርቆ ነጐደ።

ሀወኒ ድንገት ወደሌላ ርእስ ወሬ ዘለለች፣

«ለመሆኑ ስለ አክሱማይት ሰምተህ ታውቃለህ?» ስትል ጠየቀችው። አያይዛም «ከማህፈረ ጋር የነበራቸው ልዩነት እንዴት ተፈታ? መቼም የማያልፍ የለ! ረስታው ይሆናል። ልትበቀለው ቆርጣ ተነስታ እንደነበር ትዝ ይለኛል» አለች።

«የሆነውን አልሰማሽም?» ሲል ጠየቃት።

«በፍፁም! ምን ተፈጠረ?»

«ራስዋን ገደለችኮ!»

«የፈጣሪ ያለህ!» ብላ ጮኸች።

ሀየሎም ትክዝ ብሎ እንዲህ አላት፣

«... ማህፈረ እስዋን ትቶ ሌላ ማግባቱ መብቱ መሆኑን አምናለች። ተቃውሞዋን ግን የሰርጉ እለት ራስዋን በመግደል ገለፀች። ከባድ ነው! በጣም ከባድ ነው! አክሱምን በደንብ አውቃታለሁ። ሀይለኛ ናት። እልህዋ በተለይ ...» ብሎ እንደመንቀጥቀጥ አደረገው።



ሀወኒ ትክዝ ብላ "Poor Axumaite" ስትል ለራስዋ አንሾካሾከች። ያን ቀን ማታ «የሴቶች ስብሰባ መጥራት ያስፈልጋል» ያለቻትን አስታወሰች። በአሳብ ተመስጣ ከቆየች በሁዋላም፣

«የኢህአዴግ የግምገማ ባህል ግን ጨርሶ እየተበላሸ መጥቶአል ልበል? እንደ ቀድሞው አይደለም።» አለችው።

«እንዴት?» አለ ሀየሎም።

«ሁለት አብነቶችን ልንገርህ» አለች። «... እንዲያውም አንደኛው አንተን ይመለከታል። በአንድ ግምገማ 'ሀወኒን ከሀየሎም ጋር በፆታዊ ግንኙነት እንጠረጥራታለን' የሚል ነገር ተነሳ። ያለንን ግንኙነት በግልፅ እና እውነትዋን ተናገርኩ። አላመኑኝም። ወንድና ሴት ሰዎች ከፆታዊ ግንኙነት ባሻገር ባሉ ነገሮች ሊግባቡ አይችሉም ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ ባዶ ጋን ናችሁ ብዬ ተሳደብኩ። ስሜቴ ከቁጥጥር ውጪ ሆነ። ሰብሳቢው ሰለሞን ዲሳሳ ነበር። ሆን ብሎ እኔን ለማጥቃት ጥረት ሲያደርግ አየው ነበር። በሱ ላይ ሂስ እንዳላቀርብ ቀድሞ ማጥቃቱና መከላከሉ መሆኑን ስረዳ እስኪገርመው ድረስ በሱ ላይ አንዳችም ቃል ሳልተነፍስ ግምገማው አለቀ። ይገርምሀል በዚያው ግምገማ በአንድ እሁድ ቀን ወደ አዳራሹ ቱታ ለብሼ ሄድኩ። ሰለሞን ንግግሩን የጀመረው በኔ ቱታ መልበስ ነበር። 'ሀወኒ መዝናናት ያምራታል' ብሎ ውይይቱን ለቤቱ ዘረጋ። ቤቱ 'መዝናናት እንደሚያምረኝ ባንድ ድምፅ ወሰነ። ይሄን መሰል ግምገማዎች ገንቢ ናቸው ትላለህ?»

ሀየሎም በሳቅ ፈነዳ።

ከልብዋ ታወራ ስለነበር ሳቁ አስደነገጣት።

«ምን አሳቀህ?»

ሀየሎም ሲጋራውን በዝግታ እየሳበ፣

«ያጋጥማል» አላት «... ግን አትጥይው። ለግምገማ አዲስ የሆኑ ጉዋዶቻችን ሊሳሳቱ ይችላሉ። በተቻለ መጠን ማረምና ማስተማር ነው የሚያስፈልገው። የኔና ያንቺን ግንኙነት አስመልክቶ መጠራጠራቸው ምንም አይደለም። ለጥራታችን ይበጀናል። ይህን መሰል ነገሮችን በገንቢ ጐኑ ለማየት መዘጋጀት ይገባል። የቱታው በርግጥ አስቂኝ ነው። በመሰረቱ መዝናናትም ቢሆን የሚወገዝ አይደለም። ጥሩ ነገር ነው» ካለ በሁዋላ እንደገና ከልቡ እየሳቀ «አልማዝ አለሙን አስታወስኩዋት» አለ።

«ማናት አልማዝ አለሙ?»

«የተሰዋች የህወሀት ታጋይ ናት» ብሎ አይኖቹን ሩቅ ወርውሮ በሀሳብ ጭልጥ አለ:: ፊቱ ጨለምለም ሲል ሀወኒ አስተዋለች:: ሀየሎም እንዲህ ሲል አወጋት::

«... አልማዝ በአላማዋ ፅኑ፣ ተዋጊ፣ የምታስመካና የምታኰራ ጀግና ታጋይ ነበረች:: እንዲያውም ካንቺ ጋር በብዙ ነገርዋ ትመሳሰላለች:: እንዳንቺ ግልፅ፣ በሳልና ደሞም ቆንጆ ነበረች:: ውጊያ ላይ ግምባር ለግምባር ትጋፈጥ ነበር:: ታዲያ ውጊያው ሲያበቃ ምንም ያልተፈጠረ ያህል ወደ ወንዝ ትሄድና ሰውነትዋን ትታጠባለች:: ልብሶችዋን ስታወልቅ ታጋዩ ሁሉ ያያታል:: እሰዋ ግን ግድ የላትም:: ውሃው ውስጥ ተምቦጫርቃ ተሰቃልቃ ጨርቅ ቢጤ ሰውነትዋ ላይ ጣል አድርጋ ትመጣለች:: የሰውነትዋ ቅርፅ እስካሁን አይረሳኝም:: አምላክ እጁን ታጥቦ የሰራቸው ከሚባለው ተርታ የምትመደብ ነበረች:: ታዲያ ታጋዮች ሳያውቁት አይናቸው ... ልባቸው ... ቀልባቸው ... ወደ አልማዝ አለሙ ይሳብ ጀመር:: ይሄ ሁኔታ ሲደጋገም እኔና ፃድቃን 'መገምገም አለባት' ብለን ወሰንን:: ጉዳዩን ታዲያ በአንድ ግምገማ ላይ አነሳነው:: እኔ ነበርኩ ያነሳሁት፣ 'አልማዝ አለሙ በአላማ ፅናትዋና በብቃትዋ አትታማም:: ጠንካራ ታጋያችን ናት:: ቢሆንም ፆታዊ ፍላጐት አላት!' ብዬ አቀረብኩ:: ፃድቃንም ተጨማሪ ሰጠ:: የሰጠችንን መልስ ታውቂያለሽ?» አለ ሀየሎም ሀወኒን በፈገግታ እያስተዋላት፣

«ምን መለሰች?»

«'እናንተ ፆታዊ ፍላጐት የላችሁም እንዴ?' ስትል በጥያቄ አፋጠጠችን:: ፊትዋ ላይ የቀልድ ፈገግታ ይታይ ነበር:: ታጋዩ ሁሉ በሳቅ ተንቀንቀ:: አዎን ... ያቀረብንባት ሂስ ስህተት ነበር:: ፆታዊ ፍላጐትን በማነሳሳት ነበር እንጂ መሄስ ያለባት፣ ፍላጐቱ ስላላት አልነበረም:: እኒያ ጊዜያት ግን ግምገማንም የምንለማመድባቸው ጭምር ነበሩ» ካለ በሁዋላ «አልማዝ አሁን በመካከላችን የለችም» ብሎ ተከዘ:: አይኖቹ ላይም እንባ ተንቆርዘ ሀወኒ ተመለከተች::

ሀወኒ ቀጠለችና፣

«የኢህአዴግ ውስጣዊ ሁኔታስ ምን ይመስላል?» የሚል ጥያቄ አቀረበችለት::

ሀየሎም ያብራራላት ጀመር ...

ኢህአዴግ አላማዎቹን በድል እያሳካ መሆኑን ነገራት::





ያሁን እንጂ መድረኩ አዲስ በመሆኑ ቀደም ሲል ያልነበሩ፣ አፍራሽ አመለካከቶች እንደተከሰቱ በግልፅ አጫወታት:: ኢህአዴግ በአመራር ደረጃ ግምገማ አድርጐ «የኢህአዴግ አባላት ወደ አደገኛ የግለኝነት አመለካከት በማምራት ላይ መሆናቸው መቀመጡ፣ ያህ ካልተገታ ግን ድርጅቱ ለህልውናው እንደሚያሰጋው አመራሩ ማመኑን ዘርዝር ገለፀላት:: በድርጅቱ የተንሰራፋውን የግለኝነት፣ የስልጣን ጥም፣ የትምክህትና የጠባብነት አመለካከቶች ለማስወገድ ለአንድ ወር ያህል የሚዘልቅ ስርነቀል ግምገማ ለማድረግ ከፍተኛ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጭምር አጫወታት:: በቀጣዩ ሁለት ወራት ውስጥ የሚካሄደው ግምገማ በድል ካልተጠናቀቀ የኢህአዴግ አወዳደቅ ፈጣን እንደሚሆን አመራሩ እንደሚያምን ጭምር አልሸሸጋትም::

«በግምገማው መልካም ውጤት ይገኛል ብለህ ታምናለህ?» ስትል ጠየቀችው::

«አዎን:: ከዚህ በላይ ውስብስብ ችግሮችንም አልፈናል::»

«ስለሞን ዲሳሳ የሚፈፅማቸውን ተግባራት ግን ድርጅቱ አያውቅም ልበል?»

ሀየሎም እያመነታ መልስ ሰጣት፣

«ግለሰብና ድርጅትን ደርቦ ማየት ትክክል አይመስለኝም::»

ሀወኒ ተቃወመች፣

«የፖለቲካ ድርጅት ሲባል ተመሳሳይ አላማ ያላቸው ግለሰቦች ጥርቅም ማለት አይደለም እንዴ ሀየሎም? ድርጅት ዞሮ ዞሮ በግለሰቦች ይገለፃል:: ስህተት አይፈፀም አይደለም:: ካልታረመ ግን ድርጅቱ ስህተቱን እንደ በጐ ተግባር ተቀብሎታል ማለት ነው»

ሀየሎም «ባጭር ጊዜ አጥፊዎች ሁሉ እንደሚቀጡ እርግጠኛ ነኝ» የሚል ጫን ያለ መልስ ሰጣት:: አያያዘናም፣

«ስለ ሰለሞን ዲሳሳ ብቻ እያሰብሽ ወደተሳሳተ ስሜት እንዳትገፊ እሰጋለሁ» አላት::

«ተራ ነገር አይደለም»

«አንድ ግለሰብ አመራሩን አይወክልም::»

«ኢህአዴግ በግለሰቦች ባልተወከለ ቁጥር ወደ ግዙፍ የብሬት ዋንጫነት እየተለወጠ ነው የሚሄደው::» አለች በከረረ ድምፅ::

«ኦህዴድ ባጭር ጊዜ ተአምራዊ ለውጥ እንዲያመጣ መጠበቅ

የለብሽም።»

በራስዋ አሳብ ለጥቂት ደቂቃዎች ተውጣ ከቆየች በሁዋላም፤ እንዲህ አለች፤

«እመነኝ ሀየሎም፤ አህያዉድ በዚህ አያያዙ ከቀጠለ የኦሮሞ ህዝብ እንቅሮ ይተፋዋል ...»

ክንፈ ተመልሶ መጣ።

ክንፈ ለሀወኒ አንድ ጥያቄ አቀረበላት፤

«የወደፊት እቅዶችሽ ታዲያ ምንድናቸው?»

«አንገቱን ቢቆርጡኝም ባንተ መስሪያ ቤት አልሰራም»

ሀየሎምና ክንፈ በሳቅ ሞሁ!

«ቀልዱን ተዉና ንገሪኝ»

«ከነገ ወዲያ ቡርቃ መሄድ እፈልጋለሁ።» አለች ሀወኒ «... ጥቂት የማረጋጋት ስራ መስራት እፈልጋለሁ። የቡርቃ ሰዎች ጨርሶ ሁሉም ነገር ጨልሞባቸው ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ። ከዚያ መልስ ቻይና መሄድ እሻለሁ» አለች።

«ቻይና ለምን?» አለ ክንፈ ትክ ብሎ እያጤናት። ሀየሎምም ለመስማት ጉዋጉዋ።

«ከግብርና ጋር የተያያዙ ኮርሶችን መውሰድ እፈልጋለሁ። በተለይ የመስኖ እርሻን ጥበብ ሙያዉን መቀየር አለብኝ። በተለይ የመስኖ እርሻን ጥበብ ማጥናት አለብኝ። የኦሮሚያ ወንዞች ከበቂ በላይ ለዘመናት ባክነዋል። አሁን ግን ለአፍሪቃና ለአለም ጭምር በሚተርፉበት መንገድ ሊሰራባቸው ይገባል። የቡርቃ ዝምታ ማብቃቱን ማወጅ የሚገባን በተግባር ብቻ ነው። የኦሮሞ ህዝብ ስለ ምላስ ጀብደኞች በቂ እውቀት አለው። ከንግዲህ የኦሮሞን ህዝብ ሊያሳምነውና ሊያንቀሳቅሰው የሚችለው ተግባር ብቻ ነው። ጥሩ አሳብ አይመስላችሁም?»

ሁለቱም በመስማማት ራሳቸውን ወዘወዙ። ክንፈም፤ «... መለስንም ብታነጋግሪው ግን ጥሩ ይመስለኛል። ከፈለግሽ ከአስር ቀን በሁዋላ ቀጠሮ ልይዝልሽ እችላለሁ።» አላት።

«መልካም»





«ቡርቃ ከሄድሽ ላይቀር እዚያ ያሉትን አማሮችም ሰብስበሽ ብታረጋጊያቸው ምን ይመስልሻል? ስጋት ላይ ናቸው። በማያውቁት ሀጢያት እየተቀጡ ነው» አለ ሀየሎም።

ሀወኒ በመስማማት ራስዋን ላይ ታች ወዘወዘች።

«መኪና፣ ሾፌርና ገንዘብ ያዘጋጅልሻል» አለ ክንፈ።

«አዎን ሽጉጥም ባገኝ አልጠላም» አለች።

«የኔን ያገር» ብሎ ሀየሎም ሪቮልቨር ሽጉጡን ከጃኬቱ የውስጥ ኪስ መዞ ሰጣት።

የሀወኒ ፊት ደማቅ ብርሃን ለበሰ። በስሜት ተቀበለችው።

«እግረመንገድ ማስታወሻ ትሁንሽ!»

«ከልብ አመሰግንሀለሁ ሀየሎም።»

* * *

አልጋ ፊንፊኔ ሆቴል ነበር የተያዘላት። የደህንነቱ መስሪያ ቤት ነበር ያዘጋጀላት። ያን ቀን ማምሻውን ሀየሎም ሆቴሉዋ ድረስ ሸኛት። መንገድ ላይም ስለ አኖሌ ልታነሳለት ወሰነች። የልብ ምትዋ ፍጥነቱን ጨመረ።

«ሀየሎም» አለች በቁንቀት።

«ሀወኒ»

«አንድ ነገር ልጠይቅህ?»

ራሱን በመነቅነቅ እሺታውን ገለፀ።

«አትዋሸኝም?»

«ምን ሆነሻል ሀወኒ?»

«እውነቱን ንገረኝ ... አኖሌ ሞቶአል!?»

«አላወቅሁም» ሲል ፈጥኖ መለሰ።

«ሀየሎም!» አለች በተጎዳ ስሜት።

«አባቦኩ ኮረብታ ላይ አላገኘነውም። የኛ ታጋዮች ማለዳ ላይ ወደ ኮረብታው ሲወጡ ማንንም አላገኙም። የደረሰን መረጃ ስህተት ነበር። አለያም አኖሌ እኛ ሳናውቅ ከኮረብታዋ ላይ አምልጦአል።»

አላመነችውም:: ዝም አለች:: ዝም ተባባሉ:: ከዚያ በላይ መጠየቅ አልፈለገችም:: አኖሌ መሞቱን አመነች:: እንደገመተችው መሆኑን ተገነዘበች:: ረጅም የስቃይ አየር አስወጣች ...

«ምናልባት አገር ለቆ ሄዶ ሊሆን ይችላል:: ምናልባት ... አብርሃ ፀሎት እንዳያመልጥ ረድቶት ሊሆን ይችላል ...» አላት::

«ይሆናል» ስትል መለሰች - ከአንገት በላይ በሆነ ስሜት::

ፊንፊኔ ሆቴል ደረሱ::

«ወደ ቡርቃ መቼ ለመሄድ አሰብሽ?»

«ነገ ወይም ከነገ ወዲያ»

«መልካም ጉዞ! ሀወኒ»

«ቻው ሀየሉም::»

ክፍልዋ እንደገባች አጥወለወላት:: በቁምዋ አልጋዋ ላይ ተዘረጋች:: አልቻለችም:: ልብዋ ያበጠና የታፈነ ያህል ጨነቃት:: የሚያንሰቀስቅ ስሜት ከአንጀትዋ እየገነፈለ ይወጣ ጀመር:: በደረትዋ ተደፍታ የፍቅረኛዋን ስም እያነሳች ትንሰቀሰቅ ጀመር ...

«አኖሌ እወድሀለሁ ... እናፍቅሀለሁ ...»





# እንቅልፉን የማይሰዋ ትውልድ

# የፍፃሜው መጀመሪያ

## ምዕራፍ አስራ አምስት

### - 1 -

ሀወኒ ፊንፊኔ ሆቴል በተያዘላት ክፍል ተጋድማ አኖሌ ዋቆን በእንባ በመሰናበት ላይ ሳለች የክፍልዋ በር ተንኳኳ::

እንባዋን አባበሰች ...

ከመቅዐበት ተነስታ አልጋዋ ላይ ተቀመጠች:: በሰከንድ ጊዜ ውስጥ አያሌ ነገሮችን አሰበች:: ማን ሊሆን ይችላል? ሀየሉም? ሊሆን አይችልም:: ተሰናብቶአታል:: ተመልሶ ምን ሊያደርግ ይመጣል? ክንፈ? እሱም ሊሆን አይችልም:: የአኖሌ መንፈስ ይሆን

የሚያንኳኳኳው? ወይስ ራሱ አኖሌ? የተቀበረበትን መቃብር ፈንቃቅሎ መጥቶ ይሆን? ሊሆን ይችላል! ማን ያውቃል?

በሩ በድጋሚ ተንኳኳ ...

«ማነው?»

«እኔ ነኝ» የሚል ድምፅ!

የሴት ድምፅ!

ተከታትሎም «የሆቴሉ ሰራተኛ ነኝ።»

«ምን ፈለግሽ የኔ እህት?» አለች ሀወኒ በቀዘቀዘ ስሜት።

«ሊያነጋግርሽ የሚፈልግ እንግዳ አለ።»

ልብዋ ድንገት ሊፈነዳ ደረሰ!

እኮ ማን ሊሆን ይችላል!? እዚህ ሆቴል ማረፍዋን ማንም አያውቅም። እኮ ማን ሊሆን ይችላል!? እኮ ማን!? ማነው በዚህ ምሽት ...

«ማነውስ?» አለች።

«ስሙን መግለፅ አልፈለገም።»

ሀወኒ ከአልጋዋ ተስፈንጥራ ተነስታ በሩን በረገደችው። አጭር ድቡልቡል ሴት በሩ ስር ተከምራለች።

«የት ነው ያለው?»

«ሪሴፕሽን»

«አስገቢው»

ሀወኒ ይህን ብላ ወደ አልጋዋ ተመለሰች። ወዲያ ወዲህ ትንጐራደድ ጀመር። ልብዋ ሊፈነዳ ደርሶአል። ፊንድቶ መገላገሉን ተመኘች። ጡቶችዋን በሁለት እጆችዋ ጭምቅ አደረገቻቸው። አቃሰተች። እንቅ አድርጋ ያዘቻቸው። ሁለት ጡቶችዋ እያንዳንዳቸው በእጆችዋ ውስጥ ግጥም ብለው ሞሉ። እየተሰማት ስላለው ስሜት መረዳት አቃታት። ልብዋ - ቀልብዋ - አይንዋ - ጆሮዋ - ስሜትዋ ሁሉ ግን በአኖሌ ዙሪያ ተጠምዶአል።

በሩ በቀስታ ተቆረቆረ።

ማን ሊሆን ይችላል?



ዲያቢሎስ ወይስ መልአክ?

«ይግቡ» አለች።

በሩ በዝግታ ተገፍቶ ቾንድ ሰው ገባ - ሰለሞን ዲሳሳ።

ሀወኒ በርጋታ ጡቶችዋን ለቀቀቻቸው። በጥላቻ አፈጠጠችበት። ፈገግ አለ። በፈገግታ ቀረባት፤

«ጤና ይስጥልኝ፤ ሀወኒ» ብሎ እጁን ለሰላምታ ዘረጋ።

«ጤና ይስጥልኝ» ብላ የተዘረጋ እጁን ጨበጠችው።

«ይቅርታ ከመሸ ረበሽኩሽ»

«ምንም አይደለም።»

ሲጠጣ እንደቆየ ገፅታው ያስታውቃል። ወዙ በመቅለጥ ላይ ነው። ወፍሮአል። ተስማምቶታል። የቆዳው ጥራት ጉድ ያሰኛል። አለባበሱ ሽክ ያለ ነው። ሙሉ ሱፍ በክራቫት። በዚያ ላይ ግራጫ የአንገት ልብስ አንገቱ ላይ ጠምጥሟል። አምሮበታል።

«ሳነጋግርሽ ፈልጌ ነበር፣ ለጥቂት ደቂቃዎች።»

«ይቻላል - እረፍ በል» ብላ መቀመጫ አመላከተችው።

የጥላቻ ስሜትዋን ለማርገብ ከራስዋ ጋር ትግል ገጠመች። ሰለሞን ወንበር ሲይዝ እስዋም አልጋዋ ላይ አረፍ አለች።

«እዚህ መሆኔን ማን ነገረህ?» ስትል ጠየቀችው።

«ከደህንነት መስሪያ ቤት ነገሩኝ። ስላንቺ ሁኔታ ስከታተል ነው የቆየሁት። እስር ቤት መጥቼ ልጠይቅሽ ፈልጌ ነበር። ግን ደሞ ወሬኛውን ታውቂዋለሽ። ስጋሁ። በመታሰርሽ ግን ከልብ ነው ያዘንኩት። ስህተት ነው የተፈፀመው። ጉዳዩን በግልፅ ለመቃወም መድረክ እየጠበቅሁ ነበር። በአጋጣሚ ተፈታሽ። ነገሩ ግን ያበግናል»

ሀወኒ በጣም ተገረመች። 'ያበግናል!' እያለ ይናገር እንጂ ስሜቱ ግን የተረጋጋ ነበር። ያበገነው ምን እንደሆነም የሚያውቅ አይመስልም። ሀወኒ ቶሎ ይወጣላት ዘንድ ተመኘች።

«ለምን ነበር ታዲያ የፈለግከኝ?» አለችው።

«አስቀይሜሻለሁ። ይቅርታ አድርጊልኝ።»

«ምን አድርገህ ነው ያስቀየምከኝ?»

«ዜኒትን በተመለከተ የመከርሺኝን መስማት ነበረብኝ። አሁን ግን ራሴን ሙሉ በሙሉ ለማስተካከል ተነስቼያለሁ። አንቺ ብቻ ይቅርታሽን አትንፈጊኝ።»

«ግለሂስ ነው ይቅርታ?»

«ግለሂስም ሊሆን ይችላል ሀወኒ። ምን ለውጥ አለው?»

«ግለሂስ ከሆን በተለመደው መድረክ ላይ ብትገልፅ አይሻልም? ወደኔ ለምን ትመጣለህ። እኔኮ ገና ከእስር ቤት መውጣቴ ነው። በአባልነት ስለመቀጠሌም ገና የተረጋገጠ ነገር የለም። አንተ ደሞ የተከበርክ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በመሆንህ የፈፀምካቸውን ጥፋቶች ለኔ ለመናዘዝ አትገደድም።»

ሰለሞን እጁን እያጣፋ ከርዕስ ጉዳያቸው ውጭ መናገር ጀመረ፣

«ሀወኒ አንድ ሀቅ ልነግርሽ እፈልጋለሁ። አንቺ የታሰርሽውኮ በኦነግ አባልነት ተጠርጥረሽ ነው። ግን ያንቺን ጥንካሬና አመለካከት ከኔ በላይ የሚያውቅ የለም። በእውነቱ በመታሰርሽ በጣም ነው ያዘንኩት።»

ሀወኒ ግልፍ አለች፣

«እኔ ደግሞ እስካሁን አንተ ባለመታሰርህ በጣም ነው ያዘንኩት!»

እጢው ዱብ አለ!

ጮሌ ፊቱ ሲገረጣ ተመለከተች። ድንጋጤውን ለመደበቅ ሲታገል አጤነችው። ራሱን እንደምንም አረጋግቶ ምንም እንዳልተፈጠረ ለማስመሰል ይጥር ጀመር፣

«ሀወኒ ... በኔ ላይ ያሳደርሻቸው መጥፎ ስሜቶች እንዲወገዱ እፈልጋለሁ። ሁለታችንም ታጋዮች ነን። በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር የተሰለፍን የህዝብ ልጆች ነን። የአላማ አንድነታችን ሊያቀራርበን ይገባል። በኔ ላይ ብዙ አሉባልታ ተነዝቶአል። ይህን አሉባልታ የሚያናፍሱት እህዴድን የሚፈሩ ነፍጠኞች ናቸው። እህዴድ ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር በመተባበር የነፍጠኛውን ስርአት ያፈራረሰ እንደመሆኑ የበሬ ወለደ አይነት አሉባልታ ለሚነዙ ሃይሎች ቀዳዳ መክፈት የለብንም። 'ጅብ ማታ ያደረገውን ስለሚያውቅ ነው ቀን የማይወጣው' እንዲሉ እነርሱም በኦሮሞ ህዝብ ላይ የፈፀሙት ግፍ እንዳይነሳ ሲሉ ነው የእህዴድን አመራር ጥላሸት ...»





ሀወኒ በቁጣ ጮኸች አቋረጠችው!

«በቃህ! አፍህን ዝጋ!»

ድምፁ በአፍንጫው በኩል እንደ አይጥ ሾልኮ ጠፋች። በሆነታ ተውጦ አይን አይንዋን ያያት ጀመር።

«የምላስህን ርዝመት ልንገርህ!?» ስትል አምባረቀች።

ምላሽ አልሰጣትም።

«የጭላሎን ተራራ ያክላል!»

ይህን ስድብ ግን በዝምታ አላስተናገደውም። ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ተነሳ! አይኖቹን አይኖችዋ ላይ ቸክሎ ቁና ቁና እየተነፈሰ፣

«ታገስኩሽ ሀወኒ!» ሲል በተራው ጮኸ «... የወርበላው የአናሌ ዋቆ ግብረአበር እንደሆንሽ የማላውቅ አይምሰልሽ። ከእስር ቤት ስለወጣሽ ነፃ ሆኜያለሁ ብለሽ ጮቤ አትርገጪ። ማንም ደግሞ ከለላ ሊሆንሽ አይችልም። ስሚኝ ሀወኒ ...»

ሆኖም ልትሰማው ሳይቻላት ቀረ።

ሽጉጥዋን ከሽንጥዋ ስር መዛ አወጣች። አነጣጠረችበት። የሰለሞን አይኖች ተጎልጉለው ወጡ።

«ሀወኒ! ሀወኒ! ... ሽጉጡን ዘወር አድርጊው ...» እያለ ወደሁዋላ አፈገፈገ። ግድግዳው አገደው። እጁን ፊቱ ላይ ከልሎ ይለማመጣት ገባ፣

«... ስለማትችይበት ሊተኩስብሽ ይችላል ... ሀወኒ ... ዘወር አድርጊው ... ሳስቀጣሽ ብዬ አልነበረም ... በአንድ የአላማ ጃንጥላ ስር ነንኮ ሀወኒ ... በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ጃንጥላ ስር ነን ... ልዩነቶች ካሉ ... እየሽ ... ካሉ ልዩነቶች ... በአሰራሩ መሰረት ... ተወያይተን ነው ልንፈታው የሚገባው .. ካልተግባባን ሶስተኛ ሰው ... ምን ... መሰለሽ ሀወኒ ... በመድረክ ላይም ቢሆን ... ግለሂስ ሳደርግ እችላለሁ ... እኔን ብትገድይ ... ምን ትጠቀሚያለሽ? ... አንቺም ቢሆን እስር ቤት ትገቢያለሽ ... ለምን ሀወኒ ... ቆይ ... ምን ... መሰለሽ ሀወኒ ...»

በምን ፍጥነት ተገልብጦ እንደመታት አላወቀችም። ሽጉጡ ከእጅዋ ተስፈንጥሮ ወደቀ። ሰለሞን ከአይን በፈጠነ ሁኔታ ለሁለተኛ ጊዜ ተገልብጦ ሽጉጡን በጁ አስገባው። ሀወኒ እጅዋ በሰለሞን ጫማ ሲመታ በጀርባዋ አልጋው ላይ ወደቀች።

ሰለሞን ሽጉጡን በጁ ካደረገ በሁዋላ ከወደቀችበት አነሳት።

የተመታ ቀኝ እጅዋን በግራው እያሻሸች በጥላቻ አፈጠጠችበት። ቁና ቁና እየተነፈሰች፤ ገረመመችው።

«ይቅርታ ሀጠኒ» አላት።

ቀና ብላ - በታከተ ስሜት፣

«ሸንጡን አስቀምጥና ውጣ!» ስትል በቁጣ ጮኸችበት።

«ይቅርታ ሳታደርጊልኝ ከዚህ ንቅንቅ አልልም። ካሻሽ ለክንፌ ደውለሽ 'ደበደበኝ' በይው።»

ይህን ሲላት ሀጠኒ በትእዝብትና በመገረም ታጤነው ጀመር።

«ምንድነው ከኔ የምትፈልገው?»

«ቃል ግቢልኝ?»

«ምንድነው ቃል የምገባልህ?»

«የምታውቂውን በግምገማ ላይ ላለመናገር! ለክንፌና ለሀየሎምም ላለመንገር ቃል ግቢልኝ።»

«አንተ ማንን ነው የምትፈራው? ሀየሎምን ነው ወይስ የኦሮሞን ህዝብ?»

«የኦሮሞ ህዝብ ተሰብስቦ እኔን ከስራ አያባርረኝም።»

«እንዲህ ነው የምታስበው? ህሊና የለህም? ከህሊናህ ሸሽተህ ወደት ታመልጣለህ?»

«ሀጠኒ አትሞኚ» አላት ትከሻዋን ይዞ «... ህሊና የሚባል ታሪክ የለም። ህሊና የፍላጎት ታዛዥ ባሪያ ነው። ለህሊናው የሚገዛ አንድም ሰው የለም - በአለም ላይ።»

ፈገግ አለች።

በዋለችባቸው የጦር ሜዳዎች በጀግንነት የተሰውቱን ታጋዮች መለስ ብላ ማስታወስ ጀመረች። ስለ ዘመናችን ትውልድም አሰበች። ሁለት አይነት ሰዎች - በአንድ ዘመንና ትውልድ። ህይወቱን ለህዝብ የሚሰዋ ትውልድ! እንቅልፉን እንኳ ለህዝብ ለመሰዋት የማይፈቅድ ትውልድ!

ሰለሞን ቀጠለ። ዝምታዋን ወደደው። እያሳመንኩዋት ነው የሚል እምነት አደረበት።

«... ስራስሽ ልታስቢበት ይገባል ሀጠኒ። የግል ህይወቱን ለማደላደል የማይሮጥ የለም። የዋህን ብቻ ናቸው ደፋ ቀና





የሚሉት። በርግጥ አንቺ ገንዘብ የማግኘት እድል ላይኖርሽ ይችላል። ግን ከተማከርን ሁሉም ቀላል ነው። ገንዘብ የሚገዛቸው አያሌ ደስታዎች አሉ ሀጠኒ። አሁን ከእስር መፈታትሽን አትመልከቺ። የሀጠሁት ሰዎች ከንግዲህ በጥርጣሬ ነው የሚያዩሽ። እየላቁ ይገድሉሻል። ሆዳምና ግለኛ ከሆንሽ ብቻ ነው የሚወዱሽ። ፖለቲካ ውስጥ ንብተሽ ካልዘባረቅሽ በወር ብለው አያዩሽም። ህዝብ ... ህዝብ ካልሽ ግን ቀንድሽን ነው የሚሉሽ። በጣም የሚያቀርቡሽክ ሲያጠፉሽ ስለፈለጉና ወደፊት አደገኛ እንደምትሆኚባቸው ስለደረሱበት እንጂ የምር ወደውሽ አይምሰልሽ። ጥርሳቸውን ብልጭ የሚያደርጉልሽ ከልብ አይምሰልሽ። ሀጠኒ በወንድምነት ነው የምመክርሽ። አንቺም ልብሽን ቆልፊ። ቅንነትና ሀቀኝነት ለማንም አልበጀ።»

«ልክነህ» አለችው ትክ ብላ እየተመለከተችው።

የሰለሞን አይኖች እንደ ማለዳ ከዋክብት ደመቁ። የገባ ጆሮውን በመጠራጠር ሀጠኒ ተጨማሪ የማረጋገጫ ቃላቶችን ትተነፍስ ዘንድ በጉጉት ያስተውላት ጀመር። ቀርጠና ወስኖ ነበር በዚህ መንገድ ሲቀርባት። ሲጋቱ ሀጠኒ ናት። ስትታሰር በደስታ ሲያብድ ደርሶ ነበር። መፈታትዋን ሲሰማ ስሜቱ ቀዘቀዘ። ሀጠኒ እያለች ሰላም ሊያገኝ እንደማይችል ተረድቶታል። የፈፀማቸውን እያሌ ህገወጥ ድርጊቶች ማስረጃ ጠቅሳ ማቅረብ የምትችለው ሀጠኒ ናት። የሀጠኒ አፍ መዘጋት አለበት። ባንድም ሆነ በሌላ መንገድ።

«እና ምን ይመስልሻል?» አላት።

«አንተ ምን ይመስልሀል?» አለችው።

«ምኑ?»

«ምንድነው ያልከኝ?»

«አንቺ 'ልክ ነህ' ብለሺኝ የለ?»

«አዎን ልክነህ?»

«ምኑን ነው ልክ የሆንኩት?»

«ገንዘብ ጠቃሚ መሆኑን» አለችው።

ሊጨብጣት እጁን ዘረጋ። ሙትት ያለ ፈገግታ አሳይታው ጨበጠችው።

«ለጊዜው ገንዘብ ያስፈልግሻል?»

«አዎን»

«ምን ያህል ልስጥሽ?»

«መቶ ብር» አለች፡፡

ሰለሞን በሳቅ ፈነዳ!

«ምነው?» አለች፡፡

«እየቀለድሽ ነው?»

«አልቀለድኩም፡፡ ገና ከእስር ቤት መውጣቴ ነውኮ፡፡ ምንም የለኝ፡፡»

«ነገ መቶ ሺህ ብር አመጣልሻለሁ፡፡»

«እውነት!?» አለች አይኖችዋን በአድናቆት አፍጥጣ፡፡

«ስጋ ብዎት!» ሲል ማለ፡፡

ስቅጥጥ አላት፡፡ በተሰውት ታጋዮች ስም መማሉ አስደነገጣት፡፡ ብርድ እንደያዘው ሰው መንቀጥቀጥ ጀመረች፡፡ ግን መንቀጥቀጥና መደንገጥዋ እንዳይታወቅባት ትሞክር ጀመር፡፡ ሳንዱና ለመጨረሻ ጊዜ የሚጋለጥበትን ወጥመድ ለማዘጋጀት ወሰናለች፡፡ ይህም ለኦሮሞ ህዝብ የሚደረግ ትግል መሆኑ ታሰባት፡፡

«ሀወኒ ... አከብርሻለሁ!» ሲል በስሜት ተናገረ፡፡

«አመሰግናለሁ»

«ቸኮልክ አትበይኝ እንጂ ሳላስብሽ የቀረሁበት አንድም ቀንና ሌሊት የለም፡፡ ስላንቺ ሳስብ መላው ሰውነቴ ብንዳች ሙቀት መሰል ነገር ይወረራል፡፡»

«ተመሳሳይ ስሜት አለን ማለት ነው» ብላ ፈገግ አለች፡፡

«ሀወኒ እመኚኝ፡፡ ጭንቅላት ያለሽ ሰው ነሽኮ፡፡ የህወሀት አመራሮች እንዴት እንደሚያከብሩሽ አይተሻል? አንቺ በሌለሽበት ስንት ቀን ስላንቺ ያነሳሉ መሰለሽ፡፡ ግን ተጠንቀቂያቸው፡፡ ለማንኛውም ደግሞ እንቀራረብ፡፡ ያለፈውን ጠብ እርሺው፡፡ ሙሉ በሙሉ እርሺው ሀወኒ፡፡ መተማመን ነው ያለብን፡፡»

«እኔኮ አፈቅርህ ነበር፡፡ አንተ ግን እኔን ትተህ ጉዋደኛዬን ወደድክ» አለችው፡፡

«የሰማየ ስማያት ያለህ!» ብሎ ጮኸ፡፡ ስሜቱን መቆጣጠር እንክዋ አቃተው፡፡





«ይህን ሁሉ እኔ የት አውቄ?» ብሎ ይብከነከን ጀመር፡፡ ግን መልሶ ረጋብ አለ፡፡

«ደግነቱ ተለያይተን አልቀረንም፡፡ ከዚያች ከዩሲ ጋር ብቻ እንኳዋን ተለያየሁ፡፡ የሚገርምሽ የዜኒት አመለካከት እንዳለ የመአህድ ነው፡፡ መአህድ ሳትሆን አትቀርም፡፡ የሚዋደድ ሰው ግን ዞሮ ዞሮ ይገናኛል» አላት፡፡

«አጀማመራችን በጥል ሆነ እንጂ ነገሩስ ጥሩ ነበር፡፡» አለች፡፡

«አይምሰልሽ» አለ «... የሚዋደድ ሰው ሁልጊዜ በጥል ነው የሚጀምረው፡፡»

«እጄን ግን አሳመምከኝ፡፡ ካራቴ ተምረሀል እንዴ?»

ሰለሞን በኩራ ደነፋ፣

«ሁለት እጄ ወደሁዋላ ታስሮ በእግሬ ብቻ አስር ሰው መከረባበት እችላለሁ» አላት፡፡

«እውነት!?»

«ወደ አዲሳባ የገቡትን የኢህአዴግ ኮማንደሮችኮ እኔነኝ ያሰለጠንኩዋቸው?»

«እሬ ባክህ!?»

«...እንናገርም እንጂ አስተዋያአችንኮ የተየለሌ ነው፡፡ ግን ጉራ ምን ያደርጋል፡፡ ጉራ ቀለብ አይሆን ...»

«በል እንግዲህ ሰለሞን፤ አሁን መሸ፡፡ የግድ መሄድ ሊኖርብህ ነው፡፡»

«እምን ልሄድ» አለ፡፡

ከተቀመጠበት የአልጋው ጫፍ ላይ ግን ሳይነሳ ቀረ፡፡

«እጅሽን አመመሽ እንዴ?» ብሎ በጫማ የመታውን ቀኝ እጅዋን ያዘው፡፡ ይዞ ያሻሽላት ጀመር፡፡

ቀስ አድርጋ አስለቀቀችው፡፡

«ብቻሽን ማደር ይጨንቅሽ ይሆን?»

«እሬ በጭራሽ?» አለች፡፡

«ከፈለግሽ እዚሁ ልደር - እንደበረሀው፡፡ በረሀ እኮ ሴትና ወንድ ዝም ብለን ጎን ለጎን ነበር የምናድረው፡፡» ብሎ በመገናኛት

መልክ በፈገግታ ተጥለቀለቀ።

«ደህና!» አለችው ሀወኒ «... ብቻዬን ብሆንም ችግር የለውም።»

«ካልሽ እንግዲህ ደህና!»

አሁንም ግን ለመሄድ አልተነሳም።

«በል ደህና እደር»

«ደህና እደሪ» ብሎ ብድግ አለ። እሰዋም ከተቀመጠችበት ተነሳች።

«ልሳምሽ?» ሲል ፈቃድ ጠየቃት።

«ሌላ ቀን ...» አለችው።

«ነገኮ ገንዘቡን ይገር እመጣለሁ። የልቤን ነውኮ ቅድም ያልኩሽ። ድሮ የማውቀው አንድ ጉዋደኛ አለኝ። ሚልዬነር ነው። ካዝናዬ ካዝናህ ነው ይለኛል ሁልጊዜ። እኔ ግን አጣጥልበታለሁ። የሰው ልጅ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ እምነቱ እንጂ በገንዘብ አይኖርም እለዋለሁ። ለማንኛውም ነገ ማለዳ ዝምብዬ ሄድ ብዬ ከካዝናው መኻሮረጥረጥ አድርጌ እመጣለሁ። አምስት ሰአት ላይ እዚህ እደርሳለሁ። ምሳ አብረን ነው የምንበላው። በይ ቻው ሀወኒ .. አትሳመኝ ብለሻል መቼም ...»

«ነገ አታገኘኝም፤ ከነገ ወዲያ ምሳ ሰአት» አለችው፤ በዚያን እለት እንደማያገኛት እያሰበች፤ በዚያንለት የደህንነት ሰዎች ሲጠብቁት እንደሚገባ እያውጠነጠነች።

«እንዳመቸሽ» አላት።

«ከቀረህ ግን የመጨረሻችን ነው» አለችው።

«አብደሻል!?» ሲል ጮኸ።

«ልመነህ?»

«መቶ ሺህ የታሰሩ ብሮች መያዝ የሚችል ከረጢት ብቻ አዘጋጂ» ብሎ በሳቅ ተንተከተከ።

«እምነሀለሁ» አለችው። እያይዛም፤

«ሽጉጤን መልስልኝ እንጂ ታዲያ!?» አለች።

«አ! ረስቼው» ካለ በሁዋላ፤ የሀወኒን ሪቮልቨር ሽጉጥ





ከቀኝ ሽንጡ ላይ ስቦ አወጣው።

«ታምራለች» አላት።

«በጣም» አለች፤ ልትቀበለው እጅዋን እየዘረጋች።

ግን አልሰጣትም። ሽጉጥዋን እያገላበጠ እየተመለከተ፤

«ለውጪኝ። አንቺ የኔን ያዢ። ለአዲሱ ወዳጅነታችን ማስታወሻ ይሆነናል» አላት።

«አይሆንም» አለችው።

«ለምን?» አለ አይኑን አይንዋን እያየ።

«የሰው ስጦታ ነው።»

«እኔምኮ ልጠይቅሽ እያልኩ ነበር። ዛሬ ከእስር ቤት ወጥተሽ ዛሬ ሽጉጥ መያዝሽ ግራ አጋብቶኝ ነበር። ለመሆኑ የማን ስጦታ ነው?»

«የሀየሎም!»

«ሀየሎም የቱ!?» አለ ሳያስበው።

«ሀየሎም አርአያ።»

«ሀየሎም ማስታወሻ ብሎ ይህን አበረከተልሽ?»

ራስዋን ላይታች ወዘወዘች።

ሰለሞን ቃል ሳይተነፍስ ሽጉጡን አልጋው ላይ አኖረው። ድንጋጤ ግንባሩ ላይ ተፅፎ በግልፅ መነበቡን እጢና ሀወኒ በትእዝብት እያስተዋለችው ነበር።

«በይ ቻው» አለ።

«ደህናደር»

ወደበሩ አዘገመ። በሩን ከፍቶ ከመውጣቱ በፊት ዘወር አለና፤

«መልካም ሌሊት ሀወኒ» አላት።

«ቻው ሰለሞን» አለችው። አከላም እንዲህ አለች «... ቀይታችንን በጣም ወድጄዋለሁ። ከተጫወትነው በላይ የወደድኩልህ ግን ከማንዲስትነትህን ነው»

ሰለሞን ፈገግ አለ። ከልቡም እንዲህ አላት፤

«ጊዜ ካለሽ አንቺንም ላስተምርሽ እችላለሁ፡፡»

ይህን ብሎት በሩን ዘግቶ ነጉደ፡፡ ሀወኒ አዘነች፡፡ ያዘነችው በመጨረሻ የሰነዘረችውን አሽሙር ባለመረዳቱ ነበር፡፡ 'አሽሙሬ ባከኑ' አለች ለራስዋ፡፡ የራስዋ ቀልድ መልሶ አሳቃት ...

እኩለ ሌሊት አልፎ ነበር ....

ያን ቀን ከመተኛትዋ በፊት ለሰለሞን ዲሳሳ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ጥቂት የግጥም ስንኞችን ቋጠረች፣

*ድንጋይ!*

*ቀለም ፈሰሰልህ ከላይ*

*ወርቅ መስሎ የሚታይ*

*እና ...*

*እናማ ወርቅ ነኝ አልክ አሉ*

*መምሰል መሆን ላይሆን ቅሉ፡፡*

## - 2 -

የቡርቃ ገበሬዎች ሀወኒን በእልልታ ነበር የተቀበሉዋት፡፡ ከእስር ተፈትታ በመምጣትዋ በድፍን የቡርቃ ገበሬዎች ዘንድ መጠን የሌለው ደስታ ሆነ፡፡ ይህ ታላቅ ዜና ከጐጆ ጐጆ ለመድረስ ጊዜ አልወሰደበትም፡፡

ተሲያቱን ቡርቃ ባልታሰበ ፈንጠዝያ ተጥለቀለቀች፡፡ ገበሬዎቹ ሀወኒ ወዳረፈችበት ወደ አባበሩ ደጃፍ ይጐርፉ ጀመር፡፡ እንቁላሉ - ወተቱ - እንቁላሉ - አይቡ - ቅቤው - ጠቦቱ - ጠቦቱ - ጠቦቱ - ቄንዲፍቱው - ብርዙ - ኧረምኑ ቅጡ፡፡

ያባበሩ ጐጆ በገበሬዎች ሆታ ደመቀ፡፡ ሴቶቹ በልማዳቸው መሰረት የሀወኒን ጠጉር ቅቤ ከቀቡ በሁዋላ ስምዋን እያነሱ እልልታውን አቀለጡት፡፡ ምርቃቱም ጐረፈ ...

ሀወኒ ወደ ቡርቃ የመጣችበትን ምክንያት ለሁሉም በሚሰማ ድምፅ እንዲህ ስትል ነበር የገለፀችው፣

«ወገኖቼ ... ምድራችን እጅግ ሀብታም ነው፡፡ እኛ ግን ድሆች ነን፡፡ ብንታመም እጣችን ሞት ነው፡፡ እናቶች በምጥ ያርፋሉ፡፡ ህፃናቶቻችን በቀላል ህመም ይቀጠፋሉ፡፡ ይሄ ለምን የሆነ ይመስላችሁዋል? ስላልተማርን ብቻ አይደለም፡፡ ላለፉት





መቶ አመታት ሙሉ ገነርዎቻችን እኛን የሚንቁንና የሚበሉን በመሆናቸው ነው፡፡ ወገኖቼ እናንተ የምታከሩ ጀግኖች እንጂ የሚታፈርባችሁ አይደላችሁም ...»

እልልታው ድንገት ቡርቃን አናወጣት፡፡ ሀወኒ እንባ ባይኖችዋ ሞላ፡፡ ደስታ የሰራ አካላትዋን አጥለቀለቀው፡፡

«ጀግኖች ናችሁ! አይበገሬዎች ናችሁ! የኦሮሞ ሁሉ ምሳሌ ናችሁ፡፡ ቡርቃ በናንተ ኩራች፡፡ አርሲ በናንተ ስምዋ ገነነ፡፡ ኦሮሚያ ራስዋን ቀና አደረገች፡፡ እናንተ እውነትም የኦሮሚያ ቡርቃ ናችሁ፡፡ ጀግንነትና አይበገሬነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው እናንተ ልብ ውስጥ ነው ...»

ሀወኒ መቀጠል አቃታት፡፡

እንደ ከባድ ነጐድጓዋድ የሚወርደውን የእልልታ እሩምታ የገደል ማሚቶ መልሶ በድፍን ቡርቃ ላይ ያስተጋባዋል፡፡

«ስሙኝ ወገኖቼ ... የጦርነቱ ዘመን አክትሞአል፡፡ አባቶቻችን የሚመኙት ይህን ዘመን ነበር፡፡ አድባራችን ዋቆ አባዱላ ይናፍቃቸው የነበረው ዘመን ደርሶአል፡፡ መጠንቀቅ ያለብን አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ በነፍጠኛው ምትክ ኦሮሞ የሆነ ሌላ ነፍጠኛ መሸከም የለብንም፡፡ ይህ አደጋ እንዳይገጥመን ማስተዋል አለብን፡፡

«... ቀጣዩ ዘመን መንገድ የሚሰራበት ዘመን ነው - ወገኖቼ! ክሊኒክ የሚታነፅበት ዘመን ነው፡፡ ትምህርት ቤት የሚገነባበት ዘመን ነው፡፡ እኔ ምንጊዜም ከጐናችሁ ነኝ ወገኖቼ፡፡ ለኛ የሚበጀውን ሁሉ ተባብረን እንሰራለን፡፡ እናንተ ያወረሳችሁኝ የኦሮሞነት ክብርና ኩራት ልቤ ላይ እየነደደ ነው፡፡ ለዘልአለሙ ከጐናችሁ አለሁ!»

የሽማግሌዎች ምርቃት ተጅጐደጐደ፡፡

ሀወኒ ትኩስ እንባዋ ፊትዋን አጠበው፡፡ ልጃገረዶች ጉንጭዋን ለመሳም ተሻሙ፡፡ እንደ ልዩ ፍጥረት እየነካኩ ከበቡዋት፡፡ 'ሀወኒ ሁልጊዜ እየመጣሽ ትጠይቂናለሽ?' ሲሉ መልሰው መላልሰው ጠየቁዋት፡፡ ደግመው ደጋግመውም ያንኑ አነሱ፡፡ ስስታቸው የሀወኒን የደስታ እንባ አናረው፡፡ በሚወድዋት ወገኖችዋ መካከል መገኘትዋ የፈጠረባትን የደስታ ስሜት መቆጣጠር ተሳናት፡፡ በገበሬዎቹ እልልታ ተፈንቅሎ የወጣው እንባዋ ውስጥዋ መከማቸት ጀምሮ የነበረውን አንዳንድ የጥላቻና የቂም አራሙቻ ነቃቅሎና ጠራርጐ አጠበው፡፡

ግብግቡው ቀጠለ ...

ሽማግሌዎችም ምርቃቱን አሻግሮ ድንገተው እንዳበቁ አባቦሩ አንድ ጥያቄ ጣል አደረጉ፣

«ሀወኒ ልጃችን! እንኳንም ደህና መጣሽልን ... እንወድሻለን። እናምንሻለን። አንቺ የኛ እንደቡት ነሽ። እኛ ሽማግሌዎች በልባችን ያለውን ሁሉ ካንቺ ጋር ማውጋት ይናፍቀናል። ካንቺ ጋር መምከርም አስበን ... ሆዋ ልጄ ... ልክ አይደለም?»

«ልክ ብለዋል አባቦሩ»

«ደግ። ወንድምሽ አኖሌ አሁን የት ነው ያለው?»

በሀወኒ ዙሪያ የተሰባሰቡት ገበሬዎች በድንገተኛ ፀጥታ ተዋጡ። የገበሬዎቹ አይኖች ሀወኒ ላይ አፈጠጡ።

የልብ ምትዋ ፍጥነት ጨመረ። ከካ ተራራ ጋር ከተጋጨ በሁዋላ እስተጋብቶ የሚመስስ አንድ ድምፅ!

«ኢልመኮ አኖሌ ... ኤሳ ጅርታ!? ኢልመኮ አኖሌ ... ኤሳ ጅርታ!? ኤሳ ጅርታ!? ኤሳ ጅርታ!?»

ሀወኒ አቃሰተች።

«ወገኖቼ!» አለች በደከመ ድምፅ። «ወንድሜ የት እንዳለ አላውቅም!»

ገበሬዎቹ የተማከሩ ይመስል አቀረቀሩ። አባቦሩ ጥያቄያቸውን አላበቁም።

«ትግሬዎቹ ገድለውታል የሚል ወሬ ሰምተናል። እውነት ይሆን?»

ሀወኒ እንደገና አቃሰተች።

«ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። እኔ በወቅቱ እስር ቤት ነበርኩ። ከእስር እንደተፈታሁ ስለ አኖሌ ጠይቄ ነበር። ከአባቦኩ ኮረብታ ማምለጡን ነው የሰማሁት።»

ገበሬዎቹ ከዳር እዳር በተቃውሞ አጉረመረሙ።

ድንገትም ከገበሬዎቹ መካከል በእድሜ የገፉ አጭር ሽማግሌ ብድግ አሉ።

«አንድ ጊዜ አድምጡኝ ... ወገኖቼ» አሉ።





የገበሬዎቹ አይኖች ወደ ሽማግሌው ተወረወሩ። ሽማግሌው ኩራት በተሞላበት ድምፅ መናገር ጀመሩ ...

«አኖሌ ልጃችን ሞቶአል! ይኸ የማይካድሀቅ ነው። እንኳንም ሀወኒ ተረፈችልን። እስዋስ እዚያው እስር ቤት ትቀራለች ብለን አልነበረም? ዋቀዮ ሰጠ፣ ዋቀዮ ነሳ። እሱ የተመሰገነ ይሁን። አሁን መግለፅ የምሻው አንድ ታላቅ ምስጢር ግን አለኝ። አባቦኩ ኮረብታ ላይ ትግሬዎቹ አኖሌን የከበቡ ጊዜ እኔ እዚያው ነበርኩ። አኖሌን ከመሞቱ በፊት ሳናግረውም በቀቻለሁ። መልእክት አድራሽ እኔ ነበርኩ።»

ገበሬዎቹ በድንገተኛ ፀጥታ እንደተዋጡ የሽማግሌውን አፍ አፍ ያዩ ጀመር። ሀወኒ ትንፋሽዋ አጠረባት፣

«... አኖሌ ልጃችን በመጨረሻ አንድ ወረቀት ፅፎ ለሀወኒ እንዳደርስ አዞኝ ነበር። ለራስዋ ካልሆነ ለማንም መስጠትም ሆነ መንገር እንደማይገባኝ ነግሮ አስማለኝ። ሁዋላ የሀወኒ የመታሰር ወሬ ተሰማ። ይህ ሲሆን ሀዘን ተሰማኝ። ህይወቱ ከማለፉዋ በፊት አምላክ ከሀወኒ ጋር ያገናኘኝ ዘንድ ሀሎት ሳደርስ ሰነበትኩ። ይኸው ዋቀዮ ልመናዬን ሰማ።»

ይህን ብለው ሽማግሌው አጎንብሰው መሬት ሳሙ።

ገበሬዎች በድንገተኛ እልልታ ቡርቃን አናወጡት።

ሽማግሌው ደጋግመው መሬቱን ስመው ሲያበቁ ከተጨረማመተው መታጠቂያቸው ስር የተጠቀለለች ወረቀት አውጥተው በገበሬዎቹ ፊት ለሀወኒ አስረከቡ።

እልልታው ጋብ አላለም። አኖሌ ከሞት ተነስቶ የመጣ እስኪመስል እልልታው ቀጠለ፣

ሀወኒ ወረቀቱን በችኮላ ተቀብላ ገላለጠችው። ስለመሸ ማንበብ ተሳናት። ባትሪዋን ከኪስዋ አውጥታ ወረቀትዋ ላይ አበራች።

አጭር መልእክት ነበር፣

«ሀወኒ ደህና ሁኚ! ... ማስታወሻ ይሆንሽ ዘንድ አባቦኩ ኮረብታ ላይ ባለችዋ የዋርካ ዛፍ ስር አንድ እቃ አኑሬልሻለሁ። ቻው!»

አንብባ ስታበቃ ቀና አለች። አይኖችዋ በእንባ ተሞልተው ነበር። ገበሬዎቹ ትንፋሻቸውን ውጠው በጉጉት ይጠብቁዋት ጀመር፣

«ወገኖቼ!» ስትል ጀመረች «... ንፁህ ልባችሁ እንደነገራችሁ

... ልጃችሁ አኖሌ ሳይሞት አልቀረም።»

* * *

በነጋታው ተሲያት ላይ የቡርቃ ገበሬዎች ሀወኒን በአይናቸው ለማየት ስለበቁ በድጋሚ ከፍተኛ ድግስ አዘጋጁ። በአይናቸው... የአኖሌን ስም እያነሳሱም ተከዙ። በሀወኒ ደሞ ተፅናኑ። ብርዙ፣ ቁንዲፍቱው፣ የጠቦት ጥብሱ ማለቂያ የለውም። ወጣቶች የፈረስ ጉግስ ትርኢት እያሳዩ ቡርቃን እሰተ - በአል አስመሰሉዋት።

ሀወኒ ያን ቀን ማምሻውን ሆርዶፋን ጠርታ እንዲህ አለችው፣

«የአባቦኩ ኮረብታ ከዚህ ብዙ ይርቃል?»

«አኖሌ የነበረበት?»

«እህ።»

«በፈረስ ከሆነ ምናላት?»

«ዛሬማታ ወደዚያ ብንሄድስ?»

«ምን ችግር አለ?» ሲል አቃለለው።

«ማታ መሆኑ ያስፈራል እንዴ?»

«ኧረ በዋቀዮ!» ብሎ ጮኸቱን ለቀቀ። «... ኦሮሞ እንዴት ጨለማ ይፈራል?»

ሀወኒ ሳቀች። በጣም ሳቀች። ሆርዶፋ ስትስቅለት ሞቀውና ደሰኮረ፣

«ይልቁን እውነቱን ልንገርሽ ሀወኒ ... ጨለማው ራሱ እኔን ይፈራኛል! ድፍን ቡርቃ ይሄን ያወራል። ሆርዶፋ ካለ ድቅድቁ ጨለማ ወገግ ይላል። ጅብ በየጉሬው ይከተታል ... ቀበሮ ተወርቶአል»

ሆድዋን ይዛ መሳቅ ሆነ። በሳቅ ብዛት እንባዋ ባይንዋ ሞላ። የሆርዶፋ ከልክ በላይ መደሰት አዝናናት።

ከዚያም እንዲህ አለችው፣

«በል የምትይዘውን ልንገርህ። አንድ ፋኖስ - ዶማ -





አካፋ - ጠመንጃ እና ሁለት ፈረስ።»

«ይኸ ሁሉ ለምንድነው?» ሲል ጠየቀ።

«ሁዋላ እነግርሀለሁ።»

ለአይን ያዝ ሲያደርግ ቡርቃን ለቀው ወደ አባቦኩ ኮረብታ ይጋልቡ ጀመር። ሀወኒ መጋለቡን አልረሳችውም። ጭንዋ መሀል ቢቆጠቁጣትም ቻል አድርጋው ግልቢያዋን ቀጠለች። ጨረቃ ደምቃ በመውጣትዋ ጉዞው ሳያስቸግራቸው ካሰቡት ጊዜ ፈጥነው ወደ ኮረብታዋ ተቃረቡ። የሞቀ ወግ ይዘው መንገዱ ሳይታወቃቸው ተገባደደ። ሆርዶፋ መቼም ወግ አያልቅበት፤ በኦሮሞና በአማራ ገበሬዎች መካከል ግጭት በተነሳበት ጊዜ የፈፀመውን ጀብዱ እያደነቀ አጫወታት። ተርኮ ሲያበቃም፣ ጠመንጃውን ብድግ እያደረገ፣

«ይቺ እኮ አኖሌ የላከልኝ ራስዋ ናት» አላት።

«መቼ ነው የላከልህ?»

«በዚያው ሰሞን ነዋ። ምን ለኔ ብቻ። ድፍን ቡርቃ ደርሶታልኮ»

«አኖሌ የላከው?»

«እንዴታ!»

«አኖሌ ይህን ስለማድረጉ እኔ አላውቅም» አለች።

«ታዲያ ጠመንጃ ሳይልክ። 'ዘመቱ!' ቢለን 'በምናችን!' ባልነው አልነበር?»

«አኖሌ ዝመቱ ብሎአችሁዋል እንዴ?»

«ኧረ በዋቀዮ!» ብሎ ተገረ ። «... አኖሌ እኮ ቆራጥ ጀግና ነው። ድምፁ ራሱ እንደ ዋቃ ... ነውኮ።»

«ጠመንጃ የላከላችሁ እነግ ...ስሎኝ ነበር ...» አለችው፤ ሀየሉም 'የአነግ እጅ አለበት' ያላትን አስታውሳ።

«እናግ ምንድነው ሀወኒ? ዳዶኡኦ የሚባለውስ?»

የፖለቲካ ድርጅቶች መሆናቸውን በሚገባው መንገድ አስረዳችው።

ሆርዶፋ ጥያቄውን አራዘመ፣

«ኦፒዶና ኦህዴድስ ማናቸው?»

ሀወኒ ሳቀች:: በፀጥተኛው ጨለማ ውስጥ ውብ ዝማሬዋ እንደርችት ብልጭ አለ! መልሶ ግን ድርግም::

«ሀወኒ!»

«እህ»

«ስትስቂ ደስ ነው የሚለው»

«እውነት?»

ማለላት - በዋቆ አባዱላ ስም:: ምሉ ሲያበቃ ወደ ጥያቄው ተመለሰ::

«በይ ንገሪኛ! ማናቸው አፒዳና እህዲድ?»

አፒዲአና እህዴድ የዳዴኡአ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ስሞች መሆናቸውን ነገረችው::

«ዳዴአኡ ብዙ ስም ምን ያደርግለታል? ኦሮምኛ አይበቃውም?»

ሀወኒ ምላሽ አልሰጠችውም:: ለራስዋ አንድ ጥያቄ እያነሳች ነበር:: ሀወሀት የአማርኛ ስም ለምን የለውም? አነግና እህዴድስ ስማቸውን ወደ አማርኛ መተርጐም ለምን አስፈለጋቸው? ለዚህ ያበቃን ሳናውቀው የተጠናወተን ራስን የመሸሽ አባዜ ይሆን? ስትል ራስዋን ጠየቀች:: ይህን እስከዛሬ አለማስተዋልዋ ደነቃት:: ሆርዶፋ ላይ መሳቅዋ አሳፈራት:: በግልባጩ የሆርዶፋ አመለካከት የተሻለ ሆኖ ተሰማት:: ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ተጉዋዙ:: ሆርዶፋ መችም ጥያቄ አያልቅበትም:: ደሞ ስምዋን ጠራ!

«ሀወኒ!»

«ሆርዶፋ»

«ከዳዴኡአና ከአናግ ማን ይሻለናል?»

ሀወኒ ምላሽ ለመስጠት አላመነታችም::

«መጀመሪያ መንገድ ሲሰራ የሚመጣውን፤ ክሊኒክ፣ ትምህርት ቤት፣ ኤሌክትሪክ ሲገነባና ሲያስፋፋ በርቃ የሚደርሰውን ደግፉት:: በኦሮሞነቱ የሚኰራ እሱ ወገናችሁ ነው:: የናንተ ወገን ክብርና ኩራታችሁን የሚያስጠብቅላችሁ፤ አሳልፎ ለዘራፊ የማይሰጣችሁ፤ እሱ ነው ወገናችሁ:: የነካ ተራራን የሚያህል ምላስ ይዘው የሚመጡትን አዋርዳችሁ





አባርሩዋቸው::»

ሆርዶፋ ተጨማሪ የማብራሪያ ጥያቄ አልነበረውም:: ዝም አለ:: ምላሽዋ አጠገበው::

እንደገና ለደቂቃዎች በዝምታ ተጉዋዙ:: አሁን ደግሞ ጠያቂዋ ሀወኒ ሆነች!

«አንድ ነገር ልጠይቅህ ሆርዶፋ»

«የፈለግሽውን ጠይቂኝ::»

«ሚስት ለምን አላገባህም?»

ዝም አለ::

«ደሞ እዚህም እዚያም ትላለህ አሉ::»

«ካንቺ ሊያቀያይሙኝ ነው ይሄን የሚነግሩሽ?» አለ በቁጣ::

«አይደለም:: እንድመክርህ ነው የነገሩኝ:: እኔ ታላቅ እህትህ አይደለሁ እንዴ! ቢነግሩኝ ምናለበት?»

«አንቺ ካልሽ ሚስት እፈልጋለሁ::»

«ጐበዝ!» ብላ አደነቀችው::

«ግንኮ ራሳቸው ናቸው ያበላሹኝ»

«እነማ?»

«ሴቶቹ»

«ምን እያደረጉ አበላሹህ?»

«አንድ ቀን ቀምሼህ በሞትኩ እያሉ ውሃ ሲቀዱ ለምን ይዘፍናሉ?»

ሳቅዋን ለቀቀችው ...

የኦሮሚያ አእዋፍት ተሰባስበው የሚያዜሙ መሰሉ::

«ሀወኒ»

«እህ»

«በተራዬ እኔ ልጠይቅሽ?»

«ምን?»

«እውነቱን ትነግሪኛለሽ?»

«አልዋሽህም።»

«አኖሌ ከሚማረክ እዚሁ አባቦኩ ላይ ቢሞት አይሻለውም ነበር?»

«መቼ ተማረከ ታዲያ?» አለች ቆሌዋ ክው ብሎ።

«ምን ማለትሽ ነው?» አላት ተኮርሞ። «... አንቺ እንዴት ይኼን አታውቂም?»

«ምንም አላውቅም ሆርዶፋ። ምንድነው አንተ የምታውቀው? ንገረኝ እስኪ?»

«ከአባቦኩ ኰረብታ በስተቀኙ ባለው ሸጥ ሲወርድ ትግሬዎቹ ራሳቸው ነው የተቀበሉት። ከዚያም ሁሉም በየተራ ጨብጠውት በፉርጉጌዋ ይዘውት አይደለም እንዴ የሄዱት። ይህን ባይኑ ያየ ገበሬ ነው ለማንም እንዳላወራ በዋቆ አባዱላ ስም አስምሎ የነገረኝ። ላንቺ በመንገሬ ግን ግዴለኝም።»

«ይኸ ሀሰት ነው ሆርዶፋ!»

«የነገረኝ ሰው አይዋሽም ሀወኒ። ግን የምጠይቅሽ ምን መሰለሽ? ከዚህ ከወሰዱት በሁዋላ መግደላቸው ግፍ አይደለም? ተስማምተው በፉርጉጌ ወስደውት ሲያበቁ ...»

«ማነው መገደሉንስ የነገረህ?»

«ከፊንፊኔ የመጣ ሰው አንድም ሳይቀር የሆነውን ሁሉ ነግሮኛል።»

ወሬዎቹ ሁሉ መያዢያ መጨባጫ የሌላቸው ሆኑባት። አኖሌ ዞሮ ዞሮ ግን አንድ መደምደሚያ ላይ መድረስ ችላለች። አኖሌ ሞቶአል!

ዋርካው ዛፍ ስር ምን ይሆን ያኖረው? ስትል አሰበች።

«ሀወኒ»

«እህ ... ሆርዶፋ?»

«አኖሌን የምር ገለውታል?»

ረጅም አየር አስወጣች። መልስም ሳይጠብቅ ሆርዶፋ ቀጠለ።

«የምኒልክ ወታደሮችም እኮ አባቦኩን እዚህ ነው የገደሉት» አላት።





ምላሽ ሳትሰጠው ቀረች።

ከዚያ ወዲያ ጨዋታቸው ተገቀገዘ ብሎ ጥቂት ተጉዋዙ።

ዳሩ ሆርዶፋ መች ያርፋል። ወደሌላ ጉዳይ ደግሞ ዘለለ፣

«ሀወኒ።»

«እህ!»

«ግን አንቺ ለምን ታሰርሽ?»

«እኔንጃ ሆርዶፋ» አለች በተጉዳ ስሜት።

«ከአኖሌ ጋር በመተባበርሽ ነው?»

«ነው መሰለኝ።»

ከልብ አልነበረም የምታዳምጠው።

«እጮኛሽ አይደል እንዴ ብትተባበሪ ምናለበት?»

ሀወኒ ፈገግ አለች።

መልስ አልሰጠችውም። ሆርዶፋ ግን ምላሽ ፈለገ፣

«ከእጮኛው ጋር የማይተባበር ሰው አለ እንዴ?»

«ይህን ሌላ ቀን በደንብ አጫውትሀለሁ» አለችው።

«ሀወኒ ...»

«እህ ...»

«የቡርቃ ዝምታ የሚያበቃው ታዲያ መቼ ነው?»

«ትምህርት ቤት ሲከፈት» አለችው ጫን ባለ ድምፅ። ... «ያን ጊዜ ቡርቃ እንደ አባይ፣ እንደ አዳባይ፣ እንደ አንሰባ፣ እንደ ተከዜ ... በኦሮሚያ ምድር ሁሉ በኩራት ይፈሳል። ከተባበርን የማይበገር ሃይል እንሆናለን። ከተከፋፈልን ደግሞ ለሚጠሉንና ለሚንቁን እልልታ ነው።»

እንደገና ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ተጉዋዙ።

«ውድ ወንድሜ ሆርዶፋ! ያ የሚታየን የአባቦኩ ኮረብታ አይደለም እንዴ?»

«ነው፣ ሀወኒ»

«መልካም እንግዲህ። ፈረስህን አቁምና ወደዚህ ኰረብታ

ለምን እንደመጣን ላውጋህ»

ከፈረሶቻቸው ወርደው በአካባቢው ካሉ አለቶች ላይ አረፍ ካሉ በኋዋላ በኩሬብታው ላይ ስለተቀበረው ያልታወቀ እቃ አጫወተችው።

ከዚያም ወደ ኩሬብታው አናት አመሩ። በጨለማው ውስጥ ዋርካዋ ታየቻቸው። የአሮሚያ ዋርካ። ዋርካዋ በፀጥታ ቁማለች።

ሆርዶፋና ሀወኒ ዋርካዋ ስር ደረሱ። ፋኖሳቸውን በቅርንጫፉ ላይ ሲያንጠለጥሉት አካባቢው ወገግ አለ።

«ሆርዶፋ፤ በል እዚህ ላይ ቆፍር» ብላ የዋርካዋን ስር አመለከተችው።

መቆፈር ጀመረ። መሬቱ ለስላሳ በመሆኑ በቀላሉ ይጐደፈር ጀመር። በደቂቃዎች ውስጥ ግማሽ ሜትር ጉድጉዋድ ቆፈረ። ከዚያ ግን መቀጠል አልቻለም። የዋርካው ስር ከለከለው።

«ወደጐን ሞክር» አለችው።

እልፍ ብሎ መሬቱን ይበዳድሰው ጀመር። ሰስት ጊዜ እንደሰነዘረ «ቂዋ - ቂዋ» የሚል ድምፅ ሰሙ።

«ቆይ! ... ቆይ!» አለች ሀወኒ።

ቁፋሮውን አቆመ።

«በእጅህ ነካው እስኪ» አለችው።

ሆርዶፋ ዶማውን ጥሎ አፈሩን በእጁ እየዛቀ አውጥቶ ሲያበቃ፣ አራት ሊትር ሊይዝ የሚችል የዘይት መያዣያ ቆርቆሮ ጐትቶ አወጣ።

ሆርዶፋ ቆርቆሮውን ለሀወኒ አቀበላት። ተቀብላ አንላበጠችው። ቀላል ነው። ቻኰለች። ውስጡ ያለውን ለማወቅ ጉዋጉዋች። ዙሪያ ገባውን ፈታተሸችው። ተከፍቶ መልሶ የተገጠመ ነበርና ለመክፈት አልተቸገረችም። ከፈተችው። እጅዋ አንድ መፅሀፍ ይዞ ወጣ።

«ምንድነው?» አለ ሆርዶፋ።

«መፅሀፍ ይመስላል» ብላ ወደ ፋኖሱ ተጠጋች። መፅሀፍ አልነበረም። ማስታወሻ መያዣያ አጀንዳ እንጂ። ሀወኒ አስታወሰች። ከሶስት መቶ ገፅ በላይ ቅጠል ያለው የአኖሌ





**የእለት ውሎ መመዝገቢያ** ደብተር ኖሮአል። በተገናኙባቸው **ጥቂት ጊዜያት** ውሎውን በደብተሩ ላይ ሲያሰፍር ማየትዋን **አልረሳችም**።

«ሆርዶፋ።»

«ሀወኒ።»

«ጨርሰናል እንመለስ።»

የመልስ ጉዞ ጀመሩ። ጨረቃዋ ደማቅ ነበረች። ደማቅ ቢጫ። ቢያንስ ጨለማውን አባርራ ለመንገዳቸው አስተዋፅኦ ማድረግ የፈለገች ይመስል ቡርቃ ድረስ ሸኘቻቸው። ካካ ተራራ ጥላውን በቡርቃ መንደር ላይ እንደ ብርድ ልብስ አንጥፎታል። ቡርቃ በዝምታ ተውጣ ተቀበለቻቸው - በእንቅልፍ ዝምታ።

- 3 -

ሀወኒ ከቡርቃ አእዋፋት ጋር ነቃች ...

የአእዋፋቱ ዜማ ስንጥቃት በበዛበት በርና መስኮት እየሾለከ ገብቶ በጆሮዋ ሲንቆረቆር ነበር ከእንቅልፏዋ የነቃችው።

ተነስታ ወደ ኩረብቶቹ ወጣች።

በእጅዋ የአኖሌን የግል ማስታወሻ መያገርያ ደብተር ይዛለች። ኩረብታውን መውጣት እንደጀመረች ዘወር ብላ ተመለከተች። ሰማዩ እንደ ስጋጃ ከተነጠፈው ለምለም የአርሲ ምድር ጋር ተገጣጥሞ ይታያል። ለአይን አይጠገብም። የማለዳው አየር ነፋሻ ነው። ፀጥተኛ ገጠር። በደን የተሸፈነ ምድር። ውሃ የጠገበ መሬት። ውሃ ያጋተ ሰማይ ...

አንዲት ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ተቀመጠች። ደስ አላት። ይህ ሁኔታ ክሳድ ግመልን አስታወሳት። ትግራይ። የአሁኑ ስሜትዋ ግን ከዚያ ላቅ ያለ ነው። ይህ የተወለደችበት መሬት ነው። አሁን አላማ አላት። አሁን ህዝብዋን በቀጥታ በማገልገል ላይ ናት።

ሀወኒ ዋቆ!

የአኖሌን የግል ማስታወሻ ማንበብ ጀመረች ...

ጀርመን ላይ የተጀመረ ...

እንዲህ ሲል አስፍሮአል «ጀርመን ያሉ ኦሮሞ ጉዋደኞቼ 'በታላቅዋ ጀርመን እንድቆይ መከሩኝ::' ሳቅሁባቸው:: ወደ ሀገሬ መመለስ አለብኝ:: ሀብታም ሀገር አለኝ:: ከብረት የጠነከረ ፍቅር የሚለግሰኝ ህዝብ አለኝ:: ሀዊ ትናፍቀኛለች:: ሀወኒ ልጆች እንድትወልድልኝ እፈልጋለሁ ...»

ገጠመኞቹን ልቅም አድርጐ አስፍሮአል:: የእለት ገጠመኙን መዝግቦ ሲያበቃም በቀዋሚነት አንዲት ቃል ያሰፍራል::

«ሀወኒ ... አፈቅርሻለሁ!»

* * *

ሀወኒ ማንበብዋን ቀጥላለች ...

ሶስት ሰአት ያህል በፀጥታ አነበባ ቀና አለች:: ከቡርቃ ገበሬዎች ጐጆ ጢስ ይቦለቦላል:: በስራ ብዛት ወገባቸው የጕበጠ የቡርቃ ሴቶች ገንፎ እያገነፉ ይሆናል::

ከጀርባዋ ባለው ጥቅጥቅ ያለ ደን ድምፅ ይሰማታል:: የጉሬዛዎች - የዝንጀሮዎች - የጦጣዎች ድምፅ:: ከዛፍ ዛፍ እየዘለሉ የማለዳዋን ፀሃይ መሞቅ ጀምረዋል:: የዋነስ ድምፅም አለ - 'ኩኩ መለኰቴ' የሚል::

ሀወኒ የአኖሌን ማስታወሻ አጋምሳዋለች ...

ለምን ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰ ፅፎአል:: የቡርቃ ገበሬዎችን አመፅ በዝርዝር አስፍሮአል:: ስለቡርቃ ዛፎች ውፍረትም አልቀረው:: 'የቡርቃ ሰርዶ አድጐና ተመችቶት መጥረቢያ ካልሆነ ማጭድ አይደፍረውም' የሚለው አነላለፁ አሳቃት:: ቡርቃና ኦሮሚያን ከልብ እያደነቀ፤ ኦሮሞነቱን እያሰበ፤ የአመፅ ስሜት በልቡ የተቀጣጠለባቸው ጊዜያቶች መሆናቸውን ሀወኒ ተገነዘበች:: '... ማሩ በየዛፉ ሆድ ሞልቶ ይፈሳል:: የእጣን ዛፎች፤ የወይራ ዛፎች:: ዛፎቹ ተጠቅጥቀው ነው የበቀሉት:: ከወፋፍራም ዛፎቹ ስር ችግኞች ፈልተዋል:: ትንሽ ብሎ ለማያያቸው ልምላሜያቸው ይማርካል:: የረገፉ ቅጠሎች እንደ ፍራሽ ተከምረዋል' እያለ ይቀጥላል የአኖሌ ማስታወሻ:: እስቂኝ አባባሎችም ነበሩት 'ርግጠኛ ነኝ፤ እግዚአብሄር ኦሮሞ ነው' የሚለውን ስታነብ ማስታወሻ ደብተሩን አጥፋ በሳቅ ነበር





የፈነዳችው:: ሻለቃ ጉተማ ስለሚባል ኦሮሞነቱን የሸጠ ከፍተኛ መኰንንም ተርኮአል:: ጂብሪል ስለሚባል አለቃው፤ ሳሙኤል ወልደአብ ስለሚሉኝ ኤርትራዊ ጉዋደኛው በስፋት አስፍሮአል:: የብዙ ሴት ስሞችም ነበሩ:: ዜነት - ሮዛ - ዮዲት ... እዚህ ላይ ሀወኒ እንደማቃሰት አለች:: ሰውነትዋን በረዳት:: ግን ቻል አደረገችው::

ከአስመራ እስከ ሻእቢያ ነፃ መሬት ያደረገውን ጉዞ በሚደንቅ ሁኔታ ተርኮታል:: ሻእቢያ ዘንድ በቆየባቸው ጊዜያት ያገኛቸውን ልምዶችም አኑሮአል::

ከደርግ መውደቅ በሁዋላ አስመራ በተዘጋጀ አንድ ግብዣ ላይ «ኩምሳ» ከሚባል የዳዴኦኦ አመራር አባል ጋር መተዋወቁንም ያነሳል:: ኩምሳን አስመልክቶ ካሰፈራቸው አስተያየቶች አንደኛው መገረምን ጫረባት:: «... ኩምሳ እጅግ የሚገርም ባህርይ አለው:: ይህም ባህርይው 'ንዴት' የሚባል ያልፈጠረበት መሆኑ ነው:: ማንኛውንም ጉዳይ ቀለል አድርጐ ያየዋል:: ይህ ሰው እጅግ ዘሳል ሊሆን ይችላል:: አለያ ደግሞ ኦሮሞ አይደለም:: ምክንያቱም» ይላል የአኖሌ ማስታወሻ «... ኦሮሞ የሆነ ሰው ሁሉ በሚናደድባቸው ርእሰ ጉዳዮች እርሱ ተረጋግቶ ይናገራል::»

እኩለ ቀን ሲሆን ምንም አልቀረውም ...

ሀወኒ የአኖሌን ማስታወሻ ወደ ማጠናቀቁ ተቃረበች:: ትንፋሽዋ መቆራረጥ ጀመረ:: አኖሌ አባቡኮ ኰረብታ ላይ በሆዮሎም አርእያ በተከበበባት ደቂቃ በቀጥታ ለርስዋ ነበር የሚፅፍላት ...

- ሀዊ ልስናበትሽ ነው:: ለመሰዋትም ወስኜያለሁ:: ሄሊኮፕተሮች ያንዣብባሉ:: እዚህ መሆኔን እንዴት ደረሱበት? አይዞሽ ሀወኒ:: አንቺን አልጠረጥርሽም:: የአላማ ልዩነት ቢኖረንም እንኩዋ ሞቴን እንደማትፈልጊው አውቃለሁ:: ልብሽን አውቀዋለሁ:: ልቦቻችን ተመሳሳይ ዜማ አላቸው:: ሀዊ ልስናበትሽ::

አላማዬ ግቡን አልመታም:: የኔ ጉዞ እያለቀ ይመስላል:: ርግጥ ነው ትግሉ ይቀጥላል:: የኦሮሞ ልጆች እውነተኛዋን ነፃነት እስኪጨብጡ ይታገላሉ:: ለትግሉ መጠንሰሻ የሰበሰብኩትን ገንዘብ አብረውኝ የነበሩት ይዘውት ጠፉ:: ባዶዬን ነኝ:: ሁለት ታማኝ ወዳጆቼ ብቻ ናቸው አብረውኝ ያሉት ...

ዳህና ሁኝ ሀወኒ ...

የምናዘዘው ብዙ ነገር የለም። ያንቺ የልብ ወዳጅ ሀየሎም አሁን አንድ ገበሬ ልኮ 'እጅህን ስጥ' አለኝ። 'ሌላ አማራጭ የለህም' አለኝ። እንደ አላማ ቢስ ሰው አለያም እንደ ተራ ዘራፊ ቆጥሮኛል ማለት ነው። ያሳዝናል። ብቻዬን ተዋግቼ ስሰዋ ግን ማንነቴን ይገነዘብ ይሆናል። ይህንኑ ልኬበታለሁ። እጄን ታስሬ ወህኒ የምጣል ሰው አይደለሁም። ለቡርቃ ወገኖቼም ሆነ ለኦሮሞ ህዝብ አርአያ መሆን እሻለሁ።

... ሀወኒ የኔ ፍቅር ... ቻው!

ሁሉም ነገር እያበቃ ነው።

ሀየሎም ሁለተኛውን መልእክት ደግሞ ላከ። አብርሀ ፀሎት መጣ። 'እጅህን ስጥ' አለኝ አብርሀ። ህይወቱን በማትረፍ ውለታ ሊመልስ አሰበ። የሚቆነጥጥ ምላሽ ሰጠሁት። ሲጋራውን በንዴት እየማገ ተመለሰ። በፈገግታ ሸኘሁት። መሆን የነበረበት ይኸው ነው። ሆኖአልም።

በነገራችን ላይ ይህ ኮረብታ ለምን አባቦኩ እንደተባለ ታውቂ የለ? አሳማው የምኒልክ ጦር የአርሲውን አባቦኩ የከበባቸው እዚህ ኮረብታ ላይ ነበር። ሀየሎም ዛሬ እንደፈፀመው የምኒልክ ጦር ፊትአውራሪ 'እጅህን ስጥ ተከበሀል' የሚል መልእክት ለአባቦኩ ሰደዱ። አባቦኩ ምን እንደመለሱ ታስታውሽ የለ? 'አላወቃችሁም እንጂ የተከበባችሁት እናንተ ናችሁ። የኦሮሞ ህዝብ ከቦአችሁዋል' ሲሉ መለሱ።

እነሆ ታሪክ ራስዋን ደገመች።

ምን ቀረኝ የኔ ውብ?

አዎን አንቺኮ ውብ ነሽ። አንቺን የመሰለ ማን አለ? ለኔ ማንም የለ። ልስናበትሽ ነው። እንደ ግል ወዳጅሽ በምትቆጥሪው ሰው ትእዛዝ በመገደሌ የተምታታ ስሜት ውስጥ አትግቢ። እንደ ተራ አጋጣሚ ቁጠሪው። አዲሶቹ ነፍጠኞች ከምኒልክ ዘመን ነፍጠኞች በአንድ ነጥብ እንደሚሻሉ ግን ልገልፅልሽ እፈልጋለሁ። ይህም የዘመናችን ነፍጠኞች የከበቡትን ሰው ከመግደላቸው በፊት ሁለት ጊዜ ያስጠነቅቁታል። ቀልድ ነው። መራራ ቀልድ ...



**በቡርቃ ደን ውስጥ የአንዲት ወጣት ሴት የመንሰቅሰቅ ድምፅ ተሰማ። ግንባርዋን ጉልበቶችዋ ላይ ደፍታለች። ሰውነትዋ እየተንቀጠቀጠ ታነባለች። እንባዋ ማቋዋረጫ ያለው አይመስልም ...**

# ድህረ - ታሪክ

... ቀይ ባህር አፋፍ ላይ ተቀምጫለሁ፡፡

አጠገቤ ሀወኒ አለች፡፡ የምፅዋ ሙቀትና የዳህላክ ሆቴል መስተንግዶ ተስማምቶኛል፡፡ በዚህ ላይ ከምቹው የአካባቢ ሁኔታ ጋር የተዋሀደው የሀወኒ ወግ ልዩ ሀሴት ፈጠረልኝ፡፡

ሀወኒን ማዳመጥ አይሰለችም፡፡

ረጅም ታሪክዋን ስታወጋኝ አንዳንዴ ስሜት ያሸንፋታል፡፡ እንባና ሳቅ፡፡ ሁለቱም ያምርባታል፡፡

በምፅዋ ሁለት እጅግ ጣፋጭ ቀናት አሳለፍን...

ከምፅዋ ወደ አስመራ የመልስ ጉዞ ስናደርግ ሀወኒ አኖሌን በተመለከተ ጥቂት ነገሮች አጫወተችኝ፡፡

አኖሌ አልሞተም፡፡ ከአባቦኩ ኩረብታ ያለችግር ወጥቶ ኤርትራ መግባት ችሎአል፡፡ ግን ከአባቦኩ ኩረብታ እንዴት ወጥቶ ኤርትራ መድረስ ቻለ? ሀየሎም የፃፈለት ደብዳቤ ይዘትስ ምንድነው? ለመስማት እየጉዋጉዋሁ ነበር ይህን ጥያቄ ለሀወኒ ያቀረብኩት፣

ሀወኒ ፈገግ አለች፣

«ይገርምሀል፣ ይህንን እኔም እስካሁን አላውቅም፡፡ ስለጉዳዩ

ለአኖሌ እነስቼለት ነበር፡፡ ከሀየሎም ጋር አንድ የሚያግባባ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ብቻ ነው የነገረኝ፡፡ ደብዳቤውን ሊያሳየኝ ግን አልፈቀደም፡፡ አጥብቄ ስጠይቀው ያጣጥልብኛል፡፡ ተራ ጉዳይ ነው፤ እርሺው! ይለኛል፡፡»

«እኔ ብጠይቀው ይነግረኝ ይሆን ታዲያ?» ስል በጥርጣሬ ጠየቅሁዋት፡፡

«ምንር አይታወቅም» አለችኝ፡፡

«አንቺ የአኖሌን በህይወት መኖር መቼ ሰማሽ?» የሚል ጥያቄ አስከተልኩ፡፡

«አሁን ... ከአንድ ወር በፊት ...» አለች፡፡

«እንዴት?»

«ቻይና ነበርኩ፡፡ ከመስኖ እርሻ ጋር በተያያዘ የጀመርኩትን ኮርስ አጠናቅቄ ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ በተዘጋጀሁባት ደቂቃ ላይ ሀየሎም ደውሎ ነገረኝ፡፡»

«ምንለሽ?»

«አኖሌ በህይወት መኖሩንና አስመራ እንደሚገኝ ብቻ ነበረ የገለፀልኝ፡፡»

«እንዲያ ሲልሽ ምን አልሽ?»

የሀብኒ ገፅታ ተለዋወጠ፤ ጉንጮችዋ ቲማቲም መሰሉ፤

«አነቀስኩ!» አለች፡፡ አሁንም ቅንድቦችዋን እያርገበገበች «... ይህን የመሰሉ ነገሮችን በቀላሉ ማስተናገድ አልችልም፡፡ ስሜቱ ለእንባ ቅርብ ነው፡፡ በዚህ ላይ አኖሌ ለኔ ህይወት ልዩ ትርጉም ያለው ሰው ነው፡፡ ወንድሜም ፍቅረኛዬም ነው፡፡ አኖሌን በጣም እወደዋለሁ፡፡ በዚህ ምክንያት የአኖሌን በህይወት መኖር ስሰማ የተሰማኝን ደስታ እንዴት ብዬ ልገልፅልህ እችላለሁ? ሌሊቱን እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር አደረ፡፡ በነጋታው ቤጂንግን ለቅቄ አስመራ ገባሁ ...»

«ሀየሎምና ክንፈ የአኖሌን አለመሞት የደበቁሽ ግን ለምን ይመስልሻል?»

«ሳላውቅም፡፡ ምናልባት ይህን ጉዳይ የሚያውቀው ሀየሎም ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡ ለነገሩ ለዚህ መልስ መስጠት ያለበት ሀየሎም ነበር፡፡ ሀየሎም ግን አሁን በህይወት የለም» ብላ ትክዝ አለች፡፡ በዚያው ቅፅበት ሽፋሽፍቶችዋ ረጥበው ታዩ፡፡ ሰውነትዋን እንደማንቀጥቀጥ እያደረጋትም «... ምናልባት ሀየሎም ጉዳዩን በምስጢር ለመያዝ የተገደደው የድርጅቱን መመሪያ ጥሶ የፈፀመው ድርጊት ሆኖ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ርግጠኛ ግን አይደለሁም ...»

* * *

በነጋታው ሰንበት ስለነበር አኖሌን ለማግኘት ተሲያት ላይ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሄድኩ፡፡ ሀወኒ በር ከፍታ ስታስገባኝ፤

«ትናንት ስላንተ ነግሬው ነበር፡፡ እምብዛም ደስተኛ አልሆነም፡፡ ሚያናግርህ አይመስለኝም፡፡ ቢስድብህም ግን ቻለው፡፡ እጁጌውን ጠቅልሎ በጡ ሊያወርድብህም ይችላል፡፡ ምን ታደርገዋለህ?» እያለች ነበር ከአማገሪ ሳሎን ውስጥ ወስዳ ያሳረፈችኝ፡፡

ዘግይቶ ነበር ወደኔ የመጣው፡፡ ከታች ግራጫ የቱታ ሱሪ፤ ከላይ ቤዥ ቀለም ያለው ቲሸርት ለብሶ አምሮበታል፡፡ ወዙ ፊቱ ላይ ተንጠፍጥፎአል፡፡ በርጋታ ሰላምታ አቅርቦልኝ ፊቱ ካለው ፎቴ ላይ ተቀመጠ፡፡ ሀወኒ ሆን ብላ ነው መሰል ብቅ ሳትል ቀረች፡፡

«ልታናግረኝ መፈለግህን ሀወኒ ትናንት ነግራኛለች፡፡ ምንድነው ልትጠይቀኝ የፈለግከው?» ሲል በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ገባ፡፡

ፍላጐቴን በአጭሩ አብራራሁ፡፡ ማንነቴን ካስተዋወቅሁ በሁዋላ ከቡርቃ ዝምታ ጋር የተያያዙ ታሪኮችን በመፅሀፍ መልክ የማዘጋጀት ፍላጐት እንዳደረብኝ ገለፅሁለት፡፡

አኖሌ ሀሳቤን ፈጥኖ አጣጣለው፡፡ 'የቡርቃ ዝምታ' የሚባል ታሪክ አለመኖሩንና ጊዜዬን በከንቱ እንዳላጠፋ መከረኝ፡፡

እኔ ግን በአቋሜ ፀናሁ፡፡ ሌላው ቀርቶ በእርሲ የተቀሰቀሰው አመፅ ያደረሰው ውድመት ብቻውን እንኳዋ ከአምስት ያላነሰ ትላልቅ ጥራዝ መፅሀፍ ሊወጣው እንደሚችል ጠበቅ አድርጌ ተናገርሁ፡፡

ቆይቶ አሳቤ መልካም መሆኑን አመነበት፡፡ ዳሩ ግን ምንም አይነት መረጃ ሊሰጠኝ ፈቃደኛ እንዳማይሆን ገልፆ ይቅርታ ጠየቀኝ፡፡ ፈጥኖ ሊያሰናብተኝ በመፈለጉም ቀድሞኝ ከመቀመጫው ተነሳ፤

በዚህ ጊዜ ከጋዜጠኝነት ሙያ የቀሰምኩትን ልምዴን መጠቀም ተገደድሁ:: እኔም ከተቀመጥሁበት እየተነሳሁ፣

«ብትተባበረኝ እንኳዋ ደግ ነበር» ስል ጀመርኩ «ከአባቦኩ ኰረብታ በሰላም መውጣት በቻልክበት ምክንያት ላይ መረጃ ያለው በአንተና በሀየሉም መካከል ብቻ ነው:: ሀየሉም አሁን በህይወት የለም:: አንተ ፈቃደኛ ካልሆንክ የግድ በአሉባልታ ደረጃ የሚታወቀውን መረጃ መጠቀም ሊኖርብኝ ነው» አልኩት::

አኖሌ «ምንድነው በአሉባልታ የሰማኸው?» ብሎ ግንባሩን ጨምደድ አደረገ::

ጥያቄውን ያልሰማሁ መስዬ ልሰናበተው እጄን ዘረጋሁ::

«ቆይ!» አለኝ::

እንደቆምን ተፋጠጥን::

«በአሉባልታ የሰማኸው ምንድነው?»

«ላንተ ምን ያደርግልሀል?» አልኩት::

«ማወቅ እፈልጋለሁ!»

ነገርኩት:: በዚያው ቅፅበት የመጣልኝ ፈጠራ ነበር፣

«እኔ የሰማሁት ከሀየሉም ጋር በገንዘብ መደራደራችሁን ነው::»

«የምን ገንዘብ?»

«አባቦኩ ኰረብታ ላይ የሸሸግኸውን አንድ ሚሊዮን ተኩል ብር ሀየሉም ወስዶ አንተን እንደለቀቀህ በስፋት ተወርቶአል::»

አኖሌ በድንገተኛ ቁጣ ሳሎኑን አናጋው!

«ቅጥፈት ነው! » ሲል ጮኸ «...የወሬ ልማድ ያላቸው ነፍጠኞች የሚያወሩት ባዶ ወሬ! ውሾች! እኔ አኖሌ በዚህ ነፍጠኞች የሚያወሩት ባዶ ወሬ! ውሾች! እኔ አኖሌ በዚህ ነፍጠኞች ... ከሀየሉም ጋር ያሻውን ያህል የአላማ ልዩነት አልታማም! ከሀየሉም ጋር ያሻውን ያህል የአላማ ልዩነት ቢኖረንም ሀየሉም የዚህ አይነት ሰው አለመሆኑን ግን እመሰክርለታለሁ:: ነፍጠኞችን ጭራ ያስቀለፈውን የጀግና ስም ቀብነስቶች ጠላሽት ሊቀቡት ከቶ አይቻላቸውም:: የደናቁርት ወሬ ነው:: አንተም የነርሱ አጨብጫቢ ትመስለኛለህ...» ብሎ በንዴት ሲጠና! በይቅርታ መልክ እንገቴን ደፋሁ፣





«ላስቀይምህ ፈልጌ እንኳዋ አልነበረም» ብዬ ከሳሎኑ ለመውጣት ፊቴን አዞርኩ፤

«ቆይ!» አለኝ::

ቆየሁ:: የጋዜጠኝነት ልምዴን አመሰገንኩት::

«ይህን የበሰበሰ ዝቃጭ አሉባልታ ተሸክመህ እንድ ትዞር አልፈቅድልህም::»

መሳቅ ቢያምረኝም እንደምንም ቻልኩት::

«ቁጭበል» አለኝ::

ቁጭ አልኩ:: እሱም ወንበር ያዘ::

«ማነበር? ስምህ?» ሲል ጠየቀኝ::

ነገርኩት::

«ጂን ይሻልሀል ዊስኪ?»

ጂን መረጥሁ:: ተነስቶ ወደ ጉዋዳ ገባ:: በአንድ ደቂቃ ውስጥ ሁለት ብርጭቆ፣ ጎርደን ጂን ጠርሙስ፣ ከበረዶ ማስቀመጫ እቃ ጋር ይዞ ተመለሰ፤

«ለመሆኑ አማራ ነህ ትግሬ? ወይስ ኦሮሞ? » ሲል ጠየቀኝ ጂኑን እየቀዳ:: ምላሽ ከመስጠቴ በፊትም «ስምህ እንኳዋ የኦሮሞ አይደለም:: ለነገሩ ኦሮሞዎች በነፍጠኛው እየተቀጠቀጡ ስማቸውን ሲለውጡ ስለኖሩ ኦሮሞን በስሙ መለየት አይቻልም::» እያለ ፌዝ ፈገግታ ያሳየኝ ጀመር:: የጥያቄው ምክንያት ባይገባኝም በአጋ ባሚ የሶስቱም ብሄሮች አባል አለመሆኔን ገለፅኩለት::

«ደግነዋ» ሲል ጀመረ «.. የቡርቃ ዝምታ ታሪክ ዞር ዞር ሶስቱን ብሄሮች የሚነካ በመሆኑ ከሶስቱ ብሄሮች ውጪ ያሉ ፀሀፊዎች ቢሰሩት ተመራጭ ይሆናል» ብሎ ሲጋራ ለኮሰ::

«ግን የ ሙያውን የሚያከብር ማንኛውም ሰው ሚዛናዊ ስራ ሊሰራ ይችላል» አልኩት::

«አይምሰልህ» ሲል ተቃወመኝ «... ኦሮሞ የሆነ ሰው እንዴት አድርጎ ነው ስለነፍጠኛ ሚዛናዊ ሀሳብ ሊያሰፍር የሚችለው? ታሪኩን በትክክል ያወቀ ኦሮሞ የምኒሊክን ሀውልት ሳለማየት ሲል ጊዮርጊስን

እንደ ማይረግጥ ታውቃለህ? ያቃጥለዋላ! በገዛ መሬቱ ላይ የተቆላለውን ያን አሳማ መሰል ጭራቅ አይቶ ስሜቱ የማይነካ እርግጥ በድን ነው፤ እሲያም ታሪኩን አያውቅም። ወይ ደግሞ እርግጥነት አይሰማውም ...»

አኖሌ ባጭር ጊዜ ውስጥ ጂኑን ደጋገመ። ስሜታዊነቱ ገደብ የለውም። ሲናገር ደምስሮቹ ይቆማሉ። ትንፋሹ ይቆራረጣል። እልህ ያትከነክነዋል። በዚህ ስሜት እንዴት ረጅም ጊዜ በህይወት መኖር ይቻለዋል? አሳሰበኝ።

«ከኔ የምትፈልገውን አጠር አድርገህ ንገረኝ» አለ አኖሌ፤ ሲጋራውን መተርኮሻው ላይ እየተረኮሰ፣

«በመጨረሻዎቹ ሰአታት ሀየሎም ደብዳቤ ፅፎልሀል። የደብዳቤውን ይዘት ማወቅ እፈልጋለሁ» ስል ጠየቅሁት።

አኖሌ በተረጋጋ መንፈስ በዝምታ ጥቂት ቆየ - ለደቂቃ ያህል። ከዚያም ቃል እንኳ ሳይተነፍስ ተነስቶ ወደጉዋዳ ገባ። ሶስት ደቂቃ ያህል ቆይቶ ሲመለስ ነጭ ፖስታ በእጁ ይዞ ነበር። ልቤ መንጠር ጀመረች። ተመልሶ ከተቀመጠ በሁዋላ ጥቂት የወረቀት ቅጠሎች ከፖስታው ውስጥ አወጣ። አይኖቼ ተጉላጉለው ወረቀቶቹ ላይ አረፉ። የሀየሎም ደብዳቤ መሆኑን ልቤ ነገረኝ።

ምን ብሎ ይሆን የፃፈለት? ምን ሊሰው ይችላል? ምን? እኮ ምን?

«አንብበው! ለጥያቄህ ምላሽ ታገኛለህ» ብሎ የመጀመሪያዋን የወረቀት ቅጠል አቀበለኝ።

የተንጋደዱ ፊደሎች! የሀየሎም የእጅ ፅሁፍ! በዚያች ቀን ምሽት ሀየሎም ሄሊኮፕተር ውስጥ ሆኖ የፃፈው!

በጉጉት ማንበብ ጀመርኩ፣

«ውድ ወንድሜ አኖሌ ...

ይህን ደብዳቤ የምፅፍልህ ሰው ሀየሎም አርአያ እባላለሁ። የወሬ ወሬ ስለኔ ሰምተህ ይሆናል - ከሀወኒ። አንተን የከበበውን ሀይል የምመራው እኔ ነኝ። ሁለት ጊዜ እጅህን ትሰጥ ዘንድ ላቀረብኩልህ ተገቢ ጥያቄ የሰጠኸው ምላሽ 'ተዋግተህ ለመሰዋት'



መወሰንህን ነው።

«እመነኝ አኖሌ አከብርሀለሁ። መጥፎም ይሁን ጥሩ አላማ ያለውን ሰው ማክበር ተገቢ ነው። ለአላማው የሚሰዋ ደግሞ ጀግና ነው። በመሆኑም አንተ ጀግና ነህ። እጅህን ላለማስጠት መወሰንህም ከአላማህ አኩዋያ ተገቢ ሊሆን ይችላል። መሰዋትህም የማይቀር እየሆነ ነው። ምክንያቱም ኩረብታዋ በኢህአዴግ ታጋዮች ታጥራለች። ማለዳ ላይ የተኩስ ልውውጥ ይጀመራል። አንተ በቂ ሀይልና ልምድ ስለሌለህ ትሸነፍና ሁላችሁም ታልቃላችሁ። ያንተ ታሪክም በዚሁ ይደመደማል። ይህን ደብዳቤ የፃፍኩት ይህ ሁኔታ እንዳይከሰት አንድ ጥያቄ ላቀርብልህ ነው። መሞት የለብህም ብዬ ከልብ አምናለሁ። ለዚህ ደግሞ አንድ አብይ ምክንያት አለኝ። ጥያቄዬን፣ በቅንነት እንደምታየው፤ እንደምታከብረው፤ እንደምትቀበለው ጭምር አምናለሁ»

የመጀመሪያውን ገፅ በመጨረሴ ቀና አልኩ። ሁለተኛውን ገፅ ያቀበለኝ ዘንድ በችሎላ እጆቼን ወደ አኖሌ ዘረጋሁ።

ያልጠበቅሁት ዱብ እዳ!

አኖሌ ቀሪዎቹን ወረቀቶች አጣጥፎ ፖስታው ውስጥ ከቶ ጂኑን እያከታተለ መቀንደቡን ተያይዞታል፤ ቆሌዬ ነው የተገፈፈው፤ ጤነኛ አልመሰልህ አለኝ!

«ቀሪውን ስጠኝ እንጂ?» አልኩት።

«መጀመሪያ ገምት» አለኝ።

«ምኑን?»

«ሀየሎም የኔን መሞት ያልፈለገበት ምክንያት ምን ይመስልሀል? ሀየሎም ያቀረበው ምክንያት በወቅቱ እኔን ያሳመነ መሆኑን ሳትዘነጋ አስብና ገምት» አለኝ።

ከባድ ጥያቄ!

ጥቂት አሰብኩ። አልቻልኩም። ለመገላገል ያህል ግን አፌላይ የመጡልኝን ሁለት ምክንያቶች እንደዋዛ ጣል አደረግሁ፣

«ምናልባት ለሀወኒና ላንተ ግንኙነት ሲል ሊሆን ይችላል። ሀየሎም በባህሪው ሩህሩህ ስለሆነ ሰብአዊ ስሜቱ አሸንፎት ቢያደርገው

አይገርመኝም። ወይ ደግሞ አንተ ለአብርሀ ፀሎት የዋልከለትን ውለታ አይቶ ለአብርሀ ፀሎት ሲል ፈፅሞትም ሊሆን ይችላል። ይህ ቢሆን ...»

ተናግሬ እንድጨርስም እድል አልሰጠኝ፣

«...እንዲህ ያለኸው እንከፍ ኖረሀላ» ሲል በጩኸት አስበረገገኝ። እያይዞም ወረደብኝ፣ «... ለመሆኑ ጋዜጠኛና ደራሲ ነኝ እያልክ ስትደሰኩርብኝ ያረፈድከው ይቺኑ የጫጩት አስተሳሰብ ይዘህ ኖሮአል? ወደስነፅሁፍ አለም የጐተተህ የህንድ ፊልም ኖሮአላ! እነ አሚታአብ... እነሻሺ ካፑር፣ እነራጂ ካፑር፣ እነ ቂሎ ካፑር የሚሰሩትን ተረት ግማሽ ጭንቅላትህ ውስጥ ሰግስገህ ኖሮአላ የቡርቃን ዝምታ ልትፅፍ የተነሳኸው። የኛ ደራሲ! ... የቡርቃ ዝምታ ታሪክ የመቶ አመት የሰቆቃ ታሪክ መሆኑን አታውቅም? ለመሆኑ ሀየሉምን እንዲያ ነው የምታየው? እኔንስ እንዲያው እንዴት ብትገምተኝ ነው?»

ደግነቱ ሀወኒ ከጉዋዳ ወጥታ ተቀላቅላን ነበርና እየተያየን መሳቅ ሆነ። የተናገራቸውን እላፊ ቃላት ከጉርደን ጂኑ ጋር እያያዝኩለት።

«መገመት እኮ ከብዶኝ ነው» አልኩት።

«አስብና ገምት» ሲል አስገደደኝ።

ጥቂት አሰብኩና ገመትኩ፣

«ምናልባት ያንተ መሞት በቡርቃ አካባቢ ተነስቶ የነበረውን ግጭት እንደገና ይቀሰቅሰዋል ብሎ ሰግቶ ይሆን?»

«አይደለም» አለ «...ሀየሉም እንዲያ ሊያስብ አይችልም። ወያኔ ድል እያደረገ ወደአማራው ክልል ሲገባ በተለይ የከተማው ህዝብ የኤርትራና የትግራይ ታጋዮችን እየተቃወመ ዱላና ድንጋይ አቅምሶአቸው የለም እንዴ? ሀወኒ ስለዚህ ጉዳይ ነግራኛለች። ይህን መሰል ልምድ ያለው ሰው የግለሰብ ሞት ህዝብን ያነሳሳብኛል ብሎ እንዴት ያስባል? ህዝብም ቢሆን በምክንያት እንጂ በግለሰቦች ሞት ሊያምፅ አይችልም። ይልቅ ሌላ ገምት...»

«አልቻልኩም» አልኩት።

በርግጥም አልቻልኩም ነበር።





«ሞክር።»

«ፍፁም አልችልም።»

«አንድ እድል ልስጥህ?»

«ምናልባት ለሚኒስትርነት ሊያጭህ ፈልጎ ይሆን?»

ፈገግ አለና ቀሪዎቹን የወረቀት ቅጠሎች አቀበለኝ። በጉጉት ማንበቤን ተያያዝኩት፣

«... ለጥቂት አመታት ብቻ ህይወትህን እንድታቆይ ት የምፈልገው ህወሀት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ድብቅ አጀንዳ እንደሌለው በገዛ አይንህ እንድታይ ስለምፈልግ ነው። አንተ ግን ከጄርባ ሌላ የተደበቀ ፍላጐት ያለን ይመስልሀል።

ስማኝ አኖሌ ...

እኛ ከትግራይ የተነሳነው ታጋዮች ከደርግ ጋር ባደረግናቸው መራራ ውጊያዎች ሁሉ ድል ተጐናፅፈናል። ከድል በሁዋላ ስሜታችን ምን የሚሆን ይምስልሀል? ፌሽታ? ፈንጠዝያ? ጉዋይላ? አይምሰልህ? ተደብቀን እናነባለን። ምክንያቱም እያንዳንድዋን ድል የምናገኘው የጉዋደኞቻችንን ህይወት ከፍለን ነበር። ያጠሁዋቸውን ጉዋደኞቼን ስም ልዘርዝርልህ? ማርታ - ዶክተር አታክልቲ - ስሁል - ነጋሽ ሽሪፎ - ሙሴ - ብርሀነ መስቀል - አልማዝ አለሙ - መብራት - ምህረት - ዋልታ - ፀሀዬ - ሽዊት - በሀበሎም - ተስፋይ ኪነት - ኩህለን - አብርሀ ማንጁስ ... ልቀጥልልህ? ግን የአርባ አምስት ሺህ ጉዋደኞቼን ስም እንዴት አድርጌ በዚህ አጭር ደብዳቤ መዘርዘር ይቻለኛል? ታዲያ ሙሴ አስረክቦን የሄደው አደራ ምን ይመስልሀል? አህፈሮም ለትግራይ ህይወቱን በግንባር ቀደምትነት ለምን ሰጠ? አህፈሮምና ሙሴ አርባ ሺህ የትግራይ ምድር ወንድምና እህቶቻችንን ከሰዋችሁ በሁዋላ የኦሮሚያን ቡና ጫኑ የሚል አደራ ጥለ አስረክበውን ያለፉ ይመስልሀል? ሀየሉምና ኢህአዴግ የወንድሞቻቸውን ህይወት ወደ ርካሽ ሚዛን አውርደው ይደራደሩበታል ብለህ ትገምታለህ?

እውነታውን በጥሞና ታሰላስለው ዘንድ እጋብዝሀለሁ። እንደኔ ያለ እድሜውን ሙሉ በጦርነት ያሳለፈ ሰው ስድሳ ልምድ ያላቸው ታጋዮችን ይዞ ከአስር የማይበልጡ ኦሮሞዎችን በከበበባት ደቂቃ ምን ሊያስብ ይችላል ብለህ ገመትክ?

ቀረርቶ? ንቀት?

ሀየሎምም ሆነ ህወሀት - ኢህአዴግ ሰዎችን ንቀው አያውቁም። ኢህአዴግ ሰዎችን ከሚንቅ ቢደረማመስና ቢበተን ይሻለዋል። ሰዎችን መናቅ የጀመርን ቀን ወደ መቃብራችን የምንደርገውን ጉዞ እንደምናጣድፍ ይሰማኛል። ምክንያቱም ኢህአዴግ ለድርጅቱ ቀና ጉዞና አላማ ሲሉ ህይወታቸውን በከፈሉ ግለሰቦች አጥንትና ደም የተገነባ ድርጅት እንጂ በሀብታሞች መዋጮ የቆመ የጡብ ህንፃ አይደለም።

ሙሴ ላለመግደል ሲል የተሰዋ መሪያችን ነው። የሙሴ መንፈስ እኛ ውስጥ አለ። ባለፉት ዘመናት ሁሉ ላለመግደል ስንል ተሰውተናል። ታሪክ ራሱን አልደገመም እኖሌ። በዚህ ሰአት የአባቦኩን ኮረብታ የከበበው የምኒልክ ጦር አይደለም። እዚህ አባቦኩ ኮረብታ ስር ያለነው ታጋዮች የህዝብ ልጆች ነን። ነፃነት የጠማን - የታመቀ የእንባ ውቅያኖስ ደማችን ውስጥ ተቀላቅሎ የሚያስጨንቀን ታጋዮች ነን። ደም ሲፈስ ማየት የማንሻ፤ የሰው ልጆችን ደስታ ለማየት የምንንጎዋጎዋ ተጋዮች ነን። የወጣትነት ጊዜያችንን በመከራ ያሳለፍን፤ እኒያን የፈንጠዝያ የእድሜ ጊዜያት ለአንዲት ሰከንድ እንኳዋ ሳንመለከት በመራራ ትግል ውስጥ ያለፍን ሰዎች ነን ...

በጥሞና ስማኝ እኖሌ

ዋቢሸበሌ ሆቴል ከሀወኒ ጋር ታውት የነበረውን የኛ የመረጃ ሰዎች ቀርፀውታል። ለሀወኒ ስልክ ከደወልክላት እለት ጀምሮ በቴሌፎኑ አማካይነት ቴሳህን በማግኘታችን ለአንዲት ደቂቃ እንኳዋ ከአይናችን አልራቅህም ነበር። በሆነው ጊዜ እንድትያዝ ማድረግ ይቻል ነበር። ከጀርባህ ያለውን ግን ማወቅ ፈለግን። በማን እንደምትደገፍ የማወቅ ጉጉት ነበረን። በመጨረሻ ከጀርባህ ያለውን ደረስንበት። ማን ይመስልሀል? ማንም የለም። ብቻህን ነበርክ። በርግጥ በነፍጠኛው ላይ ያለህ ገደብ የሌለው ጥላቻ አብሮህ ነበር። ለኦሮሞ ወገኖችህ የነበረህ ገደብ የሌለው ፍቅርም ልብህ ላይ እየነደደ ያስጨንቅህ ነበር። ድብቅ አጀንዳ አላችሁ የምትለን ሰዎች ይህን በዝርዝር እናውቃለን።

በዚህ ጊዜ የተሰማኝን ልንገርህ? ጉዋጉዋሁ። የአንተ አይነት ቅን ሰዎች ህዝባቸውን የሚያገለግሉበት እድል ይፈጠር ዘንድ





ተመኘሁ። በነገራችን ላይ ሀወኒን እወዳታለሁ። ትመሳሰላችሁ። እሰዋም በኦሮሞነትዋ ትኩራለች። የምወዳት በዚህ ባህርይዋ ነው። በማንነታቸው የሚኩሩ ሰዎችን አጥብቄ እወዳለሁ። ጀግኖች እነርሱ ናቸው። በማንነት መኩራት ግን ሌሎችን መጥላት ማለት እንዳልሆነ እንድትረዳልኝ እሻለሁ። እዚህ ዝርዝር ውስጥ መግባት አልሻም። ይህን ደብዳቤ የምፅፍልህ ለኢህአዴግ አባልነት ልመልምልህ አይደለም። ስለህወሀት ያለህን የተሳሳተ አመለካከት ታርም ዘንድ አጥብቄ እመኛለሁ። ማረም የምትችለው ግን በህይወት ካለህ ብቻ ነው። ስለዚህ ለጥቂት ጊዜያት ህይወትህን ለማቆየት ቃል ግባልኝ። በተቀረ ይህን ቃል ሙሉ በሙሉ እመነው። መጥፎም ይሁን ጥሩ አላማ ያለህ ሰው ስለሆንክ ነው ግልፅ ሆኜ የፃፍኩልህ። ጥያቄዬን ከተቀበልከው ከሌሊቱ ስድስት ሰአት ሲል አምስት ጥይቶችን በተከታታይ ወደሰማይ ተኩስ። ከዚያም ከኮረብታዋ በስተቀኝ በኩል ባለው ገደላማ ሸጥ በኩል ባትሪ እያበራህ ከነተከታዮችህ ውረድ። በወንጀለኛነት ስለተመዘገብክ እዚህ ሀገር ለጊዜው ህጋዊ ሆነህ መኖር አትችልምና ለጊዜው ወደፈቀድከው አካባቢ ሂድ። ምናልባትም ኤርትራ ... የኛን አላማ ከተረዳህ አንድ ቀን ወደ ሀገርህ ትመለሳለህ።

ውድ እኖሌ ...

እኩለሌሊት ላይ አምስት ጥይት በተከታታይ ካልተተኮሰ ግን አላመንከኝም፤ አሊያም ጥያቄዬን አልተቀበልከም ማለት ስለሚሆን ማለዳ ላይ ታጋዮች ሳይወዱ ይተኩሱብሀል። ተኩሱም ፍትሀዊ ይሆናል።»

ጨርሼ ቀና ስል ከአፉ በሚንቦለቦለው የሲጋራ ጢስ ውስጥ አተኩሮ እያየኝ ነበር፣

«ደብዳቤው አሳመነህ?» አልኩት።

«የለም» አለ እኖሌ «... የማመንና ያለማመን ጉዳይ ሳይሆን የሀየሎምን ጥያቄ ተቀበልኩት። እነዚህ ሰዎች በርግጥ ዴሞክራት ከሆኑ የሚፈፅሙትን ለማየት ወሰንኩ። ኤርትራ ከመጣሁ በሁዋላ የወያኔን የፖለቲካ አካሄድ በጥንቃቄ ተከታተልኩት። ባጭሩ የተረዳሁት እውነት ቢኖር ሀየሎም ትንና ጀግና እንጂ ከፖለቲካው መሪዎች አንዱ አለመሆኑን ነው።»

«እንዴት?» ስል ጠየቅሁት።

«አንድ ሀቅ ልንገርህ?» አለ እኖሌ ጣቱን ወደኔ ቀስሮ «...ሀየሎም

ይህን ደብዳቤ የፃፈው ከልቡ ነው:: እንዳልኩህ ሀየሎም ጀግና ነው:: ፖለቲከኛ ግን አይደለም:: የወያኔ የፖለቲካ ሞተሮች እንደ ሀየሎም አያስቡም:: በመቆየት የተገነዘብኩት ሀቅ ይህንን ነው:: ይህ ደብዳቤ የሀየሎምን ልብ እንጂ ህወሀትን አይወክልም:: የወያኔን የሀወኒ ትልቁ ችግርም ይህን መገንዘብ አለመቻልዋ ነው:: የወያኔን የፖለቲካ ስውር ጉዞ ከሀየሎም ልብ ጋር እየቀላቀለች ነው የገባችው:: እኔ እንደማምነው በሀየሎም መምታታት ውስጥ የገባችው:: እኔ እንደማምነው በሀየሎም ይመሩ የነበሩት የእኒያ ቅን ጀግኖች ዘመን አልፎአል:: የእነርሱ ህልምና እምነት በዛሬው የፖለቲካ መድረክ ውስጥ የለም:: የዚህ አባባሌ ስነ አመክኖአዊ ትርጉም ይገባችሁዋል?» ሲል እኔና ሀወኒን በየተራ እያቃኘ ጠየቀን::

መልስ አልሰጠነውም:: ተያይተን ዝም አልን:: ቀጠለ አኖሌ፣

«ይኸው ነው ወዳጆቼ:: የሀየሎም ደብዳቤ መሳጭ ተረት ብቻ ነው - ልክ እንደ ቡርቃ ዝምታ:: የኦሮሞ ህዝብ ገና ነፃነቱን ባለማግኘቱ፣ በስውር ቅኝ አገዛዝ ስር በመውደቁ በቀጣይ በራሱ መንገድ መታገሉን መቀጠል አለበት:: የጆርጅ ኦርዌልን Animal Farm በገሀዱ አለም ለማየት መብቃቱ በእጅጉ ይደንቀኛል:: ኦርዌል ነቢይ ነበር:: አንድ ሌላ ሀቅ ደግሞ ልንገራችሁ! ወደፊት የኦሮሞ ህዝብ መራራ መስዋዕትነት ከፍሎ ነፃነቱን በጁ ማስገባቱ አይቀርም:: በዚያን ጊዜ ግን የኦሮሞ ህዝብ ስሜት አደገኛ ነው የሚሆነው:: ከባድ የበቀል ነበልባል ሊለኩስም ይችላል:: ኢትዮጵያውያን ይህ እንዳይፈፀም የሚሹ ከሆነ ከወዲሁ ሊያስቡበት ይገባል:: ያ ቀን ከመምጣቱ በፊት በሰላማዊ መንገድ ሙሉ መብቶቻችን ይከበሩልን ዘንድ እንሻለን::»

አኖሌን ከመሰናበቱ በፊት አንዳንድ ጥቃቅን ጥያቄዎችን አቀረብኩለት፣

«ምዕዋ ለሁለት ቀናት ያህል ከሀወኒ ጋር ባደረግሁት ቆይታ የእለት ገጠመኝ መመዝገቢያ ማስታወሻ ደብተርህን አውሳኝ አንብቤው ነበር:: በጣም ማራኪ ነው ...» ስል ተንደረደርኩ:: አያያዘኩናም ቀጠልኩ፣

«በማስታወሻ ደብተርህ ላይ የሰፈሩት አንዳንድ መረጃዎች ላዘጋጀው ላሰብኩት መፅሀፍ ጠቃሚ መነሻ ሀሳብ ሊሰጡኝ ስለሚችሉ እንድጠቀምበት ብትፈቅድልኝ?» የሚል ልመና ቢጤ አቀረብኩ::

አኖሌ ግን ጥያቄዬን ቀለል አድርጎ አየው፣ ትከሻውን በመስበቅና ከንፈሩን በመበልጠጥ መስማማቱን ገለፀልኝ:: ተመስገን ብዬ ወደሌላ ጥያቄ ተሻገርኩ::

«በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጂብሪል እና ጮማዬ ስለተባሉ ሰዎች አስፍረሀል:: አሁን የት እንዳሉ ታውቃለህ?»

አኖሌ ፈገግ አለ፣

«ጂብሪል አሲ ግሬይፍስ ቫልድ ከምትባል የጀርመን ከተማ ነው ያለው:: በኔ ጦስ አንድ አመት በመታሰሩ ይቅርታ ልጠይቀው ፍላጎት ነበረኝ:: አልደረስኩበትም:: ወያኔ አዲሳባ ሲገባ ከእስር መፈታቱንና በክረምቱ ወራት ወደ ጀርመን ለመሻገር መቻሉን ሰማሁ:: የአስገራሚ ባህርይ ባለቤት ስለሆነው ጮማዬ ወሬ የሰማሁት ግን በቅርቡ እዚሁ አስመራ ላይ ነው:: ጮማዬ እድለኛ ነው:: በጦርነቱ ከሞት አምልጦ አዲሳባ ቂራ በተባለ ሰፈር ስጋ ቤት ለመክፈት በቅቶአል» ብሎ በሳቅ ተንከተከተ:: እኔም በጣም አደነኩት:: አኖሌ ከጮማዬ ጋር ያደረጋቸውን ወጎች በማስታወሻ ደብተሩ ልቅም አድርጎ በማስፈሩ ይህን ልዩ ፍጥረት በቅርብ ለማወቅ ችዬ ነበር::

* * *

አኖሌን ተሰናብቼ ወጣሁ::

ሀወኒ ጥቂት መንገድ ልትሸኘኝ ፈቃደኛ ሆነች::

በመንገድ ላይ ታዲያ አኖሌን አስመልክታ ጥቂት አወጋችኝ፣

«... አኖሌ አስቸጋሪ ሰው ነው» ስትል ነበር የጀመረችው ... ዲሞክራሲያዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ያለ ክብርና ክራት ገደል ይግቡ የሚል ፈሊጥ አለው:: የዚህ አባባል መንፈስ ከቶ አይገባኝም:: እኛ ኦሮሞዎች ከኢትዮጵያውያን ጋር የተፈጠርን ኢትዮጵያውያን ነን:: ያለፉት መንግስታት በደል አድርሰውብናል:: ይህ ግልፅ ነው:: ለዚያ በደል ማካካሻ የሚሆን የበቀል ጅራፍ ልናጮህ ግን ከቶ አይገባም:: በፍፁም! በዚህ እምነቴ አኖሌ አምርሮ ይወቅሰኛል:: ቂስ እንጂ ህዝባዊ ታጋይ መሆን አትችይም ይለኛል:: አኖሌ

ጥያት መጮህ የለበትም ከሚለው አጀንዳ በፊት ስለ ክብርና ኩራት ያነሳል:: እኔ ግን ስለ ሰላም መዘመር እሻለሁ:: የህወሀት ሰዎችም ቢሆኑ አኖሌ በሚለው መልኩ ከቶ ሊታዩ አይችሉም:: በፍፁም! እኛ ኦሮሞዎች ሰላማዊውን መድረክ ተጠቅመን የስልጣን ባለቤትነታችንን ማረጋገጥ ከቻልን ማንም እጃችንን ጠምዝዞ አንበርካኪ ሊያደርገን አይችልም:: በርግጥ ...» አለች ሀወኒ ትክዝ ብላ «... በርግጥ እነ ሰለሞን ዲሳሳ አሁንም ስልጣን ላይ ናቸው:: አልተወቀሱም፤ አልተከሰሱም:: ይልቁን እየተደላደሉ ነው:: በሙስና መዘፈቃቸው ይታወቃል:: ከልካይ ግን የላቸውም:: ይህ በእጅጉ ያሳስበኛል:: ለአብነት ሰለሞን ዲሳሳ ፊንፊኔ ሆቴል ላይ እጅ ከፍንጅ እንዲያዝ ሁኔታዎችን አመቻችቼ ነበር:: ሆኖም ከቀጠሮአችን ቀደም ብሎ ይህን መፈፀሜን ማወቅ ቻለ:: እንዴት? አልገባኝም:: ይልቁን በሙስና ስለመዘፈቁ በቂ መረጃ አለመገኘቱ ተገለፀልኝ:: ይህን መሰል ሁኔታዎች ተስፋ አስቆራጭ ናቸው:: 'ኢትዮጵያ የኔ ብቻ ምናገባኝ?' እንድትል ያደርጉሀል:: 'ኢትዮጵያ የኔ ብቻ አይደለችም፤ የሚሊዮኖች ናት:: ምናንገበገበኝ? የግል ህይወቴን ብቻ ለምን አልመራም?' ብዬ ከራሴ ጋር የምሙዋገትበት ጊዜ ጥቂት አይደለም:: የቡርቃ ገበሬዎች ሲታሰቡኝ ደግሞ ልቤ ላይ የቁጣና የእልህ እሳት ይነዳል:: እኒያ ቅንና ምስኪን ገበሬዎች በኔን በአኖሌ ላይ የጣሉትን እምነትና ተስፋ ሳስብ ብቻዬን ተደብቄ በቁጭት ስቅስቅ ብዬ አለቅሳለሁ:: በዚያች ደቂቃ ታዲያ የአኖሌ የአመፅ መንፈስ ይጋባብኛል:: የኦሮሞ ህዝብ እንደ ደራሽ ወንዝ ከየጉጆው ወጥቶ አገር ምድሩን በቁጣ ያናውጥ ዘንድ እመኛለሁ:: ዳሩ ግን ይህ ስሜቱ ዘላቂ አይደለም:: መልሼ መታገስና መታገል እንዳለብኝ ራሴን በራሴ እመክራለሁ ...ዳሩ ግን እነርሱ ስልጣን ላይ እያሉ የኦሮሞን ህዝብ የስልጣኑ ባለቤት ማድረግ ይቻላል? ለዚህ መልስ የለኝም:: በእጅጉም ያሳስበኛል ... ጉደሎ ነገሮች ይታዩኛል ... መፍትሄው ታዲያ ምንድነው? አኖሌ እንደሚለው ጠመንጃ ማንሳት? በፍፁም! በፍፁም! ከነግዲህ ሌሎች ንፁህ ኢትዮጵያውያን መሞት የለባቸውም:: በፍፁም ...»

ኮምቢሽታቶ ላይ በዝምታ እየተጉዋዝን ነው:: ሀወኒን ማዳመጥ አይሰለችም:: የሀወኒን ወግ መስማት በፀጥተኛ ገጠር ውስጥ ቀልብን መቆጣጠር የሚችል ዜማ እንደማዳመጥ ይቆጠራል:: ሀወኒ ቀጠለች፤

«... በኢትዮጵያችን ውስጥ እርቅ እንደሚያስፈልግ





ይሰማኛል:: እሮሚያም በእውነተኛ የኦሮሞ ልጆች እንድትመራ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠር አለባቸው ብዬ አምናለሁ:: በመላው አለም የተበተኑ የኦሮሞ ልጆች ወደ ለምለሚቱ ኦሮሚያ እንዲመለሱ የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል:: ከዚህ በሁዋላ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ጋር ተከባብረን መኖር እንችላለን:: እኔ ስለ ነፍጠኞች እያንጉራጉርኩ ጊዜ ማባከን አልሻም:: የነፍጠኛው ስርአት ሞቶ ተቀብሮአል:: አማሮች ንፁህ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ናቸው:: አማሮች ጠንካራ ሰራተኞች፤ ደግና ጀግኖች ናቸው:: አብረን ኖረናል:: ወደፊትም አብረን መኖር እንችላለን:: የኦሮሞ ህዝብ እንደ ጠላት የሚያየው ህዝብ የለውም::»

«ስማ ልንገርህ» ስትል ቀጠለች ሀወኒ ... «እኔ የታሪክ ሰው ነኝ:: የመጀመሪያ መፅሀፌን በአማርኛ የመፃፍ እቅድ ነው ያለኝ:: በኦሮምኛም እፅፋለሁ:: የተዋሀደ ስሜትና ስርአት ሲኖር እንደሚገባ አስባለሁ:: ለህዝቦች ጥቅም የሚውል አንድነት ይኖረን ዘንድ ቅን መሆን አለብን:: ስለጠመንጃ መርሳት መጀመር አለብን:: ዋቢሸበሌ አባይና ዳቡስ ወንዞች እየባከኑ ነው:: ወገኖቻቸውን እያገለገሉ አይደሉም:: ቅን መሪዎችና ብርቱ ሰራተኛ ህዝብ መፍጠር ይጠበቅብናል:: የኔ ራዕይ ይህን ይመስላል ...»

ባር ኢምፔሮ በረንዳ ላይ ተቀምጠን ቀጭን የአስመራ ሻይ አዘዝን:: ቀዝቀዝ ያለው የአስመራ የምሽት አየር ምቾትን ያጎናፅፋል:: ሀወኒ አጠገቤ አለች:: ከርስዋ ጉን መሆን አይጠገብም:: የበሰለ እንጆሪ የመሰሉ ከንፈሮችዋን ከፊት አድርጋ፤ በኒያ ቀልብ በሚነሱ አይኖችዋ ስታተኩር የምትዘምር ፅጌረዳ አበባ ነው የምትመስለው:: እናም በዚህ ስሜትና መንፈስ ወጋችንን ቀጠልን፤

«አኖሌ አስመራ ይቆያል?» ስል ጠየቅሁዋት::

«ወደ ሀገሩ መመለስ አለበት» አለች ሀወኒ በቁርጠኝነት «የቡርቃ ሰዎች ይጠብቁታል:: በርግጥ አኖሌ አሁን ቅዥት ላይ ነው:: ከኢህአዴግ ጋር ጦርነት ለመግጠም ሌትና ቀን እየሰራ ይገኛል:: ይህ እብደት ነው:: ከኢህአዴግ ጋር በጋራ መስራት እንደሚቻል ላሳምነው እየሞከርኩ ነው ያለሁት:: የትጥቅ ትግል የመጀመር ሀሳቡን አምርሬ እየተቃወምኩት ነው::»

«የተምታታ ስሜት ውስጥ መግባትሽ ግን አይካድም ...» አልኩዋት፤ እንደዋዛ::

ሀወኒ ትክዝ አለች::

«... ምን መሰለህ?» አለች ዘግየት ብላ «... እኔ ተስፋ አደርጋለሁ:: አልችኩልም:: ለማመስገንም ሆነ ለመውቀስ አልችኩልም:: ለመቃወምም ለመደገፍም አልችኩልም:: እና ህልም አለኝ:: የኦሮሚያ ልጆች በአንድ የዋርካ ዛፍ ስር መሰባሰብ የሚችሉበት ዕለት ይናፍቀኛል:: ከዚያም ባሻገር ኢትዮጵያዊነት እንዲጠነክርና እንዲያብብ ከልብ እመኛለሁ:: ይህን ዕለት ዘወትር በተስፋ ነው የምጠብቀው:: ይህ ምኞቴ እንደ ቡርቃ ዝምታ ተረት እየሆነ ሲሄድ ሳይ ግን ልቤ ይደማል ...»

ባር ኢምፔሮን ለቀን በዝግታ እርምጃ በአስመራ የዘምባባ ጥላዎች ስር ተጉዋዝን::

«ሌላው ቁምነገር» አለች ሀወኒ አሻግራ እያስተዋለች «... ስለ ክብርና ኩራት ማሰብ ማቆም እንደሚገባን ይሰማኛል:: ለክብርና ኩራት ሲባል አንድ ጠብታ ደም እንኩዋ መፍሰስ የለበትም ብዬ በጥብቅ አምናለሁ:: ስማኝ ልንገርህ! ቢያንስ ከታሪክ መማር መቻል አለብን - ከጦርነት ታሪካችን:: AN ANCHOR OF A SHIP IS ALWAYS AT SEA. BUT NEVER LEARNS TO SWIM የሚል የፈረንጆች አባባል አለ:: እንደ ግዑዙ መልህቅ መሆን የለብንም:: ምንድነው ክብርና ኩራት? ምድር እንደሁ ለግለሰቦች የታላቅነትም ሆነ የታናሽነት ታሪክ ደንታ የላትም:: ሚልዮኖችን እንደዋዛ ሸኝታለች:: እኔ እንደማምነው መፈጠራችን ትርጉም የሚኖረው ባለንበት ዘመን ለህዝባችን የሚጠቅም ጥቂት ቁምነገር መስራት ከቻልን ብቻ ነው:: ከቁና ሙሉ ድህነት ጋር ባዶ ኩራት መውረስ የሚሻ ትውልድ የለም ...»

ሀወኒን ተሰናበትኩዋት:: አስመራን ጭምር:: እና ወደ አዲሳባ የመልስ ጉዞ ጀመርኩ - አጭር የአየር ላይ ጉዞ::

* * *

እነሆ በአይሮፕላን መንገድ ላይ ነኝ ...

ስለ ሀወኒ እያሰብኩ ነው::

«ምድር ለግለሰቦች የታላቅነትም ሆነ የታናሽነት ታሪክ ደንታ የላትም ... ከቁና ሙሉ ድህነት ጋር ባዶ ኩራት መውረስ



የሚሻ ትውልድ የለም ...»

የሀወኒ ያህ የመጨረሻ አባባል ከአእምሮዬ አልጠፋ አለ:: ደግሜ ደጋግሜ -- መልሼ መላልሼ አጠነጠንኩት:: አባባሉ አንድ ግጥም አስታወሰኝ:: አጭር ግጥም:: በአንድ ወቅት የአማራ ታጋዮች መሪ የነበረው ታምራት ላይኔ የቋጠራቸው ስንኞች፣

*ሁሉም ያልፋል ...*

*ጎርፍም እንኳ ...*

*ዶፍ ዝናሙ ያጎረፈው::*

*ሄዶ ... ሄዶ -- ሄዶ ያልቃል ...*

*ፈሶ ... ፈሶ -- ፈሶ ይደርቃል::*

*ፀሀይቱም ... ፀሐይቱም እንኳ ...*

*ቀኑን ሞቃ ... ሞቃ ሞቃ ትበርዳለች!*

*መሬት ፊትዋን ስትነሳት ... ስትርቃት ትሸሻለች!*

ይህንኑ እያዜምኩ አዲሳባ ገባሁ:: ማለዳ ነበር:: በመንጋት ላይ ያለ የሰንበት ማለዳ:: የምስራቅ ሰማይ ወለል ብሎ ታየኝ:: እያለሁ:: ይታየኛል:: የፀሀይቱ መውጫ ይታየኛል:: አስፈሪና ከባድ የተፈጥሮ የንጋት ቀለም ሰማዩን አጅጉርጉሮታል:: ጨፍጋጋ ማለዳ:: ተስፋ ቢስ ንጋት:: አዎን! ሰማዩ የአህያ ሆድ መስሎአል:: የወደል አህያ ሆድ ...